# ክርስቲያንና እንትን

## የክርስትና ግራጫ ቀጣናዎች

ዘላለም መንግሥቱ

ወሲብ
ሥልጣን
ክሮና
ዘፈን
ባህል
መጠጥ
ንዋይ
ዘረኝነት
ቁማር
ዝና
ፖለቲካ

# ክርስቲያንና እንትን

የክርስትና ግራጫ ቀጣናዎች

ዘላለም መንግሥቱ (ከፊሉ መጀመሪያ በመጣጥፎችና በቪድዮዎች © 2018-2022፤ ፳፻፲፩ እስከ ፳፻፲፬ ዓመተ ምሕረት። በመጽሐፍ © 2022 ፳፻፲፭ ዓመተ ምሕረት።)

ይህን መጽሐፍ ባለቤትነቱን ሳይወስዱና ለሽያጭ ሳያውሉ ጸሐፊውን በማሳወቅ ማባዛትም ማሰራጨትም ይፈቀዳል።

በተለይ ካልተጠቀሰ በቀር፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት ከ፲፱፻፶፬ ዓ. ም. (1962) የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ካሳተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

* * * * *

# The Christian and Grey Zones

Zelalem Mengistu (© 2022)

This work can be reproduced and disseminated by only notifying the author, without claiming ownership, and so long as it is not for profit.

All Scripture quotations are from the 1962 edition of the Amharic Bible published by the Bible Society of Ethiopia.

የሽፋን ዲዛይን፥ ዘመን ግራፊክስ።

መድረከ ዕዝራ
ለጌታ ቃል እና ለቃሉ ጌታ ታማኝ በመሆን
ezra forum
being true to the Word of God and the God of the Word

ጌታን ለተቀበልኩባት ለአምስት ኪሎ መካነ ኢየሱስ፥ አዲስ አበባ

ላመለክሁባቸው፥ ላደግሁባቸውና ላገለገልኩባቸው የመጀመሪያ ሦስት ቤተ ክርስቲያኖቼ

ለኅብረት አምባ ቃለ ሕይወት፥ አዲስ አበባ

ለአማኑኤል ቃለ ሕይወት፥ አሥመራ

እና ለደብረ ዘይት ቃለ ሕይወት፥ ደብረ ዘይት

የተበረከተች ናት።

ማውጫ


መግቢያ - - - - - ገጽ 5

መወንጨፊያ - - - - - ገጽ 7

ምዕራፍ ፩፤ ክርስቲያንና ዘረኝነት / ብሔረተኝነት - - - - ገጽ 13

ምዕራፍ ፪፤ ክርስቲያንና ፖለቲካ - - - - - ገጽ 24

ምዕራፍ ፫፤ ክርስቲያንና ኮሮና ቫይረስ - - - - - ገጽ 43

ምዕራፍ ፬፤ ክርስቲያንና ወንበር (ሥልጣን) - - ገጽ 103

ምዕራፍ ፭፤ ክርስቲያንና ወረት (ንዋይ) - - - - - ገጽ 122

ምዕራፍ ፮፤ ክርስቲያንና ወሲብ (ዝሙት) - - - ገጽ 131

ምዕራፍ ፯፤ ክርስቲያንና አስካሪ መጠጥ - - - - ገጽ 152

ምዕራፍ ፰፤ ክርስቲያንና ቁማር - - - - - ገጽ 170

ምዕራፍ ፱፤ ክርስቲያንና ዘፈን - - - - - ገጽ 189

ምዕራፍ ፲፤ ክርስቲያንና ዝና (ታዋቂነት) - - - - ገጽ 223

ምዕራፍ ፲፩፤ ክርስቲያንና ባህል (ባህላዊ አመቻማችነት) - - ገጽ 236

# መግቢያ

በዚህ ክርስቲያን እና እንትን በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት አሥራ አንድ ጉዳዮች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጉዳዮች ሆነው የሚነሡና ብዙ ጊዜ ከቅርቦቼ ጋር የተነጋገርንባቸውም፥ የተከራከርንባቸውም፥ የተማማርንባቸውም አሳቦች ናቸው። አንዳንዶቹ ከምካቴ ክርስትና ጋር ኩታ ገጠምነት ያላቸውና በዚያ ዘርፍ የተወሱ ነጥቦችንም የያዙ ናቸው። አንዳንዶቹ ጉዳዮች ብዙ የተባለባቸው፥ ትምህርት የተሰጠባቸውና የተሰበከባቸው ቢሆኑም ሌሎቹ ለመነካትም የሚያስፈሩና የማይደፈሩ ዓይነት ናቸው።

እንትን የሚለውን ቃል አልወደውም፤ ሆኖም እዚህ የመጽሐፍ ርእስም አድርጌዋለሁ። እንትን ትልቅ ቃል የሚሸፈንበት መሸፈኛ ነው። ከኔ ጋር የሚያወሩ ሰዎች፥ 'እንትን' ሲሉ ወዲያው፥ 'ምን?' እላቸዋለሁ። አንዳንዶችማ፥ 'እንትኑ እንትን ሆኖ ከዚያ እንትኑ' እያሉ በአንድ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ሲጠቀጥቁት፤ አስቆማቸውና እንደገና እንዲነግሩኝ አደርጋለሁ። እንትንን በወግ ያስጣልኳቸው ጥቂት ጓደኞች አሉኝ። እዚህ የተጠቀሱት እንትኖች በእርግጥም ስም ያላቸው ጉዳዮች ናቸው። አንዳንዶቹ ጉዳዮች ለአንዳንዶች ነገሮቹ የእንትን ያህል የማይነገሩ ናቸው። ሲነገሩ ግን ግድ ይላል።

እነዚህ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት አንዳንዶቹ ጉዳዮች ጥልቅ ምርመራና ብርበራ የሚያስፈልጋቸው እና ግላዊ ውሳኔና አቋምም የሚጠይቁ ናቸው። እንዲህ ያሉ ጉዳዮች ላይ ስናገር እስከምችለው አስቤበት፥ አንብቤና አጥንቼው ሚዛናዊ ነው የምለውን፥ የተረዳሁትን እውነት ነው የማካፍለው። በጉዳዮቹ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገርባቸው ነገሮች አሉ፤ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገርባቸው ነገሮች ምንም ጥያቄ የሌለባቸው ጉዳዮች ናቸውና እነዚህን ያለ ፍርሃት እና ያለ ጥርጥር፥ ባለመንተባተብና ባለመሳቀቅ አካፍላለሁ። ግላዊ ውሳኔ የሚጠይቁ ጉዳዮች ላይም የራሴን አቋም ሳልደናበር እገልጣለሁ። የኔን አቋም ግን ሁሉ ሊቀበሉት የተገባ ነው አልልም፤ ሆኖም ያንንም በግልጽ አጋርቻለሁ። አሁን ካወቅሁት ይበልጥ ሳውቅና የአሁን አቋሜ ጎዶሎ ወይም የተሳሳተ ሆኖ ከተገኘ እታረማለሁ። እስከተቻለኝና እስከማውቀው ድረስ ግን የኔ አቋም የቃሉ ትምህርት እንዲሆን ጥረት አደርጋለሁ። ቃሉ የሚለው ደግሞ ሁሉ ሊቀበሉት የተገባ ነው። ቃሉ ትልቁና ከሁሉ የበላይ የሆነ የሥልጣን ቃል ነው።

በዚህ መጽሐፍ ከተካተቱት ጉዳዮች ውስጥ ዘጠኙን በቪድዮ አካፍያቸዋለሁ። በYouTube ገጼ ላይም ይገኛሉ። ከነዚህ ጽሑፎች በርካቶቹን የጻፍኩት ወይም ያካፈልኩት ከምካቴ ክርስትና አገልግሎት አኳያ ነው። የምካቴ ክርስትናን ተግባር አንዳንዴ ኢታካች መሆኑን ማሳወቅ ተገቢ ይመስለኛል። ፍግ ወይም ዐዛባ እንደ መዛቅ

ነው። ዐዛባ የከብቶች እበትና በጠጥና ፋንድያና ሽንት ሲደባለቅ ማለት ነው። ፍግ ደግሞ ዐዛባው ደረቅ፥ ጠፈፍ ሲል ማለት ነው። ያንን መዛቅ ነው። ያስሸትታል፤ ያገማል፤ ያቀረናል፤ ያከረፋል። 'ይህን እየዛቁ ከመከርፋት ቢቀርስ? ቢትተውስ?' ማለት ይቻላል።

አንዳንዶች ይህንን ዋጋ መክፈል ስለማይወድዱ ከሩቅ ይሸሹታል። እውነትም የሚከፈለው ዋጋ ቀላል ስላልሆነ ምካቴ እምነት የሚሸሹት አገልግሎት ነው። የሚሸትቱበት ስለሆነ፥ የሚሸሹትም አገልግሎት ነው። ግን ወዴት ይሸሹታል? ዐዛባው ያለው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሆነስ? ካልተዛቀ ሌላኛው ሁለተኛው አማራጭ ብቻ ነው የሚቀረው፤ ያም እያሸተቱ መቀመጥ ነው። ማሽተት ብቻ ሳይሆን፥ እዚያ ከተቆየ መሽተትም አለ። ታዲያ ሁሉ ከሚሸቱ ጥቂቶች መሽተታቸው አይሻልም? ዐዛባው ካልተዛቀ፥ ክርስትና አሁን እየተሰደበ ካለበት በላይ ይሰደባል። የኮሜዲያኖች የመዋኛ ኩሬ ይሆናል። የጋዜጠኞች ሰበር ዜና ይሆናል። እንዳይሆን ትንሽም እንኳ መከላከል አይሻልም? ጥቂት ዋጋ መክፈል አይሻልም? ይሻላል።

በዚህ ሥራ ውስጥ እንደ ቃሉ ለማካፈል የሚቻለኝን አድርጌአለሁ። ከዚያ የተረፈው የግል አቋም የራሴ፥ የግሌ እንጂ የማንም ቤተ ክርስቲያን ወይም ቤተ እምነት ተደርጎ መወሰድ የለበትም። ይህን የጻፍኩት ወይም ያካፈልኩት ወክዬ አይደለም።

መልካም ንባብ።

ዘላለም መንግሥቱ (12/22/2022 / ፳፻፲፭ ዓመተ ምሕረት)

## መወንጨፊያ

እንደ መወንጨፊያ አድርጌ በመጀመሪያ የማካፍለው ክርስቲያንና ሦስቱ ወዎች በሚል ላካፈልኩት ትምህርት መንደርደሪያ አድርጌ ያቀረብኩትን የቤተ ክርስቲያንን አካልነት እና በቀላሉ ተጎጂነትን አሳብ ነው። በዚህ ክፍል የቤተ ክርስቲያንን ምንነት እና ቤተ ክርስቲያን የምትጎዳበትን ስስ ብልትነቷን በጣም በጥቂቱ እንድናይ እፈልጋለሁ። ቤተ ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ ተምሳሌቶች ተገልጣለች። ከክርስቶስ ጋር ያላት ግንኙነትም እንደዚያው በተለያዩ ምስሎች ተገልጧል። በእረኛና መንጋ፥ በግንድና ቅርንጫፍ፥ በባልና ሚስት፥ በሌሎችም ምስሎች ተገልጣለች። በአካልና ራስም ተመስላለች። አካል ቤተ ክርስቲያን የተመሰለችበት አንድ ጉልህ ምስል ነው። ቤተ ክርስቲያን አካል ናት። ጥቂት ጥቅሶች ለማየት፤

*በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን፥ የብልቶቹም ሁሉ ሥራ አንድ እንዳይደለ፥ እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፥ እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን።* ሮሜ 12፥4-5

1ቆሮ. 12 ጠቅላላው ምዕራፍ ስለዚህ አካል ይናገራል። ስለ ጸጋ ስጦታዎች ነው የሚናገረው፤ ግን ያ ጸጋ የሚሠራበት አሠራር በአካልና ብልቶች ምሳሌ ተዘርዝሯል። ቁጥር 27 እንደዚህ ይላል፤ *እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ።*

ኤፌሶን ውስጥ ይህ የአካልነት ትምህርት በብዙ ጥቅሶች ተጽፎአል፤ አንድ ብቻ ለመጥቀስ፥ ኤፌ. 1፥23 ይህን ይላል፤ *እርስዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት።* እርሷ የተባለችው ቤተ ክርስቲያን ናት። ቤተ ክርስቲያን አካሉ ናት።

ቆላ. 1፥18 *እርሱም የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፤ እርሱም በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ፥ መጀመሪያ ከሙታንም በኩር ነው።*

በነዚህ ጥቂት ጥቅሶች በትንሹ እንዳየነው፥ ቤተ ክርስቲያን አካል ናት። ስለ አካል ብዙዎቻችን ብዙ ነገር እናውቃለን። አካል በጤንነት ሊጠበቅ ይችላል፤ በተለያዩ ምክንያቶች ሊጎድዳ ደግሞ ይችላል። ጉልህ የጉዳቶች ምክንያቶች ናቸው ከምላቸው መካከል ጥቂቱን ልዘርዝር፤

1. በውጪያዊ አካላዊ ጥቃት ጉዳት ሊያገኘው ይችላል።
2. አካል በልፋትና በድካም ጉዳት ያገኘዋል።
3. አካል ዕረፍት እና እንቅልፍ በማጣት ተጠቂ ይሆናል።

4. አካል በምግብ ወይም አስፈላጊ ንጥረ ነገሮች እጥረት ወይም እጦት ተጎጂ ይሆናል።
5. አካላዊ ባልሆኑ ስነ አእምሯዊ ወይም ስነ ልቡናዊ ጫናዎችም ጉዳት ያገኘዋል።
6. በጊዜያዊ ሕመም ወይም/እና በዘላቂ በሽታ፥
7. ከውጪ በሚጣበቁ፥ ከውጪ ወደ ውስጥ በሚገቡ፥ እንዲሁም በውስጣዊ ተዋሃስያንም ጉዳት ያገኘዋል።

እነዚህ ጉዳቶች አካል ላይ ያነጣጠሩ ናቸው። ቤተ ክርስቲያን አካል ናት። ቤተ ክርስቲያን ወይም የቅዱሳን አንድነት፥ እንደ አካል እነዚህን የተዘረዘሩትን በመሰሉ ነገሮች ልትጎድዳ ትችላለች። የቤተ ክርስቲያንን ጉዳት ቀለል እና ጠቅለል በማድረግ እሦስት ቦታ ልከፈለው፤

1. ስደታዊ ጥቃት።

ቤተ ክርስቲያን ከውጪ ልትጠቃ ትችላለች፤ ለምሳሌ፥ በአሳዳጆች ልትሰደድ ትችላለች። በዘመናት ውስጥ በአሳዳጆች ስትሳደድ ኖራለች። በአገራችንም ይህ ጉዳይ ለወንጌላዊ ክርስትና እንግዳ አይደለም፤ ይታወቃል። አሳዳጆቹ የተለያየ መልክና ቅርጽ ሊኖራቸው ይችላል።

- መንግሥታዊ ሊሆን ይችላል፤ መንግሥት አድላዊ ከሆነ መብት ሊከለክላት፥ ሊወስናት፥ ሊያግዳት፥ ሊዘጋትም ይችላል።
- ስደቱ ማኅበራዊ ሊሆን ይችላል፤ ማኅበረ ሰቡ አማኞችን ማግለል፥ መልለየት፣ መለየትና መነጠል፥ ስማቸውን ማጉደፍ፥ ማጠልሸት፥ በሐሰት መክሰስ፥ ከማኅበረ ሰባውያን ግልጋሎቶች ማራቅ ሊኖር ይችላል።
- ስደቱ ሃይማኖታዊ ሊሆን ይችላል፤ በአንድ አካባቢ ወይም ክልል ከፍተኛ ተከታይ ያለው የሃይማኖት ተቋም ሊኖር ይችላል። ያ በአናሳዎቹ ላይ ጫና ሲፈጥር ስደት ነው። ወይም አንድ ሃይማኖት ብሔራዊና መንግሥታዊ ሃይማኖት ሊሆን ይችላል። ወንጌላዊ ክርስትና እንደ አዳጊ ተጽዕኖ ወይም ለውጥ ፈጣሪ ከታየ፥ 'መጤ' ይባልና በነባሮቹ ሃይማኖቶች አማካይነት በአማኞች ላይ ከፍተኛ ጫና፥ ውግዘት፥ ብሎም ጥቃትም ሊሰነዘር ይችላል።

እነዚህ የውጪ ስደቶች ናቸው። የውጪ ስደቶች ቤተ ክርስቲያንን ያጠሯታል፥ ያጠነክሯታል እንጂ አያጠፏትም። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥ ከሐዋርያት ሥራ ጀምሮ በዘመናት ውስጥ ያለው ታሪኳ የሚነግረን ይህንን እውነት ነው። ታሪክ

የሚመሰክርልን ስደትና መከራ የክርስቶስን አካል፥ ቤተ ክርስቲያንን ሲያጠነክራትና የተጠራች ብቻ ሳትሆን፥ የጠራች ዋጋ ከፋይ ሆኖ እንድትቀጥል እንደሚያደርጋት ነው።

2. ውጪያዊና ውስጣዊ የአሳቾች ጥቃት

ቤተ ክርስቲያን እንደ አካል ከውጪና ከውስጥ፥ በአሳቾችና በሐሰተኞች ትምህርት ልትጠቃ ትችላለች። የሐሰተኞች ጥቃት የሚያደርስባት ጉዳት ቀላል አይደለም። ሐሰተኛ ልምምዶች፥ የተጋነኑ የሰው አሠራሮች፥ የውሸት ትንቢቶች፥ የስሕተት ትምህርቶችና ኑፋቄዎች ቤተ ክርስቲያንን በእጅጉ ይጎዳሉ። ነገር ግን አሳቾቹ ሳይቆዩ ይታወቃሉ፤ ታውቀው ይወገዛሉ፤ ይገለላሉ፤ ይነፈቃሉ። ወይም፥ መናፍቃኑ ራሳቸው ይነፍቃሉ፤ ከዚያ ይፈነቀሉና ይወጣሉ፤ ይለይያሉ። ከሁሉም በላይ የአሳቾች ማሳት በቃሉ ትምህርት ሊገለጥና ሊገታ ይችላል። ስለዚህ እነዚህ ጉዳቶች አደገኞች ቢሆኑም ፍቱን መድኃኒትም አላቸው፤ ያም መድኃኒት ቅዱስ ቃሉ ነው።

3. ውስጣዊ ጥቃት

እነዚህ ሦስተኞቹ ውስብስብ እና ረቂቅ ናቸውና ትንሽ ላብራራ። እነዚህ ተጣባቂ ጎጂዎች ናቸው። በአካሉ ላይ ተጣብቆ አካልን እየበላ ሊጎዳ የሚችል ጎጂ ችግር አለ። ሳይታዩ፥ ወይም ምናልባት እየታዩ አብረው እየኖሩ፥ ከውጪ እያቆሰሉ፥ ከውስጥ እያበሰበሱ፥ እንደ ነቀዝ እየቦረቦሩ፥ እየበሉ፥ እየመጠጡ፥ እያሰለሰሉ፥ እያቀጨጩ፥ እያቀነጨሩ፥ እያመነመኑ ቤተ ክርስቲያንን የሚያጠቁ ተዋሃስያን አሉ።

ይህንን በምሳሌ ላሳይ፥ አንዳንድ እንስሳት ላይ የሚጣበቁ ደም መጣጮች አሉ። ይህንን በገጠር፥ በእርሻና በከብት አርቢዎች አካባቢ ያደገ ማንም ያውቀዋል። በዚያ ከባቢ እንዳደገ ሰው ይህ የማውቀው ጉዳይ ነውና ትንሽ ላብራራው። እነዚህ እንስሳት ላይ የሚጣበቁ ደም መጣጮችና አመንማኞች በጠቅላላው ሦስት ዓይነቶች ናቸው። ቤተ ክርስቲያን እንደ አካል ናት ብያለሁና በአካልነቷም በእንደዚህ ያለ መንገድ፥ በእንደዚህ ያሉ ተጣባቂዎችም ስለምትጠቃ ንጽጽሩን በማስተዋል እንመልከተው። እነዚህ ተጣባቂዎች ሦስት ዓይነት ናቸው፤

አንደኞቹ ከላይ የሚጣበቁ ናቸው፥ እንደ ቅንቅን፥ እንደ መዥገር ያሉ ነፍሳት ናቸው። ቅንቅን ብዙ ጊዜ ዶሮዎችን የሚያጠቃ ተባይ ነው። በጣም ትንንሽ በመሆኑ ሆን ብለው ካላዩት አይታይም። በዶሮዎች ላባዎች ውስጥ ይገባና ይመጠምጣቸዋል። አንዳንዴ ከዶሮዎች ወደ ሌሎች እንስሳትና ወደ ሰዎችም ያልፋል፤ ሰው ላይ ብዙ አይቆዩም፤ ሙቀት በጣም ስለሚፈልጉ ጸጉር ውስጥ ካልገቡ ግን በቀላሉ ሊጠፉ ይችላሉ።







በስዕሉ እንደሚታየው መዥገሮች ሁለት ዓይነት ናቸው። አንዳንዶቹ እንደ ፊኛ የመሰሉ ደም ሲመጥጡ የሚነፋፉ መጣጮች ናቸው። ሁለተኛዎቹ ደግሞ በጣም ጠንካራና በመጠናቸው ትናንሽ ናቸው። በተለይ እነዚህ ጠንካራዎቹ የከብቶቹን ስስ ቆዳ ነው የሚበሱት። ብዙ ጊዜ የኋላ እግሮች መጋጠሚያና ላሞችና ጊደሮች ከሆኑ ግታቸው አካባቢ ነው የሚጣበቁት። ይህን ቦታ የሚመርጡት ቆዳው ከሌሎች ቦታዎች ስስ ስለሆነ፥ ሙቀት ስላለውና በወፎች በቀላሉ ስለማይለቀሙ ነው። በንባብ እንደተረዳሁት ደግሞ መዥገሮች የደም ስር ያለበትን ቦታ ከመውጋታቸውና መምጠጥ ከመጀመራቸው በፊት የሚወጉበትን ቦታ መጀመሪያ በትንሹ ወግተው እንደ ማደንዘዣ ዓይነት ነገር ያፈስሱና ስፍራውን ያደነዝዛሉ። ትኋኖችም እንደዚያ ነው የሚያደርጉት። ከዚያ በመምጠጫ ሹል ዋግምታቸው ሰርስረው በመግባት መምጣጥ ይጀምራሉ። እነዚህ መዥገሮች ስለሚታዩ እረኞች፥ ወይም የከብቶቹ ባለቤቶች በወረንጦ ይለቅሙና ያስወግዷቸዋል። አንዳንዴም ወፎች ይለቅሟቸዋል። ከብቶች ወይም የዱር እንስሳት ላይ የሚቀመጡ ወፎች አይተን ከሆነ ያንን እያደረጉ፥ ተባይና

መኸገሮችን እየለቀሙ ነው። መኸገሮች ከፉና አደገኛ መጣጮች ናቸው። ሆኖም ግን መዝገሮች ይታያሉ።

ሁለተኞቹ በከፊል የሚታዩ ወይም በመዘዛቸው የሚታዩ ናቸው። አልቅቶች የዚህ አንድ ምሳሌ ናቸው። አልቅቶች ውኃ ውስጥና በዳርቻው ነው የሚገኙት። እርጥበት ከሌለበት ደረቅ ቦታ ላይ መቆየት አይችሉም። ከብቶች ውኃ ሊጠጡ ሲመጡ ወይ በአፋቸው፥ ወይ በአፍንጫቸው ይገቡና ይጣበቁባቸዋል። ደረቅ ቦታ መኖር ስለማይችሉ የከብቶቹ እርጥብ ቦታ ላይ ነው የሚጣበቁት። አፋቸው ውስጥ ከገቡ ብዙ አይቆዩም። ከሚበሉት ሳር ወይም ከሚጠጡት ውኃ ጋር ወደ ሆድ ይገባሉ፤ ወደ ሆድ ከገቡ በኋላ እዚያ መቆየት አይችሉም። የጨጓራ አሲድ ይገድላቸዋል። አፍንጫ ውስጥ ከገቡ ግን ተጣብቀው ደም መምጠጥ ይጀምራሉ። ቦታውም እርጥበት ስላለው ይመቻቸዋል።

ደሙ የሚመጠጥ እንስሳ ፈጥኖ ወይም ዘግይቶ መክሳት ይጀምራል። ከሌሎቹ ይልቅ መክሳት ሲጀምሩ ከብት አርቢዎቹ፥ ወይም ገበሬዎቹ፥ ወይም እረኞቹ ይፈትሹና ችግሩን ፈጥነው ሊያገኙት ይችላሉ። አንዳንዴ ግን ብዙ ጉዳት አድርሰው ነው የሚታወቁት ወይም የሚታዩት። አልቅቶች የሚታወቁበት አንድ መንገድ ደም ነው። ከብቶቹ በአፍንጫቸው ደም ከፈሰሰ ያ ምልክቱ ነው። ከብቶቹ በገመድ ታስረው እመሬት ላይ ይጣሉና እንዳይንቀሳቀሱ ተደርገው አልቅቱ ወይም አልቅቶቹ ተመንጥቀው ወይ ተቆርጠው ይወጣሉ። አንዳንዶቹ አልቅቶች ወደ ስርናቸው ስለሚገቡ በቀላሉ አይገኙም። አልቅቶች በተፈጥሮአቸው ደም አይጠግቡም፤ በቃኝ አይሉም። ስለዚህ አብጠው እስኪፈርጡና እስኪሞቱ ድረስ ነው ደም የሚመጥጡት።

ሦስተኞቹ በምንም ዓይን የማይታዩ፥ ከውጪ ያይደሉ፥ ሆድ ውስጥ፥ ጨጓራ ውስጥ፥ አንጀት ውስጥ፥ ሌሎችም ብልቶች ውስጥ የሚገኙ ውስጣዊ ተዋሃስያን ናቸው። እነዚህን የከብት ሐኪሞች ብቻ ናቸው እበታቸውን ወይም ሽንታቸውን መርምረው፥ ወይም በሌላ በተማሩበት መንገድ መርምረው የሚያውቁትና የሚያከሙት። አንዳንድ አዋቂ ከብት አርቢዎችም በብዙ ልምድ ይህንን ይደርሱበታል። እነዚህ ተውሳኮች ደምና ጠቃሚ ንጥረ ነገሮችን የሚመጥጡትና የሚወስዱት ከውስጥ ነው። ብዙ ጊዜ አንጀት ላይ ይጣበቁና ነው እዚያ የሚኖሩት። እነዚህ ከሁሉም አደገኞቹ ናቸው። አይታዩምና ቶሎ አይታወቁም። ወይም ጭራሹኑም ሳይታወቁ እያመነመኑ ይኖራሉ።

ዛሬ ቤተ ክርስቲያን በሦስቱም ዓይነት አጥቂዎች እየተጠቃች ናት። እንደ መኸገር ባሉትም፥ እንደ አልቅት ባሉትም፥ በውስጥ ተዋሃስያንም እየተጠቃች ትገኛለች። አካል ናትና እንደ አካልነቷ የሚያመነምኗት፥ የሚያከሷት፥ የሚያቀጭጯት፥ የሚያቀነጭሯት መጣጮች አሉ። ቀደም ሲል እንዳልኩት ውጪያዊው ወረራ ወይም ስደት ቤተ

ክርስቲያንን አያጠፉትም። የስሕተት አስተማሪዎች ጉዳት ያስከትላሉ። ሆኖም እነዚህም በስሕተታቸው ቶሎ ወይም ዘግይተው ይታወቃሉ፤ ይገሰጻሉ፥ ይመለሳሉ፥ ወይም ይወገዛሉ። ብዙውን ጊዜ በእውነተኛው ትምህርት ይገለጣሉ። ነገር ግን፥ ስነ ምግባራዊ ወይም ግብረ ገባዊ ችግር ያለባቸው ሰዎች አደገኛ አጥቂዎች ናቸው። እነዚህ ሦስቱም እጅግ ጎጂዎችና አጥቂዎች ቢሆኑም፥ ከነዚህ ከሦስቱ በጣም የሚጎዱት ከውጭ ከተለጠፉቱ መጣጭ መዥገሮች የበለጠ የማይታዩት፥ እውስጥ የተሸሸጉት፥ በምሥጢር የሚሠሩት ናቸው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚነሡት ጉዳዮች ቤተ ክርስቲያንን በጥቂትም በብዙም ለአደጋ የሚያጋልጡ፥ የሚያጠቁም ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንዶቹ በአግባብ የሆነ አያያዝ የሚጠበቅባቸው መሐል ሰፈር ናቸው፤ ሥልጣን፥ ገንዘብ፥ ፖለቲካ ከነዚህ ይመደባሉ። አንዳንዶቹ ግን በግልጽ የአካል አመንማኞች ናቸው። እነዚህን ነገሮች ማወቅ ለራሳችንም፥ ለክርስቶስ አካልም ጤንነት የበኩላችንን አስተዋጽዖ እንድናደርግ ይረዳናል።

እንደገና መልካም ንባብ።

## ምዕራፍ ፩

# ክርስቲያንና ዘረኛነት / ብሔረተኛነት

ዘረኝነት ሲባል ብዙ ጊዜ የቆዳ ቀለም ወይም የነጭና ጥቁር ልዩነት ወደ አእምሮአችን ይመጣል። ዘረኝነት የቆዳ ቀለም ወይም የአገርና አገር ወይም የድንበርና ዜጋ መለያየት ብቻ አይደለም። ብሔርን፥ ነገድን፥ ጎሳንም የሚያካልል ነው። አንዱ ክፍል በሌላው ላይ የበላይነትን ሲያሳይና ሌላውን ሲንቅ፥ ሲያዋርድና የበታች ሲያደርግ ነው።

የበላይነት የተለያዩ ጎብሮች ወይም ቀለሞች አሉት። የቆዳ ቀለምም፥ የጎሳም፥ የሃይማኖትም ሊሆን ይችላል። እዚህ የማተኩረው እና ዘረኝነት የምለው የዘር ወይም የጎሳ ወይም የብሔር የበላይነትን ነው። እነዚህ የብሔር ወይም የጎሳ የበላይነቶች በፍጥነት የሚከሰቱት በወረራ፥ በጦርነት፥ በሕዝባዊ አለመረጋጋት እና በመሳሰሉት አገራዊ ቀውሶች ወቅትና ማግሥት ነው። ችግሩን ከፉና ለትውልዶችም ቀጣይ የሚያደርገ ነገር የልዩነት መደቡ የተለምዶው ኢኮኖሚያዊ ወይም ማኅበራዊ መደብ ሳይሆን ብሔር፥ ጎሳ፥ ዘር መሆኑ ነው።

ጉዳዩ ኢኮኖሚያዊ ቢሆን ሠርቶ አድጎ ወደ መስተካከል ይደረሳል። የእውቀት ጉዳይ ቢሆን ተምሮ ተመራምሮ እኩል መሆን ወይም ልቆ መገኘት ይቻላል። ብሔር፥ ዘር፥ ጎሳ ከሆነ ግን ሀብታም መሆንም፥ የተማሩ መሆንም አይለውጠውም። ስለዚህ ችግሩ ለትውልድ ወይም ትውልዶችም ሊተርፍ የሚችል ነው።

ዘረኝነት ጎልቶ የሚወጣበት መልኩ የበላይነት፥ እሻል ባይነት፥ ከዚህ ተያይዞ የሚመጣው ጨቋኝነትና ረጋጭነት ነው። ዝርዝር መሰለ እንጂ ሁለት ገጽ ያለው አንድ ሳንቲም ነው። አንዱ ገጽ እኔ የሚል ነው፤ እኔ የተሻልኩ፥ የበለጥኩ፥ የበላይ፥ የከበርኩ፥ የተከበርኩ፥ ባለ መብትና ባለ ሥልጣን ነኝ የሚል ነው። ሌላው ገጽ አንተ፥ አንቺ የሚል ነው። አንተ የበታች፥ ያነስክ፥ የተዋረድክ፥ ሥልጣን የማይታሰብልህ፥ መብትም የሌለህ፥ የተሰጠህን ብቻ የምትቀበል፥ የተባልከውን ብቻ የምትሆን ነህ የሚል ነው። በዚህ ሁለት ግልጽ መደብ ይፈጠራል። መደቡም የዘር ወይም የጎሳ

ወይም የብሔር ነው። እነዚህ ቃላት የተለያዩ ቢመስሉም ከግባቸው አንጻር ሲታዩ የተለያዩ አይደሉም።

በአንዳንድ አገሮች የዚህ ችግር መልክ እንደ ነጭና ጥቁር ግልጽ ነው። ዘረኝነነቱ ራሱም የነጭና ጥቁር ነው። በባርነትና ስረ መሠረት ላይ በተቆረቆሩት እንደ አሜሪካ ባሉ አገሮች ነጭ አሳዳሪ፥ ጥቁር ደግሞ ባሪያ ሆነው ኖረዋል። የዚህ ዘረኝነት አተላ ዛሬም ተሟጥጦ አልተደፋም። የጥንቱ ባርነት የቀለም አይደለም፤ ማንም ሰው፥ የቱም ሕዝብ ባሪያ ሊሆን ይችላል። እንደ ጀርመን ብሔራዊ ሶሻሊዝም (ናዚዝም) ፍልስፍና ደግሞ የአርያን ዘር የበላይ ሲሆን፥ የተቀሩት ሁሉ ደግሞ ማንም ከማንም ባልተለየ መልኩ፥ ትናንሽ እርከን ብቻ ኖሮ፥ ሁሉም የበታች ናቸው። የአዶልፍ ሂትለር የናዚ ፓርቲ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ስንት ሚሊየን ሕዝብ ፈጀ? ከአይሁድ ብቻ እንኳ ወደ 6 ሚሊየን! በጠቅላላ ወደ 20 ሚሊየን የሚጠጉ ሰዎች (ወይም ሕዝቦች) ተፈጅተዋል። ፍጅቱ genocide ወይም ዘር ማጥፋት ሳይሆን democide ወይም ሕዝብ ማጥፋት ነው የሚባለው። ይህ ፍጅት ብዙ ሕዝቦችን ያቋረጠ ብቻ ሳይሆን በሥልጣን ላይ ባለ ጉልበተኛ መንግሥት ቀጥተኛ ትእዛዝ የተፈጸመ በመሆኑ ነው።

እንደዚህ ያሉ ጨቋኝ ፍልስፍናዎች ሰዎችን ከማጥፋትና ከማውደም ጋርም የተያያዙ ናቸው። እብደት የተጫነው አምባ ገነንነት የተጠናወታቸው መሪዎች ሕዝቦችን ያለ ርኅራኄ ለማጥፋት ሁለቴ አያስቡም። የካምቦዲያው የክሜር ሩዥ አገዛዝ፥ የሩስያው እስታሊን የዩክሬይንን ሕዝብ የፈጀበት የሆሎዶሞር ታሪኮች ዘግናኝ ናቸው። ሆሎዶሞር በኡክራይና፥ 'በራብ መፍጀት' ወይም፥ 'በጠኔ መግደል' ማለት ነው፤ በ2 ዓመት (በ1932 እና 33) ከ10-12 ሚሊየን ዩክሬይኖች ነበሩ ያለቁት። በ1994 የሆነው የሩዋንዳው የሁቱዎች ጎሳ ቱትሲዎችን እና ለዘብተኛ ሁቱዎችን ያጸዱበት ዘርን የማጥፋት ዘግናኝ ፍጅት ነው።

አፍሪቃ ውስጥ እንደ ብዙዎቹ የዓለም ክፍሎች ጎሳዎችና የጎሳዎች መስተጋብር መኖሩ ታሪካዊ እውነት ነው። እንደ ሌሎቹ ሕዝቦች ሁሉ አንድ ቦታ የሕዝቡ ቁጥር ሲበዛ መስፈሪያም፥ የግጦሽ መሬት ፍለጋም ተነሥቶ ወራሪነት፥ ተስፋፊነት፥ አናሳዎቹን ፈንቃይነት፥ በቦታቸው ተተካይነት ወይም ተሠሪነት፥ አለመረጋጋት፥ ቆይቶ ስፍራን አውቆ መረጋጋት ከጥንት፥ ከሰዎች ብታኔ ማግሥት ጀምሮ የሆነ የዓለማችን ታሪክ ነው። የሰዎች ብታኔ ያልኩት ይህንን የምረዳው፥ እንደ ክርስቲያንና እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ በመሆኑ ነው። ብታኔ የቋንቋ መደባለቅን ተከትሎ የተከሰተውን በዘፍ. 11 የምናገኘው የሕዝቦች መበተን ወይም ስርጭት ነው። በዚህ የሰዎች ዝውውር፥ ባሉበት ሆኖ ለአሸናፊው መገዛት ወይም ቦታ መልቀቅና ማስለቀቅ እየሆኑ ኖረዋል።

ታሪክን ለለፈውና አሁን ወዳለንበት ስንመጣ አሁን ያለው የዓለማችን መልክ በታሪክ ሂደት ውስጥ የተቀረጸ ነው እንጂ ተቀርጾ የተሰጠን አይደለም። ቀረጻውም በጦርነት፥ በምርኮ፥ በቅኝ አገዛዝ፥ በአርነት፥ በድርድር፥ በስምምነትም ነው። ወደኛው አህጉር ስንመጣ፥ አፍሪቃ በሙሉ ማለት እስኪቻል፥ ቅኝ አህጉር ነበረች። ከ1950ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ እስከ 60ዎቹ የነጻነት ዓመታት በኋላ ቅኝ ገዢዎቹ አፋፍተውት የሄዱት (ተክለው ሳይሆን አፋፍተው የሄዱት) የጎሰኝነት ደዌ ለመንቀል ቀላል ሆኖ ያልተገኘ መርዘኛ አራሙቻ ነው። 'ተክለው ሳይሆን አፋፍተው' ያልኩት ጎሳዎች ቀድሞም የነበሩና በጎሳዎች መስተጋብር ውስጥ የሚከሰት ጎሰኝነት ወይም ብሔረተኝነት ቀድሞም የነበረ በመሆኑ ነው። ጎሰኝነትና ብሔረተኝነትን ቅኝ ገዢዎች ሲኖሩ ተጠቅመውበታል። ለቅቀው ሲሄዱም ጊዜ እየጠበቀ የሚፈነዳ ፈንጂ አድርገው ጥላቻን እና የበላይነትና የበታችነትን ስሜት ቀብረውበት ነው የሄዱት።

ብሔረተኝነትን የማሌ (ማርክሲዝም ሌኒኒዝም) መዝገበ ቃላት እንዲህ ይተረጉመዋል፤



**ብሔረተኝነት**
*(Nationalism)*

ሕዝቦችን በብሔር የሚከፋፍል የአንዱ ብሔር ሕዝብ የሌሎች ብሔሮችን ሕዝቦች በጥላቻ ፣ በጥርጣሬና በጠላትነት እንዲመለከት የሚገፋፋ የቡርዧው ርዕዮተዓለም አድኃሪ አዝማሚያ ነው ። ብሔረተኝነት ከካፒታሊዝም የሚመነጭና በብሔሮች መካከል ያለውን የተዛባ ግንኙነት የሚያንፀባርቅ ሲሆን በሁለት መሠረታዊ መልኮች ይከሰታል ። የመጀመሪያው በአንድ ወቅት በፖለቲካና በኢኮኖሚ የበላይነትን የያዘው ብሔር ወይም ብሔረሰብ ገዥ መደብ በሚያሳየው ትምክህተኝነት ሲንፀባረቅ ፣ ሁለተኛው ደግሞ ከዚሁ በመነጨ ሁኔታ በጭቁን ብሔሮች ወይም ብሔረሰቦች በዝባዥ መደቦች አካባቢ በሚታይ የጠባብ ብሔረተኝነት አዝማሚያ ይገለጻል ። የብሔር ትምክህተኝነትም ሆነ ጠባብ ብሔረተኝነት የበዝባዥ መደቦችን ፍላጐትና ዓላማ የሚያንፀባርቁ ፣ የልዩ ልዩ ብሔሮች ወይም ብሔረሰቦች ጭቁን መደቦችን የዓላማና የትግል አንድነት የሚፃረሩ የአንድ ክስተት ገጽታዎች ናቸው ።

የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት ገጽ 206-7

ብሔረተኝነት (Nationalism) ሕዝቦችን በብሔር የሚከፋፍል የአንዱ ብሔር ሕዝብ የሌሎች ብሔሮችን ሕዝቦች በጥላቻ፥ በጥርጣሬና በጠላትነት እንዲመለከት የሚገፋፋ የቡርዧው ርዕዮተ ዓለም አድኃሪ አዝማሚያ ነው። ብሔረተኝነት ከካፒታሊዝም የሚመነጭና በብሔሮች መካከል ያለውን የተዛባ ግንኙነት የሚያንጸባርቅ ሲሆን በሁለት መሠረታዊ መልኮች ይከሰታል። የመጀመሪያው በአንድ ወቅት በፖለቲካና በኢኮኖሚ የበላይነትን የያዘው ብሔር ወይም ብሔረ ሰብ ገዥ መደብ በሚያሳየው ትምክህተኝነት ሲንጸባረቅ፥ ሁለተኛው ደግሞ ከዚሁ በመነጨ ሁኔታ በጭቁን ብሔሮች ወይም ብሔረ ሰቦች በዝባዥ መደቦች አካባቢ የሚታይ የጠባብ ብሔረተኝነት አዝማሚያ ይገለጻል። የብሔር ትምክህተኝነትም ሆነ ጠባብ ብሔረተኝነት የበዝባዥ መደቦችን ፍላጎትና ዓላማ የሚያንጸባርቁ የልዩ ልዩ ብሔሮች ወይም ብሔረ ሰቦች ጭቁን መደቦችን የዓላማና የትግል አንድነት የሚጻረሩ የአንድ ክስተት ገጽታዎች ናቸው። (የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት፤ ገጽ 206-7)።

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም በራሱ በአንድ ወቅት የከበረ፥ ኋላ ግን የከሰረ ርዕዮት መሆኑን ሁላችንም ባልል እንኳ ብዙዎቻችን የምንቀበል ይመስለኛል። እዚህ ትርጉም ውስጥም ታሪካዊ ጥርሰት አለበት። ለምሳሌ፥ 'ብሔረተኝነት ከካፒታሊዝም የሚመነጭና' የተባለው ስሕተት ነው። የብሔረተኝነት ዕድሜ ከካፒታሊዝም እጅግ ይበልጣል። እንደኔ፥ እንደ አንድ ክርስቲያን መረዳት የማርክሲዝም ወይም ኮሚኒዝም መሠረቱ የተናደበት መሪ ስሕተት እግዚአብሔርን ከስሌቱ ውስጥ ማውጣቱ ነው። በውጤቱም የታየው ይኸው ነው። መቶ ዓመት ሳይሞላው ከአናቱም ከእግሩም፥ ከስሩም ከቅርንጫፉም ፍርክስክሱ የወጣው ለዚህ ነው። ሆኖም ግን ብሔረተኝነትን በተመለከተ የፍልስፍናው አስተሳሰብ ይህ ነበር። ይህን ትርጉም የፈለግሁበት ምክንያት ያለፈውን ግማሽ ምዕት ዓመት አገራችንን የመሩት መንግሥታት ፍልስፍናቸው ማርክሲዝም ስለሆነ ነው። ደርግ ማርክሲስት የሆነው በግፊት እና ምንነቱን አጢኖ በመረዳት ባይሆንም ማርክሲስት ነበር። ደርግ ወደ ሥልጣን ሲወጣ ፍልስፍና አልነበረውም። ከደርግ በኋላ የመጣው ኢሕአዴግም ማርክሲስት ነው፤ ቢያንስ ጅምሩ ማርክሲስት ነው፤ ያውም አልባኒያዊ ዝግ ኮሚኒስት። እና ይህን ትርጉም የወሰድኩት ፍልስፍናችን ነው ብለው የተነሡበትና ያውለበለቡት በመሆኑና አሁን ላለንበት የዘር ፌዴራሊዝም ጥርጊያው መንገድ የተጠረገበት በመሆኑ ነው።

ደርግ እስከ እርሱ ከነበሩት መንግሥታት ይልቅ የብሔረሰቦችን መብት ጠብቆ ነበር። ከደርግ በኋላ የመጣው መንግሥት ደግሞ የብሔረ ሰቦችን መብት መጠበቅን ግብ አድርጎ፥ ጎሰኝነትን ወደ ፌዴራሊዝም ውስጥ አስገብቶ የፍልስፍናውን መርህ የጣሰበትን አካሄድ ልብ እንበል። የብሔር መብት እና ብሔረተኝነት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። የብሔር መብት እስከ መገንጠል የሚለው የዘረኛ ፌዴራሊዝም መርህ አስቀድሞ ለመገንጠል ወይም ለማገንጠል ተብሎ የተቀረጸና ወይም፥ እስኪገነጠሉ ለአገዛዝ ተብሎ የተቀመጠ እንጂ ከዘመናችን አስተሳሰብ ጋር የማይሄድ ነው። ደግሞም ሕዝባዊ ተሳትፎና ተአምኖት ያልነበረው፥ የሌለውም ውሳኔ ነው። ይህ ዘረኛ ፌዴራሊዝም በዓለማችን በየትኛውም የሰለጡኑ የዘመናችን አገሮች ተግባራዊ ያልሆነና እንዲሆንም የማይፈለግ የተወገዘና የተጠላ መርህ ነው። በዓለማችን ብዙ ፌዴራላዊ አገሮች አሉ፤ ማናቸውም በዘር የተመሠረተና እስከ መገንጠል የሚል መርህ ግን አይከተሉም።

ይህንን ከአሁኗ ዓለማችን ብቻ ሳይሆን ከአሁኗ አገራችንም አንጻር ማየት አለብን። አገራችን በአሁኑ ጊዜ ባልተረጋጋ መረጋጋት ወይም ለአንዳንዶች በተረጋጋ አለመረጋጋት ውስጥ ናት። የብሔር፥ የዘር፥ የጎሳ ጉዳይ አፈትልኮ ሳይሆን ጥሶ፥ ጠርምሶ እየወጣ ነው ሳይሆን ወጥቶአል። በዚህ ውስጥ እንደ ክርስቲያን

የምንጫወተው ሚና አለን። ከላይ እንዳልኩት ወደ ፊት ሮጠን አሁን ወዳለንበት ዘመን ስንመጣ የዘረኝነትን ደዌና አክሳሪነት ከሁለት አቅጣጫ ማየት እፈልጋለሁ።

አንደኛው፥ አሁን ያለው የዓለማችን መልክ በታሪክ ሂደት ውስጥ የተቀረጸ ብቻ ሳይሆን ዛሬ ዓለም መንደር እየሆነች ናት። ትንሽ እየሆነች ግን ወደ ማነስና ወደ መቀነስ ሳይሆን ወደ መብዛትና ወደ መደመር፤ (መደመር የሚለው ቃል ከጥቂት ወራት በፊት ሲለመድ ተደጋግሞ የሰማሁት የእንግሊዝኛ አቻው integration የሚል ነው።) ወደ መበተን ሳይሆን ወደ አንድነት በምታዘግምበት ጊዜ ጎሰኝነትና ጎጠኝነት፥ ብሔረተኝነትና ዘረኝነት ዘመን ያለፈበት ፍልስፍና ነው።

ሁለተኛው፥ ከዓለም መንደርነት አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን ይህን የማካፍለው ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና አንጻር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን ሰውን የፈጠረ እግዚአብሔር ነው። ሁላችንም የተፈጠርነው ከአንድ ጥንድ ወላጆች ከአዳምና ከሔዋን ነው። ከጥፋት ውኃ በኋላ ወዳለው ታሪክ ስንመጣም ሁላችንም የኖኅ ልጆች ነን፤ የካም፥ የሴም፥ የያፌት ልጆች ነን። እንዲያው ይህን አላምንም አልቀበልም የሚሉ ቢኖሩ እንኳ፥ 'የለም እኔ የመጣሁት በዝግምተኛ ለውጥ ከዝንጀሮ ነው' ቢሉ እንኳ ያው እያሉ ያሉት፥ 'ሁላችንም የመጣን ከዝጀሮ ነው' ነው። እንጂ አማራው ከዝንጀሮ (ከሉሲ)፥ አይሁድ ከአሳማ እያሉ አይደለም። (አይሁድ ከአሳማ መጣ ብለው የሚያስተምሩም አሉ።) ነጥቡ ሁላችንም ከአንድ ምንጭ መገኘታችን ነው።

ይህ የሁላችንም ከአንድ ምንጭ መገኘታችን እውነትነት ይሰመርበት። ቆዳችን ቢላጥ ሁላችንም አንድ ዓይነት ነን። የሁላችንም ፍጥረት አንድ ነው። ሁላችንም 46 ክሮሞዞም ያለን ሰዎች ነን። ሁላችንም ሰዎች ነን። ይህ ሰውነታችን፥ ሰው መሆናችን ብቻውን ከቡራንና ከቡራት ያደረገን ፍጡሮች ነን። አንዳችን ከሌላችን በቁመት ወይ በውፍረት እንበልጥ ወይ እናንስ ይሆናል እንጂ በሥሪትና በፍጥረት አንበልጥምም አናንስምም። ይህ ማለት ታዲያ በግድ የሌላውን ብሔር ጫና መቀበል ብቻ ሳይሆን የራስን ማንነት መጣልንም ይመለከታል።

ይህንን ጉዳይ፥ 'ዘረኝነት ደዌ ነው፤ ጎሰኞችና ዘረኞችም ድውያን ናቸው፤ ለፖለቲካ ግብዓትና ግብይት ከዋሉ ብሔረኝነትና ብሔረተኝነትም ደዌዎች ናቸው' በማለት በመፈክር ደረጃ ብቻ በፌስቡክ ገጼ በጻፍኩበት ስፍራ አንድ ሰው፥ 'በግድ ኢትዮጵያዊ መሆንም በሽታ ነው' ብሎ ነበር። አሁን አሁን ኢትዮጵያዊ የአንድ አገርነት ወይም ሕዝብነት ስሜት እየገነነ መምጣቱ ጠባብ ብሔረተኞችን እያስቆጣቸው መምጣቱ በግልጽ የሚታይ ነው። ይህ፥ 'በግድ ኢትዮጵያዊ መሆንም በሽታ ነው' የተሰኘው ምናልባት ይህንን የሚያንጸባርቅ አስተያየት ሳይሆን አይቀርም ብዬ እገምታለሁ። ሆኖም ግን በዚህ ጉዳይ ላይ እዚያም በአጭሩ የጻፍኩትን መልስ እዚህም ልድገመው።

ኢትዮጵያዊነት ዜግነት ነው። ዜግነት ደግሞ በአንድ አገር የመወለድ፥ የመኖር፥ እንዲሁም በምርጫ የመቀበል ጉዳይ ነው። ይህ የዜግነት ጉዳይ ግዴታ ስለሌለበት ደዌ ሊባል አይቻልም። በግዴታ ከተጫነ ሊባል ይቻላል። በግዴታ የሚጫን ዜግነት ደግሞ የለም። ብሔረተኝነትና ዜግነት የተለያዩ ናቸው። ኢትዮጵያዊነትና አማራነት ወይም ኢትዮጵያዊነትና ሲዳማነት የተለያዩ ናቸው። አማራነት አማራዊነት አይደለም፤ ዜግነት አይደለምና። የየትኛውም ብሔር ወይም ጎሳ ሰዎች ሆነን ኢትዮጵያ ውስጥ ስለተወለድን ኢትዮጵያዊ ነን። ይህንን ዜግነት ያልወደደ ሰው ከአገሩ ወጥቶ ሌላ አገር ሄዶ፥ ከመብቶቹና ከግዴታዎቹ ጋር ሂደቱን ጠብቆ የሌላ አገር ዜጋ መሆን ይችላል። ኢትዮጵያዊ መሆን ብሔር ቀይሮ ሌላ ብሔር መሆን አይደለም። ኢትዮጵያ የሚባል ጎሳ ወይም ብሔር የለም እንጂ ቢኖርና አንድ ሰው በግድ የኢትዮጵያ ጎሳ ወይም ብሔር እንዲሆን ቢደረግ ይህም ደዌ ነው ማለት ይቻላል።

ይህ ማለት ለተወለድንበት ሕዝብ ወይም ብሔር ደንታቢስ እንሆናለን ማለት ነው? አይደለም። እንደ ዜጋም፥ እንደ አማኝም ፈጽሞ፥ ከቶም ደንታቢስ አንሆንም። ያ ብሔር ከማንም ወይም ከሌላው ሁሉ ብሔር አለመብለጡን እናጸድቃለን እንጂ። አንዳንድ ብሔሮች ወይም ጎሳዎች ከደረሰባቸው ጠባሳ ወይም በታሪካዊ አጋጣሚ ከተከሰተ ክስተት የተነሣ ጊዜና አጋጣሚ ሲያገኙ ወደ ብቀላዊ የበላይነት ይዘረጋሉ። በዚህ የጎሳ ስሌት ውስጥ ደግሞ ሃይማኖታዊ ጡንቻ ሲጨመርበት እሳት ላይ ነዳጅ መጨመር ይሆናል። ይህ ክፉ አካሄድ ነው።

## ብሔረተኝነት ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና አንጻርስ?

የእስካሁኑ አጠቃላይ እይታዬ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና አንጻርስ ዘረኝነት ወይም ብሔረተኝነት እንዴት ይታያል? 'ከክርስትና አንጻር' ከማለት ይልቅ፥ 'ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና አንጻር' ያልኩት ሆን ብዬ ነው። ምክንያቱም በክርስትና ስም ዘረኝነትን ያስፋፉ ሰዎች ኖረው ያውቃሉ። የዘርም ሆነ የሃይማኖት የበላይነትን በሌሎች ላይ የጫኑ ሰዎች ኖረው ያውቃሉ። በስም ክርስቲያን ተብለው እንደ ቃሉ ያይደሉም ኖረው ያውቃሉ፤ ዛሬም አሉ። ያ ሕዝባዊ ክርስትና እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና ስላልሆነ ነው 'ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና አንጻር' የሚለውን ሐረግ ለመጠቀም የወደድኩት።

በብሔር መብት ተቆርቋሪነትና ተሟጋችነት ሳይሆን በብሔረተኝነት ፍልስፍና ውስጥ ንቁ ተሳታፊ የሆኑ ክርስቲያኖች መኖራቸው በእጅጉ አሳፋሪ ጉዳይ ነው። ሁለቱንም አሳብ ልድገመው፤ አንዱ፥ ለብሔር መብት መቆርቆርና መሟገት ተገቢ መሆኑ ነው።

አንዳንድ ጎሳዎችና ብሔሮች በተለያዩ ምክንያቶች ተንገዋልለው ወደ ጎን መገፋት ብቻ ሳይሆን የበታችነት ቀንበር ውስጥ ሊወድቁ ይችላሉ፤ ወድቀዋልም። በተለያዩ ምክንያቶች ስል ምክንያቶቹ፥ ከሌላ ጎሳ ጭቆና፥ ከመደብ ጭቆና፥ ከሃይማኖት ጭቆና፥ ከመንግሥታዊ አሠራር፥ ከንቃተ ሕሊና ማነስ፥ እና ሌሎችም ሊኖሩበት ይችላሉ።

ሁለተኛው የምደግመው አሳብ የክርስቲያኖች በብሔረተኝነት ፍልስፍና ውስጥ ንቁ ተሳታፊ መሆን በእጅጉ አሳፋሪ ጉዳይ መሆኑ ነው። ለምሳሌ፥ (ይህ ከብዙ ምሳሌዎች አንዱ ሊሆን ይችላል) በቋንቋዬ ላምልክ ማለት ትክክል ነገር ነው። በማላውቀው ግዕዝ እየተቀደሰልኝ ሳልሰማ መጥቼ ከመሄድ በማውቀው ሲዳሚኛ ወይም አገዊ ልሰበክ ማለት ጤናማ ነው። እንዲያውም ይህ ለጥያቄም ከመቅረቡ በፊት ሰባኪዎቹና ቀዳሾቹ ራሳቸው ናቸው ማድረግ የነበረባቸው። ለዚህ ነው እኮ ወንጌልን ይዘው ወንጌል ወዳልደረሰበት አገር የሚሄዱ ወንጌላውያን የዚያን ሕዝብ ቋንቋ ቀድመው ተምረው በዚያው ቋንቋ የሚያስተምሩት። ከኔ ካልበለጠ የማያንስ አማርኛ የሚናገሩ ሁለት ካናዳውያን ሴቶች ሚስዮናውያን አውቃለሁ። አንዷ አስተምራኛለች፤ ከሌላዋ ጋር አብረን መጽሐፍ ተርጉመናል። ይህ ለምሳሌ ያነሳሁትን ቋንቋን በተመለከተ ነው።

እንደ ወንጌል የሰዎችን ሕይወት የሚለውጥ ኃይል አይቼም ሰምቼም አላውቅም። ትልቁ የለዋጭነቱ ምስጢር ወንጌል ሰዎችን ከውስጥ ጀምሮ ወደ ውጪ ስለሚለውጥ ነው። ቀደም ሲል እንዳልኩት ሁላችን ከአንድ ምንጭ መቀዳታችንን ከተቀበልን ያ ብቻውን እኔ ከሌላው በፍጥረቴ የማልበልጥም የማላንስም መሆኔን ይመሰክራል። ከዚህ ባሻገር በወንጌል መለውወጥ የተለወጥን ሰዎች ደግሞ ሌላ እርከን የተሻገርን ሰዎች ነን። በክርስቶስ መስቀል አማካይነት የተፈጠረ አንድ አካል መኖሩን ያወቅን ሰዎች ነን።

ጳውሎስ ለቆላስይስ አማኞች ከክርስቶስ ጋር መሞታቸውን፥ መነሣታቸውንና በሰማያት መቀመጣቸውን፥ አዲሱን ሰው መልበሳቸውን ከተናገረ በኋላ፥ *በዚያም የግሪክ ሰው አይሁዳዊም የተገረዘም ያልተገረዘም አረማዊም እስኩቴስም ባሪያም ጨዋ ሰውም መሆን አልተቻለም፥ ነገር ግን ክርስቶስ ሁሉ ነው፥ በሁሉም ነው።* አለ፤ ቆላ. 3፥11። በዚህ ቃል ውስጥ የአገር፥ የዜግነት፥ የብሔርና የመደብ ልዩነቶች ሲሟሙ ነው የሚታየው። ክርስቲያን በክርስቶስ አምኖ ሲድን ልዩ ፍጥረት ሆኖአል፤ *ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።* 2ቆሮ. 5፥17።

ይህ አዲስ ፍጥረትነት ብሔራችንን ይደመስሰዋል ወይም ይፍቀዋል ማለት ሳይሆን ይሰርዘዋል ወይም ሰረዝ ያደርግበታል። ያንን አልነበርኩም ወይም አይደለሁም ማለት ሳይሆን፥ ያንን የሚያስንቀውንና የሚበልጠውን፥ ዘላለማዊም የሆነውን ይህኛውን

*ተቀዳጅቻለሁ* ማለት ነው። ይህን የሚያስደርገው፥ በ1ጴጥ. 1፥23 የተጻፈው እውነት ነው፤ *ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፥ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ።* ይላል። ክርስቲያን ዘረኛ አይደለም ሲባል ወይም ዘረኛ እንዳይሆን የሚያደርገው ከማይጠፋው ዘር መወለዱ ነው። ይህ የማይጠፋ ዘር ከሚጠፋው የሚበልጥ ነው። አይጠፋማ፤ ምድራዊ አይደለማ።

ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎችም ሲጽፍም ይህንን አሳብ አስምሮበታል። ከክርስቶስ ጋር አንድ ሊሆኑ የተጠመቁ ሁሉ ክርስቶስን መልበሳቸውን ከተናገረ በኋላ እንዲህ አለ፤ *አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና።* ገላ. 3፥28። ለአንድ አይሁዳዊ ሰው የግሪክን (ወይም የአሕዛብን) ሰውና ባሕል መቀበል መራራ ነገር ነው። ሁለቱም ወደ ክርስቶስ ሲመጡ ግን አንዱ ሌላውን በፍቅር ይቀበላል።

ለጨዋ ሰው ወይም ነጻ ዜጋ ባሪያን እንደ እኩያ መቀበል የማይቻል ነው። ሁለቱም በክርስቶስ ሲሆኑ ግን ወንድማማች ናቸው። ጳውሎስ ለፊልሞና ስለ አናሲሞስ ሲጽፍ በፊልሞና ቁጥር 16 ላይ እንዲህ አለ፤ *ከእንግዲህ ወዲህ እንደ ባሪያ አይሆንም፥ ነገር ግን ለእኔ በተለየ የተወደደ ወንድም ከሆነ፥ ለአንተማ ይልቅ በስጋውም በጌታም ዘንድ ከባሪያ የሚሻል የተወደደ ወንድም እንዴት አይሆንም።* አናሲሞስ ከአሳዳሪው ከፊልሞና ዘንድ ኮብልሎ ተይዞ የታሰረና በወኅኒ ቤት ሳለ ወንጌልን ሰምቶ የዳነ ባሪያ ነው። ይህ ደብዳቤ ወይም የፊልሞና መልእክት አናሲሞስ ይዞ ወደ ቆላስይስ ከተማና ራሱም ክርስቲያን ወደሆነ ወደ ቀድሞ ጌታው ሲመለስ ይዞ እንዲሄድ የተጻፈ ደብዳቤ ነው። ግንኙነቱ የባሪያና ጌታ ሳይሆን የተወደደ ወንድምነት ግንኙነት ሆነ። ወንጌል እንዲህ የሚለውጥ ኃይል ነው። ወንጌል ኃይል ስለመሆኑ ጳውሎስ ሲናገር እንዲህ አለ፤ *በወንጌል አላፍርምና፤ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው፥ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና።* ሮሜ 1፥16። አይሁድና አሕዛብን፥ ጌታና ባሪያን አስተካክሎ ወንድማማች የሚያደርግ ኃይል ነው ወንጌል።

ክርስትናና ጎሰኝነት ወይም ብሔረተኝነት ፈጽሞ አብረው የማይሄዱ ነገሮች ናቸው። አንድ ብሔረተኛ ሰው ክርስቲያን ሲሆን ብሔረተኝነቱን ይተዋል። ወይም ቀድሞ ክርስቲያን ከሆነ ብሔረተኛ ሊሆን አይችልም፤ ለዚያ የሚሆን ክፍል እቤቱም እደጁም የለም። ይህ ማለት ብሔሩን ይተዋል ማለት አይደለም፤ ይህ የሚተዉት ነገር አይደለም። አንድ ሰው የተገኘበትን ብሔር መውደድ አንድ ነገር ነው። ለዚያ ወገን ሁለንተናዊ እድገት መሥራት አንድ ነገር ነው። ያ ብሔር ልዩ መሆኑን ማሰብ ግን የተሳሳተ ሒሳብ ነው። ጥቅም የሌለው፥ ምናልባት የዚያ ብሔር ጥቂት የውሸት ልሂቃን ሰዎች ብቻ የሚጠቀሙበት፥ ሰፊው ብሔር ግን እየከፈለው የሚኖረውና ዋጋው ሲሰላ ብዙ የሆነ ተከፍሎም የማያልቅ ዕዳ ነው። ብሔረተኝነት ጥቅም የሌለው

ዕቃ ለመግዛት ከፍለው የማይጨርሱት ዕዳ ውስጥ የመግባት የሕይወት ኪሳራ ነው። የሚከፋው ደግሞ ዕዳውን አንድ ብቻ ሳይሆን ቀጣይ ትውልዶችም እንዲከፍሉት ሲደረግ ነው። የዚህ ዕዳ ወለድ ደግሞ compounded interest እንደሚባለው ያለ ሆኖ፥ እየተገላበጠ ስለሚቀጥል ከዋናው ይበልጣል። ክርስቲያን የዚህ የብሔረተኝነትና የዘረኝነት እኩይ አስተሳሰብ ተሳታፊና ተጋሪ መሆን የለበትም። ዘረኝነት ደዌ ነው፤ ጎሰኞችና ዘረኞችም ድውያን ናቸው።

መፍትሔውስ?

የዚህ መፍትሔና መድኃኒት በመጀመሪያ የዘረኝነትንና የብሔረተኝነትን በሽታነቱን፥ ደዌነቱን መቀበል ነው። ችግርን ማወቅ የመፍትሔውን ግማሽ ማወቅ ነው የሚባለው እውነት ነው። የአንድን ጎሳ ወይም ብሔር ሰው ስታስብ የሚያስጠላህ፥ ሰላምታ የምትነሳው፥ ሰላምም የምትነሳው፥ ቀና ብለህ በአፍንጫህ ስር የምታየው፥ ወይም ልታየው የማትፈልግ፥ ብትችል እንዳታየው ከክልልህ እንዲወጣ የምትፈልግ፥ ስለ ዘር፥ ስለ ጎሳ፥ ስለ ብሔር ኮርስ የወሰድክ ያህል ስለዚህ ጉዳይ ብዙ የምታወራ፥ ስታወራም አንድን፥ የራስህን ጎሳ እየካብክ፥ ሌላውን፥ ያንተ ያልሆነውን የምትንድ ከሆንክ፥ ሌላ ብሔር ስታስብ በምላስህ ላይ ሳይሆን በልብህ ውስጥ ምሬት የሚሰማህ ከሆነ እነዚህ ከበሽታው ምልክቶች ጥቂቶቹ ናቸው።

ሁለተኛው፥ የመፍትሔ እርምጃ አስተሳሰብን ለመለወጥ ፈቃደኛ ሆኖ መገኘት ነው። ደዌውን ማወቅ ብቻ ሳይሆን መድኃኒቱን ለመውሰድም ፈቃደኛ መሆንን ይጠይቃል። አካላዊ መድኃኒቶችን እንኳ ብንወስድ፥ መድኃኒቶች በመጠንም፥ በዓይነትም፥ በአሠራርም የተለያዩና ብዙ ናቸው። የአገር ባህል መድኃኒት አለ፤ ዘመናዊ መድኃኒት አለ፤ ልዩ አማራጭ ወይም alternative medicines የሚባሉ አሉ፤ ስነ ልቡናዊና ምክራዊ ልምምዶች አሉ፤ እነዚህም እንደ ፈውስ ማምጫ ይቆጠራሉ፤ ሌሎችም ዓይነት አሉ።

ዘረኝነት የጥላቻ አስተሳሰብም ነው። ይህንን አስተሳሰብ ለመለወጥ መፍቀድ ቀጣዩ እርምጃ ነው። አስተሳሰቡ ደግሞ፥ ማለትም የተበላሸው አስተሳሰብ በሌላ አስተሳሰብ፥ በታደሰ አስተሳሰብ ነው መሸነፍ ያለበት። አስተሳሰብ በአስተሳሰብ ነው የሚለወጠው። መንግሥታዊ ፖሊሲዎችን፥ የፓርቲ አጀንዳዎችን፥ የምሑራን አሳቦችን፥ አስተሳሰባዊ መሐይምነትን የሚቀርፉ አስተምህሮቶችን የዓለማችንን የቀደሙ ታሪኮችን፥ የአሁኑን የሕዝቦች ግንኙነቶችንና መስተጋብሮች ሂደቶችን፥ ሌሎችንም ለመቅሰም ክፍት መሆን

ፍፈቃደኛ መሆን፥ ለመልለወጥ እሺ ማለት፥ 'የቱ የተሻለ ነው?' ማለት፥ እነዚህ ቀጣይ የፈውስ እርምጃዎች ናቸው።

ሦስተኛው፥ እንደኔ መረዳት ሁነኛውና ዋናው መፍትሔ ይህኛው ነው፤ እርሱም የክርስቶስ ወንጌል ነው። 'እንዴት? ይህንን እየተናገርክ ያለኸው ለክርስቲያኖች አይደለም ወይ? ክርስቲያኖች ዘረኞችና ብሔረተኞች እንዳይሆኑ አይደለም ወይ? ይህ ማለት እኮ ቀድሞውኑ ክርስቲያኖች ከሆኑ ብሔረተኞች አይደሉም እያልክ ነህ ማለት ነው።' ሊሰኝ ይችላል። ለዚህም መልስ አለኝ።

በመጀመሪያ፥ ክርስቲያን ላልሆነው ሰው ልናገር፤ ፍቱኑ መድኃኒት አንድን አካል ለራሱ ሊፈጥር በመስቀል ላይ የሞተውን ክርስቶስን መቀበል ነው። ክርስቶስን መቀበል ብቻውን ከዘረኝነትና ከብሔረተኝነት ደዌና እስራት ብቻ ሳይሆን ከዘላለም ሞትና ኩነኔና ቅጣት የሚያድን መፍትሔ ነው። ዘረኝነት ጥላቻ ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ደግሞ ወንድሙን የሚጠላ ነፍሰ ገዳይ ነው ተብሎአል። *ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ አለ፥ በጨለማም ይመላለሳል፥ የሚሄድበትንም አያውቅም፥ ጨለማው ዓይኖቹን አሳውሮታልና። . . . ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው፥ ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ።* 1ዮሐ. 2፥11 እና 3፥15። ይህ ወንድሙን ነው የሚለው እንጂ ሌላውን አይደለም ሊባል ይችላል። የጌታን ትምህርት እንስማ፤ *ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና።* ማቴ. 5፥43-45። ይህ መለኪያው ነው።

ቀድሞውኑ ክርስቲያን ነን ለሚሉስ? ክርስቲያን ነን እያሉ የዘረኝነትና የብሔረተኝነት ዘፋኝ፥ አቀንቃኝ ለሆኑትስ? ለእነዚህም የምለው አለኝ። ቀደም ሲል፥ 'ዘረኝነትና ብሔረተኝነት ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና ጋር አብረው አይሄዱም' ብያለሁ። በስም ክርስቲያን ተብለው እንደ ቃሉ፥ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ የማይመላለሱ ዘረኛ ሰዎች ሊኖሩ አይችሉም አልልም። ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ ሰዎች ይህንን ለምን እንደሚያደርጉ የልባቸውን ግፊት ወይም ተነሣስቶት አላውቅም። ንቀትና ጥላቻ እንዳለበት ግን ግልጽ ነው። ዘረኞች እግዚአብሔር በመልኩና በአምሳሉ የፈጠረውን ፍጡር ይንቃሉ። የሚንቁ ከሆኑ እግዚአብሔርንም እየናቁ ናቸው። ይህ ኃጢአት ነው። ዘረኞች እግዚአብሔር በመልኩና በአምሳሉ የፈጠረውን ሰው ይጠላሉ። የሚጠሉ ከሆኑ በእግዚአብሔር መለኪያ ነፍሰ ገዳዮች ናቸው። ነፍሰ ገዳዮች ሲል ነፍሰ ገዳይነት የሚጀምርበትን ልብን ማመልከቱ ነው። እነዚህ ሰዎች ማድረግ

ያለባቸው ድርጊታቸውን ከቅዱስ ቃሉ ጋር ማነጻጸርና ወደ ቃሉ እውነት በንስሐ መምመለስ ነው።

እንደ ክርስቶስ ትምህርት ለመኖር የምንጥር ደቀ መዛሙርት ሁላችን ደግሞ በነፍስ ወከፍ፥ እንደ ክርስቲያን ከዚህ ሕመም የታከምን ወይም ከወረርሽኙ የተጠበቅን መሆናችንን ሁሉ ይወቅልን። እንደ ቤተ ክርስቲያንም ከዘረኝነትና ከብሔረተኝነት የጸዳን መሆናችን ይሰበክልን። ማን ያውቃል? እያምጣውና፥ ሚርተኛ አልሁንና፥ የሩዋንዳው የዘር ጽዳት እልቂት በአገራችን ቢከሰት ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ዘሮችና ብሔሮች መተቃቀፊያ ትሆናለች? ወይስ መነቃቀፊያና የማረጃና መተራረጃ ቄራ? ቤተ ክርስቲያን መወጋገኛ አለመሆኗንስ <u>በቃሏና በኑሮዋ</u> አሁኑኑ፥ ከወዲሁ፥ ምንም ነገር ሳይኖርም ማሳወቅ አይኖርባትም? ቤተ ክርስቲያን ለዘር አጽጂዎች ዘር አጽጂ ሳትሆን ዘረኝነትን አጽጂ መሆኗን ማሳየት የለባትም? አለባት። በነጠላም፥ እንደ ማኅበርም ይህንን የማድረግ ኃላፊነት አለብን። ስለዚህ ቅዱሳንና የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ሰባኪዎች ይህን ከመድረካቸውም ሊሰብኩት የተገባ ነው።

ራእ. 5፥9-10 *መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፥ ታርደሃልና፥ በደምህም ለእግዚአብሔር <u>ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ</u> ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው፥ በምድርም ላይ ይነግሣሉ እያሉ አዲስን ቅኔ ይዘምራሉ። <u>ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ።</u>*

እነዚህ ለዘላለም አብረናቸው የምንኖር ሰዎች ናቸው፤ ነን። እኛም ከእነዚህ ነን። ከነዚህ ውስጥ የዚህም የዚያም ብሔረ ሰብ ሰዎች አሉበት። ይህም ያም ቋንቋ፤ ይህም ያም ወገን፤ ይህም ያም ነገድ፥ ቅይጦችና ቅይጥይጦችም አለንበት። እዚያ ዘርና ጎሳ ስለሌለ እዚህ ያንን ሕይወት አሁንና እዚህ ልንለማመደው ግድ ይላል። ይህ ወደ ልባችን ዘልቆ ሊገባ የተገባው ድንቅ እውነት ነው።

ላለፉት 30 ዓመታት የጎሰኝነት ፖለቲካ ሲዘፈንበት እንደኖረው እንደ አገራችን ባለ የጎሳ ፌዴራሊዝም ውስጥ ከጎሰኝነት መጽዳትን ማሰብን ራሱንም እንደ ወንጀልም የሚያዩት አይጠፉም። ሆኖም እንደ ክርስቲያን ስናስብና ስንኖር ዘረኝነትና ብሔረተኝነት ደዌ ነው። ዘረኞችና ብሔረተኞችም ድውያን ናቸው። ከዚህ ክፉ ደዌ መድኃኒት የሆነው፥ ጌታ የዓለም መድኃኒት እርሱ ይታደገን። አሜን።

## ምዕራፍ ፪

# ክርስቲያንና ፖለቲካ

ይህንን አሳብ በቪድዮ ከማካፈሌ በፊት መጀመሪያ የጻፍኩበት መንደርደሪያው፥ በኖቬምበር ወር 2016 'መንግሥት፥ ቤተ ክርስቲያን እና ደቀ መዝሙር' በሚል ርእስ የጻፍኩት መጣጥፍ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ነገሮች ሁሉ አይናገርም። ስለ አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ ግን ያስተምራል። ስለ ፖለቲካ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል ክርስቲያኖች ማወቅ አለብን። ከላይ ያልኩትን መጣጥፍ አዳብሬ የ2018ቱ የኢትዮጵያው የተሐድሶው ፖለቲካ ትኩሳት ሁሉን ነገር አግሎ፥ አያይዞ፥ አቀጣጥሎ በነበረበት ጊዜ ክርስቲያንና ፖለቲካ ብዬ አካፈልኩት። በዚያ መጣጥፍ ውስጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር የመንግሥት እና የቤተ ክርስቲያን ሚናዎች ምን እንደሆኑ፥ እንዲሁም ፖለቲካን እና ክርስትናን በተመለከተ የደቀ መዝሙር ወይም የነፍስ ወከፍ ክርስቲያን ሚና ምን መሆን፥ ምን መምሰል እንዳለበት ነበር ያካፈልኩት።

ክርስቲያንና ፖለቲካን በተመለከተ ዋና ነጥቤና እዚህም እንደ መፈክርና እንደ አዝማች የምደጋግመው 'ክርስቲያኖች ፖለቲከኛ ከሆኑ ጤናማ ፖለቲካውያን ይሁኑ፤ ቤተ ክርስቲያን፥ ወይም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ግን ከፖለቲካ ትጽዳ።' የሚል ነው። ይህንን ከጅምሩ አስምሬበት ነው የምንደረደረው። ይህንን አሳብ ለማካፈል እንደ መነሻ የሆነኝ በካሊፎርኒያ በምትገኝ አንዲት አጥቢያ የተከሰተው ጎሰኝነት ያቀለመው ፖለቲካዊ ክፍፍል ነበረ። በጊዜው በአገራችን የነበረውን ፖለቲካ የሚመስል ሽኩቻ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ተከስቶ ነበር። 'ምን ማድረግ አለብን?' ብሎ አንድ ወንድም ለጠየቀኝ ጥያቄ የሰጠሁት አጭር የጽሑፍ ምክር ነው እንደ መንደርደሪያ የሆነው።

ፖለቲካን በተመለከተ ክርስቲያኖች ያላቸው አመለካከት የተራራቀ ነው። አንዳንዶች ፖለቲካን ከርቀት ሲሸሹት አንዳንዶች ሙሉ በሙሉ ይጠልቁበታል። በዓለም ከ40 በላይ አገሮች ውስጥ ክርስቲያን ፓርቲዎች (ክርስቲያናዊ እሴቶችን ያነገቡ ፓርቲዎች ) አሉ። እነዚህ ፓርቲዎች አንዲት አገር በክርስቲያናዊ መርሆ መመራት አለባት የሚሉ ፓርቲዎች ናቸው። በአገራችንም በ90ዎቹ አጋማሽ እንደዚህ ዓይነት ፓርቲ ለመመሥረት ወይም ለመጀመር ሙከራ ተደርጎ እንደነበር አስታውሳለሁ። በጊዜ እሠራ የነበርኩት በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋናው ቢሮ ነበረና፥

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ቢሮም እዚያው ሕንጻ ውስጥ ነበረና አሳቡን የሰማሁት በዚያ ዞግ ነው።

ፓርቲውን ለመጀመር ወይም ለመጠንሰስ አሳቡን ያቀረበው ሰው በማላስታውሰው ምክንያት ወደኛም ቢሮ መጥቶ አሳቡን ሲያካፍለን፥ እኔ ጣል ያደረግሁት አሳብ፥ አንድ ፓርቲ ሃይማኖታዊ ሲሆንና መንፈሳዊ ቀናዒነት ሲኖርበት፥ ሃይማኖቱን በማይከተሉት ዘንድ ጥላቻና ነቀፌታ ስለሚያተርፍ ፓርቲው ብቻ ሳይሆን ሃይማኖቱም የተነቀፈ እንዲሆን ያደርጋል፤ በውስጡ ያሉት ሰዎች የሚያስነቅፍ ነገር ከተገኘባቸውም ፓርቲው ብቻ ሳይሆን ስሙን የተሸከመበት ሃይማኖትም ሰለባ ይሆናል። ደግሞም መንግሥት ራሱ ሃይማኖታዊ ይሆናልና ሃይማኖታዊ ስደትም ሊከሰት ይችላል የሚል ነበረ።

በእኔ መረዳት ሃይማኖታዊ ፓርቲ ትክክል አይደለም ባይ ነኝ። ክርስቲያኖች ግን ከሙሉ እውቀትና ከሙሉ እምነት ጋር በየትኛውም የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ገብተው እንደ ጨው የአስሚነት ሚና መጫወት አለባቸው። በጊዜው የግዛት ስነ መለኮት (Dominion Theology) የሚባለው ትምህርት ዘር በአገራችንም እየተዘራ ነበረ። ቀድሞ የነበርንበት ሶሻሊስታዊ የክህደት ርዕዮተ ዓለም የተከተለው የፖለቲካ ታሪካችን እና የጊዜው የዘረኝነት ፖለቲካ አሰላለፍ ለክርስቲያኖች እድልም አስፈሪም ነበረና ፓርቲውን መመሥረቱ ሂደት የተሳካ አልመሰለኝም። ቢሳካ ከፖለቲካዊው ባሻገር፥ ከዘረኛውም ባሻገር፥ ሃይማኖታዊው ፖለቲካ ሌላ ጽንፍ ሊፈጥርም ይችላል ባይ ነኝ።

በዚህ ጉዳይ ከግዛት ስነ መለኮት (Dominion Theology) አስተምህሮ ጋር አልስማማም። የግዛት ስነ መለኮት ወይም Dominion Theology ዋና ትምህርት በአጭሩ ቤተ ክርስቲያን በፍጻሜ ዘመናት ኃያል ትሆንና በማኅበረ ሰቡ ውስጥ የገዢነትና የበላይነት ሚናን በመጫወት ታላቁን ተልዕኮ ታስፈጽማለች፤ የክርስቶስንም መምጣት ታፋጥንና ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ መንግሥቱን አዘጋጅታ ትታስረክበዋለች የሚል ፖለቲካዊ ቅኝት ነው።

የግዛት ስነ መለኮት እንደ ንቅናቄ ዶሚኒየኒዝም ይባላል። ንቅናቄውም፥ ክርስቲያኖች በመጨረሻው ዘመን የዓለምን የተለያዩ ተቋማት (ሰባቱ ታራራዎች፥ መንግሥቶች ወይም ግዛቶች ይሏቸዋል) በመቆጣጠር ልክ በብሉይ ኪዳን ዘመን እስራኤላውያን በሙሴ ይመሩ በነበረ ጊዜ እንደነበረችው ያለች እስራኤል የምትመስል በመጽሐፍ ቅዱስ ሕግና ደንብ የምትመራ ዓለምን ለመፍጠር የሚደረግ ንቅናቄ ነው። ሕግና ደንቡ ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን ሆኖ ቅጣቶቹም ያንን የተከተሉ ይሆናሉ። ይህ ዓለም አቀፍ መንግሥት ሃይማኖታዊና ማንግሥታዊ ሥርዓት ቤተ ክርስቲያን የምትመራው መንግሥት ሆኖ፥ ወይም ቤተ ክርስቲያን ባትመራውም ለመጽሐፍ ቅዱስ ሕግ የተንበረከከ መንግሥት ተመሥርቶ ለሺህ ዓመታት ይገዛና መግዛቱ ሲፈጸም ክርስቶስ ዳግም ይመጣል። ይህ ነው ዶሚኒየኒዝም፤ ይህ የተሳሳተና ከአዲሱ ኪዳን ትምህርት ጋር የተጣላ የአገዛዝ አስተሳሰብ ነው። የአንዳንድ አገሮች ክርስቲያን ፓርቲዎች ይህንንም ይጋራሉና ሃይማኖታዊ ፓርቲዎች ትክክል አይደሉም የምለው ስለዚህ ነው።

በ2008 የአሜሪካ ፕሬዚደንታዊ ምርጫ ሰሞን (ባራክ ኦባማ ያሸነፈበት ምርጫ ማለት ነው) Andrew Jackson የተባለ አገልጋይ የጻፈውና በ*Christian Research Journal* ታትሞ የወጣ አንድ አጭር ጽሑፍ ነበረ። በዚያ የምርጫ ሰሞን ሊስተዋሉ የተገባቸው ብሎ ያሳሰባቸው አሥር ነጥቦችን የያዘ ጽሑፍ ነው። በአሜሪካ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ሴት ተወዳዳሪ እና ጥቁር ተወዳዳሪም የቀረቡበት ጊዜ ነበረና ፖለቲካዊ ትኩሳቱ፥ በተለይም መምረጥ በሚችለው ወጣት ትውልድ፥ 18 ዓመት በሞላቸውና በ20ዎቹና 30ዎቹ በሚገኙት ዘንድ፥ በሴቶችና በጥቁሮችም ዘንድ ተጋግሎ ነበር። በጽሑፉ ውስጥ ጸሐፊው ያስቀመጣቸው እንደ ክርስቲያን መረዳት ያለብን ትልልቅ እውነቶችና አንኳር የሆኑ ትምህርታዊ አሳቦች ናቸው። እነዚህን አሥር ነጥቦች ጥቂቱን ብቻ ከመጥቀስ፥ አንዳቸውም የሚቀናነስ ነገር የለባቸውምና ሁሉንም ላስቀምጣቸው፤ (ትርጉሙ የራሴ ነው።)

1. መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ከምንም አገር ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ጋር አታስተካክል። የሁለቱን፥ ማለትም የእግዚአብሔርን መንግሥት እና የምድራዊ መንግሥታትን ልዩነት ጠንቅቀን ማወቅ አለብን፤ ሁለቱን ማደባለቅ የለብንም፤ (ዮሐ. 18፥36፤ ማቴ. 6፥33)።

2. ለፖለቲከኞች የመሢሕ [ወይም የታዳጊ] ስፍራ አንስጣቸው። ብዙውን ጊዜ ሰዎች ፖለቲከኞች በገዛ እጃቸው ዲበ ፍጥረታዊ የሆነ ማኅበራዊ ውጤት የሚያመጡ ይመስላቸዋል። እኛ አንድ ጌታ አለን፤ እናም ፖለቲከኞችን ገደብ ወደሌለው ከፍታ ለማውጣት መሞከር የለብንም፤ (ማቴ. 7፥15፤ 1ጴጥ. 3፥15)።

3. ለምርጫ ስንወጣ ድምጽ ብቻ አንስጥ፤ ለፖለቲካ ፓርቲዎች መሪዎችም እንጸልይ። ክርስቲያኖች የሚደግፏቸውን ፖለቲከኞች ለመባረክና የነዚህን ተቃዋሚዎች ደግሞ ለመርገም ይፈተናሉ። ልብ እንበል፤ እኛ ለጠላቶቻችንም እንኳ እንድንጸልይ ተነግሮናል፤ (1ጢሞ. 2፥1-2፤ ማቴ. 5፥44)።

4. እኛ የምንፈልገው መሪ ወይም የፖለቲካ ቡድን ካላሸነፈ የዓለም መጨረሻ ነው ብለን አናስብ፤ የእኛ የመጨረሻው ዋስትናችን ያለው በማይናወጠው በእግዚአብሔር መንግሥት መሆኑን አንርሳ፤ (ዕብ. 12፥26-29)።

5. የደጋፊ / ነቃፊ ፖለቲካዊ ወገንተኝነትን ወደ እግዚአብሔር ቤተ ሰብ ውስጥ አናምጣ። እያንዳንዱ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ፊት የኅሊና ነፃነት አለውና ፖለቲካዊ አመለካከታችን ቤተ ክርስቲያንን እንዲከፍል መፍቀድ የለብንም፤ (ሮሜ 16፥17፤ 1ቆሮ. 1፥11-12)።

6. ሰዎችን አናሰይጥን ወይም አካይስታዊ አናድርግ። ማንም ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ነውና እንደ ክርስቲያንነታችን ከፖለቲካዊ አቋሙ ጋር ብንስማማም ባንስማማም ሰውን ሰይጣናዊ ወይም ከሰውነት የወረደ ፍጡር አናድርግ፤ (ቆላ. 3፥8፤ ያዕ. 4፥12)።

7. በንዴትና በጠላትነት አተካራ ውስጥ አንግባ፤ ይልቅስ ፖለቲካዊ እምነታችንን ጨዋነትን በተሞላ ክርክርና አእምሮአዊ በሆነ የእርስ በርስ ንግግር (dialogue)

ማቅረብ አለብን። የጥላቻ አተካራ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያዋርድ አስቀያሚ ትዕቢትን የሚገልጥ ባህርይ ነው፤ (ያዕ. 1፥19-20፤ 1ጢሞ. 2፥14)።

8. የማንነት ነፃነትህን እስከታጣ ድረስ በአንድ የፖለቲካ ጎራ ውስጥ ተጠላልፈህ አትታሰር። ይህን ካደረግህ በፖለቲከኞችና በፖለቲካ ፓርቲዎች ዘንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እውነት ስትናገር የመደመጥ ዕድልህን ታጣዋለህ፤ (1ጢሞ. 3፥15፤ ሮሜ 3፥4)።

9. በዘር ወይም ጎሳ፥ በጾታ፥ በሀብት፥ በዕድሜ የሚለያይ ከፋፋይ ፖለቲካ ከአንድነት ይልቅ መለያየትን የሚያመጣ ነው። ክርስቲያኖች በሕዝባዊ አደባባይ የሰላምና የእርቅ መሣሪያዎች መሆን አለባቸው እንጂ ለፖለቲካዊ ጥቅም ሕዝብን ከሚከፋፍል ቡድናዊ የስሜት ፈተና ሊጠበቁ ይገባል፤ (ማቴ. 5፥9፤ 2ቆሮ. 5፥18-19)።

10. ጨለማውን መርገም ብቻውን መፍትሔ አይደለም፤ [በአብሪነት] መጋፈጥ አለብን። የእግዚአብሔር መንግሥት አመለካከት ያላቸው ክርስቲያኖች ተልእኮ የዓለምን ጨለማ መራገም ሳይሆን እንደሚያበራ መብራት እና ሳይበላሽ እንደሚጠብቅ ጨው በመሆን፤ እንዲሁም መልካም በማድረግና ክፋትን በማሸነፍ የእግዚአብሔርን እውነት ብርሃን በማካፈል የሕዝብን የጋራ ደኅንነት መጠበቅ ነው፤ (ማቴ. 5፥13-16)።[1]

እነዚህ አንኳር ነጥቦች ክርስትናችን እንደተጠበቀና ነፍሳችን ሳትጎሳቆል ፖለቲካዊ አቋማችንን ወይም አመለካከታችንን በጨዋነት ማካፈል እንድንችል ብልጭታ ሊሰጡን ይችላሉ ብዬ አምናለሁ። ፖለቲካዊ ንግግርና ጽሑፍ ከክርስትና መስመርም እንኳ ሊያንሸራትት የሚችል ጉልበት አለውና ክርስቲያኖች ወደ ፖለቲካ መስክ ሲገቡ ብቻ ሳይሆን አሳባቸውን ሲገልጡም ጥንቃቄ ሊያደርጉ የሚገባው ጉዳይ ነው።

ጁን 28, 2018 ቀን Abiymania በሚል ርእስ ስለ ክርስቲያናዊ ፖለቲካ ወይም ፖለቲካዊ ክርስትና ሚዛናዊነት አንዲት ገጽ ጽፌ ነበር። መቼም ጽንፈኝነት ባለበት ሚዛንን እንደመጠበቅ የመሰለ መልካም ነገር የለም። ፌስቡክ ላይ የተለጠፈ ጽሑፍን ማንም ማንበብ የሚችል ሰው ሊያነብበው ቢችልም የኔ ተነባቢዎች ክርስቲያኖች ናቸውና መልእክቴ በቀጥታ የሚመለከተው እነርሱን ነው። ጠቅላላው ጽሑፍ በፌስቡክ ገጼ በስፍራው ስለሚገኝ እዚህ ከጽሑፉ ሁለት ሦስት አንኳር ነጥቦችን ብቻ ላውሳ።

በነዚያ ሳምንታትና ጥቂት ወራት እንደ ዶ/ር ዐቢይ አህመድ የኢትዮጵያውያንን ሙሉ ቀልብ መቶ በመቶ የሳበ ምንም ነገር ኖሮ አያውቅም። አንዳንዶች የገዢው ፓርቲ መሪ እንጂ ሌላ እንዳይደለ ይላሉ። ሌሎች ከሰማይ የወረደ ስጦታ አድርገው እንደ መሢሕ እና እንደ ሙሴ ቆጥረውታል። [እላይ ቁጥር 2 ላይ የተጠቀሰውን ይመለከቷል።] እርግጥ፥ ምንም ሥልጣን ከሰማይ ካልተሰጠ አፈፍ አድርገው የሚቀዳጁት እንዳልሆነ

[1] Andrew Jackson, How to Engage in Politics without Losing Your Soul, Christian Research Journal, volume 31, number 04 (2008).

በጥልቀት አምናለሁ። ይህ የሮሜ 13 ትምህርትም ነው። የእግዚአብሔርን ልጅ ለመስቀል ሞት አሳልፎ የሰጠው ጲላጦስም እንኳ ሥልጣኑ የተሰጠው ከላይ መሆኑ በግልጽ ከተጻፈ፥ (ዮሐ. 19፥10-11) ሌላው ሁሉ ከላይ መቀበሉን መቀበል አያዳግተንም። ክፉው እንኳ ሥልጣንን ከላይ ከተቀበለ መልካሙ ከላይ መቀበሉ ምንም አያጠያይቅም። የዚያ አጭር ጽሑፍ ሦስቱ አንኳር ነጥቦች እነዚህ ናቸው፤

1ኛ. የቃሉ ትርጉም። አቢይሜኒያ ያልኩትን ቃል ልተርጉመው። ቃሉን እኔ ባላነበበውም ቀድሞም በማኅበራዊ ሚድያ የነበረ ቃል መሆኑን ሰምቻለሁ፤ ቃሉን ከኔ በፊት የተጠቀመው ሰው የጻፈውንም ኋላ እጠቅሰዋለሁ። ሜኒያ ወይም ማኒክ ሲንድረም ጤናማ ያልሆነ ከልክ ያለፈ መነሣሳት የሚፈጥረው ሚዛን የሳተ የአካል ወይም የልቡና መግነን፥ ወይም መቃወስ ነው። ሜኒያን ውጫያዊ ወይም ውስጣዊ ምንጮች ሊለኩሱት ይችላሉ። ሃይፖሜኒያ የሜኒያ አንድ ምሳሌ ነው። ሃይፖሜኒያክ ሰዎች ሊወነጨፍ እንደሚሽከረከር ወንጭፍ ናቸው፤ ብዙ መለፍለፍ፥ በጣም መተማመን፥ አጉል ድፍረት፥ ያልተጤነ ወኔ ይጠናወታቸዋል። የነውርና የይሉኝታ ስሜታቸው ይጠፋል፤ የማያልቅ የጉልበት ምንጭ እንዳላቸው ይሰማቸዋል፤ ለጊዜውም ይኖራቸዋል። በደስታ የመፍነክነክ (euphoria ይሉታል) እና ፈጥኖ የመቆጣት ባህርይም ይታይባቸዋል። በሕክምና ሊቃውንት ዘንድ ግን ይህ የአካላዊ አሠራር ተቃውሶ በመሆኑ ከሕመም ተፈርጆ ሕክምና የሚሻ ሕመም ነው። የብዙ ነገሮች ሜኒያዎች ሊኖሩ ይችላሉ። አቢይሜኒያ ያልኩት ከዚህ በተመሳሰለ መልኩ ዶ/ር አቢይን ከመከተል ወደ መታመን (አንዳንዴም ወደ ማምለክ) የሚቃጣ አካሄድን ነው። 'We worship you' የሚሉ ሰዎችም ተደምጠዋል።

ከክርስትና አንጻርስ? ይህ የአገራችን መሪ፥ ሰው ብቻ መሆኑን መርሳት የለብንም። እንደ መጥፎ ዕድል ሆኖብን እኛ አፍሪቃውያን፥ እኛም ኢትዮጵያውያን የሕዝብ ልብ ያለው፥ ሕዝብ ሕዝብ የሚሸትት መሪ አይወጣልንም። ወይም ቢያንስ፥ እስካሁን አልወጣልንም። አሁን ሕዝባዊ ሰው ማየት (መኪና እያስቆመ ከሕዝብ ጋር መተቃቀፍ የሚፈልግ መሪ ማየት) እንግዳ ነገር ሆኖብናል። ሕዝብ ሕዝብ የሚሸት ያልኩት እንዲህ ያለውን ሕዝባዊ ትስስር ነው። እናም ሁላችንም ከነፍን። በዚህ ውስጥ ግን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አማኞች ጨርቃችንን መጣል እንደሌለብን የበኩሌን ማሳሰብ ወደድሁ። የሰውየው ማንነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሰው ላይ ሳይሆን፥ ሰውን በዘሩና በቀለሙ ሳይሆን በሰውነቱ ብቻ የሚያከብርና የሚያስከብር ፍትሐዊ መሠረት ጥሎ ራሱን ገለል በሚያደርግ ማንነት ላይ ብናተኩር እናተርፋለን እንጂ አንከስርም። ትርፉም ነገ በደርዘን የሚቆጠሩና ቀና ብለን የምናያቸው መሪዎች ማግኘታችን ይሆልናል። የመጀመሪያው ይህ ነው፤ የቃሉ ትርጉም።

2ኛው ነጥብ፥ ክርስቲያኖች ፖለቲከኞች ሲሆኑ ነው። ክርስቲያኖች ፖለቲከኞች ከሆኑ ወይም ሲሆኑ ግን ከልብ ፖለቲከኞች እንዲሆኑ እንጠብቃለን። ቅደም ተከተሉም እንደዚያ መሆን አለበት፤ በመጀመሪያ ክርስቲያን፥ ከዚያ ፖለቲከኛ እንዲሆኑ እንጠብቃለን። ይህንን መጠበቅ ብዙ መጠበቅ ወይም ከልክ በላይ መጠበቅ አይመስለኝም። በልኩና በልካቸው መጠበቅ ነው። ክርስትናን እንደ ክትባት የተወጉ ወይም የተለበለቡ ክርስቲያኖች አደገኞች ክርስቲያኖች እንደሆኑት ሁሉ የተለበለቡ

ወረተኛ ፖለቲከኞችም አደገኞች ፖለቲከኞች ናቸው። በሰሞነኛ ፖለቲካዊ ወላፈን ተገርፈን ወረተኛ ፖለቲከኞች እንዳንሆን እፈራለሁ። የማያልፍ የለምና ይህም ወረት ሆኖ ያልፍ ይሆናል። አናውቅም። [ይህ በፈረንጆች 2018 የጻፍኩት ነው፤ አሁን በ2022 ይህ ወረት ከብዙዎች መከሰሙ እሙን ነው።] ተንባዮች ቢተነብዩም፥ ንግርተኞች ቢናገሩም ከእኛ ማንም ስለ ነገ አያውቅም። ነገን አይቶ የተመለሰ ሰው ኖሮን አያውቅም። ምንም ቢሆን ግን እንደ ክርስቲያን ያሉንን እሴቶች ጨብጠን ወደ ነገ የምንጓዝ መሆናችንን መርሳት የለብንም። ሦስቱ መፈክር ከማለት፥ አንዱ መፈክር ቀርቶ፥ አንዴ ፈክሮ አንዴ መጸለይ ጥበብ ነው። ሌሎቹ ክርስቲያናዊ የዜግነት ጉዳዮቻችን እንደተጠበቁ ሆነው እንደ ክርስቲያን ለመሪዎች መጸለይን መዘንጋት የለብንም።

3ኛውና የመጨረሻው፥ በዚያ ጽሑፍ ያልኩት ነጥብ የቤተ ክርስቲያን ሚና ነው። ቤተ ክርስቲያን አንድና አንድ ብቻ ተልእኮ ያላት የክርስቶስ አካል ናት። ያ ተልእኮም ወንጌል ነው። ቤተ ክርስቲያን እንደ ቤተ ክርስቲያን የፖለቲካ ድርጅት አይደለችም፤ መሆንም የለባትም። በነፍስ ወከፍ ክርስቲያኖች ግን እንደ ጥሪያቸውና እንደ ትምህርታቸው፥ እንደ ሥልጠናቸውና እንደ ዝንባሌያቸው ከስነ ምኅዳራዊው እስከ ሰብዓዊው፥ ከማኅበራዊው እስከ ፖለቲካዊው ድረስ በንቃት መሳተፍ ተገቢያቸው መሆኑንም አምናለሁ።

ስለ ጸሎት ግን ቃሉ ይህን ይለናል፤ *እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፥ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ።* 1ጢሞ. 2፥1-2። ፖለቲካና ክርስትና ለቅደም ተከተል ምርጫ ቢቀርቡልኝ ወይም ከቀረቡልኝ፥ ክርስትናን ከሚያስረሳኝ ፖለቲካ ይልቅ ፖለቲካን የሚያስረሳኝን ክርስትና እመርጣለሁ። ፖለቲከኞች ሆንንም፥ አልሆንንም ክርስቲያኖች እንደ ክርስቲያን የተሰጠንን ዋነኛውን ሰማያዊ አደራና ግዴታ የማንረሳ ሰዎች እንድንሆን ላሳሰብ ወይም ላስታውስ ወይም ላስጠነቅቅ ግድ ይሰማኛል። ቃሉ እንደሚለው ለአገራችን፥ ለመሪዋና ለመሪዎቿ እንጸልይ። መታመናችንን ግን ሁሌም በእግዚአብሔር እና በእግዚአብሔር ብቻ ላይ እናድርግ። ኤር. 17፥5 እና 7 እንዲህ እንደሚል፤ *እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በሰው የሚታመን ሥጋ ለባሹንም ክንዱ የሚያደርግ ልቡም ከእግዚአብሔር የሚመለስ ሰው ርጉም ነው። . . . በእግዚአብሔር የታመነ እምነቱም እግዚአብሔር የሆነ ሰው ቡሩክ ነው።*

የዚያ አጭር ጽሑፍ ሦስት ትልልቅ አንኳሮች እነዚህ ናቸው። ያቺን አንድ ገጽ ጽሑፍ አንዳንድ አንባቢዎች በፈርሱ አነበቧት እንጂ ጽሑፏ በዶ/ር አቢይ ላይ የተጻፈች አይደለችም። እስካሁን [በፈረንጆች 2018 ነው ይህ የተጻፈው።] ባለው አካሄድ በዶ/ር አቢይ ላይ ከምስጋናና ከአድናቆት ቃል በቀር ሌላ ምንም ሊጻፍ አይቻልም። የዚያች ጽሑፍ ዒላማ ስሜታዊ የሆነው የሰዎች አካሄድ ነው። እንደሚታወቀው፥ ስሜታዊነትን የሚያመነጩ ነባራዊ ሁኔታዎች መኖራቸው እውነት ነው፤ ያንን አልክድም። ሆኖም፥ ለቀጥተኛ ተነባቢዎቼ በጊዜው ላስተላልፍ የሞከርኩት ስሜት እና አእምሮ አይፋቱ የሚል አሳብ ነው። መንፈሳዊነትና ቃሉ ከስሌቱ ውስጥ አይውጡ

የሚል ነው። እንጂ በእውነቱ ዶ/ር አቢይ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አስተዳደር፥ አገዛዝ፥ ሕዝበኝነት ምን መምሰል እንዳለበት መለኪያውን፥ ደረጃውን የሰቀለ ሰው ነው። ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያውያን ከዚህ ያነሰ፥ የወረደ አስተዳደር ቢቀርብላቸው አይጥማቸውም። ስለዚህ አቢይሜኒያ ስል ሰውየው ላይ የተቃጣ ጽሑፍ አይደለም። ሰውየው ሰው ነው፤ ከልቡ። [ሦስቱ አንኳሮች በፈረንጆች 2018 የተጻፉ ናቸው።]

ወደ ፖለቲካው ስመለስ አሁንም ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር መረዳቴን ላካፍል እፈልጋለሁ። አንዳንድ ሰዎች እንደዚህ እኔ እንደማካፍለው ላይረድዱ ይችላሉ፤ ወይም እንደዚህ መረዳት አይፈልጉም። ይህ የአመለካከት ልዩነት ወይም የአረዳድ ርቀት ነውና ጦርነት አያስከፍተንም። ቁም ነገሩ፥ እንደ ክርስቲያን የምንናገረው ነገር በቃሉ የተደገፈ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው።

እነዚህን ነገሮች ስል ክርስቲያኖች ፖለቲከኞች መሆን የለባቸውም ማለቴ አይደለም። 'ቤተ ክርስቲያን ግን ፖለቲከኛ መሆን የለባትም' ነው የምለው። ቤተ ክርስቲያን ስል አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ማለቴ ነው። ክርስቲያኖች እንደ ግለ ሰብነታቸው እስከ ጥግ ድረስ፥ በፖለቲካውም፥ በማኅበራዊውም፥ በሰብዓዊውም፥ በሕጋዊውም፥ በሙብት ተሟጋችነት፥ በስነ ምሕዳር ጠባቂነትም፥ በሌሎቹም መስኮች ሁሉ እስከ ጥግ ድረስ መሄድ ይችላሉ፤ መሄድም አለባቸው። ክርስቲያን ፖለቲከኞች ፖለቲከኛ ሲሆኑ ፖለቲከኛ ብቻ ሳይሆን፥ ጤናማ ፖለቲከኛ፥ ክርስቲያን ፖለቲከኛ እንዲሆኑ የተገባቸውና የሚጠበቅባቸውም ነው።

መፈክሬን ልድገመው፤ ክርስቲያኖች ፖለቲከኞች ሲሆኑና ቢሆኑ መልካምና ተገቢ ነው። ቤተ ክርስቲያን ግን ፖለቲከኛ መሆን የለባትም። አንዳንድ ሰዎች፥ 'ቤተ ክርስቲያን የመንግሥት ሕሊና ናት፥ የኅሊና ሚና መጫወት አለባት' ይላሉ። ይህንን አሳብ ከየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንዳገኙት አላውቅም። ይህ በታሪክ ውስጥ አንድ ሰው የተናገረውና ተቀብለው ያስተጋቡት የተሳሳተ ንግግር ነው። እንደሚታወቀው፥ ሕሊናችን የማንነታችን አንድ ክፍል መሆኑ እሙን ነው፤ ደግሞም ሕሊናችን የተነገረንን ነገር ይደግምልናል እንጂ አዲስ ነገር አያስተምረንም። በዚህ ስሌት ከሄድን፥ 'ቤተ ክርስቲያን የመንግሥት ሕሊና ናት' የሚሉ ሰዎች፥ 'ቤተ ክርስቲያን የመንግሥት አሠራር አንድ ክፍል ናት' ማለታቸውም ነው። ሕሊናችን የኛ ከሆነና ቤተ ክርስቲያን የመንግሥት ሕሊና ከሆነች፥ ቤተ ክርስቲያን የመንግሥት አንድ ክፍል ናት ማለት ነው። በታሪክም፥ በአገራችንም ጭምር፥ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ጋር የተጋመደችባቸው አገሮች ኖረው ያውቃሉ። እንደዚያ ባለ መንግሥት ውስጥ ምናልባት ይህ አባባል ትርጉም ሊሰጥ ይችል ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ይህንን አያስተምርም። ቤተ ክርስቲያን የመንግሥታካል ብልት ወይም ሕሊና አይደለችም። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ እጮኛና ሙሽራና የእርሱ አካል ናት።

ማንም ዓለማዊ መንግሥት የራሱ ሕሊና አለው። ሕሊናውን አደድቦ፥ አደንዝዞ፥ አልሰማም ብሎ ካልተቀመጠ በስተቀር የራሱ ሕሊና አለው። ጋዜጠኞች፥ ጦማሪዎች፥ ደራሲዎች ሕሊና ናቸው፤ ከያንያንና አርቲስቶች ሕሊና ናቸው፤ የሕዝብ ውክልና ያላቸው እንደራሴዎች ሕሊና ናቸው፤ ሌሎችም በመንግሥታዊ መዋቅር ውስጥ የሚገኙ የሕሊና ሚና የሚጫወቱ ክፍሎች፥ መንግሥት ራሱን የሚያይበት፥ ራሱን

የሚፈትሽበት መፈተሻዎች፥ መለኪያዎች በውስጡ፥ በመዋቅሩ ውስጥ አሉት መንግሥት። የሕዝብ ድምጽ የሆኑ የዜግነት፥ የመብት፥ የስብእና ሞጋቾችና ተሟጋቾች አሉት። በእነዚህ ላይ ደግሞ ክርስቲያን ፖለቲከኞችም አሉ። የክርስቶስ ልብ ያላቸው፥ የእርሱን አሳብ የሚያስቡ፥ ቃሉ የሚለውን የሚያውቁ ሰዎች አሉ። እነዚህን እያገለለ፥ እያወገደ፥ እያስወገደ፥ እያሰረ፥ ዝም እያሰኘ ከሆነ፥ መንግሥት ሕሊናውን እያዶለዶመ ብቻ ሳይሆን እያወደመ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ልዩ ፍጡር ናት እንጂ የመንግሥት ቅጥያና ሕሊና አይደለችም። ቤተ ክርስቲያን ልዩ ተልእኮ ያላት አካል ናት። ያም ተልእኮ ወንጌል ነው። የእርሷ ዓይነት ልዩ ተልእኮ ያለው ሌላ አካል በምድር ላይ የለም። በፍጹም የለም። መንግሥት ውጪያዊ ቁጥጥር ሊያደርግ የተሾመ ሲሆን ቤተ ክርስቲያን ግን በሰዎች ውስጥ ውስጣዊ ለውጥን ለመፍጠር ልዩ አደራና ተልዕኮ የተሰጣት አካል እና ተቋም ናት። ይህን ማድረግ የሚቻላት ውስጣቸው በተለወጡ ሕያዋን ሰዎች የተሠራች በመሆኗ ነው። በዚህ ረገድ ቤተ ክርስቲያን ሁለቱም ናት፤ ማለትም፥ ሕያው ዘአካል (organism) ናት፤ ደግሞም ተቋም (institution) ናት። ሕያው ዘአካል ናት ሲባል ከማይጠፋ፥ ከሕያውና ለዘላለም በሚኖር ቃል የተወለደች በመሆኗና ከማይጠፋና ሕያው ከሆነ ዘር በተወለዱ ሰዎች በመሠራቷ እና በሕያዋን ድንጋዮች የተሠራች መንፈሳዊ ቤት በመሆኗ ነው፤ በ1ጴጥ. 1፥23 እና 2፥5። ተቋምነቷ ደግሞ የእነዚህ ሰዎች ስብስብ መሆኗና በአንድ አጥቢያ ያሉ ቅዱሳን ተሰባስበው ጌታን የሚያመልኩባት፥ የሚያድጉባት፥ የሚያገለግሉባት ድርጅት ወይም ተቋም በመሆኗ ነው። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የምድራዊ መንግሥት ሕሊና ሳትሆን ራሷ የተከበረች አካል ናት። ቤተ ክርስቲያንን የመንግሥት ተለጣፊ አናድርጋት።

ቤተ ክርስቲያን የአገር መንግሥትም አይደለችም፤ ተቃዋሚ ፓርቲ ወይም ደጋፊ ፓርቲም አይደለችም፤ የሰብዓዊ መብቶች ጉዳይ ተሟጋች ድርጅትም አይደለችም። ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን ናት። የተጠራችለትን ራሷን እንድትሆን ነውና ይህንን እንዳትሆን ከልክለን ሌላውን እንድትሆን ማስገደድ የለብንም። እንዴት ነው ራሷን የምትሆነው? ራሷን የምትሆነው የተጻፈውና የተነገራትን በመሆን ነው፤ እንጂ ስሜታችንን ወይም በዚህ አገርና በዚህ ዘመን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ያደረገችውን በመሆንና በማድረግም አይደለም። የተጻፈውን በመሆን።

በዚያ ባሰራጨሁት አንድ ገጽ ጽሑፍ ከተናገርኩት አንዱ ይህም ነው። ቀደም ሲል ይህ አቢይሜኒያ እኔ የቀመርኩት ቃል አይደለም ብያለሁ። አለመሆኑን ያወቅኩትም ለዚያ ጽሑፍ ከተሰጡት ምላሾች ውስጥ ነው። ስጽፈው ከዚያ በፊት አልሰማሁትምና ስለዚያ ነው የተረጎምኩት። እንደተሰጠኝ ምላሽ ቃሉን ዶ/ር ብርሃኑ ሌንጂሶ የተባለ የሳን ሆዜ ካሊፎርኒያ ሰው ነው የጻፈው። እኔ የጻፍኩት ጁን 28 ነው፤ እርሱ የጻፈው ደግሞ ኤፕሪል 26 ነው፤ ከሁለት ወራት ቀድሞ ማለት ነው። ስለዚህ ቃሉ በእርግጥ የኔ አይደለም። እርሱ ስለ አቢይሜኒያ በቆንጆ እንግሊዝኛው የጻፈው ይህ ነው፤


Birhanu M Lenjiso
April 26 ·

AbiyMania vs AbiyPhobia

I have been carefully examining the rapidly changing characteristics of the dual group created around Abiy Ahmed`s appointment as the prime minister of Ethiopia over the last 30 days. The symptoms are now at the stage where they can be described as AbiyMania and AbiyPhobia.

AbiyMania represents a group that is excessively obsessed with the new Prime Minister. I called them blind supporters two weeks ago. But they evolved very fast and assumed the AbiyMania status. This group pay less attention to what the Prime Minister has to say. Their focus is more on what his critics has to say. In that sense they are the anti-thesis of the critics. They are obsessed people. But an obsession is simply a way for damaged people to damage themselves more. Once obsessed it is very hard to imagine things with the rational mind.

እኔ ያልኩትም ይህንን ከመጠን ያለፈ አትኩሮትና አክብሮት የሚመለከት ነው። ከመጠን ያለፈ ሲባል፥ 'በማን መለኪያ ተለክቶ ነው ከመጠን ያለፈው?' ሊባል ይችላል። መለኪያችን ሊለያይ እንደሚችል አውቃለሁ፤ በመለያየቱ ደግሞ እስማማለሁ። ዶ/ር ብርሃኑ ሌንጂሶ የጻፈው የዚህኛው ተቃራኒ ደግሞ አቢይፎቢያ የሚሰኘው አለ። ይህኛው አስተሳሰብ ደግሞ እንዲህ ያለውን የምሕረት፥ የፍቅር፥ የዕርቅና የሰላም ነገር የሚጠሉ፥ ይህ እንዳይሆን የሚፈልጉ፥ ግጭትን፥ ፍጅትን የሚናፍቁና በዚያ ውስጥ እንጀራቸውን የሚጋግሩ ሰዎች አመለካከት ነው። ይህኛው ተቃራኒው ጽንፍ ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች፥ እንደ ክርስቶስ ተከታዮችም ሚዛናዊ መሆን አለብን።

እርግጥ ነው ማንኛውንም መሪ የሚያስነሣው እግዚአብሔር ነው። ሥልጣን ሁሉ ከሰማይ ካልሆነ ከየትም እንደማይገኝ ቅዱስ ቃሉ ያስተምረናል። እንደ ክርስቲያን ይህንን ሳንጠራጠር እናምናለን፤ እንቀበላለንም። ሮሜ 13፥1 *ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው።* ይላል። ይህ ጥቅስ የሥልጣንን ምንጭ ብቻ ሳይሆን የእኛንም ግዴታ ይናገራል። ለየትኛውም መንግሥት መገዛት የተገባን መሆኑ ነው ትምህርቱ። ይገዛ ሲል መገዛትን የምርጫ ጉዳይ አድርጎ አላቀረበም። መልካም ለመሰለን መገዛት ላልመሰለን እንቢ ማለትን ቃሉ አያደፋፍርም። ቁጥር 2 *ስለዚህ ባለ ሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል፤ የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ።* ይላል። ይህንን የጻፈው ጳውሎስ እና የጻፈውም ለሮሜ ክርስቲያኖች መሆኑንም አንዘንጋ። ጳውሎስ ይህንን የጻፈው

ኔሮ የተባለው ቄሣር ይገዛ በነበረበት ዘመን መሆኑንም ታሳቢ እናድርግ። ያ መንግሥት ክርስቲያኖችን እና ቤተ ክርስቲያንን ያሳድድ የነበረ አገዛዝ መሆኑንም እንወቅ።

ስለዚህ መንግሥትን መቃወም ለቤተ ክርስቲያን ወይም ለቅዱሳን ጉባኤ ለምርጫ አልቀረበም። ጥሩ የሆነ መንግሥት፥ ጥሩ መሪ፥ ጥሩ ፓርቲ፥ የተወደደ የአስተዳደር ዘይቤ በአንዲት አገር በሚነግስበት ጊዜ መደሰት መልካም ነው። ከመደሰት ጋር መጸለይ ደግሞ የቃሉ ትምህርት ነው። 1ጢሞ. 2፥1-2 ይህንን ነው የሚነግረን፤ የሚመክረን *እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፥ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ።* ያ መንግሥት መልካምም ይሁን፥ መልካምም አይሁን ለዚያ መንግሥት እንደ ክርስቲያን የመጸለይ ኃላፊነት አለብን። ይህ ጸሎት የተለየ እድል መሆኑንም እንወቅ። ከእውነተኛው አምላክ ጋር ግንኙነት ያለን እኛ፥ ለሚሰማና ለሚመልስ ለዚህ አምላክ ልመናን ስለ መንግሥት ማቅረብ መቻል ልዩ እድል ነው። እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው ሁለት ነጥቦች፥ ማለትም መገዛትና መጸለይ የተሰጡን ትልልቅ ግዴታዎችና ኃላፊነቶች ናቸው።

መንግሥትን ሁሌ መታዘዝ አለብን? መቃወምስ ከቶውኑ ይቻላል? መንግሥትን መቃወም ወይም እንቢ ማለት የምንችልበት ምንም ምክንያትና አጋጣሚ የለም ማለት አይደለም። ሊኖር ይችላል። አንድ መንግሥት በእኛና በአምላካችን መካከል የሚገባና የኛንና የአምላካችንን ግንኙነት ሊበርዝ ወይም ሊሰርዝ የሚፈልግ ከሆነ ያኔ ለእምነታችን መቆም የግድ ነው። ዳን. 1-3 የዚህ አንድ ምሳሌ የሚሆኑን ምዕራፎች ናቸው። ዳንኤልና ሦስቱ ጓደኞቹ ስማቸው ሲሰረዝና የከለዳውያን ስም ሲሰጣቸው ብዙም አልተቸገሩም። የከለዳውያን ትምህርት ሲማሩም እንቢ አላሉም፤ እንዲያውም የላቀ ብልጫ አሳዩ። መብሉና መጠጡ ግን የሚያረክሳቸው በመሆኑ ጥያቄ አቅርበው እንዲለወጥላቸው አደረጉ። ፍላጎታቸውን እንጂ ምክንያታቸውን እንደተናገሩ አልተጻፈም። ይህ በዳን. 1 የምናገኘው ታሪክ ነው።

በዳን. 2 ለግድያ ሲፈለጉ የዓመጽ ወይም የአጸፋ ምላሽ ወደ አሳባቸው አልመጣም። በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ቀርበው ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ብዙ ጠቢባን መትረፍም ምክንያት የሆነው የጸሎታቸው መልስ መጣ። ወደ ዳን. 3 ስንመጣ ግን በእርግጥ እምነታቸውን የሚያስከድ ውሳኔ ተወስኖ ነበር። ለጣዖት እንዲሰግዱ ነበር ትእዛዙ። ይህ በእነርሱና በአምላካቸው መካከል የገባ ትእዛዝ ነውና ሲድራቅ፥ ሚሳቅ፥ እና አብደናጎ እንቢ አሉ። አልሰገዱም፤ የጀርባ አጥንት እንዳለው ሰው ቆሙ። የሚከፍሉት ዋጋ እንዳለ እያወቁ፤ ያ ዋጋ ሞት መሆኑን እያወቁ ለመሞት ቆረጡ። ይህንን በልባቸው ውሳኔ ብቻም አላደረጉም በአፋቸው ቃልም ተናገሩ። *ሲድራቅና ሚሳቅ አብደናጎም መለሱ ንጉሡንም፡- ናቡከደነፆር ሆይ፥ በዚህ ነገር እንመልስልህ ዘንድ አስፈላጊያችን አይደለም። የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል፤ ከእጅህም ያድነናል፥ ንጉሥ ሆይ! ነገር ግን፥ ንጉሥ ሆይ፥ እርሱ ባያድነን፥ አማልክትህን እንዳናመልክ ላቆምኸውም ለወርቁ ምስል እንዳንሰግድለት እወቅ አሉት።* ዳን. 3፥16-18። በዳን. 6ም በዳን. 3 ከተጻፈው ጋር ተቀራራቢ ውሳኔና አዋጅ መታወጁ የዳንኤልንም ውስጣዊ ማንነት ገለጠ። በእርሱና በአምላኩ መካከል

ለሚገባ ምንም አዋጅ እንደማይንበረከክ፥ ለአምላኩ ግን እንደሚንበረከክ በተግባር አሳየ። በእልከኝነት በፊት ከሚያደርገው አብልጦ አላደረገም። ፈርቶም ቀድሞ ያደርግ ከነበረው አጉድሎ አላደረገም። የጸሎት ክልከላው አዋጅ መታወጅም አለመታወጅም የዳልኤልን የዘወትር ጸሎት ከቶም አልለወጠውም። አዋጁ በእርሱና በአምላኩ ውስጥ በቀጥታ የገባ አዋጅ ነው። ያ እንዲገባ አልፈቀደም። በሁለቱም እግዚአብሔር ለአምላኪዎቹ አዘነበለ። ባይሆን ኖሮ ለመሞትን ወስነው የወሰዱት እርምጃ ነው።

ከአዲስ ኪዳን በሐዋ. 4 የምናገኘው ታሪክም ከዚህ ይቀራረባል። 'ይቀራረባል' ያልኩት፥ በቁጥር 17-18፥ *ከእንግዲህ ወዲህ ለማንም ሰው በዚህ ስም እንዳይናገሩ እየዛትን እንዘዛቸው ብለው እርስ በርሳቸው ተማከሩ። ጠርተውም በኢየሱስ ስም ፈጽመው እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ አዘዙአቸው።* የተባሉት በቀጥታ መንግሥት ያልሆኑ፥ ነገር ግን በሃይማኖት ስም፥ ፍርድን በእጃቸው ወስደው እስከ መግደል ድረስ የሚደርስ መንግሥታዊ ሥራ የሚሠሩም የአይሁድ ሸንጎ የሚባለው ሃይማኖታዊ አመራርና መሪዎች ናቸው። ለዚህ አካል የጴጥሮስና ዮሐንስ መልስ ይህ ነበር፤ *እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ እናንተን እንሰማ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት የሚገባ እንደ ሆነ ቍረጡ፤ እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም አሉአቸው።* ሐዋ. 4፥19-20።

አንዳንዴ መንግሥት በአማኞች ግለ ሰባዊ ሕይወት ብቻ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ላይም መንግሥታዊ ጫና ለማድረግ እጁን ያስገባል። እዚህ ላይ አማኞችም ቤተ ክርስቲያንም ከላይ እንደተመለከትነው እንደ ዳንኤልና ጓደኞቹ በጨዋነት ለእምነታቸው በጽናት፥ ለአምላካቸው ክብርም እንቢ ሊሉ የሚገደዱበት ጊዜያት ይኖራሉ። ቤተ ክርስቲያን (እዚህ ቤተ ክርስቲያን ስል አማኞችን ማለቴ ነው።) በእምነት ምክንያት በምድራዊ መንግሥት ስትሳደድ ዋጋ ለመክፈል መቍረጥና መቆም አለባት። በአማኝና በአምላኩ መካከል የሚገባ ማናቸውም አስካጅ ነገር መፈቀድ የለበትም። የሚጠይቀውን ዋጋ ለመክፈልም መቁረጥ ተገቢ ነው።

መንግሥት ቤተ ክርስቲያንን እንደ ተቋም የራሱ መገልገያ ማድረግም የለበትም። ይህንን መንግሥታት ሊያደርጉ ይመኛሉ፤ ሲያደርጉም ኖረዋል። ሁለቱም አካላት ጥቅም የመለዋወጥ፥ እከከኝ ልከክህ እና ሰጥቶ መቀበል ድርድር ውስጥ ሲገቡ መንግሥት መልኩ አይቀየርም፤ ቤተ ክርስቲያን ግን ትቀየራለች። በታሪካችን መንግሥትና ቤተ ክህበት እጅና ጓንት ሆነው ኖረዋልና ይህ በአንድ ፊቱ እንግዳ ሊመስል ይችላል። ቤተ ክርስቲያን የነገሥታት አንጋሽ፥ መንግስትም የቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ ሆነው እየተደጋገፉ ኖረዋል። ይህ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና ባዕድ ልምምድ ነው። በአገራችን በፈረንጆች 2019 እና 2020 የተከወነው የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል አመሠራረትና ክዋኔ ጅምሩም ልደቱም በቤተ መንግሥት ስለዚህ መንግሥት መሆኑም ጤናማ ያልሆነ አካሄድ ነው። መንግሥት በቤተ ክርስቲያን አሠራር ውስጥ ጣልቃ መግባት የለበትም፤ ቤተ ክርስቲያንም ፖለቲከኛ መሆን የለባትም።

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ፖለቲከኛ መሆን የለባትም ስል በዚያች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን የሚያመልኩ ሆነው ፖለቲካዊ አቋምን በተመለከተ በተለያየ ጎራ

የተሰለፉ ሰዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ ነው። በአንድ ጉባኤ ውስጥ የገዢ ፓርቲ ደጋፊዎች ሊኖሩ ይችላሉ፤ ተቃዋሚዎች ሊኖሩ ይችላሉ። የዚህ ወይም የዚያ ፓርቲ አባላት ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ ወገኖች በፖለቲካ አቋማቸው የተለያዩ ናቸው፤ ግን ሁለቱም ወገኖችና የሰማያዊ መንግሥት ዜጎች ናቸው። ሁለቱም በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያመልኩና የሚያገለግሉ ሊሆኑ ይችላሉ። በቤተ ክርስቲያን የጌታን ራት አብረው ይቀበላሉና የአንድ አካል ብልቶች ናቸው። እዚያም ቢሆን የአንዲት አገር ዜጎች፥ የአንድ ሕዝብ መሪዎች ናቸው፤ ሆኖም ግን፥ ፖለቲካ አንዳንዴ ለዚያ የሚሆን የልብ ስፋት ላይኖረው ይችላል። እዚያ የሚከራከሩበት፥ የሚነታረኩበት፥ የሚጨቃጨቁበት ነገር ሊኖር ይችላል። እዚህ ግን የአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባላት ናቸው። ስለዚህ ያቺ ቤተ ክርስቲያን፥ ከአንዱ ወይ ከሌላው ጋር እንድትወግን ወይም ወግና እንድትቆም፥ አቋሟን እንድትገልጥ መገደድ የለባትም።

በአገር አቀፍ ደረጃ ቢሮ ያላቸው ትልልቅ ቤተ እምነቶች የራሳቸው የሆነ የአገሪቱን የአስተዳደር አካሄድ፥ የሕጉን አዝማሚያ የሚቃኙበት፥ የሚያዩበት፥ የፖለቲካውን ትኩሳት የሚለኩበት፥ አስተያየትና አሳብ ቢጠየቁ፥ ምክርና ዝክር ወይም እዝናት ቢጠየቁ ሊለግሱ፥ ሊሰጡ የሚችሉበት መድረክ ከኖረ ግን ያንን የሚጠቀሙበት፥ ታዛቢ ሆነው በፓርላማ ወይም በሌሎች መንግሥታዊ ስብሰባዎችና ሸንጎዎች የሚቀመጡበት አጋጣሚ ሲኖር ለጸሎትም፥ ለምክር ቃልም ቢፈለጉ የሚገኙበት ሚና ሊኖራቸው ይችላል፤ ከኖረ መልካምም ነው። በአንዳንድ አገሮች እንደዚህ ታዛቢ ሆነው የቤተ እምነት ተወካዮች የሚገኙባቸው ዕድሎች አሉ። መንግሥትም እነዚህን ሰዎች ለአስተያየትም፥ ለምክርም፥ ለጸሎትም ይፈልጋቸዋል። ይህ ቀደም ሲል ለተባለው የሕሊናነት ጉዳይ መጠነኛ አስተዋጽዖም ይኖረዋል።

እንግዲህ በብሔራዊ ቢሮ ደረጃ ቤተ እምነቶች እንዲህ ያለ ዕድል ቢኖራቸው፥ ወይም ቃኚና ታዛቢ ቢሮ ቢኖራቸው፥ ይህ ጠቃሚ ነው። የቤተ እምነቶች ቢሮ ማለት ታዲያ ቤተ ክርስቲያን ማለት አለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል። እንደየ ቤተ እምነቱ አሠራር ሥልጣንና ኃላፊነቱ ሊለያይ ቢችልም፥ ያ ቢሮ አስተባባሪ ቢሮ፥ ሥራ አኪያሂያጅ፥ የአጥቢያዎች የእርስ በርስም ይሁን የሌላ ውጪያዊ ግንኙነቶችን አሳላጭ መሥሪያ ቤት እንጂ ቤተ ክርስቲያን አይደለም። እንዲህም ሆኖ እንደ አስተባባሪ ቢሮ ይህ ብሔራዊ ድርጅት እንደ ቤተ ክርስቲያን ድርጅት ዋና ተልዕኮውን፥ ዋናውን ሚናውን፥ ዋናውን ሥራውን፥ ድርሻውን ሳይጥል መሆን ይጠበቅበታል። ያም ወንጌል ነው። ወንጌሉ ዋናው ሆኖ ነው ሌሎቹ ቅጥያዎች የሚደረጉት። እነዚህ ቅጥያዎች ሰብዓዊ፥ ማኀበራዊ፥ የተራድዖ፥ የረድኤት፥ የግብረ ሰናይ፥ ሌሎችም ሊሆኑ ይችላሉ።

በአንዳንድ አገሮች ወይም አገዛዞች ሃይማኖትና ፖለቲካ ወይም ሃይማኖትና አስተዳደር የተዋሰቡ፥ የተቆራኙ፥ የተጣበቁ ናቸው። አንዱ ከሌላው ከተለየ ሁለቱም አይኖሩም። ለምሳሌ በቫቲካን ግዛት የካቶሊክ ሃይማኖትና አስተዳደሩ ተለይቶ መታየት አይቻልም። ወይም የሸሪዓ ሕግ በሚገዛበት የእስላም አገሮች ሃይማኖቱና አገዛዙ አይለያዩም። ሕጉ ሃይማኖታዊ ነው፤ ወይም ሕጉ ሃይማኖቱ ራሱ ነው። ይህ አካሄድ ሲንር የሃይማኖቱ ተከታይ የሆኑቱ ባለ መብቶቹና ባለ ሥልጣኖቹ ሆነው፥ ያልሆኑቱ

እንደ ሁለተኛ ዜጋ ይታያሉ። ለዚህ ነው ከላይ ያልኩት ሃይማኖታዊ ፓርቲ ጤናማ ያልሆነው። የከህደት ወይም ኢ-ሃይማኖታዊ ሥርዓት ባለበት እንደ ናዚዝም፥ ፋሺዝም፥ ኮሚኒዝም በመሰሉ አገዛዞች የሕዝቡ ስነ ልቡና በፍልስፍናው ተጠፍሮ ስለሚያዝ የሕሊና ነፃነት የለም፤ አይኖርምም። እነዚህ መንግሥታት፥ ማለትም ፍልስፍናው ወይም ሃይማኖቱ የገነነባቸው መንግሥታት አሓዳውያን መንግሥታት ናቸው። ማኅበረ ሰቡም አሓዳዊ ማኅበረ ሰብ (unitary society) ነው።

ዲሞክራሲያዊ ወይም ዲሞክራሲ ዘመም በሆኑ አገሮች ውስጥ ይህንን አሓዳዊ አሠራር አናይም። የሕሊናና የሃይማኖት ነፃነት የተፈቀደ ብቻ ሳይሆን የተከበረም ነው። በአንዳንድ መንግሥታት ዘንድ ለይስሙላም ቢሆን፥ በወረቀት ላይ ብቻ የተቀመጠም ቢሆን፥ ግን ሃይማኖታዊ ነፃነት የተፈቀደ ነው። ዜጎቹ የሚለማመዱት የየዕለቱ ድርጊት ነው። እኔ ይህን የምናገረው ከወንጌላዊ ክርስትና አቅጣጫ ነው። በአገራችን የወንጌላዊ ክርስትና በምን ዓይነት ሂደት፥ በምን ዓይነት ጉዞ እንደተጓዘ በታሪክ እናውቃለን። ብልጭ ብለው ከከሰሙት መነቃቃቶች ውጪ ስር የሰደደ ወንጌላዊ ክርስትና ገና የአንድ ምዕት ዓመት ታሪክ ነው ያለው። በነዐፄ ቴዎድሮስ ዘመን የመጡትን የወንጌል መልእክተኞች ወደ ስሌቱ ካስገባን ቢበዛ የሁለት ምዕት ዓመት ታሪክ ነው።

በነገሥታቱ ዘመን በአገራችን ወንጌላዊ ክርስትና ውጉዝ ነበረ። በደርግ ዘመን ደግሞ ቁስ አካላዊነትና ሐሳባዊነት በሚል ፈርጅ ተለክተው ማናቸውም ሃይማኖቶች በፍልስፍናው የተናቁ ነበሩ። ወንጌላዊው ክርስትና በተለይ የስደት ጊጤ፥ የስደት ዒላማ ነበረ። ከደርግ በኋላ በተከተለው ዘመን ዘረኝነት የተጠናወተው ቢሆንም፥ ባለው አንጻራዊ ዲሞክራሲ ሃይማኖት ነጻነትን አግኝቶ እየተንቀሣቀሰ ይገኛል። ይህ ነጻነት ታዲያ ፥ ቤተ ክርስቲያንን፥ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን (ላስምርበት፥ <u>አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን</u>) በቀደሙት ዘመናት ያልሆነችውን ፖለቲከኛ ሊያደርጋት የተገባ አይደለም።

እርግጥ ነው ከ2018 በኋላ እየሆነ ያለው የፖለቲካ ተሐድሶ አካሄድ ያልተለመደ ብቻ ሳይሆን ብዙዎችን የሚያስፈነጥዝ አካሄድ ነው። በጅምሩ ወራት ይነገሩ የነበሩት ፍቅር፥ ምሕረት፥ ይቅርታ፥ ዕርቅ፥ ሰላም፥ እነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ክርስቲያናዊ እሴቶች ናቸው። ስለዚህ ይህ የማያስደስተው ክርስቲያን ሊኖር አይችልም፤ የለምም። በዚህ ውስጥ ክርስቲያን ፖለቲከኞች ጤናውን የጠበቀ ጤናማ ፖለቲካዊ ሚናቸውን ሲጫወቱ፥ ክርስትናቸው ቀዳሚ፥ ፖለቲካቸው ተከታይ እስከሆነ ድረስ በፖለቲካው ንቁ ተሳታፊ መሆናቸው ትልቅ ፋይዳ አለው። እንደዚህ ያሉ ጤናማ ክርስቲያን ፖለቲከኞችንም እያየን ነንና እግዚአብሔር ይመስገን።

ክርስትናቸውን ያነገቡ፥ ፖለቲካቸውንም የሚያውለበልቡ ጤናማ ክርስቲያን ፖለቲከኞች በየዘመናቱ ነበሩ፤ ጠፍተውም አያውቁም። በአገራችንም በንጉሡም ዘመን፥ በደርግም ዘመን ነበሩ። አሁንም አሉ። አንዳንዶቹ አብረው መሥራት እስከቻሉበት ድረስ ሄደው፥ ማንነታቸውን ገልጠው፥ ትክክለኛ ያልሆነ ነገር ለማድረግ ሲጋበዙ ወይም ሲገደዱ፥ ሕሊናቸውን መሸንገል አቅቷቸው፥ ትክክለኛ ያልሆነ ነገር ማድረግ እንደማይችሉ አሳውቀው፥ ከሥራቸው የተሰናበቱ፥ ከአገርም የወጡ አሉ። አብረው መሥራት እስከቻሉበት ድረስ ሄደው ማለት ነው። እኔም የማውቃቸው አሉ።

ይህ የፍቅር፥ ምሕረት፥ ይቅርታ፥ ዕርቅ፥ ሰላም ጉዳይ የሚያስደስት ነገር ይሁን እንጂ ታዲያ ከበሮና አታሞ ይዘን መንገድ ላይ መውጣት አለብን ማለትም አይደለም። እንደ ክርስቲያን አገልጋይ ለቤተ ክርስቲያን፥ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪም ለክርስቲያኖች ነው ይህንን የምጽፈው። መልካም መሪ እግዚአብሔር ስለሰጠን ይህንን የምናደርግ ከሆነ፥ ያ መሪ በኛ መለኪያ ተለክቶ መጥፎ የሆነ ቀን፥ ወይም ደግሞ መጥፎ መሪ የተነሣ ቀን በከበሮና በዘንባባ ፈንታ ጦርና ሰይፍ ይዘን ወደ ጎዳና ልንወጣ ነው ማለት ነው? እንደ ክርስቲያን፥ እንደ ቤተ ክርስቲያን ይህን ልናደርግ ነው? ስለዚህ ነው ሚዛናዊነት የተገባ ነው የምለው።

እንደ ክርስቲያን ደቀ መዛሙርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሚናችንን ለይተን አውቀነዋል? አንዳንዴ የፖለቲካ ትኩሳት ባየለበት ጊዜ ሚዛናዊነት ራሱ ጽንፈኝነት የሚመስልበት ጊዜ ይኖራል። ከላይ በጠቀስኳቸው ሁለት አጫጭር ጽሑፎች ላይ ልል የፈለግኩት ዋና ነጥብ ሚዛናዊነት ነው። ሚዛናዊ እንሁን ነው። ምክንያቱም ፖለቲካ አስተዛዛቢ ነገር ነው። በእርግጥም በፍጥነት ተለዋጭ ነገር ስለሆነ አስተዛዛቢ ነው። 'ፀሐዩ ንጉሥ ሺህ ዓመት ይንገሥ!' ባሉበት አፍ፥ 'ሌባ ሌባ!' ማለት፤ 'ያለምንም ደም' ብሎ አገርን በደም አበላ መክደን፤ 'ሕዝባዊ ወይም አብዮታዊ ዲሞክራሲ' ብሎ ሕዝብን በዘርና በጎሳ እየገደቡ ለግጭት ማሰናዳት አስተዛዛቢ ነገሮች ናቸው። ይህ እንግዳ ነገር አይደለም። 'ሆሣዕና! ሆሣዕና!' ብሎ፥ 'ስቀለው! ስቀለው!' ማለት ለፖለቲከኞች አዲስ ነገር አይደለም። እነዚያ ጌታን፥ 'ሆሣዕና!' እያሉ በዘንባባ ዝንጣፊ የተቀበሉት ቁርበታቸውን ስንመለከት ሃይማኖተኞች ይመስሉናል፤ አይደሉም። ቀርበን ስናጤናቸው ፖለቲከኞች ናቸው። ፖለቲካዊ መንግሥት ነበር የፈለጉት፤ ጌታ የሮምን መንግሥት ገርስሶ የዳዊትን መንግሥት እንዲመልስላቸው የፈለጉ ሰዎች ናቸው። ለዚህ ነበር፥ *በጌታ ስም የምትመጣ የአባታችን የዳዊት መንግሥት የተባረከች ናት፤* እያሉ ያዜሙ የነበረው።

ስለዚህ ሚዛናዊ መሆን አለብን። መፈክሬን ልድገመው፤ 'ክርስቲያኖች ጤናማ ፖለቲካውያን ይሁኑ፤ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ግን ከፖለቲካ ትጽዳ።' ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች የሁለት አገር ዜጎች መሆናቸውን ነው። የሰማይም የምድርም። የሁለቱም ስፍራቸው መታወቅና መጤን አለበት። ሰማያዊው ዘላለማዊው ነውና ዋናው መሆኑም መረሳት የለበትም። ይህንን ከራሱ ከጳውሎስ ሕይወት በተግባር ተመልክተነዋል።

ጳውሎስ ሰማያዊና ምድራዊ ዜግነቱን በትክክል ያስተናገደ ሰው ነው። በፊል. 3፥20 *እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፥ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን፤* ያለውና ይህን የሰማይ አገር የሚናገረው ጳውሎስ ምድራዊ ዜግነት የሌለው ሰው ሆኖ አይደለም። ጳውሎስ ሮማዊ ዜጋ ነው። ጳውሎስ ይህን የተናገረው ደግሞ ለፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች ነው። በፊልጵስዩስ እና በዜግነቱ ምን ተፈጽሞ ነበር?

ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ያሳለፈው መከራና ወንጌልን መስበኩ በሐዋ. 16 ተጽፎአል። ፊልጵስዩስ በመቄዶንያ የምትገኝ የወረዳ ዋና ከተማና ቅኝ አገር ናት፤ ሐዋ. 16፥12። ቅኝ አገር ናት ማለት ከተማዋ የሮሜ ቀጥታ ተገዥ ናት ማለት ነው። ስለሆነም

የከተማዋ ሕጋዊ ነዋሪዎች በቀጥታ የሮሜ ዜጎች ናቸው። ለዚህም ነው በቁ. 21 ላይ ክሳቸውን ሲያቀርቡ፥ *እኛም <u>የሮሜ ሰዎች ሆነን</u> እንቀበላቸውና እናደርጋቸው ዘንድ ያልተፈቀደልንን ልማዶች ይናገራሉ* ያሉት። እነዚህ ሰዎች የፊልጵስዩስ ሰዎች ናቸው እንጂ የሮሜ ሰዎች አይደሉም፤ ግን ዜጎች ናቸውና፥ 'የሮሜ ሰዎች ሆነን' አሉ። በዘመኑ የሮሜ ዜጋ መሆን እጅግ የሚቋምጡለት በረከትና ሲሳይ ተደርጎ ስለሚታይ የከተማዋ ሰዎች ይህን ዜግነት አክብረውና አጥብቀው ይይዙታል። የሮሜ ዜግነት የማንነት ማስከበሪያ የክብር መታወቂያ ነውና ከዚህ የሚያጎድላቸውን ነገርም በጥብቅ ይቃወማሉ።

በዚህች ከተማ እነ ጳውሎስን (ጳውሎስንና ሲላስን) አንገላትተው፥ ደብድበው ነበር ወደ ወኅኒ የጣሏቸው። ጳውሎስና ሲላስ ምንም ሮማዊ ዜግነት ያላቸው ቢሆኑም፥ ጳውሎስ ፊልጵስዩስ መጀመሪያ በገባ ጊዜ የተቀበለው መከራ ሊደርስበት ሲጀምር የዜግነት ፓስፖርቱን አውጥቶ ሊያሳይ አለመሞከር ብቻ ሳይሆን ጨርሶም አላሰበም ነበር። ወደ ፊልጵስዩስ ሲገባ እንደ ሮም ዜጋ ሆኖ አልገባም። የገባው፥ ያገለገለው፥ መከራ የተቀበለው እንደ ሮማዊ ዜጋ ሳይሆን እንደ ሰማያዊ ዜጋ ሆኖ ነበር። ወንጌልን ነው የሰበከው፤ ስለ ወንጌል ነው ያንን መከራም የተቀበለው። አለመቀበል ይችል ነበር። ጳውሎስ በሌላ ጊዜ (ሐዋ. 22፥24-30) የሮም መንግሥት ወታደሮች ሊያንገላቱትና እየገረፉ ሊመረምሩት ሲሰናዱ ወይም በገመድ ሲገትሩት ሮማዊ ዜጋ እንዲህ መደረግ የለበትምና የዜግነት መታወቂያውን አወጣ። ማንነቱን ተናገረ። ይህ የሆነው በኢየሩሳሌም ነው። ይህን ካደረገ በኋላ በአክብሮት ተያዘ። ኋላ በዚሁ ሊገረፍበት በተከሰሰበት ጉዳይ ይግባኝ ጠይቆ ነው ሮም ድረስ የሄደው። ይግባኝ መጠየቅና ወደ ቄሣር ፊት መቅረብም የሮማዊነት መብት ነው። ይህን ያደረገውም እንደ ዜጋ ሕገ ወጥና ፍርደ ገምድል ሥርዓትን በሕግ መንገድ ለመታገል ብቻ ሳይሆን የተነገረለት ትንቢት መፈጸሚያው መንገድ መሆኑንም ስለተረዳ ይመስላል፤ ሐዋ. 22፥21።

በፊልጵስዩስ የሆነው ግን ሌላ ነው። ሐዋ. 16፥21-22። እንዲህ ይላል፤ *<u>በነጋም ጊዜ</u> ገዢዎቹ፦ እነዚያን ሰዎች ፍታቸው ብለው ሎሌዎቻቸውን ላኩ። የወኅኒውም ጠባቂ፦ ትፈቱ ዘንድ ገዢዎቹ ልከዋል፤ እንግዲህ አሁን ወጥታችሁ በሰላም ሂዱ ብሎ ይህን ቃል ለጳውሎስ ነገረው። ጳውሎስ ግን፦ እኛ የሮሜ ሰዎች ስንሆን ያለ ፍርድ በሕዝብ ፊት ደብድበው በወኅኒ ጣሉን፤ አሁንም በስውር ይጥሉናል? አይሆንም ራሳቸው ግን መጥተው ያውጡን አላቸው። ሎሌዎቹም ይህን ነገር ለገዢዎች ነገሩ። የሮሜ ሰዎችም እንደ ሆኑ በሰሙ ጊዜ ፈሩ፤ መጥተውም ማለዱአቸው፥ አውጥተውም ከከተማ ይወጡ ዘንድ ለመኑአቸው። ከወኅኒውም ወጥተው ወደ ልድያ ቤት ገቡ፥ ወንድሞችንም ባዩ ጊዜ አጽናኑአቸውና ሄዱ።*

በፊልጵስዩስ መከራ ሲቀበል ምንም ያላለው ጳውሎስ፥ በማግሥቱ (በነጋም ጊዜ) 'ውጡና ሂዱ' ሲባል ነው ሮማዊ ዜግነቱን የተናገረው። መብቱን ቢጠቀም ኖሮ የማይደርስበትን መከራ ከተቀበለ በኋላ ሮማዊነቱን መግለጡ፥ ይህንን በፊል. 3 እየተናገረ ያለውን ነገር፥ 'አገራችን ወይም ዜግነታችን በሰማይ ነው' ብሎ ለመናገር ሙሉ አፍ አለው። በፊልጵስዩስ እርሱ በሮማዊ ዜግነቱ ምክንያት መከራን ከመቀበል

ቢጠበቅ ኖሮ ምን ዓይነት ምሳሌነትን ሊተው ይችላል? ሌሎቹ ዜጋ ያልሆኑትስ? የሮም ዜጋ የከተማዋ ሕጋዊ ነዋሪ ያልሆኑቱ የፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች በመከራና በሰቀቀን፥ ዜጋ የሆኑቱ ደግሞ በድፍረትና በልበ ሙሉነት ሊኖሩ ነው ማለት ነው። ደግሞም ዜግነት የሌላቸውና ሊኖራቸውም የማይችሉ ባሪያ የሆኑ ክርስቲያኖች ብዙ ናቸው። በዚህ ረገድ ሁለት የክርስቲያኖች መደብ ሊፈጠር ይችል ነበር። ጳውሎስ ይህ እንዲሆን ቀዳዳ አልበሳም። በሁለቱ ዜግነቶቹ መሐል መስመር አሰመረ። ሮማዊም፥ አረማዊም ሁለቱም የሰማዩ አገር ሰዎች መሆናቸው እንዲገባቸው ሲል መከራ ሲቀበል ዝም አለ። ሲለቀቅ ግን ማንነቱን ተናገረ። ሲለቀቅ። ያኔ ያሰራቸው ሰው ራሱ መጥቶ ነው እንዲወጡ የማለዳቸው። ደግሞም ከወጡ በኋላ በሰላም ወጥተው ሄዱ እንጂ በፊልጵስዩስ ከተማ ቆይተው በወረዳው አስተዳደር ላይ ክስ አልከፈቱም፤ መቀጮ እንዲጣልባቸው አላደረጉም፤ ካሳም አልጠየቁምም። ከብዙ ጊዜ በኋላ ነው ለፊልጵስዩስ ሰዎች ደብዳቤውን ሲጽፍላቸው ጳውሎስ ይህንን የሰማያዊ ዜግነት ጉዳይ ያነሣው። እነርሱ የመጀመሪያዎቹ የፊልጵስዩስ መልእክት ተቀባዮችም፥ ከሩቅ ያለን እኛም ሰማያዊ ዜጋዎች መሆናችንን የተናገረው።

እኛ አገራችን በሰማይ ነውና ተብሎ እንደተጻፈው ይህ እውነት ከገባን የዜግነታችንን ምንነት ወይም የመኖሪያችንን ቅደም ተከተል አንስተውም። እኛ በምድር ለጥቂት ዓመታት በዓላማ የምንኖር ብንሆንም በክርስቶስ መንግሥት ለዘላለም የምንኖር ሰዎች ነን። ስለዚህ ኑሮአችንና አካሄዳችን ዘላለማዊውን ጌታችንን የሚያከብር እና ዘላለማዊውን ዜግነታችንን የሚያንጸባርቅ ሊሆን ግድ ነው። መዝገባችንና ልባችን ሊጠባበቁ ግድ ነው። ክርስቲያኖች በዚህች ምድር ተድላንም ሆነ ስደትንና መከራን ሲቀበሉ ለጊዜው እንደሆነ በማወቅ ነዋሪ አገራቸውን ያስባሉ። ስደትና መከራ ደግሞ አስቀድሞም የተነገረላቸው እውነት ነው። ስደትና መከራ ዘላለማዊ ርስታቸውን እንዲያስቡና ከቶም እንዳይረሱ የሚያደርጋቸው ማሳሰቢያም ነው። ያንን ሲያስቡ እዚህ እንዴት መኖር እንዴት መኖር እንዳለባቸውም ይረዳሉ። ድርብ ዜግነት አላቸውና።

ፖለቲካ የሚለውን ቃል ስናስብ ይህ እዚህ ፊል. 3፥20 'አገራችን' የተባለው ቃል ፖለቲካ ከሚለው ጋር የተቆራኘ መሆኑንም እንይ። ቃሉ πολίτευμα ፖሊቲውማ የሚል ቃል ነው። ፖለቲካ የሚለው ቃልም ከዚህ የተቀራረበ ብቻ ሳይሆን ምንጩም አንድ ነው። πολιτεία ፖሊቴያ የሚለው ቃል ዜግነት ማለት ሲሆን ቃሉ የወጣበት ግስ እንደ ዜጋ በጨዋነት መኖር ማለት ነው። ይህ አገራችን የሚል ቃል ከምድራዊ ስፍራ ያለፈ መታወቂያን፥ አኗኗርን፥ አመላለስን፥ ንግግርን፥ ወግን፥ ዜግነትን፥ ጨዋነትን ያቀፈ ቃል ነው። አንዳንድ ትርጉሞች ዜግነታችን ሲሉ ተርጉመውታል። ቀለል ባለ አማርኛ የተተረጎመው የ1972 ትርጉም ለምሳሌ፥ 'እኛ ግን የመንግሥተ ሰማይ ዜጎች ነን' ይላል። ማለፊያ ትርጉም ነው።

አገራችን በሰማይ ነው ማለት ምድራዊ ዜግነት የለንም ማለት አይደለም። ወይም በአዲስ ኪዳን የምንገኝ አማኞች ከአገራዊ ኃላፊነትና ግዴታ የጸዳን ሰዎች ነን ማለት አይደለም። እንደ ክርስቲያን ዜጋዎች ኃላፊነታችንን ሳንታክት የምናከናውን ሰዎች መሆን ይጠበቅብናል። ነገር ግን፥ እኛ የአዲስ ኪዳን የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት

በምድራዊ አገር ተጠፍረን የታሰርን አለመሆናችንም ሊገባን ያስፈልጋል። በብሉይ ኪዳን ምድራዊ አገር፥ አርበኝነትና ብሔራዊ ስሜት የገነኑትን ያህል መግነን በአዲስ ኪዳን አናይም። የአዲስ ኪዳን የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት እንደ ብሉይ ኪዳን አይሁድ አንድ ወገን ሳይሆኑ፥ ከነገድና ከቋንቋ፥ ከወገንና ከአሕዛብ የተውጣጡ የግሪክ ሰውና የአይሁድ ሰው፥ የተገረዘና ያልተገረዘ፥ ባሪያና ጨዋ፥ አረማዊና እስኩቴስ፥ ወንድና ሴት ያልተባለበት አዲስ ፍጡር ሕዝብ ነው፤ 1ቆሮ. 12፥13፤ ቆላ. 3፥11፤ ራእ. 5፥9-10።

ወደ ድምዳሜው ስመጣ፥ ሁለት ነገሮች ላይ ላስምር። <u>አንደኛ፥</u> ክርስቲያን ፖለቲከኞች፥ ፖለቲከኞች ሲሆኑ ንጹሕ ፖለቲከኞች ሊሆኑ ግድ ነው። ንጹሕ ፖለቲከኞች ስል በፖለቲካ ውስጥ መቆሸሽ ስላለ ነው። በምዕራቡ ዓለም፥ 'ፖለቲካ ቆሻሻ ጨዋታ ነው' የሚሉት አባባል አለ። ሊሆን ይችላል። ግን ቆሻሻ ጨዋታ የሚሆነውን ያህል ጤናማ አገልግሎትም ሊሆን ይችላል፤ ነውም። ስለዚህ ክርስቲያን ፖለቲከኞች ጤናማ አገልጋዮች ይሁኑ። ጤናማ የአገር አገልጋዮች፤ ንጹሕ የሕዝብ አገልጋዮች። ይህን የምለው እንደ ፖለቲካ ተንታኝ ሳይሆን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ ነው። ፖለቲከኛም፥ የፖለቲካ ተማሪም አይደለሁም። ቃሉ ግን ስለዚህ የሚለው አለው።

ክርስቲያኖች እንደ ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን እንደ ክርስቲያን በፖለቲካው መስክ መሰማራታቸው በጣም አስፈላጊ መሆኑን መጀመሪያ የሰማሁትና የተማርኩት ለሴሚነሪ ትምህርት ወደ ካናዳ ካመጡኝና ከቤተ ሰባቸው ጋር እየኖርኩ እንድማር ካደረጉኝ ከዶ/ር ራበርት ቶምሰን ነው። ከዶ/ር ቶምሰን መጽሐፎች መካከል አንዱ From The Marketplace የተባለው እንዲያውም በዚህ ዋና ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥን፥ ክርስቲያኖች በየመስካቸው እንዴት የወንጌል ዜጎች መሆን እናለባቸውና እንደሚችሉ የተጻፈ ነው። ያ ዘመን የደርግ ዘመን መጨረሻ ነበረና ፖለቲካና ክርስትና ዓይንና ቁልቋል ከሚመስሉበት ጊዜና አገር ነው የመጣሁት። ዶ/ር ቶምሰን ደግሞ በካናዳ የተቀመሙ ፖለቲከኛና ቀደም ባሉት ዓመታት ሶሻል ክሬዲት (ወይም በአጭሩ ሶክሬድ) የተባለው ፓርቲ መሪም ነበሩ። ኢትዮጵያን ደግሞ ከውስጥ እስከ ውጪ የሚያውቁ፥ ጣሊያን ሲወጣ የእንግሊዝ ጦር የአየር ኃይል አብራሪ ሆነው የገቡ፥ ከዚያ በኋላም ከአስተማሪነትና ከትምህርት ቤቶች ከፋችነት እስከ ንጉሡ እስከ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ አማካሪነትም የተመሰገነ አገልግሎትን ያገለገሉ ሰው ናቸው። እርሳቸው ስለ ምሥራቁም ስለ ምዕራቡም ፖለቲካ ሲናገሩ መስማት በራሱ ድንቅ ነው።

ከላይ የጠቀስኩት መጽሐፋቸው ክርስቲያን ፖለቲከኞች እንደ ክርስቲያንነታቸው መጠን በተቀመጡበት ስፍራ ሁሉ ለሾማቸው እግዚአብሔርም፥ ለመረጣቸው ሕዝብም ታማኝ ክርስቲያን ፖለቲከኛ እንዲሆኑ የሚያስተምር ነው። እኔ የማውቃቸው ዶ/ር ቶምሰን እንዲህ ያለ ምርጥ የክርስቲያን ፖለቲከኛ ምሳሌ ናቸው። ክርስቲያን ፖለቲከኞች እንዲህ ሊሆኑ የተገባ ነው። ይህ ክርስቲያኖችን የተመለከተ ነው።

<u>ሁለተኛ፥</u> አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥታዊና አገራዊ ፖለቲካ የጸዳች ትሁን። አትግባ እዚያ ውስጥ፤ እጇን አታስገባ። አንድ ነገር በተከሰተ ቁጥር መግለጫ

አታውጣ። አንድ ሰሞን ይህ መግለጫ ማውጣት የተለመደ ፋሽን ሆኖ ነበር። አንዴ አንድ መግለጫ ካወጣች መግለጫ ማውጣት ማቆሚያ የለውም። ቤተ ክርስቲያን የደስታ መግለጫ፥ የኀዘን መግለጫ፥ የውግዘት መግለጫ፥ የድጋፍ መግለጫ፥ የተቃውሞ መግለጫ እያወጣች መዋዠቅና እዚያ አዙሪት ውስጥ መግባት የለባትም። ይህን ስታደርግ ራሷን የምታስርበትን ገመድ እየገመደች ናት። 'ያኔ የተቃውሞ መግለጫ አውጥታ አሁን ለምን ዝም አለች?' ይባላል። 'ያኔ የድጋፍ ደብዳቤ ጽፋ አሁን ዝም ያለችው ብትቃወመን ነው፤ አይደል?' ያስብላል። ከመንግሥት ጋር የጎሪጥ፡ የምትተያይ አካል ትሆናለች። ግድብ ሲሰራ መግለጫ፥ ቦንብ ሲፈነዳ መግለጫ፤ መሪ ሲሾም መግለጫ ሲሻር መግለጫ ካወጣች መግለጫ ማብቂያ የለውም። ሊኖረውም አይችልም። የነዳጅ ዋጋ ሲጨምር መግለጫ፥ ዝናብ ሲቋረጥም መግለጫ ልታወጣ ነው ማለት ነው?

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ማተኮር ያለባት ዋና ተልእኮ፥ ታላቁ ተልእኮ፥ የወንጌል ጉዳይ ነው። ወንጌልን መስበክ፥ ማጥመቅ፥ ማስተማር፥ ደቀ መዛሙርት ማድረግ፥ ደቀ መዛሙርት አድራጊዎችን ማፍራት። ማቴ. 28፥19-20 *እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።* ነው የሚለው። ይህ ነው ጥሪዋ፤ ይሄ ነው ተልእኮዋ። ይህንን ደግሞ ከቀዳሚዋ ቤተ ክርስቲያን፥ ከመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን፥ በመጀመሪያው ምዕት ዓመት ካሉት አብያተ ክርስቲያናት ያየነውና የተማርነው፥ ያነበብነው ነው። የቤተ ክርስቲያን ታሪክም የነገረን ያንን ነው። ያ መሠረታችን ነው። የቤተ ክርስቲያን መሠረተ ትምህርትም ያ ነው። አሁን ከ20 እና 21 መቶ ዓመታት በኋላ ያ መሠረት ተንዶ አዲስ መሠረት አይመሠረትም። ወይም በተመሠረተው ላይ ጨምረን የራሳችንን ሌላ መሠረት ልንደርት አልተነገረንም።

ስለዚህ፥ 'የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ምን አደረገች? የመጀመሪያዎቹ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖች ምን አደረጉ?' ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። አንድ ቄሣር ወርዶ ሌላ ቄሣር በሚመጣበት ጊዜ የጦር መሣሪያ ይዘው፥ ወይም የዘንባባ ዝንጣፊና ከበሮ ይዘው ወደ አደባባይ መውጣታቸው አልተጻፈልንም። እንደ ዜጋ ማድረግም መሆንም ያለብንን ነገር እናድርግ። ቤተ ክርስቲያን፥ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፥ ከዚህ የፖለቲካ አዙሪት ውስጥ እጇን ማስገባት የለባትም፤ ካስገባችም ማውጣት አለባት።

ግለ ሰብ ክርስቲያኖች የፖለቲካ ሚና ሊጫወቱ ከተጠሩ ይጫወቱ፤ ያምርባቸዋል። ቤተ ክርስቲያን ግን እዚህ እሽክርክሪት ውስጥ አትግባ። ቀደም ብዬ እንዳልኩት የቤተ እምነቶች ብሔራዊ ወይም አገር አቀፍ ቢሮዎች የመንግሥትን አካሄድ የሚቃኙበት፥ ቃኚ የሆነ፥ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትንንና ቅዱሳንን ሊሆን ላለው ነገር በጸሎትም፥ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርትም፥ በሕሊናዊ ንቃትም ጭምር የሚያዘጋጁ ቢሮዎች ቢኖሯቸው መልካም ነው። የውክልናና የታዛቢ ወንበር ካገኙም በዚያ ሆኖ የሚሆኑና ሊሆኑ ያላቸውን ነገሮች መመልከቱ ይጠቅማል። ይህ ጸሎትን ያነሣሳል፤ ክርስቲያን ፖለቲከኞችም በጉዳዮቹ ሚዛናዊ፥ ተጽእኖ ፈጣሪ ሚና እንዲኖራቸው፥ ቅዱስ የሆነ ተጋቦት እንዲኖራቸው፥ ጸሎትና ምክክርም እንዲደረግ፥ አንዳንድ ሕጎች

ከመጽደቃቸው በፊት በረቂቅ ደረጃ ላይ እያሉ አሳብ የመስጠት ዕድል እንዲኖር ያደርጋልና መልካም ነው። ታዲያ ያም ሁሉ ሆኖ የነዚህ ብሔራዊ ቢሮዎች አጀንዳ ዋናው ተልእኮአቸው፥ ወንጌሉ ሳይሸፈን መሆን አለበት።

በአገራችን አሁንም ወደፊትም እየሆነ ካለው ነገር አንጻር መልካም ወሬ ማውራት መልካም ነው። ግን ክርስቲያኖች ከሰሞናዊ ትኩስና ሰበር ፖለቲካዊ ወሬ ያለፈ አጀንዳ እንዳለን መርሳት የለብንም። ወንጌል ዋና ጥሪያችን ነው። መፈክሬን ወይም አዝማቼን ደግሜ ልጨርስ፤ ክርስቲያኖች ፖለቲከኞች ሲሆኑ፥ ጥሩ ፖለቲከኛ፥ ክርስቲያን ፖለቲከኛ ይሁኑ። ቤተ ክርስቲያን፥ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ግን ፖለቲከኛ አትሁን።

## ምዕራፍ ፫

# ክርስቲያንና ኮሮና

ክርስቲያን እና ኮሮና ቫይረስ በቪድዮ በስድስት ተከታታይ ክፍሎች ተዘጋጅቶ የተሰራጨ ትምህርት ነው። በነዚህ ስድስት ቪድዮዎች ላይ የተላለፈው ትምህርት ወደ ጽሑፍ ተቀይሮና በጥቂት ቦታዎች ከተጨማሪ አሳቦች ጋር ነው በዚህ መልኩ ለንባብ የቀረበው። ተከታታይ ቪድዮዎቹ የተዘጋጁት ኮቪድ-19 መላዋን ዓለም በናጠበትና ብዙ ነገሮች በተዘጋጉበት፥ ብዙዎች በወረርሽኙ በተያዙበት፥ በሞቱበት፥ ቤተ ክርስቲያንም ተዘግታ አምልኮና ስብሰባዎቹ በኢንተርኔት አማካይነት ይደረጉ በነበሩባቸው ጊዜያት ውስጥ ከDecember 2020 እስከ March 2021 ባሉት ሦስት ወራት ውስጥ ያካፈልኳቸው ናቸው።

ከቪድዮው ወደ ጽሑፍ የቀየሩትን ወገኖች ጌታ በብዙ ይባርክ። ይህንን ጽሑፍ በመጽሐፊት መልክ በፒዲኤፍ ለብቻም በማኅበራዊ ትስስር መስመሮቼ አጋርቻለሁ። ለቡድን ውይይትም ይሆኑ ዘንድ ጥያቄዎች በመጽሐፊቱ በመጨረሻ ገጾች ላይ ተያይዘው ቀርበዋል።[2]

## ኮቪድ-19 እና ፍርሃት

በመጽሐፉ መግቢያ እንዳልኩት በዚህ ክርስቲያንና እንትን እያልኩ የምጽፍባቸው ጉዳዮች አንዳንዶቹ ጉዳዮች ጥልቅ ምርመራና ብርበራ የሚያስፈልጋቸው እና ግላዊ ውሳኔና አቋምም የሚጠይቁ ናቸው። እንዲህ ባሉቱ ጉዳዮች እስከተቻለኝ አስቤበትና

[2] ተከታታይ ቪድዮዎቹ ከዚህ ከመጀመሪያው ቪድዮ ጀምሮ ይገኛል፤ *https://www.youtube.com/watch?v=mFc9xNs4-Hs* መጽሐፊቱ ደግሞ እዚህ ትገኛለች፤ *https://t.me/zelalemmengistu/465*

አጥንቼው ሚዛናዊ ነው የምለውንና የተረዳሁትን እውነት የማካፍለው። በጉዳዮቹ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚናገርባቸው ነገሮች ያለ ፍርሃት እና ያለ ጥርጥር አካፍላለሁ። ግላዊ ውሳኔ የሚጠይቁ ጉዳዮች ላይም የራሴን አቋምና የግል ውሳኔ ሳልደናበር እገልጣለሁ። የኔ አቋም ሁሉ ሊቀበሉት የተገባ ነው አልልም። ቃሉ የሚለው የቃሉ ትምህርት ግን ሁሉ ሊቀበሉት የተገባ ነው። በተለይም የቃሉ አማኝ የሆንነው ክርስቲያኖች ያለ ምንም ጥርጥር ልንቀበለው የተገባ ነው።

በዚህ ዝግጅት ስለ ኮሮና ወይም ኮቪድ-19 አካፍላለሁ። የማካፍለው ይህ መረዳቴ በዜና አውታሮችና በምሑራን ገጾች የተሰራጨ ሆኖ የግሌ መረዳትም ነው። እጅግ ጥልቅና ሳይንሳዊ ምርምር የተደረገበት ሳይሆን በግል ያጠናሁት እና ቃሉን እንደሚያነብብ፥ ዘመኑን እንደሚመረምር፥ መረጃዎችን እንደሚያይ እንደሚሰማ አገልጋይና የቃሉ አስተማሪ የገባኝን መረዳቴን ያካፈልኩበት መረዳት ነው። ኮቪድ ኮሮና ቫይረስ ዲዚዝ (Corona Virus Disease) ማለት ነው። 19 የተባለው የተከሰተው ወይም የታወቀውና ስርጭቱ በፍጥነት መከሰት የጀመረው በፈረንጆቹ 2019 መጨረሻ ስለሆነ ነው። 19 መለያው የሆነው ሌሎች ኮቪዶች ኖረው ስለሚያውቁ ነው ኮቪድ-19 የተባለው። ኮቪድ የእንፍሉዌንዛ ዓይነት በሽታ ነው።

ይህን ዝግጅት በመጀመሪያ ሳካፍል ኮቪድ ከተከሰተ ገና ዓመት ሆኖት ነበር። እስከዚያ እስከ December 2020 አጋማሽ፥ December 11 ቀን 2020 በወሰድኩት ዳታ መሠረት፥ በዓለም በጠቅላላ ወደ 70 ሚሊየን ተይዘዋል። በትክክል 70,902,031። 71 ሚሊየን ብሎ ማጣጋት ይችላል። ከተያዙት ውስጥ 49.4 ሚሊየን (70%) ድነዋል፤ 1.59 ሚሊየን 1.6 ሚሊየን ማለት ይቻላል (2.2%) ሞተዋል። 2.2% ከተያዙት ሲሰላ ነው። ከ2.2ቱ እና ከዳኑት 70% ሌላ የቀሩቱ በሙሉ ገና ተይዘው የሚገኙት ናቸው። በዓለም የኮቪድ ስርጭ ግንባር ቀዳሚዎቹ 1ኛና 2ኛ አገሮች አሜሪካ እና ሕንድ ናቸው። እነዚህ ሁለት አገሮች በሕዝብ ብዛት፥ በብልጽግናና በቴክኖሎጂ ምጥቀትና አቅርቦት ደረጃ አይገናኙም። ሆኖም በሁለቱም ጉዳቱ ትልቅ ነው። በዚሁ ጊዜ በኢትዮጵያ 115 ሺህ ተይዘዋል፤ 79 ሺህ (78%) ድነዋል፤ 1,779 (1.5%) ሞተዋል። 1.5% ከተያዙት ነው። የኢትዮጵያው ካልተያዙት ሲሰላ፥ ከአንድ ሚሊየን ሰዎች 15 ሰዎች ናቸው የሞቱት። 0.0015% ማለት ነው። ከዓለም ሲሰላ ኢትዮጵያ ከ209 አገሮች 64ኛ ተርታ ላይ ናት። ምንጭ፥ https://epidemic-stats.com/

ከሦስት ዓመታት በኋላ (November 1, 2022) የተያዙ ሰዎች ቁጥር፥ ወደ 630 ሚሊዮን (በትክክል 627,573,679) ሲሆን የሞቱት 6.5 ሚሊየን (በትክክል 6,570,363) ነው።

ይህ እስታቲስቲክሱ ነው። ወደ ኮቪድ-19 ምንነት ስንመጣ፥ ኮቪድ መቅሰፍት ነው? ወይስ ቸነፈር? ወረርሽኝ ነው? ወይስ ሰው ሠራሽ ሴራ? ሁሉንም ቃላት በማብራራት በተለይም የሴራ ንድፈ አሳብ በሚለው ጉዳይ በመጠኑ እናገራለሁ። በመጀመሪያ ግን፥ ኮቪድ-19 ስለፈጠረው ፍርሃት እና ፍርሃት ራሱ አስፈሪ ስለሆነበት አሳብ በማካፈል እጀምራለሁ።

## ኮቪድ እና ፍርሃት

ኮቪድ የተከሰተው በ2019 መጨረሻ ቢሆንም መዛመት የጀመረው በ2020 መጀመሪያ ነው። በአጭር ጊዜ በብዙ አገሮች መዛመቱና ዓለም አቀፋዊ ትኩረት ብቻ ሳይሆን ከትኩረትም ያለፈ ድንጋጤና ፍርሃት መፍጠሩ በጉልህ ታይቷል። በሰዎች ልብ ውስጥ ግር መሰኘት፥ ግራ መጋባት፥ ድንጋጤ፥ ፍርሃት ሽብር ነገሠ። ኮቪድ ፍጡር ቢሆን ኖሮ ትልቁ ሽብርተኛ በሆነ ነበር። ይህ እዚህ የማካፍለው አሳብ በመጀመሪያዎቹ የኮቪድ ወራት በአንድ ቤተ ክርስቲያን፥ 'ኮቪድ እና ፍርሃት' በሚል ርእስ ያስተማርኩት ነው።

2020 በባተ ከ3ኛው ወር ጀምሮ ሰው ግራ የገባው፥ የፈራበት፥ የደነገጠበት ጊዜ ነው። ከቫይረሱ ፍርሃት የበለጠ የሰው ፍርሃት ራሱ የሚያስፈራ የሆነበት ጊዜ ነው። ፍርሃት ራሱ እንደሚያስፈራ ታየ። ይህ የፍርሃት ፍርሃት በስነ ልቡና ቋንቋ Phobophobia ፎቦፎቢያ ይባላል። ፍርሃትን ራሱን መፍራት ማለት ነው። በአንዳንድ እንዲህ ባሉ ፍርሃት በሚያስጨንቃቸው ሰዎች ዘንድ የጭንቀት ወረራ ይካሄድባቸዋል፤ panic attack ይሉታል።

ፍርሃትን ስለመፍራት በጣም የታወቀው ቃል፥ በ2ኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የአሜሪካ ፕሬዚደንት የነበረው Franklin Delano Roosevelt የተናገረው ቃል ነው። እንዲህ ነበር ያለው፤ So, first of all, let me assert my firm belief that the only thing we have to fear is . . . fear itself - nameless, unreasoning, unjustified terror which paralyzes needed efforts to convert retreat into advance. ስተረጉመው፥ "በመጀመሪያ ጽኑ የሆነ እምነቴን ግልጽ ላድርግ፤ መፍራት ያለብን አንድ ነገር ፍርሃትን ራሱን ነው፤ ያም፥ አስፈላጊ ተግባርን አሽመድምዶ ማፈግፈግን ወደ ግስጋሴ እንዳንለውጥ የሚያደርግ ስም የለሽ፥ ምክንያት የለሽ፥ ተቀባይነት የሌለው ሽብር ነው።" ፕሬዚደንቱ ይህን የተናገረው ማርች 4፥ 1933 ነው፤ ከ90 ዓመታት በፊት ማለት ነው።

ኮቪድን በተመለከተ በመጀመሪያዎቹ ወራት የነበረው ፍርሃት አሸመድማጅ ነበር። እግዚአብሔር ራሱ በሆነውና በሚሆነው ነገር ግራ ተጋብቶ ይሆን? ግር ብሎት ይሆን? ደንግጦ ይሆን? ብለው የሚያስቡም አይጠፉም። ኳራንቲን (ወይም ወሸባ) ዋናዋ እውቅ ቃል ነበረች። ለአንዳንዶች እግዚአብሔርም ራሱ ኳራንቲን ውስጥ የገባ ያስመሰለው ወቅት ነው። እሺ እግዚአብሔር ግራ አይግባው፤ እኛ ግን በእግዚአብሔር ግራ ብንጋባስ? መጠርጠር ሳይሆን ግር ብንሰኝስ? ኢዮብ ያንን ሆኖ ነበር፤ በማይገባው፥ በማያውቀው ምክንያት መከራ እንደ ናዳ፥ እንደ ዶፍ ዝናብ ወርዶበት ነበር። ዝም አላለም፤ እግዚአብሔርን ጠየቀ፤ ግን እምነቱንም ንጽሕናውን ጨብጦ ነው የጠየቀው። ይህ ጥያቄ ክሕደት አይደለም፤ ጥርጥርም አይደለም፤ ጥያቄ ነው። ጥርጥርና ክህደት ቢሆን፥ 'ቢገድለኝም እንኳ እርሱን እጠብቃለሁ' አይልም ነበር። በኋላ፥ በመጨረሻው እግዚአብሔር መለሰለት በድንቅ፤ እንዴት እንደመለሰለት በኢዮ. 38-42 ይገኛል።

የኮቪድ የመጀመሪያ ወራት ሰው የፈራበት ጊዜ ነው። ፍርሃት ግን ምንድር ነው? ፍርሃት ስሜት ነው፤ ልክ እንደ መውደድ፥ ማዘን፥ መቆጣት ሁሉ መፍራትም ስሜት ነው። ፍርሃት እንደ ስሜት ሁለት ዓይነት ነው።

አንደኛው ዓይነት ፍርሃት ጤናማ ስሜት ነው። ጤናማው ፍርሃት፥ ጤናማው መፍራት ወይም መደንገጥ ሁለት ነገሮች አሉበት፤

1፥ ጥንቃቄ አለበት፤ ጉዳትን መፍራት ጥንቃቄን ያመጣል።

2፥ አክብሮትም አለበት፤ እግዚአብሔርን እንድናከብር ያደርገናል። እግዚአብሔርን እንድንፈራ ቃሉ ያስተምረናል። ይህ ፍርሃት የአክብሮት ፍርሃት ነው።

ሁለተኛው፥ ጤናማ ያልሆነ ፍርሃት ነው። ይህኛው የመሸማቀቅ፥ የመጨነቅ፥ የመታወክ፥ የመረበሽ፥ የመሸበር ስሜትን የሚያንር፥ የሚያጋንን ስሜት ነው። ፍርሃትና ድንጋጤ በሰውነታችን የሚፈጥሩትን ነገሮች በሳይንሱ በመጀመሪያ እንየውና ወደ መንፈሳዊው ግንዛቤ እመለሳለሁ። ፍርሃት ስሜት ነው ብያለሁ። ጤናማ አስጠንቃቂ ስሜት ነው። ፍርሃት አጉልና ጎጂ የሚሆነው ይህ የፍርሃት ስሜት ገዢና ተቆጣጣሪ ሲሆን ነው። ውሎ ሲያድር፥ ሲሰነብት፥ ሲባጅና ሲከርም፥ ሲኖር አደጋ ነው። ለምሳሌ፥ ይህ እየተዛመተ ያለው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ፥ ከቫይረሱ ከራሱ ወረርሽኝ ይልቅ የፍርሃት ወረርሽኝ ሆኗል። ሰው ባለማቋረጥና በማያቋርጥ ፍርሃት ውስጥ ይገኛል። ፍርሃቱ የማያልቅ፥ የማይከስም ሆኖ ለአያሌ ወራት ቆየ።

ፍርሃት ወይም ድንጋጤ በጤናማና በአስጠንቃቂ መልኩ የሰውነታችንን ቅመም እና ደም ዝውውር ለጊዜው ይለውጣል፤ ጊዜያዊ ጉልበት እንድናገኝ ይረዳናል፤ የተለየ ፈጣን እንቅስቃሴ እንዲኖረንም ያደርጋል። ለምሳሌ፥ ጎርፍ ወይም አውሬ በአቅጣጫችን ሲመጣ ብናይ እንደነግጣለን፥ እንፈራለን፥ ከዚያም ለመከላከል እንዘጋጃለን፤ ወይም ለማምለጥ እንሸሻለን። ያ ሲሆን፥ በመፍራትና በመደንገጣችን በሰውነታችን ውስጥ አኅልባች ቅመሞች ተረጭተው ቀድሞ ያልነበረንን ተጨማሪ ጉልበት እናገኛለን። ሂደቱ እንደሚከተለው ነው።

ፍርሃት በአእምሯችን ሲከሰት ወይም አእምሯችንን ሲይዘው እንደነግጣለን። ስንደነግጥ አእምሯችን ለጭንቅ ጊዜ የሚሆኑ ቅመሞችን እንዲመነጩ ያዝዝና በትእዛዙ መሠረት ወደ አስፈላጊው የሰውነት ክፍል ይረጫል። ይህ ጤናማ ነገር ነው። ፍርሃት ወይም ድንጋጤ ሲይዘን አንጎላችን አካላችንን ለአንድ ዓይነት የጥቃት ምላሽ የሚያዘጋጅ፥ የማጥቂያ፥ ወይ የመከላከያ፥ ወይ የማምለጫና መሸሻ አኅልባች ቅመሞችን እንዲያመነጩ ዕጢዎችን ያዝዛል። በተለይም አድሬናል የተባለው ኩላሊታችን ላይ ያለው ዕጢ አድሬናሊን፥ አልዶስትሮን፥ ኮርቲሶል እና ኖሬፒኔፍሪን (adrenaline, aldosterone, cortisol and norepinephrine) የተባሉ ብርታት ሰጪ ቅመሞች ወይም ሆርሞኖች እንዲያመነጭና እነዚህ ወደ አንዳንድ ቦታዎች እንዳይሄዱና ወደ ሌላ ቦታዎች ደግሞ በፍጥነት እንዲሄዱ የሚያደርግ የሰውነትን የደም ፍሰትና ዝውውር ሥርዓቶች እንዲከናወን ያደርጋል። ይህ የሚሆነው ፍርሃቱ ወይም ድንጋጤው ባለበት ጥቂት ጊዜ ውስጥ ነው። ለዘለቄታው አይደለም። ይህ ስርጭት ፍርሃትና ድንጋጤ እንደዚያ ሆኖ ከቆየና ስርጭቱ ለዘለቄታው ከሆነ ጉዳት ያመጣል። በዚያኑ ጊዜ የሰውነታችንን የጥቃት ተከላካይ የሆኑ ሂስታሚን እና ሳይቶካይን (histamine and cytokines) የሚባሉ ቅመሞችንም አመንጭቶ ያሰራጫል። የሚያሰራጨውም በደማችን አማካይነት ነው። በፍጥነት እንዲሰራጩ ዝውውሩ ፍጥነቱ ይጨምራል፤ ይህ እንዲሆን ልባችን ምቱ ይጨምራል።

በማንደነግጥባቸው በአዘቦቱ ቀናት የደም ዝውውራችን የተረጋጋና አስፈላጊዎቹ ቅመሞች በአብዛኛው የሰውነታችን ውስጣዊ ብልቶች ላይ ይሰራጫሉ። እነዚህ የውስጥ ብልቶች ሰውነታችን እንዲያድግ፥ እንዲጠበቅ፥ ጤና እንዲሆን፥ ሕመምን እንዲከላከልና ሕመም ሲመጣም እንዲዋጋ፥ አዳዲስ ሴሎች እንዲፈጠሩ፥ የተበላሹት እንዲጠገኑ የሚያደርጉት ብልቶች ናቸው። ስንደነግጥ ወይም ስንፈራ የሚፈጠረው ችግር ምንድነው ቢባል፥ ወደነዚህ የሚፈሰው ይቋረጣል ወይም በጣም ይቀንሳል። ያ ሲቀንስ ወደ እግርና እጆቻችን ጡንቻዎች የሚሄደው ደግሞ በጣም ይጨምራል። ለምን? እነዚያ (እነ ኩላሊት፥ ጣፊያ፥ ጉበት፥ አንጀት፥ ወዘተ) ለጊዜው መቆየት ይችላሉ። እነዚህ ግን (እግርና እጅ) የማጥቂያ ወይም የመከላከያና የማምለጫ

ብልቶቻችን ስለሆኑ ኃይል ያስፈልጋቸዋል። እናም በነዚህ የፍርሃትና የድንጋጤ ጊዜዎች ማድረግ የማንችላቸውን ነገሮች የምናደርገው ወይም ማድረግ የምንችለው በዚህ ምክንያት ነው።

እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን ነገር፥ በማንደነግጥባቸው በአዘቦቱ ቀናት የደም ዝውውራችን በአብዛኛው የሚያተኩርባቸው የሰውነታችን ውስጣዊ ብልቶች አንዱ ተግባራቸው የበሽታ መከላከል ሥርዓት ወይም (immune system) የሚባለው ነው። immune system ተጎዳ ማለት ልክ የአገር መከላከያ ሠራዊት ተጎዳ ማለት ነው። መከላከያ ሲሰበር ዜጋው ይጎድዳል። ስንደነግጥ ወደነዚህ የመከላከያ ብልቶች የሚፈሰው የደም ዝውውርና የቅመሞች አቅርቦት ሲቋረጥ ወይም በጣም ሲቀንስ የሰውነታችን የበሽታ መከላከያ ስርዓት ይቃወሳል፤ ግን ለጊዜው ነው። ለ10 ወይ 15 ደቂቃ፥ ወይም ለግማሽ ሰዓት ብንደነግጥ ምንም ችግር የለውም። ከአደጋው ካመለጥን በኋላ ስንረጋጋ ስርጭቱ ተመልሶ ወደ ጤናማ ዝውውር ይመለሳል። በፍርሃት ውስጥ ሆነን ግን ለ15 ደቂቃ ወይ ለግማሽ ሰዓት ሳይሆን ለሰዓታት፥ ለቀናት፥ ለሳምንታት ብንቆይ ወይም ስንቆይ ግን እጅግ ይቃወሳል። በዚህ ጊዜ የውስጡ ሰውነታችን ጉልበት ያጣል፤ የበሽታ ተከላካይ የሆነው immune system ጉዳት ያገኘዋል። ይህ ከተጎዳ ሰውነታችን በቀላሉ ይጠቃል፤ መከላከያው፥ የጦሩ ቢሮ ተጠቅቷላ! እሱ ጉልበት ሲያጣ ሰውነታችን በሙሉ ጉልበት ያጣል፤ ሕመምን መቋቋም አቅቶት በበሽታ ተጠቅቶ ይተኛል።

በሽታ ከብዙ ምንጮች ሊመጣ ይችላል። ምንጮቹን መዘርዘር ውስጥ አልገባም። አንዱ ምንጭ ግን ይህ ፍርሃትና ድንጋጤ ነው። ፍርሃትና ድንጋጤ የበሽታ መከላከያችንን ስለሚጎዳ፥ የመከላከል አቅማችንን በማሳነስ ቀላል የሆኑ በሽታዎች እንኳ ሳይቀሩ እንዲያጠቁን የሳሳን ያደርገናል። ስለዚህ የሚሰነብትና የሚሠለጥንብን ድንጋጤና ፍርሃት የበሽታ ምንጭ መሆኑ ግልጽ ነው።

## ክርስቲያን እና ፍርሃት

ፍርሃት ስንል ቀደም ሲል እንዳልኩት ጤናማ የጥንቃቄ ፍርሃት አለ። ጤናማ ድንጋጤ አለ። ነገር ግን ፍርሃትና ድንጋጤ ሊሰለጥንብን፥ ሊሰነብትብን፥ ሊገዛን መፍቀድ የለብንም። እኛ ክርስቲያኖች ከሌሎች ሰዎች ሁሉ ይልቅ ፍርሃትን የምንቋቋምበት መንገድ የተጠረገልን ሰዎች ነን። 'አትፍሩ' ተብሎ ተደጋግሞ የተነገረን ሰዎች ነን። ሰዎች የተለያዩ ነገሮችን ሊፈሩ ይችላሉ። በጥቅሉ ግን ሁለት ትልልቅ ነገሮችን

ይፈራሉ። አንዱ ኑሮ ነው፤ የኑሮ ፍርሃት። ሁለተኛው ሞት ነው፤ የሞት ፍርሃት። መኖርም፥ መሞትም ሊያስፈሩ ይችላሉ። ሁለቱንም በመጠኑ እንያቸው።

## 1. የኑሮ ፍርሃት

የኑሮ ፍርሃት ማለት ኑሮን በመግፋት ውስጥ የሚገኝ መታወክ፥ በሕይወት ግራ በመጋባት መጨነቅ ነው። ኑሮ የዋዛ አይደለም። ለአንዳንዶች ኑሮ እንደ ላባ ቀላል ነው። ለሌሎች፥ ድንጋይ ተሸክሞ ዳገት መውጣት ነው። ለብዙዎች ደግሞ የሁለቱም አማካይ ነው። ውጣም ውረድም ነው። እኛ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር እኛን፥ 'እንደ ፍጥርጥራችሁ' ብሎ ለኛ ለራሳችን የተወን ሰዎች አይደለንም። በሚያስፈሩ ነገሮች መካከል የምናልፍ መሆናችንን ስለሚያውቅ የሚያበረታታን አምላክ ነው። እግዚአብሔር የሩቅ ጌታ ሳይሆን የቅርብ አባት ነው።

የኑሮ ፍርሃት ወይም በኑሮ ግራ መጋባት ሲባል አንዱ ገጽታው ከጊዜ ጋር የተያያዘ ነው፤ ሌላው ደግሞ ከቦታ ወይም ከዙሪያችን፥ በዙሪያችን ከሚሆነው ጋር የተያያዘ ነው። ሁለቱንም እንይ፤

ሀ. ከጊዜ ጋር ሲባል ያለፈውም፥ የአሁኑም፥ ነገ የሚባለው የወደፊቱም ነገርም ነው። ያለፈው ጥፋት እንደ ጸጸት ሰዎችን እየወረረ፥ እየረበሸ ሊቆይ ይችላል። የአሁን ሁኔታም ሊያውክ ይችላል። ግን ዋናው ነገ የሚባለው ጊዜ ነው። ላተኩር የምፈልገው ስለ ነገ ነው።

ነገ የሚሆነውን ያለማወቅ ፍርሃት ሰዎችን ያስፈራል። ነገ ያስፈራል ስል፥ ነገ ምን እንበላለን? ምን እንጠጣለን? ምን እንለብሳለን? ምን ይሻለናል? ምን ሊበጀን ነው? የት እንገባለን? ምን ሊውጠን ነው? ወይ ጉዴ! የሚባለውን ነገር ማለቴ ነው። ነገ የሚባለው ነገር ያስፈራል። የማናውቀው ነገር ውስጥ፥ የማናውቀው ቦታ፥ ስፍራ፥ የማናውቀው መንገድ፥ አገር መግባት እንድሚያሰጋ ያህል ያሰጋል። ያ ስፍራ ነው፤ ይህኛው ግን እዚያው ቦታ ሆነን፥ እዚያው ስፍራ ሆነን፥ ቦታው ሳይቀየር ጊዜው ሲለወጥ ነው፤ ነገን የአለማወቅ፥ የሚሆነውን የአለማወቅ ስጋት ነው። ብናውቅ ኖሮ ምናልባት ባናውቅ ከምንሰጋው የበለጠ ልንሰጋም እንችላለን። ሆኖም ስለ ነገ ጭንቀት ጥቂት አሳቦች እንይ።

ለነገ ስላለመጨነቅ ጌታ የተናገረውን እናስተውል፤ ማቴ. 6፥25-34።

25-27 *ስለዚህ እላችኋለሁ፥ ስለ ነፍሳችሁ በምትበሉትና በምትጠጡት፥ ወይም ስለ ሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ፤ ነፍስ ከመብል ሰውነትም ከልብስ አይበልጥምን? ወደ ሰማይ ወፎች ተመልከቱ፤ አይዘሩም አያጭዱምም በጎተራም አይከቱም፥ የሰማዩ አባታችሁም ይመግባቸዋል፤ እናንተ ከእነርሱ እጅግ አትበልጡምን? ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማን ነው?* ስለ መብል ነው በመጀመሪያ የሚናገረው። *ስለ ነፍሳችሁ* ሲል ነፍሳችሁን ለማኖር፥ ለማቆየት ማለቱ ነው እንጂ ከሞት በኋላ ስላለችው ነፍስ መናገሩ አይደለም። ወፎችን ምሳሌ ይሰጥና፥ የሰማዩ አባታቸውም ሳይሆን፥ *የሰማዩ አባታችሁም ይመግባቸዋል፤* ይላል። እርሱ የእናንተ አባት ነው፤ የእናንተ አባት የሚመግባቸው ደግሞ እነርሱን ነው። 'የእናንተ አባት እነርሱን ከመገበ እናንተንስ?' ነው ትምህርቱ።

28-30 *ስለ ልብስስ ስለ ምን ትጨነቃላችሁ? የሜዳ አበቦች እንዴት እንዲያድጉ ልብ አድርጋችሁ ተመልከቱ፤ አይደክሙም አይፈትሉምም፤ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ ሰሎሞንስ እንኳ በክብሩ ሁሉ ከነዚህ እንደ አንዱ አልለበሰም። እግዚአብሔር ግን ዛሬ ያለውን ነገም ወደ እቶን የሚጣለውን የሜዳን ሣር እንዲህ የሚያለብሰው ከሆነ፥ እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ እናንተንማ ይልቁን እንዴት?* ስለ ልብስስ ለምን ትጨነቃላችሁ ብሎ የሜዳ አበቦችን ምሳሌ ይሰጣል። ዛሬ ታይተው ነገ ጠፊ የሆኑ አበቦች ውበታቸው እጅግ ይደንቃል። አበቦችን፥ የቀለማቸውን ኅብርና ውሕደት ማየት ይመስጣል። ግን ከእርሱ በፊትም፥ ከእርሱ በኋላም በብልጥግና የሚመስለው የሌለ ሰሎሞን እንኳ ከአበቦቹ እንደ አንዳቸውም አልለበሰም። እነዚህ ግን ታይቶ ጠፊ ውበቶች ናቸው።

ቀጥሎ የወቀሳ ወይም የነቀፋ ቃል ተነገረ፤ *እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥* ይህ የጎደላቸው ነገር ትልቅ ነገር ነው። እምነት ነው። የፍርሃት፥ የድንጋጤ፥ የስጋት፥ የጭንቀት፥ የጥበት መድኃኒቱ ወኔ፥ ጀግንነት፥ ድፍረት ሳይሆን እምነት ነው። እምነት መታመን፥ መደገፍ፥ አለመጠራጠር ነው።

31-34 *እንግዲህ፦ ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ፤ ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይፈልጋሉ፤ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና። ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል። ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ፤ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል።*

ነገ የኛ አይደለም፤ ባለቤት ግን አለው፤ ባለቤቱንም እናውቃለን። ስለዚህ መታወክ የለብንም። ከእናንተ ተጨንቆ . . . ይላል። እኛ ሰዎች ተጨንቀን የምናደርገው ጥቂት

ነው። ምናልባት ምንም ነው። ጭንቀት፥ ስጋት፥ ድንጋጤ፥ ፍርሃት በአካልና በነፍስ ምን እንደሚያመጡ በማየት ነው የጀመርነው። ፍርሃት አካልን ይጎዳል። እግዚአብሔር መጋቢያችን፥ እረኛችን ነው። 'የሰማዩ አባታችሁ' ነው የተባለው፤ እና አባታችን መሆኑን መርሳት የለብንም፤ የነፍስና የሥጋ መጋቢያችን መሆኑን ለአፍታም መዘንጋት የለብንም።

*ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይፈልጋሉ፤ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና።* እዚህ ጥቅስ ውስጥ ያሉትን ሁለት ነገሮች እናስተውል፤ አንዱ ፍላጎት ለው፤ ሌላው አስፈልጎት ወይም አስፈላጊ ነገር ነው። የምንፈልገው ብዙ ሊሆን ይችላል። የምንፈልገው ሁሉ ግን አስፈላጊ ነው ማለት አይደለም። አባታችን የሚያስፈልገንን ያውቃል። የምንፈልገውን ሳይሆን የሚያስፈልገንን። ያንን ደግሞ አያሳጣንም። ፊል. 4፥19 *አምላኬም እንደ ባለ ጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል።*

ነገ ሊያስፈራ ይችላል። ግን ጌታ ሲያስተምር፥ *ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ፤ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል።* እንዳለው፥ ነገን ማን እንደያዘው፥ የነገ ባለቤት ማን እንደሆነ ካወቅን፥ ይህንን አትጨነቁ ያለው ደግሞ ራሱ የነገ ባለቤት መሆኑን ስናውቅ አንፈራም። ነገ የራሱ ጭንቀት ካለው የነገውን ጭንቀት ለዛሬ ተበድረን ወደ ዛሬ አምጥተን፥ የዛሬው ላይ ጨምረንበት፥ ለምን ድርብ ጭንቀት እንጨነቃለን? እንኳን ድርቡን ነጠላውንም እንዳንጨነቅ ተነግሮናል። ይህ ከጊዜ ጋር የተቆራኘ ነገን መፍራት፥ የወደፊት ፍርሃት ነው።

ለ. ሁለተኛው ዙሪያን አይቶ መፍራት ነው። ይህኛው ከጊዜ ጋር ሳይሆን ከቦታና ከሁኔታ ጋር የተያያዘ ነው። ነገን ብቻ ሳይሆን ዛሬም ዙሪያ ገባን አይቶ መፍራት ያሸመደምዳል። ኮቪድ እንደታወቀና እንደጀመረ ሰው ሲጨነቅ ማየት ራሱ ያስጨንቅ ነበር። ቀደም ሲል ፍርሃትን መፍራት ወይም ፍርሃትን ያስፈራል ያልኩት ያንን ነው። ኮቪድ እንደጀመረና የወሸባ (ኳራንቲን) አዋጅ እንደታወጀ፥ ምግብና የጽዳት ዕቃዎች ለመግዛት የሚራኮተው ሕዝብ፥ በጥቂት ቀናት ባዶ የሆኑ መደብሮች መደርደሪያዎች፥ ሰው ሰውን ከሩቅ ሲያይ መንገድ ሲለቅቅ፥ ሰው ሌላውን ሰው ሳይሆን ጥላውን እንኳ ሲፈራ፤ መተቃቀፍና መጨባበጥ ሲያሳቅቅ፥ ቀድሞ ሳንባ ሙሉ ሙሉ አየር ሲስብ የኖረው ሰው አየር መሳብ ሲፈራ፥ ቲቪ ሲከፈት ዜናው ሲያስፈራ! ጋዜጣ ማንበብ ሲያስፈራ! ጋዜጣውን መንካትም ሲያስፈራ! ዙሪያ ገባው ፍርሃት ይጭራል። ዙሪያን ማየት ያስፈራል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ የፈሩ ሰዎች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ደስ የሚለው ነገሩ፥ የሰውን ድካም ሳይሸፍን መግለጡ ነው። ለካስ ይህ ፍርሃት የማያውቅ የመሰለው

እገሌም ፈርቶ ነበር? እንድንል የሚያደርጉን ታሪኮች በብዛት ተጽፈውልናል። ባይሆንማ ኖሮ በፈሪነታችን ራሳችንን ኮንነን በተጎሳቆልን ነበር። ዙሪያቸውን አይተው የፈሩ በጣም ብዙ ቢሆኑም፥ ሁለት ሰዎችን ብቻ እንደ ምሳሌ እንይ።

ኤልያስ፤

1ነገ. 19፥3 *ኤልያስም ፈርቶ ተነሣ፥ ነፍሱንም ሊያድን ሄደ፥ በይሁዳም ወዳለው ወደ ቤርሳቤህ መጥቶ ብላቴናውን በዚያ ተወ።*

ኤልያስ! ይህ ጀግና፥ ይህ ኃያል ሰው፥ በአምላኩ ፊት የቆመ ስለሆነ በንጉሥ ፊት መቆም ያልፈራ ሰው፥ እሳት ከሰማይ እንዲወርድ ምክንያት የሆነ ሰው፤ የበኣልንና ማምለኪያ አፀድ ጣዖት ካህናትን በቂሶን ያሳረደ ሰው፥ አሁን የንጉሡ ሚስት በሆነች አንዲት ጣዖት አምላኪ፥ ኤልዛቤል በምትባል አንዲት ሴት ዛቻ ምክንያት ፈርቶ ተነሣ።

ፍርሃቱ ደግሞ ተራ ፍርሃት አልነበረም፤ አንዳንድ ፍርሃቶች ሞትን ይጣራሉ። የኤልያስ ፍርሃት እንዲህ ያለው ፍርሃት ነው። ኤልያስ ሞትን እስኪመኝ ድረስ ፍርሃቱ ጠንካራ ነበር። ፍርሃት ብቻ ሳይሆን ድባቴ ወይም depression የተቀላቀለበት ፍርሃት ነው። ራስን ለማጥፋት የሚያስኬድ ፍርሃት። ነገር ግን ያንን ፍርሃቱን የሚያስወግድ ፈውስን ጌታ አደረገለት። መልአክ ልኮ አበላው፤ አጠጣው፤ ተናገረው፤ አበረታው፤ አደሰው፤ እንደገና ላከው። ፈርቶ የተነሣው ሰው ደፍሮ፥ ሊሞት የተመኘው ሰው ሳይሞት ወደመጣበት ተመለሰ። ሞትን የተመኘው ድባቴያም ሰው ሞትን ሳያየት ተወሰደ። እስከዛሬም አልሞተም።

ጴጥሮስ፤

ዙሪያን አይቶ የፈራ ሌላ ሰው ጴጥሮስ ነበር። የነፋሱን ኃይል አይቶ፤ ጴጥሮስ ፈርቶ ነበር፤ ታሪኩ በማቴ 14፥22-34 ይገኛል።

22 *ወዲያውም ሕዝቡን ሲያሰናብት ሳለ፥ ደቀ መዛሙርቱ በታንኳይቱ ገብተው ወደ ማዶ እንዲቀድሙት ግድ አላቸው።* ታሪኩ ጌታ በ2 ዓሣና በ5 እንጀራ ከ5ሺህ በላይ ሰዎችን ከመገበ በኋላ የሆነ ነው። የግርግር፥ የትርምስ ጊዜ ነው። 12 ሰዎች ወደ 12 ሺህ ሰዎችን ሊመግቡ አጋፋሪ ሲሆኑ አስቡት። ሴቶችና ልጆች አልተቆጠሩምና ከ12

ሺህም ሊበልጡ ይችላሉ። ልክ የሜዳ ገበያ ቀን ዓይነት የሕዝብ ትርምስ ነው። የሆነውን ነገር ለማስተዋል እንኳ የጥሞና ጊዜ አልነበራቸውም። ሕዝቡን አሰናበተ፤ ደቀ መዛሙርቱን፥ ሐዋርያቱን ወደ ማዶ እንዲሄዱ ግድ አላቸው። ቃሉ ሕዝቡን አሰናበታቸው ነው የሚለው። ለቀቃቸው፥ ወደየመጡበት ይሄዱ ዘንድ ፈትቶ ለቀቃቸው። ደቀ መዛሙርቱን ግን አዘዛቸው፤ ግድ አላቸው፤ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ነው የነገራቸው፤ ወደ ማዶ እንዲቀድሙት። ያኛው መለቀቅ ነው፤ ይህኛው ትእዛዝ ነው።

*23 ሕዝቡንም አሰናብቶ ይጸልይ ዘንድ ብቻውን ወደ ተራራ ወጣ። በመሸም ጊዜ ብቻውን በዚያ ነበረ።* ኢየሱስ ሕዝቡን አሰናብቶ፥ ሐዋርያቱን አዝዞ እርሱ ግን ይጸልይ ዘንድ ብቻውን ወደ ተራራ ወጣ። ከዘላለም ጀምሮ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በኅብረት የኖረው ወልድ በሥጋው ወራት፥ ይህንን ኅብረት ለመጠበቅ ከግርግሩ፥ ከትርምሱ ይወጣና ለብቻው ይሆን ነበር። የጌታ የጸሎት ሕይወት ይገርማል! ለጌታ፥ ለጸሎት የተመቸ ስፍራ መኖር የለበትም። እንደዚህ ያለ የተመቸ ስፍራ የሌለበት የጥሞና ጊዜ ወደኛ በግድ እንዲመጣ መጠበቅ የለብንም። ምቹ ጊዜ ሳለ የጸሎት ሕይወታችንን ለማጎልበት መታተር አለብን። ለጌታ ምንም ቦታ፥ ምንም ጊዜ ከጸሎት አላገደውም።

*24 ታንኳይቱም አሁን በባሕር መካከል ሳለች፥ ነፋስ ከወደ ፊት ነበርና በማዕበል ትጨነቅ ነበር።* ኢየሱስ ወደ ማዶ ቅደሙ ካለ ቅደሙ ነው። ወደ ማዶ ሂዱ ካለ ሂዱ ነው። በመንገድ ምንም ይግጠም ምን፥ ሂዱ ወደተባሉበት ወደ መድረሻቸው መጓዝ ግድ ነው። በመካከል በመንገድ ላይ አደናቃፊ ላይኖር ይችላል፤ ሊኖርም ይችላል። ግን ጌታ ካለ መታዘዝ ወደ መድረሻ ለመድረስ መራመድ ነው።

በማቴ. 8 እና ማር 4 ውስጥ ተመሳሳይ ግን ሌላ ታሪክ እናገኛለን። እዚያም ጌታ ወደ ማዶ እንሻገር ብሏቸው እየተሻገሩ ሳሉ ማዕበል ተነሥቶ ታንኳዋ ትናወጥ፥ ውኃም ወደ ውስጧ ይገባ ነበር። ልዩነቱ እዚህኛው ጌታ እንዲቀድሙት የነገራቸው ሲሆን፥ እዚያኛው ግን አብሯቸው ነው የነበረው። እንሻገር ሲላቸው አብሯቸው ነው፤ ሂዱ ሲላቸውም ቃሉን ሰጥቶ ነው። በእውነቱ፥ ልዩነት የለውም። ቃሉ የመገኘቱን ያህል ሥልጣን አለው። በሁለቱም ጉዞዎችም ማዕበል ነበረ። የጌታም፥ የቃሉም መኖር ማዕበሉን አላስቀረም። የጌታ ከኛ ጋር መሆንና የቃሉ ወይም የተስፋው ከኛ ጋር መሆንም ማዕበሉንና ወጀቡን ከጉዞአችን እንዳይኖር አያግደውም። 'በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ' ብሎናል ጌታ። በጌታ መሆናችን በወደቀች ምድር በመኖራችን መከራዋንም ከመሳተፍ አያግደንም።

*25 ከሌሊቱም በአራተኛው ክፍል ኢየሱስ በባሕር ላይ እየሄደ ወደ እነርሱ መጣ።* በአይሁድ አቆጣጠር ቀኑም ሌሊቱም በአራት እኩል ክፍሎች ይከፈላሉ። ከሌሊቱ አራተኛው ክፍል የሌሊቱ የመጨረሻው ክፍል ወይም ከሌሊቱ ከ3-6 ā. m. (በኛ አቆጣጠር ከሌሊቱ 9-12) ያለው ጊዜ ነው። ካሰናበታቸውና እንዲሄዱ ካዘዛቸው በኋላ ለብዙ ሰዓታት፥ 7 ወይ 8 ያህል ሰዓታት እየጸለየ ቆይቷል ማለት ነው። የጌታ የጸሎት ሕይወት አስገራሚ ነው። ስላስገረማቸው ነበር አንዴ፥ 'እንጸልይ ዘንድ አስተምረን' ያሉት።

ኢየሱስ በባህር ላይ እየሄደ ወደ እነርሱ መጣ። ባህር ለጌታ መሄጃ፥ መረማመጃ ነው። ተገቢው አካሄድ በየብስ ላይ መሄድ ነው፤ ግን ጌታ በውኃም፥ በደመናትም ሊሄድ ምን ያግደዋል? ተመሳሳይ ታሪክ በተጻፈበት በማር. 6፥48 *<u>ነፋስ ወደ ፊታቸው ነበረና እየቀዘፉ ሲጨነቁ አይቶ፥</u> ከሌሊቱ በአራተኛው ክፍል በባሕር ላይ እየሄደ ወደ እነርሱ መጣ፤ <u>ሊያልፋቸውም ይወድ ነበር።</u>* የሚል ቃል አለ። ሊያልፋቸው ፈለገ፤ ግን፥ በጭንቀታቸው አብሯቸው መሆንን መረጠ። በመገኘቱ፥ በማንነቱ ማረጋጋትን መረጠ።

*26 ደቀ መዛሙርቱም በባሕር ላይ ሲሄድ ባዩት ጊዜ፦ ምትሐት ነው ብለው ታወኩ በፍርሃትም ጮኹ።* ማርቆስ እንደጻፈው ሊያልፋቸውም ይመኝ ነበር እንዳለው በውኃው ላይ እየተራመደ ቢያልፋቸው ኖሮ የባሰ ነበር የሚታወኩ። አንድ የሆነ ነገር፥ የሆነ ምትሐት የመሰላቸው ነገር እየታያቸው አልፏቸው ሲሄድ ይበልጥ ያስደነግጣል። ልጆች ቢደነግጡ፥ ቢበረግጉ ማረጋጋት ይቻላል። ግን ትልልቅ ሰዎች፥ ሙሉ ሰዎች፥ አዋቂዎች፥ አሥራ ሁለት ሰዎች በአንድ ላይ ባሉበት ጀልባ ውስጥ ሲታወኩና ከዚያ አልፈው በፍርሃት ሲጮኹ ማየትና መስማት በራሱ ያስደነግጣል። ታወኩ በፍርሃትም ጮኹ። ምትሐት ነው ብለው።

*27 ወዲያውም ኢየሱስ ተናገራቸውና፦ አይዞአችሁ፥ እኔ ነኝ፤ አትፍሩ አላቸው።* አትፍሩ። ስለ ፍርሃት ምንነት ስናስብ ፍርሃትን የሚያስወግድ ከሌላ ከምንም ነገር በላይ ፍቱን መፍትሔ የጌታ መገኘት ነው። 'እኔ ነኝ' የሚለው ቃል ነው። 'እኔ ነኝ' የሚለው ቃል ማንነትን የሚያሳይ ነው፤ ድርጊትን ሳይሆን ማንነትን። ድርጊት በማንነት ውስጥ ነው የሚገኘው። ድርጊት የሚደረገው በማንነት አማካይነት ነው። እግዚአብሔር ይምራል ስንል መሐሪ በመሆኑ ነው። መማር ድርጊቱ ሲሆን መሐሪነት ባህርይው ወይም ማንነቱ ነው።

*28 ጴጥሮስም መልሶ፦ ጌታ ሆይ፥ አንተስ ከሆንህ በውኃው ላይ ወደ አንተ እንድመጣ እዘዘኝ አለው።* ለምን እንዳለው አላውቅም። የተለየ ለመሆን? ምናልባት። በፍጥረቱ ችኩል ስለሆነ? ምናልባት። በድንጋጤ የሚለውን ባለማወቅ? ምናልባት። የእምነት

ጉዳይ ይኖርበት ይሆን? ምናልባት። ከሆነ፥ ጌታ ደግሞ እምነትን ማለማመድ ይወድ የል?

*29 እርሱም፦ ና አለው። ጴጥሮስም ከታንኳይቱ ወርዶ ወደ ኢየሱስ ሊደርስ በውኃው ላይ ሄደ።* የጴጥሮስ የውኃ ላይ ጉዞ ትንግርት ነው። ግን በውኃ ላይ እየተራመደ ብዙ አልቆየም።

*30 ነገር ግን የነፋሱን ኃይል አይቶ ፈራ፥ ሊሰጥምም በጀመረ ጊዜ፦ ጌታ ሆይ፥ አድነኝ ብሎ ጮኸ።* ጴጥሮስ ፈራ። ቅድም በጋራ ነበር የፈሩት። አሁን የጴጥሮስ ፍርሃት የግሉ፥ የብቻው ፍርሃት ነው። ይህ ፍርሃት ምንጭ አለው። የትኛውምና ማንኛውም ፍርሃት ሁሌም ምንጭ አለው። አንዳንድ ጊዜ የሌለ ነገርን አስቦ መፍራት ቢኖርም፥ ያ መሳቀቅ ራሱም ምንጭ ነው። ጴጥሮስ ያየው ነገር ያ የፍርሃቱ ምንጭ ነው። የነፋሱን ኃይል አይቶ ነው የፈራው። ሲጀምር ኢየሱስን እያየ መራመድ የጀመረ ይመስላል። የነፋሱ ኃይል ቀድሞም ነበረ። ቀድሞ መራመድ ሲጀምር ያላየውን የነፋሱን ኃይል አሁን ካየ፥ አንድ ነገር ማየት ብቻ ሳይሆን ሌላ ነገር አለማየትም ጀምሯል ማለት ነው። ዓይኑን ከኢየሱስ ላይ አንሥቷል ማለት ነው። እንደ ክርስቲያን ስናስተውለው፥ ፍርሃት ከማየት፥ ዙሪያን ከማየት የሚመጣ ብቻ ሳይሆን፥ ካለማየትም የሚመጣ ነው፤ ጌታን ካለማየት። በተቃራኒው፥ ድፍረትም ደግሞ ከማየት፥ ጌታን ከማየት ነው የሚመጣው።

*31 ወዲያውም ኢየሱስ እጁን ዘርግቶ ያዘውና፦ አንተ እምነት የጎደለህ፥ ስለምን ተጠራጠርህ? አለው።* የፍርሃት ተቃራኒ ወይም የፍርሃት ምንጭ የድፍረት ማጣት ሳይሆን የእምነት መታጣት ነው፤ መጠራጠር ነው፤ አለማመን ነው። አንተ እምነት የጎደለህ አለው እንጂ፥ 'አንተ ድፍረት የጎደለህ፥ ወኔቢስ!' አላለውም። ድፍረት የፍርሃት ጊዜያዊ መፍትሔ ነው። ለክርስቲያን የፍርሃት መፍትሔና መድኃኒቱ ወኔና ድፍረት ሳይሆን እምነት ነው። ማን ከኛ ጋር እንዳለ ወይም ከማን ጋር እንዳለን ማወቅ ነው።

ዳዊት በመዝ. 56፥3 እንዲህ አለ፤ *እኔ ግን ፈራሁ፤ በአንተም ታመንሁ።* ዳዊት ይህን ያለው ፍልስጥኤማውያን በጌት በያዙት ጊዜ ነው። ታሪኩ በ1ሳሙ. 21 (ቁ. 10-15) ይገኛል። ጌት የጎልያድ አገር ነው። ጎልያድን የገደለው ደግሞ ዳዊት ነው። ዳዊት ያኔም ጎልያድን የመታውና የገደለው ኧረ ጎራው፥ አካኪ ዘራፍ! እትትትትትት! ብሎ ሳይሆን በአምላኩ ታምኖ ነው። አሁን በጌት ቢፈራ ሰው የመሆኑ ብቻ ምልክት ነው። በጌት የፈራው ይህ ዳዊት እንደገና እንደ ቀድሞው በአምላኩ ታመነ። መፍራቱን አልደበቀም። መፍራቱን ሳይደብቅ መታመኑንም ገለጠ። እኔ ግን ፈራሁ፤ በአንተም

ደፈርሁ፤ በአንተ ጀገንሁ አላለም። በአንተም ታመንሁ አለ። የፍርሃት ተቃራኒ ድፍረት ሳይሆን እምነት ነው።

*32-34 ወደ ታንኳይቱም በወጡ ጊዜ ነፋሱ ተወ። በታንኳይቱም የነበሩት፡- በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብለው ሰገዱለት። ተሻግረውም ወደ ጌንሴሬጥ ምድር መጡ።* የጌታ መገኘት፥ የጌታ ወደ ታንኳችን መግባት እነዚህን ነገሮች ያስደርጋል። ነፋስን ያስተዋል፤ ዝም ጸጥ ያሰኛል፤ ስግደትና አምልኮን ይፈጥራል። ያሻግራል። በማቴ. 8 እና ማር 4 ውስጥ ሌላ ከዚህ ጋር የሚቀራረብ ታሪክ መኖሩን አይተናል። እዚያ ጌታ፥ 'ወደ ማዶ እንሻገር' ብሏቸው እየሄዱ፥ እየተሻገሩ ሳሉ ማዕበል ተነሥቶ ታንኳዋ ትናወጥ፥ ውኃም ወደ ውስጧ ይገባ እንደነበር ተጽፏል። ልዩነቱ እዚህኛው ጌታ እንዲቀድሙት ነው የነገራቸው፤ እዚያ ግን አብሯቸው ነበር።

እዚያ፥ 'እንሻገር' ብሏቸዋል። እዚህ፥ *በታንኳይቱ ገብተው ወደ ማዶ እንዲቀድሙት ግድ አላቸው።* ቅደሙ ብሎ ቃሉን ሰጥቶም፥ እንሻገር ብሎ ቃሉን ሰጥቶም፥ አብሯቸው ሆኖም ማዕበልና ወጀብ መኖሩ ይደንቃል። በክርስትና ሕይወትም፥ በክርስቲያን ሕይወትም እንዲህ ነው። ከጌታ ጋር ሆነን፥ በፈቃዱ መካከል ሆነን፥ ማዕበልና ወጀብ ሊኖር ይችላል። ኑሮ ራሱ አስፈሪ ሊሆንም ይችላል። በክርስትና ጉዞ፥ በክርስቲያን ኑሮ ውስጥ ውጣ ውረድ ብቻ ሳይሆን አስፈሪ ማዕበልና ወጀብም ሊኖር ይችላል። ቢኖርም፥ ቃሉንና ተስፋውን እናስብ። የእርሱን አብሮን መሆን እናስብ።

እስካሁን የተመለከትነው የኑሮ ፍርሃትን ነው። ነገን ስለመፍራትና ዙሪያን ስለመፍራት ነው ያየነው። ቀጣዩ ደግሞ የኑሮ ሳይሆን የሞት ፍርሃት ነው።

## 2. የሞት ፍርሃት፤

ሞት እንግዳ ነገር ነው። ሰው ሲፈጠር በመጀመሪያ ለሞት አልነበረም የተፈጠረው። ሞት ከዚያ በኋላ የተከሰተ ባዕድ ነገር ነው። ሰው ሞትን መቀበል የማይችለው ወይም የማይፈልገው በፍጥረቱ ውስጥ ያልነበረ እንግዳ በመሆኑ ነው። ሆኖም ከመጀመሪያው ሰው ጀምሮ እስከ መጨረሻው ሰው ድረስ እያንዳንዳችን አንድ ቀን የምንጋፈጠው ጠላት ነው። ሞት ጠላት መሆኑን ጳውሎስ ሲጽፍ፥ *የኋለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው፤* ይለዋል፤ 1ቆሮ. 15፥26። ይህንን ሞት የተባለ ጠላት እንዳንፈራ የሚያደርጉን ጥቂት እውነቶች አሉ።

1. ሞትን ድል የነሣ፥ ከሞት የተነሣ ጌታ አለን።

ሞት የመጨረሻው መድረሻ ሳይሆን ወደ ዘላለማዊው መግቢያ መሆኑ የተረጋገጠው በጌታ ትንሣኤ ነው። ከዚያ በፊት ከሙታን የተነሡ ጥቂት ያልሆኑ ሰዎች ነበሩ። ይሁን እንጂ፥ ከሞት ቢነሡም በትንሣኤ አካል አልተነሡም። የጌታ ትንሣኤ የማዳኑ እርግጠኝነት ብቻ ሳይሆን የትንሣኤ አካል ተጨባጭ ማረጋገጫም ነው።

2. በዚህች ምድር እንግዶችና መጻተኞች መሆናችንን ማወቅ።

ይህንን ካወቅን፤ አገራችን በሰማይ መሆኑን ካልረሳን፥ በምድር እየኖርን ዘላለማዊ ስፍራ እንዳለንና እዚያ እንደምንሄድ ካወቅን እንፈራለን? አንፈራም። ይህ እውቀት ከኖረን፥ እኛ በዚህች ምድር ስንኖር አላፊ መንገደኞች፥ እንግዶችና መጻተኞች መሆናችንን፤ አገራችንና ዘላለማዊ ዜግነታችን በሰማይ መሆኑን፥ ከሞት በኋላ ሕይወት መኖሩንና የት እንደምንሄድ በእርግጥ ከተረዳን፥ ሞት ከዚህ መውጫና ወደዚያኛው መግቢያ በር ብቻ መሆኑን እናውቃለን። ሞት ለክርስቲያን በር ብቻ ነው።

ይህንን ከተረዳን ሞትን አንፈራም። ሞት በሩ መሆኑን እንድናውቅ የቻልነው ደግሞ ሄደን አይተን፥ ወይም መንግሥተ ሰማይ ደርሰን ስለመጣን አይደለም። ወይም ደርሰን መጣን የሚሉትን ሰምተንና ወይም የጻፉትን አንብበን አይደለም። ጌታ ራሱ ከሙታን ስለተነሣ ነው።

3. በዚህ እንግዳ መሆን ብቻ ሳይሆን በዚያኛው በኩል የሚጠብቀን ከተማ እንዳለን ማወቅ።

የት እንደምንሄድ እናውቃለን። እነዚያ የቀደሙት አባቶች ከተማ ይጠብቁ ነበር፤ ዕብ. 11፥10 እና 16 *መሠረት ያላትን፥ እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠብቅ ነበርና። አሁን ግን የሚበልጠውን እርሱም ሰማያዊ አገር ይናፍቃሉ። . . . ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካቸው ተብሎ ሊጠራ በእነርሱ አያፍርም፥ ከተማን አዘጋጅቶላቸዋልና።* ይልና ከዚያ፥ *በዚህ የምትኖር ከተማ የለችንምና፥ ነገር ግን ትመጣ ዘንድ ያላትን እንፈልጋለን።* ይላል፤ ዕብ. 13፥14።

ይህንን ያልተረዳን፥ ከምድር ጋር የተጣበቅን፥ ከሞት ባሻገር ምን እንዳለ የማናውቅ ከሆንን፥ የት እንደምንሄድ ካላወቅን ሞትን በእርግጥ እንፈራለን። ዕብ. 2፥14-15

*እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፥ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፥ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፥ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ፥ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ።* ይላል። በክርስቶስ አርነት ያልወጣ ሰው ሞትን ይፈራል፤ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት የታሰረ ሰው ነው። በጌታ ማመን ደግሞ ከዚህ እስራት መፈታት ነው። ሞት መውጊያው የተወሰደ ጠላት ነው። እኛም ከጳውሎስ ጋር፥ *ሞት ሆይ፥ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ፥ ድል መንሣትህ የት አለ?* ለማለት እንደፍራለን።

4. አብሮን የሚሆን እረኛ እንዳለን ማወቅ።

እግዚአብሔር እረኛው የሆነ ሰው መኖርን ብቻ ሳይሆን መሞትንም አይፈራም። ዳዊት በመዝ. 23፥4 ይህን አለ፤ *በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም።* እስከዚህ እስከ ቁጥር 4 ድረስ ዳዊት፥ 'እግዚአብሔር እርሱ' እያለ በ3ኛ መደብ ነጠላ ነበር የሚናገረው። ቁጥር 4 ላይ ግን፥ 'እግዚአብሔር አንተ' አለ። ከ3ኛ መደብ ወደ 2ኛ መደብ ተሻገረ። ያንን ማድረግ የሚችል አምላኩን፥ እረኛውን ያወቀ ሰው ብቻ ነው። እግዚአብሔርን ያወቀ ሲሞት ወዴት እንደሚሄድ እርግጠኛ ሆኖ ስለሚያውቅ ሞትን አይፈራም።

ሰዎች በጠቅላላው ሞትን የሚፈሩት፥ ከላይ እንዳልኩት፥ ሰው ሲፈጠር ለመኖርና ላለመሞት የተፈጠረ ስለነበር ነው፤ ሞት እንግዳ ስለሆነ ነው። እንግዶችና መጻተኞች መሆናችንን ካወቅን፥ አገራችን በሰማይ መሆኑን ካልረሳን፥ ከምድር ጋር ካልተጣበቅንን፥ የት እንደምንሄድ ካወቅን፥ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፥ ሞትን ድል የነሣ ጌታ ካለን ሞትን እንፈራለን? አንፈራም።

በኮቪድ ይሁን ያለ ኮቪድ፥ በአደጋ ይሁን በሕመም፥ በድንገት ይሁን በዝግመት፥ በወጣትነት ይሁን አርጅተን እንሞታለን። በዚህ ሥጋ ለዘላለም አንኖርም። ሞታችንን የሞተ ጌታን ስለምናውቅ፥ ስንሞት በፍርሃትና በመሳቀቅ መሆን የለበትም።

ኮቪድ አስፈሪ ነገር ነው። በኑሮ አስፈራርቷል፤ በሞትም አስፈራርቷል። ሁለቱም ነገሮች ያስፈራሉ። እኛ ግን ክርስቲያኖች ነን፤ እንዳንጨነቅና እንዳንታወክ የነገረን አባት አለን። ሞቶ የተነሣ ጌታ አለን። ስለዚህ ኑሮም ሞትም ሊያስፈራን አይገባም። ስንኖር የምንኖርለት ጌታ አለን፤ ስንሞትም የምንሞትለት እና ከሞት በኋላም ለዘላለም አብረነው የምንኖረው ጌታ አለን። ለዚህ ነው ጳውሎስ በፊል. 1፥21 እንዲህ ያለው፤

ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ፥ ሞትም ጥቅም ነውና። እኛም ከጳውሎስ ጋር ይህንን እናስተጋባ። ለኛም ሕይወት ክርስቶስ ነው፤ ሞትም ጥቅም ነው።

## ኮቪድ ምንድር ነው?

ኮቪድ መቅሰፍት? ቸነፈር? ወረርሽኝ? ወይስ ሰው ሠራሽ ሴራ? በ2020 መጀመሪያ አካባቢ ኮሮና እየተስፋፋ ሳለ በአንድ ቃለ ምልልስ ላይ የተጠየቅኩት ጥያቄ ነበረ፤ እግዚአብሔር ይህ ሁሉ ሲሆን የት አለ? ጥርጥር ሳይሆን ለሚጠይቁ ሰዎች ምን ትላለህ? የሚል ጥያቄ ነበር።

ይህ ጥያቄ አንድ ከብዙ ዓመታት በፊት ያነበብኩትን ታሪክ ያስታውሰኛል። በ1956 ጁን 30 በፈረንጆች አቆጣጠር የአየር ላይ የአውሮፕላን ግጭት (mid air collision ይሉታል) ተከስቶ በአውሮፕላኖቹ ውስጥ ያሉት በጠቅላላ 128 ሰዎች በሙሉ ሞቱ። አደጋው የተፈጸመው እዚህ እኔ ከምኖርበት 4 ሰዓት ርቀት ላይ የሚገኝ Grand Canyon የሚባል ቦታ ነበር። የነጠላ ቀብር ስነ ሥርዓት ስለማይኖር የጋራ የቀብር ስነ ሥርዓት ብቻ እዚያው አውሮፕላኖቹ በተላተሙበት ሰማይ በታች ያለ ስፍራ ላይ ተደረገ። ያ ሥርዓት እየተደረገ፥ አገልጋዩ ቃል እያካፈለ ሳለ፥ ቤተ ሰቡ ያለቀበት አንድ ሰው፥ ድምጹን ከፍ አድርጎ፥ 'የት ነው የነበረው እግዚአብሔር ልጄ ሲሞት፥ የት ነው ያለው?!' አለ። ሰባኪው ወጣትና ብዙ ልምድ ያልነበረው አገልጋይ ነውና ምን እንደሚል በልቡ እየጸለየ ሰውየው እንዲጮኽ ዝም አለለት። ሰውየውም ድምጹን አሰምቶ፥ 'የት ነበር እግዚአብሔር?! የት ነበር?' ብሎ ጮኸና ተቀመጠ። ከዚያም አገልጋዩ በተረጋጋ ድምጽ፥ 'ወንድሜ፥ እግዚአብሔር ያንተ ልጅ ሲሞት፥ የራሱ ልጅ ሲሞት የነበረበት ስፍራ ላይ፥ እዚያው ነው የነበረው።' አለው።

ዛሬም እግዚአብሔር እዚያው ነው። ዛሬም በዙፋኑ ላይ፥ ዛሬም በተቀደሰ መቅደሱ ነው። ሆኖም፥ ይህ፥ 'የት ነው እግዚአብሔር?' የሚለው ጥያቄ የድፍረት ጥያቄ አይደለም፤ የክሕደት ጥያቄም አይደለም። ግር የመሰኘትና ግራ የመጋባት ጥያቄ ነው። በዘመናት ውስጥ ግራ የተጋቡ፥ ግር የተሰኙ የእግዚአብሔር ሰዎች ኖረው ያውቃሉ። መጥምቁ ዮሐንስ አንዱ ነው። በሉቃ. 7፥19 *የሚመጣው አንተ ነህን ወይስ ሌላውን እንጠብቅ?* ብሎ ወደ ኢየሱስ እንደላከ ተጽፎአል። ይህ ኢየሱስ እኮ አስቀድሞ በዮሐ. 1፥29፥ *እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ።* ሲል የመሰከረለት ነው።ግን ከተከበበት ሁናቴ የተነሣ ሊጠይቅ ተገደደ። ዕንባቆም ሌላው ነው። በዘመኑ ይደረግ የነበረውን ግፍ አየና ጠየቀ፤ ዕን. 1፥1-4። እግዚአብሔር መለሰለት። መልሱ ግን ይብሱን ግራ አጋባው። አሁንም መለሰለት። እዚያ መልስ ውስጥ የመጨረሻው

ጥቅስ እንዲህ ይላል፤ ዕን. 2፥20 *እግዚአብሔር ግን በተቀደሰ መቅደሱ አለ፤ ምድርም ሁሉ በፊቱ ዝም ትበል።* ይላል። ዕንባቆም ይህንን ከሰማ በኋላ አለመካከቱ ተለወጠ። የሙግት፥ የክርክር፥ የንትርክ ሰው የነበረው አሁን የጸሎት መዝሙር ዘማሪ ሆነ። ምንም እንኳ . . . አለ፤ ምንም እንኳ ይህ ቢሆን፥ እኔ ግን . . . አለ፤ 3፥17-18።

ቀደም ሲል ከኢየሱስና ሐዋርያቱ ታሪክ እንዳየነው፥ ማዕበሉ ይናወጣል፤ ጌታ ግን በታንኳዋ አለ። ቃሉን ሰጥቶ አዝዞ ልኮአቸዋል፤ ነፋስ ግን ከወደፊት ሆኖ ይጋፋል። የጌታ መኖሩ ወይም የቃሉ መስጠት ማዕበሉን አልከለከለም፤ ዛሬም አይከለክልም። እኛን ግን ያረጋጋናል፤ ያሳርፈናል። በወደቀች ምድር፥ በተረገመች ዓለም ነው ያለነው። ፍጥረትም ተፈጥሮም በሚቃትትበት፥ በሚያቃስትበት ዓለም ነው የምንኖረው። ጌታ ከመምጣቱ በፊት ባሉት ዘመናት ደግሞ ነገሮች ይብሱን እየጨመሩ፥ እየከፉ፥ እየተበላሹ፥ እየረበሹ እንደሚሄዱ ነው በቃሉ የተነገረን። መቅሰፍቶችና ቸነፈሮች ይሆናሉ። ከኮሮና ቫይረሶች አንዱ የሆነው ኮቪድ-19 ከወረርሽኞቹ አንዱ ነው። ሌሎችም ይመጣሉ፤ ወደ ፊት ሌሎች አስደንጋጭ ነገሮች ይመጣሉ። ሌላም የሚመጣ አለ፤ አንድ ቀን ጌታ ይመጣል፤ ጽድቅ እንደ ጅረት ይፈስሳል። ከጌታ ጋር ለዘላለም እንኖራለን። ይህ ተስፋ ካለን ከመከራውና ከወረርሽኙ ባሻገር አቅንተን ማየት ይቻለናል። ማየት ያለብንን ካላየን እንፈራለን፤ ዙሪያችንን እንፈራለን፤ ኑሮን እንፈራለን፤ ሞትን እንፈራለን።

ይህ ወረርሽኝ ያልፋል። ምንም እንኳ ይህ መከራ ካለፈ በኋላ ነገሮችም፥ እኛም የተለወጥን ሰዎች መሆናችን እርግጥ ቢሆንም፥ እኛና ሁኔታዎች እንለወጣለን እንጂ እግዚአብሔር ግን ጥንትም፥ ዛሬም፥ ወደፊትም፥ አልተለወጠም፤ አይለወጥምም። ለዘላለምም በስፍራው፥ በዙፋኑ አለ። ወደ ኮቪድ ስንመለስ፥ ኮቪድ መቅሰፍት ነው? ቸነፈር ነው? ወረርሽኝ ነው? ወይስ ሰው ሠራሽ ሴራ? በሚለው አሳብ ላይ ላተኩር። ሁሉንም ቃላት በመተርጎም ልጀምር።

ቸነፈር

ቸነፈር ማለት በአጭር ጊዜ በፍጥነት የሚፈጅ፥ የሚያጠፋ ጥፋት ነው። ዳዊት አንዴ እግዚአብሔርን በበደለ ጊዜ፥ በነቢዩ በጋድ በኩል ሦስት ቅጣቶች ቀርበውለት አንዱን እንዲመርጥ ተልኮበት ነበር፤ *ጋድም ወደ ዳዊት መጥቶ፦ የሦስት ዓመት ራብ በአገርህ ላይ ይምጣብህን? ወይስ ጠላቶችህ እያሳደዱህ ሦስት ወር ከእነርሱ ትሸሽን? ወይስ የሦስት ቀን ቸነፈር በአገርህ ላይ ይሁን? አሁንም ለላከኝ ምን መልስ እንደምሰጥ አስብና መርምር ብሎ ነገረው።* 2ሳሙ. 24፥13። የሦስት ቀን ቸነፈር ከሦስቱ አንዱ

ነው። ቸነፈር ቅጣት ነው፤ ውድመት ነው። ታሪኩን በስፍራው ስናነበው በ3ቱ ቀን ቸነፈር አንድ መልአክ ተልኮ ሰይፉን መዘዘ ሰባ ሺህ ሰዎች ሞቱ። እንዴት እንደሞቱ ወይም እንደተፈጁ ዝርዝር አልተጻፈልንም። ብቻ አለቁ። ዳዊት ንስሐ ገባ፤ መቅሰፍቱም ተከለከለ።

## መቅሰፍት

መቅሰፍት ማለት የኃጢአት መዘዝ የሆነ፥ የመለኮታዊ ቁጣ ምላሽ የሆነ ቀሳፊ ቅጣት ነው። መቅሰፍት እንደ ቸነፈር ሁሉ ቅጣት ነው። በአካል ላይ የሚገለጥ፥ የሚከሰት፥ የሚያሰቃይም ቅጣት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናያቸው ስለ ሰዎች ኃጢአት ቅጣት የተላኩና ወደፊትም ገና የሚመጡ የተለያዩ መቅሰፍቶች ተጠቅሰዋል። ለምሳሌ፥ በግብጽ የወረዱ መቅሰፍቶች ነበሩ፤ በሰዶምና ገሞራ የወረዱ ቅጣቶች ነበሩ። መቅሰፍቶች መጠነ ሰፊ ሊሆኑም ላይሆኑም ይችላሉ፤ ግን ለይተው የሚያጠቁ ናቸው። አንዳንድ መቅሰፍቶች እንደ ስማቸው ቀሳፊዎች ናቸው።

እንደ ኤድስ ያሉት ነገሮች በሽታ ወይም ሕመም ብቻ አይደሉም። በሽታ ናቸው፤ ግን፥ ከውስጥ ስለማይወጡና ስለማይጠፉ ከበሽታ በላይ ናቸው፤ መቅሰፍት እንዳይባሉ ተጠራርገው የሚጠፉ፥ ወይም በፍጥነት ጠራርገው የሚያጠፉ አይደሉም። ከባህርይ እና ከድርጊት ጋር የተያያዙም ናቸውና ቀሳፊ የሚባሉት ለዚህ ነው። እንደ አተረጓጎማቸውና መረዳታቸው ኮቪድ-19ን መቅሰፍት ነው፤ ቸነፈር ነው የሚሉ ይኖራሉ።

## ወረርሽኝ

ወረርሽኝ እንደ ስሙ የሚወርር በሽታ ነው። ወራሪ ነው፤ አጥቂ ነው፤ አንዳንዱ ይተርፉሉ፤ አንዳንዱ ይሞታሉ። አንዳንድ ወረርሽኞች ሰፊ፥ አንዳንዶች ጠባብ ናቸው፤ ሰፊዎቹ pandemic እና ጠባቦቹ endemic ይባላሉ። ወረርሽኞች በተፈጥሮ ምክንያት፥ በተለያዩ የጤና ጉድለቶች፥ በአካባቢ ብክለት፥ አንዳንዴም በሰው ሠራሽ ምክንያቶች ሊመጡ ይችላሉ። ፈጥነው ሊጠፉ፥ ብዙ ሊቆዩ፥ ጭራሽ ላይጠፉም ይችላሉ።

ሰው ሠራሽ ሴራ

ሰው ሠራሽ ሴራ ወይም የሴራ ንድፈ አሳብ ሌላው ነው። አንዳንድ ሰዎች ኮቪድ-19 ሰው ሠራሽ ነው የሚሉ ይላሉ። ይህ ጉዳይ ከራሳቸው ከአድራጊዎቹ፥ ከሠሪዎቹ ካልተረጋገጠ ይህንን እርግጠኛ ሆነን፥ 'ነው' ማለት አይቻልም። የሴራ ንድፈ አሳብ በሌሎች ሲነገር ግምት ብቻ ነው። ሆኖም አንድ ንድፈ አሳብ መሆኑን ማየት ተገቢ ነው። 'የሴራ ንድፈ አሳብ ብሎ ነገር የለም' የሚሉ አሉ። እኔ እንደዚህ ከሚሉት አይደለሁም። ሊኖር ይችላል እላለሁ። የለም ከሚሉት ባልሆንም በሴራ ንድፈ አሳብ ግን አልታወክም፤ አልጨነቅም። ለምን? ከማንም እና ከምንም በላይ የሆነ፥ ከሴረኞችም የሴራ አሳብ እና ከሽረባቸውም ሽረባ በላይ የሆነ አምላክ ስላለ እና ስላለ ብቻ ሳይሆን፥ ይህ አምላክ ለኔ ለግሌ የሚያስብልኝ እና የሚወደኝ አምላክና አባት እግዚአብሔር መሆኑን ስለማምንም ነው የማልጨነቀው። በክርስቶስ የምናምን ሰዎች በግል የሚያስብልን አምላክ፥ እረኛ፥ ጠባቂ፥ አባት ያለን መሆናችንን ቃሉ ስለሚያስተምረን መደንገጥና መርረበሽ የለብንም። ስንኖር የእርሱ ነን፤ ብንሞትም ወደ እርሱ የምንሄድ የዘላለም ባለ ቃል ኪዳኖች ነን።

የሴራ ንድፈ አሳብ ስል አሳቤን ላብራራው፤ ሴራ ማለት በስውር፥ በድብቅ፥ በምስጢር መዶለትና ማቀድ ነው። በምስጢር የሚያዘው ጉዳዩ በሌሎች ላይ ጉዳት፥ ለሴረኞቹ ደግሞ ጥቅም ስላለበት ነው። ጉዳቱ ከአንድና ጥቂቶች እስከ ብዙኃን ሆኖ ጥቅሙ ደግሞ ለሴረኞቹና ለተባባሪዎቻቸው ብቻ ይሆናል። ሴራ ግቡ ከመግዛት፥ ከመጨቆን እስከ መፍጀት ሊደርስ ይችላል። ድብቅ ነው፤ ምስጢር አለበት፤ ጥቂት ጥቅምና ብዙ ጉዳትም አለበት። ወይም ጥቂት ተጠቃሚዎችና ብዙ ተጎጂዎች አሉበት። ግልጽና ሕጋዊ አይደለምና ሕዝባዊ ተቀባይነት የለውም። ስለዚህም አሳታፊ አይደለም። ተሳታፊ ላልሆኑት ግምት ብቻ የሚሆነውም ስለዚህ ነው።

በታሪክ ውስጥ ከቀላል የመንግሥት ግልበጣና ሥልጣን መንጠቅ እስከ ትልልቅ አብዮቶች ድረስ ተፈጽመው ይታወቃሉ። ትልልቅ የተቃውሞ ሰልፎች በመንገድና በአደባባይ ከመደረጋቸው በፊት የተደረጉ ምስጢራዊ ስብሰባዎችና የተጠነሰሱ ሴራዎች አሉ። አንዳንዶቹ ይደረስባቸውና ይከስማሉ፤ ከሸፉ ይባላል። ክሽፈት ሲኖር ጥይቱ ተተኩሷል፤ ግን ወይ በጥይቱ፥ ወይም በጠመንጃው ሥሪት ብልሽት ስላለበት ቃታው ቢሳብና ቢተኮስም ድምጹም የለም፤ ጉዳትም አልደረሰም። ወይም እንደ መከነ ፈንጂ ነው። የተቀበረበት ወይ የተደበቀበት ቦታ ታውቆ፥ ተደርሶበት ሳይፈነዳና የታሰበውን ጉዳት ሳያደርስ ሲመክን ነው። ይህንን ለሴራ ክሽፈት ማሳያ ምሳሌ አነሣሁት እንጂ የሴራ ምንጩ ጥቂት ልሂቃን፥ ዒላማው ደግሞ አላዋቂ ሕዝብ ነው። ሴራ ይህ ሲሆን የሴራ ንድፈ አሳብ ደግሞ፥ 'ለአንድ የሆነ፥ ወይም የሚሆን ጉዳይ፥

ሁኔታ፥ ክስተት፥ ምሥጢራዊ የሆነ ግን ትልቅ ተጽዕኖ አድራጊና ያንን ክስተት ጀማሪ ወይም አስጀማሪ አካል አለ፤' የማለት አሳብን መቀበል ነው።

ታሪክ እንዲህ ስላሉ ሴራዎች ብዙ የሚለን አለ። ወደዚያ ዝርዝር ውስጥ አልገባም። የታሪክ ሊቃውንት ቢሉት ያምርባቸዋል። በቀላሉ ግን፥ ከአገራችን ከመቶ ዓመት ታሪካችን ብቻ ብናይ፥ የ1910ራዎቹን የዐፄ ኃይለ ሥላሴን ወደ ሥልጣን የመምጣት ዳራ ብንፈትሽ፥ ወይም በ5ቱ ዓመታት ወረራ ሙሶሊኒ በሕዝባችን ላይ ያደረገውን ፍጅት ብንመረምር፥ የ1953ቱን ግርግር፥ የ1966ቱን አብዮት እና የደርግን በዝግ ስብሰባዎች ጅማሬና ውሳኔዎች፥ እስከ ደርግ ላይ የተሞከረው መፈንቅል፥ እስከ ወያኔ ንቅናቄና አገዛዝ፥ አሁንም ያለውን ለውጥ ስናይ በተለይ ጅማሬዎቻቸው ላይ ምስጢራዊ፥ ሴራዊ አካሄድ እናገኛለን። ተሳታፊዎቹ ሲናገሩትና፥ ሲጽፉት ይህ በሌላው ያልታየ ነገር ይታያል።

ሴራ ጉዳትም ጥቅምም ያለበት ሆኖ፥ ጥቅሙ ለሴረኞቹና ለተባባሪዎቻቸው፥ ወይም ለአንድ ወገን ብቻ ሆኖ፥ ግቡ ብዙኃኑን ከመግዛት እስከ መፍጀት ሊደርስ ይችላል ብያለሁ። አንዳንዱ ለሰፊው ሕዝብ ይባልና፥ አብዮት ይፈነዳና ግርግሩ ሲጠራ፥ ሰፊው ሕዝብ በጠባቡ ሕዝብ ይለወጣል፤ ወደ ጎሳና ወደ ቡድንም ያልፋል። ብዙኃን ብዙኃን ይባልና፥ ሰፊው ሕዝ ሰፊው ሕዝብ ይባልና እንዲያውም ብዙኃኑን ወደ መፍጀትም ይለወጣል። ወደ ሥልጣን ስግብግብነት እና አምባ ገነንነትም ይሻገራል። ሴራ በተንኮልና በውሸት የተሸረበ ገመድ ነው።

## የሴራ ምሳሌዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ

እኔ ታሪክን ብወድድም የታሪክ ሊቅ አይደለሁም። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ተማሪና አስተማሪ ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቂት የሴራን ምንነት የሚያሳዩ አንድ ሁለት ምሳሌዎች ላንሣ። በዘፍ. 34 የተጻፈው አንድ ምሳሌ ነው። ያዕቆብ ኋላ እስራኤል የተባለው እና የ12 ወንዶች ልጆች አባት ነው። 12ቱ ኋላ የእስራኤል ነገዶች የሆኑት ናቸው። በዚህ በዘፍ. 34 ታሪክ ጊዜ 12ቱም ገና ልጆችና ወጣቶች ናቸው። አንዳንዶቹ በ20ዎቹ ዕድሜ የሆኑና ያገቡ ሳይሆኑ አይቀሩም። ልጆቹ ያዕቆብ ለአጎቱ በተገዛባቸው 20 ዓመታት ጊዜ ውስጥ የተወለዱ ናቸው። የመጨረሻው ልጅ እንዲያውም ወደ ከነዓን በተመለሱበት ጉዞ በመንገድ ላይ ነው የተወለደው። ያዕቆብ የሁለት ወንዞች መካከል ከሚባለው አገር ከመስጴጦምያ ወደ ተወለደበት አገር ተመልሶ መጣ። ወደ ሴኬም ከተማ በደህና መጥቶ መኖር ጀመረ። እንደ መጣ ድንኳኑን ተክሎበት የነበረውን ስፍራና እርሻውን ከሴኬም አባት ከኤሞር ገዛውና የራሱ አደረገው። አገሩ

ወይም ከተማው የተሰየመው በሴኬም በራሱ ነው። የአመጣጡን ሁኔታ በዘፍ. 31-33 ባሉት ምዕራፎች እናገኛለን። ይህኛው ታሪክ የተጻፈው ደግሞ በዘፍ. 34 ነውና ከተመለሰ ብዙ አልቆየም።

ያዕቆብ አንዲት ሴት ልጅ ነበረችው፤ ዲና የምትባል። የአገሩን ሴቶች ልጆች ለማየት በወጣችበት ሴኬም አያት፤ ሴኬም የአገሩ አለቃ ነው። ወሰዳት፤ አስነወራት፤ ተኛት፤ ወደዳት፤ በፍቅሯ ተነደፈ። ቅደም ተከተሉ የተዛነፈ ይመስላል፤ ተዛንፏልም። ሆኖም ተጠልፋ በሴኬም ቤት ሳለች ጉዳዩ ወደ ጋብቻ መስመር እንዲያመራ በሽምግልና ተያዘ። ይህ እንደተሰማ የያዕቆብ ልጆች ከብቶቻቸውን ከሚጠብቁበት ከምድረ በዳ መጡ። ተወያዩ፤ አሴሩ፤ ዘፍ. 34፥13 *የያዕቆብም ልጆች ለሴኬምና ለአባቱ ለኤሞር በተንኰል መለሱ፥* ይላል። ተንኮሉ ሴራው ነው። መልሳቸው፥ ከቁ. 14-17 ይገኛል፤ *እንዲህም አሉአቸው፡- እኅታችንን ላልተገረዘ ሰው ለመስጠት ይህንን ነገር እናደርግ ዘንድ አይቻለንም፤ ይህ ነውር ይሆንብናልና። እንደ እኛ ሆናችሁ ወንዶቻችሁን ሁሉ ብትገርዙ በዚህ ብቻ እሺ እንላችኋለን፤ ሴቶች ልጆቻችንን እንሰጣችኋለን፥ የእናንተንም ሴቶች ልጆች እንወስዳለን፤ አንድ ሕዝብም ሆነን ከእናንተ ጋር እንኖራለን። ትገረዙ ዘንድ እኛን ባትሰሙ ግን ልጃችንን ይዘን እንሄዳለን።*

የሴኬም አባት ኤሞር ሕዝቡን ለመናቸው፤ አሳመናቸው፤ ልጃቸውን ይዘው ከሚሄዱብን እባካችሁ ሁላችንም እንገረዝ አሉ፤ እሺ ብለው የከተማዋ ወንዶች በሙሉ ተገረዙ። በተገረዙ በ3ኛው ቀን የተገረዙት ገና እርጥብ ቁስል ላይ እያሉ ከያዕቆብ ልጆች ሁለቱ ስምዖንና ሌዊ ሳይፈሩ ሰይፋቸውን ይዘው ወደ ከተማዋ ገብተው ወንዶቹን ሁሉ ፈጁ፤ ንብረታቸውን ዘረፉ፥ ከብቶቻቸውን ወሰዱ፥ ሴቶቹንና ልጆቻቸውን ማረኩ። ተንኮሉ ምንድር ነው? ሴራው ነው። እንዲገረዙ እንጠይቃቸው ብቻ ሳይሆን ከዚያ ቆስለው ሳሉ እንፍጃቸው ነው። እነዚህ ዶልተዋል፤ አሲረዋል፤ እነዚያ አያውቁም። ፈጇቸው።

ሴራ ሳይታወቅም፥ በማን አለብኝነትም የሚደረግ የጥፋት፥ የፍጅት ዕቅድ ነው። አንዳንዴ ስልታዊ የሆነ የዘር ማጥፋትም ነው። እነዚሁ ያዕቆብና የያዕቆብ ልጆች ከዓመታት በኋላ ወደ ግብጽ ሄደው መኖሪያቸው በዚያ ሆኖ ከ400 ዓመት በላይ ኖረዋል። በመጀመሪያ እንደ ክቡራን እንግዶች ሆነው ሲኖሩ በመጨረሻዎቹ ዓመታት ግን ጭቆና በዛባቸው። በተለይ ቁጥራቸው ስለበዛ ፈርዖን አሴረ፤ ታሪኩ በዘጸ. 1፥15-16 እንዲህ ይላል፤ *የግብፅም ንጉሥ አንዲቱ ሲፓራ ሁለተኛይቱም ፋሐ የሚባሉትን የዕብራውያንን አዋላጆች እንዲህ ብሎ ተናገረ። እናንተ የዕብራውያንን ሴቶች ስታዋልዱ፥ ለመውለድ እንደደረሱ ባያችሁ ጊዜ፥ ወንድ ቢሆን ግደሉት ሴት ብትሆን ግን በሕይወት ትኑር።* ይህ ሌላ የሴራ ታሪክ ነው። ሴቶቹ በእርግጥ የተባሉትን አላደረጉም፤ ግን የወንድ ልጅ ግድያው የታወቀ፥ የታወጀ ጉዳይ ነው። ለዚህ ነበር

የሙሴ እናት ሙሴን በቅርጫት አድርጋ በዓባይ ወንዝ የሰደደችው። ፈርዖንና አዋላጆቹ ያውቃሉ፤ ኋላ ጉዳዩም ለዕብራውያንም የታወቀ ሆኗል። ግን ሴራ ነው፤ ስልታዊ ዘረ ፈጅነት ነው።

አንዳንዴ የሚፈጁት ሕዝብ አናሳ ከሆነ ድብቅና ምስጢር ሳይደረግ በማስፈራራትና በማስደንገጥ፥ በማሳቀቅና በማስጨነቅ፥ ሕዝቡን ለመፍጀትና ለሌላው መቀጣጫ ለማድረግ፥ ሌላው ፈርቶ እንዲገዝዛ ለማድረግ የሚፈጸም ፍጅትም አለ። በግብጽ ግብጻውያን አይሁድን በግልጽ፥ በገሃድ በግፍ የገዙበት ጽኑ ማስጨነቅ ከዚህ የሚቀራረብ ነው።

አንድ የመጨረሻ የሴራ ታሪክ ልጨምር። አይሁድ ተማርከው በባቢሎን በነበሩበት ጊዜ ሁሉንም እንደ አንድ ሕዝብ ለማጥፋት የተደረገ ሴራ ነበረ። ጠቅላላው መጽሐፈ አስቴር የዚህ ጥፋት ሴራና የመታደግ ታሪክ ነው።

አይሁድ ተማርከው በምርኮ ምድር በባቢሎንና በምድርም ሁሉ ተበትነው በነበሩበት ዘመን ሐማ የተባለው የአይሁድ ጠላት በአይሁድ ላይ ያደረገው ሴራ ነበረ። ይህም ሴራ ተንኮል ተብሏል። አስ. 8፥3-5 እንዲህ ይላል፤ *አስቴርም እንደ ገና በንጉሡ ፊት ተናገረች በእግሩም ላይ ወድቃ እያለቀሰች የአጋጋዊውን የሐማን ክፋትና በአይሁድ ላይ የተተነኰለውን ተንኰል ይሽር ዘንድ ለመነችው። ንጉሡም የወርቁን ዘንግ ለአስቴር ዘረጋላት፤ አስቴርም ተነሥታ በንጉሡ ፊት ቆመችና፡- ንጉሡን ደስ ቢያሰኘው፥ በፊቱም ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ፥ ይህም ነገር በፊቱ ቅን ቢሆን፥ እኔም በእርሱ ዘንድ ተወድጄ እንደ ሆነ፥ አጋጋዊው የሐመዳቱ ልጅ ሐማ በንጉሡ አገር ሁሉ ያሉትን አይሁድ ለማጥፋት የጻፈው ተንኰል ይገለበጥ ዘንድ ይጻፍ። እኔ በሕዝቤ ላይ የሚወርደውን ክፉ ነገር አይ ዘንድ እንዴት እችላለሁ? ወይስ የዘመዶቼን ጥፋት አይ ዘንድ እንዴት እችላለሁ? አለች።* ይላል። ተንኮል ተደርጓል፤ ሴራ ተሲሯል፤ አንድ ሕዝብ፤ አስቴር የዚያ ወገን የሆነችበት የአይሁድ ሕዝብ፥ እንዲጠፉ ተወስኗል። *አሥራ ሁለተኛው ወር፥ አሥራ ሦስተኛው ቀን* ተብሎ ቀን ተቀጥሯል። ድንገት ቢሆን አንድ ነገር ነው፤ ቀን ተቀጥሮ በዚህ ቀን ይህ ሕዝብ ይፈጅ ተብሎ፥ ሕዝቡም ምንም ማድረግ ስለማይችል የተቀጠረለትን የፍርድ ቀን በፍርሃትና በሰቀቀን ሲጠብቅ ስቃይ ነው። እግዚአብሔር በሚገርም መንገድ ታሪኩን ገለበጠው። ሌሎችም የሴራ ታሪኮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ፤ ግን ይህኛው ውብ የሆነውና እግዚአብሔር የታየበት ስለሆነ ሌላ ሳልጨምር ከመጽሐፍ ቅዱስ የምወስደውን ታሪክ በዚህኛው ላብቃ።

ሰዎች ያቅዳሉ፥ ያሴራሉ፤ ራሳቸውን በእግዚአብሔር ስፍራም ያስቀምጣሉ። ፍርድን በእጃቸው ይወስዳሉ፤ እግዚአብሔር ግን በተቀደሰ ዙፋኑ አለ። ይህንን አንድና ትልቅ

እውነት እንዳንረሳ፤ እግዚአብሔር ግን በዙፋኑ፥ በተቀደሰ ዙፋኑ አለ። ሴረኞች ቢኖሩም እግዚአብሔር ግን አይሴርበትም። ይህ የሚያሳርፈን እውነት ነው።

ብዙ ነገሮችን አናውቅም። ስንት ዓመት እንደምንኖር ወይም መቼ እንደምንሞት አናውቅም። ጌታን ያመንን ሰዎች ግን ስንሞት ወዴት እንደምንሄድ እርግጠኞች ነን። ነገ ምን ይዞ እንደሚመጣ አናውቅም። ነገ ላይ ቀድሞ የሚጠብቀን ጌታ እንዳለን ግን እናውቃለን። ነገን ራሱን በእጁ የያዘ ጌታ ጌታችን መሆኑን እናውቃለን። አሁን በዚህች ሰዓት ስንት የሰውና የአጋንንት ፍላጻ እየተወረወረብንና እየተወነጨፈብን እንደሆነ አናውቅም። በእረኛችን ጥበቃ ውስጥ እንዳለን ግን እርግጠኞች ሆነን እናውቃለን። እርሱ ያልፈቀደውና የማያውቀው ነገር አይነካንም። ስንት የሴራ ፖለቲካ፥ የሴራ ምጣኔ ሀብት፥ የሴራ ምጣኔ ሕዝብ ተነድፏል። መንግሥታት ያሴራሉ፤ ትልልቅ ኮርፖሬሽኖች ያሴራሉ፤ ትልልቅ ባለ ሀብቶች ያሴራሉ፤ የሴራ ንድፈ አሳብ አለ። ኮቪድ-19 ሰው ሠራሽ የሰው ዘር መቀነሻ ነው ብለው የሚከራከሩና ብዙ ማስረጃ የሚያቀርቡ ግለ ሰቦችና ቡድኖች አሉ። ነው ብሎ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፤ ከውስጡ የወጡ ሰዎች ካልገለጡት በቀር። አይደለም ብሎ መከራከርም አይቻልም። ሊሆንም ይችላልና። ከሆነ ሰዎች የጥቂቶች መጫወቻ መሆናቸው ይረብሻል። ጥቂቶች እንደ ሰው ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር እግዚአብሔር እየተጫወቱ መሆኑ ያስደነግጣል።

የሴራ ጉዳይ ቢኖርም ግን፥ እግዚአብሔር ከዘላለማዊ ዕቅዱ ጋር በክብሩ ዙፋን አለ። ጌታ ሁሉን ያውቃል፤ ሁሉን ያያል፤ ሁሉን ይቆጣጠራል። የተንኮለኞችን አሳብ ከንቱ እንደሆነ ያውቃል፤ ከንቱም ያደርጋል፤ ጠቢባንን በተንኮላቸው ይይዛቸዋል፤ ኢዮ. 5፥ 12-13። ይህ ቃል በአዲስ ኪዳንም በ1ቆሮ. 3፥19-20 ተደግሞአል። የሚሆኑ ነገሮችን ማወቅ ብቻ ሳይሆን፥ ማየት ብቻ ሳይሆን፥ ከዚያም በላይ የመፍቀድም፥ የመቆጣጠርም፥ የማገድም ሥልጣን የእርሱ ብቻ ነው። ሰዎች ምንም ያሲሩ የማወቅና የመመርመር እርምጃ መስወድ የኛም ኃላፊነት መሆኑ ሳይጠፋን፥ እንደ ክርስቲያን፥ እኛ ግን መጠለያ ጥላና ሮጦ ማምለጫ ዓለት እንዳለን መርሳት የለብንም።

## ዓለም አቀፍ ቤተ ሙከራ፥ ቁጥጥር፥ እና ክትባት

ኮሮና ቸነፈር ነው? ወይስ መቅሰፍት? ወይስ ወረርሽኝ? ወይስ ሰው ሠራሽ ሴራ? ወይስ ቀውስ? የሚለውን ጥያቄ ተመልክተናል። በተለይም ስለ ጥፋት ሴራ ምንነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በማውሳት አይተናል። ሰው ሠራሽ ቀውሶች የሴራ ንድፈ አሳብ አንድ ክፍል ወይም ገጽታ ናቸው። ድርቅ ወይም ጎርፍ ቢመጣ የወደቀች ዓለም

የተፈጥሮ ክስተት መሆኑ ይገባናል። አንድ ዓይነት ወረርሽኝ ሲመጣ ግን ምንጩ የቅጣት መቅሰፍት ሊሆን ይችላል፤ ወይም የተፈጥሮ ክስተትም ሊሆን ይችላል፤ ወይም ሰዎችም ሊሆኑ ይችላሉ። ኮቪድ ሰው ሠራሽ ቀውስ ይሆን? ሊሆንስ ይችላል?

ሰው ሠራሽ ቀውሶች የቁጥጥር ገጽታዎች ናቸው። 'የዓለም ሕዝብ በዝቷል ባለበት መቆም አለበት፤ እንዲያውም መቀነስ አለበት' የሚሉ ሴረኞች እና ኢኮኖሚስቶች አሉ። የዓለም የምግብ አቅርቦትና የሰው ቁጥር ዕድገት ስለማይመጣጠን በግራፍ ላይ፥ ልክ የአቅርቦቱ መጠንና የሕዝቡ ቁጥር እኩል ከሆነበት (ግራፉ ከሚገናኝበት) ነጥብ ወይም ቅጽበት ጀምሮ የሰው ቁጥር እንዳይጨምር በሆነ መንገድ መቆም አለበት የሚል አሳብ በመጀመሪያ ያቀረበው ቶማስ ማልተስ የተባለው እንግሊዛዊ ኢኮኖሚስት ነው። ከዚያ ወዲህ በምንም በምንም እየተደረገ የሕዝብ ቁጥር እንዳይጨምር ለማድረግና፥ እንዲያውም ለመቀነስ የተለያዩ ነገሮች ይደረጋሉ።

ቶማስ ማልተስ የዓለምን ሕዝብ ቁጥር ባለበት ለማቆም ወይም ለመቀነስ ያቀረበው ሁለት ዘዴዎችን ነው። አንደኛው የመከላከል እርምጃ ወይም preventive checks ይባላል፤ ሁለተኛው የደንብ እርምጃ ወይም positive checks የሚባለው ነው። የመጀመሪያው preventive checks የሚባለው፥ ሰዎች እንዳይወልዱ ማበረታታት፥ እስኪበለጽጉ እንዳይወልዱ መከልከል፥ ለአንዳንድ ሰዎች በሕግ ጋብቻን መከልከል፥ እና የመሳሰሉት ሲገኝበት፥ በሁለተኛው የደንብ እርምጃ ወይም positive checks በሚባለው ደግሞ የሰው ቁጥር ከአቅርቦቱ እኩል ሆኖ ማለፍ ሲጀምር እድገቱን ለማስቆም የተፈጥሮ አደጋ ካልተከሰተ እንደ በሽታ፥ ረሃብ፥ ጦርነት፥ እና መሰል ሰው-ሠራሽ አደጋዎች መፍጠር ነው። ይህ እርምጃ ማልቶሳዊ ቀውስ ወይም Malthusian catastrophe ይባላል። ይህ የማልተስ ኢኮኖሚያዊ ንድፈ አሳብ ብዙና ጠንካራ ተቃውሞ የገጠመው ንድፈ አሳብ ነው። በአንድ ወገን የሰው ዘርን የሚጠላ፥ ጨካኝ፥ ጸለምተኛ ሲባል፥ በአንጻሩ ወገን ደግሞ፥ ዘዴው ይለያይ እንጂ የሰው ዘር ቁጥር እድገት በአንድም ሆነ በሌላ መገታት አለበት የሚሉ ደጋፊዎችም አሉ።

ዛሬም እንዲህ ያለ ንድፈ አሳብ የሚያስተናግዱትና የሚያራምዱት፥ የዓለማችን ከርሰ ምድር ሀብት ውሱን ነው፤ አየራችንም፥ ውኃችንም ውሱን ነው፤ ያልቃል፤ መቆጠብ አለብን፤ የቁጠባው አንድ መንገድ ሰውን መቀነስ ነው የሚሉ ይገኛሉ። 'በተለይ፥ ተፈላጊዎቹ ንጥረ ነገሮች ያሉባቸው አገሮች መታወክ አለባቸው፤ ሰላም መሆን የለባቸውም፤ በአንድ መንገድ ወይ በሌላ፥ በቁጥጥር ስር ሆነው መገኘት አለባቸው' ብለው ያስባሉ። ይህ እንዲሆን የሚፈለገውም ሰዎቹ መቀቀነስ አለባቸው ብሎ በማመን ነው። 'የሰዎቹ ቁጥር በወሊድ ቁጥጥርም፥ በክትባት በማምከንም፥ በሰው ሠራሽ በሽታም፥ በጦርነትም ቁጥራቸው መልለጎም አለበት' ብለው ያስባሉም፤ ያምናሉም። እንዲህ ያለውን ዓይነት ነገር በዓለም አቀፍ መልኩ፥ በክልላዊ ወይም

ቀጣናዊ መልኩ፥ በአንድ አገር ውስጥም አንድ ጎሳ በሌላው ላይ ሲያደርግ ይታያል። በእንደዚህ ያሉት ሰው ሠራሽ ሴራዎች ወይም ቀውሶች ውስጥ ተጠቂዎቹ ብዙኃኑ ሲሆኑ፥ ተጠቃሚዎቹ ጥቂት ልሂቃን ወይም አንዱ ጎሳ፥ ወይም ይህንን ነገር ተቆጣጣሪው መደብ ብቻውን ይሆናል።

ሰው ሠራሽ ቀውሶቹ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሆነ ቅንብሩ ረቂቅ፥ አድማሱና መዳረሻው ሰፊ፥ ውጤቱና መዘዙም ጥልቅና እጅግ ብዙዎችን የሚነካ ሊሆን ይችላል። በላቦራቶሪ ውስጥ ካሉት ነገሮች የሚሠሩና አዳዲስም የሚፈጠሩና የሚሞከሩ ብዙ ዓይነት ገዳይና አውዳሚ ንጥረ ነገሮች አሉ። አንዳንዶቹ እንደ መጠነ ሰፊ አውዳሚ መሣሪያዎች (weapons of mass destruction) ያሉት ተሰናድተው ለጦርነት ቀን ተብለው ይጠበቃሉ። አንዳንዴ በሕዝብ ላይ ይተገበራሉ። ጣሊያን አገራችንን በወረረበት የ2ኛው የዓለም ጦርነት ወቅት፥ የመርዝ ጋዝ ምንም መከላከያ ባልነበረው በኛ ሕዝብ ላይ ረጭቶ ነበር። በጃፓን ሁለት ከተሞች የተጣሉት ሁለት ቦምቦች 140 ሺህ ሰዎችን በቅጽበት ነበር የፈጁት። ሁለት ቦምቦች ብቻ 140 ሺህ ሕዝብ። ባዮሎጂካል መሳሪያዎችን ኢራቅ በኩርዶች ላይ፥ ሶርያ ደግሞ በሶርያ ተቃዋሚዎች ላይ ለፍጅት ተጠቅመዋል።

በዘመናት ውስጥ የዓለም ሕዝብ ቁጥር በጣም እየጨመረ መሆኑ የታወቀ ነው። ገናም ይጨምራል። በመጀመሪያ ሲፈጠሩ እንዲበዙና እንዲባዙ ምድርንም እንዲሞሉ የተሰጠ አምላካዊ ፈቃድ አለና፥ አሁን ካለው ብዙ እጥፍ ቢጨምርም እንኳ ምድራችን ለመሸከምም ለማኖርም አይከብዳትም። ሆኖም ሕዝብ እየበዛ፥ የምግብና አስፈላጊ ግልጋሎቶች አቅርቦት በዚያ መጠን እያደገ አለመሄዱም የታወቀ ነው። ደግሞም የሰዎች ሥራዎች በሮቦቶች እና (AI) አርቲፊሻል ኢንቴሊጀንስ እየተተካ መሄዱም የታወቀ ነው። ስለዚህ ሰው አላስፈላጊና የጥቂቶችን ፍጆታ፥ መብልና መኖሪያ ተሻሚ እየሆነ ወይም ተደርጎ እየታየ እየመጣ ነው ማለት ነው። አንዳንድ ሰዎች በተለይ ከሚለግሱት በረከት ይልቅ የሚፈጁት ፍጆታ ብዙ ስለሆነ የሚኖሩት ላይ ጫና ፈጣሪ ናቸው ይባላል። እናም 'ሰው ይቀነስ' የሚሉ ሰዎችና ድርጅቶች በሰው ዘር ላይ የማጥፋት ጉዳት ሲያስቡና ሲያካሂዱ ከነዚህ አሳቦች በመነሣት ነው። የማልተስ preventive checks እና positive checks የሚሉት የማምከን፥ የመለጎም፥ እና የመቀነስ አካሄድ እንግዲህ ከዚህ አንጻር የሚታይ ነው።

እንዲህ ከሆነ ሰው ሠራሽ ቫይረሶችና ወረርሽኞች ቢፈጠሩ አዲስና እንግዳ ነገር እንደሆነ ማሰብ የለብንም። እነዚህ አውዳሚ መሳሪያዎችና ባዮሎጂያዊና ኬሚካላዊ ንጥረ ነገሮች አንዳንዴ በእውቀት ወይም ሆን ተብለው፥ አንዳንዴም አፈትልከው ይወጣሉ፤ ጥቂቱን ወይም ሰፊውን የዓለም ሕዝብ ሊፈጁም ይችላሉ። ኮሮና ቫይረስ

ወይም ኮቪድ 19 ከተለያዩ ምንጮች የመነጨ ነው በማለት አምስት ምንጮች ይጠቀሳሉ።

- ኮሮና ቫይረስ፥ 'የተፈጥሮ ወረርሽኝ ነው፤ ከሌሊት ወፍ የመነጨና ከዚያ ከወፍ ወደ ሰው ከገባበት ጊዜ ጀምሮ፥ ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው የተላለፈ ወይም የሚተላለፍ ቫይረስ ነው' ይባላል።
- 'ከመቶ ዓመት በፊት በ1918 በዓለም ከናኘውና ወደ 50 ሚሊየን ሰዎችን ከፈጀው ኢንፍሊዌንዛ ተያይዞ የመጣ የH1N1 ዝርያ የሆነ፥ ቅርጹን በፍጥነት እየቀየረ (በሕክምና ቋንቋ mutate እያደረገ) የመጣ የፍሉ ዓይነት ነው' ይባላል።
- ደግሞ፥ 'ከዚያው ከመነጨበት ከውሃን (ቻይና) ቤተ ሙከራ አፈትልኮ የወጣ የተፈጥሮ ቫይረስ ነው። እዚያ የተገኘው የተሠራውም ይሁን የተፈጥሮውም ይሁን ብቻ አፈትልኮ የወጣ ነው ይባላል።
- ደግሞ፥ 'የተፈጥሮው ቫይረስ ሆኖ በዘረ-መል ምህንድስና ሙከራ ላይ ሳለ አፈትልኮ የወጣ ነው' ይባላል።
- የተፈጥሮ ሳይሆን በሰው የተፈጠረ ሰው ሠራሽ ቫይረስ ነውም ይባላል። ወይም ከዚህ በተጓዳኝ፥ 'ሌላ አገር ተመርቶ እዚያ (ቻይና) ተወስዶ እንዲያፈተልክ የተደረገ ወይም ሆን ተብሎ የተለቀቀ ቫይረስ ነው' ይላሉ።

እነዚህ ከላይ ያየናቸው አምስት የምንጭ ንድፈ አሳቦች ናቸው። ሰዎች ይከራከሩባቸዋል፤ አንዱን እውነት እንደሆነም ይቀበላሉ። እዚህ ላይ እያካፈልኩ ያለሁት ስለ ሰውሠራሽ ወረርሽኝ ነውና፥ ሰው ሠራሽ ወረርሽኞች ቢፈጠሩ እንደ አዲስ ወይም እንግዳ ነገር ማሰብ የለብንም ካልን ወረርሽኞቹ አንዳች የሆነ ግብ ያላቸው ሊሆኑ እንደሚችሉ ማሰብም ይቻላል። ግቦቹ ከገበያ እስከ ምጣኔ ሀብት ቀውስና ተቆጣጣሪነት፥ ከአገር የውስጥ ፍንቀላና ስደት ከዚያ እስከ ሰፊ ግሎባዊ ብታኔ፥ ከፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት እስከ ብሔራዊ ቁጥጥር፥ ከሕዝብ ቁጥር መግታት እስከ መቀነስ፥ እስከ ዘር ማጥፋት ድረስም ሊሄድ ይችላል። እነዚህ ሁሉ አካባቢያዊ ወይም አገራዊና አህጉራዊ፥ ወይም ዓለም አቀፋዊ ሊሆኑ ይችላሉ።

ኮቪድ-19ን በእርግጠኝነት፥ 'ሰው ሠራሽ ቀውስ ነው' ማለት አይቻልም። አለማለትም ወይም አይደለም ማለትም አይቻልም። ሰው ሠራሽ ቀውስ ከሆነ ምክንያቱ ምን ሊሆን ይችላል? አሁንም ይህ ነው ብሎ በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም። ምናልባት ከነዚህ ቀጥሎ ከማቀርባቸው ከሁለቱ አንዱ ወይም ሁለቱም፥ ወይም ከሁለቱም ሌላ ሊሆን ይችላል። ልብ እንበል፤ ሰው ሠራሽ ከሆነ ነው ያልኩት።

1. ዓለም አቀፍ ቁጥጥር ቤተ ሙከራ ሊሆን ይችላል።

ዓለማችን ወደ መንደርነት እየገባች ናት። ሉላዊነት (globalism) የክፍለ ዘመኑ፥ የ21ኛው መቶ ዋና ቃል ነው። ቴክኖሎጂው አቀራርቦናል። ኢኮኖሚው አገሮችን አስተሳስሯል። የአንድ አገር ኢኮኖሚ ወይም የአክሲዮን ገበያ (stock market) ከተናጋ የሌሎቹ አገሮች ኢኮኖሚም አብሮ ይናጋል። ሞኖፖሊዎች ኩባንያዎችን እና የግብይት መድረኮችን እየገዙና እየተቆጣጠሩ ነው። የየቀጣናው አገሮች የንግድ ትብብርና ማኅበር እየመሠረቱ ነው። በቀጣናዎቹ የንግድ ትስስሮች አንዱ ከሌላው ይልቅ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል። አንዳንዶቹ አገሮች መበጣጠቅ ቢያምራቸውም፥ ሌሎች ብዙዎች አንድ መሆንን እየተለማመዱም እየወደዱም ናቸው። በአውሮጳ እንደሚታየው፥ አገሮችና ሕዝቦች ራሳቸው እየተዋሃዱም ይመስላል።

እነዚህ በጥናትና በሂደት፥ በጥቅምና በግንኙነት ወይም ጉርብትና የሚሆኑና እየሆኑ፥ እየታዩ ያሉ ነገሮችም ናቸው። አንዳንዴ ደግሞ ረጃጅም ሂደቶች ሳይሆን ድንገተኛና ያልታሰቡ ክስተቶች የዓለምን ሁኔታ በፍጥነት ይለውጡና ትብብሮች ይፈጥራሉ። ሁለቱ የዓለም ጦርነቶች ትልልቅ ዓለም አቀፍ ኅብረቶችና ድርጅቶች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆነዋል። League of Nations እና United Nations የነዚህ ሁለት ጦርነቶች ውጤቶች ናቸው። ብዙ አገሮችን አንድ ያደረጉ የተለያዩ ክስተቶች ቢኖሩም፥ እስካሁን ዓለምን በሙሉ በጥልቀት የለወጠና አቅልጦ አንድ ያደረገ፥ በአንድ አጀንዳ ያሰረና የጠፈረ፥ በአንድ አእምሮ እንዲያስቡ፥ በአንድ ሳንባ እንዲተነፍሱ ያደረገ፥ እንቅስቃሴን ቀጥ አድርጎ የገታ፥ ድንጋጤና ፍርሃትን በሰው ልብ ውስጥ እንደ ችካል ወግቶ የተከለ፥ አንድ መፍትሔ፥ አንድ ተስፋ፥ አንድ የቁልፍ መክፈቻ እንዲፈልጉ ያደረገ እንደ ኮቪድ 19 ያለ ጉዳይ ኖሮ የሚያውቅ አይመስለኝም።

ይህ ዓይነቱ አካሄድ ዓለምን በአንድ አስተሳሰብ መቅረጽ፥ በአንድ አእምሮ ማሰብ እንዲቻል ያደረገ ወይም ያስደረገ ሙከራ ነው ማለት ይቻላል። በ2020 ከማርች ጀምሮ ለቀጣይ 3ና 4 ያህል ወራት በዓለም ዜና አውታሮች ሌላ ምንም ነገር አይነገርም ነበር። ሁሉም ዜና አንድ ነገር ብቻ ላይ ያተኮረ ሆነ፤ ኮቪድ-19 ላይ። ዓለም በመላዋ አንድ ነገር ብቻ እንድታስብ፥ እንድታወራ፥ እንድትሰማ፥ እንድትጠብቅ፥ እንድትከታተል ተደረገች። አፍሪቃ ወይም እስያ ውስጥ ጦርነት ቢነሣ፥ አንዳንዴ ዜና የአንዲት አገር ብቻ ወይም የጥቂት አገሮች ይሆናል። አንዳንዱ ሳይሰማም ይጠናቀቃል። በነዚያ 4 ወራት ብዙ ነገሮች ተከስተዋል፤ ግን ማንም ቁብ ያላቸው አልነበረም። ይታይና ይሰማ የነበረው ስንት ሰዎች ተያዙ? ስንት ሞቱ? ስንት ዳኑ? ክትባት ተሠራ? መፍትሔ አለው? ይህ እና ይህ ብቻ ነበር ጉዳዩ።

ኮቪድ-19 እንዲያ ያለ ተሰምቶም እስከማይታወቅ ገዢ ዜና ሆኖ ባጀና ከረመ፤ በዓለሙ ሁሉ። እንዲህ ያለው ነገር ለግንኙነት ብቻ ሳይሆን ለሙሉ ቁጥጥርና እንቅስቃሴን ለመግታትም አመቺ ነው። ቁጥጥር ዋናው ቁልፍ ቃል ነው። የቤተ ሙከራነቱ ጉዳይ እዚህም ላይ ነው። ሁለተኛው ነጥብም እርሱ ነው።

2. የቁጥጥር መንገድ

ቁጥጥሩ ከስሜት እስከ ስነ ልቡናና እስከ አካል፥ እስከ እንቅስቃሴዎች፥ እስከ ግንኙነቶችና ማኅበራዊ መስተጋብሮች፥ እስከ ኢኮኖሚና ፖለቲካ አካሄዶችም ድረስ ነው። ኮቪድ-19 ይህንን አላደረገም ማለት አንችልም። በእርግጥ እና በጥንካሬ አድርጎአል። መሥሪያ ቤቶችና ትምህርት ቤቶች፥ የየብስና የአየር መንገዶች ተዘጋጉ። ሰው ከቤትም እንዳይወጣና የቤት ሰው ብቻ ካልሆነ እንዳይቀበልም የታገደባቸው አገሮች ነበሩ።

ሐሰተኛው ክርስቶስ እንደሚመጣ እናውቃለን። ዳንኤል፥ ኢሳይያስ፥ ሕዝቅኤል በትንቢቶቻቸው፥ ጌታችንም በወንጌላት ውስጥ፥ ዮሐንስ፥ ጴጥሮስ፥ በተለይም ጳውሎስ በመልእክቶቻቸው በስፋት ነግረውናል። ይህ ሐሰተኛ ሲመጣ ዓለምን የሚገዛው በድንገትና በመላምት አይደለም። አስቀድሞ የተመቻቹ ሁኔታዎች ተሰናድተውለት፥ ጥርጊያው ተጠርጎለት፥ ጉዝጓዙ ተጎዝጉዞለት ነው። 'ኮቪድ-19 ሰው ሠራሽ ቀውስ ነው፤ እናም፥ ለሐሰተኛው ክርስቶስ መድረክና መንገድ ጠራጊ ነው' ማለቴ አይደለም። ቀደም ሲል፥ ኮቪድ መቅሰፍት ነው? ወይስ ቸነፈር? ወረርሽኝ ነው? ወይስ ሰው ሠራሽ ሴራ? በሚለው አሳብ ላይ ተናግሬአለሁና በዚያ የተብራራውን አልደግመውም። 'ኮቪድ-19 ሰው ሠራሽ ቀውስና ለሐሰተኛው ክርስቶስ መድረክ ሠሪና መንገድ ጠራጊ ነው' ሙሉ በሙሉ ባይባልም፥ ሊሆን አይችልም ማለት ግን አንችልም። ሊሆን ይችላል? አዎን፤ ሊሆንም ይችላል።

ዓለም በሞላዋ ዝግት፥ ዝግትግት ስትደረግ አየን። እንደዚህ ባለ ቀውስ ውስጥ ኢኮኖሚንና ፖለቲካን ብቻ ሳይሆን፥ ማኅበራዊ ግንኙነቶችንና መስተጋብሮችንም መቆጣጠር ይቻላል። የእርስ በርስ ግንኙነቶችን ብቻ ሳይሆን የራስን ከራስ ጋር ግንኙነትንም ሳይቀር መቆጣጠር ይቻላል። የሰዎችን ግላዊ እንቅስቃሴ መቆጣጠርም ይቻላል። እንቅስቃሴን ብቻ ሳይሆን የሰውን ስሜትም መቆጣጠር ተቻለ። ፍርሃት ስሜት ነው፤ የሰው ስሜት በፍርሃት የተወጠረበት እንደዚህ ያለ ጊዜ ኖሮ አያውቅም። ሰዎች ሲፈሩ፥ ፍርሃት ጨምድዶ ሲይዛቸው ምንም ነገር እንዲያደርጉ ሲነገራቸው በቀላሉ ማስደረግ ይቻላል።

ፍርሃት ሰዎችን የገዛበት፥ ፍርሃት ራሱ ያስፈራበት እንደዚህ ያለ ጊዜ ኖሮ አያውቅም። ቀደም ሲል ስለ ፍርሃት ስንካፈል ፍሬንክሊን ዲ ሩዝቬልት ከ87 ዓመታት በፊት የተናገረውን እናስታውስ፤ 'መፍራት ያለብን ነገር፥ ፍርሃትን ራሱን ነው' ነበር ያለው። ያ ጊዜ ታላቁ ድባቴ (The Great Depression የሚሉት) የኢኮኖሚ ድሽቀት ዓለምን ጨምድዶ የያዘበትና ሰው በትልቅ ስጋት ውስጥ የነበረበት ጊዜ ነው። ሰው በእርግጥም ፈርቶአል። ፍርሃት ራሱም አስፈሪ ሆኖአል። መንግሥት መፍትሔ ነው ብሎ ያቀረበውን ነገር ለመቀበል ሰዎች ደጋግሞ ለማሰብ ጊዜ አይኖራቸውም።

በ2020 ከኮቪድ-19 በላይ ፍርሃት የሚባለው ነገር ራሱ ድባቡ የሚያስፈራ ሆኗል። ሰው መታመሙ አዲስ አይደለም፤ የታመመ ሰውን ማስታመም አለመቻል ግን ያስፈራል። ሰው መሞቱ አዲስ አይደለም፤ የሚሞት ሰውን ከመሞቱ በፊት እጅ ይዞ ወደ ጌታ እንደሚሄድ መንገርና በመጨረሻ ላይ አብሮ መጸለይ፥ እየዘመሩ መሸኘት አለመቻል ያስፈራል። የሞተ ሰውን መቅበር ወግ ነው። መቅበርና የቀብር ስነ ሥርዓት ማድረግ አለመቻል ግን ያስፈራል። በኀዘን ጊዜ ተቃቅፎ ማልቀስ የሰው ልጅ ልማድ ነው፤ ይህንን ማድረግ አለመቻል ያስፈራል። ለምጽ ወይም ሥጋ ደዌ እንደ ያዘው ሰው በተዘጋ ቤት ውስጥ መሰንበትና ተራርቆ መሄድ ያስፈራል። ፍርሃት ራሱ ያስፈራበት እንደዚህ ያለ ጊዜ ኖሮ አያውቅም። ስሜት ለፍርሃት የተገዛበት ጊዜ ነው የኮቪድ ጊዜ።

ዜጋ ፈሪ ሲሆን መሪዎች መግዛት ይመቻቸዋል። መንግሥታት የዜጎችን ስሜት መቆጣጠር መቻላቸው ሰጥ ለጥ አድርጎ ለመግዛት ያመቻቸዋል። የደርግ መንግሥት ሲመጣ በሁከት ውስጥ ነበር የመጣው፤ ጊዜው የተረባበሸ ነበር፤ የሰዎች ስሜትም የተደበላለቀ ነበር። ተስፋ፥ ደስታ፥ ጥርጥር፥ ስጋት፣ ጥያቄ፥ ግር መሰኘት ነበረ። ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም ተባለና ደም እንደማይፈስስ ተስፋ ተጨበጠ፥ መሬት ላራሹ፥ ዕድገት በኅብረት፥ መሠረተ ትምህርት፥ መሠረተ ልማትና ጤና፥ ንቃት፥ መንቃት፥ ማንቃት፥ መነቃቃት መጣ። የደፈረሰው ትንሽ መረጋጋት ጀመረ። የመጀመሪያው ፍርሃት እንደ ቦምብ በአገሪቱ የፈነዳው ስድሳዎቹ በአንድ ቀን ሲገደሉ ነበር። ከዚያ ነጭ ሽብር፥ ቀይ ሽብር ተብሎ አገሪቱ በደም አበላ ስትርስ፥ ሬሳ ስትታቀፍ ድንጋጤና ፍርሃት ነገሠ። ከዚያ በኋላ የነበረው የደርግ ዘመን ፍርሃት የነገሠበት ነበር። ለምሳ ያሰቡንን ቁርስ አደረግናቸው ካለ በኋላ ሕዝቡ ፈራ። ሰው ሲፈራ መንግሥት ለመግዛት ይመቸዋል። ፍርሃት ደግሞ ከስሜቶች ሁሉ ጠንካራ ስሜት ሳይሆን አይቀርም። ኮቪድ-19 እንደዚያ ያለ የፍርሃት ስሜት መፍጠሩ ግልጽ ነው። ሰው ሲፈራ ለመታዘዝ ምቹ ይሆናል። በኮቪድ-19 ወቅት፥ ከጥቂቶች ይህ ነገር ሴራ ነው ብለው ከሚያስቡት በቀር፥ ሕዝቡ አድርጉ የተባሉትን ያለ ጥያቄ ያደርጉ ነበር።

ሐሰተኛው ክርስቶስ ከእውነተኛው ክርስቶስ የሚለየው ፍርሃትን መጠቀሙና በማስፈራሮ መግዛቱ ነው። እውነተኛው ክርስቶስ ጌታችን በፍቅር፥ በውዴታ፥ በነፃነት ነው ወደ መዳን የሚጋብዘው። ሐሰተኛው ክርስቶስ ግን ወደ ፊት እንዴት አስጨንቆ እንደሚገዛ፥ እንደሚሰገድለት፥ እንደሚመለከም በቃሉ አመልካች ትንቢቶች ተጽፈውልናል። እንደዚህ ያሉ ነገሮች ለዚያ መሰል አስፈራሪ አገዛዝ ጥርጊያ አይደሉም ማለት ወደ የዋኅነት የተጠጋ አመለካከት ነው። ክትባት ለምሳሌ፥ ከሥራም፥ ከትምህርትም፥ ከጉዞም ጋር ሲገናኝና ግዴታ ሲሆን ሰው ለሕልውናው፥ ለሥራው፥ ለትምህርቱም፥ ለጉዞውም ሲል ለመውሰድ ተገደደ። ወደ ክትባቱ ስንመጣ ራሱ ክትባቱ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው።

## የክትባት ጉዳይስ?

የክትባት ጉዳይ ከኮቪድ-19 ጋር አብሮ መነሣት ያለበት ሌላው ትልቅ ርእስ ነው። ሰው ሁሉ በትልቅ ፍርሃት ውስጥ ባለበት ጊዜ ክትባት ተገኘ ሲባል ክትባቱን ለመውሰድ ዓይኑን የሚያሽ ወይም ሁለቴ የሚያስብ የሚኖር አይመስለኝም። ክትባቱ ከተሠራ ቢቆይም በሙከራ ሂደት ላይ ከርሞ በJanuary አጋማሽ 2021 ላይ በይፋ መሰጠት ተጀምሮአል። አንዳንድ አገሮች በብዛት አዝዘው ይዘዋል። አንዳንዶች ራሱን ክትባቱን በስጋት አይተውታል።

ከክትባት ጋር ምንም ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸው አካላትና ኮርፖሬሽኖች ስለ ክትባት ሲናገሩ መስማትና ማየት ደግሞ፥ 'ለምን?' ብሎ መጠየቅን ይጠይቃል። እንደ ማይክሮሶፍቱ ቢል ጌትስ ያሉ ከሕክምና ወይም ከጤና ጥበቃ፥ ወይም ከስነ ሕዝብ ጋር ምንም ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸው ሰዎችና ድርጅቶች ስለ ክትባት በጥብቅናና በጥብቅ ሲናገሩና ሲደመጡ፥ 'ምን አጀንዳ ኖሯቸው ነው?' ያስብላል። ሰዎች አውቀው ወይም ሳያውቁ የሰይጣንን አሳብ ሊፈጽሙ እንደሚችሉ እናውቃለን። ሰይጣን የማያምኑትን ልብ ያሳወረ የዚህ ዓለም ገዥ መሆኑ በቃሉ ውስጥ ተጽፎአል። ማሳወር ደግሞ ለመቆጣጠር ዋና መሳሪያ ነው። ዕውር መሪ ያስፈልገዋል። ሰይጣን የማያምኑትን ልብ ካሳወረ ልባቸውን መምራት ይቻለዋል።

ክትባት ሰዎችን በቀላሉ መቆጣጠሪያ መንገድ ሊሆን እንደሚችልም ማሰብ ይቻላል። ማዳኛና መከላከያ ሊሆን እንደሚችል ሁሉ አንዳንድ ክትባት ተበርዞና የክትባትነት ዘዴውን ብቻ በመእቀም ማጥፊያና ቀደም ሲል እንዳየነው እንደ ማልተስ ንድፈ አሳብ የሕዝብ ቁጥር መለጎሚያና መቀነሻም ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ቅን ምሑራን እና ሊቃውንት በንጹሕ ሕሊና ለሰዎች ደህንነት የሚሠሩት መከላከያና መድኃኒት

በተንኮለኞችና እኩያን ሴረኞች ተጠልፎ ሊወሰድና ሊቀየጥ አይችልም ለማለት አንችልም። ስለዚህ አንዳንዶች፥ 'ከክትባቱ ጋር የሚሰጥ ሌላ ነገር ቢኖርስ?' በማለት፥ አንዳች አደጋ ሊኖር እንደሚችል በመገመት ቢሰጉ ሊፈረድባቸው የተገባ አይደለም።

ይህ ዓይነቱ ወይም ተቀራራቢ ሁኔታ ደግሞ ወደ ፊት የሚመጣ አንድ ዓለምን ሊገዛና ሊቆጣጠር የተነገረለት ሐሰተኛ ክርስቶስ አለና ለዚያ ምቹ መድረክና ቤተ ሙከራ ሊሆን አይችልም ብሎ አለማሰብም አይቻልም። ክትባቱን ከሐሰተኛው ክርስቶስ ማንተም ጋር አቆራኝተው የሚያዩ ሰዎች ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ይላሉ። በቀጥታ ከ666 ጋር አያይዘው ያስተማሩና የሚያስተምሩ ጥቂት ያልሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎችም አሉ። 666 ብዙ ስሕተቶችና መላ ምቶችን ያስተናገደ ትንቢትና ቁጥር ነው። እንደታዘብኳቸው ደግሞ፥ ከዚህ ቁጥር ጋር የተያያዙ ስሕተቶችን በማባዛት ክርስቲያኖችን የሚያስበረግጉ አስተማሪዎች ቃሉን በወጉ ያልተማሩና የስነ አፈታት ጉዳተኞች የሆኑ ሰዎች ናቸው።

አንዳንድ ሰዎች ይህንን የክትባት ጉዳይ የ666 ምልክትና ኤሌክትሮኒካዊ ቺፕ በሰዎች ውስጥ መግባት አድርገው የሚያሳዩት ክትባቱ በአካል ስለሚወሰድ ነው። እነዚህ ሰዎች እንደሚሉት 666 የኤሌክትሮኒክ ቺፕ ከሆነ የሰዎች ግላዊ ሰነድ መሆን አለበት እንጂ እንዲህ በጅምላና የማንም ከማንም ሳይለይ፥ የማንም ለማንም የሚሰጡት ክትባት ሊሆን አይችልም። የባንክ ካርድ ወይም ዘመናዊ መታወቂያ ካርድ፥ ወይም የመንጃ ፈቃድ (በምዕራቡ ዓለም የመንጃ ፈቃድ መታወቂያም ነው) የግላችን መረጃዎችና ግብዓቶች ብቻ ናቸው ያሉባቸው። የማንም ለማንም ሊሆን አይችልም። ካርዱ ላይ ወይም ውስጥ ባርኮድ ወይም QR ኮድ ወይም ሌላ የሰነድ ተሸካሚ የኤሌክትሮኒክ ቺፕ ሊኖር ይችላል፤ ያንን መመሥጠሪያ የሚያነብብ ወይም ማንበብ የሚችል ሌላ ቴክኖሎጂ ደግሞ በሌላኛው ጫፍ አለ፤ እነዚህ ተናብበው ስለ ካርዱ ባለቤት መረጃው ይገኛል። ይህ ካርዱ ውስጥ ያለ ቺፕ በመጠን አንሶ ተሠርቶ ቀለበቴ ወይም አውራ ጣቴ ውስጥ ቢሆን ልዩነት የለውም፤ ወይም የጆሮ ጉትቻሽ ወይም ጆሮሽ እራሱ ላይ ቢሆን ኪስ ወይም ቦርሳ ውስጥ ከመሸከም ልዩነት የለውም። በእውነቱ አሁን በምንጠቀምበት አጠቃቀም መልኩ ከሄድን ካርድ በቦርሳ መያዝ እና ኤሌክትሮኒክ ቺፕ መዳፍ ውስጥ መግባት ልዩነት የላቸውም። እንዲያውም ይህኛው የመዳፉ ስለማይጠፋና ስለማይሰረቅ ስጋት ይቀንሳል።

ይህ ማለት ግን፥ 'ወደፊት እንዲህ ያለው ቴክኖሎጂ ተግባር ላይ አይውልም፤ ሰዎችንም ለመቆጣጠር አይተገበርም' ማለት ሳይሆን፥ በጣም የተዛባውና ጥንቆላ የሚመስለው የዚህ የ666 አፈታት ስሕተት መሆኑን እንድናስተውል የተገባ ነው። ስለ 666 የሚያስተምር ሰው ጠቅላላውን የራእይን መጽሐፍ ሳያስተምር፥ ሳያስጠና ራእ.

13፥18 ብቻ ቦጭቆ የሚያስተምር ከሆነ ያንን ሰው አትስሙት። ያ ሰው የተሳሳተ አፈታት እየፈታ ያለ ሰው የመሆኑ ዕድል በጣም ሰፊ ነው።

ወደ ክትባቱ ስንመጣ፥ በተለይ እንደ ኮቪድ-19 ዓለምን በሙሉ የወረረና የዓለምን ብዙ ገጽታ የተቆጣጠረ ወረርሽኝ ሲኖር ክትባቱ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ሊሆን ይችላል። ወረርሽኙ እጅግ ከተጋነነና አስፈሪ ከሆነ መከላከያው የምርጫ ጉዳይ እንዳይሆን ሊደረግ ይችላል። የግዴታው መልክም ሊለያይ ይችላል። የውዴታ ግዴታ በቀላሉ ይደረጋል። ክትባቱ ከሥራ ጋር ከተቆራኘ፥ ይህ ከሕልውና ጋር ተያያዘ ማለት ነው። ሰው በሥራ ገበታው ለመገኘት ሲል ይወስደዋል። ከትምህርት ጋርም ሊቆራኝ ይችላል። ለመማር መከተግ ግድ ከተባለ የትምህርት ገበታ ላይ ለመገኘት መውሰድ ግድ ይሆናል ማለት ነው። የወሰዱ ሳይሆኑ፥ ያልወሰዱ ሰዎችም ዒላማ ሊደረጉ ይችሉ ይሆናል። የክትባት ሰርቲፊኬት ያላሳየ ሰው በአውሮፕላን መጓጓዝ ወይም ኬላ ማለፍ ሊከለከል ይችላል። በሰው እንቅስቃሴ ላይ ማዕቀብ ተጣለ ማለት ነው። ይህ ሁሉ ታዲያ ለቁጥጥር ሊሆን እንደሚችል ሁሉ ለጥንቃቄና ለመከላከል ሊሆንም ይችላል። ለሁለቱም ሊሆን ይችላል።

ክትባቱን ከዚህ በፊት እንደወሰድናቸው ብዙ ክትባቶች ብቻ ብናየው፥ የተለያዩ የክትባት መሥሪያ መንገዶች አሉ። ይህንን የኮቪድ-19ን ክትባት ከሌሎቹ የተለየ የሚያደርገው፥ ይህኛው ክትባት ምጡቅና አዲስ ዓይነት፥ ትውልድ አለፍ (next generation የሚሉት) ዘረመልላዊ ክትባት (genetic vaccine) እና viral vector vaccine የሚባሉት መንገዶችን ተከትሎ የተሠራ መሆኑ ነው። ይህ ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ እየተሞከረ ያለው በኮቪድ-19 ነው። የተለመደው የክትባት መንገድ pritein subunit እና virus-like particle የሚባለው ነው። ይህ ረቂቅና ሳይንሳዊ ትንተና የሚጠይቅ ነው፤ እንደኔ ያለ ከሕክምና እና ቅመማ ሙያ የራቀ ሰው ሊተነትነው ቀርቶ በወጉ ሊረዳውም አይችልም። ይህንን እዚህ የማካፍለውን ጉዳይ ሳዘጋጅ ስለ ጉዳዩ ያነበብኩባቸውን አንድ ሁለት ምንጮችን አስቀምጣለሁ፤ https://www.youtube.com/watch?v=KMc3vL_MIeo&list=PLbpi6ZahtOH6CBHw5k8mNUmqm0yg-gfC_

በአማርኛ ስለዚህ ጉዳይ የተደረገ ቃለ ምልልስ ከዚህ ይገኛል፤

https://www.youtube.com/watch?v=XN_dP8aizHo

በዚህ ቃለ ምልልስ የተናገረው ዶ/ር ዳንኤል ዮሐንስ ስለ ክትባቱ በሰፊ ዝርዝር የተናገረበት ልዩ ዝግጅት ደግሞ ከዚህ ይገኛል፤

https://www.youtube.com/watch?v=LQcxsXtRUv0

የብዙዎች ፍርሃት ክትባቱ የቁጥጥር መሣሪያ፥ በተለይ ከሕዝብ ቁጥር እገታ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል የሚል ነው። ክትባት ሁሉ በጥርጥር መታየት አለበት ማለት አይደለም። ክትባት ሁሉ በጥርጥር መታየት የለበትም ማለትም አይደለም። ይህ በጥሞናና በጥንቃቄ መታየት ካለባቸው ጉዳዮች አንዱ ነው። ግን ምንጫቸውና ምንነታቸው ያልታወቁና ያልተረጋገጡ ወሬዎች ስሜትንና አእምሮአችንን መናጥና ማወክ ይችላሉ። ይህ ደግሞ መሆን የለበትም። ያለ ምንም ማስረጃ ክትባቱን አሰይጥነው በሚያሳዩ ሰዎች መወናበድ የለብንም። ክትባትን፥ 'መከላከያ ብቻ ነው' በሚሉ የዋህ ሰዎችም መሞኘት የለብንም። እንደ ክርስቲያን በጸሎት፥ በምስጋናና በማስተዋል መወሰን ይኖርብናል።

እንደ ክርስቲያኖች ስንኖር የማን መሆናችንን፥ ስንሞት ወዴት እንደምንሄድ እንርሣ። ጌታን የማታውቁና ይህን የምታነብቡ ወገኖች ደግሞ ወደ ጌታ ኑ በማለት ልጋብዛችሁ እወድዳለሁ። ወደ ጌታ መምጣት እረፍት ነው፤ ሰላም ነው፤ ወደ ጌታ መምጣት ሕይወት ነው፤ ዘላለማዊ ሕይወት። እርግጠኛ ዋስትና ያለው ዘላለማዊ ሕይወት ነው። ይህ ሕይወት ጌታን በመቀበል ይጀምራል። ስለዚህ ጉዳይ ይበልጥ ለመረዳት፥ ዩቲዩብ ገጼ ላይ፥ 'ጌታን ተቀብለሃል?' በሚል ርእስ ያካፈልኩትን በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ በጽሑፍ አስቀምጫለሁ። ይህንን ጌታን ተቀብለሃል? ተቀብለሻል? በሚል ርእስ የተሰናዳ አጭር አጭር የ10 ደቂቃ የቪድዮ ዝግጅት ከዚህ ሊንክ ይገኛል። https://www.youtube.com/watch?v=YcOmswunVC0

## ኮቪድ-19 ክርስትና እና የእምነት ተቋማት (ጉዳትና ጥቅሞች)

ኮሮና እና የእምነት ተቋማት እና አገልግሎቶች ጉዳይ ሌላው መመልከት ያለብን ነገር ነው። እርግጥ ነው፤ አንጻራዊ ጉዳት አለው፤ ሆኖም፥ ኮሮና ሃይማኖት እየለየ የሚወርር ቫይረስ አይደለም። እንደ ክርስቲያን ፍርሃትንም በሽታውንም ሞትንም እንዴት መጋፈጥ እንዳለብን ቀደም ባሉት ክፍሎች በተለይም ተመልክተናል። በዚህ ክፍል ኮቪድ-19 ወይም ኮሮና በቤተ ክርስቲያን ላይ ስላመጣው ጉዳይ እናያለን። ይህ ጉዳይ ጉዳይም ጉዳትም ነው። ጥቅምም ጉዳትም አለበት፤ ያንንም እንመለከታለን። ከጥቅሞቹ ልጀምር።

# የኮሮና መልካም ገጽታዎች።

## 1. ቤተ ክርስቲያንን ወደ አየር አውጥቶአታል።

ቤተ ክርስቲያን ስል አገልግሎቶቿን ማለቴ ነው። ቤተ ክርስቲያን ማለት ጣራና ግድግዳ አለመሆኗ ዱሮም የታወቀ ነው። ኮቪድ ይበልጡን ያንን መልኳን ገልጦታል። እርግጥ ነው፤ ይህ አሠራር ለቁጥጥርና ማን ምን እያደረገ፥ በየትኛው ስብሰባ ምን እየተባለ እንደሆነ፥ እነማን ምን እየዶለቱ እንደሆነም ለማወቅና ለቁጥጥር አመቺ መሆኑም እውነት ቢሆንም፥ የቁጥጥር ጉዳይ ወይም የሴራ ንድፈ አሳብ ያልኩት እንዲህ ያለውንም ነገር እንደሚያካትትም ቢታወቅም፥ ምንም በሌላ በማንም የማይደመጥ ዝግ ወይም secure ስብሰባ እናድርግ ማለት ባይቻልም፥ በኮቪድ ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ አለመሆኗ ይበልጥ የተገለጠበት አጋጣሚ ተፈጥሯል። ወይም ይህ ወረርሽኝ ይበልጥ ገልጦታል። የማኅበራዊ ሚድያ አገልግሎት በሰፊው ተዘርግቷል።

ማኅበራዊ የግንኙነት አውታሮች ወይም መረቦች ኢንተርኔትን መሠረት ያደረጉ ከየትኛውም ቦታ ሆኖ በቴክኖሎጂ አንድነት መገናኘት የሚቻልባቸው መድረኮች ናቸው። አስቀድሞም በተግባር ላይ የዋሉ ቢሆኑም በዝጉ ወራት ቤተ ክርስቲያን መድረኳ ያደረገችውና አማኞች መንፈሳዊ ምግባቸውን የሚያገኙበት መስመራቸው ሆኖአል። ኮሮና የቤተ ክርስቲያንን በሮችን ሲዘጋ፥ ጌታ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን ከመሬት ወደ አየር ላይ ከፍ አድርጓታል። ቀድሞም አየሩን ስትጠቀምበት ቆይታለች፤ አሁን ግን በሰፊው ገባችበት።

በሰለጠነው ዓለም ከጥቂቶች በቀር መሥሪያ ቤቶች ሁሉ የተዘጉ ሲሆኑ ሥራዎች ሁሉ ከቤት መሠራት ተጀመረ። ይህ አሠራር ቀጣይነት ያለው ሆኖም እየተሠራበት ነው። ቢሮ መግባት በአካል መሆኑ ቀረ ወይም በጣም ተቀነሰ። ስብሰባዎች virtual ሆነዋል። በቴክኖሎጂ ወደ ኋላ በቀሩት ዘንድ ችግር ቢሆንም ተማሪዎች ከቤት እየተማሩ ቆይተዋል። በዘመናችን፥ ጦርነትም እንኳ በአካል መሆኑ እየቀረ እየመጣ፥ በሜዳ ሳይሆን hsituation room እየሆነ ነው።

የእሁድ አምልኮዎች ከቤት ሆነን የምንሳተፍበትና የምንካፈልበት ሆኖ ለሳምንታት እና ለወራት ዘልቋል። በአካል መገናኘት ቀረ እንጂ ትምህርቱ አልተጓደለም። ቤተ ክርስቲያን ደግሞ አካል ናትና አካላዊው ግንኙነት ይርባል፤ ይጠማል። ሆኖም ባያጠግብም የራብ ማስታገሻ ሆኗል። ቴክኖሎጂው ራሱ ጥሩ ጎን ነው። ራሱን ቴክኖሎጂውን ለጉሞ መንዳት መቻቻሉ ትልቅ በረከት ነው። በአንድ ጉዳይ ላይ ተመሳሳይ፥ ተቀራራቢ፥ ወይም የተለያየና ተቃራኒ አሳብ ያላቸው ሰዎችም ቀርበው

መነጋገር መቻላቸው ድንቅ ነው። ከአመቺ ቦታ ሆኖ መሳተፍ ይቻላል። ቀድሞ የፓነል ውይይት ለማካሄድ በአካል መገናኘት ግድ ነበር፤ አሁን አይደለም። ይህ የቴክኖሎጂ አዝማሚያ ደግሞ ቀጣዩ ትውልድ የሚደረስበት ነውና ጠንካራ ብቻ ሳይሆን ጠቃሚ ጎኑም ነው። ይህ አዝማሚያ እንደ ማኅተም ሆኖ የሚቆይ ነው። ይህ አሠራር ቤተ ክርስቲያን ከተከፈተች በኋላም የሚቀጥል ይሆናል።

## 2. ከሐሰተኞች መጠነኛ እፎይታ ሰጥቶናል።

ለክርስቲያኖች የማኅበራዊው ሚድያና የአየር ስብሰባዎች ቀላል የማይባል ትልቅ ሥራ ሠርተዋል። በዚሁ ልክ የአየር ባየር ጉባኤዎችም ተፈጥረዋል። ወደ ማኅበራዊ ሚድያ ወጥቶ ገንዘብ ለመሰብሰብ መረብ አበጅቶ መዘርጋት የታወቀ ስልት ሆኗል። በዚህ መልኩ እንዲያውም ሐሰተኞቹን የነዛቸውና ያባዛቸው ይመስላል።

ሆኖም፥ ሐሰተኞቹ ነቢያትና ሐዋርያት በትንሹ እና ለተወሰነ ጊዜ አደብ እንዲገዙ ማድረጉ ታይቷል። የነሱ ድራማና ገበያ የሚደራው ጉባኤ ባለበት ነው። ሰዎች በአካል ሲገኙ ነው ሰነዶች የሚሰረቁትና የተጻፉት ነገሮች ከሰማይ እንደወረደ ምስጢር ተደርገው የሚተወነው። ደንግጠው ለወራት ከተቀዛቀዙ በኋላ ግን፥ አንዳንዶቹ እንደምንም አንገት ከደፉበት እየተንደፋደፉ ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል። 'እገሊት የምትባዪ ማነሽ?' ባይሉም፥ 'እኔ ነኝ! የዝጋቤር ሰው!' ብላ ብቅ የምትል ሴት ባትኖርም፥ የገስት ሃውሳቸውን ገበያ ቀዝቀዝ ቢያደርገውም፥ ጉባኤ ከሌለ ጭር ሲል የማይወዱት ሐሳውያን መልክ ማንነታቸው በትንሹ በግልጽ እንዲታይ ለሕዝብ ፋታ ሰጥቶአል። አሁን ግን መልካቸውን ቀይረው እንደገና ወደ አየር መጥተዋል። እነዚህ ሰዎች እንደማይጠፉ የታወቀ ነው። ቃሉም ይበዛሉ አለን እንጂ ይጠፋሉ አላለንም።

## 3. ከአስመጋቢዎች ግብዣና ከአጉራሽና ጎራሾች ግርግር ተረፍን።

ኮንፈረንስ የሚሉት ነገር ለጊዜው ቆመ። 'ልዩ መንፈሳዊ ጉባኤ' ታላቅ የመነቃቃት ኮንፍራንስ' ከሚባሉ ማስታወቂያዎች አረፍን። በዚያው ልክ፥ አውሮጳና አሜሪካና ሌሎች ገንዘብ የሚታጨድባቸው ያደጉ አገሮች እየሄዱ የሚቀፍሉ አገልጋይ ተብዬዎች ግብዣ መቅረቱ አሳራፊ ጉዳይ ሆነ። ይህ ለጊዜው እፎይታ ነው። 'አገልጋይ ተብዬ' ስል እነዚህን አሚሚቂዎችና ስሜት ኮርኳሪዎች ማለቴ ነው፤ እንጂ ጤናማ አገልጋዮች መኖራቸውን መርሳት የለብንም። ሐሰተኞቹን ነቢያት ማለቴም አይደለም፤ ሐሰተኞቹ

የታወቁ ናቸው። ግን እነዚህ በየሄዱበት፥ በዚህ በሚድያ ዘመን ሳይቀር አንድ ስብከት ብቻ እየደጋገሙ የሚሰብኩትን ሰዎች ማለቴ ነው። በሚድያ ዘመን አንድ ስብከት አንድ ቦታ ከተሰበከ ዓለም ይሰማዋል እኮ። በቀጣዩ ከተማ ያንን መልሰህ ስትከልስ፥ በቀጣዩም ያንኑ ስትሠልስ ሰዎች ይታዘባሉ፤ ይመዝናሉ። እርግጥ ነው በጥቂት መስኮች የተካበተ የሚያካፍሉት እውቀት ያላቸው ሰዎች ቢጋበዙና ያንን ትምህርት ቢደግሙት ይህ መልካም ነው። ግን ማመንዥከም አንዴ ብቻ ነው የሚደረገው። ነገር ግን እንዲያው በዓመት ሁለቴ ከተኙበት በጩኸትና ጫጫታ ለመንቃት የሚደረግ ግብግብ የመነቃቃት ሳይሆን የማባነን ዘመቻ ነው። ከዚህ እፎይ ብለናል።

እውነቱ ደግሞ፥ አንድ የደረጀች፥ የቆየች ቤተ ክርስቲያን በውስጧ አገልጋይ የሚሆኑ ሰዎች ጠፍተው አይደለም ጋባዥቹ መድረካሞችን የሚጠሩትና የሚጋብዙት። ሲጀመር ጋባዥቹ ለስሙ መጋቢዎች ይባላሉ እንጂ መጋቢዎች ሳይሆኑ አስመጋቢዎች ናቸው። አንዳንዶቹማ ራሳቸውም ተመጋቢዎች ናቸው። የሚመግቡት ሲጠፋቸው ግብዣ ጋብዘው፥ ድግስ ደግሰው፥ ሞቅ ሞቅ አድርገው በአንድ ቅዳሜና እሁድ የበሉትን ለጥቂት ወራት እያገሱ እያስገሱ ይቆያሉ። በእውነቱ ቤታቸውን ቢፈትሹ ለራሳቸው አጥቢያ ቀርቶ ለሌላም የሚተርፉ አገልጋዮች በውስጣቸው አሉ። ብቻ ኮሮና ከነዚህ ዓይነቶቹ፥ የመሟሟቅ ኮንፈረንሶች ፋታም ሰጥቶናል። ይህ ጥሩ ገጽታውም ነው።

## 4. ትምህርቶች በብዛትና በስፋት ተገኝተዋል

በኮሮና ዝግ ምክንያት ብዙ የኦንላይን ትምህርቶች መኖራቸው እውነት ነው። ገለባዎችና መርዞችም አሉ። ሆኖም፥ ጥሩው ትምህርትም በብዛትና በስፋት መገኘቱ ሌላው በረከት ነው። በነዚህ የዝግ ወራት ሁሌም ተገብቶ የሚበሉት ምግብ መኖሩና ያ ደግሞ ልክ ፍሪጅ ውስጥ እንደሚቀመጥ ምግብ ሳይበላሽ ተቀምጦ የሚጠብቅ መሆኑ፥ ካስፈለገ ደጋግመው የሚበሉት፥ ወይም እንደገና የሚሰሙት የሚያዩት መሆኑ፥ ሌሎች ሰዎችም ያንን ትምህርት በአስተያየትና በጥያቄና መልስ የሚያዳብሩት መሆኑ፥ ጥሩው ነገር ነው።

## 5. አምልኮ የግልና የቤተ ሰብነቱ ግልጽ ሆኗል

ሌላው የኮሮና ዝግ ጠንካራ ጎን ሰዎች በማኅበርና በደቦ ሳይሆን በግልና በቤተ ሰብ ክርስትናን የሚለማመዱበት አጋጣሚ ደምቆ መውጣቱ ነው። በቡድን ተሸፍነው የነበሩ ክፍተቶች አሁን በግል ጥረት ይደረግባቸዋል። ግልጽ ሆነ ማለት ተጠናከረ ማለት አይደለም። ከሰመ ማለትም አይደለም። ግልጽ ሆነ ነው። በሽፋን ውስጥ ተሸፍኖ መቆየት ቀረ። የሰነፎቹ ጉዳት እንደተጠበቀ ሆኖ፥ በግል የማይተጉቱ ሰነፎቹ ይበልጡን ሰንፈው መጎዳታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፥ በዝጉ ወራት ሰዎች በግላቸው ቃሉ ምን እንደሚል መመርመርና መፈለግ ጀምረዋል። እንደ ቤተ ሰብ በሳምንት ውስጥ በርካታ ጊዜያት ቃሉን አብረው ማንበብና ተንበርክከው መጸለይ ሆኖላቸዋል። ይህ ጥሩ ጎን ነው።

## የኮሮና ጎጂ ገጽታዎች።

ወደ ፊት ሐሰተኛው ክርስቶስ እንደሚመጣና በሚመጣበት ጊዜ ሰዎችን የሚገዛው ስሜትን ብቻ ሳይሆን እምነቶችንም በመቆጣጠር እንደሆኑ በቃሉ ውስጥ ተመልክቶልናል። የሚሰገድለትና የሚመለክም ሰው ይሆናል። በ2ተሰ. 2፥4 *እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ፥ አምላክ ከተባለው ሁሉ፥ ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው ተቃዋሚ እርሱ ነው።* ይላል። *እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ* አዋጅ መንገር እንዲሁ በቀላሉ የሚሆን ነገር አይደለም። ከዚያ በፊት እና ከዚያ በኋላም የሚመጡ፥ የሚሆኑ ነገሮች አሉ። 'እኔ ክርስቶስ' ነኝ ካለ፥ በተለይ የክርስቶስን እምነት መዝጋት እና ቤተ ክርስቲያንን ማዳፈን ከተግባሮቹ አንዱ ነው፤ ይህንን የራእይ መጽሐፍ ይጠቁመናል። 'አውሬው' እየተባለ ከራእ. 13 ጀምሮ የተጠቀሰው ይህ ሰው ምልክቱን ያልተቀበሉትን ለይቶ ያሳድዳል። ምልክቱን የማይቀበሉት የበጉ (በጉ የተባለው ክርስቶስ ነው) ተከታዮች ናቸው። አሁን በአዋጅ አምልኮ ሳይከለከል ቤተ ክርስቲያን ስትዘጋ ምን እንደምትመስል በመጠኑ ካየን፥ በስደት ስትዘጋ ምን እንደምትመስል የተሰደዱት አማኞች ያውቁታል። የኢትዮጵያ ክርስቲያኖችም መጠነኛ እውቀት አለን። ጠቅላላው የመዘጋት ስዕሉ አለን። ወደ ኮሮና ጉዳቶች ስናልፍ፥

### 1. እንደ አካል ያለመሰብሰብ ጉዳት

ኮቪድ-19 ቤተ ክርስቲያንን መጠርቀሙ አንድ አሉታዊ ገጽታው ነው። እንዲህ ያሉ ወረርሽኞች በሚከሰቱባቸው ጊዜያት ብዙ ወይም ሁሉም ተቋማት የሚዘጉ

ቢሆኑም፥ የእምነት ተቋማት ያላቸው ስነ ልቡናዊ አዎንታዊ ግብዓቶች አሉና፥ በተለይም መንፈሳዊ የማበርከት ድርሻ አለና፥ የእምነት ተቋማት ከተዘጉ እነዚያ ግብዓቶች ይጠፋሉ። ሰዎች ሲፈሩ፥ ሲደነግጡ ወደ እግዚአብሔር ፊታቸውን ይመልሳሉ። እግዚአብሔርን መፈለጊያ የሆነው ወይም ምልክቱ የሆነው ያ ስፍራ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነች ያውቃሉ። ቤተ ክርስቲያንን በሚያውቋት መልኳ ፈልገው ከስፍራዋ ሲያጧት ግራ ይገባቸዋል። የባሰም ይፈራሉ። ይህ ሕዝባዊ ጉዳትም ነው።

ቤተ ክርስቲያን አካል ናትና የቤተ ክርስቲያን የኅብረት አምልኮ ለቤተ ክርስቲያን ሕልውና ትልቅ አስተዋጽዖ አለው። በኮቪድ-19 ስርጭት የመጀመሪያዎቹ ሰለባዎች ቻይናና አውሮጳ ቢሆኑም፥ በዓለም ቀዳሚዋ ተጎጂ ዩ ኤስ አሜሪካ ናት። በአሜሪካ ግንኙነቶች ለቀቅ ይደረጉ በተባለበት በ2020 የበጋ ወራት ሬስቶራንቶችና ካፌዎች፥ ቡና ቤቶችና ናይት ክለቦች እንኳ በመጠኑ ሲከፈቱ ቤተ ክርስቲያን ግን እንደተዘጋች እንድትቆይ ተደርጋ ነበር። ይህ ጉዳይ አንዳንዶችን እንዲጠረጥሩና እንዲጠይቁ አድርጎም ነበር። ቤተ ክርስቲያን ተለይታ ለምን እንደተዘጋች እንድትቆይ ተፈለገ?

የSun Valley, Californiaዋ ግሬስ ኮሚኒቲ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ጆን ማካርተር ይህ ቤተ ክርስቲያንን የመዝጋት አካሄድ ተገቢ ባለመሆኑና በኮቪድ የሞቱት ወይም የሚሞቱት ሰዎች 99.99 ተርፈው ከ0.02% ያነሰ (0.017%) በመሆኑ ይህ ፍርሃት መሠረተ ቢስ መሆኑን ተናግሯል። ማካርተር፥ ለመጀመሪያዎቹ 4 ሳምንታት ሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ያደርጉት እንደነበረው ሁሉ ሕንጻው ተዘግቶ በአካል መገናኘት ቀርቶ፥ ከቤተ ክርስቲያኑ በየእሁዱ በቀጥታ ስርጭት ማስተላለፍ ጀመረ። ስርጭቱን ከዚያ እንደሚያስተላልፍ ስለሚያውቁ እቤታቸው ሆነው ከመስማት ይልቅ እዚያ ተገኝቶ መስማትን ፈልገው ሰዎች በመጀመሪያ ጥቂት አሥሮች፥ ከዚያ በመቶዎች የሚቆጠሩ፥ ከዚያ ከሺህ በላይ ሆነው ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት ጀመሩ። የካሊፎርኒያ መንግሥት ይህንን አካላዊ ስብሰባ ለመዝጋት ሦስቴ የፍርድ ቤት ትእዛዝ አመጣ። ግን ፍርድ ቤት ሲኬድ ዳኛው ይህ የቤተ ክርስቲያን መዝጋት CDC የሚባለው ድርጅት ምክር እንጂ መንግሥታዊ የፍርድ ቤት ትእዛዝ አለመሆኑን አሳውቆ ማምለካቸውን እንዳይከለከሉ ፈረደላቸው።

በፌብሯሪ ወር 2021 በካናዳ በአልበርታ ግዛት በዚህ በአምልኮ ስብሰባ ምክንያት አንድ መጋቢ እስከመታሰርም ደርሷል። እንዲህ ባለ ጊዜ ሕግ አውጪና ሕግ ተግባሪው ራሳቸውም በብዥታ ውስጥ የሚሆኑበት ሁኔታ መኖሩ ግልጽ ነው። እነ ጆን ማካርተር አምልኮውን የቀጠሉት በሁለት ምክንያቶች ነው።

አንደኛው፥ የአገሪቱ ሕግም፥ የእግዚአብሔር ሕግም አምልኮን እንደማይከለክል በግልጽ የተጻፈ በመሆኑ ነው። የCDC ምክር ምክርና ማሳሰቢያ ብቻ ነው። መንግሥታዊ ትእዛዝ አይደለም። መንግሥታዊ ትእዛዝም እንኳ ቢሆን ይህ መተላለፍ አይደለምን? ማምለክ ከአገሪቱ መሠረታዊ ሕገ መንግሥታዊ መብቶች አንዱ በመሆኑ፥ ደግሞም፥ ከምድራዊ መንግሥት ይልቅ ቃሉን የሰጠውን አምላክ መታዘዝ ክርስቲያናዊ ግዴታ በመሆኑ ነው አምልኮአቸውን የቀጠሉት። ለመምጣት ወይም በአካል ተገኝቶ ለማምለክ ያልፈቀዱ እንደ ቀድሞው በማኅበራዊ ስርጭቶች መካፈላቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፥ የፈለጉት ጥንቃቄያቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በየእሁዱ መሰብሰብና በአካልም እየተገኙ ማምለክ ጀምረው ቀጠሉ።

ሁለተኛው ምክንያት ተግባራዊው ግንዛቤ ነው። ሰዎች በጥቂት ቁጥር ሠርግ ቢያደርጉ ወይም በጥቂት ቁጥር ልደት፥ ምረቃ፥ እና የመሳሰሉትን የደስታ ጉዳዮች ቢያከናውኑ ችግር የለውም። እንዲያውም ሠርግ በትንሽ ቁጥር በኛ ባህል የተለመደ አይደለም እንጂ በምዕራቡ ዓለም ቀድሞም የታወቀ ነው። ድል ያለ ሠርግ መደገስ ያልቻሉ በትንሽ ስነ ሥርዓት ተጋብተው፥ 'እወቁልን' ማለት በኛም ባህል እየተለመደ መጥቷል። መገናኘት ደስታ ነው፤ ቢቀርም ጉዳት የለበትም። እንደ ምረቃ፥ ልደት፥ በቀላሉ ልንተዋቸውና ቢቀሩብንም የሚቀርብን ነገር የሌለባቸው ጉዳዮች ናቸው። እነዚህ የደስታ ግንኙነቶች ቅንጦቶች ናቸው። ነገር ግን፥

- ሰው መታመሙ አዲስ ነገር ሳይሆን፥ ቃሉ እንደሚል ለታመመ ዘይት ቀብቶ መጸለይ ወይም የታመመ ሰውን ማስታመም አለመቻል ጉዳት ነው። በኮቪድ ተላላፊነት ፍርሃት በአጠገባቸው ሰው ሳይኖር የሞቱ ጥቂት አይደሉም።
- ሰው መሞቱ ራሱ አዲስ አይደለም፤ የሚሞትን ሰው ግን አጠገቡ ተገኝቶ፥ እጁን ይዞ አብሮ መጸለይ አለመቻል፥ ወደ ጌታ እንደሚሄድ ነግሮ አበረታትቶ፥ እየዘመሩ መሸኘት አለመቻል ጉዳት ነው።
- የሞተ ሰውን መቅበር ወግ ነው፤ ግን መቅበርና የቀብር ስነ ሥርዓት ማድረግ አለመቻል፥ በኀዘን ጊዜ ተቃቅፎ ማልቀስ የሰው ልጅ ልማድ ሆኖ እያለ፥ ይህንን ማድረግ አለመቻል ጉዳት ነው። ጉዳት ብቻ ሳይሆን ግፍና ጡር ነው። ለጥንቃቄ ቢባልም ከስፍር ያለፈ ጉዳት አላበት።

በነዚህ ምክንያቶች በአካል መገናኘት መከልከሉን ወድደው ተላልፈዋል። አንድ የአካል ብልት ለሌላው ማድረግ ያለበትን ማድረግ ሳይችል ሲቀር ጉዳት ነው። ሌሎቹ ለደስታ የሚደረጉ ስብሰባዎች ቅንጦቶች ናቸው። ከላይ የተዘረዘሩት ግን ቅንጦቶች አይደሉም። ያኔ በደርጋዊ የስደት ዘመናት እንኳ ቁጥር ይነስ እንጂ ቅዱሳን በየቤቱ በጥቂት ቁጥር ይገናኙ ነበር። ይህኛው ማንኛውንም ዓይነት አካላዊ ስብሰባ ያገደ

ክስተት ነው። በተለይ ለኛ ለኢትዮጵያውያንና እንደኛ ለመሰለ ባህል፥ እንኳን በሞት ቀርቶ በአዘቦቱም ቀን መተቃቀፍ ትልቅ ነገር ነው። ይህን ማጣት ይከብዳል።

ይህ አካሄድ፥ በተለይ ቤተ ክርስቲያን የምትሆንበት አኳኋን ትክክል ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን መወሰን ያለበት ማን ነው? መንግሥትን መታዘዝ ክርስቲያናዊ ወይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግዴታ ነው። ግን መታዘዙ ዳርቻ አለው? ድንበር አለው? መታዘዙ አምልኮን ሲነካስ? አምልኮን ሲነሳስ? አታምልኩ ወይም ለማምለክ አትሰብሰቡ ሲባልስ? ያኔ ቆም ብሎ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ መፈለግ ተገቢ ነው። የመጀመሪያዎቹን አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ከአዲስ ኪዳን ገጾች ስናነብብ፥ ቤተ ክርስቲያን የተወለደችው በሕጋዊ ጫና ውስጥ ነው። በሕጋዊ ብቻ ሳይሆን በሃይማኖታዊ ጫና ውስጥም ነው። ተላላፊ ወረርሽኝ አልነበረም። ግን ለክርስቲያኖች መሰብሰብ ሕጋዊ አልነበረም። አለመሆን ብቻ ሳይሆን፥ እንዲያውም እንዳይሰበሰቡ ሕጋዊ ጫናም ነበረበት። 'ቄሣር ጌታ ነው!' በሚባልበት ዓለምና ጊዜ፥ የቄሣርን ለቄሣር ብለው፥ 'ኢየሱስ ጌታ ነው!' ያሉ ሰዎች ነበሩ። የደረሰባቸው ስደትና ጉዳት አለ? አዎን፥ አለ። አታምልኩ ሲባሉ በነፍሳቸው ተወራርደው ያመለኩ ነበሩ። አታምልኩ ሲባሉ ያመለኩ ሰዎችም መኖራቸው በቅዱስ ቃሉ ውስጥ ተጽፎልናል።

ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳንን ከማገልገልና ወንጌል ላይ ከማተኮር ይልቅ፥ 'ዓለም ምን ትለኛለች? መንግሥት ምን ይለኛል?' የምትል ከሆነች፥ ወይም የዓለምን አመለካከትና አስተያየት ስብሳቢና በዚያ ተመዛኝ ስትሆን፥ ያኔ፥ ባህል ቀያሪ መሆኗ ቀርቶ ከባህሉ ወንዝ ጋር ፈሳሽ ትሆናለች። ያኔ፥ ዓይናፋርና ብሎም እስረኛ ትሆናለች። በጊዜውም አለጊዜውም ቃሉን የምትሰብክ አትሆንም። በአዲስ ኪዳን መሰብሰብ፥ ተሰበሰቡ፥ መሰብሰባችሁን፥ ወዘተ፥ እየተባለ ስለ መሰብሰብ በብዛትና በግልጽ ተጽፎአል። *በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደ ሆነው፥ መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ።* ዕብ. 10፥25። ይህ በስደት ውስጥ እያለፉ ላሉ አማኞች የተነገረ ቃል ነው። ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል፥ ቃሉ ራሱ በግዕዝ አቅሌስያ የሚለው ቃል፥ ምንጩ የግሪኩ ኤክሌሲያ ነው። ኤክሌሲያ ስብሰባ ወይም ጉባኤ ማለት ነው። ተጠርተው የወጡ ወይም የተሰበሰቡ ሰዎች ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያን አካልና አካላዊ ስብስብ ናት። ጉባኤና ማኅበርም ናት።

ይህ ማለት ግን አላግባብ በሆነ መንገድ ለወረርሽኙ መጋለጥና ሌሎችንም የማጋለጥ ምክንያት መሆን አይደለም። ከልክ በላይ መበርገግና ፈጽሞ ከክርስቲያናዊ ስብሰባዎችና አገልግሎቶች መጾም ማለትም አይደለም። እየሆነ ያለውን፥ እመሬቱ ላይ ያለውን ሁኔታ፥ ቁጥርና እስታቲስቲክስን፥ የጤና ተቋማትን ምክር እና የመንግሥት ድንጋጌዎችን፥ የቤተ ክርስቲያንን ማንነትን በተለይም የቃሉን ትምህርት ጠንቅቆ

ማወቅ ተገቢ ነው። በወረርሽኙ ወራት ይህንን ታሳቢ አድርገው ብዙ ቅዱሳንና ማኅበራት ሲሰበሰቡና ሲያመልኩ ቆይተዋል።

## 2. የሐሰተኞች መብዛትና የስሕተቶች መጉዳት

ከላይ በጥቅሞቹ ዝርዝር ውስጥ ሐሰተኞቹ የጉባኤ ግርግር ለሌብነታቸው ስለሚመች ጉባኤ ከሌለ ማምታታታት እንደማይችሉ አሳይቻለሁ። ይሁን እንጂ ጊዜያዊውን ዝምታ ተከትሎ የአየር ባየር ነቢያት ነን ባዮች ፈሉ። ጊዜው የሚድያ ስለሆነ ማንም ካሜራ ወይም ካሜራና ኮምፒዩተር ያለው ወይም ስልክና የኢንተርኔት ግንኙነት ያለው ሁሉ ሰባኪም፥ አስተማሪም፥ ተንባይም መሆን ቻለ። ፈታሽ የለ፤ ጠያቂ የለ፤ መርማሪ የለ፤ ማን ነህ? ማን ነሽ? ባይ የለ፤ ኬላ የለ፤ አጥር የለ፤ አጥር ሰበር፥ ኬላ ሰበር ተንባዮች በዙ። እልፍ ሰባኪዎችና ከነዚያም ብዙ ሐሰተኛ አስተማሪዎች፥ ሐሰተኛ ነቢያት፥ ሐሰተኛ ሐዋርያት ፈሉ። እንደ እንጉዳይ፤ ያለ ከልካይ ፈሉ። ብዙዎች ክርስቲያኖች ደግሞ ሁሉን ማመን ብቻ ሳይሆን፥ ሁሉንም በቀላሉ ያምናሉ። መጽሐፍ ቅዱስ የከፈተ ሁሉ እውነት ተናጋሪ ይመስላቸዋል። ከብዛታቸው የተነሣም ሰው ደግሞ ዓይን አዋጅ ሆነበት፤ ሁሉ ልክ መሰለው።

አሳቾቹ ደግሞ አንዳንዴ እውነት ይናገራሉ፤ ያጠኑትን ካልሆነ ግምት ስለሆነ የሚናገሩታንዳንዱ ይሠራላቸዋል። ደግሞ ገዳይ መርዝ ይቀይጣሉ፤ ይቀላቅላሉ። ያኔ ከየገስት ሃውስና ከየጉባኤው የሚሰበስቡትን የሰዎችን ፕሮፋይል አሁን ከየፌስቡኩና ከየሌሎች አካውንቶች ያነብቡና መተንበይ ነው። እና ሰው ያገኘውን ሁሉ መብላት፥ መብላት፥ መብላት። የተበላ ነገር ደግሞ ትንሽ ቆይቶ ነው ወይ ወደ ላይ፥ ወይ ወደ ታች የሚያደርገው። እና በሽተኛ በዛ። ይህ በሽታ በጣም እና በቀላሉ ተላላፊ ነው። እንደ ራሱ እንደ ኮሮና። ሐሰተኞቹም ያለ ከልካይ፥ ያለ ታዛቢ በዙ፤ ይህ ችግር ነው፤ ይህ ጉዳት ነው።

## 3. የአገልጋዮች ጉዳት

ጤናማዎቹ አብያተ ክርስቲያናትም እየተጎዱ መሆናቸውም ታይቷል። አገልጋዮች የሚከፈላቸው እየጠፋ የተቸገሩባቸው አሳዛኝ ሁኔታም ታይቶአል። የአገልጋዮች መጎዳት በአካል ተገናኝቶ ማምለክና ማገልገል በሌለባቸው ያላደጉ አገሮች አብያተ ክርስቲያናት በቴክኖሎጂው መገናኘትም ስለሌለ አገልግሎትም የለም። አገልግሎት

ከሌለ እንደ ተግባርና እንደ ሥራ ተቆጥሮም ቢሆን የሚታሰብ ክፍያም የለም። እና የቤተ ክርስቲያን ተከፋይ የሆኑ አገልጋዮች ተጎዱ። ድንኳን ሰፊ አገልጋዮች ሥራም ሙያም ስላላቸው ትንሽ የሚወላዱበት ዕድል ኖሯቸዋል። ብዙዎች የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ግን ተጎድተዋል።

በሰለጠኑት አገሮች ኢኮኖሚውም ቴክኖሎጂውም የተራመደ ስለሆነ ላለመጎዳትና ከጉዳት በፍጥነት ለማገገምም የተመቻቸ ነው። ለቤተ ክርስቲያን መስጠት ቀድሞም ኤሌክትሮኒክ መሆኑ፥ ከባንክ በቀጥታ እየተቆረጠ መሰጠቱ፥ እና የመሳሰሉት ቀድሞም ስለተለመዱ ችግሩ አስደንጋጭ አልሆነም። በአገራችንና አገራችንን በመሰሉት አዳጊ አገሮች ግን ጉዳቱ ሰፊም፥ ጥልቅም፥ ፈጣንም፥ አስደንጋጭም ነው የሆነው።

ወረርሽኙ ከጤንነት ቀውስ ቀጥሎ ያደረሰው ጉዳት የኢኮኖሚው ጉዳይ ነው። ባደጉት አገሮች እንኳ በኢኮኖሚ መመታት ከፍተኛ ቀውስ አስከትሏል። ብዙ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች፥ የንግድ ድርጅቶችና ሕዝባዊ ተቋማትንም ጨምሮ የአገልግሎት መስጫዎች ለተወሰነና ላልተወሰነ ጊዜ ተቋርጠዋል፤ ተዘግተዋል። ብዙ ሚሊየኖች ከሥራ ገበታ ለጊዜው ወይም ለዘለቄታው ተፈናቅለዋል። አንዳንድ አገልግሎቶች እንዳይሞቱ መንግሥት የድጎማ በጀት (stimulus bill) መድቧል። ለዜጎችም፥ በተለይም ለተፈናቀሉት መንግሥት የተለየ የድጎማ በጀት አፍስሷል። ይህ አቅማቸው በዳበሩ አገሮች ነው። በአዳጊ አገሮች እነዚህን ማድረግ የሚቻል ቀርቶ የሚታሰብም አይደለም። አቅም የለም።

የጤንነት ቀውስ የምጣኔ ሀብት ቀውስ ፈጥሯል፤ ገናም በሰፊው ሊፈጥር ይችላል የሚል ስጋት አለ። የምጣኔ ሀብት ቀውስ ከማኅበራዊ ቀውስ ጋር ሩቅ አይደለም። እነዚህ ሁለቱ ደግሞ ከፖለቲካ ቀውስ ጋር የተቆራኙ ናቸው። በአንድ በኩል ይህ ጊዜ የወረርሽኝ ጊዜ ብቻ ይመስለኛል። በሌላ በኩል ግን፥ ቀደም ሲል እንዳልኩት እንዳልኩት ይህ ጊዜ የፍተሻ ጊዜም ይመስለኛል። ምጣኔ ሀብት ሲቃወስ ቤተ ክርስቲያን ተነጥላ ከለላ ውስጥ ትቆያለች ማለት አይቻልም።

በኮሮና ምክንያት በአዳጊ አገሮች ባሉ አብያተ ክርስቲያናት በተለይ አገልጋዮች መጎዳታቸው በጣም ግልጽ ነው። ይህ ጉዳይ እንደገና ሊታሰብበት የተገባው ጉዳይ ነው። በኔ መረዳትና ከልምድም እንዳለፍኩበት አገልጋዮች ድንኳን ሰፊዎች ቢሆኑ ይመረጣል። ድንኳን ሰፊ አገልጋይነት መደነቅና ማሸብረቅ፥ መለመድና መደረግ፥ መደገፍና መበረታታትም አለበት። ጳውሎስ በሐዋ. 20፥33-34 እንዲህ አለ፤ *ከማንም ብር ወይም ወርቅ ወይም ልብስ አልተመኘሁም፤ እነዚህ እጆቼ በሚያስፈልገኝ ነገር ለእኔና ከእኔ ጋር ላሉት እንዳገለገሉ እናንተ ታውቃላችሁ። እነዚህ እጆቼ* ሲል በእጁ

ሠራተኛ መሆኑን መናገሩ ነው። በሐዋ. 18፥1-3 ይህንን ተግባሩን እናገኛለን። ጳውሎስ ድንኳን ሰፊ አገልጋይ ነበረ።

ይህ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች መኖር የለባቸውም ማለት አይደለም፤ ያስፈልጋሉ። እነዚህ አገልጋዮች ታዲያ ሸክምም፥ ትምህርትም፥ ጸጋም፥ ጥሪም ያላቸው ሰዎች መሆን አለባቸው። ይሰመርበት፤ አራቱም ንጥረ ነገሮች ያሏቸው ሰዎች መሆን አለባቸው። በሚያሳዝን መልኩ አንዳንድ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች የሚባሉት ሰዎች 'አገልግሎት' የሚሉትን ነገር ቀላልና አቋራጭ የገንዘብ ማግኛ አድርገው የሚያዩ ናቸው። አንዳንዶች ትምህርት የጠጠረባቸው ናቸው። እነዚህ ከአገልጋይነት ይልቅ አውደልዳይነት እንደሚበዛባቸውም የታወቀ ነው። አንዳንዶቹ እንዲያውም ዱርዬዎች ናቸው፤ ሐሰተኛ ሆነው አገሩን የሞሉትና የቤተ ክርስቲያን በዝባዥ የሆኑት እነዚህኛዎቹ ናቸው። እነዚህ ከአራቱ የአገልጋይ ንጥረ ነገሮች አንዱ ላይ፥ ጥሪ ላይ ያሰምሩና፥ 'ጌታ ጠርቶኛል' ይሉና፥ የሐኬት እንጀራ መብላት ይጀምራሉ። ይህኛው 'ጥሪ' የሚባለው ደግሞ በቀላሉ ተፈትሾ ልክ ነህ ወይም አይደለህም የሚባል አይደለም። ደግሞም እግዚአብሔር ጠራኝ ሲባል፥ 'አልጠራህም' ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መጣላት ይመስላልና ፍርሃት አለበት። ትምህርት የምትባለው ነገር ስትነሣ ጠያቂም ተጠሪም ይሸመደመዳሉ። ብዙዎቹ የመድረክ የጉባኤ አስተናጋጅና አስመጋቢ ሆነው ይቀራሉ።

አንዳንዶች ደግሞ የሙሉ ጊዜ አገልግሎት ሥልጣንን መለማመጃቸውና ገንዘብን መሰብሰቢያ፥ ወይም የጡረታ ዋስትና አድርገው ዘመናቸውን የሚገፉ ናቸው። መተካት የሚባል ነገር አይታሰብም። በተለይ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም በሌላ መስክ ሲሠሩ ኖረው ለጡረታ ሲቃረቡ ተጠራን የሚሉ፥ ሥራ አቁመው ወደ አገልግሎት የሚገቡ ሰዎች ሥራቸውን ሳይተዉ ቢያገለግሉ ጥሩ አርዓያ መሆን ይችሉ ነበር። ሌሎች ወጣቶችም እየሠሩ እንዲያገለግሉ ጥሩ ምሳሌ ይሆኑ ነበር። አገልጋይነትን መኖሪያ ከማድረግ ይልቅ የእውቀት፥ የእጅ ጥበብ፥ የንግድ፥ የሌላም መስክን መሰማሪያ አድርጎ ማገልገል እጅግ ጠቃሚ ነው። አገልጋይነቱ እኮ አይቀርም፤ በሥራ መስክ መሳተፍ ደግሞ ይበልጥ ትጉህ እንደሚያደርግ፥ ይበልጥ ፍሬያማ እንደሚያደርግ፥ ይበልጥ ኃላፊነትን እንደሚጠይቅና ዋጋም እንደሚያስከፍል በሁለቱም መስመሮች እንዳገለገለ ሰው መናገር እችላለሁ።

እርግጥ ነው፤ የሥራና የአገልግሎት ሚዛን፥ የአገልግሎትና የቤተሰብ ሚዛን መጥጠበቅ አለበት። ሆኖም፥ ለሌላም የተረፉት እነ ጳውሎስ ምሳሌዎቻችን ናቸው። በቀድሞዎቹ የአገራችን አብያተ ክርስቲያናት ያገለገሉት አባቶች አብነቶቻችን ናቸው። በእርሻ ጊዜ አርሰው፥ ዘርተው፥ አርመው ለወንጌል እየዘመቱ፥ በአዝመራ ጊዜ ተመልሰው ያጭዱ፥ ይወቁ፥ እጎታና ጎተራ ያገቡ የነበሩ ገበሬ ወንጌላውያን ምስክሮቻችን ናቸው። በአሁኑ ጊዜ የቻይና ቤተ ክርስቲያን በዓለም ካሉት አብያተ ክርስቲያናት በፍጥነትና በጥራት

እያደገች ያለች ቤተ ክርስቲያን ናት ነው የሚባለው። በዚያው ልክ አገልጋዮች ድንኳን ሰፊዎች ናቸው። ይህ ከሆነ ምንም ቢፈጠር የሚያስደነግጥ፥ የሚያስበረግግ ነገር አይኖርም። መኖሪያችንና መታመኛችን የዘላለም አምላክ መሆኑን ሳንረሳ እየሠሩ ማገልገል ውብ ጣዕም አለው። ከጉዳትም መትረፊያ ይሆናል።

## እናስ ምን ይሁን? ከዚህ በኋላስ? እንዴት እንኑር?

'ክርስቲያን እና ኮሮና' በሚል ርእስ የምንካፈለው የዚህ ሰፊ አሳብ የመጨረሻውና መደምደሚያው አሳብ፥ ከዚህ በኋላስ ምን ይሁን? እንዴት እንኑር? እንዴት እንቀጥል? የሚለው ነው። 'እና ምን ይፈጠር? ታዲያ ምን ይሁን?' የሚለው ጥያቄ አሳብ ላይ እናተኩራለን። የነዚህ ጥያቄዎች መልሶች ቀድሞም በየክፍሉ በከፊል ተወስተዋል። ለመደምደሚያ ግን ተግባራዊ ግንዛቤዎች ላይ እንደገና ማተኮርና ተግባራዊ ብቻ ሳይሆኑ ክርስቲያናዊ ግንዛቤዎችም ላይ ማተኮሩና መጨረሱ ተገቢ ነው።

### እግዚአብሔር አለ።

ኮቪድ-19 በፈረንጆች 2020 (በኛ 2012) የዓለምን መልክ የቀየረ ክስተት ነበር። ነበር ሆኖ አልቀረም አሁንም አለ። ከዚህ በኋላ ምን ያህል እንደሚቆይም አናውቅም። በዚህ አስጊና አዋኪ ጊዜ፥ 'እግዚአብሔር የት ነው ያለው?' ብለው የሚጠይቁና እርሱ ራሱም ኳራንቲን የገባ የመሰላቸው ሰዎች አልጠፉም፤ ወይም አሉ። እግዚአብሔር ዛሬም እዚያው ነው። ዛሬም በዙፋኑ ላይ፥ ዛሬም በተቀደሰ መቅደሱ ነው። እግዚአብሔርን በትላልቅና በጥቃቅን ነገሮችና ምክንያቶች ሕልውናውን መጠርጠር የለብንም፤ ይህ የአማኝ ጠባይ አይደለም። የሆነው ቢሆን እርሱ ሁሌም እርሱ መሆኑን መርሳት የለብንም።

### አንፍራ።

ስለ ፍርሃት ስንካፈል እንዳልኩት ማዕበሉ ይናወጣል፤ ጌታ ግን በታንኳዋ አለ። ትልቁ ነገር የጌታ በታንኳዋ መኖር ነው። በ1912 የተሠራችውና 'ማንም፥ እግዚአብሔርም እንኳ ሊያሰጥማት የማይችል መርከብ' ተብላ የነበረችውና ገና በመጀመሪያው

የሙሽርነት ጉዞዋ (maiden voyage) የሰጠመችው ታይታኒክ፥ ዝነኛ መርከብ ነበረች። በወንጌል ውስጥ የተጻፈችው ጌታ የነበረባት ጀልባ ከታይታኒክ ጋር ስትወድደር ምናምንቴ ነገር ናት። ነገር ግን በዚያች ደካማ ነገር ውስጥ፥ በውስጧ የማዕበልና ወጀብ አዛዥ ብቻ ሳይሆን፥ የሁሉ ፈጣሪ ጌታ ነበረ። ስለዚህ ያለመስጠም ዕድሏ 50-50 ወይም 50/100 ሳይሆን 100/100 ነው። እንኳን ታንኳ ምድርም ብትነዋወጥ ጻድቅ መታመኛ አለው። *አምላካችን መጠጊያችንና ኃይላችን፥ ባገኘን በታላቅ መከራም ረዳታችን ነው። ስለዚህ ምድር ብትነዋወጥ፥ ተራሮችም ወደ ባሕር ልብ ቢወሰዱ አንፈራም።* መዝ. 46፥1-2። ልንፈራ እንችላለን? አዎን። ነገር ግን መታወክና መጨነቅና መሳቀቅ አለብን? የለብንም። ጭንቀትና ፍርሃታችንን በእርሱ ላይ እንጣል። *እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት።* 1ጴጥ. 5፥7። በእርሱ እንታመን። በኛ ላይ የእርሱ ፈቃድ ሁሌም ለበጎ እንደሆነች እርግጠኞዎች ሆነን እንወቅ።

ማዕበሉ ግን ይኖራል። የጌታ በታንኳዋ መኖሩ ማዕበሉን አልከለከለም። ዛሬም እንደዚያው ነው፤ አይከለክልም፤ እኛን ግን በማዕበሉ ውስጥ እያለን ያረጋጋናል። ፍጥረትም ተፈጥሮም በሚቃትትበት በወደቀች፥ በተረገመች ዓለም ነው ያለነው። ጌታ ከመምጣቱ በፊት ባሉት ዘመናት ደግሞ እነዚህ የሚረብሹ፥ የሚያውኩ ነገሮች ይብሱን እየከፉ፥ እየተበላሹ እንደሚሄዱ ነው ቃሉ የነገረን። የምድር መናወጦች፥ ራቦች፥ ቸነፈሮች፥ ጦርነቶች፥ ቁጣዎች፥ ወረርሽኞች፥ መቅሰፍቶች ይሆናሉ። ኮቪድ-19 ከብዙ ወረርሽኞች አንዱ ነው። አንድ ቀን ጌታ ይመጣል፤ ያኔ፥ ጽድቅ እንደ ጅረት ይፈስሳል። ከጌታ ጋር ለዘላለም እንኖራለን። ይህ ተስፋ ካለን ከመከራውና ከወረርሽኙ ባሻገር አቅንተን ማየት ይቻለናል። ሕይወትም ሞትም ያስፈራሉ፤ ግን ተስፋ ያለን ሰዎች ነን። ማዕበሉ ይኖራል፤ መታመናችን ግን ከሁሉ በላይ ይቀጥል።

## እንጽዳ፥ እንሸፈን፥ ርቀትን እንጠብቅ።

ከኮቪድ ያገኘናቸውን መልካም ልምዶችና ልምምዶች እና ትምህርቶች ይዘን እንቀጥል። መታጠብ፥ መሸፈን፥ ርቀትን መጠበቅ። እነዚህ ሦስቱ ዋናዎቹ ናቸው።

እጅ መታጠብን የመሰለው ንጽሕናን መጠበቅ መልካም ባህል ነው። የእጅ መታጠብ በተለይ በማደግ ላይ ባሉት አገሮች ሌሎችንም ተዋሃስያንና በሽታዎች ለመከላከል ምክንያት የሆነልን ነገር ነው ተብሏል። ከብዙ ነገሮች ጋር እንነካካለን። ከኮሮና ጋር ከተያያዙ ነገሮች ብቻ ሳይሆን ከብዙ ጎጂ ጀርሞችም ጋር እንነካካለን። እና በመታጠባችን ከሌሎችም ተላላፊ ነገሮች ተጠብቀናል ማለት ነው። ከእጃችን ጋር

ደግሞ፥ በየቀኑ ልባችንን፥ አእምሯችን፥ ሕሊናችንን መታጠብም፥ ማጽዳትም ልማዳችን ይሁን፤ ይህንንም አንርሳ። የውጪ ብቻ ሳይሆን የውስጥ ንጽሕናችንም ይጠበቅ።

መሸፈንም መልካም ነው። ሲያስለንና ሲያስነጥሰን ተጠንቃቂዎች መሆናችን ይቀጥል። ኮሮና ከጠፋ በኋላም እንኳ ይቀጥል። ይህም ከብዙ ተላላፊ የአየር ተላላፊዎች ጥሩ መከላከያ ነው። በካይ ቆሻሻ አየርና ቫይረስ ወደ አፋችንና አፍንጫችን እንዳይገባ እንደምንሸፈን ነፍስና መንፈስን የሚያረክሱ ቆሻሻዎች ወደ ውስጣችን እንዳይገቡ ተጠንቃቂዎች ደግሞ እንሁን። ወደኛ ከሚገባው ብቻ ሳይሆን ከኛ የሚወጣውም ሌሎችን እንዳይበክል እንጠንቀቅ። 'ሰውን የሚያረክሰው ከውስጥ የሚወጣው ነው' ብሏል ጌታ አይደል? ማስክ ስናስብ ይህንንም እናስብ። ቆሻሻ ወደ ወስጣችንም እንዳይገባ፥ ከውስጣችንም እናይወጣ እንጠንቀቅ።

መራራቅም መልካም ነው። ለጥንቃቄ ተብሎ የተደነገጉ አካላዊና ማኅበራዊ መራራቆች ሰዎችን ከሰዎች ጋር ማራራቅ ጀምረዋል። ወሸባ መግባት ዱሮም የነበረ ነገር ነው። የአንኮበር ገዢ የነበሩት አዛዥ ወልደ ጻድቅ በዐፄ ምኒልክ ዘመን ክፉ ቀን የተባለው ወረርሽኝ ወቅት የሚገርም ነገር አድርገው ነበር። ከበዕውቀቱ ሥዩም፤ ከአሜን ባሻገር፤ የሰፈረው እንዲህ ይላል፥ "ክፉ ቀን የተባለው ዘመነ ወረርሽኝ ወቅት በበሽታው መጠቃቱን ሲያውቅ [አዛዥ ወልደ ጻድቅ] ወደ ሌላ ሰው ላለማዛመት ዱር ውስጥ ለብቻው ኖሮ፥ ሲድን ተመልሷል። አደን የተባለው የፈረንሳይ መንገደኛ፥ 'በጣም ብሩህ አእምሮ ያለውና ለወዳጆቹ የታመነ' ብሎ ያመሰግነዋል።" ሲል ጽፏል። (ገጽ 210-211።) መራቅ መልካም ነው። ከዚህ ጋር ደግሞ፥ ሌሎች ራቁ የተባልናቸው ነገሮች አሉ፤ ከነዚያስ እየራቅን ነን? በዚህ አጋጣሚም ራቁ ከተባልናቸው ነገሮች መራቅንም መለማመድ አንርሳ፤ እንለማመድ። ጥቂት ራቁ የተባልናቸውን ነገሮች ላንብብ፤

1ተሰ. 5፥22 *ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር ራቁ።*

*ነገር ግን ለዚህ ዓለም ከሚመችና የአሮጊቶችን ሴቶች ጨዋታ ከሚመስለው ተረት ራቅ።* 1ጢሞ. 4፥7

1ጢሞ. 6፥4-5፤ *እግዚአብሔርን መምሰል ማትረፊያ የሚሆን በመሰላቸው ሰዎች ይገኛሉ። እንደነዚህ ካሉት ራቅ።*

2ጢሞ. 2፥16 *ነገር ግን ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍ ራቅ፤*

*ጠብን እንዲያመጣ አውቀህ ከሰነፎችና ካልተማሩ ምርመራ ራቅ፤* 2ጢሞ. 2፥23።

ከነዚህ በራቅን ልክ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር የመቀራረብስ ነገራችንስ እንዴት ነው? ለብቻ እኛና እኛ፥ እና ለብቻ ከጌታ ጋር የመሆን የጥሞና ጊዜስ ጉዳይ? ከጌታ ቃልና ከቃሉ ጌታ ጋር የመሆን ጊዜስ? ወደ እርሱ እየቀረብን ነን? ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ላለው፥ ግን ወደሚቀረበው፥ ሊቀረብ ደግሞ ወደተገባው፥ እየቀረብን ነን?

*መዝ. 34፥5 ወደ እርሱ ቅረቡ ያበራላችሁማል፥ ፊታችሁም አያፍርም።*

*ያዕ. 4፥8 ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል።*

## በሐሰተኞች አንወናበድ።

ሐሰተኞች፥ 'ኮሮና በመጋቢት ወር፥ በግንቦት ወር ይጠፋል፥ በእጄ ዱቄት ሆነ፥ ምናምን' እያሉ ዋሽተዋል። ለውሸታቸው ማብቂያ የለውም። ሐሰተኞች፥ ተንባዮች፥ ቃልቻዎች ጠፍተው አያውቁም፤ ወደፊትም አይጠፉም። አንስማቸው፤ አንፍራቸው። ፍርሃት የሐሰተኛ ነቢያት የምግብ ጠረጴዛና የችርቻሮ መደብራቸው ነው። ወደ ሐሰተኛ ነቢያት ከሚሄዱ ሰዎች ምናልባት 100% ባይባል እንኳ ከ95% በላይ ወይ አንድ ወይ ሌላ ፍርሃት ያለባቸው ሰዎች ናቸው። ሐሰተኞችን አሁንም ሁሌም አትስሟቸው። እነዚህ ሰዎች ሐሰተኞች መሆናቸውን የምናውቀው ኮሮና ከመምጣቱ ከወራት ወይም ዓመታት በፊት አንዲትም ቃል ስለ ኮሮና አልተነፈሱም። እውነት፥ እንደሚሉት ነቢያት ቢሆኑ ኖሮ ኮቪድ-19 መላውን ዓለም ጥርቅም አድርጎ እንደሚዘጋው ቀድመው በስሙ ጠርተው አይናገሩም ነበር? ምንም አልተናገሩም፤ ማንም አልተናገረም። ከመጣ በኋላ ነው ከኛ ጋር መምጣቱን ያወቁት፤ መናገር የጀመሩትም ዓለምን ካዳረሰ በኋላ ነው። ከዚያ በማስፈራራት ሊነግዱ ሞከሩ። ውሸታሞች ናቸው፤ እንደ ስማቸው ሐሰተኛ ነቢያት ናቸው፤ አንወናበድ።

ትንቢትን በተመለከተ፥ ወደፊት የሚሆነውን ነገር በግልጽና በማያሻማ ቃል የሚናገረውና የተናገረው ነቢይ ቅዱስ ቃሉ ብቻ ነው። አስቀድሞ የተነገረውን ትንቢት ንድፍ ተከትለን የሚሆንትን ነገሮች መተለምና መጠባበቅ ይቻለናል። ነገር ግን የዛሬ ዓመትና የዛሬ ስድስት ወር የሚሆኑ ነገሮችን የሚናገሩ ሰዎች ዛሬ የሉም። ነሲባውያን እና ግምታውያን የሉም ማለቴ አይደለም። እነዚህ በመቶዎች የሚቆጠሩ አሉን። በእርግጥ እና እርግጠኛ ሆኖ ስለ ወደፊቱ የሚናገር 'ነቢይ' የሚባል እውነተኛ ሰው ዛሬ የለም። <u>እርግጠኛ</u> ይሰመርበት። ነሲባውያኑ ታዲያ በድፍረት ሲናገሩ ወደ ከርሞና

ከዚያም ቀጥሎ ወዳለው ዓመት የደርሶ መልስ ቲኬት ተሰጥቷቸው ተነጥቀው ደርሰው አይተው የመጡ ይመስላሉ። አንወናበድ።

ከወዲያኛው፥ ብዙዎቻችን ከኖርንበት ትተነው ከመጣነው ዓለም ደብተራዎችና መጽሐፍ ገላጮች፥ ጠጠር ጣዮች፥ ሞራ ገላጮች እንደሚያደርጉት የመሰለ እኛምጋ እንዲህ ያሉ የቀለሉ ነገሮች የሚያደርጉ መጥተዋል። ግን እነዚህ የወደፊቱን የሚናገሩ ሰዎች አይደሉም። እንደዚህ ያሉ ነቢያት ኖረው ቢሆን ኮቪድ-19 መላውን ዓለም ጥርቅም አድርጎ እንደሚዘጋው ይነግሩን ነበር። ኮሮና ክንፍ እያበቀለ በነበረባቸው ወራት እኮ የኛ ነቢያት ተብዬዎች፥ 'የምንትስ ዓመት' እያሉ መስከረም 2012 ሲጠባ ጨፍረው አስጨፍረው ነበር፤ ከሦስት ወር በኋላ ነው ነገር ሁሉ ሲዘጋ፥ የእንትን ዓመታቸውም በሦስት ወር ሲጠናቀቅ የደነገጡት። ምን ያላሉት 'የምንትስ ዓመት' ነበረ? የከፍታው፥ የበረከቱ፥ የመጣሱ፥ የተከፈተ ሰማዩ፥ የንጋት ጮራው፥ የመውረሱ፥ ምን ያላሉት አለ? ያኔ የኮሮና ሽታውም፥ ሽውታውም አልነበራቸውም። ማዕዘኑ ላይ ደርሶም እንኳ አላዩትም፤ አያዩማ! በነዚህ ሐሳውያን አንወናበድ።

በእውነቱ ስለ ወደፊቱ የሚናገር ነሲባዊ ገማች እንጂ እርግጠኛ ነቢይ የለም እንጂ ኖሮ ቢሆንና ኮሮና እንደሚመጣ ሃቻምና በዚህ ጊዜ ነግረውን አውቀነው ቢሆን ኖሮ ከሰማንበት ጊዜ ጀምሮ እኮ ስንጨነቅም እንቆይ ነበር። አለመኖራቸው በጀን እንጂ! አንዳንዶቹ ደፋሮች እኮ፥ በምዕራቡ ዓለም፥ 'ጌታ በዚህ ቀን ይመጣል' እያሉ ስንት የውሸት አዋጅ አውጀው የስንቶችን ሕይወት አፍርሰዋል! በተለይ በ2ሺህ መግቢያ አካባቢ ስንቱ ከሰረ! ጌታ የሚመጣበትን ቀን እንኳን እነዚህ ውሸታሞች፥ ጌታ ራሱም አልተናገረም። መጪው እራሱ ያልተናገረውን የማይመጡቱ የሚገምቱት አገማመት ያስገርማል! ጌታ የሚመጣበትን ቀን ያልተናገረው ለኛ ማወቅ አስፈላጊያችን ስላልሆነ ነው። እንጂ፥ በ2024 የፋሲካ ቀን እመጣለሁ ቢል ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። እና ኮቪድ-19 የሚባል ወረርሽኝ በሚቀጥለው ዓመት ዓመት ይመጣና ብዙ ሕዝብ ይፈጃል የሚሉ ነቢያት አለመኖራቸው በጀን። ለአንድ ቀን አትጨነቁ ተብለን ለዓመት የሚያስጨንቁ እንዳይኖሩ ጌታ ማድረጉ፥ ይህ የእርሱ ኪነ ጥበብ ነው። በሐሳውያን አንወናበድ።

## በነገ አንጨነቅ።

ነገ የሚሆነውን አናውቅም። ነገ ምን እንደሚሆን አናውቅም እንጂ ነገ በማን እጅ መሆኑን ግን ፈጽሞም አንጠራጠር። አሳብ የለሾችና ግድ የለሾች እንድንሆን ሳይሆን ለነገ እንዳንጨነቅ ጌታ አስተምሮናል፤ ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ፤ ለቀኑ

ከፋቱ ይበቃዋል። ማቴ. 6፥34። ነገን ባለማወቃችን አንጨነቅ፤ አለመጨነቅ ብቻ ሳይሆን፥ እንዲያውም እንረፍ። ነገ የሚሆነውን ብናውቅ እኮ የባሰ ልንጨነቅም እንችላለን። እንዲያውም ከምንናፍቀው ይልቅ ልንሸሸው እንፈልግ ይሆናል። ግን አንጨነቅ። ሁላችንም፥ ከኛ ማናችንም፥ አንዳችንም፥ ነገን አናውቅም። ነገን ባለማወቅ ግን መታመናችን ይጨምር እንጂ አይቀንስ። በአዲስ ኪዳን ወደ ፊት የሚሆን፥ መቼ እንደሆነ ግን የማናውቀው አንድና ትልቅ ትንቢት አለ። ያም የጌታ መምጣት ነው። በናፍቆት እንጠብቀው። እስከዚያ ግን ያዕ. 4፥13-16 እንዳለው ለየቀኑ ኑሮአችን በእምነት እንኑር፤

*አሁንም፡- ዛሬ ወይም ነገ ወደዚህ ከተማ እንሄዳለን በዚያም ዓመት እንኖራለን እንነግድማለን እናተርፍማለን የምትሉ እናንተ፥ ተመልከቱ፥ ነገ የሚሆነውን አታውቁምና። ሕይወታችሁ ምንድር ነው? ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፋዋለት ናችሁና። በዚህ ፈንታ፥ ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ማለት ይገባችኋል። አሁን ግን በትዕቢታችሁ ትመካላችሁ፤ እንደዚህ ያለ ትምክህት ሁሉ ክፉ ነው።* ስለ ነገ አንመካ።

## እናገልግል፤ በዘመናችን ሁሉ በፊቱ እንቁም።

ብንኖር ወይም ስንኖር የእርሱ ነን፤ እናገልግለው፤ ለእርሱ ክብር እንኑር። ስንኖር የተደላደልን፥ የማንነቃነቅ፥ የጌታ ሥራ የበዛልን እንሁን። ቃሉ እንደሚል፤ 1ቆሮ. 15፥58 *ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥* ድካማችሁ በጌታ ከንቱ እንዳይሆን *አውቃችኋልና የምትደላደሉ፥ የማትነቃነቁም፥ የጌታም ሥራ ሁልጊዜ የሚበዛላችሁ ሁኑ።* ስንኖር እንዲህ እንኑር። መደላደል እና አለመነቃነቅ መታመን ነው። ስንኖር በመታመን እንኑር።

ስንኖር እናገልግለው። ስናገለግል በሰዎች ሳንታይም፥ ያለ ቲፎዞና ያለ አጃቢም፥ ያለ ጎሸታና አጨብጫቢም እናገልግል። በማኅበራዊ ወይም አካላዊ መራራቅ ምክንያት የጉባኤ ስብሰባዎች በቀሩበት ኮሮና እንደጀመረ ሰሞን የወቅታዊ የእስፖርት ጨዋታዎች በዓመቱ ውስጥ አስቀድሞም መርሐ ግብር የተያዘለት ጉዳይ ነውና ጨዋታዎችና ውድድሮች መቀጠል ነበረባቸው። ጨዋታዎች ሰዎች በብዛት የሚሰበሰቡበት ስለሆነና ያ ደግሞ ስለተከለከለ ውድድሮች በባዶ እስቴዲየም ነበር የሚደረጉት። ጨዋታዎቹን የሚያደምቁ ጭብጨባዎች የሉም፤ ጩኸትና ሁካታ የለም፤ ነጥቦች ግን ይቆጠራሉ፤ ሕጎችም ይከበራሉ፤ የሚያዩ የሉም ተብሎ ፋውል አይሠራም። ዳኛው ብቻ እያያቸው ሕጋዊ ጨዋታ ይጫወታሉ። በሚሊየን የሚቆጠር የቲኬት

ሽያጭ ገቢ ባይኖርም፥ ተመልካች ባይኖርም፥ ዳኛው እና ጥቂት ታዛቢዎች፥ ፊልም ቀራጮች፥ እና የተወሰኑ የስፖርት ተንታኞች ብቻ ባሉበት ውድድሮች ተካሂደዋል።

ይህን ሳይ አንዳንድ ሕዝበኛ ሰባኪዎቻችንን አሰብኩ፤ በተለይም ሰብኮ አደሮቹን አሰብኩ። አዳራሽ ሙሉ ሕዝብ እያስጨበጨቡ እያንጫጩ የሚያስጮኹትን፥ ጭር ሲል የማይወዱትን፥ ከማሳየት ይልቅ መታየት የሚናፍቃቸውን፥ መድረክ ሞልተው የሚንጎራደዱትን፥ ሳምንታዊ አዲስ ልብሳቸውን የሚያስመርቁትን፥ እነዚህን አሰብኳቸው። የሚያዩን ሲኖሩ እንደምናገለግለው የሚያዩን ሳይኖሩም እናገለግላለን? ዳኛው ብቻ እያየን እናገለግላለን? ገቢ ሲቀርም፥ ሙዳይ ሳይዞርም፥ መባ ሲቀንስም እናገለግላለን?

ማገልገል ማለት መቆም ነው፤ በፊቱ መቆም። *ልጆቼ ሆይ፥ በፊቱ ትቆሙና ታገለግሉት ዘንድ፥ አገልጋዮቹም ትሆኑ ዘንድ፥ ታጥኑለትም ዘንድ እግዚአብሔር መርጦአችኋልና ቸል አትበሉ።* 2ዜና 29፥11 በፊቱ የምንቆም ሰዎች ነን? በፊቱ መቆም ዕድል ነው፤ መታደል ነው። በፊቱ መቆምና በሰዎች ፊት መቆም የተለያዩ ናቸው። ከመጽሐፍ ቅዱስ በፊቱ የቆሙና መቆማቸውንም ያወቁ ሁለት ምሳሌዎች ልውሰድ። አንዱ ኤልያስ ነው።

ኤልያስ በፊቱ፥ በአምላኩ ፊት የቆመ ሰው ነበረ፤ *በገለዓድ ቴስቢ የነበረው ቴስብያዊው ኤልያስ አክዓብን፦ በፊቱ የቆምሁት የእስራኤል አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን! ከአፌ ቃል በቀር በእነዚህ ዓመታት ጠልና ዝናብ አይሆንም አለው።* 1ነገ. 17፥1።

*ኤልያስም፦ በፊቱ የቆምሁት የሠራዊት ጌታ ሕያው እግዚአብሔርን! እኔ ዛሬ ለእርሱ እገለጣለሁ አለ።* 1ነገ. 18፥15።

በአምላኩ ፊት የቆመ ሰው በሰዎች ፊት መቆም ይችላል። በሁኔታዎችም፥ በችግሮችም ፊት መቆም ይችላል። እንዲህ ያሉ ሰዎች የሚቆሙበት እግሮችም፥ የጀርባ አጥንትም አላቸው። ለሌሎቹም የብርታት ምክንያትና የብርታት አጋሪ ይሆናሉ። ብርታትና እምነት ልክ እንደ ፍርሃት ተላላፊም ነው።

የኤልያስ አገልጋይ የነበረውና ኋላ በስፍራው የእስራኤል ነቢይ የነበረው ኤልሳዕም ቋንቋው ብቻም ሳይሆን እርሱም እንደ ኤልያስ ነበረ። እንደ መንፈሳዊ አሳዳጊው ሁሉ መቆምን የቆመ ሰው ነበረ። በአምላኩ ፊት የቆመ ሰው፤

*ኤልሳዕም፦ በፊቱ የቆምሁት የሠራዊት ጌታ ሕያው እግዚአብሔርን! የይሁዳን ንጉሥ ኢዮሣፍጥን ያላፈርሁ ብሆን ኖሮ አንተን ባልተመለከትሁና ባላየሁ ነበር።* 2ነገ. 3፥14።

*እርሱም፦ በፊቱ የቆምሁት ሕያው እግዚአብሔርን! አልቀበልም አለ። ይቀበለውም ዘንድ ግድ አለው፤ እርሱ ግን እንቢ አለ።* 2ነገ. 5፥16።

በአምላካቸው ፊት የቆሙ ሰዎች ሕዝበኞች አይሆኑም። ሕዝባሞችም አይሆኑም። በሚያያቸው ፊት መቆምን ያወቁ ናቸውና ሁሌ የሚታዩ የመሆን ስሜትን የተጎናጸፉ

ናቸውና፥ 'ታየሁ ወይ? የምታይ ያለህ!' እያሉ አያገለግሉም። እርሱ አምላካቸው ያያቸዋላ! ያንንም ያውቃሉ።

ስንኖር እናገልግለው፤ በፊቱ እንቁም።

## ሞትን አንፍራ።

ስንኖር የማን መሆናችንን ብቻ ሳይሆን ስንሞትም የት እንደምንሄድ እናውቃለን። ብንሞት የት እንደምንሄድ እርግጠኛ ሆኖ የሚያውቅ እንደኛ ያለ ማንም ሕዝብ የለም። ስለዚህ ሞትንም አንፍራ፤ ነገ የሚሆነውን አናውቅም፤ ከነገ በስቲያ የሚሆነውን ግን እናውቃለን። በጌታ የሆንን እኛ፥ ከምድራዊ ኑሮአችን በኋላ የት እንደምንሄድ በእርግጥ እናውቃለን። መቼ እንደምንሞት አናውቅም፤ ከሞት ማዶ፥ ከሞት ባሻገር የሚሆነውን ግን እናውቃለን። የምናውቀው በግምት አይደለም፤ ከመካከላችን አንዱን ልከነው ሰልሎ ስለመጣም አይደለም። ሞቶ የተነሣ ጌታ ስላለን እና እርሱ የነገረን ነገር ስላለ አንፈራም።

ፊል. 1፥21-23 *ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ፥ ሞትም ጥቅም ነውና። ነገር ግን በሥጋ መኖር ለእኔ የሥራ ፍሬ ቢሆን፥ ምን እንድመርጥ አላስታውቅም። በእነዚህም በሁለቱ እጨነቃለሁ፤ ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፥ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና፤* አለ። እጅግ የሚሻል! ከሞት በስቲያ ያለው ሕይወት እጅግ የሚሻል መሆኑን የሚያውቅ ሰው ይናፍቃል እንጂ አይሳቀቅም።

## ተስፋን እናካፍል።

በመጨረሻ፥ ለሌሎች ላልዳኑት የምንዘረግጋ፥ ተስፋን የምናካፍልና ዘላለማዊውን የምንመሰክር እንሁን። ጌታ ዛሬ በመካከላችን ቢገኝ ምን ያደርግ ይሆን? ራሱን ከኛ ያርቅ ይሆን? አያርቅም። ያኔ ካደረገው ምንም የተለየ ነገር አያደርግም። ሰዎችን ለንስሐ ይጠራ ነበር፤ ወንጌልን ይሰብክና ያስተምር ነበር፤ ርኩሳን መናፍስትን ያወጣና ተአምራትን ያደርግ ነበር፤ ድውያንን ይፈውስ ነበር፤ የማይነክኩትንም ይነካ፥ የማይዳሰሱትንም ይዳስስ ነበር።

*እነሆም፥ ለምጻም ቀርቦ፦ ጌታ ሆይ፥ ብትወድስ ልታነጻኝ ትችላለህ እያለ ሰገደለት። እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና፦ እወዳለሁ፥ ንጻ አለው። ወዲያውም ለምጹ ነጻ።* ማቴ. 8፥2-3። ለምጻም ከሩቅ ሆኖ ርኩስ ነኝ፤ ርኩስ ነኝ እያለ እንዳይነኩት ይከላከላል

እንጂ ቀርቦ ጥያቄ አይጠይቅም፤ ሉቃ. 17፥11-19 እና ዘሌ. 13፥45-46። ፈውስን ቢጠይቅም እንኳ በሌላ ሰው መድዳሰስ የለበትም። ለምጽ መተላለፍ ብቻ ሳይሆን መርከስም ያለበት ደዌ ነው። ለዚህ ነው በሩቅ የሚቆሙት። ይህ ማኅበራዊና አካላዊ መራራቅ ዱሮም የነበረ ጉዳይ ነው።

ጌታ የሚያረክሱትን ዳስሶ ነበር፤ በሌሎች የሚያረክሱም ተዳስሶ ነበር። *እነሆም፥ ከአሥራ ሁለት ዓመት ጀምሮ ደም የሚፈስሳት ሴት በኋላው ቀርባ የልብሱን ጫፍ ዳሰሰች፤ በልብዋ፦ ልብሱን ብቻ የዳሰስሁ እንደ ሆነ፥ እድናለሁ ትል ነበረችና። ኢየሱስም ዘወር ብሎ አያትና፦ ልጄ ሆይ፥ አይዞሽ፤ እምነትሽ አድኖሻል አላት። ሴቲቱም ከዚያች ሰዓት ጀምራ ዳነች።* ማቴ. 9፥20-22። ይህች ሴት ደም ይፈስሳት የነበረች ሴት ናትና በአሮጌው ኪዳን ሕግ መሠረት ርኩስ ናት፤ የነካትም፥ የነካችውም ይረክሳል። ጌታ የሚያረክሱትን ለመንካትም በሚያረክሱት ለመነካትም እሩቅ አልነበረም።

ከጥቂት ዓመታት በፊት ያነበብኩት የJohn Ortberg *God Is Closer Than You Think* የተባለ መጽሐፍ ውስጥ የአባ ዴሚየን (Father Damien) ትንሽ ቅንጫቢ ታሪክ ተጽፎአል። ይህ ከ1840-1889 (ቀደም ሲል የጠቀስኩት የአገራችን ወህኒ አዛዥ ወልደ ጻድቅ በኖሩበት ዘመን ማለት ነው) የኖረ በሞሎካይ (ሐዋይኢ) ውስጥ የሚገኝ ካላዋኦ የሚባል መንደር ያገለገለ መነኩሴ ነው። ያገለግላቸው የነበሩት በተለምዶ ለምጽ የምንለው ቢስ ገላ ወይም ቁምጥና የያዛቸውን ሰዎች ነበር። ደዌው ተላላፊ ስለሆነ ሰዎቹ ከዚያ መንደር አይወጡም እዚያው ይኖራሉ፤ እዚያው ይሞታሉ። እንዲህ ያለው የኳራንቲን መኖሪያቸው leper colony ይባላል፤ የለምጻሞች መንደር ማለት ነው።

አባ ዴሚየን በመካከላቸው ለ16 ዓመታት አገለገለ። ወንጌል ሰበከ፤ ትምህርት ቤት ከፈተ፤ ክሊኒክ ከፈተ፤ ያክማቸው ጀመር። በጉንድሽ እጆቻቸው ከሠሩት ዳስ እንዲወጡ ቤቶችን ሠራላቸው፤ ሲሞቱ ተጎትተው አፈር እንዳይለብሱና በክብር እንዲቀበሩ ሳይቀር እስከ 2ሺህ የመቀበሪያ ሳጥኖች በገዛ እጁ ሠርቶላቸዋል። ሰፈራቸው የሙታን ሳይሆን ሕይወት ሕይወት እንዲሸት አደረገ። ይህን ሲያደርግ እነዚያን ለምጻሞች ወድዶአቸው ነበርና ከእነርሱ ተለይቶና ከርቀት ሳይሆን በመካከላቸው ሆኖ ነበር ያገለገላቸው።

ከዓመታቱ በመጨረሻዎቹ፥ አንድ የገና በዓል ቀን ቃል ሊያካፍል ተነሥቶ ሲቆም መጀመሪያ የተናገራቸው ሁለት ቃላት በብዙ መጻሕፍት ውስጥ የተጠቀሱና በብዙ ተናጋሪዎችም የተነገሩ ቃላት ናቸው። እነዚህ ሁለት ቃላት 'እኛ ለምጻሞች . . .' ብሎ የጀመረባቸው ቃላት ናቸው። "We lepers . . ." በአገልግሎቱ መጨረሻ አባ ዴሚየን

ለምጻሞችን የሚረዳ ሐኪምና አስተማሪና የወንጌል ሰባኪ ብቻ ሳይሆን ራሱም ለምጻም ሆኖ ነበር። በመረጣቸው ሰዎች መካከል አገልግሎ እንደነሱ ሞተ። 'እኛ ለምጻሞች' ብሎ መስሏቸው፥ ተመሳስሏቸው፥ ሆኗቸው ሞተ።

ያ የመጀመሪያው አዳም ከፈጣሪ አምላኩ ፊት እንደሸሸና እንደጠፋ እግዚአብሔር ሊፈልገው እንደወደደ፥ ጌታ በሥጋ ሲመጣም ያንን ሊያደርግ ነው የመጣው፤ *የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና አለው።* ሉቃ. 19፥10። የሰው ችግር ጦርነትና ረብሻ፥ ወረርሽኝና በሽታ፥ ድኅነትና እጦት አይደለም። እነዚህ ነገሮች ሊገድሉም ላይገድሉም ይችላሉ። የሰው ችግር ሁሌም ገዳይ የሆነውና ዋጋው ሞት የሆነው ኃጢአት ነው። ኮሮና ሊገድልም ላይገድልም ይችላል። ይህንን ክፍል እስካካፈልኩበት እስከ ማርች 6፥ 2021 ድረስ በመላው ዓለም የተያዙ 116.8 ሚሊየን (116,824,161) ሲሆኑ፥ የሞቱ 2.5 ሚሊየን (2,594,675) ናቸው። የሞቱ ከመቶ ሲሰላ ወደ 2% ነው። ኃጢአት ግን 2% ወይም 20% ወይም 50% ሳይሆን 100% ይገድላል። ኃጢአት 100% ገዳይ ነው። በሉቃ. 13፥1-5 ጌታ ይህን አስተማረ። *ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንደዚሁ ትጠፋላችሁ።* አላቸው። ሁላችሁ።

ጌታ የመጣው ከሩቅ ሊያግዘን ሳይሆን፥ ከእኛ እንደ አንዱ ሆኖ ነው። በኃጢአት ለተበከለ ክቡር ሰው ከዚያ፥ *ሥጋ* ከለበሰው አምላክ፥ የእግዚአብሔር ልጅና የሰው ልጅ፥ ያነሰ መድኃኒት አልተገኘለትም። ሊገኝለትም አይችልም። ኃጢአት ከቫይረሶች ሁሉ የሚበልጠው ገዳይ ነው። ጌታ ያንን ቫይረስ ለመዋጋት፥ ለዚያ ቫይረስ መድኃኒት እንዲሆን ነው በሥጋ የመጣው። በሥጋ የመምጣቱ ዋናው ጉዳይ ደግሞ በመስቀል መዋሉና መሞቱ ነው። ያ ሞት ትክክለኛውና ተገቢው ሞት መሆኑን ያረጋገጠልን ትንሣኤው ነው። ያ ቫይረስ ኃጢአት ነው። ኃጢአት ሁሉን የበከለ በካይ ነው። በአዳም ውስጥ ሆነን ሁላችንም ወድቀናል፤ በራሳችን በደልም ኃጢአተኞች ነን። ማንም ኃጢአተኛ ያልሆነ የለም። ሮሜ 3፥23-24 እንዲህ ይላል፤ *ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤ በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ።* ሁሉ ማለት ማንም ያልተረፈበት ሁሉ ነው። ሁላችንም ተበክለናል። ሁላችንም ረክሰናል። ሁላችንም ኃጢአተኞች ነን።

ለሌሎች ላልዳኑት የምንዘረግጋ፥ ተስፋን የምናካፍልና ዘላለማዊውን የምንመሰክር እንሁን ያልኩት ይህንን ነው። ወንጌል ለሰው ውድቀት ብቸኛው መፍትሔ ነው። ላልዳኑት የምለው ቀላልና ግልጽ ነገር ይህ ነው፤ ሕይወት ዘላለማዊት ናት። በዚህች ምድር በሥጋ ብዙ ኖርን ከተባለ የምንኖረው ሰባና ሰማንያ ዓመት ብቻ ነው። ሕይወት ግን ያ ብቻ አይደለም። ሕይወት ዘላለማዊት ናት።

ከሥጋ ኑሮ በኋላ ሞት አለ። ከሞት በኋላ ትንሣኤ አለ፤ ከትንሣኤ በኋላ ፍርድ አለ። ፍርዱም ዘላለማዊ ብጽዕና ወይም ዘላለማዊ ጉስቍልና ነው። ፍጻሜም ሁለት ነው፤ ዘላለምን የት ማሳለፍ ትወድዳላችሁ? ከጌታ ጋር በመንግሥቱ? ወይስ ለሰይጣንና ለመላእክቱ በተዘጋጀ ቅጣት? ወንጌለ ማቴዎስ እንዲህ ይላል፤ *በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል፦ እናንተ ርጉማን፥ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ።* ማቴ. 25፥41። እዚህ ሦስት ጎራዎች ተጠቅሰዋል፤ ሰይጣን፥ መላእክቱ፥ እና ርጉማን የተባሉት ሰዎች። ይህን የተናገረው ደግሞ ሌላ ማንም ሳይሆን፥ ራሱ ጌታ ነው።

ላላመኑ የማካፍለው አራት ነጥቦች እነዚህ ናቸው፤

- ሰዎች ኃጢአተኞች ናቸው፤ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል ከክብሩም ጎድለዋል። *ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤* ሮሜ 3፥23።
- ኃጢአት ደመወዝ አለው፤ ደመወዙም ሞት ነው። የዘላለም ሞት። *የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤* ሮሜ 6፥23።
- የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ደግሞ የዘላለም ሕይወት ነው። እዚያው ሮሜ 6፥23 *የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤* ካለ በኋላ፥ *የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው።* ይላል።
- ይህ ስጦታ ደግሞ የጸጋ፥ የነጻ ስጦታ ነው። እርሱም ክርስቶስን መቀበል ነው። *የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።* ዮሐ. 1፥11-12።

ላልዳኑት የምለው ይህንን ጌታ ጌታችሁ አድርጋችሁ፥ ብቸኛው አዳኛችሁ ተቀበሉት ነው። መቀበል ምንም የተወሳሰበ ስነ መለኮት አይደለም። [ከዚህ በፊት ያዘጋጀሁት አጭር የ10 ደቂቃ፥ ጌታን ተቀብለሃል? ተቀብለሻል?' የተሰኘች ቪድዮ አለች ያቺን ለማየት ሊንኩ ይህ ነው፤ https://www.youtube.com/watch?v=YcOmswunVC0 የቪድዮው መልእክት በጽሑፍ ደግሞ ይህ በቀጣዮቹ ገጾች የሚገኘው ነው።

# ጌታን ተቀብለሃል? ተቀብለሻል?

ሰዎች ጌታን ተቀበይ ወይም ተቀበል ብለው ሲጋብዙን ወይም፥ ጌታን የግል አዳኝህ አድርገህ ተቀብለሃል? ተቀብለሻል? ሲሉ፥ ወይም እኔ ጌታን የተቀበልኩት በዚህ

በዚህ ቀን ነው ሲሉ ሰምተን እናውቃለን? ለምሳሌ፥ እኔ ጌታን የተቀበልኩት በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1975 ከፋሲካ ቀጥሎ በነበረው ማክሰኞ ግንቦት 2 ቀን ነው። [ወይም May 10, 1983 ነው።]

ታዲያ ምንድርን ነው ይህ ጌታን መቀበል? ጌታን መቀበል የተወሳሰበ የስነ መለኮት ቃል አይደለም። ፍቺና ፊቺ የሚፈልግ ጥልቅ አስተምህሮም አይደለም። ይህንን ትልቅ እና ድንቅ እውነት እግዚአብሔር የተወሳሰበ አድርጎ አላቀረበም። በጣም ግልጽ፥ በጣም ቀላል ነው። ሁላችንም ሰጥተንም ተቀብለንም እናውቃለን። ይህ መስጠትና መቀበል ከሰው ፍጥረት ጀምሮ የኖረ ልምድ ነው። በመስጠትና በመቀበል ውስጥ ሰጪ አለ፤ ተቀባይ አለ፤ ስጦታ ደግሞ አለ።

ይህንን ጌታን መቀበል የሚለውን እውነት የሚያስረዱን ሁለት ጥቅሶች እንመልከት።

የመጀመሪያው፥ የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው። የሚለው ነው፤ ዮሐ. 1፥11-12።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የመጣ አምላክ ነው። ሙሉ አምላክ ሆኖ ከአምላክነቱ ምንም ሳይቀነስ ፍጹም ሰው ሆኖ የመጣ ነው። በሥጋ መምጣት የኖረበት ምክንያት ሊቤዠን ወይም ቤዛ ለመሆን ነው። ቤዛ ማለት ምትክ ማለት ነው። በምትካችን ሊሞት፥ ኃጢአታችንን ሊወስድ ማለት ነው። ሳይሞት ኃጢአታችንን ሊወስድ ወይም ሊደመስስ አይችልም ነበር ወይ? ኃጢአት እንዲህ በቀላሉ ድምስስ የሚል ነገር አይደለም። ኃጢአት ደመወዝ አለው፤ ደመወዙም ሞት ነው፤ ሮሜ 6፥23። ኃጢአት የእግዚአብሔር ተቃራኒ ባህርይ ነውና ኃጢአት ሁሉ ሕይወትን ይጠይቃል።

ሰው ሁሉ ደግሞ በአዳም በኩል እና በራሱም ሥራ ኃጢአተኛ ነው። ማንም ኃጢአት የለብኝም ወይም ኃጢአተኛ አይደለሁም ማለት አይችልም። ሮሜ 3፥23። ሁሉ ከኃጢአት በታች፥ ከፍርድ በታች ናቸው። የኃጢአት ደመወዙ ሞት ከሆነ ደግሞ ሁሉ ሟቾች ናቸው። አንድም በሕይወት የሚተርፍና የሚኖር የለም። ማንም ደግሞ የማንንም ሞት መውሰድ አይችልም። አዳኝ ወይም ቤዛ ለሰው ልጅ ኃጢአት መሞት ከኖረበት ያ ቤዛ ማሟላት ያለበት አራት ነገሮች አሉ። (ከአንድ ጓደኛዬ የትርጉም መጽሐፍ የወሰድኩት ነው።) እነዚያም

1ኛ፥ ሰው መሆን አለበት። ጌታ አምላክ እያለ ሰው የሆነው በዚህ ዋና ምክንያት ነው። ለመሞት ሥጋ መልበስ አለበት። ደሙን ለማፍሰስ ደም እንዲኖረው ያስፈልጋል፤ ደም እንዲኖረው ሰው መሆን አለበት።

2ኛ፥ ምንም ኃጢአት የሌለበት መሆን ይገባዋል። ያለዚያ ራሱም ኃጢአተኛ ነዋ! የራሱ ኃጢአት ምን አድርጎ ለሌላው ይሞታል? ለራሱ ኃጢአት ብቻ ነው የሚሞተው። ሌላውን ማዳን አይችልም።

3ኛ፥ አምላክ መሆን አለበት፤ ይኸውም በምትክነት የሚሰዋው ቁጥር ስፍር ለሌለው ኃጢአትና እጅግ ብዙ ኃጢአተኞች በመሆኑ ነው። ሰው ብቻ ከሆነ ከሰው ይህን ማድረግ የሚችል ንጹሕ ሰው የለም። ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና። ይህ ቤዛ ከተራ ሰው በላይ የሆነ ሰው መሆን አለበት።

4ኛ፥ እራሱን ለሌሎች ኃጢአት ሲል አሳልፎ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን አለበት።

ጌታችን እነዚህን መስፈርት የሚያሟላ ቤዛ ነው። ይህንን ሆኖ ነው ወደ ወገኖቹ የመጣው። የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። ሰው ሆኖ መምጣት ከኖረበት ወደ አንድ ወገን መምጣት አለበት። ያ ወገን ማንም ሊሆን ይችላል። ያንን ወገን ከአብርሃም ወገን እንዲሆን እግዚአብሔር መረጠ። ተስፋ ሰጠ። በትንቢት ተናገረ፤ ሕጻን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል እያሉ ነቢያት ተናገሩ። ተሰጥቶናል ሲሉ ስጦታ መሆኑን መናገራቸው ነው።

ስጦታ ከሆነ ይህ ስጦታ የሚቀበሉት ስጦታ ነው። ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው። የሚለው ነው። ስጦታ ዋጋ የተከፈለበት፥ ግን ተቀባዩ ያልከፈለበት፤ እንዲቀበሉት የተገባ ግን ግዴታ የሌለበት የፈቃድ ነገር ነው።

ይህ ነው መቀበል። መቀበል መውሰድና የራስ ማድረግ ነው። ስጦታው ዕቃ ከሆነ ወስዶ መጠቀሚያ ማድረግ ነው። ስጦታው ጌጥ ከሆነ ተቀብሎ ማጌጥ ነው። ስጦታው ጌታ ከሆነ ተቀብሎ ጌታ ማድረግ ነው። ክርስቶስን ጌታ አድርጎ መቀበል ማለት በራስ ላይ ጌታ እንዲሆን መፍቀድ ነው።

ይህ 'የግል አዳኝ' የተባለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም። ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አሳብ ነው። የግል ማለት የራስ ማለት ነው። የግል አዳኝ አድርጎ መቀበል ሲባል ተቀባዩ ራሱ በውሳኔው የሚቀበለው መሆኑን መናገሩ ነው። ወላጆቼ ስለ እኔ ጌታን አይቀበሉልኝም። ኦርቶዶክሳውያን ሃይማኖተኞች ስለነበሩ በ40 ቀኔ አስጠምቀውኛል፤ የክርስትና ስም ተሰጥቶኛል፤ ያንን ማድረጋቸው ለኔ ክርስቲያን መሆን አስበው ነው። መልካም ምኞት ነው፤ ያስመሰግናቸዋል። ግን ያ እነርሱ ለኔ ያደረጉት ነገር እኔን አያድነኝም። ፈቃዴ የለበትማ! ይልቅስ ከዚያ በኋላ ቃሉን በማስተማር፥ ክርስቶስን በማሳየት ተግተው ኖሮ ቢሆን መልካም ነበር። ያንንም እንኳ አድርገው እኔ በራሴ ውሳኔ፥ በራሴ ፈቃድ ጌታን ጌታዬ አድርጌ ካልተቀበልኩ አይሆንም።

ምክንያቱም ይህ የጌታና የተከታይ ግንኙነት ነው። በግድ ከሆነ ፈቃድ የለበትም። ተገድጄ ነው የምከተለው። ፈቃድ ደግሞ እግዚአብሔር ማንንም ሳይለይ ለሰው ልጆች ሁሉ የሰጠው ድንቅ ስጦታ ነው። ለዚህ ነው የግል አዳኝ የተባለው። ውሳኔው ማንም ለማንም የማያደርገው የግልና የፈቃድ ውሳኔ ስለሆነ ነው።

አንዴ ከካናዳ ትምህርቴን ጨርሼ እንደተመለስኩ በዲላ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አንድ እሁድ አገለግል ሳለሁ ከካናዳ የገዛኋትን ቆንጆ ሰዓት አሳየሁና፥ ይህችን ሰዓት የሚወስድ ካለ መጥቶ መውሰድ ይችላል፤ የሚወስድ አለ? ብዬ ጠየቅሁ። ሰው አፍሮ ዝም። ፈልገዋል፤ ግን ምንተፍረት ያዛቸው። ኋላ ትንሽ ልጅ ወደ ፊት መጣና እጁን ዘረጋ፤ በገዛ እጄ አውጥቼ ሰጠሁት። ስጦታ ነው፤ የሚቀበል ካለ ብዬ ጋበዝኩ፤ አንድ መጣ፤ ተቀበለ። እንግዲህ መቀበል ይህ ነው። ተቀብሎ የራስ ማድረግ። የምንቀበለው ጌታ ከሆነ ተቀብሎ የራስ ጌታ ማድረግ ነው። ጌታን ተቀብለሃል? ጌታን ተቀብለሻል? አሁን ጥያቄው ግልጽ ነው።

ሁለተኛው፥ እንግዲህ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ተቀበላችሁት በእርሱ ተመላለሱ። የሚል ቃል ነው፤ ቆላ. 2፥6። ጌታን ስንቀበል የተቀበልነው እንደ ጌጥ ወይም እንደ መብል ሳይሆን እንደ ጌታ ነው። ስለዚህ በኛ ላይ በፈቃዳችን የሆነ

ጌትነቱን ነው የተቀበልነው። ባንቀበለውም እርሱ ጌታ ነው። አንድ ቀን ጉልበት ሁሉ ለእርሱ ይንበረከካል፤ መላስ ሁሉ ለአብ ክብር ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክራል። ይህ እውነት ነው። ግን ጌትነቱን መቀበል በኛ ላይ ጌታ፥ አለቃ፥ አዛዥ፥ ባለ ሙሉ ሥልጣን፥ ንግሡ፥ አምላክ እንዲሆን ፈቅደን መቀበላችን ነው።

ይህ ከሆነ እንደተቀበልነው በእርሱ መመላለስ አለብን። እርሱ ጌታችን ስለሆነ እኛ እንደ እርሱ ተከታዮች፥ ደቀ መዝሙሮች፥ እንደ ክርስቲያኖች ሆነን መመላለስ አለብን። እንግዲህ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ተቀበላችሁት በእርሱ ተመላለሱ። ሰዎች ጌታን መቀበል የማይፈልጉት ስጦታውን ሳይፈልጉ ቀርተው ሳይሆን ስጦታው ጌታ ነውና ጌታ ስለሆነ የሚጠይቀው የፈቃድ ዋጋ ስላለ ነው። የመመላለስ ዋጋ። እርሱን የመምሰል ዋጋ። ግን ይህ ዋጋ ኋላ ከምንቀበለው ደመወዝ ጋር ሲነጻጸር ተመን የለውም።

የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው። ሮሜ 6፥23

ይህንን አጭር ትምህርት ስጨርስ ልጋብዛችሁ እወዳለሁ። እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ሰጥቶናል፤ ስጦታ ነው። እኛስ ተቀብለነዋል? ይህ መቀበል ከላይ እንዳልኩት ሥርዓት መፈጸም አይደለም። ፈቃድን ለፈቃዱ ማስገዛት ነው። እርሱን የሕይወታችን ጌታ ማድረግ ነው።

ምናልባት ጌታን መቀበል ሳይገባችሁ ኖራችሁ አሁን የተከሰተላችሁና ጌታን ለመቀበል የምትፈልጉ ከኖራችሁ፤ ሁለት ነገሮች አድርጉ፤

1. ኃጢአተኛ መሆናችሁን አውቃችሁ ተጸጸቱና እግዚአብሔርን ይቅርታ ጠይቁት። እኔ ኃጢአተኛ ነኝ ይቅር በለኝ። በሉት። የዚህ ይቅርታ መገኛ ደግሞ ከላይ ያልኩት ክርስቶስ አምላክ ሳለ ሰው ሆኖ ኃጢአታችንን በመስቀል ላይ መውሰዱ ነው። ይቅር በለኝ ስንል ይህ የኃጢአታችን ደመወዝ በዚያ መስቀል ላይ መከፈሉን መገንዘባችን ነው።

2. ይቅርታ ከጠየቅን በኋላ ጌታ እርሱ ጌታችን እንዲሆን ወደ ልባችን እንዲገባ መጋበዝ ነው። ጌታ ሆይ ና ወደ ሕይወቴ፥ ወደ ልቤ፥ ወደ ኑሮዬ ግባ፤ መሪዬ ጌታዬ ሁን እንበለው።

ይህን ካደረግን እንደ ተስፋ ቃሉ ታማኝ ነውና ወደ ሕይወታችን ይገባል። አዲስ ፍጥረትም ሆነናል። ከዚህ አዲስነት በኋላ በቅርባችን የምትገኝ ወንጌልን የምትሰብክ፥ ቃሉን የምትኖር ቤተ ክርስቲያን ፈልገን አብረን ማምለክ፥ ይህን ያገኘነውን አዲስ ሕይወት ለሌሎች ማካፈል እና በቆላ. 2፥6 እንደተጻፈው በእርሱ መመላለስ እንጀምር።

ጌታን ተቀብለሃል? ጌታን ተቀብለሻል?

# የክርስቲያን እና ኮሮና የውይይት ጥያቄዎች

ስለ ኮሮና ማንበብና መወያየት አስፈላጊ ነው? ለምን?

ኮቪድ-19 ምን ማለት ነው? የስሙ ትርጉምና ቁጥሩ ምን ማለት ነው?

ፍርሃት ምንድር ነው?

ፍርሃት ጤናማ ነገር ነው? ከሆነ በምን እናውቃለን? ካልሆነስ በምን እናውቃለን?

ፍርሃት ራሱ ያስፈራል? እንዴት?

ኮቪድ-19ን አስፈሪ ያደረገው ምንድር ነው?

ግራ መጋባትና እግዚአብሔርን መጠየቅ መጠርጠር ነውን?

ሁለቱ ፍርሃቶች የተባሉት ምንና ምን ናቸው?

ክርስቲያኖች ስለ ነገ ወይም ስለሞት ስናስብ መፍራት የሌለብን ለምንድር ነው?

ፍርሃት ምንድር ነው? ምን ያደርግብናል?

የኤልያስ እና የጴጥሮስ መፍራት ምን ያስተምረናል?

ክርስቲያን ሞትን መፍራት የለበትም ስንል ምክንያት የሚሆኑን አራት ነጥቦች ምን ምን ናቸው?

. . . . .

ኮቪድ መቅሰፍት ነው? ቸነፈር? ወረርሽኝ? ወይስ ሰው ሠራሽ ሴራ?

ኮቪድ ለሐሰተኛው ክርስቶስ መንገድ ጠራጊ ሊሆን ይችላል ሲባል ምን ይታሰባል? ወይም የቁጥጥር ቤተ ሙከራ ነው ሲባልስ? እንዴት

በኮቪድ ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ላይ ምን ተፈጠረ? ሐሰተኞችስ ምን ሆኑ? አገልጋዮች ምን ደረሰባቸው?

ከቤተ ክርስቲያን መዘጋት ስለ ቤተ ክርስቲያን ምንነትና ስለ አገልግሎት ምን እንማራለን?

የክትባት ጉዳይ እንዴት መታየት አለበት?

በዚህ ሁሉ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ላላ ወይስ ጠነከረ?

በክርስቶስ ላይ ያለን እይታ ጠራ ወይስ ደበዘዘ?

. . . . .

የዓለም ሕዝብ በዝቷል ባለበት መቆም አለበት፤ እንዲያውም መቀነስ አለበት የሚሉ ሴረኞች እና ኢኮኖሚስቶች አሉ፤ ይህን የሚሉት ለምንድር ነው?

ቶማስ ማልተስ የተባለው ኢኮኖሚስት ማልቶሳዊ ቀውስ ወይም Malthusian catastrophe የሚባለው ነገር ምንድር ነው? ከቀውሶቹ መካከል ምሳሌ ስጡ።

ኮሮና ቫይረስ ወይም ኮቪድ 19 ምንጮች ናቸው ተብለው የሚጠቀሱት አምስት ምንጮች እነማን ናቸው?

ኮቪድ-19 ዓለም አቀፍ ቁጥጥር ቤተ ሙከራ ሊሆን ይችላል?

ኮቪድ-19 ሰው ሠራሽ ቀውስና ለሐሰተኛው ክርስቶስ መድረክ ሠሪና መንገድ ጠራጊ ነው ሊባል ይቻላል?

ዜጋ ፈሪ ሲሆን፥ መንግሥታት የዜጎችን ስሜት መቆጣጠር መቻላቸው ለመግዛት ያመቻቸዋል፤ ዜጎች ፈርተዋል? የእንቅስቃሴ እገዳና ገደብ ጉዳይስ እንዴት ይታያል?

ሰው ሁሉ በትልቅ ፍርሃት ውስጥ ባለበት ጊዜ ክትባት ተገኘ ሲባል ክትባቱን ለመውሰድ ዓይኑን የሚያሽ ወይም ሁለቴ የሚያስብ ይኖራል?

ክትባቱ የሕዝብ ቁጥር መለኃሚያና መቀነሻም ሊሆን ይችላል? እንቅስቃሴ መግቻስ ይሆናል? ከ666 ጋርስ ይገናኛል?

. . . . .

በጠቅላላው እይታ፥ እንደ ክርስቲያን እንዴት እናስብ? እንዴት እንኑር?

ጌታን የማታውቁ፥ ከእርሱ ጋር በግል ግንኙነት የሌላችሁ፥ ጌታን ተቀብላችኋል?

## ምዕራፍ ፬

# ክርስቲያንና ወንበር (ሥልጣን)

ቀጥሎ የሚገኙት 3 ምዕራፎች ክርስቲያንና ሦስቱ ወዎች በሚል ያካፈልኩት ተከታታይ ትምህርቶች ናቸው። ሦስቱ ወዎች ያልኩትን ሦስቱ ወዎች ያልኩት ለመያዝ እንዲመች ነው፤ ሦስቱ ፈተናዎች ማለትም ይቻላል። ሦስቱ ወዎች ወንበር፥ ወረት፥ እና ወሲብ ናቸው። ወንበር ሥልጣንን ለማመልከት ነው። ሁለተኛው ወ ወረት ነው፤ ወ ወርቅም፥ የምንጠቀመው ገንዘብ የወረቀት ስለሆነ ወ ወረቀትም ማለት ይቻላል። ሦስተኛው ወ ወሲብ ነው። ሦስቱንም የለብቻ እንመለከታቸዋለን።

ከዓመታት በፊት ይህንን አሳብ ሳስተምር ሦስቱ ወዎች ሳይሆን፥ 'ወሥን' የሚል የቃል ቀመር ነበር የተጠቀምኩት። ወ ወሲብ፥ ሥ ሥልጣን፥ ን ንዋይ። መወሰን ከሚለው ምክር ጋር በመጨረሻ ስለሚጠናቀቅ ነው ወሥን የተሰኘው። ሰይጣን ብዙ ቦታዎች ይገባል፤ ግን ሰይጣን ፈታኙ ነው እንጂ ፈተናው አይደለም። እነዚህ ሦስቱ ፈተናዎቹ ናቸው። ሰይጣን እነዚህን መሳሪያ አድርጎ ይጠቀምባቸዋል። ከነዚያ ከሦስቱ ጋር አራተኛ ሆኖ ቢቀርብ የሚመርጠው የለም። ለነገሩ ዛሬ ሰይጣንን እንደ ሦስተኛ ክፍል ተማሪ እርሳስና ደብተር አስይዘው ቁጭ አድርገው የሚያስተምሩ እርሱን የሚያስንቁ፥ ሰይጣን እንኳ ከነሱ አዳዲስ ስልት የሚማርባቸው አሳቾችና ከይሲዎች አሉ። ያውም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ። እነዚህን ሦስት ወዎች በመጠነኛ ዝርዝርና ለየብቻ በዚህና በቀጣይ ምዕራፎች እናያቸዋለን።

ወደ መጀመሪያው፥ ወደ ወንበር እንምጣ። ወንበር ሥልጣን ነው፤ ሥልጣንን ይወክላል፤ ወንበር መንበር ነው፤ ዙፋን ነው። ሥልጣን ከፍታ፥ ከፍ የማለት ወይም ብሎ የመታየት፥ በላጭ የመሆን፥ ቀዳሚ የመሆን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፥ ወይም በማንም ሥር ወይም የማንም እኩያ ያለመሆን ሳይሆን፥ ሌላውን የመግዛትና የመቆጣጠር ጉዳይም ነው። ወንበር ከትምክትህ ጋር ኩታ ገጠም የሆነ በላይነት ነው።

በአገር አገዛዝ ቢታይ አምባ ገነንነት ሊባል የሚችል አገዛዝ ዓይነት ሥልጣን በቤተ ክርስቲያን ውስጥም አስተዳደርን፥ ገንዘብንም፥ መንፈሳዊ፥ ቁሳዊ፥ ሥጋዊውን ሁሉ ነገር የመጨበጥ ዝንባሌ የሚታይባቸው ሰዎች ይገኛሉ። የነዚህ ሰዎች ግባቸው ማንም አይቆጣጠረን ብቻ አይደለም፤ ሁሉንም እንቆጣጠር፤ ሁሉም በኛ ስር ይሁን ነው። በሚያደርጉት ነገር ሁሉ ማንም አይናገራቸውም። ሲያለሙ ምስጋናውን ይቀበላሉ። ሲያጠፉ ደግሞ ወንጀሉን መቀበል ነበረባቸው፤ ግን፥ የቁጥጥር እርከን ስለሌለ ጥፋታቸውም ማጥፋታቸውም ይሰወራል። ሚሙቶ ይጠፋል። ጥፋታቸው ብዙ ጊዜ ጉዳቱ ታፍኖ ይቆይና ይከሽፋል። የሚታየውና የሚታወቀው ሲገነፍልና ሲወጣ ነው። ይህንን ወንበር የሚባለውን ችግር ራሱን ከሦስት የችግሮች አቅጣጫ እንመልከተው።

## አንደኛ፥ የገዥነት ወንበር።

ይህ ማለት ሹመቱ፥ መሪነቱ ወይም ከፍታው፥ ሥልጣኑ፥ ወንበሩ ራሱ፥ ስሙ፥ ከስሙ ጋር የተያያዘው ዝናና ክብር የሚፈጥረው ርቀት ችግሩ መሆኑ ነው። ይህ፥ 'ክቡር፥ ፓስተር፥ ነቢይ፥ ሐዋርያ፥ shepherd, major, super, ብፁዕነታቸው፥ ሊቅ፥ ሊቀ እንትን፥ reverend, ወዘተ፥ እየተባሉ የሚጠሩበት አጠራር በራሱ የሚፈጥረው ከፍተትና ከፍታ፥ ርቀትና ምጥቀት አለበት። ክፍተቱና ርቀቱ ደግሞ የከፍታ ወይም ወደ ላይ የማየልና የመምጠቅ ነው፤ ወደ ጎን ሳይሆን ወደ ላይ ነው። ቀና ተብሎ፥ በጣም ቀና ተብሎ እንዲታዩ የሚያደርግ ነገር ነው።

ስለዚህ የሥልጣን ጉዳይ ጌታ በማቴ. 23፥1-12 ያስተማረው ትልቅ ትምህርት ነውና እንመልከተው፤ ማቴ. 23፥1-12፤

1፥ *በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለሕዝቡና ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ብሎ ነገራቸው፦* ለሕዝቡም ለደቀ መዛሙርቱም ነው የነገራቸው።

2፥ *ጻፎችና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠዋል።* ወንበር ነው የተቀመጡበት። ስለ ወንበር ነው የምንነጋገረው፤ ወ ወንበር። የሙሴ ወንበር በአይሁድ ምኵራቦች፥ ቢያንስ በትልልቆቹ ምኵራቦች፥ የሚገኝ ከሙሴ መጻሕፍት፥ ወይም ከሌሎች የምንባብ ክፍሎች ከተነበቡ በኋላ አንባቢው ወይም የሚያብራራው ረቢ ወይም አስተማሪ የሚቀመጥበት ነው። በሉቃ. 4 ጌታ በናዝሬት ምኩራብ ተገኝቶ ቆሞ አንብቦ ተቀምጦ ተናግሮ ነበር፤ ከቁ. 16-21 ይላል፤ *ወዳደገበቱም ወደ ናዝሬት መጣ፤ እንደ ልማዱም በሰንበት ቀን ወደ ምኵራብ ገባ፥ ሊያነብም* <u>*ተነሣ።*</u> *የነቢዩንም የኢሳይያስን መጽሐፍ ሰጡት፥ መጽሐፉንም በተረተረ ጊዜ፦ የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ*

*ነው፥ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፥ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል ተብሎ የተጻፈበትን ስፍራ አገኘ። መጽሐፉንም ጠቅልሎ ለአገልጋዩ ሰጠውና <u>ተቀመጠ፤</u> በምኲራብም የነበሩት ሁሉ ትኵር ብለው ይመለከቱት ነበር። እርሱም፦ ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ ይላቸው ጀመር።* ሊያነብ ተነሣ፤ አነበበና ተቀመጠ። ያ የተቀመጠበት ወንበር ነው የሙሴ ወንበር የሚባለው። በዘመኑ በሕጉ እውቀት የጠለቁትና የተስፋፉት ፈሪሳውያንና ጻፎች ነበሩና፥ ሁለቱም ደግሞ ሕጉን አሳምረው የሚያውቁ አዋቂዎች ናቸውና ሲያብራሩት የሚደንቁ ናቸው። የሙሴ ወንበር ያ ሲያብራሩ የሚቀመጡበት ወንበር ነው። የሥልጣን ወንበር ነው። የቃል ተናጋሪ፥ የሕግ አዋቂ ወንበር ነው። ከዚህ ወንበር የሚወጣው ቃል ከወንበሩ የተነሣ የሥልጣን ቃል ነው።

በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን Ex-Cathedra የሚባል ሐረግ አለ። 'ከካቴድራው የወጣ' ማለት ነው። ካቴድራ ወንበር ወይም መቀመጫ ማለት ነው። እዚህ ማቴ. 23፥2 ላይ የተጻፈው ወንበር የተባለው ቃልም ራሱ ካቴድራ (καθέδρα) ነው። λέγων· ἐπὶ τῆς Μωϋσέως καθέδρας (ሌጎን፤ ኤፒ ቴስ ሙሴዎስ ካቴድራስ) በሙሴ ካቴድራስ ላይ። ካቴድራል የሚለው ቃል የመጣውም ከዚያ ነው። ካቴድራል 'የወንበር ስፍራ፥ የካቴድራ ስፍራ የመንበር ስፍራ' ማለት ነው። ስለዚህ፥ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን Ex-Cathedra ወይም 'ከካቴድራው የወጣ' ማለት ከጳጳሱ መንበር የወጣ የሥልጣን ቃል ለማለት ነው። ይህ ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ ያልተናነሰ ወይም የተካከለ ሥልጣን ያለውና የሚታዘዙት ቃል ነው። ስለ ወንበር ነው የምንነጋገረው፤ *ጻፎችና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠዋል።*

3-4፥ *ስለዚህ ያዘዙአችሁን ሁሉ አድርጉ ጠብቁትም፥ ነገር ግን እየተናገሩ አያደርጉትምና እንደ ሥራቸው አታድርጉ። ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ ይጭናሉ፥ እነርሱ ግን በጣታቸው ስንኳ ሊነኩት አይወዱም።* በጣም አደገኛው ልዩነት ነው ይህ። የማስደረግ፥ ግን የአለማድረግ። ሌሎች እንዲጠብቁ ይነግራሉ፤ እነሱ አይጠብቁም። ሌሎችን አድርጉ ይላሉ፤ ይናገራሉ፤ እነሱ አያደርጉም። ተቀደሱ ይላሉ አይቀደሱም። ትልልቅ ሸክሞች፥ አስቸጋሪ ሸክሞች ተብትበው ይጭናሉ፤ እነሱ ግን ያንን ሸክም የሚነኩት በሚሸከሙት ላይ ለማድረግ ለማንሣት እና ለመጫን ብቻ ነው። ከተጫነ በኋላ በጣታቸውም አይነኩትም።

5-7፥ *ለሰውም እንዲታዩ ሥራቸውን ሁሉ ያደርጋሉ፤ ስለዚህ አሸንክታባቸውን ያሰፋሉ ዘርፋንም ያስረዝማሉ፥ በምሳም የከበሬታ ስፍራ፥ በምኵራብም የከበሬታ ወንበር፥ በገበያም ሰላምታና፦ መምህር ሆይ መምህር ሆይ ተብለው እንዲጠሩ*

*ይወዳሉ።* እነዚህ ሰዎች ምን እንደሚመስሉ እነዚህ ገላጭ ቃላት ያሳያሉ። አሸንክታብ ማለት በአማርኛ የክታብ አሸን ማለት ነው። ብዙ ክታቦች፤ ብዙ ጥፈቶች ማለት ነው። ጥፈት ወይም ክታብ በተለምዶ ደብተራዎች የሚጽፉትና በጨርቅ ተሰፍቶ አንገት ላይ የሚታሰር ነገር ነው። በተጻፈበት ቋንቋ ፉላክቴሪዮን ወይም ፊላክቴሪዮን የተባለው ይህ ቃል በእንግሊዝኛም በቀጥታ ተወስዶ ፊላክትሪስ ተብሏል። የጥፈት ማስቀመጫ ሳጥን ማለት ነው።

አይሁድ ዘዳ. 6፥3-9 ያለውን *እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤ አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ። እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ። ለልጆችህም አስተምረው፥ በቤትህም ስትቀመጥ፥ በመንገድም ስትሄድ፥ ስትተኛም፥ ስትነሣም ተጫወተው። በእጅህም ምልክት አድርገህ እሰረው፤ በዓይኖችህም መካከል እንደ ክታብ ይሁንልህ። በቤትህም መቃኖች በደጃፍህም በሮች ላይ ጻፈው።* የሚለውን ቃል እጅግ ለመጠበቅ ከመጓጓት የተነሣ በልባቸው፥ በግንባራቸው፥ በእጃቸው ጥፈት አድርገው ያስሩታል፤ በሦስቱም ቦታዎች በሰውነታቸው ላይ ያስሩታል። አሸንክታብ ትንንሽ ሳጥን ነው። እነዚህ ሰዎች ግን ያሰፉታል፤ ያስረዝሙታል። *አሸንክታባቸውን ያሰፋሉ ዘርፋንም ያስረዝማሉ።*

*በምሳም የከበሬታ ስፍራ፥ በምኵራብም የከበሬታ ወንበር፥ በገበያም ሰላምታና፦ መምህር ሆይ መምህር ሆይ ተብለው እንዲጠሩ ይወዳሉ።* ዝና ፈላጊዎች፥ ከፍ ያለ የታይታ ስፍራ ፈላጊዎች ናቸው። *በምኵራብም የከበሬታ ወንበር፥* የሚለው ቀደም ሲል ያየነው የተወደደው ቃላችን ካቴድራ ነው፤ ፕሮቶካቴድሪያ፤ ቀዳሚ፥ ከፍ ያለ፥ የጎላ፥ የሚታይ ወንበር።

መጠራት ደግሞ ይፈልጋሉ፤ በስማቸው ሳይሆን በማዕረጋቸው፤ ምን ተብለው? ረቢ! ረቢ! ተብለው። በአማርኛ መምህር የተባለው ቃል በቋንቋቸውም፥ ወንጌሉ በተጻፈበት ቋንቋም ረቢ የሚል ነው። ቃሉ ከመምህር ያለፈ ቃል ነው። ልክ እንደኛው፥ 'የኔታ' እንደሚባለው ቃል ያለ ነው፤ የኔታ ማለት፥ መምህሬ አስተማሪዬ እንደ ማለት ሆኖ፥ የኔታ፥ 'የኔ ጌታ' ወይም ጌታዬ ማለት ነው። ረቢ፥ ራብ רַב ከሚል የአይሁድ ቃል የመነጨ ከፍተኛ ማዕረግ ነው፤ ትርጉሙም ከፍ ያለ ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች በማዕረግ መታወቅም፥ መጠራትም ይፈልጋሉ። ከላይ ያልኳቸው ቅጽሎች፥ 'ክቡር፥ ፓስተር፥ ነቢይ፥ ሐዋርያ፥ shepherd, major, ብፁዕነታቸው፥ ሊቅ፥ ሊቀ እንትን፥ reverend, ወዘተ፥ ከስማቸው በፊት ካልተጠራ ጉድ ፈላ! 'ወንድም እገሌ' አይባልም፤ አይታሰብም። ወንድምነት ቤተ ሰብነት ብቻ ሳይሆን አቻነት እኩያነት አለበት። ይህ እኩያነት አይታሰብም። ቀጥሎ ጌታ ምን አለ?

8-12፥ *እናንተ ግን፦ መምህር ተብላችሁ አትጠሩ፤ መምህራችሁ አንድ ስለ ሆነ እናንተም ሁላችሁ ወንድማማች ናችሁ። አባታችሁ አንዱ እርሱም የሰማዩ ነውና በምድር ላይ ማንንም፦ አባት ብላችሁ አትጥሩ። ሊቃችሁ አንድ እርሱም ክርስቶስ ነውና፦ ሊቃውንት ተብላችሁ አትጠሩ። ከእናንተም የሚበልጠው አገልጋያችሁ ይሆናል። ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳል፥ ራሱንም የሚያዋርድ ሁሉ ከፍ ይላል።* ይህ ክፍል የሚነግረን ሰዎችን ስለማዋረድ ሳይሆን ሰዎችን በእውነተኛ አቻነት ማወቅን ነው። ሦስቱንም ትልልቅ ማዕረጎች፥ ወይም የሥልጣን ቅጽሎች እዩ፤ መምህር፥ አባት፥ ሊቅ።

መምህርን ወይም ረቢን አይተናል። አባት ጨዋ ቃል ይመስላል፥ አባ እገሌ፥ ወይም አቡነ እገሌ ሲባል እንደ አባት የማየትና የአክብሮት ነገር ብቻ ይመስላል። ነገር ግን፥ አይደለም፤ ከዚያ ያልፋል። ልክ አባት እንዳለው ሥልጣን ዓይነት ሥልጣን አለበት። ልብ እንበል፤ አጠራሩ፥ 'ወንድም እገሌ' አይደለም፤ አባ እገሌ ነው። አቻነትና እኩያነትና ወንድማማችነት የለበትም። አንድን ሰው 'አባ' ብሎ ጠርቶ የአባት ሥልጣን መንፈግ አይቻልም። ሊቅ ወይም ሊቃውንት የሚለው ቃል ስለ እውቀት የሚናገር ይመስለናል፤ አይደለም፤ እዚህ ሊቅ የሚለው ቃል ልሂቅ፥ የላቀ፥ ከፍ ያለ፥ መሪ ማለት ነው። ከማመልከት ወይም መምራት፥ ከማዘዝ፥ ከመግዛት ጋርም የተቆራኘ ነው።

*እናንተም ሁላችሁ ወንድማማች ናችሁ።* ወንድማማች! ይህ የወንድማማችነት ነገር ሲኖር እና የወንድማማችነቱ ነገር ሳይኖር የበላይና የበታች እርከን ብቻ ሲኖር ግንኙነቱ ግልጽ መልክ ይኖረዋል። በጣም ግልጽ። *ከእናንተም የሚበልጠው አገልጋያችሁ ይሆናል።* ባለ ሥልጣናችሁ ይሆናል አይደለም። አባታችሁ፥ መምህራችሁ፥ ሊቃችሁ ይሆናል አይደለም። <u>አገልጋያችሁ።</u> በሌላው ላይ መግዛት፥ መሠልጠን የተጀመረው ከኃጢአትና ከውድቀት በኋላ ነው። ከዘፍ. 3 በኋላ ማለት ነው። ፈቃድሽ ወደ ባልሽ ይሆናል የተባለው በኃጢአት መዘዝ ነው። ከዚያ በፊት፥ 'የምትመቸው ረዳት' ነበረች። አቻ ረዳት። የበላይነትና የበታችነት፥ የገዢና ተገዢነት፥ የአለቃና ምንዝርነት ሳይሆን የአቻ አጋርነት ጉዳይ ነበር። የተዋጁ ሰዎች አመራርም ይህንን መሆን ነበረበት። የተዋጁ ሰዎች አመራር የጸጋና የስጦታ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ፥ ከእኩያዎች ወይም ከአቻዎች መካከል የሚመራ መሪ አመራር መሆን ነበረበት። በእንግሊዝኛ ይህንን የቡድን አመራር ቃል leader among peers ይሉታል። በእኩያዎች መካከል የሚመራ ማለት ነው። ሥልጣን ሳይሆን መሪነት። ጌታ ወንድማማች ናችሁ ነው ያለው።

የምንነጋገረው ስለ ቤተ ክርስቲያን ነውና፥ በተለይም ስለ ወንጌላውያን ቤተ እምነቶች አብያተ ክርስቲያናት ነውና፥ ይህ የሥልጣን ጉዳይ የፖለቲካ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን

ሥልጣን ጉዳይ ነው። የወንጌላውያን ቤተ እምነቶች አብያተ ክርስቲያናት የአስተዳደር መታወቂያ የቡድን አመራር ነው። በቡድን አመራር ውስጥ፥ ከየትኛውም የአመራር ሞዴሎች ይልቅ ሚዛን የመጠበቅና የተጠያቂነት ጉዳይ አለ። የበላይነት እና የአምባገነንነት ስሜት አይታይም። ባለ ራእይና መሥራች ባለ ሥልጣን የለም፤ ዋና ነቢይና ሐዋርያ የሚባል ነገርም የለም።

ሌሎች አብያተ እምነቶች በበላይ አንድ ሰው የሚመሩ ናቸው፤ ኦርቶዶክሳውያን ርእሳነ ሊቃነ ጳጳሳት በሆኑ ፓትርያርኮች ነው የሚመሩት፤ እና አመራሩም በአወቃቀሩ አገራዊ ነው። ከፓትርያርኩ በታች የሚገኙ እርከኖችም አሉ። በካቶሊክ ቤተ እምነትም ከጴጥሮስ እንደጀመረ በሚባለው ጳጳሳዊ አመራር የሚመራና፥ መንበሩ (ወይም ቀደም ሲል ያየነው ቃል ካቴድራው) ቫቲካን ሆኖ ዓለም መዋቅሩ አቀፋዊ ነው። በካቶሊክ አመራር፥ ዋናው ጳጳስ የክርስቶስ ወኪል፥ የጴጥሮስ መክፈቻ ያዥ ስለሆነ ቃሉ ወይም ከመንበሩ የሚወጣው ቃል Ex-Cathedra ወይም 'ከካቴድራው የወጣ' የሚባለው፥ ያ ጳጳሱ ቃል እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል ያህል ሥልጣን አለው። ገዢ ነው።

ኑፋቄዎች የሆኑም ያልሆኑም ሌሎችም አገር አቀፍ፥ አገር ዘለል፥ ወይም ዓለም አቀፍ የሆኑ አመራሮች አሉ። ለምሳሌ፥ የይሆዋ ምስክሮች ከጀማሪው፥ ከቆርቋሪው ጀምሮ በየተራ አንድ መሪ ከላይ፥ ከአናት ያለበት መዋቅር ነው። አንዳንዴ ቡድን የሚመስሉበት መልክ ቢኖርም የአስተዳደሩ ስልት የነጠላ ሰው አገዛዝ ነው፤ ሰውየው ወይም ቡድኑ የበላይ ሆነው ከዚያ የሚወጣው ቃል ያለ ምንም ጥያቄ ተቀባይ ብቻ መሆን አለበት። የማይቀበል ሊኖር አይችልም፤ ከኖረ ያለ ምሕረት ከማኅበሩ መልለየት አለበት።

ከኑፋቄዎቹ ሳንርቅ እንደ ከአገራችን ምሳሌ ብናይ፥ የኢትዮጵያው የአሸናፊዎች መቅደስ ከናይጄሪያ የመነጨና ከናይጄሪያዊ መሪ ስር ሆኖ የኢትዮጵያው ቅርንጫፍ ነው። እግረ መንገዳችንን የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ቅርጾችንም ለማየት ነው ይህንን የማነሣው። እነዚህ አንድ ሰው ከላይ ሆኖ የሚመራቸው አመራሮች ከአገራዊ የፖለቲካ አመራር መዋቅር ጋር በጣም ይቀራረባሉ። ከላዕላይ ጀምሮ እስከ ታህታይ መዋቅር ድረስ ከርእሰ ብሔር ጀምሮ እስከ ተራ ዜጋ ድረስ ያለውን ግንኙነት ይመስላሉ።

የወንጌላውያን አብያተ እምነት መዋቅር ሲታይ ደግሞ የራስ ገዝ (autonomous) አጥቢያዎች ማኅበራት ናቸው። አንዳንዶቹ በርከት ሲሉ አገር አቀፍ ቢሮ የሚያስተባብራቸው ናቸው። አገር አቀፍ ቢሮ ቢያስተባብራቸውም፥ ቢሮው አስተባባሪ፥ ማኅበራቱም የትብብር ማኅበራት ናቸው እንጂ አጥቢያዎቹ ነጻ ናቸው። ይህ ደግሞ አዲስ ኪዳናዊው አሠራር ነው። በአዲስ ኪዳን በየአጥቢያውና በየከተማው ነበር መሪዎች የሚሾሙላቸው። ቲቶ 1፥5 *ስለዚህ ምክንያት የቀረውን እንድታደራጅ*

*በየከተማውም፥ እኔ አንተን እንዳዘዝሁ፥ ሽማግሌዎችን እንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ፤* ይላል። አንድ መሪ ሳይሆን ብዙ ሽማግሌዎችን ነው የሚሾመው። እንዲህ ያሉ የብዝኀ ቁጥር አመራርን የሚያመለክቱ በርካታ ምስክሮች በአዲስ ኪዳን ይገኛሉ። ሌላ አንድ ጥቅስ ለመጨመር፤ *የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያዎች የሆኑ ጳውሎስና ጢሞቴዎስ በፊልጵስዩስ ለሚኖሩ ከኤጲስ ቆጶሳትና ከዲያቆናት ጋር በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ቅዱሳን ሁሉ፤* ይላል ፊል. ፩፥፩። እዚህም የቡድን መሪዎች ይታያሉ።

በቡድን አመራር ውስጥ አንዱ ብቻውን አፈትልኮ ወጥቶ አምባገነን የሚሆንበት አካሄድ የመኖሩን ዕድል ያመነምነዋል፤ እንዲያውም ያከስመዋል፥ ያከሽፈዋል፥ ያመክነዋል። ይሁን እንጂ አስተዳደሮች ቅርጻቸውን እየለወጡ እየመጡ አሁን አሁን የአንድ መሪ የበላይ አመራር እየታየ መጥቶአል። የሥልጣን ወይም የሹመት ወንበር ችግር የሚከሰተው ደግሞ የቡድንና የጋራ አመራር ባለበት ሳይሆን የአንድ ሰው አመራር ባለባቸው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደሮች ነው። ያ አንድ ሰው ፈላጭና ቆራጭ፥ አዛዥና ናዛዥ፥ ሿሚና ሻሪ፥ መሪና ሠሪ ስለሚሆን ማንም አይናገረውም። ይህ አደጋ ነው።

ይህ የአንድ ሰው ብቻ የበላይነት ስሕተት፥ 'መሥራችና ባለ ራእይ' የሚባሉቱ ዘንድ ብቻ ሳይሆን በአንዳንድ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትም መጋቢያዊ አመራር (ወይም pastoral leadership) የሚባለውን የአመራር ስልት ወይም ፈለግ በመከተል፥ የአንድ ሰው ባለ ሙሉ ሥልጣንነት ዘይቤ በሚከተሉቱ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትም ይታያል። እንዲህ ባሉቱ ዘንድ፥ መጋቢው አስተዳደሩንም፥ መመገቡንም፥ ገንዘቡንም፥ ግንኙነቱንም ይጨብጥና አፉ ከሚችለው በላይ ጎርሶ ለመዋጥ ይቸገራል፤ ሁሉንም ስለሚይዝ አንዱንም በወግ አይሠራም። ስለዚህ፥ ልክ እንደ አንዳንድ የአገር መሪዎች ማገልገል ሳይሆን መስጋት ይይዘዋል። ስጋት የያዘው ሰው ደግሞ ደንባራ ነው፤ ኮሽ ባለ ቁጥር ከቆዳው ውስጥ ተመዝዞ ሊወጣ ይደርሳል፤ ተጠራጣሪ ይሆናል፤ የሚነገረውን ነገር ሁሉ ይተረጉማል፤ ምክር ዛቻ ይመስለዋል። ተግሳጽማ አይታሰብም፤ ሲያጠፋም ማንም ምንም አይለውም። ማንም የማይናገረው ይሆንና የቤተ ክርስቲያን ብቸኛ መሪ ይሆናል። በሂደት ሳያውቀው የቤተ ክርስቲያን ባልና ራስ ይሆንና ክርስቶስንም ይተካል።

አንድ ሰው ራሱን መሥራችና መሪ፥ ባለ ራእይና ባለ አደራ ብሎና አድርጎ የሚያስተዋወቅበት ሁኔታም፥ በመጋቢያዊ አመራር ስም ሁሉን በመዳፍ ስር በማድረግ ሁኔታም፥ እንዲህ ያለው ሰው ቤተ ክርስቲያንን እንደ ክርስቶስ መንጋ ሳይሆን እንደ ግል ኩባንያ አድርጎ ነው የሚያየው እና እንደ ግል ድርጅት መምራት ሳይሆን መግዛት ይታይበታል። ይህንን ከለመደ በኋላ ከላዩ ተቆርሶ የሚወሰድ ሥልጣን እንዲኖር አይፈልግም። ወንበር ማጋራት አይታሰብም። በዕድሜ ሁሉ ሥልጣኑ የራስና የብቻው

ነው። እንደዚህ ያለው ሰው ከወንበሩ በግድ ተገፍቶ፥ ወይም በሆነ ወደ አደባባይ በድንገት የወጣ የግብረ ወጥነት ጉዳይ ተገኝቶበት ካልሆነ በቀር አይወርድም። ሌላ መተካት አይታሰብም፤ አይገመትም። እንደ ካህኑ ዔሊ አርጅቶ ከወንበሩ ወድቆ እስኪሰበር ድረስ፥ ዕድሜው ካለፈ በኋላም፥ ከጃጀ በኋላም፥ ከሳተ በኋላም ተከፋይ ሆኖ ይኖራል። ይህ የተከፋይነት ጉዳይ የችግሩ ሌላ ዘርፍ ነውና በሌላው ሁለተኛውን 'ወ' ስናይ ለብቻ እንመለከተዋለን። እዚህ ግን እንደ ሁለተኛ ንዑስ ነጥብ አድርገን በትንሹ እንየው።

## ሁለተኛ፥ ንዋያዊ ወንበር

የንዋይን ወይም የገንዘብን ጉዳይ ለብቻው ራሱን በቻለ ርእስ ክርስቲያንና ወረት ወይም ንዋይ በሚል ርእስ ስር እንመለከተዋለን፤ እዚህ ግን ከሥልጣን አንጻር ሲታይ አንድ ነገርላይ ብቻ ማስታወሻ ማስቀመጥ ተገቢ ይሆናል። ወንበር ወይም ሥልጣን ከገንዘብ ጋርም የሚያያዝ ሆኖ ቤተ ክርስቲያኗ ወይም አገልግሎቱ ውሎ አድሮ የባለ ሥልጣኑ የራስ፥ የግል ድርጅት እንደሚሆን መታወቅ አለበት። የግል የሚለው ይሰመርበት። ኃላፊነቱ የተወሰነ ወይም ያልተወሰነ ምንም አክሲዮን የሌለበት የግል ኩባንያ ይሆናል፤ ኩባንያ ብቻ ሳይሆን መጦሪያም ነው።

ወንበሩን አልለቅም ባይነቱ ግን የሥልጣን ጉዳይ ሲሆን ተከፋይነቱ ከገንዘብ ጋር የተያያዘው ስሌት ነው። ንዋያዊ ሥልጣን ወይም ንዋያዊ ወንበር አምባ ገነን የአገር መሪዎች እስኪሞቱ እንደሚገዙት ብቻ ሳይሆን እስኪሞቱ ከገንዘብ ምንጩ እንደሚጠጡት ማለት ነው። ለነዚህ ባለ ወንበሮች ቤተ ክርስቲያን የማትነጥፍ የምትታለብ ጊደር ትሆንላቸዋለች። አምባ ገነኖች ተተኪ አያፈሩም፤ መትተካት ይፈራሉ፤ መተካትም ይፈራሉ። ከተኩም የራሳቸው ሥርወ መንግሥት እንዲሆን ከቤተ ሰብ ወይም ከቅርብ ዘመድ ነው የሚሾሙት። የአገልጋይ መስፈርት ያልናቸው ጸጋና ሸክም አይታዩም፤ ጥሪና ስልጠና ወይም ትምህርትም አይታዩም። ብቻ ቦታው ተይዞ እንዲቆይ ይደረጋል። የራሳቸውን ግዛተ ዓፄ ይመሠርታሉ ማለት ነው። በስነ አስተዳደር ይህ ኔፖቲዝም ይባላል። የአንድ ቤተሰብና ቤተ ዘመድ ድርጅት ይሆናል።

ከአምባ ገነንነት አልፈው አንዳንዶች መመልኮትና መመለክም ይጀምራሉ። መሥራችና ባለ ራእይ የሚሉቱ ባለ ሥልጣኖች ሰዎቻቸው ተከታዮቻቸው ናቸው። ተከታይ ሲባል ምንም ጥያቄ የማይጠይቁ ጭፍን ወይም እንደ ጋሪ ፈረስ አንድ አቅጣጫ ብቻ የሚያዩ ተከታዮች ናቸው። በተለይ ገንዘብን በተመለከተ የቼክ ፈራሚ፥ የመዝገብ ያዥ፥ የወጪ አዛዥ እርሱ ነው። እንዳልኩት ይህ ጉዳይ ራሱን ችሎ ከሦስቱ ወዎች

አንዱ ሆኖ ስለሚቀርብ ለብቻም እንመለከተዋለን። የመመለክና መመልኮት ወይም ዝናን ጉዳይም ለብቻው እናየዋለን።

## ሦስተኛ፥ መንፈሳዊ ሥልጣን

የዚህ የወንበር ጉዳይ ጎጂነት ሌላው ገጽታ የሥልጣኑ መንፈሳዊ ሥልጣንነት ነው። ሰዎቹ የሰው መንፈስ ወይም የሰው መንፈሳዊነት ወይም መንፈሳዊ ሕይወት ላይ የሚሠለጥኑ መሆናቸው ነው። ባለ ሥልጣኑ በፈለገ ነገራቸው ውስጥ ቃል ብቻ በመናገር ይገባል። በሕይወታቸው ምንም ነገር ያደርጋል፤ ያስደርጋል። እነዚህ ሰዎች ንብረትና ገንዘብን ይወስዳሉ፤ እንዳይናገሯቸው፥ እነሱን የሚናገር እንደሚቀሰፍ ያወራሉ፤ ያስወራሉ፤ ሁሉን አዋቂ ይመስላሉ፤ ኪሩቤልና ሱራፌል የመሰሉ አጃቢዎች በዙሪያቸው ይኮለኩላሉ፤ የማይመቿቸውን ሰዎች ከዙሪያቸው ያርቃሉ፤ ከአገልግሎት ያግዳሉ፤ ያስወግዳሉም። በአጭር ቃል፥ ልክ እንደ ዕቃ ዕቃ፥ አምላክ አምላክ መጫወት ይጀምራሉ። ሰዎቻቸውን እንደ ፈረስ ይጋልባሉ፤ ልጓም መያዝ ይወድዳሉ። መቆጣጠር ሱሳቸው ነው።

እነዚህ ሰዎች ሥራ ያስጥላሉ፥ የማይተዋወቁትን ያጋባሉ፥ የሚተዋወቁትን ይለያሉ። ትዳር ውስጥ ሲገቡ እንደ አማካሪ ሳይሆን እንደ ባለ ሥልጣን ነው። ሲገቡ ደግሞ ትዳርን በመረበሽም ነው፤ ቅርም ሳይላቸው ትዳርን ያፈርሳሉ፤ ባልና ሚስትንም ይለያሉ፤ ያፋታሉ። ቆይተው የለየላቸው የስሕተት አስተማሪዎች፥ የኑፋቄ መሪዎች ስለሚሆኑ ይህንን በግልጽ ወይም በድብቅ ይፈጽሙታል። ይህ የወንበር አፍቅሮት መዘዙም አደጋውም ከባድ ነው። የወንበር ፍቅር ክፉ ነው፤ ሥልጣን በራሱ መልካም ሆኖ ሳለ፥ ገደብ ከሌለው አደጋ አለበት። 'ሥልጣን ያባልጋል፤ ፍጹም ሥልጣን ደግሞ ፍጹም ባለጌ ያደርጋል' የሚባል የእንግሊዝኛ አነጋገር አለ። Power corrupts; absolute power corrupts absolutely. ይላሉ። ሥልጣን ያባልጋል፤ ያበላሻል።

የአንድ ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን ስናስብ ወይም ስንሆን ይህንን የሥልጣን አያያዝም እንጠይቅ፤ እንፈትሽ። የቤተ ክርስቲያኒቱን መተዳደሪያ ደንብ እንጠይቅ፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ በአስተምህሮ ንጹሕ ከመሆኗ፥ ወንጌል ላይ የምታተኩር ከመሆኗ፥ ቃሉን የምታስተምር ከመሆኗ፥ ደቀ መዛሙርት የምታደርግ ከመሆኗ ጋር፥ (እነዚህ ዋና ዋናዎቹ ሆነው) አስተዳደሩ የቡድን ነው ወይስ የግለሰብ? የሥልጣን ተዋረድ ምን ይመስላል? የተጠያቂነት ጉዳይስ? የገንዘብ አያያዝ ንጽሕና የተጠበቀና ግልጽ ነው? የሚሉትንም እንጠይቅ። የመተዳደሪያ ደንብ ስትጠይቁ አለመኖሩ ሲነገራችሁ፥ ወይም ያልሆነ የማይጥም መልስ ሲሰጣችሁ፥ ወይም ደንቡ በአጭሩ የተጻፈበት አንድ ወይ

ሁለት ገጽ፥ ወይም ድረ ገጽ ላይ የሚገኝ የእምነት አንቀጽ እንደ ደንብ ተቆጥሮ ከተሰጣችሁ፥ ይህ ችግር መኖሩን ጠቋሚ ነው። ወደዚህች ቤተ ክርስቲያን ይህንን አውቀን ስንገባ ችግር ለመጋፈጥ እንግባ፤ ወይም መጋፈጥ የማንፈልግ ከሆንን አንግባ። ሌላ ቤተ ክርስቲያን እንፈልግ።

ከችግሩ ጋር መፍትሔውንም አብረን እንይ። በቀደመው ክፍል ጌታ ከማቴ 23 ስለ እልቅና ለደቀ መዛሙርቱ የተናገረውን ስናይ፥ ያ የጌታ ትምህርት የሥልጣን ሞዴል ነው ማለት ይቻላል። ከኛ ማናችንም በሌላው ላይ ባለ ሥልጣን አይደለንም። መሪዎች ከሆንንም አገልጋይዮች ወይም አገልጋይ መሪዎች ወይም በቡድን ውስጥ አቻ መሪዎች ነን።

ቤተ ክርስቲያን ሁለት ነገር ናት፤ አካልም፥ ዘአካልም ናት። አካላዊ ድርጅት ናት፤ ሕያው ወይም መንፈሳዊ ዘአካልም ናት። በእንግሊዝኛ organization እና organism የሚባለው ማለት ነው። እንደ ዘአካል ክርስቶስ ራሷ የሆነች መንፈሳዊ ማንነት አላት። አዲስ ኪዳን ይህን በግልጽ ያስተምራል፤ ለምሳሌ፥ ኤፌ. 1፥22-23 *ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው። እርስዋም <u>አካሉና</u> ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት።* ይላል። ቆላ. 1፥18 *እርሱም <u>የአካሉ</u> ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፤ እርሱም በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ፥ መጀመሪያ ከሙታንም በኩር ነው።* ይላል። ይህ አካል ቤተ ክርስቲያን ከተወለደችበት ከበዓለ ኀምሳ ዕለት እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ ያሉትን አማኞች ሁሉ ያቅፋል። አሁን ያሉትን እውነተኛ አማኞችም ሁሉ ያቅፋል። ይህች ቤተ ክርስቲያን ናት፤ ይህች አካል ወይም ዘአካል ናት። የዚህች  አካል ራስ ክርስቶስ ነው።

እንደ ድርጅት አካል ደግሞ የሰዎች ስብስብ ናት። በአንድ አጥቢያ ወይም አካባቢ የሚገኙ ቅዱሳን ተሰባስበው የሚያመልኩበት፥ የሚያገለግሉበትና ወንጌልን የሚሰብኩበት ማኅበር ናት። የአጥቢያ ማኅበር ራስም ክርስቶስ ነው። ስለሆነም፥ ይህ የሰዎች ማኅበር የሰዎች መሪዎች ያስፈልጉታል። ይህ የሰዎች መሪዎች አመራር ወይም መዋቅር፥ ቀደም ሲል እንዳየነው ሊለያይ ቢችልም፥ ዓይነተኛው አመራር የቡድን አመራር ነው። የቡድን አመራር ማለት አንድ ሰው የማይሠለጥንበት፥ ባለ ሙሉ ሥልጣን የማይሆንበት፥ ልክ እንደ አገር አምባ ገነን ሰው ጠቅላይ ገዢ የማይሆንበት አሠራር ነው።

መሪ ደግሞ መሪ ብቻ ሳይሆን ተከታይም ነው። በዮሐ. 21፥15-18 ጌታ ጴጥሮስን ሦስት ጊዜ ደጋግሞ እንደሚወድደው ሲጠይቀውና ትልልቅ ኃላፊነቶች ሲሰጠው እናያለን። ግልገሎቼን አሰማራ፤ ጠቦቶቼን ጠብቅ፤ በጎቼን አሰማራ፤ ብሎት፥ በምን ዓይነት ሞት እንደሚሞት አስረድቶትም ከጨረሰ በኋላ፥ ቁጥር 19፥ *ይህንም ብሎ፦ ተከተለኝ*

*አለው።* ይላል። ይህ አስማሪና ጠባቂ መጋቢ ሆኖ ተከታይም ነው። መሪ እረኛ ተከታይ እረኛ ነው፤ የትልቁ እረኛ ተከታይ ነው። ይህ ጴጥሮስ እራሱ ስለ ትልቁ እረኛ ወይም ስለ እረኞች አለቃ በመልእክቱ ውስጥ ጽፏል፤ በ1ጴጥ. 5፥2-4 ይህንን አለ፤ *በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፥ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጐብኙት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ።*

ተከታይ መሪ እንዲህ ያለ እረኛ ነው። መንጋውን የሚጠብቅ፥ የሚጎበኝ፥ እንዴት? እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ፥ በግድ ያይደለ፥ በውድ፥ በበጎ ፈቃድ፥ መጥፎ ረብ ወይም የግፍ ገንዘብ ባለመመኘት። ምሳሌ የሚሆን፥ በኃይል የማይገዛ፥ የማይሠለጥን። ይህ ነው ተከታይ መሪ፥ ለተከታይ መሪዎች የሰጠው ምክር። *ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ* ሲል ነው። ምሳሌነትን ትቶልን ነው፤ 1ጴጥ. 5፥3። ጴጥሮስ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ ሲል ራሱም ሆኖ ነው። የመሪነትን ተግባር ወይም ዓይነተኛ የመሪ ባሕርያትና ምሳሌዎችን በቃሉ ውስጥ በብዛት እናገኛለን።

ከአዲስ ኪዳን ሌላ አንድ መሪ ሰውን እንደ ናሙና እንይ፤ ጳውሎስን። ጳውሎስ ብዙ መለዮዎችን የለበሰ ሰው ነው። ሐዋርያ፥ ወንጌላዊ፥ ሰባኪ፥ አስተማሪ፥ መሪ የሆነ ሰው ነው። ጳውሎስ ደብዳቤ ከጻፈላቸው አብያተ ክርስቲያናት አንድዋ የፊልጵስዩስ ቅዱሳን ማኅበር ናት። ሲጽፍላቸው ራሱን እንደ ባሪያ ሲጠቅስ፥ የቤተ ክርስቲያኒቱን መሪዎች ደግሞ፥ 'ከኤጲስ ቆጶሳትና ከዲያቆናት ጋር' ተብሎ ነው። እዚህም የቡድን አመራር ይታያል። ኤጲስ ቆጶስ የሚለው ቃል ከላይ ሆኖ የሚያይ ማለት ሆኖ መሪን ያመለክታል። አንድ ኤጲስ ቆጶስ ሳይሆን ኤጲስ ቆጶሳት ተብሎ ብዙ መሆናቸው ደግሞ የቡድን አመራርን ያመለክታል። ዲያቆን ማለት የጉልበትም፥ የአእምሮም፥ የጥበብም ሥራ የሚሠራ ሠራተኛ ወይም አገልጋይ ማለት ነው። ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አንጻር ስናየው የአገልግሎቱ ግብ በመንፈሳዊው አገልግሎት ዘርፍ፥ በተለይም ቃሉን በማስተማር የሚተጉት በሌሎች የቤተ ክርስቲያን ሥራዎችና ተግባራት እንዳይጠመዱ ከትከሻቸው ይህንን የተግባር ኃላፊነት መውሰድና ማቅለል ነው።

የዲያቆናትን አገልግሎት ጅማሬ በቤተ ክርስቲያን የምናየው በሐዋ. 6 ነው። በሐዋ. 6፥2-4 *አሥራ ሁለቱም ደቀ መዛሙርት ሁሉን ጠርተው እንዲህ አሉአቸው። የእግዚአብሔርን ቃል ትተን <u>ማዕድን እናገለግል ዘንድ</u> የሚገባ ነገር አይደለም። ወንድሞች ሆይ፥ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፥ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን፤ እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን* ይላል። በጥቅሱ ውስጥ ያሰመርኩበት፥ ማዕድን

እናገለግል ዘንድ የሚለው ሐረግ *διακονεῖν τραπέζαις* (ዲያኮኔዪን ትራፔዛይስ፤ ጠረጴዛ እናገለግል ዘንድ) የሚለው ዲያቆን የሚለው አገልግሎትና ስያሜ በቤተ ክርስቲያን ጅማሬ ነው። እነዚህ ዲያቆናት፥ አገልጋዮች፥ ሠራተኞች ናቸው። የቃሉና የጸሎት ሥራ እንዲሮጥ እነዚያን የሚያሮጡትን የሚረዱ አርድዕት ወይም ረዳቶች፥ አጋዦች ናቸው።

ይህ የመሪዎች ብዛት የሚያሳየን በቤተ ክርስቲያኒቱ አንድ ዋና መሪ ሳይሆን የቡድን መሪዎች መኖራቸውን ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ ሰው ብቻውን ልፋት ከሆነ መልፋት፥ ሥልጣን ከሆነም መሰልጠን የለበትም። በእርግጥ መሪ የሚሆን፥ ቀዳሚ፥ ዋነኛ የሚሆን ሰው ማስፈለጉ እውነት ነው። ያም ከብጤዎች መካከል የሆነ መሪ የሚመራው የቡድን አመራር ነው እንጂ አንድ ሰው በአምባ ላይ የሚገነንበት አይደለም። የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ጳውሎስ መልእክት ከጻፈላቸው ቤተ ክርስቲያኖች መካከል በውበትና በደስታ፥ በአገልግሎትና በትጋት፥ በስደትና በመጽናት የተመሰገነች ቤተ ክርስቲያን ናት። ይህች ቤተ ክርስቲያን ትመራ የነበረውም በአንድ ሰው ሳይሆን በቡድን መሪዎች ነበረ። ይህ ዓይነተኛው አመራር ናሙና ነው።

የቡድን አመራር ከጥንት ከመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያንም ጀምሮ የነበረ ሁነኛው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር ስልት ነው። የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የተመራችው በሐዋርያትና በሽማግሌዎች ነበር። አንድ ሐዋርያ፥ 'ሊቀ ሐዋርያት' ተብሎ አልተሾመም። ሐዋርያት ብቻም ሳይሆኑ ሽማግሌዎችም አብረው ነበሩ። እርግጥ ጌታ ኃላፊነትን ሰጥቶታል፤ ያ ግን የተለየ ሹመትና ሥልጣን ሆኖ በሐዋርያት ሥራ ውስጥም በጴጥሮስ መልእክቶች ውስጥም አልታየም።

በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንደምናየው ያለው የጴጥሮስ ሊቀ ሐዋርያነት በሐዋርያት ሥራ ወይም በጠቅላላው አዲስ ኪዳን ውስጥ አይታይም። ግዝረትን የተመለከተው የመጀመሪያው የአስተምግሮ ውዝግብ በተከሰተ ጊዜ ክርክሩን ሊፈቱ የተቀመጡት እነዚህ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ነበሩ፤ *ሐዋርያትና ሽማግሌዎችም ስለዚህ ነገር ለመማከር ተሰበሰቡ፤* ሐዋ. 15፥6። በጉባኤው ጴጥሮስና ያዕቆብ የጎላ ነገር መናገራቸው ተጽፎአል። በምዕራፉ መጨረሻ ችግሩ ለተከሰተባት ለአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ደብዳቤ ሲጽፉ፥ ላኪዎቹ፥ *ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ወንድሞችም* ነበሩ። እንዲሁም 'እኛና መንፈስ ቅዱስ' ብለው ነበር የጻፉት፤ ሐዋ. 15፥23-29። የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን አመራርና ከዚያ የተከተሉት አብያተ ክርስቲያናት አመራር የነጠላ ሰው ከቶም አልነበረም። ስለዚህ፥ ይህ ልንከተለው የተገባው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ፈለግ መሆን አለበት።

በቤተ ክርስቲያን በተለይም ከቅርብ ዓመታትና ዐሥርታት ወዲህ በቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ቤተ ክርስቲያንን አጋር ድርጅቶች ውስጥ በሥልጣን የሚባልጉና ከንዋይ ላይ እጃቸው እንዳይነሣ የሚፈልጉ ሰዎች መፍላታቸው ገሃድ ሆኖአል። ይህ አሳሳቢ ጉዳይ የአንድ ሰው ብቻ መሪነትን የሚያጎላ ብቻ ሳይሆን ለአደጋና ለውድቀት የሚዳርግ ክፍት በር ተደርጎ የሚታይ የመሪነት ስልት አድርጎታል። ብቸኛ መሪነት ባለበት ስፍራ መሪው ባይወድቅም እንኳ የሚወድቅበት ገደል ሣይርቅ እንደሚከተለው እርሱም ሌሎችም፥ እኛም ልንገነዘብ ያስፈልጋል። የዚህን መጣጥፍ አዝማች ልድገመው፤ ሁነኛው የቤተ ክርስቲያን አመራር ነጠላ ሳይሆን የቡድን አመራር ነው።

የዘንድሮ ሐዋርያት እንደ ቃሉ ትርጉም የሐወሩ ሐዋርያት ወይም የሄዱ መልእክተኞች፥ ቤተ ክርስቲያን ወንጌል አስጨብጣ፥ መርቃ፥ ወንጌል ወዳልሰሙት የሰደደቻቸው ሳይሆኑ እንደ ጀነራል ወይም ሊቀ መንበር የመሰለ ሹመት የተቀዳጁና የበዓለ ሢመት ድግስ ተደግሶ የተቀበሉት ሥልጣን መሆኑ ነው ችግሩ። የዘመናችን 'ሐዋርያት' ብለው በራሳቸው እጅ ራሳቸውን የቀቡ ሰዎች እንደ ብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት በካህናት ላይ ከፍ ሊሉ የሚወዱ፥ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የመግባት ብቸኛ ቶምቦላ የወጣላቸው የሚመስላቸው፥ በአገልጋዮችና በአብያተ ክርስቲያናት ላይ ሊሰለጥኑ በኩራት የሚራመዱ ልዩ ባለ ማዕረጎች ናቸው።

ጳውሎስን የመሰለ ተግባራዊ ሐዋርያ በቃሉ ውስጥ አላየሁም። የላከችው የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ግን መለከት አስነፍታና ቃለ አዋዲ አስነግራ፥ ጉባኤ አስጠርታና ድግስ ደግሳ ሳይሆን ጸልያ፥ እጅ ጭና ነው የላከችው፤ ሐዋ. 13፥1-3። ተልእኮውን ሲፈጽምም ወደዚያችው ወደላከችው አጥቢያ ተመልሶ ዘገባ ያቀርብ ነበር፤ ለምሳሌ፥ ሐዋ. 14፥ 26-28። ጳውሎስም ራሱን ሐዋርያ፥ መጋቢ፥ አስተማሪ ብሎ ጠርቷልና እነዚህ ስሞች ከኃላፊነት ጋር ተቋጥረው የተሰጡት ነው። ጳውሎስ ጥቂት ባልሆኑ መልእክቶቹ፥ ራሱን ሐዋርያ (ማለትም መልእክተኛ) እያለ ጠርቶአል። የቃሉ ትርጉምም መልእክተኛ ማለት ነው። ራሱን እንዲህ ሐዋርያ እያለ ከጠራባቸው ቦታዎች መካከል እነዚህ ይገኛሉ፤ *ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ* (ሮሜ. 1፥1)፥ *በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ* (1ቆሮ. 1፥1)፥ *በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ ጳውሎስ* (2ቆሮ. 1፥1)፥ *በኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታንም ባነሣው በእግዚአብሔር አብ ሐዋርያ የሆነ* (ገላ. 1፥1)፥ *በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ ጳውሎስ* (ኤፌ. 1፥1)። ለፊልጵስዩስ ምእመናን ግን ባሪያ ማለቱ በምን ምክንያት ይሆን? ስለምን ራሱን ባሪያ አለ? ይህ ዓይነተኛ ጥያቄ ነው።

የፊልጵስዩስ መግቢያ የሆነውን ሐዋ. 16ን ስንመለከት ፊልጵስዩስ የሮም ቅኝ ከተማ መሆኗን እናገኛለን። ይህ ማለት ከተማዋ ወይም የከተማዋ ሕጋዊ ነዋሪዎች ነፃና የሮም

ዜግነት ከሙሉ መብቱ ጋር የተሰጣቸው ሰዎች ናቸው። ፊልጵስዩስ የሮሜ ዜግነት በቅኝነቷ ምክንያት በሮሜ መንግሥት ቸርነት እንዲያው የተሰጣት ከተማ ናት። ባሪያዎች የሉባትም ማለት አይደለም። ሆኖም፥ የከተማዋ ሕጋዊ ነዋሪ ሁሉ ባሪያ ተብሎ የማይጠራባት፥ በዜግነቱ፥ በመብቱ የሚኮራባት ከተማ ናት። እንደዚህ ባለች ከተማ ለሚኖሩ አማኞች፥ ባርነት ጸያፍና ነውር በሆነበት ሥርዓት ባሪያ ብሎ ራስን ማስተዋወቅ ያሳፍራል። ግን *የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያዎች* ብሎ ጻፈ።

ደግሞም ሐዋ 16ን ስናይ ራሱ ጳውሎስም የሮሜ ዜጋ ሳለ የሮሜ ዜግነቱን እንዳልተጠቀመበት ይታያል። ሲደበደብና ሲታሰር፥ 'እኔ እኮ ሮማዊ ነኝ!' አላለም። በተደበደበ በማግስቱ ግን፥ አንድ ቤተ ሰብም በግሩም ወደ ጌታ ከመጣ በኋላ፥ ዜጋ መሆኑን ተናገረ። በመብትና በነፃነት በሚኩራሩ ሰዎች መካከል ኃላፊነትና ግዴታን የሚያውቅና የሚያሳውቅ ሰው መኖሩ አስፈላጊ ነው። ባሪያዎች ጌታ ያላቸው፥ ባለቤት ያላቸው፥ የወደደውን የሚያደርግ፥ ወደፈለገበት የሚልክ፥ ሲፈልግ ተነሡ፥ ሲፈልግ ተቀመጡ የሚል ባለቤት ያላቸው ናቸው። ጳውሎስና ጢሞቴዎስ ባሪያዎች ናቸው። ጳውሎስ መሪ ነው፤ በእርግጥ መሪ ነው። ግን ባሪያም ነው።

ጳውሎስ በፊልጵስዩስ መልእክቱ ስለ ጌታችን እንኳ ሲናገር (ፊል. 2፥7) ነገር *ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፥* ይላል። ጳውሎስ የጌታን የባሪያ መልክ በገለጠበት መልእክት ውስጥ ራሱን እንደ ባሪያ ባያቀርብ ስሕተት ስለሚሆን ብቻ ሳይሆን በእርግጥም በዋጋ የተገዛ ባሪያ መሆኑን ስላወቀ ነው ጳውሎስ ይህን ባሪያ የሚል ቃል የተጠቀመው። የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆን ያስተማረው ራሱ ጌታችንም አገልግለን ስናበቃ፥ *እንዲሁ እናንተ ደግሞ የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ የማንጠቅም ባሪያዎች ነን፥ ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል በሉ* አለ፤ ሉቃ. 17፥10። ጳውሎስ ሐዋርያ ነው፤ መሪ ነው፤ ባሪያ ደግሞ ነው። ሐዋርያ ባሪያ ነው፤ መሪ ተከታይ ነው።

ጳውሎስ እንደ መሪ ዓይነተኛ ናሙናም ነው። ሌሎች እንዲመስሉት፥ ፈለጉን እንዲከተሉ፥ እንዲኮርጁትም ግልጽ ሰው ነበረ። በፊል. 3፥17 *ወንድሞች ሆይ፥ እኔን የምትመስሉ ሁኑ፥ እኛም እንደ ምሳሌ እንደምንሆንላችሁ፥ እንዲሁ የሚመላለሱትን ተመልከቱ።* በፊል. 4፥9 ደግሞ፥ *ከእኔ የተማራችሁትንና የተቀበላችሁትን የሰማችሁትንም ያያችሁትንም እነዚህን አድርጉ፤ የሰላምም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል* አለ። *ያያችሁት* ካለ እርሱ ሲያደርግ ያዩት ነገር አለ፤ አድራጊ ነው ማለት ነው። በ2ተሰ. 3፥9 ደግሞ፥ *ይህም እኛን ልትመስሉ ራሳችንን እንደ ምሳሌ እንሰጣችሁ ዘንድ ነበር እንጂ፥ ያለ ሥልጣን ስለ ሆንን አይደለም* አለ።

እግዚአብሔር ዋጋን የሚከፍል አምላክ ነው። ፍጹም ደመወዝን የሚሰጥ አምላክ ነው። እርሱንና ሕዝቡን የምናገለግለው ወደንና ፈቅደን ነው። ለጥቅም አይደለም፤ ለክፍያ አይደለም፤ ከሆነ ግንኙነቱ የሽርክና ሊሆን ነው። የ'አደርግልሃለሁ አድርግልኝ' ሊሆን ነው። ብዙ ሰዎች፥ ብዙ አገልጋዮች በዚህ ዘመን አገልግሎትን ከገንዘብና ከሥልጣን ጋር አያይዘው ያዩታል። ስላገለገሉ የሚገባቸውን ስለሚያገኙት ሰዎች ይህን አልልም፤ ይህ ተገቢ ነው። ግን ለሥራው ባለቤትና ለማንነቱ ሲሉ ሳይሆን ከባለቤቱ ለሚገኘው ጊዜያዊና ሥጋዊና ምድራዊ ጥቅም ሲሉ፥ ለዚያ ነገር ብቻ ሲሉ የሚያገለግሉትን ማለቴ ነው። የሚያሳዝነው ደግሞ ያንን ጥቅም ለማግኘት የሕዝቡን እጅ ሲጠመዝዙና በሕዝቡ ላይ ሲሰለጥኑ ሲታይ ነው።

ሥልጣንን ስናስብ ከአዲስ ኪዳን ጳውሎስን እንደ ምሳሌ አየን። ከብሉይ ኪዳን ደግሞ አንድ መሪ እንደ ናሙና እንይ። ነህምያን። ነህምያ ምሳሌ የሆነ መሪ ነው። ሲጀመር ከምቾት ስፍራ፥ ከቤተ መንግሥት፥ ከንጉሥ ጠጅ አሳላፊነት (ወይም ጠጅ ቀማሽነት) ተነሥቶ ወደ ጎስቋላ ከተማ ሄዶ ጥገና መጀመር፥ ወደ ኢየሩሳሌም ከመምጣቱ በፊት ደግሞ ለወራት እስኪጠወልግ ድረስ መጦምና መጸለይ፥ የሸክምና የጥሪ ጉዳይ ነው። ወደ ኢየሩሳሌም ከሄደ በኋላ፥ ሐቴርሳታ ወይም የገዢ ያህል ሥልጣን ያለው ቢሆንም፥ ነህምያ በሕዝቡ ወይም በሰዎች ላይ ሲሠለጥን አይታይም። መልካም ካደረገ በኋላ፥ 'አምላኬ በመልካም አስበኝ' ጸሎቱ ነበረ። ሰዎች እንዲያሞካሹት ሳይሆን አምላኩ እንዲያስበው ነበር ልመናው።

ነህምያ መለዮ ቀያያሪ መሪ ነበረ፤ አናጢና ግንበኛ ነበረ፤ ስልት ነዳፊና የጦር መሪም ነበረ፤ በጦርነቱ ወቅት ዘብ አስቁሞ ለጥ ብሎ መተኛት ሲችል እንደ ሌሎቹ ልብሱን ሳያወልቅ ይተኛ ነበረ፤ ለአለቃ የሚገባውን ስንቅ አልጠየቀም፤ እንዲያውም ለ12 ዓመታት መደበኛ ቀለብ ብቻ ይቀበል ነበር እንጂ የአለቃ ዳረጎት አልጠየቀም፤ እንደ መሪ ራሱን መጠበቅና መደበቅ ሲችል አላደረገም፤ ለንዝነዛና ለሐሜት ግድ አልነበረውም፤ በውሸት ሲከሰስ ስሙን ለመጠበቅ ከመስመር ወጥቶ አልሄደም፤ እንደ ከተማዋ ቅጥርና እንደ ግንቡ የሕዝቡን ሞራላዊ፥ ማኅበራዊና መንፈሳዊ ግንባታ ሳይታክት የፈጸመ መሪ ነው፤ የሕዝቡን ዕዳ ሲያስምር፥ ሲያስተው እርሱ ራሱም ዕዳና ብድር የተወ ምሳሌ ነው፤ መሪዎች ከኋላ ሆነው እየነዱ እነርሱ የማያደርጉትን፥ 'አድርጉ' እያሉ ሲያዝዙ እና ምሳሌ ሆነው እያደረጉ 'አድርጉ ወይም እናድርግ' ሲሉ የተለያየ ነው። ሕዝቡን ከድብልቅነት ሲያጸዳ የጨከነ መሪ ነበረ። ነህምያ ዓይነተኛ መሪ ነው።

መሪዎች የማያደርጉትን ነገር ሲያስደርጉ ያንን መብትና ሥልጣን ከየት እንዳገኙት ማስፈተሽ አለባቸው። ጳውሎስ ወይም ነህምያ፥ ከሁሉም በላይ ክርስቶስ፥ መብታቸውን የተዉ መሪዎች ነበሩ። በተለይ ክርስቶስ። መለኮት እያለ፥ ምንም

ያልጎደለው አምላክ እያለ፥ ራሱን ባዶ አደረገ። ወንበር ወይም ሥልጣን አደገኛ ጠላፊ ነው። በ90ዎቹ መጀመሪያ በጀመርናት አንዲት ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያና የውስጥ አሠራር ደንብ፥ መጋቢ በጊዜው ገና ባይኖረንም እንኳ፥ በሚኖርበት ጊዜ መጋቢው ከመጋቢነቱ ጥሪና ኃላፊነት ባሻገር አስተዳደርን በተመለከተ ከሽማግሌዎች ጋር እንደሚሠራና ገንዘብን ግን ጭራሽ መንካት እንደሌለበትም በግልጽ አሰፈርን። ከዓመታት በኋላ ለመጋቢነት ከታጩት መካከል አንዱ መጥቶ ከጠየቃቸው ቀዳሚ ጥያቄዎች አንዱ የገንዘብ ወጪና ገቢዋን ደብተር ለማየት መፈለጉ ነበር። ሌሎችም እጩዎች በየተራ መጥተው አገለገሉና፥ ይህኛው ሰው መጋቢ ሆኖ ተመረጠ፤ ተሾመ። ብዙም ሳይቆይ አንድ ቀን ከአንድ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌ ጋር፥ 'እንደዚህ መተዳደሪያ ደንብ ለእግዚአብሔር ሥራ እንቅፋት የሆነ ነገር የለም።' አሉ። ይህ መጋቢ የፈለገው ነገር አስተዳደሩንም ገንዘቡንም ለብቻው መቆጣጠር ነበረ። አሳዛኙ ነገር፥ ሁለቱም፥ ሽማግሌውም መጋቢውም፥ እዚያ አልቆዩም። በተለይም መጋቢው ከዚያችው ሲያገለግላት ከነበረችው ቤተ ክርስቲያን ገምሶ ወጣና ሌላ ማኅበር መሠረተ። ችግሩ ምን ነበር? ሥልጣንና ገንዘብ።

ሥልጣንን ግባቸው ያደረጉ ሰዎች፥ ብዙዎቹ በማንም ያልተሾሙ ብቻ ሳይሆኑ አንዳንዶች ራሳቸውን በራሳቸው የሾሙ ናቸው። የራሱን ዘውድ በገዛ እጁ እንደደፋው ናፖሊዎን። ከታሪክ ውስጥ ናፖሊዮን የጉልበተኛና እብሪተኛ መሪነት ሁነኛ ምሳሌ ነው። ዣክ ሉዊ ዴቪድ የተባለ ፈረንሳዊ ሰዓሊ የሳለውና በይፋ ያላለቀው የናፖሊዮን በዓለ ንግሥ ስዕል በጣም ገላጭና ታሪኩ በሆነበት ጊዜ የነበረውን መልክ ያስቀመጠ ነው። ናፖሊዮን ቀድሞ የመንግሥት ግልበጣ ቢያደርግም ለንግሥ ያጨውና ያነገሠው ሴኔቱ ነበር። ናፖሊዮን ለበዓለ ሢመቱ የሮማውን ጳጳስ በክብር ቢያስመጣም በመጨረሻ ዘውዱን ጳጳሱ ይደፋለታል ተብሎ በሁሉ ሲጠበቅ፥ በራሱ ላይ የደፋው በገዛ ራሱ እጅ ነበረ። ይህን ካደረገ በኋላ የሚስቱን የጆዜፊንን ዘውድ ደግሞ ራሱ ጫነላት። ራስን በራስ መቀባት እንዲህ ነው! ዛሬም በራሳቸው እጅና በራሳቸው ቅባት የተቀቡና፥ ከተቀቡ በኋላ አይደረሴ የሆኑ ብዙ አሉ። የወንበር ፍቅር!

በኤፌ. 4፥11-12 ያለው *እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤* የሚል በሐዋርያት ጀምሮ በአስተማሪዎች የሚጨርሰው ዝርዝር መነሻ ነው የብዙዎች ቀልብ የተወሰደበት። ሐዋርያትና ነቢያት ላይ ያለው ትኩረት አዲስ የሐዋርያትና ነቢያት መሠረት እየተጣለ ያለም አስመሰለው። ቤተ ክርስቲያን ቀድሞውኑ በነቢያትና ሐዋርያት መሠረት ላይ ከተመሠረተች (ኤፌ. 2፥19) ይህ ለምን እንዳስፈለገ አይናገሩም። ይህ አሐዳስ (አዲሱ ሐዋርያዊ ዳግም ሥሪት) የወለደው አዲስ ንቅናቄ ነው። ቁርበቱን ጫር ጫር ስናደርገው ሥጋው ሥልጣን ነው። አንዴ እርካብ

ከተቆናጠጡ በኋላ መከላከያ አጥር አጥረው አትድረሱብን ይላሉ። ዋና ጥቅስ አላቸው፤ ‘የቀባኋቸውን አትዳስሱ’ የሚል። እነዚህ ከመደዴው አማኝ እየራቁ 'ጨርቃቸውም ጥላቸውም' የማይደረስበት ሆኑ፤ ለበነ እንኳ እንዳይዳሰሱ። ቅባት የሚሉት ነገራቸው፥ የጸጋና የማዕረግ ጉዳይ ሳይሆን የሹመት ጉዳይና የሥልጣን ጥም ነው። ለአገልግሎት ሳይሆን ለሥልጣን፤ ለወንበር!

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከዐውደ ምንባቡ ፈልቅቀው ከወቀሳና ከተግሳጽ ለመዳን ሲፈልጉ እንደ ባንዲራ የሚያውለበልቡት ይህ ‘የቀባኋቸውን አትዳስሱ’ የሚለው ሐረግ የተወሰደው ከመዝ. 105፥14-15 ነው። ጥቅሱ እንዲህ ይላል፥ *የቀባኋቸውን አትዳስሱ፥ በነቢያቴም ክፉ አታድርጉ ብሎ፥ ሰው ግፍ ያደርግባቸው ዘንድ አልፈቀደም፥ ስለ እነርሱም ነገሥታትን ገሠጸ።* ጥቅሱን ብቻ ሳይሆን ምዕራፉን በመላው በቦታው ስናጠና ይህ ቃል የተጻፈው ወይም የተዘመረው በታሪካዊ ትውስታነት ሲሆን ቃሉ መፈተሽ ስለሌለባቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሳይሆን እግዚአብሔር ተስፋ ስለሰጣቸውና ቃል ስለገባላቸው ስለመጀመሪያዎቹ የአይሁድ አባቶች ሆኖ እናገኘዋለን። ይህ ሐረግ በኋላ በሕጉና በሥርዓቱ ውስጥ የኪዳኑ ሕዝብ መሪዎችና ካህናት ሊሆኑ ስለተቀቡ ሰዎችም እንኳ የተነገረ አይደለም። ይልቁንም ስለ አዲሱ ኪዳን አማኞችና ደቀ መዛሙርት፥ አገልጋዮችና መሪዎችም የተነገረ ከቶም አይደለም። ስለ ሥልጣን ጥመኞችማ ፈጽሞውኑ አይደለም። ጥቅስን ያለቦታው መሰንቀር ከትጉህ የቃሉ አስተማሪዎች የማይጠበቅ ነው። ይልቁንም ለራስ ሥልጣን የራስ ጠበቃና ሥልጣን አስከባሪ መሆን ከአገልጋይ የሚጠበቅ ባህርይም አይደለም። በእውነቱ ‘አገልጋይ’ የሚለው ቃል በፍጥነት እየሳሳና ከእይታ ውጪ እየሆነ እየመጣ ነው።

በእርግጥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መሪዎችና አገልጋዮች ማክበር ሊያጠያይቅ የተገባ ወግ አይደለም። በብሉይ ኪዳን ዘመን ይከበሩ ነበር። ለዚህ ክብር ውብ ምሳሌ የሚሆንልን ሰው ራሱም ተቀብቶ የነበረው ዳዊት በዘመኑ ንጉሥ ሆኖ የተቀባውን ሳኦልን ሊያጠፋው ሲችል ነፍሱን ደጋግሞ ያለማጥፋቱ ብቻ ሳይሆን ‘የተቀባ’ እያለ ማክበሩ ነው። ራሱም የተቀባ ሳለ እንዲህ ማድረጉ ሌሎቹ ከዚህም በላይ ሊያደርጉ እንዲጠበቅባቸው ጉልህ አስረጅ ነው።

ወደ አዲስ ኪዳን ስንዘልቅ አገልጋዮች ‘አክብሩን’ ሲሉ ሳይሆን ‘አክብሩአቸው’ ሲባል እናያለን። የጳውሎስ የራሱ አገልግሎት ክብርን ወደራሱ የሚስብ አገልግሎት አልነበረም። ለተሰሎንቄ ምእመናን እንዲህ አለ፥ *የክርስቶስም ሐዋርያት እንደ መሆናችን ልንከብድባችሁ ስንችል፥ ከእናንተ ቢሆን ወይም ከሌሎች ክብርን ከሰው አልፈለግንም፤* 1ተሰ. 2፥6። የጳውሎስ ዒላማ አክብሮት ከቶም አልነበረም። 1ጢሞ. 5፥17 እንዲያውም ስለ እጥፍ ክብር እንዲህ ይላል፥ *በመልካም የሚያስተዳድሩ*

*ሸማግሌዎች፥ ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት፥ እጥፍ ክብር ይገባቸዋል።* ይህ እውነት ነው። እነዚህ በመልካም የሚያስተዳድሩ፥ በመስበክና በማስተማርም የሚደክሙ ናቸው። መልካም አስተዳዳሪዎች ከሆኑና በመድከም የሚያገለግሉ ከሆኑ እነዚህም እንደምን በደስታ ሊከበሩ ይገባል! እነዚህ 'አክብሩን' እያሉ በግንባራቸው ራስ ወርቅ የሚያስሩ ገዥዎች ሳይሆኑ ሌሎች አክብሩአቸው እያሉ የሚናገሩላቸው ሁነኛ መሪዎች ናቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ምእመናን ስለ አፍሮዲጡ ሲጽፍ፥ *እንግዲህ በሙሉ ደስታ በጌታ ተቀበሉት፥ እርሱን የሚመስሉትንም አክብሩአቸው፤ በእኔ ዘንድ ካላችሁ አገልግሎት እናንተ ስለሌላችሁ የጎደለኝን እንዲፈጽም፥ በነፍሱ ተወራርዶ ከጌታ ሥራ የተነሣ እስከ ሞት ቀርቦአልና* ብሎአል፤ ፊል. 2፥29-30። እንዲህ ነፍሳቸውን አስይዘው የሚያገለግሉ አገልጋዮች በደስታ ሊከበሩ ይገባል!

ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ ራሳቸውን የቀቡና የሾሙ ብቻ ሳይሆኑ ሰዎች ብቻ የሾሟቸውና ተከታዮች ያነገሧቸው ባለ ወንበሮችም አሉ። <u>ሕዝብ የሾማቸው</u> ወይም የሕዝብ ጥያቄ ምላሽ የሆኑ እንደ ጎበዝ አለቃ ያሉ ሰዎች አሉ። ሳኦል የዚህ ምሳሌ ነው። እርግጥ ነው፤ እግዚአብሔር በሳሙኤል በኩል ቀብቶታል። የሹመቱ መነሻ ግን የሕዝቡ ጥያቄ ነውና ለመረጠው ወይም ለመንገሡ ምክንያት ለሆነው ሕዝብ እንደሚሰባበር ፖለቲከኛ እየወደቀ ሊነሣለት ቢጥር በአንድ ወገን አያስገርምም። ሳኦል ከእግዚአብሔር ይልቅ ሕዝቡን ይሰማ ነበር። ለውድቀቱ ምክንያት የሆነውም ከራሱ እንቢተኝነትና እልከኝነት በተጨማሪ ሕዝቡም ነው። 'ፈጽመህ አጥፋ' የተባለውን ሕዝቡ ምርጥ ምርጡን ሲያስቀሩ ዝም ማለቱ ትልቅ ኃጢአት ነበር።

በ1960ዎቹ ደርግ መንግሥት ሲሆን፥ ያ የ120 ወታደሮች ስብሰባ መንግሥት የመሆን አሳብ አልነበረውም፤ ታሪካቸውም ያንን ነው የሚተርከው። ከሁኔታዎች ምቹነት በቀር ተሳታፊዎቹ አገር ለመምራት የስነ ልቡናም ሆነ የፖለቲካ ዝግጅትም ሆነ ብቃት አልነበራቸውም። የተሰበሰቡት ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የመመሥረት አጀንዳ ይዘው አልነበረም። መነሻ ጥያቄያቸው ሌላ ነበር። መንግሥትም ሆነው እንኳ ርዕዮተ ዓለሙ የተቀረጸው በመንገድ ላይና በድንገት ነበር። ሰፊው ሕዝብ የዘመኑ ዋና ቃል ሆነ። የሕዝብ ሰዎች ሆኑ። ይሁን እንጂ የኋላ ታሪኩ ሲታይ የሕዝብ ሰዎች ሳይሆኑ የሥልጣንና የወንበር፥ የስምና የጥቅም ሰዎች ሆነው ተገኝተዋል። ሕዝብ ሕዝብ አሉ እንጂ የተፈጀውን አንድ ትውልድ እንደ ሕዝብ አልቆጠሩትም።

ክብር የተገባ ቢሆንም፥ አገልጋዮች አክብሩኝ ሲሉ አትድረሱብኝ፥ አትንኩኝ፥ አትድፈሩኝ፥ አትመዝኑኝ ማለታቸው ከቶም መታሰብ የለበትም። ይልቁንም ይህንን አክብሮት በቃሉ ውስጥ ካልተጻፈ የቅብዓት ትምህርት ጋር አቆራኝቶ ማሳት የለባቸውም። አገልጋዮች ፈጽሞ እንደማይሳሳቱ ሁሉ በአመላለስም ሆነ በአስተምህሮ

ግልጽ ከመሆንና ከመመርመርም ነጻ መሆን የለባቸውም። አንዳንድ ጊዜ ትልልቅ አገልጋዮችና መሪዎች ብዙ መዘዝ ያለበት ትልልቅ ስሕተት ይሳሳታሉ። የወርቅ ጥጃ የሠራ አሮን ነበረ። ጌታ ስለ ሞቱ ሲናገር 'ይህ አይሁንብህ' ያለ ጴጥሮስ ነበረ። እነዚህ ሰዎችና የእነርሱን የመሰለ ስሕተት የሚደግሙ ሰዎች ዝም መባል አለባቸው? ከቶም የለባቸውም። አገልጋይ የአደባባይና የመድረክ ሰው ሲሆን ለመፈተሽ ፈቃደኛ መሆን አለበት። ይልቁንም ለመፈተሽ የማያስቀርቡቱ የበለጠ መፈተሽ አለባቸው። ይልቁንም፥ በጌታ የተቀባውን አትዳስሱ' የሚሉ ሊጠየቁ ግድ ይላል። መጠየቅና መገዳደር ነውር በሚመስልበትና ሰዎችን አክባሪና ፈሪ በሆነ የእኛ ዓይነቱ ባህልና ማኅበረ ሰብ ይህ ችግር ይጎላል። ቅባትን ስናስብ ይህን እናስብ። የተቀባን ነን ባዮች ለመፈተሽ የማይፈልጉት ቢፈተሹ የሚገኝባቸው ነገር በመኖሩ ነው። ኬላ ላይ መቆም የማይወዱ የኮንትሮባንድ ነጋዴዎች ብቻ ናቸው። በአውሮፕላን ማረፊያ የፍተሻ በር ለመግባት የሚሳቀቁ ጎጂ መሣሪያ የያዙ ብቻ ናቸው።

በአዲስ ኪዳን የተቀባና ያልተቀባ የሚባል የክርስቲያን መደብ የለም። *እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል፥ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፤ ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ፥ እውነተኛም እንደ ሆነ ውሸትም እንዳልሆነ፥ እናንተንም እንዳስተማራችሁ፥ በእርሱ ኑሩ።* 1ዮሐ. 2፥27። ክርስቲያን ክርስቲያን ሲሆን ተቀብቷል። የተቀባው የክርስቶስ ተከታይ ሲሆን ተቀብቷል። በዚህ ክፍል ሁለቱንም ዓይነት መሪዎች፥ አደገኞቹንም ሁነኛዎቹንም ነው ያየነው። ከአደገኞዎቹ እንጠንቀቅ፤ ሁነኛዎቹን በአክብሮት እንጠብቅ።

## ምዕራፍ ፳

# ክርስቲያኑና ወረት (ኀዋይ)

ወረት ማለት በቀላሉና በአጭሩ ገንዘብ ማለት ነው። ያንን ሆኖም ወረት ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ትርጉሙን ስንመረምር ከዚያም ይጠልቃል። ወረተ እና ወረሰ፥ መውረት እና መውረስ አንድ ዘር ናቸው። ወረተ፥ መውረትን ደስታ ተከለወልድ መውረስ፥ ለጊዜው ማግኘት ይሉታል። ወረትንም የጊዜ ገንዘብ ይሉታል። (ገጽ 465)። በዚህ ትርጉም፥ 'ጊዜ' የምትለዋ ቃል በጣሙን ሊሰመርባት የተገባት ቃል ናት፤ ወረት ለጊዜው የተገኘ፥ የጊዜው ገንዘብ፥ ጊዜያዊ ገንዘብ ማለት ነው። ጊዜያዊ ማለት የጊዜው፥ ዘላቂ ያልሆነ፥ ዘላለማዊ ያልሆነ ማለት ነው። መውረስ ደግሞ ያልተለፋበት፥ ሌላው የለፋበትን መውረስ፥ ማጋበስ ነው። ጥሪት ያይደለ፥ (ጥሪት ማለት በጥረት፥ በላብ የተገኘ ማለት ነው) እና ጥሪት ያልሆነ፥ በጥረት፥ በላብ፥ በወዝ ያልተገኘ የጊዜው ገንዘብ ማለት ነው።

ወረት ሌላ ትርጉሙ የጊዜው፥ ጊዜያዊ ማለት ነው። ወረተኛ ሲባልም፥ ቶሎ የሚጠፋ ጊዜያዊ፥ አላፊ ማለት ነው። ወረተኛ ፍቅር፥ ወረተኛ ጓደኛ፥ ወረቱ አለቀ ሲባል ያ ነው። እንደ ግስ፥ ወረተ ማለትም ወረሰ፥ ገንዘብ አገኘ ብቻ ሳይሆን ጊዜያዊ ወዳጅ ያዘ ማለትም ነው። የጊዜ ነገር፥ የጊዜያዊነት ነገር አለበት። ስለዚህ ወረት ወይም ገንዘብ ጊዜያዊ ነገር ነው። ቃሉ ራሱ ነገሩ ጊዜያዊ ብቻ እንጂ ዘላቂና ዘላለማዊ የአለመሆኑ መግለጫ ነው።

ጳውሎስ፥ *ወደ ዓለም ምንም እንኳ አላመጣንምና፥ አንዳችንም ልንወስድ አይቻለንም፤* ብሏል፤ 1ጢሞ. 6፥7-8። ገንዘብ እዚሁ የምንገለገልበት መገልገያ ብቻ ነው። ጳውሎስ እዚህ 1ጢሞ. 6 ውስጥ ስለ ገንዘብ ነው በተለይ የሚናገረው። ይህ ክፍል ስለ ገንዘብ፥ ስለ ወረት ስንካፈል መወሳት ያለበት ክፍል ነውና ከቁጥር 5 እስከ 11 ያለውን፥ ክፍል

ብዙም ባላብራራው ክፍለ ምንባቡ ራሱን በራሱ የሚያብራራ ነውና ከቁጥር 5 ጀምሮ ባለው ክፍለ ምንባብ ጥቂት ብቻ ልበል፤ 4 እና 5 አንድ ላይ ናቸውና ከ4 ጀምሮ፥

> 4-5 በትዕቢት ተነፍቶአል አንዳችም አያውቅም፥ ነገር ግን ምርመራን በቃልም መዋጋትን እንደ በሽተኛ ይናፍቃል፤ ከእነዚህም ቅንዓትና ክርክር ስድብም ክፉ አሳብም እርስ በርስ መናደድም ይወጣሉ፥ አእምሮአቸውም በጠፋባቸው እውነትንም በተቀሙ፥ እግዚአብሔርን መምሰል ማትረፊያ የሚሆን በመሰላቸው ሰዎች ይገኛሉ። እንደነዚህ ካሉት ራቅ።
> 6 ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው፤
> 7 ወደ ዓለም ምንም እንኳ አላመጣንምና፥ አንዳችንም ልንወስድ አይቻለንም፤
> 8 ምግብና ልብስ ከኖረን ግን፥ እርሱ ይበቃናል።
> 9 ዳሩ ግን ባለ ጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያሰንፍ በሚጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ።
> 10 ገንዘብን መውደድ የክፉት ሁሉ ሥር ነውና፥ አንዳንዶች ይህን ሲመኙ፥ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ።
> 11 አንተ ግን፥ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ከዚህ ሽሽ፤ ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም ፍቅርንም መጽናትንም የዋህነትንም ተከታተል።

እግዚአብሔርን መምሰል ማትረፊያ የሚመስላቸው ሰዎች አሉ። እግዚአብሔርን መምሰል እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ ማክበር፥ እርሱን መፍራትና ማምለክ ነው። ቃሉ አምልኮን አመልካች ነው። ዛሬ እግዚአብሔርን መምሰልን ወይም ማምለክን ብቻ ሳይሆን ራሱን እግዚአብሔርንም የትርፍ መሣሪያ፥ የትርፍ መሥሪያ፥ መነገጃና ማትረፊያ የሚያደርጉ ሰዎች አሉ። እግዚአብሔርን መምሰል እርሱን መፍራት እና እርሱን ማምለክ ከሆነ፥ ይህ በእውነቱ ለመነገጃነት ወይም መነገጃና ማትረፊያ ለመሆን አይመችም፤ አያመችም። ስለዚህ አትራፊዎቹ ምን ያደርጋሉ ቢባል፥ መሆኑን ሳይሆኑ መምሰሉን ብቻ ወስደው ድራማ በመሥራት መነገጃና ማትረፊያ ያደርጉታል። ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ ይህንንም መስለው ይገኛሉ። አምላኪ ሳይሆኑ፥ እግዚአብሔርን ፈሪ ሳይሆኑ አምላኪና ፈሪ መስለው ይተውናሉ። ግብዝነትን በየፈርጁ ይኖሩታል።

እነዚህ ኑሮዬ ይበቃኛል የማይሉ፥ የማይጠግቡና የማይጠረቁ፥ የማይበቃቸው ናቸው። ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚሉት ገንዘብ ቢመጣም ባይመጣም እግዚአብሔርን መምሰል ሕይወት ነው። ደግሞም ልንመስለው ነው የተጠራነው። ሮሜ 8፥29 *ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና።* ይላል። እግዚአብሔርን መምሰል ሕይወት ነው። ደግሞም ልንመስለው ነው የተጠራነው። ማንን ልንመስል? ክርስቶስን።

ክርስቶስ የገንዘብ ሰብሳቢና አካባች አልነበረም። የክርስቶስ ኑሮ በዓላማና በግብ ስለነበረ ውስብስብ አልነበረም። ሚስቴን ድስቴን፥ ቅሌን ጨርቄን አላለም።

ጳውሎስም ይህንን ነው ያለው፤ ወደ ዓለም ምንም አላመጣንም፤ ምንም ይዘንም አንሄድም። ብር ይዘን አልመጣንም፤ ይዘንም አንሄድም፤ እዚሁ የምናገኘው ነው፤ እዚሁ የሚቀር ነው። በብር ዘላቂ ነገር ማድረግ ከቻልን፥ ያ ዘላቂ ነገር ያንን ብር ለዘላለማዊ ጉዳይ ስናውለው ብቻ ነው። ያም ወንጌል ነው። በወንጌል ስም መነገድ እንዳለም ሳይረሳ ነው ታዲያ! በወንጌል ስምም ይነገዳል። ስንት የወንጌል ነጋዴዎች፥ ስንት የጅምላና የችርቻሮ ነጋዴዎች አይተናል!

ልናሰምረንበት የተገባው አንድ ጉዳይ አለ፤ ያም፥ ገንዘብ መሥሪያ መሣሪያ መሆኑ ነው። ልብ እንበል፤ በመጽሐ ቅዱስ ውስጥ ገንዘብ ክፉ ነው አልተባለም። ክፉ ነው የተባለው የገንዘብ ፍቅር ነው፤ ቁጥር 10 *ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፥ አንዳንዶች ይህን ሲመኙ፥ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ።* ይላል። ገንዘብ ሳይሆን ገንዘብን መውደድ ነው የክፋት ሁሉ ስር የተባለው።

እዚህ ሦስት ትልልቅ ምስሎችን ከሳች የሆኑ ቃላትን እንይ፤ አንዱ ስር ነው፤ ስር እንደ ግንድ እና ቅርንጫፍ የሚታይ ነገር አይደለም። አይታይም፤ ግን ዋና ነገር ነው። ስር ተሸካሚ ነው፤ መጋቢ ነው። የገንዘብ ፍቅር እንደ ስርነቱ፥ ስር እንደመሆኑ አይታይም፤ እልብ ውስጥ የሚቀረቀር ደዌ ነው። መውደዱ ሥሩ ነው። ሥሩ ከሰደደ ግንዱ እርጥብ ነው። ግንዱ እርጥብ ከሆነ ቅርንጫፉ እርጥብ ነው። ቅጠልም ፍሬም አለው። ቆይቶ የራሱን ፍሬ ያፈራል። የክፋት ሁሉ ስር የገንዘብ መውደድ ነው የተባለው፤ መውደድ ፍቅር ነው፤ ፍቅር ወደ አምልኮት ይወስዳል። ይህንን የገንዘብ አምላክነት ጥቅስም በቆይታ እናየዋለን። አንዱ ምስል ስር ነው።

ሁለተኛው ምስል ደግሞ ወጊነት ነው። ይህ ቃል መዘዙ ነው። *አንዳንዶች ይህን ሲመኙ፥ [ገንዘብን ሲመኙ] ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ።* ይላል። ውጊት ጉዳትና ስቃይ አለበት፥ ሕመም አለበት። የገንዘብ ወዳጆች የተወጉ ሰዎች ናቸው፤ ሕመምተኞች ናቸው፤ ያልታወቀ፥ ዶክተር የማያስነበኝ፥ ሆስፒታል የማይወስድና የማያስተኛ በሽታ ሰለባዎች ናቸው። የገንዘብ መውደድ ስለታምና ሹል ወጊ ነው፤ ቁስሉ ደግሞ በቀላሉ የማይሽር ነው። *ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ።* በስቃይ ብቻ አይደለም፤ በብዙ ስቃይ። ገንዘብን መውደድ ይህን ያደርጋል። ቀደም ሲል ያለው ቁጥር 9፥ *ዳሩ ግን ባለ ጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያሰንፍ በሚጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ።* ይላል።

ሦስተኛው፥ መሳት ነው። የገንዘብ መውደድ መዘዝ አለው፤ ከሃይማኖት መሳሳት አለ፤ መሳት አለ፤ ከመስመር መውጣት አለ። ይህ 'ከሃይማኖት ተሳስተው' የሚለው ቃል ከእምነት ምሕዋር ወጥተው ማለት ነው። ነገሮች የሚሄዱባቸው መስመር አላቸው። ፕላኔቶች ምሕዋር አላቸው። ፕላኔት የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ነው፤ በመስመሩ የሚሄድ ማለት ነው። በመስመር መሄድ πλανάω ፕላናኦ ይባላል፤ ፕላናኦ ግሱ ነው። ፕላኔት ማለት ፕላናኦ የሚያደርግ ወይም በመስመሩ የሚሄድ ማለት ነው። ይህኛው ቃል ጳውሎስ እዚህ የጠቀሰው፥ ἀποπλανάω አፖፕላናኦ የሚል ነው። ፕላኔት ምሕዋር ስታ ስትወጣ እንደምትሆነው ማለት ነው። ἀπο የሚለው ጭማሪ መውጣትን፥ መልቀቅን፥ ማፈንገጥን አመልካች ነው። ከሃይማኖት ስተው ማለት፥ ምሕዋራቸውን ስተው፥ ትተው፥ ለቀው፥ አፈንግጠው ወጥተው ማለት ነው። መንገዳቸው ወዳልሆነ፥ ወይም ጨርሶም መንገድ ወዳልሆነ መውጣት ማለት ነው። ባቡር ሐዲድ ስቶ እንደሚወጣ ስተው ወጥተው ማለት ነው። ከሐዲድ የወጣ ባቡር ምን እንደሚሆን ግልጽ ነው። ጥፋት፥ መፍረስ፥ መስጠም፥ ጉዳት፥ ፈተና ወጥመድ። ትልልቅ ቃላት ናቸው። በጣም ግልጽ ቃላትም ናቸውና ማብራሪያ አይፈልጉም።

*አንተ ግን፥ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ከዚህ ሽሽ፤* ይህ 'የእግዚአብሔር ሰው' የሚለው መጠሪያ በጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ 32 ጊዜ ተጽፏል። ከ32ቱ 30ው በብሉይ ኪዳን ሲገኙ ሁለቱ ብቻ በአዲስ ኪዳን ይገኛሉ። ከሁለቱ ጥቅሶች አንዱ ይህ፥ *አንተ ግን፥ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ከዚህ ሽሽ፤ ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም ፍቅርንም መጽናትንም የዋህነትንም ተከታተል።* የሚለው ነው። አንተ ማን? የእግዚአብሔር ሰው። 1ጢሞ. 6፥11። ከምን ሽሽ ነው የተባለው? ክፍለ ምንባቡን ስናጤነው ገንዘብን ከመውደድ ሽሽ ነው የተባለው። የእግዚአብሔር ሰውነት ወይም የእግዚአብሔር ሰው የመሆን አንድ መታወቂያ ይህ ከገንዘብ ፍቅር መሸሽ ነው።

ሁለተኛው፥ 'የእግዚአብሔር ሰው' የሚለው ሐረግ የሚገኘው በ2ጢሞ. 3፥16-17 ነው። እንዲህ ይላል፤ *የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።* የእግዚአብሔር ሰው ከምን ጋር የተቆራኘ እንደሆነ ያሳየናል፤ ከቃሉ ጋር።

ከነዚህ ሁለት ጥቅሶች የምንማረው 'የእግዚአብሔር ሰው' (man of God) ምን እንደሚመስል ነው? ዛሬ፥ 'man of God' ማዕረግ ነው። ጥሩ መነገጃና መብያ ገበታም ነው፤ ሳህን ነው። በአዲሱ ኪዳን የምናገኘው 'የእግዚአብሔር ሰው' (man of God) ምን ይመስላል? ከነዚህ ከጥቅሶች እንደምንረዳው፥ አንደኛ፥ በገንዘብ ፍቅር

ያልተያዘ፤ ሁለተኛ፥ በእግዚአብሔር ቃል በመጽሐፉ መሠረት የተዘጋጀና ቃሉን የሚያገለግል ነው። ገንዘብን የማይወድድ፥ ቃሉን የሚወድድ።

የእግዚአብሔር ሰዎች የሚባሉት ሰዎች መለኪያ መሆን ያለበት ይህ ነው። ገንዘብ ይወድዳል? ወይስ አይወድድም? ቃሉን ይወድዳል? ወይስ አይወድድም? በዚህ ለክተናቸው ቃሉን ከወደዱ፥ ገንዘብን ካልወደዱ፥ እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰዎች ናቸው ስሟቸው። ለገንዘብ ሲሉ ማጅራት ከመቱና ካስመቱ፥ ከደፉና ካስደፉ፥ ከዋሹና ከቀጠፉ፥ ከቀሙና ከዘረፉ የእግዚአብሔር ሳይሆኑ የገንዘብ ሰዎች ናቸው። ገንዘብ አምላክ ነው። የእግዚአብሔር ሳይሆኑ፥ የእውነተኛው አምላክ ሳይሆኑ፥ የሌላኛው አምላክ ሰዎች ናቸው። የራሳቸው ሰዎች ናቸው። የእግዚአብሔር ሰው የእግዚአብሔር የሆነ ሰው ነው። ባለቤት አለው፤ ጌታ አለው። ይህ ሰው የጌታው ባሪያ ነው።

*ለዚህ ነው ጌታ፥ ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።* ያለው፤ ማቴ. 6፥24። እግዚአብሔር እና ገንዘብ በእኩል አቀራረብ ነው እዚህ ጥቅስ ውስጥ የተጠቀሱት። ገንዘብ ጥሩ ባሪያ እንደሚሆን ሁሉ ክፉ ጌታም ይሆናል። አምላክም ይሆናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ገንዘብ የሚለው፥ ገንዘብን የምናውቅበት ቃል ብዙ ቦታዎች ተጠቅሶአል፤ ይህኛው እዚህ ገንዘብ የተጠቀሰው μαμμωνᾶς (ማሞናስ) የተባለው ቃል ግን እዚህ ማቴ. 6፥24 እና ሉቃ. 16፥9-13 ውስጥ 4ቴ ብቻ የተጠቀሰ ቃል ነው። እንዲያው ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ከዓመፃ ወይም ከኃጢአት ጋር የተቆራኘ ገንዘብ ነው። እንዲህ ያለው ገንዘብ እና የገንዘብ ፍቅር አምላክ በመሆን የእግዚአብሔርን ቦታ በቀላሉ ይወስዳል።

ገንዘብን መውደድ ጥጋብ የለበትም፤ እርካታ የለበትም። ይህንን ያለው ትልቁ የዓለማችን ሀብታም ሰው ነው። ትልቁ ሲባል በእርግጥ ትልቁ ሀብታም ነው። የአማዞን ወይም የማይክሮሶፍት ወይም ሌላ ድርጅቶች ወይም ኩባንያዎች ባለቤቶችን ማለቴ አይደለም። ከእርሱ በፊትም በኋላም (ዛሬም ጭምር) እንደሱ ያለ ሀብታም የሌለ ሰው ነው ይህ ሰው፤ እና ይህ ሰው ምን አለ? *ብርን የሚወድድ ሰው ብርን አይጠግብም፤ ባለጠግነትንም የሚወድድ ትርፉን አይጠግብም፤ ይህም ደግሞ ከንቱ ነው።* አለ፤ መክ. 5፥10። ይህ ሀብታም ሰው ሰሎሞን ነው። ብር አይጠገብም፤ የሚፈልጉት፥ የሚወድዱት አይጠግቡትም። ገንዘብ ትልቅ ፈተና ነው። የገንዘብ ፍቅር ሰዎችን እውር ያደርጋል፤ በገንዘብ ምክንያት ቤተ ሰቦች ተለያይተዋል፤ ወዳጆች ተካክደዋል፤ ቅዱሳንም ተቋስለዋል፤ ተፈትነውበት ተጠልፈውበት ወድቀዋል። 'ብዙዎች ወደቁ ተጠልፈው፤ በገንዘብ ፍቅር ተነድፈው፤ ብልጽግና ያታልላል፤ ይሁዳ ጌታውን ሸጧል።' አለ መጋቢ ተስፋዬ በመዝሙሩ።

የገንዘብ ፍቅር፥ 'ባልተወለደ ይሻለው ነበር' የተባለለት ይሁዳን አጉል ያደረገ አጉል ነገር ነው። ይሁዳ ጌታውን ሸጠ። ለዚያውም በ30 ብር! ለዚያውም ላይበላበት፤ መሬት ላይገዛበት፥ ቤት ላይሠራበት። ዛሬም ለገንዘብ ሲሉ፥ ሰዎች እንኳን ሌላውን፥ ራሳቸውንም ይሸጣሉ። እንኳን ራሳቸውን ጌታቸውንም ይሸጣሉ። ሐሰተኞች ነቢያትና ሐሰተኞች ሐዋርያት ይህንን ያደርጉታል፤ ሐሰተኞች ያልሆኑም ያደርጉታል። ጤናማዎች የምንላቸው ሰባኪዎችና አስተማሪዎችም በገንዘብ ፍቅር እግር ተወርች ተይዘው ይገኛሉ። ዘማሪዎች ከድሃ ቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ጥሪ ሲቀበሉ እሺ ይሉና፥ የደለበ ብር የሚሰጡትን ይጠብቃሉ። በዚያ ቀጠሮ ቀን ከጋበዟቸው፤ ደውለው እንኳ ቀረን ሳይሉ እዚያ እየተጠበቁ ይቀራሉ፤ እዚህ ደግሞ ይጎደፍራሉ። አገልግሎታቸውን በብር ይለውጣሉ። ስንቱን ታዘብን!

እነዚህ 'የብልጽግና ወንጌል' የሚሉትን ሸቀጥ የሚያራግፉብን አሳቾች ሸቀጥ በውድ እየሸጡ ነው፤ ስግብግቦች ናቸው። እነዚህ ሸቃጮች ባለ ጠጎች ሳይሆኑ ስግብግቦች ናቸው። እነሱ እንደሚሰብኩት ያለው ብልጽግና ብልጽግና አይደለም፤ በእውነቱ በረከት አይደለም። እንዲህ እየሰበሰቡ 'ተባርኬአለሁ!' ይላሉ። ይህ በረከት ሳይሆን መርገም ነው። የኤልሳዕ ሎሌ ግያዝ ተረገመበት።

*ባለ ጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል።* አለ ጌታ። ግመል በመርፌ ቀዳዳ ነው እኮ ያለው። በሦስቱም ወንጌላት ውስጥ ተጽፏል ይህ ቃል። ይህንን ያለበትን ቦታ ሄደን ብንመረምረው አስገራሚ ታሪክ እናገኛለን። ከገንዘብ ጋር የተጣበቀ አንድ ወጣት ባለጠጋ ታሪክ ነው። ጌታን ላለመምረጥ፥ ላለመከተል፥ ደቀ መዝሙር ላለመሆን ብልጥግናው አገደው። ከገንዘብ ፍቅር በቀር እንዴት ያለ እንከን የለህ ወጣት ነው! ስሙ ራሱ አልተጻፈልንም እንጂ፥ 'እንከን የለህ' ብንለው ሳይመጥነው አይቀርም።

ባለጠግነትን አፈንፍነው፥ በፍቅር የሚፈልጉ ሰዎች፥ ገንዘብን በፍቅር የሚወድዱ ሰዎች ቸሮች አይደሉም፤ ቀርባችሁ ተመልከቷቸው፤ ቸርነት የለባቸውም፤ ልብ እንበል፤ የማይሳሳተው ቃል፥ *ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፥* ብሎታል፤ ክፋት የመልካምነት ተቃራኒ ነው። መልካምነት ውስጥ ቸርነት ይገኛል። እኔ ብዙ ባለጠጎችን አላውቅም፤ ጥቂት ቸሮችን አውቃለሁ። እነዚህ ቸሮች ስላላቸው ሳይሆን ባይኖራቸውም የሚሰጡ ናቸው። እንደ መቄዶንያ ሰዎች፤ ቸርነት እውስጣቸው የሆኑ ሰዎች ናቸው።

ሌሎች ገንዘብ ወዳድ የሆኑ፣ አንዳንዶቹ አገልጋዮችም ናቸው፤ ለራሳቸው በባልዲ እየዛቁ ከጎናቸው አብሯቸው ቀን ከሌት ለሚለፋው አገልጋይ ኪኒኒ የምታህል የሚከፍሉ መጋቢዎችንም አውቃለሁ። ሁሉን በመዳፋቸው ስር አድርገው የያዙ

ጩብጤዎች ናቸው እነዚህ። እንኳን በድሀ አገር፥ በበለጠጉት እንደ ሰሜን አሜሪካ ባሉት አገሮች እንኳ በሰቀቀን የሚያገለግሉ ችግረኞች አገልጋዮች አሉ። ስንቱን ታዘብን! እነዚህ ወረት የጠፈራቸው ቸርነትን የያውቋት ሰዎች ናቸው። የክፋት ሁሉ ስር ነዋ! ገንዘብን መውደድ።

በምዕራቡ ዓለም፥ ገንዘብ እያግበሰበሱ፥ መንግሥትንም እንኳ ሳይቀር እያጭበረበሩ፥ ቤተ ክርስቲያናቸውንም እያስዋሹ የሚያገለግሉ አገልጋዮች አሉ። አገልጋዮች ይሁኑ ተገልጋዮች ራሳቸው ያውቁታል። ቤተ ክርስቲያንን ያስዋሻሉ። መንግሥትን እያታለሉ ከሚያገኙት ገቢ በታች እያስመዘገቡ፥ በሚያገኙት ገቢ አገር ቤት ንግድ የሚያጧጡፉ፥ ቤቶች እያሠሩ የሚያከራዩ ልማታዊ አገልጋዮች አሉ። ከብልጽግና ወንጌል የጨቀየ ትምህርት ጋር የተፈጣጠሙቱማ ምን ጥያቄ አለው? እነዚህ አገልጋይ ሳይሆኑ ድውያን ነጋዴዎች ናቸው። በምዕራቡ ዓለም መንግሥት አትራፊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ወይም አገልግሎቶችን ያበረታታል። የዚያኑ ያህል ተጠያቂም ያደርጋቸዋል። ለምሳሌ በዩ ኤስ አሜሪካ IRS የተባለው የገቢዎች አገልግሎት ቢሮ Form 990 የተባለውን ቅጽ አትራፊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሞሉ በሕግ ያስገድዳል። በዚህ ገቢና ወጪ፥ ትልቅ ተከፋይ ሰዎች፥ የቦርድ አባላት ስሞች፥ ሌሎችም ይጠየቃሉ። እንዲህም ሆኖ አንዳንዶች ይህንን ኬላም የሚሰብሩባቸው መንገዶች አሏቸው። አብያተ ክርስቲያናት ይህንን ቅጽ የመሙላት ግዴታ ስለሌለባቸው አንዳንድ የታወቁ አትራፊ ያልሆኑ አገልግሎቶች ራሳቸው ቤተ ክርስቲያን ሳይሆኑ እንደ ቤተ ክርስቲያንም አድርገው ይመዘገባሉ። ለማጭበርበር ሕሊናቸውን በበረኪና ለማጠብ አይቸግራቸውም።

የብልጽግና ወንጌል ብልጽግናም፥ ወንጌልም አይደለም። ደዌ ነው። እነዚህ አገር ቤት ሲሄዱ ወይም እዚያ ላሉቱ ቸር ለመምሰል በፊልም እየተቀረጹ ድራማ ይሠራሉ፤ ፊልሚን ደግሞ ሲወዷት! ሲወድቁላት! ጆንያ እየተሸከሙ ይቀረጻሉ፤ ውኃ እያደሉ፥ ጫማ እያደሉ ይቀረጻሉ፤ የቤት ቁልፍና የመኪና ቁልፍ ስጦታ እየሰጡ ቪድዮ ይቀረጻሉ፤ አንዳንዶቹ የሰጡ ለመምሰል ነው። እመድረክ ላይ ለማኝ አቁመው አጠገቡ ከረጢት አድርገው ይለምናሉ፤ ሰብስቤዎች ናቸውና ይሰበስባሉ፤ በጓዳ የሚደረገውን ግን የሚያውቁት ያውቁታል። መለመኛ ለሆኑቱ የሚደርሰውንም የደረሳቸው ያውቁታል። ስንቱን ታዘብን! ወረት ትልቅ የክርስቲያኖች ፈተና ነው። በወረት ተፈትኖ ያልወደቀ ብፁዕ ነው። በገንዘብ ፍቅር ያልታወረ ብፁዕ ነው፤ ገንዘብ ያሳውራላ!

በለዓም በገንዘብ የተገዛ ቃልቻ ነበረ። ዋጋ ተልኮ፥ ገንዘብ ተሰጥቶት ነው የተጠራው። *የሞዓብ ሽማግሌዎችና የምድያም ሽማግሌዎችም የምዋርቱን ዋጋ በእጃቸው ይዘው ሄዱ፤ ወደ በለዓምም መጡ፥ የባላቅንም ቃል ነገሩት።* ይላል ዘኍ. 22፥7። የምዋርቱን ገንዘብ በእጃቸው ይዘው ነው የሄዱት። ይህ በለዓም በአዲስ ኪዳንም ሲጠቀስ

ኃጢአቱ ይኸው መሆኑ ተጽፎአል፤ ስለ ደመወዝም ለበለዓም ስሕተት ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል። ይሁ. 11። የባሶርን ልጅ የበለዓምን መንገድ ተከተሉ፤ እርሱ የዓመፃን ደመወዝ ወደደ። 2ጴጥ. 2፥15። ሁለቱም ጥቅሶች ውስጥ ስለ በለዓም የተነገረው ደመወዝ የሚል ቃል ነው። ገንዘብ ነው፤ ወረት ነው። የገንዘብ ፍቅር ያሳውራል።

ይህ ሰው እያየ የታወረ ሰው ነበረ። ኋላ ትንቢቱን ሲመስል ምን አለ? የወደቀው ዓይኖቹም የተከፈቱለት አለ፤ (ዘኁ. 24፥3-4 እና 15-16) እውነትም ታውሮ ያላየው ነገር እንደነበረ ያሳያል። በለዓም ዓይኖቹ በገንዘብ የታወሩ ቃልቻ ሰው ነበር። የገንዘብ ፍቅር ያሳውራል። በለዓም ለጥቅም ሲል፥ ለዓመፃ ደመወዝ ሲል የሚሄድበት መንገድ ላይ የቆመውን፥ የተቀመጠባት አህያ ያየችውን ከልካይ መልአክ እንኳ ማየት ተስኖት ነበር። አህያ ስታይ ይህ አለማየቱ ዕውርነት አይደል? የገንዘብ ፍቅር ያሳውራል። ልብን ያሳውራል።

አንድ አዛውንት ለአንድ ወጣት ስለ ገንዘብ አሳዋሪነት ሲያሳዩት ራቅ ብለው ቆሙና ሁለት ትናንሽ ባለ 10 ሳንቲም ይዘው እንደሚታዩትና እንደማይታዩት ጠየቁት። ‘ይታዩኛል’ አለ፤ ከሳንቲሞቹ ኋላ ምን እንደሚታየው ጠየቁት፤ መስኮቱ፥ በመስኮቱ በኩል ውጪው ዛፎች ሰማዩ ተራራው እንደሚታየው ተናገረ። ቀጥሎ ወደ መሐል መጡና ሳንቲሞቹን ከፍ አደረጓቸው፤ አሁንም ይታየዋል ትንሽ ቦታ ብቻ ከመሸፈኑ በቀር። ቀጥሎ ወደ ዓይኖቹ በጣም አቀረቧቸውና፥ ‘አሁንስ ምን ይታይሃል?’ አሉት፤ ‘ምንም! ሳንቲሞቹ ብቻ ብዥ ብለው ይታዩኛል።’ አለ። አዛውንቱ ሰውዬም፥ ‘ገንዘብ ወደ ውስጥህ ሲጠጋ እንደዚህ ነው የሚያሳውርህ፤ ዙሪያህን ብቻ ሳይሆን ገንዘቡንም በወጉ አታየውም። በብዥታ ነው የምታየው።’ አሉት። የገንዘብ ፍቅር ያሳውራል፤ ጊዜያዊ ዕውር ወይም ለዘለቄታው ዕውር ያደርጋል። ልብን ይደፍናል። በትምክህትም ልብን ይደፍናል፤ እግዚአብሔርን ባለመፈለግ ልብን ይደፍናል፤ ለሌሎች ጨካኝ በማድረግ ልብን ይደፍናል።

ገንዘብ ሲያሳውር፥ አስደንጋጩ ነገር፥ ለኃጢአትም ዕውር ያደርጋል። አንዳንድ መጋቢዎች ረብጣ ገንዘብ የሚሰጡ ሰዎች የሚሠሩትን ኃጢአት እንዳላየ ያልፋሉ። ሲሰሙ ጆሮ ዳባ ልበስ ይላሉ። ኃጢአትን በገንዘብ ይለውጣሉ ማለት ነው። እነዚያን ሰዎች እመድረክ ላይ አውጥተው ያስገለግላሉ፤ መድረኩን ያረክሳሉ። ለገንዘብ ሲሉ። ገንዘቡን በማጭበርበርና በማምታታት የሚያመጡትን ሰዎች ይመርቃሉ፤ ሠርተውም እንኳ ቢያመጡት የሰዎቹ ሕይወት ከቅድስና የጎደለ ከሆነ ወይም እንደሆነ እያወቁም ደፍረው አይናገሯቸውም። ሳያውቁ ቀርተው ሳይሆን አውቀው፥ ወደው ይታወራሉ። ገንዘቡንም ይቀበላሉ። አመንዝረሽም ውሰጂ ይቀበሉሻል። ቆምረህም፥ ኪስ አውልቀህም ውሰድላቸው ሳይጠይቁ ይቀበሉሃል። በጽድቅ ስለመሥራትና ስለማግኘት

አያስተምሩም። ይህን በማድረግ፥ ሌሎቹንም የገንዘብ መውደድ ሰለባ ያደርጓቸዋል። የገንዘብ ፍቅር ያሳውራል።ወረት እንዲህ ነው። ትልቅ ፈተና ነው። ብዙዎች ወድቀውበታል፤ ቆስለውበታል፤ ጎስቁለውበታል። ቀደም ሲል ካየናቸው ጥቅሶች ጥቂቱን ደግመን እንደ መደምደሚያ እንይ፤

*ብርን የሚወድድ ሰው ብርን አይጠግብም፤ ባለጠግነትንም የሚወድድ ትርፉን አይጠግብም፤ ይህም ደግሞ ከንቱ ነው።* መክ. 5፥10።

*ወደ ዓለም ምንም እንኳ አላመጣንምና፥ አንዳችንም ልንወስድ አይቻለንም፤ . . . ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፥ አንዳንዶች ይህን ሲመኙ፥ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ።* 1ጢሞ. 6፥7-10።

*ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።* ማቴ. 6፥24።

ጌታ እግዚአብሔር የክፋት ሁሉ ስር ከሆነው ከገንዘብ ፍቅር ሁላችንንም ይጠብቀን፤ አሜን።

## ምዕራፍ ፲

# ክርስቲያንና

# ወሲብ (ዝሙት)

ወሲብ ፍትወት ወይም ፍትወተ ሥጋ፥ ሩካቤ ሥጋ፥ አፍቅሮተ ሥጋ ማለት ነው። ፍትወት ማፍቀር ነው፤ ለዚህ ነው አፍቅሮተ ያልኩት። ቀደም ባሉት ሁለት ምዕራፎች የተመለከትናቸው አፍቅሮተ ወንበር (ሥልጣን) እና አፍቅሮተ ንዋይ (ገንዘብ) ናቸው። ይህ ሦስተኛው አፍቅሮት ነው። ሦስቱም ጤናማ ገጽታዎች አሏቸው። ሥልጣን በስፍራው ጤናማ ነው። ጤና የሚያጣው በሌሎች ላይ መሠልጠን ሲጀምር ነው። ገንዘብም በልኩና በአግባቡ ጤና ነው፤ ጤናቢስ የሚሆነው ገንዘብ ሳይሆን የክፋት ሁሉ ስር የሆነው ገንዘብን መውደድ ሰውን ሲገዛና ልብን ሲደፍን ነው። ወሲብም በተፈቀደለትና  እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር በፈጠረለት በቦታው፥ ጤናማ ነው። ጤናቢስና እኩይ የሚሆነው፥ ከታቀደለት፥ ከተሠራለት መስመር ሲወጣና አንድ ሰው የእርሱ ካልሆነች ሴት ወይም ሴቶች ጋር፥ ወይም በአንጻሩ፥ አንዲት ሴት የሷ ካልሆነ ሰው ወይም ሰዎች ጋር ሲዘሙቱና ሲያመነዝሩ ነው።

ክርስቲያንና ወረትን ስንመለከት ስለ 'የእግዚአብሔር ሰው' ማንነት አንሥቼ ነበር። 'የእግዚአብሔር ሰው' የሚለው መጠሪያ በጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ 32 ጊዜ እንደተጻፈና ከ32ቱ ውስጥ 30ው በብሉይ ኪዳን ሲገኙ ሁለቱ ብቻ በአዲስ ኪዳን ይገኛሉ ብዬም ነበር። በአዲስ ኪዳን ውስጥ 'የእግዚአብሔር ሰው' የሚለው ሐረግ የተጻፈባቸውን ሁለት ጥቅሶችም አመልክቼ ነበር። ከሁለቱ ጥቅሶች አንዱ፥ *አንተ ግን፥ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ከዚህ ሽሽ፤ ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም ፍቅርንም መጽናትንም የዋህነትንም ተከታተል።* የሚለው በ1ጢሞ. 6፥11 የሚገኘው ነው። አንተ ማን አለ? አንተ የእግዚአብሔር ሰው። ምን አድርግ አለ? ሽሽ! ሽሽ ነው የተባለው። ሽሽ ብቻ ሳይሆን ከአንድ ነገር ሽሽ ነው የተባለው። ክፍለ ምንባቡን ስናጤነው ከገንዘብ መውደድ ሽሽ ነው የተባለው። የእግዚአብሔር ሰውነት ወይም የእግዚአብሔር ሰው መሆን አንድ መታወቂያ ሽሽት ነው። ከንዋይ ፍቅር ሽሽት።

ይህ የእግዚአብሔር ሰው፥ ጢሞቴዎስ ሌላም 'ሽሽ' የተባለው ነገር አለ፤ *ከክፉ የጎልማሳነት ምኞት ግን ሽሽ፥ በንጹሕም ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር ጽድቅን እምነትን ፍቅርን ሰላምን አጥብቀህ ተከተል።* ተብሎ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶታል፤ 2ጢሞ. 2፥22። የጎልማሳነት የሚለው ይህ የአዲስ ኪዳን ቃል በጠቅላላው ኪዳን ውስጥ እዚህ ብቻ የተጠቀሰ ቃል ነው። ወጣትነት እንደ ማለት ነው። ያስጠነቀቀው ግን በደፈናው፥ 'ከወጣትነት ምኞት ሽሽ' ብሎ አይደለም። ወጣትነት ብዙ መልካም ምኞቶች፥ መልካም ሕልሞች፥ መልካም ውጥኖች፥ መልካም ራእዮች አሉበት። ከነዚህ ሁሉ እንዲሸሽ አልነገረውም። ይህ ቃል ἐπιθυμία (ኤፒቱሚያ) በጥቅሉ ምኞት ማለት ነው። ምኞት ሲባል ምኞት ሁሉ ክፉ ነው ማለት አይደለም። መልካካም ምኞቶችም አሉ። የመልካም ምኞት መግለጫ እየተባሉ የሚላኩ ካርዶችና ሌሎች የዚህ መግለጫ ነገሮችም አሉ። መልካም ምኞት መልካም ነው።

ነገር ግን እዚህ ሽሽ የተባለው እንዲያው በጥቅሉ ከምኞት አይደለም። ይህ 'ምኞት' የተባለው ቃል መልካም ምኞቶችንም የሚገልጥ ቃል ነው። ለምሳሌ፥ ሉቃ. 22፥15 *እርሱም፦ ከመከራዬ በፊት ከእናንተ ጋር ይህን ፋሲካ ልበላ እጅግ እመኝ ነበር፤* ባለበት የተጠቀሰው ምኞት ይህ ተመሳሳይ ቃል ነው። ይህ መልካም ምኞት ነው። በሌላ ቦታ ደግሞ ይኸው ቃል ጎጂ ምኞትም ተጠቅሶበታል፤ *የዚህም ዓለም አሳብና የባለጠግነት ማታለል የሌላውም ነገር ምኞት ገብተው ቃሉን ያንቃሉ፥ የማያፈራም ይሆናል።* ማር. 4፥19። ይህኛው ምኞት ክፉ ምኞት ነው። ቃሉ የተነገረው ስለ አራቱ አፈሮች በተነገረበት ነው። ከአራቱ አፈሮች ይህ ሦስተኛው በእሾህ መካከል የወደቀው ዘር ነው። ጥሩ ያልሆነ ምኞት ይህንን ዘር ፍሬ እንዳያፈራ አደረገው።

እዚህ ጢሞቴዎስ ሽሽ የተባለው ከምኞት አይደለም። ከጎልማሳነት ምኞትም እንኳ አይደለም። ምክንያቱም መልካም የሆኑ የጎልማሳነት ምኞቶችም አሉና። ነገር ግን ሽሽ የተባለው፥ <u>ከክፉ</u> የጎልማሳነት ምኞት ነው። ቆላ. 3፥5 ላይ ይኸው ቃል ራሱ ክፉ ምኞት ተብሏል፤ *እንግዲህ በምድር ያሉቱን ብልቶቻችሁን ግደሉ፥ እነዚህም ዝሙትና ርኵሰት ፍትወትም <u>ክፉ ምኞትም</u> ጣኦትንም ማምለክ የሆነ መጎምጀት ነው፤* ይህ ክፉ ምኞት ከምን ከምን ጋር እንደተዘረዘረ ስናይ ምንነቱ ግልጥ ነው። *ዝሙትና ርኵሰት ፍትወትም ክፉ ምኞትም።*

ለጢሞቴዎስ፥ *ከክፉ የጎልማሳነት ምኞት ግን ሽሽ፥* ተብሎ በተጻፈበት ቃል 'ክፉ' የሚለው ቅጽል የለበትም፤ ምኞት ብቻ ነው የሚለው፥ ከጎልማሳነት ምኞት ሽሽ ነው ቃሉ የሚለው። ግን ያ ምኞት የሚሸሹት ምኞት ከሆነ፥ ያንን መሆኑ በራሱ ክፉ መሆኑን ያሳያልና ያንን ለማመልከት ነው በአማርኛው ትርጉም፥ 'ክፉ ምኞት' የተሰኘው። ከምኞት ሽሽ ቢባል፣ 'ከምን ምኞት? ምንም ምኞትን መመኘት የለብኝም ማለት ነው?' ተብሎ እንዳይጠየቅ የተጨመረ ከሳች ቅጽል ነው። የ1879 ትርጉም፥ 'ከብላቴንነትም ፍትወት ራቅ።' ይለዋል።

> ፳፪፡ ከብላቴንነትም፡ ፍትወት፡ ራቅ። ጽድቅንና፡ ሃይማኖትንም፡ ፍቅርንም፡ ሰላምንም፡ ለመሻት፡ ሩጥ፡ የጌታን፡ ስም፡ በንጹሕ፡ ልቡና፡ ከሚጸሩ፡ ጋራ።
> 
> ²ኛ፡ ጢሞ፡ ፪፡ ፳፪።

ይህ፥ 'የብላቴንነት ፍትወት' የሚለው ሐረግ፥ በተለይም 'ፍትወት' የሚለው ቃል ትክክለኛና ገላጭ ቃል ነው። በሮሜ 1፥24 ጳውሎስ ፍትወት ያለው ቃል ይህ ቃል ነው። ስለዚህ ምኞት ፍትወት ተብሎ ሊተረጎም ይቻላል። *ስለዚህ እርስ በርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ ርኵስነት አሳልፎ ሰጣቸው፤* ሮሜ 1፥24። ክፉ ምኞት እና ፍትወት የሚሉት ቃላት ምንነት እዚህ ላይ ይታያል። የጎልማሳነት ክፉ ምኞት ፍትወት ነው፤ ከመስመር የወጣ ወሲባዊ ፍላጎትና ድርጊት ነው። ከዚህ ነው ሽሽ የተባለው ጢሞቴዎስ። ጢሞቴዎስ ከሐዲ ወይም ያላመነ ሰው አይደለም። ጢሞቴዎስ ለብ ያለ ክርስቲያን ወይም እዚህም እዚያም የሚረግጥ ወላዋይ ሰውም አይደለም። ጢሞቴዎስ የነጠረ፥ የተመሰገነ፥ የተመሰከረለት፥ የተጨበጨበለት ወጣት አገልጋይ ነው። ይህ ሰው ነው ሽሽ የተባለው። ጤናማ ሰው ነው ሽሽ የተባለውና የሚባለው። ጤናማ ሰው ነው መሸሽ ያለበት። በእርሱ አቅምና አቋም ያለ ሰው ይህንን ከተባለ ትእዛዙ ለሁላችንም ጮክ ብሎ የሚናገር ይመስለኛል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወሲብን የሸሹም፥ አፈንፍነው የፈለጉም ጥቂት ያልሆኑ ምሳሌዎች እናገኛለን። መጽሐፍ ቅዱስን የሐቅ መጽሐፍ መሆኑን እንድንቀበል ከሚያደርጉን ነገሮች አንዱ ገመና ሸፋኝ አለመሆኑ ነው። የሰዎችን ውድቀትም ይጽፍልናል፤ እንድንጠነቀቅ። የሰዎችን በጎና ጠንካራ ጎንም ይጽፍልናል፤ እንድንማር። እናም፥ ፍትወትን አፈንፍነው ከፈለጉት ውስጥ ዳዊት ዓይነተኛ ምሳሌ ነው። ዳዊት የኦርዮን ሚስት ቤርሳቤህን ሲተኛት በዚያን ጊዜ፥ አንድ አይደለም፤ ሰባት ሚስቶች ነበሩት። የናባል ሚስት የነበረችው አቢግያ፥ ዒይዝራኤላዊቱ አኪናሆም፥ የሳኦል ልጅ ሜልኮል፥ የጌሹር ንጉሥ የተልማይ ልጅ መዓካ፥ አጊት፥ አቢጣል፥ ዔግላ፥ በጠቅላላ ሰባት ሚስቶች ነበሩት፤ 2ሳሙ. 3። እነዚህ ሁሉ እያሉት ነው ያቺን፥ ናታን ለዳዊት ፍርድን ሲናገርበት፥ 'አንዲት ታናሽ በግ' ብሎ በግልገል በግ የመሰላትን ቤርሳቤህን የተኛት። ዳዊት ፍትወትን የተፈላለገና ያገኘ ሰው ነው። ኋላም የፍትወቱን ዋጋ ከነወለዱ የከፈለ ሰው ነው።

እንደ ዳዊት ያለ በሴት የፍትወት ፍቅር የተነደፈና ማንነቱን የለወጠ ሌላ ሰውም በመሳፍንት ታሪክ ውስጥ እናገኛለን። ሶምሶን ይባላል። *በሶሬቅ ሸለቆ የነበረች ደሊላ የተባለች አንዲት ሴትን ወደደ።* ደሊላ ወገኗ በግልጽ ባይጻፍልንም ፍልስጥኤማዊት ሳትሆን አትቀርም። እሱ ወደ‌ዳታል፤ እሷ ደግሞ እያስማማችው ናት፤ ልትሸጠው። ሆነላት፤ ተሳካላት፤ ሸጠችው። በዚያ ገንዘብ ምን እንዳደረገች አልተነገረንም። እሱ ግን ተዋረደ። ቀላል አልተዋረደም። መጀመሪያ ዓይኖቹን አወጡት፤ ወደ ጋዛ አመጡት፤ በናስ ሰንሰለት አሰሩት፤ በግዞት ቤት እህል አስፈጩት፤ ኋላ እንዲጫወትላቸው ጠሩት፤ ተጫወተላቸው፤ ተዘባበቱበት። የዚህ ሁሉ ጅማሬ የት ነው? የደሊላ ጉልበት ላይ መተኛቱ ነበር ጅማሬው።

እርግጥ ነው ሲሞት ብዙዎችን ፈጅቶ ነው የሞተው፤ ግን ያ ነበር ጥሪው? ወይስ ለፍትወት ሲል ተጠልፎ ተወስዶ ነው የሆነውን የሆነው? ምሳ. 7፥22-23 ውስጥ እንደተጻፈልን አእምሮ እንደጎደለው ወጣት ነው ሶምሶን የሆነው? ቃሉ እንዲህ ይላል፤ *እርሱ እንዲህ ስቶ ይከተላታል፥ በሬ ለመታረድ እንዲነዳ፥ ውሻም ወደ እስራት እንዲሄድ፥ ወፍ ወደ ወጥመድ እንደሚቸኩል፥ ለነፍሱ ጥፋት እንደሚሆን ሳያውቅ፥ ፍላጻ ጉበቱን እስኪሰነጥቀው ድረስ።* ጠቅላላውን ምሳ. 7ን አንብቡት። እዚህ ግን ሦስት ምሳሌዎች ተጽፈውልናል፤ *<u>በሬ</u> ለመታረድ እንዲነዳ፥ <u>ውሻም</u> ወደ እስራት እንዲሄድ፥ <u>ወፍ</u> ወደ ወጥመድ እንደሚቸኩል* ውጤቱ ይህ ነው። እነዚህ ሦስቱም ሕይወት ያላቸው ነገሮች ናቸው፤ መሸሽ ይችሉ ነበር፤ አልሸሹም፤ ወደ ጥፋት ሄዱ። ዳዊትና ሶምሶን ዋጋ ከፈሉ፤ አልሸሹምና።

በሌላ በኩል ደግሞ፥ ከነዚህ በተቃራኒ፥ ዮሴፍን እናገኛለን። ዮሴፍ ድንቅ የሽሽት ምሳሌ ነው፤ ግን እሱም ዋጋ ከፍሏል። ሽሽት ራሱም ለካ ዋጋ ያስከፍላል?! የጽድቅ ዋጋ! ታሪኩን በዘፍ. 39 እናገኛለን። አስደናቂ ታሪክ ነው። ዮሴፍ ከዳዊት ወይም ከሶምሶን በፍጥረቱ የተለየ ሰው አይደለም። እንደነሱ የሆነ ሰው ነው። እንዲያውም በዕድሜ ከሶምሶን ምን ያህል እንደሚያንስ ባናውቅም፥ ከዳዊት በጣም ያነሰ ነው። ወይም በሌላ ገጽታው፥ ዳዊትና ሶምሶን ለዮሴፍ የሆነው ጸጋ ሊሆንላቸው የማይችል ሰዎች አልነበሩም። ልዩነቱ ምንድር ነው? ልዩነቱ በእግዚአብሔር ፊት የመመላለስ ምሥጢር ነው።

የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍን አብሯት እንዲተኛ ስትጠይቀው የተናገራት ይህንን ምሥጢር የሚያሳይ ነው፤ *እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?* ዘፍ. 39፥9። የማሸነፉ ምሥጢር በእግዚአብሔር ፊት የመመላለሱ ምሥጢር ነው። ማንም ሳያይ ምንም ነገር ማድረግን ሰዎች፥ 'ቀላልና ምንም ያይደለ ነገር' ሊሉት ይችላሉ። ዮሴፍ ግን ምን አለው? 'ትልቅ ክፉ ነገር!' አለው። ከጲጥፋራ ሚስት ጋር ቢተኛ ማንም አያያቸውም፤ ከሁለቱ በቀርም ማንም አያውቀውም። ዮሴፍ ግን የሚያይና የሚያውቅ መኖሩን ያምን ነበር። 'ሁሌ በሚያየው በእግዚአብሔር ፊት!' የሚመላለስ ሰው ነበረ።

ይህ እዚህ የምንመለከተው ወሲብ የፍትወት ፈተና ነው። ይህኛው ከሌሎቹ ፈተናዎች ይልቅ ጠንካራው ሳይሆን አይቀርም። ምሥጢራዊውና አደገኛው ፈተናም ነው። አደጋው ምሥጢራዊነቱ ራሱም ነው። እንደ ሌሎቹ የሚታይ አይደለምና ምሥጢራዊው ጎጂ ፈተና ነው። ወሲባዊ ወይም የፍትወት አደጋ ምሥጢራዊ ነው ሲባል ምሥጢራዊነቱ በሁለት ደረጃ ድርብ ነው።

አንደኛ፥ በአካል ሳይገናኙም ማመንዘር ይቻላል። ምንም ሳይታዩ፥ በማንም ሳይታዩ በልብ ማመንዘር ይቻላል፤ ማቴ. 5፥27-28 *ኢታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።* ጌታ በተራራው ስብከት (ማቴ. 5-7) ይህንንና ሌሎቹንም ነገሮች ሲያስተምር ወደ ልብ እያመለከተ ነው። ለምሳሌ፥ በዱሮው፥ በአሮጌው ኪዳን፥ 'እንደተባለ ሰምታችኋል' በተባለለት ኪዳን፥ (ልብ እንበል ጌታ ይህን ሲል አዲሱ ኪዳን ገና አልቆመም፤ አዲሱ ኪዳን በመስቀል ላይ ነው የተመሠረተው፤ ግን የአዲሱን

ኪዳን ሕግ፥ ልብ ላይ የሚቀረጸውን ሕግ ነው እያስተማረ ያለው።) በዱሮው ኪዳን መግደል ሲባል በአካል መግደል ነው። ጌታ ግን መጥላትን መግደል ነው አለው። መግደል ከመጥላት ነዋ የሚጀምረው። መጥላት ልብ ውስጥ ነዋ የሚጀምረው፤ አንድን ሰው ባትጠላው አትገድለውማ።

ማመንዘርም ልክ እንደዚያው ነው። በዱሮው፥ በአሮጌው ኪዳን ማመንዘር የሚባለው ሁለት ሰዎች ከጋብቻ በፊት ወይም ከጋብቻ ውጪ በአካላቸው በፍትወተ ሥጋ ሲገናኙ ወይም ሩካቤ ሥጋ ሲፈጽሙ ነው። ግን ለምን ፈጸሙ? ያ መፈጸም እንደ ስሙ መፈጸም ነው፤ ፍጻሜ ነው፤ ግን ወደ ወፈጸሙ፥ ወደ ፍጻሜው ምን ወሰደው? ምን ወደ ዳር አደረሰው? የት ጀመረ? ምን ውስጥ መነጨ? ብንል መልሱ፥ 'ልብ ውስጥ!' ነው። ድርጊቱ የሚመነጨው እልብ ውስጥ ነው። አንዳንዴ እዚያው እልብ ውስጥ ይበቅልና እዚያው ውስጥ ይከስማል። እዚያው ይከሽፋል። አንዳንዴ እዚያው ቤቱን ሠርቶ ይኖራል፤ እንደ ተጣለ ዕንቁላል፥ ሊፈለፈል ቀን እንደሚቆጥር ሆኖ ይኖራል። እዚያው እውስጡ፥ እዚያው እውስጧ። እልብ ውስጥ ተተክሎ ይኖራል። በአሳብ እያየ፥ በምናብ እያየች በልባቸው ያመነዝራሉ። አሳቡና ምናቡ ደብዘዝ ሲል ደግሞ ምናቡን የሚያጦዝ ነገር ይጨምሩበታል። የፖርኖግራፊ ምስሎች እያዩ እራሳቸውን በራሳቸው ያረካሉ። ቆይቶ ምስሎቹም በቂ አልሆን ሲሉ ወደ ተንቀሳቃሽ ምስሎች ይቀየራሉ።

ያም አይበቃም። የፖርኖግራፊ ችግር፥ እንደ ሱስ ነው፤ ይጨምራል እንጂ፥ ከዚያ የበለጠ ይፈልጋል እንጂ አይቀንስም፤ ከዚያ ባነሰው አይረካም። እንደ ኢትዮጵያ የዕቃ ዋጋ ነው። የኢትዮጵያ ዕቃ ዋጋ አንዴ ከወጣ ወይ እዚያ ይቆያል፤ ወይም ብዙ ጊዜ ይጨምራል፤ እንጂ አይቀንስም። እንዲቀንስ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ቢኖሩም ወይም ሲኖሩም እንኳ አይቀንስም። ይህም እንደዚያ ነው። ፖርን እንደ ሱስ ነው፤ ከበፊቱ የበለጠ ይጠይቃል። ቪድዮውም ወረቱ ሲያልቅ ወደ ስልክ ወሲብ ይቀይሩታል። Phonesex እና sexting ይባላል። የሚታይ ነገር ከኖረ፥ ልብ እንበል፤ ምናብ ብቻ ሳይሆን ከዚያ ሊያልፍም ይችላል፤ ደግሞም ያልፋል። ይህ ሩቅ ለሩቅ ይሁን እንጂ ላይቭ የሆነ፥ ወይም በዚያው ሰዓት የሚካሄድ ምስለ አካላዊ ግንኙነት አለበት። በምስል እና በድምጽ እያወሩ ራሳቸውን በራሳቸው ያረካሉ። ፈተናው ግን በዚያ አያቆምም፤ ርቀት ነው በስልክ በድምጽ ወይም በምስል ብቻ እንዲገናኙ ያደረጋቸው እንጂ፥ ርቀቱ ቢከነዳስ? ወይም ሲከነዳስ? ርቀቱ ሲወገድ ወደ አካላዊ ግንኙነት ይዛወራል። ርቀት ከለከለው እንጂ ርቀቱ እንደ መጋረጃ ሲነሣ ምንም ኢጋጅ፥ ምንም ጋራጅ የለም። ይህ አንደኛው የምሥጢራዊ ግንኙነቱ ገጽታ ነው። ወሲባዊ ወይም የፍትወት አደጋ ምሥጢራዊ ነው ሲባል ምሥጢራዊነቱ በሁለት ደረጃ ድርብ ነው ብያለሁ ይህ አንደኛው ነው።

ሁለተኛው፥ ምሥጢራዊ ግንኙነት ከምናባዊው ወሲብ ባለፈ በአካል ሁለቱ ሰዎች ሲገናኙም በምሥጢርና በድብቅ ነው። ብዙዎቹ ኃጢአቶች ምናልባት ሁሉም፥ ሲፈጸሙ በድብቅ ነው፤ ለዚህኛው ደግሞ ተጨማሪ፥ ተደራቢ፥ ካብ ይደረግለታል። በምሥጢር ይጠበቃል፤ ውርደት ስላለበት፤ ቅሌት ስላለበት፤ የስም መጥፋትና የታሪክ

መጉደፍ ስላለበት። ስለዚህ ምሥጢርነቱ ራሱ በምሥጢርነት የተደበቀ፥ በሽፋኖች የተሸፈነ ነገር ነው።

ወሲብ ከባድ ፈተና ነው። ፈተና ሁሉ ፈተና ነው፤ ከባድ ነው፤ የፈተና ቀላል የለውም። እርግጥ ነው፤ የአንዱ ከባድ ፈተና ለሌላው ቀላል ፈተና ሊሆን ይችላል። የወሲብ ፈተና ምናልባት ከፈተናዎች ሁሉ ከባዱ ሳይሆን አይቀርም። ያላገቡ ብቻ ሳይሆኑ፥ ያገቡት ካላገቡ ጋር፥ ወይም ሁለቱም ያገቡና በትዳር ውስጥ ያሉ ሰዎችም በዚህ ፈተና ይወድቃሉ፤ ወድቀዋል፤ በዚህ ውስጥ ተገኝተዋል፤ ይገኛሉም።

መውደቅ አንድ ነገር ነው፤ ወድቆ መገኘት ወይም ወድቆ መነሣትም አንድ ነገር ነው። ወድቆ በዚያ ውድቀት ውስጥ <u>መኖር</u> ግን ሌላ ጉዳይ ነው። ወድቆም ያንን ውድቀት እያጣጣሙ፥ እየተደሰቱበት <u>መኖር</u> ግን ሌላ ጉዳይ ነው። ስለ ክርስቲያኖች ነው የምናገረው። ስመ ጥር የሆኑ፥ ስማቸው የተጠራ አገልጋዮችም በዚህ የወሲብ ፈተና ወግተዋልም፥ ተወግተዋልም። የሚከፋው ነገር፥ አንድ የወደቀ ሰው፥ ከወደቀ በኋላ በጸጸትና በንስሐ ቢመለስ፥ ይህ ንስሐ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ልማድ መሆኑ የታወቀ ሆኖ ሳለ፥ ቤተ ክርስቲያን ብትገስጸውና ብትቀጣው፥ ወይም ከአገልግሎት ብታግደው ይህ የተለመደ የቤተ ክርስቲያን አደራረግና ወግና ባህልና ልማድ ሆኖ ሳለ፥ <u>ብዙ ሰዎች፥ አገልጋዮችም ጭምር፥ በድፍረት ይህንን ድብቅም፥ ልቅም የሆነ ወሲባዊ ግንኙነት እንደ መደበኛ የኑሮ ክፍላቸው ቆጥረውት እየኖሩና፥ እየኖሩ ብቻ ሳይሆን እዚያ ውስጥ እየኖሩ ሳሉ እያገለገሉም ነው።</u>

ምንድር ነው ያልኩት? እዚያ ውስጥ እየኖሩ እያገለገሉም ነው። ይህ እውነት ነው። ሲያገለግሉ ደግሞ ያንን ኃጢአት ባያደርጉት ኖሮ ከሚኖራቸው የበለጠ ሰው-ሠራሽ ድፍረትና ወኔ ይኖራቸዋል። ሰው-ሠራሽ ነው ያልኩት። ይህኛው ሰው-ሠራሽ ወኔ ምናልባት ውድቀትን ለማካካስ፥ ንጹሕ መስሎ፥ ጨዋ መስሎ ለመታየት የሚደረግ ሙከራ ሳይሆን አይቀርም። ልክ ሶምሶን እንዳደረገው፤ *እርስዋም በጉልበትዋ ላይ አስተኛችው፤ አንድ ሰውም ጠራች፥ እርሱም ሰባቱን የራሱን ጉንጉን ላጨው። ልታዋርደውም ጀመረች፥ ኃይሉም ከእርሱ ሄደ። እርስዋም፦ ሶምሶን ሆይ፥ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ አለችው። ከእንቅልፉም ነቅቶ፦ <u>እወጣለሁ እንደ ወትሮውም ጊዜ አደርጋለሁ አለ።</u> ነገር ግን እግዚአብሔር ከእርሱ እንደ ተለየው አላወቀም።* መሳ. 16፥19-20። ሶምሶን ፍልስጥኤማውያን ሲይዙት፥ *እወጣለሁ እንደ ወትሮውም ጊዜ አደርጋለሁ* ነው ያለው። ምናልባት ሳይጎደፍርና አቧራ ሳያስነሣ አልቀረም። ተርታ ሰው መሆኑን እስኪያውቅ።

እና እነዚህም ይጎደፍራሉ፤ ያገለግላሉ። ቆሻሻ ያጥናሉ፤ ነውር ይሠዋሉ። ያገለግላሉ ሲባል መጥቶ የሚሄድ አገልግሎትን ማገልገል ሳይሆን አንዳንዶቹ መደበኛ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ሆነው በየሳምንቱና በሳምንት ሁለቴ ሦስቴ በመድረክ ላይ ለሳምንታት፥ ለወራት፥ ለዓመታትም እየቆሙ፥ በየጀማ ጉባኤዎች እየታደሙ፥ ራሳቸውም ኮንፈረንስ እያዘጋጁ እየተናገሩ፥ በማኅበራዊ መገናኛዎች በየቀኑ እየሰበኩና እያስተማሩ፥ ነገር ግን በወሲብ ወጥመድ ውስጥ ተጠምደው፥ በቀንበሩ ስር ተይዘው፥ ያንን መይያዝ እንደ ወጥመድ ሳይሆን እንደ <u>ኑሮ</u> አድርገው ቆጥረውት የሚኖሩ፥ ቅርም የማይላቸው፥

ጎሊናቸውም የማይከስሳቸው፥ ኃጢአቱ የማይቆረቁራቸው፥ የሚታወቁም የማይመስላቸው ስመ ጥር፥ ስማቸው የተጠራ ሰዎች ብዙ ናቸው።

ዛሬ እንደ ዔሊ ዘመን እግዚአብሔርን የማያውቁ ምናምንቴዎች፥ የቅድስናው ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች፥ በቤተ ክርስቲያን መድረክ መሥዋዕት እያሳረጉ ይገኛሉ። የዔሊ ልጆች መሥዋዕት እያሳረጉ፥ በመቅደስ ከሚያገለግሉ ሴቶች ጋር ይተኙ ነበር። ምናልባት የሚተኙትም በቤተ መቅደስ ሳይሆን አይቀርም። አገልግሎታቸውም አይቋረጥም፤ ማመንዘሩም አይቋረጥም። እያገለገሉ ያመነዝራ፤ እያመነዘሩ ያገለግላሉ። አባታቸውም ሰምቶ አልተቆጣም። በቁርባኑ በሚያደርጉት ብቻ ሳይሆን በምናምንቴነታቸውም ቁርባኑ ራሱም የተናቀ ይሆን ነበር። በድርጊታቸው ብቻ ሳይሆን በአድራጊዎቹ በራሳቸው ማንነትም የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተናቀ ይሆን ነበር። ይህ ያስደነግጣል።

ዛሬም በዘመናችን፥ አይደለም ከሴት ጋር፥ ከሴቶች ጋርም መተኛት ምንም ማለት እየሆነ መጥቷል። ባደፈ ሰውነት፥ በረከሰ ቁመና ወደ መድረክ ወጥተው ሰዎች ይቆማሉ፤ ያገለግላሉ፤ መሥዋዕት ያሳርጋሉ፤ ምንም ሳይመስላቸው። አንዳንዴ፥ በነዚያው በወሰለቱባቸው ሰዎች ፊት ቆመው ይዘምራሉ፥ ያስተምራሉ፥ ይሰብካሉ። ወደ ማኅበራዊ ሚድያ ቀርበው ያሰራጫሉ፤ ይሰራጫሉ፤ ዓለሙን ይሞሉታል። በነዚያው ሰዎች ፊትም ለመቆም አይደነግጡም።

ይህ ወንዶችን ብቻ ሳይሆን ሴቶችንም ይመለከታል። ፈተናው ወሲብ፥ ተፈታኞቹና ፈታኞቹ ሁለቱም ጾታዎች ናቸው። ነገሩ በምሥጢርና በሁለት ወይም በጥቂት ሰዎች ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ስለሆነ ብዙዎቹ ውስልትናዎች አይታወቁም። ቀደም ሲል እንዳልኩት ነገሩ ራሱ በምሥጢር ስለሚያዝና ስምምነት ስላለበት አፈትልኮ አይወጣም። አንዳንዴ ብቻ፥ አንዱ ወገን ጎጂና አጥቂ፥ ሌላው ወገን ተጎጂና ተጠቂ ሲሆን፥ ማስገደድና መድፈር ሲኖር፥ ጉዳቱም ሲሰፋና ሲጠልቅ አንዳንዶቹ ጥቃቶች ወይም ጉዳዮች ወደ አደባባይ ሊመጡ ግድ ይሆናል። እየሆነም ነው። ወደኔ ከመጡት ጥቂት ያልሆኑ ስሞታዎች መካከል፥ ጆሮ ጭው ከሚያደርጉት መካከል አንዱን አቀርባለሁ።

ክርስትና ደረጃና መለኪያ ያለው፥ መመሪያ ቃል ያለው እምነት ነው። ቅድስና መታወቂያው የሆነ እምነት ነው። አሁን አሁን፥ ‘የሆነ’ ሳይሆን ‘የነበረ’ ማለት ይቻላል። ቅድስና ዛሬ ከመድረክ አይሰበክም። ቀረ ዱሮ። ‘መቼ ነው ስለ ቅድስና ሲሰበክ የሰማችሁት?’ ብዬ ብጠይቅ፥ ‘ኧህ? ቅድስና? ምንድነው ቅድስና?’ የሚል ሁላ አይጠፋም። ቅድስና ሲሰበክ እንኳ ብንሰማ ትንሽ እንፈራ ነበር። ኃጢአትን ከመዳፈር እንታቀብ ነበር። መሰበኩ ሲቀር የሌለ ይመስለንና መፋነን እንጀምራለን። ቅድስና ከመድረክ መሰበክ ሲያቆም ርኵሰት ስፍራውን ይወስደዋል። ርኵሰት ባይሰበክም ይወስደዋል ይወርሰዋል። ልክ ጨለማ ስፍራውን የሚወርሰው ብርሃን ሲጠፋ እንደሆነ ሁሉ ማለት ነው። ጨለማ መጥቶ ብርሃንን ገፍቶ አይደለም ቦታውን የሚወስደው፤ ግን ብርሃን ቦታውን ሲለቅ ጨለማ ከየት መጣ ሳይባል ይወርሰዋል። ቅድስና ሲሰበክ ቢያንስ አስታዋሽ ነው፤ አሳሳቢ ነው፤ አመልካች ነው፤ ካልተሰበከስ? ካልተሰበከ ልዩ ልዩ ርኩሰቶች ቦታውን ይቀራመቱታል።

*የስርቆት ውኃ ይጣፍጣል፥ የተሸሸገም እንጀራ ደስ ያሰኛል።* ምሳ. 9፥17። ይህን ያለችው ሰነፍ ሴት ናት። አስረጂዋ ደግሞ ጥበብ ወይም ጠቢብ ሴት ናት። በምሳሌ መጽሐፍ ውስጥ እነዚህ ሁለቱ እንደ ፈረቃ አስተማሪ እየተፈራረቁ ሲያስተምሩ ይታያሉ። ጠቢቧ ጥበብን፤ ሰነፏም ስንፍናን ያስተምራሉ። እነዚህን ሁለቱን አናጋሪው፥ 'ልጄ . . .' እያለ የሚናገረው ጸሐፊ ነው። በአብዛኛው ይህንን የጻፈው ሰሎሞን ነው። ሰሎሞን ጥበብን የለመነና ከለመነውም በላይ የተሰፈረለት ሰው ነው። ስለዚህ ጉዳይ ከተሰጠው ጥበብም፥ ከሕይወቱ ተሞክሮም ጭምር ነው የሚያስተምረው።

ከላይ የተጻፈውን የተናገረችው ወይም ግብዣውን ያቀረበችው ወ/ሮ ሰነፍ ሴት ስትሆን ተጋባዡ፥ አቶ አላዋቂ ወይም አቶ አእምሮ የጎደለው ነው። ግብዣው በሌላ ገጽታ ሲታይ ቢችልም፥ ጠሪዋም ተጠሪውም የግድ አንድ ፆታ ብቻ ናቸው ማለት አይደለም። ወደ ተግባራዊው ግንዛቤ ስንወርድ ሁሌም ጠሪዋ ሴት፥ ተጠሪው ወንድ አይደሉም። ዝውውሩ ከሁለቱም ወደ ሁለቱም ሊሆን ይችላል። ግብዣው፥ በሌሎች የመጽሐፉ ክፍሎች እንደሚታየው የወሲብ ግብዣ ነው።

የስርቆት ውኃ ድብቅ ወሲባዊ ተራክቦ ነው። ውኃው መጣፈጡ ስርቆቱን ወይም ውኃው የተገኘበትን መንገድ አይሰርዘውም። መሰረዝ ቀርቶ አያሳሳውም፤ አያቀጥነውም፤ አያደበዝዘውም። የተገኘበት መንገድ ስርቆት ነው። ስርቆት የራስ ያልሆነን በድብቅ የመውሰድ ሂደት ነው። ነገሩ ስርቆት ሳይሆን መሰራረቅ ነው። ሁለቱም ሰራቂዎች ናቸው፤ ሁለቱም ተሰራቂዎች ናቸው። በሂደቱ ሁለቱም የራሳቸው የሆነ ነገርን አጥተዋል። የራሳቸው ያልሆነ ነገር ወደ ሕይወታቸው ውስጥ ላይወጣ ገብቷል።

ወሲባዊ ተራክቦ ስፍራ አለው። ስፍራውም ትዳር ይባላል። በዚያ ስፍራ ከተራክቦ በፊት መሳቀቅና መሸማቀቅ የለም። በዚያ ስፍራ በተራክቦ ጊዜ ፍርሃትና ስጋት የለም። በዚያ ስፍራ ከተራክቦ በኋላ ቁጭትና ጸጸት የለም። የነዚህ ነገሮች አለመኖር የትዳር ወሲባዊ ተራክቦን ውበትና ጣዕም ያገንነዋል።

## ክርስቲያንና ወሲባዊ ጥቃቶች

የወሲባዊ ጥቃቶች ጉዳይስ? ስለ ክርስቲያንና ወሲብ ስንመለከት ቀደም ሲል፥ 'ክርስቲያኖች ሁሉ አመንዝራ እንዳይመስሉን እንጠንቀቅ። እንዲህ የሚያደርጉ ከበጣም በጣም ብዙ አንድ ናቸው፤' ብያለሁ። ምንም እንከን የሌለብን ንጹሐንና ፍጹማን ነን ብንል እንዴት ቆንጆ ነበር! ግን አይደለም። ፍጹማን አይደለንም። እንከን አለብን። እዚያ ያነሣነውን ከመስመር የወጣ ወሲባዊ ልቅነትን ኑሮዬ ብለው ወይም lifestyle አድርገው የሚኖሩበት ደግሞ ከብዙ ብዙ ሺህዎች ውስጥ አንድ ወይ በጣም ጥቂት ቢሆኑም መኖራቸውን የማንክደው ነው። አንድም ወይም ጥቂትም ቢሆኑ ግን

የብዙኃኑን ስም ማጉደፍ የሚችል ኃይል አላቸው። እነዚህ ሰዎች የተገለጡ፥ የታወቁ ቀን ክርስትና የተጠላ ይሆናል፤ የጌታ ስም ይሰደባል፤ ቤተ ክርስቲያንም ትነቀፋለች።

ለምን? ይህ ከኛ የማይጠበቅ ነው። በቃሉ የተሰጠን መታወቂያ አለ። 'ክርስቲያኖች እንዲህ ያሉ ናቸው' ተብሎ የሚታወቅ ቀድሞ በብዙዎች የተሰጠን ምስልና መታወቂያም አለ። በአገራችን ዱሮ፥ በተለይም በ1960ዎቹ 70ዎቹ፥ ስም አጥፊ ሰዎች፥ 'አማኞች፥ (ወይም በነሱ ቋንቋ ጴንጤዎች) መብራት አጥፍተው ብር ይበትኑና፥ ብር ከጣራ ዘነበ ይላሉ፤ መብራት አጥፍተው ክርስቶስ ከኛ ይወለዳል ብለው ያመነዝራሉ፤' ብለው ያስወሩ ነበር። ከወሬዎቹ አንዱ፥ ወይም አንዱ ሐሜትና ስም ማጥፋት በር ዘግቶ መብራት አጥፍቶ ማመንዘር ወይም መዘሞት ነው። ይህ ፈጠራ መሆኑን ፈጣሪዎቹ ራሳቸውም ያውቁታል። ሌሎቹም እየቆዩ አውቀውታል።

ያ የ60ዎቹና 70ዎቹ ዘመን በምዕራቡ ዓለም በተለይም በአሜሪካ፥ 'The Hippy era' ወይም 'the sexual revolution era' የሚባለው ዘመን ነበረ። እኛጋ የዚያ ዘመን አማኞች ከታሙ የሚታሙት በምንዝርና ሳይሆን በቅድስና ነው። በመዘሞት ሳይሆን ለሥጋ ፍላጎት በመሞት ነው። 'በር ዘግተው . . .' የሚባለው ወሬ የፈጠራ ወሬና የማጠልሸት አሉባልታ ብቻ ነበር። እየቆየ ግን፥ እየኖርን ስንመጣ ግን፥ በተለይም ከነፃነት ዘመን ወዲህ ግን፥ ከሐሰተኞች ነቢያትና ሐዋርያት መብዛት ወዲህ፥ ከቴክኖሎጂው ፍንዳታ ወዲህ የሚታዩት ነገሮች የሥጋ ገበያ እየሆኑ ነው።

አዲስ ኪዳን ስለ ሦስት ዓይነት ሰዎች ይነግረናል፤ ሦስቱንም በ1ቆሮ. 2 እና 3 እናገኛቸዋለን። በአጭሩ ሦስቱም ሰዎች እነዚህ ናቸው፤ አንደኛው ፍጥረታዊ ሰው ነው፤ እንደተፈጠረ ያለ፥ ያልዳነ፥ መንፈሳዊነትን የማይለማመድ፥ መለማመድም የማይችል፤ በፍጥረታዊ ሥርዓት የሚኖር ፍጥረታዊ ሰው ነው። ሁለተኛው መንፈሳዊ ሰው ነው፤ የዳነ፥ የክርስቶስ ልብ ወይም አሳብ ያለው፥ ክርስቶስን ለመምሰል እየተጋ የሚኖር ነው። ሦስተኛው ሥጋዊ ሰው ነው፤ ይህ ሰው የዳነ ሆኖ ሥጋው ወይም ሥጋዊ ባህርዩ ወጥሮ የያዘው፥ ለሥጋዊ ፍላጎቶች በቀላሉ የሚወድቅ ሰው ነው። መንፈስ ቅዱስ ያልገዛው፥ ያላሸነፈው፥ ከዚህ በፊት በዚህ ዝግጅት ውስጥ ያየናቸው ሦስቱ ወዎች በቀላሉ የሚጠልፉት ሰው ነው።

ይህኛው ሦስተኛው ዓይነት ሰው ሳይድን የዳነ የሚመስል ከቅዱሳን ጋር የተደባለቀ፥ የሚመስል ግን ያልሆነ ሰውም ሊሆን ይችላል። እንዲያ ከሆነ ሥጋዊ ሳይሆን ያልዳነ ደባል ሰው ነው። የዳነ ሰው ዋናው ውጫያዊ መታወቂያው ፍሬ ነው። ከፍሬዎቹ አንዱ የንስሐ ፍሬ ነው። በኃጢአት ውስጥ ሆኖ ኃጢአት የማይረብሸውና የማይቆረቁረው ከሆነ ያ ሰው ያልዳነ ሰው ነው። ገና ሙትና በድን ሰው ነው። ለዚህም ነው ኃጢአት የማይቆረቁረውና የማይጎረብጠው። ግን ቅዱስ መስሎ በቅዱሳን መካከል ጉድ ጉድ ሊል ይችላል። ቀደም ሲል እንዳልኩት፥ መውደቅ አንድ ነገር ነው፤ አንዴ መውደቅና ወድቆ መገኘት ወይም ወድቆ መነሣት አንድ ነገር ነው። ወድቆ በዚያ ውድቀት ውስጥ <u>መኖር</u> ግን ሌላ ጉዳይ ነው። ወድቆም ያንን ውድቀት እያጣጣሙ፥ እየተደሰቱበት <u>መኖር</u> ይህ ሌላ ጉዳይ ነው። ይህ ሥጋዊነት ሳይሆን ከሥጋዊነትም የወረደ አደገኛ ማንነት ነው።

ወደ ሥጋው ገበያ ልመለስ። ከላይ እንዳልኩት፥ እየቆየ ግን፥ እየኖርን ስንመጣ ግን፥ በተለይም ከነፃነት ዘመን ወዲህ፥ ሐሰተኞች ከመብዛታቸው ወዲህ ግን የሚታዩት ነገሮች የሥጋ ገበያ እየሆኑ ነው። ቤተ ክርስቲያንን ልኳንዳ ቤት ያስመሰሏት ሰዎች በገፍ እየታዩ ናቸው። እንደ ካህኑ እንደ ዔሊ ዘመን እያገለገሉና እያመነዘሩም፥ እያመነዘሩና እያገለገለገሉም፥ ሁለቱንም በእኩል እያስኬዱ የሚገኙበት ዘመን እየሆነ ነው። የዔሊ ልጆች ይህንን በድግግሞሽ ማድረጋቸውን ቃሉ ግልጽ አያደርግልንም። *ቃሉ እዚያ የሚለው፥ ዔሊም እጅግ አረጀ፤ ልጆቹም በእስራኤል ሁሉ ላይ ያደረጉትን ሁሉ፥ በመገናኛውም ድንኳን ደጅ ከሚያገለግሉት ሴቶች ጋር እንደ ተኙ ሰማ። እርሱም አላቸው፡- ስለ ክፉ ሥራችሁ ከዚህ ሕዝብ ሁሉ ሰምቻለሁና ስለምን እንዲህ ያለ ነገር ታደርጋላችሁ? ልጆቼ ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ኃጢአተኛ በማድረጋችሁ ስለ እናንተ የደረሰኝ ወሬ መልካም አይደለምና ይህ አይሆንም። ሰውስ ሰውን ቢበድል እግዚአብሔር ይፈርድበታል፤ ሰው ግን እግዚአብሔርን ቢበድል ስለ እርሱ የሚለምን ማን ነው? እነርሱ ግን እግዚአብሔር ሊገድላቸው ወድዶአልና የአባታቸውን ቃል አልሰሙም።* 2ሳሙ. 2፥22-25።

የዔሊ ልጆች ይህንን በድግግሞሽ ማድረጋቸውን ቃሉ ግልጽ ባያደርግልንም፥ አንዴም ብቻ ማድረጋቸው ትልቅ ጉዳት ነው። ስገምተው፥ ምናምንቴዎች ሰዎች ናቸውና አንዴ ብቻ ያደረጉትም አይመስልም። እንዲህ ያለው ነገር በመደበኛ መልኩ የሚደረግ ከሆነስ? ከሆነ ይህ ደግሞ መደበኛ ጉዳት ነው። ይህ የጉዳት አገልግሎት ወይም የጎጂነት አገልግሎት ሊባልም ይቻላል። የጉዳት አገልጋዮች በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ይገኛሉ።

ይህን የክርስቲያንና ወሲብ ትምህርት ወይም ጽሑፍ ስጀምር፥ ቤተ ክርስቲያን አካል መሆኗን በመግለጥ ነበር የጀመርኩት። አካልን የሚጎዱ ነገሮች አሉ በማለትና እነዚህን ጎጂ ነገሮች በማሳየት ነበር የጀመርኩት። ሌላው ቀደም ሲል የጠቀስኩት ነገር፥ 'ጉዳቶች በምስጢር ይያዙና፥ (በተለይም ወሲባዊ ጉዳት) አንዳንዴ ብቻ፥ አንዱ ወገን ጎጂና አጥቂ፥ ሌላው ወገን ተጎጂና ተጠቂ ሲሆን ብቻ፥ ጉዳትም ሲሰፉና ሲጠልቅ ብቻ፥ አንዳንድ ጉዳዮች ወደ አደባባይ ሊመጡ ግድ ይሆናል፤' ብዬ ነበር።

ቤተ ክርስቲያን አካል እንደመሆኗ መጠን እንዲህ ያለው ከትዳር ውጪ የሆነ ልቅና፥ ድብቅ ወሲባዊ ግንኙነት አገልግሎትን ያሳድፋል፤ ታሪክን ያጎድፋል፤ ምስክርነትን ያበላሻል፤ አካሉን ማለትም፥ ቤተ ክርስቲያንን ይጎዳል። ቤተ ክርስቲያን አካል ናት። ሌሎችም ጉዳቶች አሉ። ኃጢአቱ ተከትሎን ይሄዳል፤ የሚፈርስ ትዳር፥ የሚጎድዱ ልጆች፥ ግራ የሚጋቡ ክርስቲያኖች መኖራቸው ውስብስቡን ይጨምረዋል። የጌታ ስም ይሰደባል፤ ቤተ ክርስቲያን ትንቋሸሻለች፤ ቅሌት ይሆናል፤ ወንጌል ይደናቀፋል፤ ሰዎች ወደ ጌታ እንዳይመጡ መሰናከል ይሆናል። 'እናንተ ከኛ በምን እኮ ነው የምትለዩት?' ሲባል፥ 'በምንም!' ካልን ወንጌል መነገር አይቻልም። ይህ ሆኖ ያውቃል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሳዮችና አስመሳዮች አሉ፤ ሥጋውያንና ግብዞች አሉ። ግብዝ ማለት ተዋናይ ማለት ነው። የሚተውኑ ሰዎች አሉ። በኃጢአት የታሰሩ ሰዎችም አሉ። አንዳንዶቹ ግን የታሰሩ ሳይሆኑ የተፈቱና የተለቀቁ አራዊቶች ሆነው እየነከሱ፥

እያቆሰሉ የሚኖሩ ናቸው። የጎጂነት አገልግሎት ያልኩት ይህንን ነው። ድርጊቱ ቀጣይ ሲሆን ጉዳቱም ቀጣይ ነው።

በተለይ ታዋቂ አገልጋዮች ከሆኑ አንዳንዴ ነገሩ ካለፈ በኋላም እንኳ ታሪኩ ተመልሶ ሊመጣ ይችላል፤ ይመጣልም። ሌላው ቀርቶ ሰውየው ከሞተና ከተቀበረ በኋላም ይወጣል። የሰውየው ሳይሆን የታሪኩ አስከሬን ይወጣል። አስከሬን ደግሞ፥ የሰውም ይሁን የታሪክ አያምርም። በ2020 አጋማሽ ወደ ጌታ የሄደው የምናከብረው፥ እኔ እጅግ የማደንቀው የምካቴ ክርስትና ታዋቂ አገልጋይ ራቪ ዘካሪያስ ከሞተ በኋላ የወሲብ መተላለፍ (sexual misconduct) ፈጽሞብናል ያሉ ሴቶች መጥተው ነበር።

ወደ ራቪ ጉዳይ እመለሳለሁ። ጌታን የማያውቁ ሰዎች የፈለጉትን አድርገውም፥ እንዲህ ያለውን መተላለፍ ጉዳይ ማንም ከቁብ አይቆጥረውም። እንኳን ከሞቱ በኋላ በሕይወት እያሉም ማንም ምንም አይላቸውም። ለምን? እዚያ ያለው የሞራል ኮምፓስ ወደ ብዙ አቅጣጫዎች አመልካችና የተምታታ ነው። ወይም የሞራል ከፍታው ከፍ ያለ አይደለም። መለኪያው የተሰበረ ነው። ያ ማለት ግን ግብረ ገባውያን ሰዎች የሉም ማለት አይደለም፤ አሉ። እንዲያም ሆኖ፥ ከዓለማውያንም ትልልቅ ወይም ስማቸው የተጠራ ሰዎች ይህንን ሆነው ሲገኙ ድንጋጤ ይፈጠራል። ቢል ክሊንተን ከሞኒካ ጋር ወሰለተ ተብሎ ጉዳዩ 'ተራገበ' አይገልጠውም፤ ተርገበገበ። ክሊንተን የአሜሪካ ፕሬዚደንት ሳይሆን አንድ ዓለማዊ የሱቅ ነጋዴ ወይም ደላላ ቢሆን ነገሩ ዜና ይሆን ነበር? አይሆንም። ግን ሆነ፤ ለምን? ይህ ሰው እላይ የወጣ ሰው ነው። ብዙ የሚጠበቅበት ሰው ነው። ምሳሌ እንዲሆን የሚጠበቅ ሰው ነው።

የእንግሊዙ ልዑል ቻርልስ ከካሚላ ጋር፥ ወይም ሚስቱ የነበረችው ልዕልት ዳያና ከዶዲ አልፋየድ ጋር ግንኙነት እንዳላቸው ሲታወቅ 'ተራገበ' አይገልጠውም፤ ተናፈሰ! ለነፋስ የተሰጠ ዱቄት ሆነ። ለምን? እነዚህ እላይ ያሉና ስማቸው የገነነ፥ ምሳሌነትም የሚጠበቅባቸው ሰዎች ናቸው።

ክርስቲያኖችም እንደዚህ ናቸው። ክርስቲያኖች የራሳቸው ስም ብቻ ሳይሆን የጌታቸው ስም የተጠራባቸው ሰዎችም ናቸው። የተጻፈ፥ የሚናገሩት፥ የሚያስተምሩት ቃል፥ የሚያውለበልቡት አርማ ያላቸው ሰዎች ናቸው። የግብረ ገብነት መለኪያው እላይ የተሰቀለ ሚዛን አላቸው፤ ይህ ሚዛን ሌሎችን የሚመዝኑበት ብቻ ሳይሆን ራሳቸውም የሚመዘኑበትም ነው። ይህ ካልሆነ ግብዝነት ነው። ጂም ቤከር ከጄሲካ ሃን ጋር ከተኛ በኋላ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ነው አገልግሎቱ ሁሉ፥ ሙሉ በሙሉ ወደ እንጦርጦስ፥ እርሱም ወደ ወህኒ የወረዱት።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዝሙት ወይም ስለ ማመንዘር ምን እንደሚል ቀደም ሲል በመጠነኛ ስፋት አይተናል። ይህ እዚህ በጽሑፍ የማካፍለው በቪድዮም የሰጠሁት ትምህርት ነውና ይህንን ያተመለከተ አንድ ወንድም፥ ወሲብና ዝሙት ልዩነት አላቸው ወይ? ምንድነው ልዩነታቸው የሚል ጥያቄ አቅርቦ ነበር። አጭሩ መልስ ወሲብ አጠቃላይ ወይም የወል ስሙ ሲሆን ዝሙትና ማመንዘር ግን ከክልሉ የወጣው ድርጊት ነው። ወሲብ በባልና ሚስት መካከል የሚደረግ ንጹሕ ግንኙነትም ነው። ወሲብ ስል ስሙን በጥቅል መናገሬ እንጂ ያካፈልኩት ዋናው ጉዳይ ስለ ዝሙትና

ምንዝርና ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ምንዝርና ሲናገር ከቶም አይኮላተፍም፤ አይንተባተብም፤ አያፍርም። ያመነዘሩ ሰዎችንም ምንም የተወደዱ ቢሆኑ እንኳ አይደብቃቸውም፤ ጉዳቸውንም አይደብቅላቸውም።

*ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።* 1ቆሮ. 6፥9-10

'አመንዝሮች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም' ነው የሚለው። ትምህርቱ ግልጽ ነው። ሲጀመር ከ10ቱ ትእዛዛት አንዱ፥ *አታመንዝር!* ነው፤ ዘጸ. 20፥14። አመንዝራ መሆን ወይም ማመንዘር ማለት በአጭር ቃል ያንቺ ባል ካልሆነ ወንድ፥ ወይም ያንተ ሚስት ካልሆነች ሴት ጋር በወሲባዊ ግንኙነት፥ በሩካቤ ሥጋ ውስጥ መሆን ነው። አጭሩና ግልጹ ትርጉም ይህ ነው። ማመንዘር ምን መሆኑን ጌታ ሲያስተምር ደግሞ አብራራው፤ *አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።* ማቴ. 5፥27-28። ሲያብራራው፤ እንዲያውም ከአካል ወደ ልብ ውስጥ ገባ። ይህንንም በመጠነኛ ስፋት ቀደም ሲል አይተነዋል።

ምሳ. 6፥30-33 *ሌባ በተራበ ጊዜ ነፍሱን ሊያጠግብ ቢሰርቅ ሰዎች አይንቁትም፤ ቢያዝም ሰባት እጥፍ ይከፍላል፥ በቤቱም ያለውን ሁሉ ይሰጣል። ከሴት ጋር የሚያመነዝር ግን አእምሮው የጐደለ ነው፤ እንዲሁም የሚያደርግ ነፍሱን ያጠፋል። ቍስልንና ውርደትን ያገኛል፥ ስድቡም አይደመሰስም።* ይላል።

ከላይ ወደጠቀስኩት ወደ ራቪ ዘካሪያስ ልመለስ። ራቪ የአገልግሎቱ ቢሮ በሚገኝባት አትላንታ አጠገብ የገዛቸው ሁለት እስፓዎች ነበሩት። እስፓ በዋናነት የማሳጅ ወይም መታሻ ቤት ነው። የማሳጅ ቤቶች ሁሉ ግብረ ወጥ ድርጊቶች የሚፈጸሙባቸው ናቸው ማለት አይደለም። የሚፈጸምባቸውም መኖራቸው ደግሞ የታወቀ ነው። አንድ እውቅ የምካቴ ክርስትና ሰው ለምን ከአንድም ሁለት እስፓ ገዝቶ ንግድ እንደሚሠራበት ለብዙዎች አልገባቸውም፤ ለኔም አልገባኝም። ይህን በመጀመሪያ እስካካፈልኩበት ጊዜ ድረስ ሦስት ሴቶች ናቸው ክስ የከፈቱበት። ከዚያ በፊትም አንድ የተከፈተና የተዘጋ ፋይል ነበረ። ሌሎችም እንደሚኖሩ ይገመታል።

ነገሩን እንግዳ ያደረገው ሰውየው ከሞተ በኋላ ጉዳዩ ከተደበቀበት መምጣቱ ነው። ይህ የተለመደ አይደለም። ይህን ያደረገው ሌላ ተራ ሰው ቢሆን ኖሮ ያደርጉት ነበር? አላውቅም። 'ይህ ውሸት ነው፤ አልሆነም፤ አልተደረገም፤' ብሎ ማለፍ ቢቻል መልካም ነበረ። ግን አይደለም። RZIM የተባለው አገልግሎቱ ጉዳዩን በግልጽ ተናግሮ ይቅርታ ጠይቆበት በሕግ ሂደቶችም በተጠያቂነት ተሳትፏል። ሰውየው በሕይወት ስለሌለ ስለ ራሱ መናገር ስለማይችል ክሱ ሲጀመርም ውድቅ መሆን ነበረበት ወይም አለበት ሊባል ይቻላል፤ ግን አልሆነም። ይህን የጠቀስኩት አንድ ነገር መደረጉ ነገሩን ወደ አለመደረግ እንደማይቀይረው ምስክር እንዲሆነን ነው። እንዳልኩት ሰውየው ራቪ

ሳይሆን ሌላ ሰው ቢሆን ኖሮ ያደርጉት ነበር? አላውቅም፤ ስገምተው አይመስለኝም፤ የሚያደርጉት አይመስለኝም።

እዚህ ላይ አንድ አራት ነጥቦችን በጥቂቱ ማለት እፈልጋለሁ፤

<u>አንደኛ፥ ክስን እንመርምር።</u> ማንም በማንም ላይ ክስ ሲከፍት ዝም ብለን ተቀብለን አናናፍስ። በተለኮሰ እሳት ላይ እንጨትና ቤንዚን ጨምረን ቋያ አናድርገው። የውሸት ክሶች ሊኖሩ እንደሚችሉ እንወቅ። ክስ መነሻው የእውነት ጉዳይ ቢሆንም እንኳ የውሸት ክስም ሊኖር ይችላል።

<u>ሁለተኛ፥ አንታወር።</u> በምንወዳቸው፥ በምናደንቃቸው፥ የታወቁ፥ የገነኑ፥ ስመ ጥር የሆኑ፥ ስማቸው የተጠራ ሰዎች፥ የኛ የምንላቸው ሰዎቻችን ላይ ክስ ሲከሰት እኛ ለነሱ ያለን የላቀ ግምትና አድናቆት፥ 'ውሸት ነው፤ ፈጽሞ ሊሆን አይችልም! እርሷ? አይወጣትም! እርሱ? አያደርግም!' ብለን ክሱን እንዳንቀበልና ለእውነታው እንድንታወር አያድርገን። አንዳንዴ ለመቀበል ስለሚከብደን ሽንጣችንን ገትረን መከራከር ብቻ ሳይሆን ይህንን ክስ የሚያቀርቡትን ሰዎች አጥብቀን ወደ መጥላትም እንደርሳለን። አንድረስ።

ይህ ከሆነ፥ በስሜት፥ 'ሊሆን አይችልም!' ብለን ከመዝጋት መስማት፥ ራስን ከመደለል መመርመር፥ መፈተሽ፥ መጠየቅ፥ ማረጋገጥ ተገቢ መሆኑን እናውቃለን። ለሰዎቻችን ያለን ጣዖታዊ አድናቆት እውነትን እንዳናይ መጋረጃ ሊሆን ይችላል። ይህ እንዲሆን አንፍቀድ። ያ ሰው ጓደኞችን፥ ወዳጃችን፥ ዘመዳችን ስለሆነ፥ ወይም ከሆነ፥ ለእርሱ ዘመድ ወይ ወዳጅ ነን፤ ጉዳዩ ግን ጉዳይ ነው። ጉዳዩ ዘመዳችን ወይም ጓደኛችን አይደለም። እናም፥ በጉዳዩ ላይ ወግነን አቋም አንያዝ። እርሱ ዘመዳችን ወይም ወዳጃችን እንደሆነው የተከሰሰበት ጉዳይ ወይም ካሳሹን ሰው ጠላታችን አድርገንም አይን።

<u>ሦስተኛ፥ ግር አይበለን፤ ግራ አይግባን።</u> ከዚህ 'ጣዖታዊ አድናቆት' ካልኩት ነገር ጋር የተቆራኘ ሌላ ነገር ደግሞ አለ። ያም፥ የምናደንቃቸው ሰዎች ወደቁ ማለት እምነታችንን ሊፈታተንና ሊገዳደር የሚችል ነገር ነው። ግራ መጋባት ውስጥ ልንገባ እንችላለን። ግራ መጋባትና ግር መሰኘት ብቻ ሳይሆን እኛም አብረን ልንወድቅም እንችላለን። እምነታችን የተፈተነ ብቻ ሳይሆን የተፈታም ሊሆን ይችላል፤ ሊጠፋብን ይችላል። 'እሱ እንዲህ ከሆነ፥ እሷ እንዲህ ካደረገች፥ ሁሉም ነገር ይቅርብኝ፥ የነሱ የሆነው ነገር ሁሉ ይቅርብኝ' ወደማለት እንወርዳለን። 'እኔን ወደ ጌታ ያመጣኝ ሰው፥ ያሳደገኝ ሰው፥ ምሳሌና ሞዴል የሆነችኝ ሴት፥ ደቀ መዝሙር ያደረገችኝ ሴት ከወደቁ ያ ሁሉ የነገሩኝ ነገር ውሸት ነበር ማለት ነው?' እንላለን። ግን ውሸት አይደለም።

ይህ ሲሆን ማወቅ ያለብን ነገር፥ በዚያ ሰው ሕይወት ወይም በዚያ ሰው አማካይነት የተደረገው ነገር ሁሉ በዜሮ ይባዛል ማለት አይደለም። ቀድሞ ያገለገላቸው መልካም ነገሮች በሙሉ ተለቅመውና ተሰብስበው ወደ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ መግባት አለባቸው ማለት አይደለም። ሰዎቹ ሰዎች ብቻ መሆናቸውንና እምነታችን በሰዎቹ ላይ አለመሆኑን ማወቅ አለብን። ሰዎቹ በቃሉ ይለካሉ እንጂ ቃሉ በሰዎቹ የማይለካ መሆኑ ይግባን። ሰዎቹ በክርስቶስ ይመዘናሉ እንጂ ክርስቶስ በሰዎቹ እንደማይመዘን

ይግባን። ሰዎቹ ግብዞች ሆኑ ማለት ክርስቶስ ያንን ነው ማለት አይደለም። ወይም አንድ ሰው እንደዚያ ሆነ ማለት ክርስቲያኖች ሁሉ እንደዚያ ናቸው ማለትም አይደለም።

እግዚአብሔር በነዚህ ሰዎች የተደረገውን ነገር ቀጥሎም፥ እነርሱ በስፍራቸው ባይኖሩም፥ ሳይኖሩም ሊገለገልበት ይችላል። መዝሙሮቻቸው ደግመው ሊያንጹን፥ መጽሐፎቻቸው ደግመው ሊያስተምሩን፥ ስብከቶቻቸው ደግመው ሊያነቃቁን ይችላሉ። መውደቃቸውን ካላወቅን ደግሞ መዝሙሩንም፥ ትምህርቱንም፥ ስብከቱንም ያለ ምንም ጥያቄ ነው የምሳተፈው። እና በዚያ ሰው ሕይወት ወይም በዚያ ሰው አማካይነት የተደረገው ነገር ሁሉ በዜሮ አይባዛም።

<u>አራተኛ፥ እና የመጨረሻው፥ እንጠንቀቅ።</u> ይህ ነገር ለሁላችንም ትምህርትና ማስጠንቀቂያ ሊሆነን የተገባ መሆኑን ማስመር አለብን። በተለይ በሥልጣን ላይ፥ በወንበር ላይ፥ በትልልቅ የማስተማሪያ መድረክ፥ በቤተ ክርስቲያን ጉባኤም ይሁን በማኅበራዊና ሕዝባዊ ስርጭቶች የምንገኝ ማናችንም ብረት ለበሶች አለመሆናችንን ማወቅ አለብን። የቆምን እና የምንቆም ብቻ እንጂ ከቶም የማንወድቅ አዕማድ አድርገን ራሳችንን አናስብ። ፈተናዎች ዓይነታቸው ብዙ ነው፤ እኔ በዚህ አልወድቅም፤ እኔ ይህ አይነካኝም፤ ይህ የማይታሰብ ነው፤ ብለን አንኩራራ። በአንድ ፈተና ባን ፈተንና ብንፈተንም በአብረቅራቂ ውጤት ብናልፍ በሌላው ከዜሮ በታችም የናመጣ ልንሆን እንችላለን፤ ወይም ሆነን እንገኛለን። ራሳችንን እንፈትሽ፤ ተጠያቂ ከመሆን አንሸሽ፤ ለቤተ ክርስቲያን ሰዎቻችን፥ ለመሪዎች፥ ለጓደኞች ክፍት እንሁን፤ አንታበይ፤ ታዋቂነታችን አናታችን ላይ ወጥቶ አያስክረን። ምንም የማንሆን አይምሰለን፤ እንጠንቀቅ፤ በጸሎት የምንሸፈን የምንከደን እንሁን። መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎቻችን ቡትቱ ያልሆኑ፥ ያልተቀደዱ፥ ያልተቦጨቁ መሆናቸውን አስረግጠን እንፈትሽ፤ አሳምረን እንልበስ። ስንወድቅ ይዘናቸው የምንወድቃቸው ሰዎች መኖራቸውን አንርሳ። ፍጹማን ሰዎች አለመሆናችንን አውቀን በሚያድጥ መንገድ ላይ በድፍረት አንራመድ። እንጠንቀቅ።

## ወሲባዊ ትንኮሳና ጥቃቶች እውነት ናቸው።

ይህን ካልኩ በኋላ፥ ቀደም ሲል፥ 'ወደኔ ከመጡት ጥቂት ያልሆኑ ስሞታዎች መካከል አንዱን አቀርባለሁ። ብዬ ነበር። ጥቂት አይደሉም፤ ከጥቂት በላይ ናቸው። ሁሉም ከፉ ናቸው፤ አንዳንዶቹ ከሌሎቹ ይከፋሉ። ሁሉም ለመናገር አይመቹም። አንዱን ግን አቀርባለሁ። ይህኛው የማቀርበው ጉዳይ ይህ ሰው በዚህ አኗኗሩ እየተደሰተበትም እያገለገለም ስለኖረበትና ስለሚኖር ነው። ቀደም ሲል፥ 'መውደቅና ወድቆ መነሣት አንድ ነገር ሆኖ፥ እዚያ ውስጥ መኖር እና፥ መኖር ብቻ ሳይሆን በዚያ እየተደሰቱ መኖር ደግሞ ሌላ ነገር ነው' ብያለሁ። ደግሞም ያለ ምንም የሕሊና ጥዝጠዛ ሁለቱንም በደባልነት ማኖር፥ እንደ ምናምንቴዎቹ እንደ ዔሊ ልጆች ሁለቱንም አብሮ ማካሄድን የሚያካሂዱ ሰዎች አሉ።

በመጀመሪያ ስለ ሂደቱ ልናገር።

1ኛ እርምጃ፤ በዚህ ሰው ፆታዊ ወይም ወሲባዊ ትንኮሳ የተቸገሩ ሴቶች (በቁጥር ብዙ ናቸው) ጉዳዩን ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሳያውቁ ለብዙ ጊዜ ቆዩ። ይህ ተንኳሽ ሰው የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱ በመካከለኛው ምሥራቅ የምትገኝ ቤተ ክርስቲያን ናት። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ነው የወንዶች ቁጥር እየበረከተ የመጣው እንጂ ወደ ዐረብ አገር የሚሄዱ ብዙ ወገኖቻችን እንደሚታወቀው ሴቶች ናቸው። ይህች ቤተ ክርስቲያንም ስትጀመር 100% በሴቶች የተሠራች፥ ስታድግም ከ90% በላይ በሴቶች የተቀናጀች ቤተ ክርስቲያን ናት። ይህቺ ቤተ ክርስቲያን በቤይሩት የምትገኘው፥ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያኖች ኅብረት (ወይም የኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ኅብረት በቤይሩት ሊባኖስ) የምትባለው ቤተ ክርስቲያን ወይም ኅብረት ስትሆን መጋቢዋ ኤልያስ ገብሬ ይባላል።

ይህ ጉዳይ ያሳሰባቸው ጥቂቶቹ እኅቶች ከፊት መንሳት እስከ ማስጠንቀቂያ፥ እስከ አትድረሱ ድረስም ተነገራቸው። ይህ በነጠላ የተደረገ ሙከራ ማን ተጠቂ፥ ማን ሰለባ የሆነበት ሁኔታ ያልታወቀበት የተናጠል ሙከራ ነው።

2ኛ እርምጃ፤ እነዚህ እኅቶች ይህንን ሰው መጋቢ አድርጎ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ወደሾመው ሰው ስሞታ አቀረቡ። ያቺን ቤተ ክርስቲያን የተከሉት በጣም ጥቂት፥ ስድስት ወይ ሰባት ወገኖች ሲሆኑ ይህንን መጋቢ የሾመላቸው ሰው ቤተ ክርስቲያኒቱ ከተተከለችበት ቀጥሎ ባሉት በቀጣዮቹ በርካታ ዓመታት እየሄደ ይጎበኛቸውና ያስተምራቸው የነበረ እውቅና የተመሰገነ አገልጋይ ነው። ለብዙ ዓመታት ባለመታከት እየተመላለሰ ካገለገላቸው በኋላ ነው ይህንን ሰው መጋቢ አድርጎ የሾመላቸው። ቤተ ክርስቲያኒቱ ከተመሠረተች አሁን 25 ዓመት አልፏታል። እነዚህ እኅቶች ስሞታውን ያቀረቡለት አገልጋይ ብዙዎቻችን ወይም ምናልባት ሁላችንም የምናውቀው ዶ/ር መለሰ ወጉ ነው። ዶ/ር መለሰ ከመጋቢው ጋር የቅርብ ዘምድናም አለው፤ አጎቱ ነው። ይህ ዝምድና ጫና ሊፈጥር እንደሚችልም መገመት ይቻላል። ስሞታው ቢቀርብም ዶ/ር መለሰ ስሞታውን የውሸት ክስና የስም ማጥፋት ዘመቻ ነው ብሎ አልተቀበላቸውም፤ ሊቀበላቸውም አልፈለገም። እነዚህ እኅቶች በዚህ አዝነው ተዉት።

3ኛ እርምጃ፤ ዶ/ር መለሰ ወጉ ሳይቀበላቸው ሲቀር ጣልያን አገር ኮሞ ውስጥ የሚኖር አንድ የሚያውቁት አገልጋይ ዘንድ ጉዳዩን ያቀርቡለታል። ወንድም ለገሠ ይልማ ይባላል። ይህ ወንድም መጋቢ ኤልያስ ገብሬን ኢትዮጵያም ሳለ ያውቀዋል። ሲያውቀውም እውቂያ ብቻ ሳይሆን ኋላ የተቆራኘው ወሲባዊ ችግርም ያኔም ጭምር እንደነበረ የሚያውቅ ወንድም ነው። እንዲያውም ወደ ቤይሩት እንደሚመጣ ሲያውቅ

ሊጠብቀው የሚችለውን ፈተና ከሚገኝበት ችግር አንጻር በግልጽ ነግሮታል። እነዚህ እኅቶች ይህንን ጉዳይ ለወንድም ለገሠ አቀረቡ።

4ኛ እርምጃ፤ ጉዳዩን በመጀመሪያ አንዲት እኅትና ጓደኛዋ፤ በዚያኑ ሰሞን ደግሞ ሌላ እኅት፥ ሁሉም ከዚያችው ቤተ ክርስቲያን የሚገኙና የነበሩ ለኔም አዋዩኝ። ከኔ ጋር ምንም እውቂያ አልነበረንም። በዚያ ሰሞ የቲቶን መልእክት ለቤተ ክርስቲያናችን ወጣቶች አስተምር ነበር። የማስተምረውን ለካ ጥቂት ያልሆኑት በቤይሩት የሚገኙ ወገኖች ይከታተሉ ነበር። በዚያ ትምህርት ውስጥ፥ 'ሴቶች ሽማግሌዎች መሆን ይችላሉ ወይስ አይችሉም?' የሚለው ጥያቄ ተነሥቶ ያንን ስመልስ፥ በሴቶች ብቻ ስለሚመሠረቱ ቤተ ክርስቲያኖች ምሳሌ ስሰጥ ስለ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ጠቅሼ ነበር። ቤይሩት አላልኩም፤ ግን በእርግጥም ስለ ቤይሩት ቤተ ክርስቲያን ነበር ምሳሌው። ምሳሌውን የሰማሁትም አንድ ቀን ከዶ/ር መለሰ ጋር በስልክ ስናወራ የነገረኝ ታሪክ ነው። ያቺን ቤተ ክርስቲያንም ከላይ እንዳልኩት ከታናሽነቷ ጀምሮ በትምህርትም፥ በምክርም ያገለግላት ስለነበር እርሱው ያካፈለኝ ገጠመኝ ነው። እና በቲቶ ጥያቄ መልስ ውስጥ ያንን ሳወሳ፤ ስለነሱ የምናገርና የማውቃቸው መስሎ ስለተሰማቸው ነው ጉዳዩን ወደኔ ሊያቀርቡ አሰቡ። ሁለቱም ምንም ሳይነጋገሩና ሳይመካከሩ በየራሳቸው መንገድ ጉዳዩን አካፈሉኝ።

በመጻጻፋችን ሂደት ውስጥ በመጀመሪያ ስለማይመለከተኝ ልተወውና፥ ግን ማድረግ ያለባቸውን ነገሮች በቅደም ተከተል ልነግራቸው አሰብኩ፤ ነገርኳቸውም፤ በጽሑፍ ብቻ ሳይሆን በስልክም አወራን። 'ተገናኙ፤ ጸልዩ፥ ለሽማግሌዎች ጉዳዩን ንገሩ፤ ለዶ/ር መለሰ አሳውቁ፤ ከዚያ ለመጋቢው በቀጥታ ይነገረውና ከአገልግሎቱ ይረፍ፤ ራሱን ይጎብኝ፤ ይህንን ደግሞ ሽማግሌዎች ያድርጉት፤' አልኳቸው። ተስፋ በማድረግ እንጂ፥ እንደዚህ ያሉ መጋቢዎች ሽማግሌ እንደማይኖራቸውና ቢኖሩም እነሱ በጣታቸው ለቅመው የሚያስቀምጧቸው ሎሌዎች መሆናቸውን ረስቼው አይደለም።

ይህ ጉዳይ ወደዚህ ሰውም፥ ለዚያ ሰው አገልግሎቱን ወዳሸከመው ባለ አደራ ሰውም ቀርቦ ምንም ምላሽ ያላገኘ ጉዳይ እንደሆነ ሲነግሩኝና ስለ ወንድም ለገሠም ሲነግሩኝ፥ ከወንድም ለገሠ ጋር እንዲያስተዋውቁኝ ነገርኳቸው።

5ኛ እርምጃ፤ ከወንድም ለገሠ ይልማ ጋር ተዋወቅን። ከለገሠ ጋር ማንን ማንን በቅደም ተከተል ማግኘት እንዳለብን ዕቅድ ነደፍን። በመጀመሪያ ከዶ/ር መለሰ ልንጀምር ተስማማንና ዶ/ር መለሰን አገኘነው። በኮንፈረንስ ስልክ፤ ለገሠ ከጣሊያን እኔና ዶ/ር መለሰ ከአሜሪካ። ዶ/ር መለሰ በመጀመሪያ ያቀረበልን ጥያቄ፥ 'ምንድነው ማስረጃችሁ?' ነው። ተገቢ ጥያቄ ነው። እጅ ከፍንጅ የተያዘበትን ማስረጃ ማቅረብ አንችልም፤ ቀደም ሲል ስለ ወሲብ ሳካፍል ይህ ምስጢራዊ ግንኙነት በድርብ ካብ የሚታጠርና የሚጠበቅ ምስጢር መሆኑንም ተናግሬ ነበር። ምንም ነገር እጅ ከፍንጅ ማቅረብ አንችልም። ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሲያደርጉ የተቀረጸ ቪድዮ ማቅረብም አንችልም።

"ነገር ግን ልናቀርባቸው የምንችላቸው የድምጽና የተጻጻፏቸው ነገሮች አሉ። እነዚያም ከእርሱ ወገን ብዙዎቹ ተሰርዘዋል፤ ግን ከመሰረዛቸው በፊት screen shot የተደረጉ አሉ፤ እነዚህ ኤግዚቢቶች ናቸው፤ እነዚህን ምስክር አድርገን መጥራት እንችላለን፤" አለን። ሁለተኛ፥ "አሁን እዚህ እየተነጋገርን እያለንም በአራተኛ መስመር ተራ በተራ የቃል ምስክርነት የሚያቀርቡ ፈቃደኛ እኅቶች አሉ፤ እነሱን ማቅረብ እንችላለን። እነዚህ ደግሞ የአካል ምስክሮች ወይም material witnesses ናቸው።" አለን። ይህ እኛ ያልነው ነገር ቀድሞ እነዚያ እኅቶችም ያሉት ነገር ነው።

አሳዛኙ ነገር፥ ዶ/ር መለሰ አሳባችንን ሊቀበልና ምስክሮቹን ሊፈትሽ ፈቃደኛ አልሆነም። 'ስም ለማጥፋት የተደረገ ዘመቻ ነው እንጂ ሌላ አይደለም' ብሎን በሌላ ጊዜ ልንገናኝ ተስማምተን ተለያየን። በቀጣዩ ሳምንት ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ተገናኘን፤ ሁለተኛውም ውይይት በዚያው በመጀመሪያው መልክ ውጤት አልባ ሆኖ ተደመደመ። ይህ የሆነው በNovember 2020 ነው። አሳባችንና ምኞታችን እንደ አገትም፥ እንደ ሺሚም፥ እንደ በሳልና የተከበረ አገልጋይም ከምክርና ተግሳጽ እስከ ከአገልግሎት መታገድ ድረስ ይሄዳል የሚል ነበር። አልሆነም።

6ኛ እርምጃ፤ ከሳምንት በኋላ በዚያው ወር፥ በNovember 2020 ከቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ከኤልያስ ገብሬ ጋር ለመገናኘት ቀጠሮ ያዝኩ። የደወልኩት እኔ ነኝ። ከመደወሌ በፊት በዋትሳፕ በጽሑፍ አሳብ ተለዋውጠን ቀጠሮ ይዘን ነው። ስደውል ዋትሳፕ ሦስተኛ ሰው መኖሩን ይነግረዋል። ማን መሆኑን እሱም ሳይጠይቀኝ እኔም ሳልነግረው መነጋገራችንን ቀጠልን። የሰማኋቸውን ስሞታዎች በመንገር ጀመርኩና በዚያ ጉዳይ የሚለው ነገር ከኖረው ጠየቅሁት።

በመጀመሪያ እነማን መሆናቸውን ነው ለማወቅ የፈለገው። ያ በሂደት የሚታወቅ ስለሆነ አሁን በጉዳዩ እውነታ ላይ እንድንነጋገር ጠየቅሁት። ጉዳዩ ወይም ክሱ ከኖረ ማንነታቸውን እርሱ ራሱም ስለሚያውቃቸው መጠየቅም አስፈላጊ አይደለም። ደግሞም ብዙ መሆናቸውንም በግልጽ ነግሬዋለሁ። በአንድ ወገን ምንም ነገር እንደሌለ ሲናገር፥ በሌላ ወገን እርሱ ኢትዮጵያ ሳለ የተመሠረተና ውድቅ የተደረገ ክስ እንደነበረ ነገረን። ክሱን ውድቅ ያደረጉትም ሽማግሌዎች መርምረው እንደሆነና በንግግራችን ውስጥ ሽማግሌዎችንም እንድጠይቅና ቁጥራቸውንም እንደሚሰጠኝ ነገረኝ። በዚህ ተስማምተን የሽማግሌዎቹን ቁጥር ስጠይው የከሳሾቹን ስም ዝርዝር ካልሰጠሁት ቁጥራቸውን እንደማይሰጠኝ በግልጽ አስረዳኝ።

ወደ 45 ደቂቃ ያህል ካወራን በኋላ ወደ የትም ፈቀቅ እንዳላልን ሲገባኝ በሦስተኛው መስመር ያለው ሰው ለገሠ ይልማ መሆኑን እና እርሱ እንዲናገር መስመሩን ለሱ እንደምተው ነገርኩት። ለገሠ ገና ሊናገር ሲል ወዲያውኑ ኤልያስ መስመሩን ዘጋውና ከእርሱ በኩል ያለው መስመር ተቋረጠ። ከዚያ በኋላ በጽሑፍ እንዲህ ብሎ ጻፈልኝ፤

'ተቋርጦ ነው ይቅርታ። አክብሬህ ሀሳቤን ሰጥቼሃለሁ። ማውራት ምፈልገው ለጊዜው ከአንተ ጋራ ነው።'

በተጨማሪ ጽሑፍ፥ 'በተጨማሪ የሰዎቹን ስም ዝርዝር ብትልክልኝ በጣም ጥሩ ነው እዚህ ከመሪዎች ጋራ መነጋገር ይችላሉ። አመሰግናለሁ።' በማለት ነበር የጻፈው።

ሁለቱም አሳቦች ግልጽ ናቸው፤ አንደኛ ከኔ ብቻ ጋር ነው ማውራት የፈለገው፤ እኔ ደግሞ፥ ምንም እንኳ የምንነጋገረውን ነገር መቅረጽ ብችልም፥ ለብቻዬ ላወራው አልፈለግሁም፤ ከኔ ይልቅ፥ ከኔ ቀድሞ ከሚያውቀው ሰው ጋር ነው ላወራው የፈለግሁት። ለገሠ ቀድሞ የሚያውቀው ወንድም ነው። ባያውቀውም እንኳ፥ በምናወራው ጉዳይ ምስክር እንዲኖር አስፈላጊ ነው። ሁለተኛ የእኅቶቻችንን ስም ዝርዝር (ዝርዝር የሚለው ይሰመርበት) ላክልኝና ከመሪዎች ጋር መነጋገር ይችላሉ ነው ያለው። ከኔ የሚፈልገው ዝርዝር ነው። እነሱን የሚያገኙትም የማላውቃቸው ሰዎች ናቸው። ሰዎቹን ሊያገናኘኝ ወይም ቁጥራቸውን ሊሰጠኝ ቃል የገባው ውሸት ነበረ። ለቀጣይ የቡድን ውይይት መስመሩ የተዘጋ መሰለ። 'እነሱና ሽማግሌዎች መጨረስ ይችላሉ' ዓይነት ነገር ነው።

በጽሑፍ ግን በዚያው ቀንና በማግሥቱ ጥቂት ቀጠልን። ከላይ የጻፈውን ከጻፈ በኋላ እኔ የጻፍኩለት ይህ ነበር፥

> 'የእኅቶቻችንን ስም ዝርዝር ከመላክ ይልቅ ከራሳቸው ከእኅቶቻችን ጋር በድምጽ ብንነጋገርስ ምን ይመስልሃል? ይህ ከድምጽና ከቴክስቶች ይልቅ እኅቶቻችን ሕያው ምስክር ናቸው። ቅድም እንድንነጋገር የጋበዝኩት ወንድም ከቀድሞም የምትተዋወቁት ወንድም ለገሠ ነው። ከእርሱ ጋር ሆነን ጥቂት እኅቶችን ሦስተኛ መስመር በየተራ በማስገባት ብንነጋገር ይህ ትክክለኛ አካሄድ ይመስለኛል። እንዲህ መነጋገር እንችላለን?
>
> ለገሠን ያስገባሁት ጉዳዩን ከኔ በፊትም የሚያውቀውና ካንተም ጋር ከቀድሞም ስለምትተዋወቁ ነው። ዶ/ር መለሰንም ያነጋገርነው ከእርሱ ጋር ሆነን ነበር። ከኔ ይልቅ ለዚህ ጉዳይ ቅርብ የሆነው እርሱ ስለሆነ እርሱ መግባቱ አስፈላጊ ነው።'

በማለት ነበር። ከዚህ በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ የጻፈልኝ የሚከተለው ነው፤

> 'ከይቅርታ ጋራ የደወልክልኝ አንተ ነህ እናም የነገርከኝም አንተ ነህ። ለትክክለኛ አካሄድ የልጆቹን ስም ምን እንደተደረጉ ከግልጽ ማስረጃ ጋራ ብትነግረኝ መልካም ነው። እናም ልክ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንደ ቤተክርስቲያን እዚሁ መሪዎች አሉ ከእነርሱ ጋራ ተነጋግረው ባለው አካሄድ መሄዱ የተሻለ ነው። ምክኒያቱም በእርቀት ሳይሆን እኔም ሀሳቤን ለመሪዎች በመግለጥ መነጋገር እንችላለን። እኔም ስማቸውን ስትልክልኝ አለኝ የምለውን ማስረጃ እልክልሃለሁ። ከዚህ በተጨማሪ መሪዎችም ስላሉ ያነጋግሩሃል ስልክህን እሰጣቸዋለሁ። ከዚህ ባለፈ ሁሉንም ለጌታና ለህሊና ፍርድ እተወዋለሁ።
>
> እናም እዚህ ያሉ መሪዎች በሚወስኑትና ውሳኔ እስማማለሁ በህብረቱ ላይ ለሚፈጠረው ማንኛውም ችግር ኃላፊነት ስለሚወስዱ ማለት ነው። ከአንተ ጋራም ሆነ በእርቀት ላይ ካሉት ጋራ ያደረኩትም ሆነ የማደርገው ምናልባት እዚህ ላለው የእግዚአብሔር ስራ ኃላፊነት ለመውሰድም የሚያስችል ስላልሆነ ማለቴ ነው። በተረፈ ወንድሜ የጌታ ቀን በቅርቡ እንደሚመጣና ከዚህ እንደ እሳት ከሚለበልብ አካባቢ ጌታ መንገዱን እንደሚያዘጋጅ አምናለሁ። በሚያቃጥል ችግሮችም ውስጥ እያለፍኩ ይህንን ትልቅ ኃላፊነት የሚቀበል እስኪመጣ እታገሳለሁ፣ አንተም ሆነ ለዚህ ትልቅ የእህቶች አገልግሎት የምታስቡ ሁሉ እንደምትጸልዩ ተስፋ አደርጋለሁ። ወደፊት ደግሞ በተሻለ ሁኔታ እንተዋወቃለን ብዬ አስባለሁ። ይህንን የጻፍኩልህን እዚህ ላሉ መሪዎች ልኬዋለሁ።'

ለዚህ ምላሽ የጻፍኩለት የመጨረሻው ጽሑፌና ከዚያ ቀጥሎ ምንም መልስ ያልመለሰልኝ ይህ ነበር፤

> 'እርግጥ ነው የደወልኩልህ እኔ ልሁን እንጂ የደወልነው ከለገሥ ጋር ነው። አሁንም ስንደውል አብረን ልንደውል ነው የምናስበው።
>
> የኛ አሳብ አንተን ማግኘትና ክርስቲያናዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ መንገድ ከአንድ መጋቢ (ከአንተ) የማይጠበቁ ፆታዊና ወሲባዊ ትንኮሳዎች ደረሱብን ካሉ እኅቶች ጋር እንድንነጋገር ነው። እነዚህ እኅቶች በቁጥር ጥቂት አይደሉም።
>
> አንተ ስማቸውን በዝርዝር እንድሰጥህ ነው የጠየቅኸኝ። ነገር ግን ከስማቸው በላይ ራሳቸውንም በድምጽ በስልክ ልናቀርባቸው ስለሚቻል ሲቀርቡ የምታውቃቸው ስለሚሆን አስቀድሞ መስጠቱ አስፈላጊ አይደለም። ስማቸውን ሳልሰጥህ የቤተ ክርስቲያኒቱን (የኅብረቱን) መሪዎች ቁጥር እንደማትሰጠኝ ነግረኸኛል። ባትሰጠኝም መልካም ነው፤ በስልክ እስከተገናኘን ድረስ። ፈቃደኛ ከሆንክ በስልክ በምንነጋገርበት ጊዜ ከመሪዎች ጋርም ብትሆን ደስ ይለናል።'

ይህንን ከጻፍኩለት በኋላ አልመለሰልኝም። አልተገናኘንም። በመስመራችን እስካሁን ድረስ ያለው ይህ የመጨረሻው ጽሑፍ ነው።

ከዚህ በኋላ መንገዱ የታጠረ ነበር። እኔንም ለገሥንም ያገኙን እና ገጠመኞቻቸውን ያካፈሉን በድምጽም ምስክርነታቸውን የሰጡን በጠቅላላ አሥር እኅቶች ናቸው። በቁጥር ከነሱ የሚበልጡ ደግሞ ጉዳዩ ምንም መፍትሔ እንደማይኖረው ስለገመቱ ለመናገር ያልፈለጉ አሉ።

ይህ ጉዳይ የአገልግሎት ብቻ አይደለም የትዳርም ጉዳይ ነው። ይህ ሰው ሳያገባ ብዙ ዓመታት እያገለገለ የቆየ ቢሆንም በመካከል ትዳር መሥርቶአል። ከመሠረተ በኋላም ባለቤቱ አገር ቤት እርሱ ቤይሩት ነው የሚኖሩት። ይህም ሌላ ራሱን የቻለ የችግር ፍግኝ ማፍያ ነው። መፍትሔ በመፍጠር ፈንታ ችግሩን ያደመቀና ያሰፋ ችግር ነው። የሰማናቸው ችግሮችም ከዚያ በፊትም፥ ከዚያ በኋላም የተከሰቱ መሆናቸው ጋብቻ ከዝሙት ለመራቅ ዋስትና አለመሆኑንም ይመሰክራል።

7ኛና የመጨረሻው እርምጃ፤ ይህ ጉዳይ ከላይ እንዳልኩት ትዳር ያለበት በመሆኑ ወደ አደባባይ ሲወጣ ባለቤቱም ልትሰማው የምትችለው ጉዳይ ስለሆነ፥ ይህ ከመሆኑ በፊት እርሷም እንድትሰማው ተደርጓል። የሂደቱ ዝርዝር አስፈላጊ አይመስለኝም።

እነዚህ ሰባት እርምጃዎች የተሄዱትና፥ ይህ ሁሉ ሲሆን አሳባችን ይህ ሰው አገልግሎቱን አቁሞ ራሱን እንዲያይ፥ የተጎዱትን ይቅርታ እንዲጠይቅ፥ ወደ መንፈሳዊ መታደስ እንዲመጣ ነበር። አልሆነም። አገልግሎት እንዲያቆም አድራጊዎቹ እኛ አይደለንም። እኛ ግን እራሱ ፈጥኖ ራሱን ቢያይ መልካም ነው በማለት ነው ይህንን መንገድ የሄድነው። ቢያይ እዚያ ላይ ያበቃ ነበር። ካልሆነ ደግሞ ጉዳዩ በመስመር ወደሚመለከታቸው እንዲሄድ ነበር፤ ከዶ/ር መለሰ ጀመርን፤ እዚያም ሊያልቅ ይችል ነበር። እዚያም አላለቀም። 'ሽማግሌዎች' ካላቸው ሰዎች ጋር በስልክ ለመነጋገርም

ተመኝተን ነበር፤ ያም አልተሳካም፤ ቁጥራቸውን ሊሰጠኝ ቃል ገብቶ ሊያደርገው አልፈለገም። ምኑም አልሠራልንም።

ጉዳዩ ዝም ተብሎ ከተተወ የተተወ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ጉዳትም ሆኖ የሚቀጥል ነው። ምክንያቱም አገልግሎቱ አልቆመም። ችግሩም ቀጣይ ነው፤ ገናም ሊቀጥል ይችላል። መነገሩ ወይም ጉዳዩን ወደ አደባባይ ማውጣቱም ችግሩ መፍትሔ እንዲያገኝ ዋስትና አይሰጥም። ግን መፍትሔ አይሰጥምና ይቅር ብሎ መተውም አይቻልም። ስለዚህ ከሁለቱ አማራጮች ሁለተኛው አማራጭ አድበስብሶ ከመተው ይልቅ ችግሩን ወደ አደባባይ ማውጣት የተሻለ መሆኑን በጉዳዩ ሂደት ውስጥ ያለፍን ወገኖች አምነንበታል። ያ ሰው ባይመለስ እንኳ የማስጠንቀቂያ ደወል መደወል፥ ፊሽካ መንፋት ተገቢ መስሎ ታይቶናል። ይህንን ጉዳይ ከኔ ይልቅ ሌሎች ሰፋ ያለ ተደራሽነት ያላቸው ሁለት ወንድሞች እንዲያወጡት ታስቦ ነበር። ከሁለቱ አንዱ ጀምሮትም ነበር። ጉዳዩ ግን በጣም ስስ ጉዳይ ነውና ራሴው በያዝኩበት ልጨርሰው ሆነ። ነገሩንም በዩቲዩብ አካፈልኩት።

ይህ ነገር ለሌሎችም ማስጠንቀቂያና ማስተማሪያ ሊሆን ይችላል? አላውቅም። ከሆነ እሰይ። ካልሆነም እንዲህ ያለ ነገር በቤተ ክርስቲያንም እንደሚደረግ ገመናችንን በትንሹ መግለጥ አስፈላጊ ይመስለኛል። ለምን ቢባል ሕመማችንን ደብቀን መድኃኒት ሳናገኝ የምንኖር ሰዎች ሆነን መቀጠል የለብንም።

ተራ የቤተ ክርስቲያን አባላት ሲያጠፉ መሪዎች ይቀጣሉ። መሪዎችና መጋቢዎች ሲያጠፉስ? ጉዳዩ ከሥልጣን ጋር የተያያዘ ሲሆንና ስለ ወንበር ወይም ሥልጣን ስንመለከት እንዳየነው የሥልጣን መባለግ ያለበት ጉዳይ ከሆነስ? እንዲህ ያለው ጎጂ ሰው እነዚህን ሴቶች የሚያጠቃው መንፈሳዊ ሥልጣኑን በመጠቀምም ከሆነስ? ጉዳቱ ደግሞ ወሲባዊ ከሆነና ከቤተ ክርስቲያን አካል ውስጥ በጣም ደካማው ክፍል ብቻውን የሚጎዳበት ከሆነስ? ይህ ፊሽካ መነፋት የተገባው ጉዳይ ነው።

ይህ ጉዳይ ብዙ ጊዜ ከምጽፍበትና ከማስተምርበት ከምካቴ ክርስትና ጋር እንዴት ይገናኛል? ለምን በዚህ ጉዳይ እንደዚህ መናገር አስፈለገኝ? ለመሆኑ ይገናኛል? አዎን፤ ይገናኛል። እንዴት እንደሚገናኝ ጥቂት ነጥቦችን ላሳይ፤

አንደኛ፥ ቀጥተኛ ትምህርትና ቀጥተኛ ተግባር እጅ ለእጅ የተያያዙ ናቸው። ተግባራዊ ቅድስና የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ውጤት ነው። ተግባራዊ ቅድስና ከክርስቶስ ጋር ካለን ግንኙነት ሞልቶ የሚፈስስ ጅረት ነው። ርኵሰት ከኖረ የተበላሸ ትምህርት አለ ማለት ነው። ወይም ከክርስቶስ ጋር ግንኙነት የለም ማለት ነው።

ሁለተኛ፥ የሥልጣን መባለግ ባለበት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተዳደር የለም ማለት ነው። የቡድን አመራርና ተጠያቂነት በሌለበት ውኃውን የሚያደፈርሱና የሚያጨቀዩ፥ ሃይ ባይ የሌላቸው እረኞች አሉ ማለት ነው። የቆሸሸ ውኃ የሚጠጡ በጎች ደግሞ አሉ ማለት ነው። የቆሸሸ ውኃ መጠጣት ደግሞ ደዌ አለበት።

ሦስተኛ፥ ሥጋዊነት ከኖረ ቆሮንቶሳዊነት አለ ማለት ነው። ይህ የአለማደግ ችግር፥ የመቀጨጭ፥ የመቀንጨር ችግር ብቻ ሳይሆን የአለመዳን ሁኔታም ሊኖር እንደሚችል

ጠቃሚ ነው። በኃጢአት እየተደሰተ የሚኖር ማንነት ባለበት በዚያ፥ መሠረቱ የተናጋ ቤት አለ ማለት ነው። በዓለቱ ላይ አለመመሥረት አለ ማለት ነው። ሳይድኑ የዳኑ የመሰሉ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ አገልጋዮችም አሉ ማለት ነው። ፍጥረታውያንም ሥጋውያን መስለው ከመንፈሳውያን ጋር የሚገኙበት፥ ስንዴና እንክርዳድ አብረው የሚበቅሉበትና የሚያድጉበት ሁኔታ አለ ማለት ነው።

አራተኛ፥ የሐሰት ትምህርቶች ሥጋዊነትን ያደፋፍራሉ፤ በሥጋ የምናደርገው ኃጢአት ነፍሳችንን እና መንፈሳችንን አይነካትም የሚሉ መናፍቃን አሉ፤ 'ሰው መንፈስ ነው' የሚሉ መናፍቃን ይህንን ሲሉ ከሥጋ አርነት ጋር የተቆራኘ ተግባራዊ ስሕተትም ነው እያስተማሩ ያሉት። አርነታችን ለሥጋ ምክንያትን መስጠት የለበትም።

ወደ ጉዳዩ ልመለስና ልደምድመው። ከነዚህ እኅቶች መካከል አንዳንዶቹ ጌታን ያገኙት እዚያው ቤይሩት ነው። አንዷ እኅት ከጥንቆላ ቤተ ሰብ ውስጥ ነው ወደ ድነት የመጣችው። ይህ ወሲባዊ የትንኮሳ ብቻ ሳይሆን የሩካቤ ሥጋ ነገር በጣም ግር ብሏት ነበር። ከጥንቆላ ቤት ነው የመጣችው፤ በጥንቆላ ቤትም የማይደረግ ነገር እዚህ ሲፈጸምባት ለቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች የተለየ መብት እንዳላቸው አድርጋ ቆጥራው ተቀብላው ነበር። እዚያ በነበረችበት ጠንቋዩ ወይም 'አዋቂው' የፈለገውን እንደሚያደርግ ማለት ነው። እንዲያውም እዚያ ወንድ የማያውቁ ደናግል እየተመረጡ ነው ወደ ጠንቋዩ ካዳሚነት የሚቀርቡት። ይደንቃል፤ እንዲህ ያለውን አሳብ ራሱን እንድታስተናግደው ተደርጋለች። ይህች እኅት አሁን የተረዳችና ያወቀች እኅት ናት። የተጓዘችበት መንገድ ግን ጎጂ ነበር። የጉዳት ጉዞ።

ሌላዋ እኅት ካላቸው የቀረበ ግንኙነት የተነሣ ሊያገባት እንደሆነ ትጠብቅና ትጠባበቅ ነበር። በዚህ መካከል አንድ ቀን ከሥራዋ ጠባይ የተነሣ በጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለአምልኮ በሰዓቱ አልደረሰችም። አርፍዳ፥ ዘግይታ ነበር የደረሰችው። ስትመጣ ለመጋቢው ሲጸለይለት ትደርሳለች። የሚጸለይለት ለጋብቻ ወደ ኢትዮጵያ ሊሄድ ስለሆነ ጸሎቱ ለዚያ መሆኑን ስታውቅ ራሷን ስታ ትወድቃለች። ሌላ የተበላሸ ሕይወት።

ይህ የቤይሩት የኢትዮጵያ ወንጌላውያን ቤ/ክ ክርስቲያኖች ኅብረት (ወይም የኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ኅብረት በቤይሩት ሊባኖስ) ክስተት ከብዙ የሰማኋቸው ችግሮችና የሚረብሹ ታሪኮች አንዱ ብቻ ነው። ይህንን የሚመስሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሊኖሩ ይችላሉ። ጉዳዩ ምስጢራዊ ስለሆኑ ጉዳቱም ምስጢራዊ ነው።

ይህ የመደምደሚያ ክፍል ራሱ የሕመም ክፍል ስለሆነ በሕመምነቱ ልጨርሰው። የምክር አገልግሎቶች በብዛት የሉንም። ሙያዊ እገዛ የሚያደርጉ ሰዎችም በብዛት የሉንም። ስለዚህ ሕመማችን ቀጣይ ነው፤ ቁስላችን የቆላ ቁስል እየሆነ ይሄዳል። አናሳዝንም? እናሳዝናለን። በሕመም ላለመደምደም አንድ ቃል ልጨምር። ቁስላችን የማይፈወስ ቢመስልም ግን ቁስልን የሚያውቅ ቁሱል የሆነ የቆሰለ ፈዋሽ አለን።

## ምዕራፍ ፺፤

# ክርስቲያንና አስካሪ መጠጥ

ይህ ሌላ የማንነጋገርበት ጉዳይ ነው። የደረስንበት ዘመን 'የተከፈተ እስፐራይት' የሚባል የአልኮል መጠጥ ለክርስቲያን አገልጋይ ተብዬዎች የሚቀርብበትና የሚጠጥጣበት ዘመን ነውና በዚህ በአስካሪ መጠጥ ጉዳይ ላይ ለመነጋገር መሽማቀቅ የለብንም። አሁን እዚህ ትንሽ ሰፋ አድርጌ የማቀርበውን ትምህርት በመጀመሪያ ያካፈልኩት በ2011 (በኛ በ፪ሺ፫ ዓመተ ምሕረት) ነው።

ስለ መጠጥ የተለያዩ ጥያቄዎች ይቀርባሉ፤ ክርክሮችም ይደረጋሉ። አንዴ በአንድ ክርክር ውስጥ ገባሁ። አንድ ወንድም ክርስቲያን መጠጥ መጠጣት አልተከለከለምና በምግብ ቤት ውስጥ መጠጥ ቢሸጥ ገበያውን እስከሳበ ድረስ ክፋት የለበትም የሚል አቋም ይዞ፥ ሌላዋ እኅት ደግሞ ከቶውኑ ለምን መጠጥ መጠጣት ታሰበ? እኛ የማንጠጣ ከሆንን የማንጠጣውን ነገር ለሌላ መሸጥ ስለምን አስፈለገ? የሚል ነው። ጉዳዩን ስንለጥጠው ወደ መሸጥና አለመሸጥ ብቻ ሳይሆን በአልኮል መጠጥ ፋብሪካዎች ውስጥ መሥራትንም ሊነካ ይችላል። ከቀረቡልኝ ጥያቄዎች አንዱ ይህም ራሱ ነው። ጥያቄው በቢራ ፋብሪካ ውስጥ ስለመሥራትና አለመሥራት ነው። ጥያቄው ይህ ነው፤

> ጋሽ ዘሌ፥ እኔ የተማርኩት chemical engineering ነው። አብረውኝ ካሉ ጋር ብዙ ጊዜ ምንጨቃጨቅበት ጉዳይ አለ፤ ይሔም አንድ ክርስቲያን ቢራ ፋብሪካ ገብቶ መስራቱ እንዴት ይታያል? የሚለው ነውና፥ እኔ በራሴ አልደግፍም፥ ያንተን አቋም ብሰማ ብዬ ነው። [AK]

ይህ እዚህ የምንነጋገርበት ጥያቄ ቢራ ስለመጠጣትና ስላለመጠጣት ሳይሆን በቢራ ፋብሪካ ውስጥ ስለመሥራትና አለመሥራት የሞራል ጥያቄ መሆኑ በራሱ ስፍራችንን እና ጉዳያችንን የሚያሳይ ነውና በጣም አስደስቶኛል። ጠያቂውና ጓደኞቹ የሚከራከሩበት ጉዳይ የእንጠጣ? ወይስ አንጠጣ ጉዳይ ሳይሆን በዚያ ስፍራ እንሥራ ወይስ አንሥራ የሚል የሞራል ጥያቄ ነው። የምሳሌነት ጉዳይ ነው። 'እንጠጣ ወይስ አንጠጣ?' የሚለው ራሱም፥ 'አንጠጣ' የሚሉትን ስለሚያካትት የግብረ ገብነት ጥያቄ ነው መባል ይችላል። ይህኛው ግን የንጽሕናና የጥንቃቄ ፍላጎት ነው። በምርኮ ምድር

የነበረውን ዳንኤልን አሳሰበኝ። ዳንኤል በመብሉና በመጠጡ እንዳይረክስ በልቡ አሰበ።

በዚያ ጥያቄው በተለጠፈበት ማኅበራዊ ገጽ፥ በኔ እምነት ከልብ የሆኑ የምር መልሶች ተሰጥተዋል። እርግጥ እዚህም ስለ መጠጣትና አለመጠጣት፥ ስለሌሎችም ኃጢአቶች ተወስተዋል። የጠያቂውን ጥያቄ ለመመለስ ከመሞከር ይልቅ ሞጋችም፥ ፍልስፍናዊም፥ ባዶም ጥያቄዎች በማቅረብ ገጹን እብድ የበላው በሶ ያስመሰሉ ነጥቦችም አሉ።

ይህ ለጠያቂው የተሰነዘረው የኔ መልስ ከመልሶቹ አንዱ ነው። ነጥቦቼ በአንድ መንገድ ወይ በሌላ በሌሎቹም ተጠቅሰዋል። ከኛ ጋር ከዩኒቨርሲቲ የተመረቀች አንዲት እኅታችን የተመደበችው በቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ፋብሪካ የጥራት ቁጥጥር ክፍል ነበረ። ያኔ የግዴታ ምደባ እንጂ የምርጫ ምደባ አልነበረም። የሥራው ጠባይ መቅመስን ይጨምራል። ፈቃደኛ አልሆነችም፤ ያኔ እምነታችን የተወገዘ ቢሆንም ጥያቄዋ ወይም ፈቃደኛ አለመሆኗ ከእምነቷ አንጻር መሆኑን አስረድታ ከመቅመሱ ኃላፊነት ነጻ ተደረገች። ያ ሶሻሊስታዊው የደርግ ዘመን ነውና በጊዜው ያስገረመን ውሳኔ ነበረ።

አንዳንድ መንግሥታት ለሕሊና ነጻ መሆን ስለሚጠነቀቁ ለሰዎች ሕሊና ሲሉ ከመስመር ወጥተውም ይሄዱላቸዋል። በ2ኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ለምሳሌ፥ የአሜሪካ መንግሥት በጦርነቱ በቀጥታ መሳተፍ ያልፈለጉ ሃይማኖተኞች በደጀን የሲቪል ሥራዎች እንዲሳተፉ ነጻ አድርጎአቸዋል። በድርድር ስፍራችንን የምናስጠብቅበት ዕድል ከኖረን ያንን ማድረግ ድንቅ ነው።

በግልጽ በቃሉ ውስጥ ላልተጻፉ፥ ነገር ግን ሕሊናችንን የሚያቆሽሹ ከመሰሉን ነገሮች ሁሉ ላለመሰናከል እና ላለማሰናከል ብሎ ለመራቅ የመንፈስ ቅዱስን ምሪት መፈለግ የልጅነት መብታችንና በረከታችን ነው። ለሁለቱም፤ ማለትም፥ ለራስም፥ ለሌሎችም ነው ጥንቃቄው። ጉዳዩ የምርጫ ነገር ወደ ስሌቱ የሚያስገባ ከሆነ ዋጋን መተመን ሊኖር ነው። እንደ ክርስቲያን፥ 'የቱ ጠቃሚ ነው?' ብቻ ሳይሆን፥ 'የቱ ጌታን ያስከብራል?' የሚለው ጥያቄ ትልቁና ደማቁ መሆን ያለበት ነው።

*ዳንኤልም በንጉሡ መብልና በሚጠጣው ጠጅ እንዳይረክስ በልቡ አሰበ፤ እንዳይረክስም የጃንደረቦቹን አለቃ ለመነ።* ዳን. 1፥8። ዳንኤል ሁለት ነገሮች አደረገ፤ <u>እንዳይረክስ፥ አሰበ፤ ለመነ።</u> የሚያረክሰው ነገር ምንነት አልተጻፈልንምና መገመት ብቻ ነው የምንችለው። ግን ዋናው ነጥብ ላለመርከስ የተደረገ ትንቅንቅ ነው። የጃንደረቦቹ አለቃ፥ 'አይሆንም!' ቢል ዳንኤል ምን እንደሚያደርግ አናውቅም። አሁንም መገመት ብቻ ነው የምንችለው።

ጠያቂያችን የኬሚካል ኢንጂኒየሪንግ ምሩቅ ስለሆነ ሊሠራ የሚችልበት መስክና ሥራ የቢራና የመጠጥ ፋብሪካ ብቻ አይመስለኝም። ምናልባት በአገራችን በመስኩ ያለው ግዙፉ ኢንደስትሪ ያ ሊሆን ይችላል። ከሆነ ከላይ እንዳልኩት ከተጻፈው ባሻገር ላለው የሕሊና ጥያቄ ጸሎት ተገቢ ነው። መሰናከል ላለመሆን የተገባ ከሆነ በሌላ መስክ መሰማራት ማለፊያ ነው።

ጳውሎስ በ1ቆሮ. 8፥13 *ስለዚህም መብል ወንድሜን የሚያሰናክለው ከሆነ፥ ወንድሜን እንዳላሰናክለው ለዘላለም ከቶ ሥጋ አልበላም።* አለ። በምዕራፉ የተናገረው ለጣዖት ስለተሠዋ ሥጋ ቢሆንም ሲደመድም ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ ብቻ ሳይሆን፥ 'ከቶ ሥጋ' ነው ያለው። ሌላውን፥ ለጣዖት ያልተሠዋውንም ጭምር ማለቱ ነው። ለምን? ከኔ ነጻነት የወንድሜ መታነጽ ይበልጣል።

ለራሳችንና ለሌላው ሕሊና መጠንቀቅ የሚያስከፍለን ዋጋ አለ? አዎን፤ አለ። ልብ እንበል፤ ሕሊናችን መንፈሳችን አይደለም። ሕሊናችን ትክክል ተብሎ የተነገረንን ነገር ብቻ ነው የሚያሳስበን እንጂ ቅዱስ ቃሉን አያስተምረንም። ያ የመንፈስ ቅዱስ ተግባር ነው። ስለዚህ ከሕሊናችን ጠልቀን ቅዱስ ቃሉን የምንመረምርና ቃሉ እንዲጻፍ ያደረገውን መንፈስ ቅዱስን መስማት አለብን። ይህ ምርጫም አማራጭም የለውም።

ለዚያ ወንድም ጥያቄ ወደመለስኩት መልስ ወይም ወደ መጠጥ ጥያቄና ጉዳይ ከማለፌ በፊት ከዚህኛው መንደርደር የፈለግሁት በዚህም ልክ የሚጠነቀቁ መኖራቸውን ለማሳየት ነው። ለመጠጣት ሳይሆን በሚጠመቅበት ላለመገኘትም የሚጥሩ መኖራቸውን ለማሳየት። እንዲህ የሚጠነቀቁ ቅዱሳንን ማየት በራሱ በረከት ነው።

ለክርስቲያን ወይን መጠጣትና ማጠጣት የተፈቀደ ነውን? በአንድ ጎራ አስካሪ መጠጥን የሚኮንኑ ከቶም ሊጠጣ ይቅርና ሊታይም፥ ሊታሰብም የተገባ አይደለም የሚል አቋም የያዙ አሉ። በሌላው ደግሞ መጠጥ መጠጣት ይፈቀዳል ስካር ነው የሚከለከለው? የሚል አቋም ያላቸው አሉ።

መጠጣትን የሚደግፉት፥ 'በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙዎች የተመሰገኑና የተመሰከረላቸው ሰዎች የወይን ጠጅ ጠጥተዋል፤ ጌታም የወይን ጠጅ ጠጥቶአል፤ ታዲያ መጠጣት ምን ክፋት አለበት?' የሚሉ ናቸው። 'በመጠጥ ደስታ ይገኛል ብላችሁ፤ መጠን አትለፉ ትቃጠላላችሁ' ነው ያለው ዘፋኙ የሚሉ ዓይነቶቹ ናቸው፤ ምንም እንኳ ዘፋኙን ባይጠቅሱም። ከነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹ፥ 'እስከ መስከርስ ቢሆን? ወደ አፍ የሚገባ እኮ አያረክስም ነው የተባለው' በማለት ራቅ የሚል እርምጃ ይራመዳሉ።

በሁለቱም መሐል ያሉቱ ደግሞ፥ 'ይህ የግለሰቡ ኅሊና ጉዳይ ነውና ለግሉ ውሳኔ መተው ነው እንጂ በዚህ ጉዳይ መነጋገር አስፈላጊ አይደለም።' የሚሉ መሐል ሰፋሪዎች ናቸው። 'የማይጠጣ ለጌታ ብሎ አይጠጣ፤ የሚጠጣም መንፈስ ከመሰከረለት ይኮምኩም።' ባዮች ናቸው። ስለዚህ አስካሪ መጠጥም ሆነ ሌሎችም ሱስ የሚያስይዙም ሆኑ የማያስይዙ ነገሮች የግለሰቡ ኅሊና ውሳኔ ነው የሚል ኅሊናዊ አቋም ይይዛሉ። እነዚህ ብዙውን ጊዜ ራሳቸውም በወጥመዱ የተያዙት ናቸው።

ጥያቄ ውስጥ መግባት የለበትም ከሚሉት ከነዚህ የማይርቁቱ ሌሎች ደግሞ፥ 'መጠጣትም ሆነ አለመጠጣት ሰውነታችንን ወይም ነፍሳችንን የማርከስ አቅም ስለሌለውና ደኅንነታችንን ከቶም ሙሉ ወይም ጎዶሎ ስለማያደርገው ይህ ጉዳይ እጥያቄ ውስጥም መግባት የለበትም።' የሚል ዳኝነት ይዳኛሉ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጻፈው አገባባቸው በመነሣት ወይንና የወይን ጠጅ እንዲሁም የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ የተለያዩ መሆናቸውን ማወቅ እንችላለን። ምክንያቱም እነዚህ ቃላት ተነባብረው የተቀመጡባቸው ስፍራዎች አሉና፤ ለምሳሌ ያህል እነዚህን ጥቅሶች ተመልከቱ፤ ዘሌ. 10፥9፤ ዘዳ. 29፥6፤ መሳ. 13፥4-14፤ 1ሳሙ. 1፥15፤ ኢሳ. 24፥9፤ ሉቃ. 1፥15። ከነዚህ አጠቃቀሶች በመንደርደር የወይን ጠጅ ሁሉ አስካሪ መጠጥ ነው ብለን እንዳንደመድም ሊያስገድደን የሚችል እውነት መኖሩን እናስተውላለን።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ጥቂት አሳቦችን በነጥብ አስቀምጣለሁ። ለእያንዳንዱ ነጥብም ጥቂት ናሙና ጥቅሶች አከላለሁ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው የወይን ጠጅ በዘመናችንም ያንኑ ቃል ይወከላል። አስካሪ መጠጥም ማናቸውንም አስካሪ መጠጥ ሊወክል ይችላል።

<u>1. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወይን ልብን የሚያስደስት መሆኑ ተጽፎአል።</u>

አንድ የኢትዮጵያ የወይን ጠጅ ፋብሪካ፥ አዋሽ የወይን ጠጅ ፋብሪካ ይመስለኛል፥ በመጠጥ ማከፋፈያ የጭነት መኪናዎቹ ላይ የመዝ. 104፥15ን ቃል በግዕዝ *ወይን ያስተፌስህ ልበ ሰብእ* ብለው ጽፈው ነበር። አሁንም ያ ጥቅስ በተሽከርካሪዎቻቸው ላይ ይኑር አይኑር አላውቅም። መጽሐፍ ቅዱስ በተወገዘበት የደርግ ዘመን እንኳ ሳይቀር ይህ ጥቅስ መነገጃ ሆኖ የነበረው ለምን ነበር? የእግዚአብሔር ቃል ቢሆንም ሕዝቡ ሃይማኖታዊ በመሆኑ ነው። በጥቅሱ ወደ መንፈሳዊነት የሚያመለክት ነገር ባይኖረውም ወደ እግዚአብሔር የሚያመለክት ባለመሆኑም ነው የተመረጠው። ደግሞም የንግድ ጥሩ ማስታወቂያ ቃልም ነው። እውን ወይን ያስተፈስሃል? ወይም የወይን ጠጅ ልብን ያስደስታል? አዎን የቃሉ ምስክርነት ነው፤ ወይን ልብን ያስደስታል።

> መሳ. 9፥13 *ወይኑም፥ <u>እግዚአብሔርንና ሰውን ደስ የሚያሰኘውን የወይን ጠጄን</u> ትቼ በዛፎች ላይ እንድሰፍፍ ልሂድ? አላቸው።* በዚህ ጥቅስ ወይን ሰውን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርንም የሚያስደስት መሆኑ ተጠቅሶአል። ልብ እንበል ተናጋሪው ወይን ነው፤ ሰው አይደለም። ይህ በምሳሌያዊ ንግግር ውስጥ የተጠቀሰ ቃል ነው። ሆኖም ወይን መናገር አይችልምና ስለ ወይን ሆነው ሰዎች ሲናገሩ ሰውን የሚያስደስት መሆኑን ጠቅሰዋል።
>
> ዘካ. 10፥7 *የኤፍሬምም ሰዎች እንደ ኃያላን ይሆናሉ፥ <u>ልባቸውም የወይን ጠጅ እንደ ጠጣ ሰው ደስ ይለዋል</u> ልጆቻቸውም አይተው ደስ ይላቸዋል፥ ልባቸውም በእግዚአብሔር ሐሤት ያደርጋል።*
>
> መክ. 2፥3 *የሰው ልጆች በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ ከፀሐይ በታች ሊሠሩት መልካም ነገር ምን እንደ ሆነ እስካይ ድረስ ልቤ በጥበብ እየመራኝ፥ <u>ሰውነቴን በወይን ጠጅ ደስ ለማሰኘት</u> ስንፍናንም ለመያዝ በልቤ መረመርሁ።*

*መዝ. 104፥15 <u>ወይን የሰውን ልብ ደስ ያሰኛል፥</u> ዘይትም ፊትን ያበራል፥ እህልም የሰውን ጉልበት ያጠነክራል።*

ከነዚህ ጥቅሶች የምንረዳው ወይን በእርግጥም ሰውን ወይም ሰውነትን ደስ እንደሚያሰኝ ነው። ሰውን ወይም ሰውነትን ደስ የሚያሰኙ ብዙ ነገሮች አሉ። ወይን ከነዚህ አንዱ ነው። ሰውን ወይም ሰውነትን ደስ የሚያሰኙ ነገሮች ሁሉ ትክክለኛ ነገሮች ናቸው ማለት ነው? አይደሉም። ሌሎችን ደስ የሚያሰኙ፥ ግን ትክክል ያልሆኑ ነገሮች መኖራቸውን እናውቃለን። እነዚህ ጥቅሶች ምሳሌያዊ ንግግሮችና የትረካ ክፍሎች ናቸው እንጂ ትእዛዛት አይደሉም።

<u>2. ወይን / ወይን ጠጅ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳናት ዘመን የተለመደ ባህላዊና ማኅበራዊ መጠጥ ነው።</u>

ወይን በአይሁድና በጥንቱ የመካከለኛው ምሥራቅ ባህል ለመስተንግዶ፥ ለሠርግ፥ ለበዓላት፥ ለድግስ፥ ለነገሥትና ለመኳንንት፥ ለስጦታ፥ ለክፍያም ይውል ነበር። ንጉሦች ወይንና የወይን ጠጅ የሚያከማቹባቸው ማከማቻዎችና በተለይ ለዚህ የተሾሙ ሹሞችም ነበሩአቸው።

ዘፍ. 14፥15 *የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅም እንጀራንና <u>የወይን ጠጅን</u> አወጣ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበረ።*

1ሳሙ. 16፥20 *እሴይም እንጀራና <u>የወይን ጠጅ አቁማዳ የተጫነ</u> አህያ የፍየልም ጠቦት ወስዶ በልጁ በዳዊት እጅ ወደ ሳኦል ላከ።*

1ሳሙ. 25፥11 *እንጀራዬንና <u>የወይን ጠጄን</u> ለሸላቾቼም ያረድሁትን ሥጋ ወስጄ ከወዴት እንደ ሆኑ ለማላውቃቸው ሰዎች እሰጣለሁን? ብሎ መለሰላቸው።*

1ሳሙ. 25፥18 *አቢግያም ፈጥና ሁለት መቶ እንጀራ፥ <u>ሁለት አቁማዳ የወይን ጠጅ፥</u> አምስትም የተዘጋጁ በጎች፥ አምስትም መስፈሪያ ጥብስ እሸት፥ አንድ መቶ ዘለላ ዘቢብ፥ ሁለት መቶም የበለስ ጥፍጥፍ ወሰደች፥ በአህዮችም ላይ አስጫነች።*

2ሳሙ. 16፥1-2 *ዳዊትም ከተራራው ራስ ጥቂት ፈቀቅ ባለ ጊዜ የሜምፊቦስቴ ባሪያ ሲባ ሁለት መቶ እንጀራ፥ አንድ መቶም ዘለላ ዘቢብ፥ አንድ መቶም በለስ፥ <u>አንድ አቁማዳም ወይን ጠጅ</u> የተጫኑ ሁለት አህዮች እየነዳ ተገናኘው። ንጉሡም ሲባን፦ ይህ ምንድር ነው? አለው። ሲባም፥ አህዮቹ የንጉሥ ቤተ ሰቦች ይቀመጡባቸው ዘንድ፥ እንጀራውና በለሱ ብላቴኖቹ ይበሉት ዘንድ፥ የወይን ጠጁም በበረሀ የሚደክሙት ይጠጡት ዘንድ ነው አለ።*

1ዜና 12፥40 *ደግሞም በእስራኤል ዘንድ ደስታ ሆኖአልና እስከ ይሳኮርና እስከ ዛብሎን እስከ ንፍታሌምም ድረስ ለእርሱ አቅራቢያ የነበሩ በአህያና በግመል በበቅሎና በበሬ ላይ እንጀራና ዱቄት የበለስ ጥፍጥፍና የዘቢብ ዘለላ <u>የወይንም ጠጅ</u> ዘይትም በሬዎችንና በጎችንም በብዙ አድርገው ያመጡ ነበር።*

2ዜና 2፥10 *እነሆም፥ እንጨቱን ለሚቈርጡ ለባሪያዎችህ ሀያ ሺህ የቆሮስ መስፈሪያ የተበጠረ ስንዴ፥ ሀያ ሺህም የቆሮስ መስፈሪያ ገብስ፥ <u>ሀያ ሺህም የባዶስ መስፈሪያ የወይን ጠጅ፥</u> ሀያ ሺህም የባዶስ መስፈሪያ ዘይት እሰጣለሁ።*

1ዜና 27፥27 *በወይንም ቦታዎች ላይ ራማታዊው ሰሜኢ ሹም ነበረ <u>የወይንም ጠጅ ዕቃ ቤት</u> በሚሆነው በወይኑ ሰብል ላይ ሸፋማዊው ዘብዲ ሹም ነበረ።*

ነህ. 2፥1 *በንጉሡ በአርጤክስስ በሀያኛው ዓመት በኒሳን ወር <u>የወይን ጠጅ በፊቱ በነበረ</u> ጊዜ ጠጁን አንሥቼ ለንጉሡ ሰጠሁት። ቀድሞ ግን በፊቱ ያለ ኃዘን እኖር ነበር።*

ነህ. 5፥18 *ከወፎችም በቀር ለአንድ ቀን አንድ በሬና ስድስት የሰቡ በጎች፥ በአሥር በአሥር ቀንም <u>ብዙ ልዩ ልዩ ዓይነት ወይን ጠጅ ይዘጋጅልኝ ነበር</u> ነገር ግን አገዛዝ በሕዝቡ ላይ ከብዶ ነበርና ለአለቃ የሚገባውን ስንቅ አልሻም ነበር።*

ጌታ በመጀመሪያ ያደረገው ተአምሩ ውኃን ወደ ወይን መለወጡ ነበር። ይህንን ተአምር አስካሪ መጠጥ የመጠጫ ዋነኛ መከራከሪያ የሚያደርጉ ጠጪዎች አሉ። ይህ ወይን ጠጅ የሚጠጣበት ባህላዊ ድግስ ነው። ሠርግ ነው። ወይን ጠጁም ከመናኛ ወይም ከቀጠነው እስከ መልካሙ ወይም ኃይለኛውና አስካሪው የሚለያይ ነው። ጌታ ውኃውን ወደ ወይን የለወጠው ወደ መናኛው ሳይሆን ወደ መልካሙ ነው። ይህ በሰው እጅና ጊዜ የተጠመቀው ስላልሆነ ከመልካሙም እጅግ የተሻለው መሆን አለበት።

ዮሐ. 2፥3 እና 9-10 *የወይን ጠጅም ባለቀ ጊዜ የኢየሱስ እናት፥ የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም አለችው። . . . አሳዳሪውም የወይን ጠጅ የሆነውን ውሃ በቀመሰ ጊዜ ከወዴት እንደ መጣ አላወቀም፤ ውኃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን ያውቁ ነበር፤ አሳዳሪው ሙሽራውን ጠርቶ፥ ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል፥ ከሰከሩም በኋላ መናኛውን፤ <u>አንተስ መልካሙን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሃል</u> አለው።*

ይህ ሠርግ ጌታ ተጋብዞ ወይም ታድሞ የሄደበት ሠርግ ነው። እናቱ ማርያም ውስጠኛና የቅርብ ሰው ሳትሆን አትቀርም። ባይሆን የጓዳውን ምስጢር ወይም የወይን ጠጁን ማለቅ፥ አታውቅም፤ ለጌታም አትናገርም ነበር። ይህ የወይን ጠጅ መጠጥ የሚጠጣበት ድግስ ስፍራ ነው፤ ወይን ጠጅ ደግሞ አለቀ። ጌታ በጉዳዩ ተሳታፊ ካልሆነ የሚያሳፍር ነገር ሊከሰት ነው። ጌታ ተአምራትን ያደርግ የነበረው ሁኔታዎችን ለመለወጥና ተአምራትን ማድረጉ አስፈላጊ ሲሆን ነው። ጌታ ተአምራትን እንዲያው እንደ በታኝ ዘሪ ሲበትን አይታይም። እዚህ አስፈልጎ ነበር። ደግሞም የመጀመሪያ ተአምሩ ነው። ጌታ በአካል በተገኘበት ሠርግ ጎዶሎነት አይኖርምና በመልካሙ ወይን ተአምር ሠርጉን ከጎዶሎነትና ከእፍረት ጠበቀ። ሠርጉን የታደገው ወይን ጠጁ ሳይሆን የጌታ መገኘት ነው። የጌታን የራሱን ምሳሌነት በሌላ ነጥብ እንመለከታለን። ይህም ታሪካዊ ድርጊት እንጂ ትእዛዝ አለመሆኑን እናስተውላለን። ታሪኮች ሁሉ ይደገማሉ ወይም ይደጋገማሉ ማለት አይደለም።

3. ለመቅደስ አገልግሎትና ለመሥዋዕት ይቀርብ ነበር።

የወይን ጠጅ እንደ መጠጥ ቁርባን እና የሚፈስስ መሥዋዕት በመሆን ይቀርብ ነበር። የወይን ጠጅ እንደ አስራትም በኵራትም ሆኖ ለሌዋውያን ይሰጥ ነበር። ሕዝቡ በዓመታዊ በዓላቸው ደስ እንዲላቸው ወይን ጠጅና ብርቱ መጠጥ ሊጠጡ ተፈቅዶላቸዋል።

> ዘሌ. 23፥13 *የእህልም ቍርባን ከመስፈሪያው ከአሥር እጅ ሁለት እጅ የሆነ በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ እንዲሆን ለእሳት ቍርባን ይሁን የመጠጡም ቍርባን የወይን ጠጅ የኢን መስፈሪያ አራተኛ እጅ ይሁን።*

> ዘኊ. 15፥4-7 *ቍርባኑን ለእግዚአብሔር የሚያቀርብ ከሚቃጠል መሥዋዕት ወይም ከሌላ መሥዋዕት ጋር ለእያንዳንዱ ጠቦት የኢን መስፈሪያ አራተኛ እጅ በሆነ ዘይት የተለወሰ ከመስፈሪያው ከአሥር እጅ አንድ እጅ የሆነ መልካም ዱቄት ለእህል ቍርባን፥ የኢን መስፈሪያ አራተኛ እጅ የወይን ጠጅ ለመጠጥ ቍርባን ያዘጋጃል። ለአንዱም አውራ በግ ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ እንዲሆን የኢን መስፈሪያ ሢሶ በሆነ ዘይት የተለወሰ ከመስፈሪያው ከአሥር እጅ ሁለት እጅ መልካም ዱቄት ለእህል ቍርባን ታዘጋጃለህ የኢን መስፈሪያ ሢሶም የወይን ጠጅ ለመጠጥ ቍርባን ታቀርባለህ።*

> ዘዳ. 12፥17 *የእህልህን የወይን ጠጅህን የዘይትህንም አሥራት፥ የላምህንና የበግህንም በኵራት፥ የተሳልኸውንም ስእለት ሁሉ፥ በፈቃድህም ያቀረብኸውን፥ በእጅህም ያነሣኸውን ቍርባን በደጆችህ ውስጥ መብላት አትችልም።*

> ዘዳ. 14፥23 እና 26 *ሁልጊዜ አምላክህን እግዚአብሔርን መፍራት ትማር ዘንድ፥ ስሙ እንዲጠራበት በመረጠው ስፍራ በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት የእህልህን የወይን ጠጅህንም የዘይትህንም አሥራት የላምህንና የበግህንም በኵራት ብላ። በዚያም በገንዘቡ ሰውነትህ የፈለገውን፥ በሬ ወይም በግ ወይም የወይን ጠጅ ወይም ብርቱ መጠጥ ሰውነትህም የሚሻውን ሁሉ ትገዛለህ በዚያም በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት ትበላዋለህ፥ አንተና ቤተ ሰብህም ደስ ይላችኋል።*

> ዘዳ. 18፥4 *የእህልህን የወይን ጠጅህን የዘይትህንም በኵራት፥ አስቀድሞም የተሸለተውን የበግህን ጠጕር ለእርሱ ትሰጣለህ።*

ይህን መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ያዘዛቸውም፥ የሚያቀርቡትን ባርኮ የሰጣቸውም ራሱ እግዚአብሔር ነው።

> ሆሴ. 2፥10-11 *እርስዋም እህልንና ወይንን ጠጅ ዘይትንም የሰጠኋት፥ ለበኣልም የተሠራውን ብርና ወርቅ ያበዛሁላት እኔ እንደ ሆንሁ አላወቀችም። ስለዚህ እህሌን በጊዜዋ፥ ወይን ጠጄንም በወረትዋ እወስዳለሁ፥ ዕራቁትነትዋንም እንዳትሸፍን ጥጤንና የተልባ እግሬን እገፍፋታለሁ።*

<u>4. የእግዚአብሔር አገልጋዮች በአገልግሎት ወቅት ወይም በአገልግሎታቸው ዘመን ወይን እንዳይጠጡ ተደንግጎአል።</u>

የወይን ጠጅ ለመሥዋዕትና ለስጦታ ይቅረብ እንጂ ሌዋውያን በአገልግሎታቸው ወቅት መጠጣት አልተፈቀደላቸውም።

> ዘሌ. 10፥9 *እንዳትሞቱ ወደ መገናኛው ድንኳን ስትገቡ አንተና ልጆችህ <u>የወይን ጠጅና የሚያሰክርን ነገር ሁሉ አትጠጡ ይህም ለልጅ ልጆችሁ የዘላለም ሥርዓት ይሆናል።</u>*

> ሕዝ. 44፥21 *ካህናቱም ሁሉ በውስጠኛው አደባባይ ሲገቡ <u>የወይን ጠጅ አይጠጡ።</u>*

በሕዝቅኤል የተጠቀሰው በራእያዊው መቅደስ ሲሆን በዘሌዋውያን የተጠቀሰው በምድራዊዋ ያገለገሉባት የመገናኛ ድንኳን ነው። የወይን ጠጅ እንዳይጠጡ ለምን ተከለከሉ? አገልጋዮች ናቸው። አገልግሎታቸው አምልኮአቸው ነው። በእግዚአብሔር ፊት ሊያመልኩት፥ ሊያገለግሉት የሚቀርቡ ሰዎች ናቸውና አእምሮአቸው በምንም ማደንዘዣ መበረዝ የለበትም። በአንቂና በአነቃቂም፥ በአደንዛዥ ንጥረ ነገርም መበወዝ የለበትም።

ይህ በተለይ ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች ትልቅ ትምህርት ነው። የአዲስ ኪዳን አማኞች በሙሉ አገልጋዮች ናቸው፤ ሁሉም የንጉሥ ካህናት ናቸው። አገልግሎታቸው ደግሞ የተወሰነ ቀን አይደለም። በአዲስ ኪዳን ሌዋውያን የሉም። የካህናትና የምዕመናን መደብም የለም። በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር እንደ ብሉይ ዘመን የተለየ የአምልኮ ጊዜና የመመለኪያ የመቅደስ ቦታ የሚወሰንለት ሳይሆን በአማኞች ወይም አምላኪዎች፥ ወይም በአገልጋዮች ሁሉ በመንፈስና በእውነት ሁሌም እና የትም የሚመለክ አምላክ ነው። ስለዚህ አምላኪዎቹና አገልጋዮቹ ሁሉ፥ ሁሌም ንቁ፥ በሃይማኖት የቆሙ ሊሆኑ የተገባ ነው። ሁሌም አገልጋዮች ናቸውና።

የብሉይ ኪዳን ናዝራውያን የዚህ ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ። ናዝራውያን በናዝራዊነት ዘመናቸው ወይንና የወይን ጠጅ፥ የወይኑን ፍሬና ዘቢቡንም ጭምር አይቀምሱም። ናዛር (נָזַר) ማለት በዕብራይስጥ የተለየ መሆን፥ ከሚያረክስ ነገር ራስን መለየት፥ ማግለል ማለት ነው። ናዝራዊ ሰው ራሱን ለተወሰነ ጊዜ ለእግዚአብሔር ለይቶ የሚሰጥበት ሥርዓት ነው፤ ዘዳ. 6፥1-21፤ አሞ. 2፥11-12። ናዝራዊ ራሱን በለየበት ዘመኑ ከተለያዩ የሚያረክሱ ነገሮች መራቅ ይጠበቅበታል። ከሚርቃቸው ነገሮች አንዱ ከወይንና የወይን ውጤቶች ነው።

> ዘኁ. 6፥3-4 *<u>ከወይን ጠጅና ከሚያሰክር መጠጥ</u> ራሱን የተለየ ያድርግ <u>ከወይን ከሌላ ነገር የሚገኘውን ሆምጣጤ አይጠጣ፥ የወይንም ጭማቂ አይጠጣ የወይን</u>*

> *<u>እሸት ወይም ዘቢብ አይብላ።</u> ራሱን የተለየ ባደረገበት ወራት ሁሉ <u>ከወይን የሆነውን ነገር ሁሉ ከውስጡ ፍሬ ጀምሮ እስከ ገፈፎው ድረስ አይብላ።</u>*

ዘኍ. 6፥20 ላይ የናዝራዊነቱን ወራት ከጨረሰ በኋላ *ከዚያም በኋላ ናዝራዊው <u>ወይን</u> ይጠጣ ዘንድ ይችላል።* ተብሎ ተጽፎአል። በናዝራዊነት ዘመኑ ሁሉ ወይን አይጠጣም። ራሱን ለእግዚአብሔር ለይቶአልና።

ሶምሶን ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ ነበረ፤ መሳ. 13፥5-7፤ 16፥17-20። ሶምሶን ከመጸነሱ ጀምሮ ናዝራዊ ነበርና ሳይወለድ ጀምሮም እናቱ እንድትጠነቀቅ ተነገራት። አንዱ እንድትጠነቀቅ የተነገራት የወይን ጠጅና የሚያሰክር ነገር እንዳትጠጣ ነው።

> መሳ. 13፥4 እና 7 *አሁንም ተጠንቀቂ <u>የወይን ጠጅን የሚያሰክርም ነገር አትጠጪ፥</u> ርኩስም ነገር አትብዪ። . . . እርሱም፦ እነሆ፥ ትፀንሻለሽ፥ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ልጁም ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ እስኪሞት ድረስ ለእግዚአብሔር የተለየ <u>ናዝራዊ</u> ይሆናልና አሁን <u>የወይን ጠጅ የሚያሰክርም ነገር አትጠጪ፥</u> ርኩስም ነገር አትብዪ አለኝ ብላ ተናገረች።*

> መሳ. 13፥14 *<u>ከወይንም ከሚወጣው ሁሉ አትብላ፥ የወይን ጠጅንም የሚያሰክርንም ነገር አትጠጣ፥</u> ርኩስም ነገር ሁሉ አትብላ ያዘዝኋትን ሁሉ ትጠብቅ አለው።*

ሬካባውያን ሌላ ምሳሌዎች ናቸው፤ ታሪካቸው በኤር. 35 ይገኛል።

> ኤር. 35፥2 *ወደ ሬካባውያን ቤት ሄደህ ተናገራቸው፥ ወደ እግዚአብሔርም ቤት ከጓዳዎቹ ወደ አንዲቱ አግባቸው <u>የወይን ጠጅም አጠጣቸው።</u>*

> ኤር. 35፥5-9 *በሬካባውያንም ልጆች ፊት <u>የወይን ጠጅ የምላባቸውን ማድጋዎችንና ጽዋዎችን አኑሬ፥ የወይኑን ጠጅ ጠጡ አልኋቸው።</u> እነርሱ ግን እንዲህ አሉ፥ <u>የወይኑን ጠጅ አንጠጣም፥</u> አባታችን የሬካብ ልጅ ኢዮናዳብ እንዲህ ብሎ አዝዞናልና። እናንተና ልጆቻችሁ <u>ለዘላለም የወይን ጠጅ አትጠጡ።</u> በምትኖሩባት ምድር ላይ ብዙ ዘመን እንድትኖሩ፥ በዕድሜአችሁ ሙሉ በድንኳን ውስጥ ተቀመጡ እንጂ ቤትን አትሥሩ፥ ዘርንም አትዝሩ፥ <u>ወይንም አትትከሉ፥</u> አንዳችም አይሁንላችሁ። እኛም የአባታችንን የሬካብ ልጅ የኢዮናዳብን ቃል ባዘዘን ነገር ሁሉ ታዝዘናል እኛም ሚስቶቻችንም ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችንም ዕድሜአችንን ሙሉ <u>የወይን ጠጅ አልጠጣንም።</u> የምንቀመጥበትንም ቤት አልሠራንም <u>የወይን ቦታና</u> እርሻ ዘርም የለንም።*

የአዲስ ኪዳን አገልጋዮች ወይም አማኞች እንደ ናዝራውያንና እንደ ሬካባውያን ስለምን ራሳቸውን አይቋጥሩም? ስለምን ራሳቸውን የተለዩ አያደርጉም? ቢያደርጉ ወይስ ባያደርጉ? የትኛው ነው የሚሻለው? ቢያደርጉ ወይስ ባያደርጉ? የትኛው ነው የሚጎዳው?

እስራኤል በምድረ በዳው ጉዞአቸው ዘመንም ወይንና የሚያሰክር አልጠጡም። ያ ጉዞ የግንኙነትና የአምልኮ ጉዞ ነበረ፤ ወልመጥማጣ ትውልድ ሆኑና በምድረ በዳ ቀሩ እንጂ የወጡትስ የካህናት መንግሥት ሆነው ሊያገለግሉት፥ ሊያመልኩት ነበረ። ፈርዖንም የተባለው በምድረ በዳ ያገለግለኝ፥ ይሠዋልኝ፥ በዓል ያደርግልኝ ዘንድ ተብሎ ነው፤ ዘጸ. 5፥1፤ 7፥16፤ 8፥28።

> ዘዳ. 29፥6 *እኔ አምላካችሁ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቁ ዘንድ እንጀራ አልበላችሁም፥ <u>የወይን ጠጅና የሚያሰክረውን መጠጥ አልጠጣችሁም።</u>*

መጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎቱ ከወይን ጠጅና አስካሪ መጠጥ የጸዳ ነበረ።

> ሉቃ. 1፥15 *በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና፥ <u>የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም፤</u> ገናም በእናቱ ማኅፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል፤*

ናዝራውያን በናዝራዊነታቸው ዘመን፥ ሌዋውያን በአገልግሎት ዘመናቸው፥ ሬካባውያን በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ፥ እስራኤል በነጻነት ጉዞአቸው ወቅት፥ መጥምቁ በዘመኑ ሁሉ መጠጥ አልጠጡም ነበር። ለእግዚአብሔር መለየት ማለት እግዚአብሔርን ማምለክና እርሱን ማገልገል ነው፤ ከእርሱ ጋር አብሮ የመሆንና የኅብረት ጊዜ ነውና አእምሮ በምንም ሌላ ገዢና ተቆጣጣሪ ስር መሆን የለበትም።

እነዚህ ያልጠጡቱ ወይም እንዳይጠጡ የተከለከሉቱ ለምን እንደተከለከሉ ስናጤን ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 14፥17 *የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና።* ያለውን በውል መረዳት አይከብደንም። የእግዚአብሔር አገልጋዮችና፥ ተከታዮችና አምላኪዎች ከሆንን አስካሪ መጠጥ ላለመጠጣት በቂና ከበቂም በላይ ምስክሮችና ምሳሌዎች አሉን። እግዚአብሔርን ስናመልክና ስናገለግል በተበረዘ ማንነት ማምለክና ማገልገል የለብንም። አራተኛው ነጥብ የእግዚአብሔር አገልጋዮች፥ የእርሱ አምላኪዎች በአገልግሎት ወቅት ወይም በአገልግሎታቸው ዘመን ሁሉ ወይም ራሳቸውን በፈቃዳቸው ለእግዚአብሔር በሰጡበት ዘመን ሁሉ እንዳይጠጡ የተደነገገ መሆኑ ነው።

<u>5. ወይን ጠጅ አስከፊ መልክ አለው። በርካታ ምሳሌዎችም ተዘርዝረውልናል።</u>

ጥንት ግሪካውያን አስተማሪዎች ለተማሪዎቻቸው የአስካሪ መጠጥን አስቀያሚነት ለማሳየት ወደ ማስተማሪያ ክፍላቸው ሰክሮ ጥንብዝ ያለ ሰው አምጥተው ሲለፋደድ ወይም መሳለቂያ ሲሆን ያሳዩአቸው ነበር። ስለ ስካር ትምህርት የሚሆን ከሰካራም በላይ ምንም የለም። ስካር በቀላሉ አታልሎ የሚወስድ ስለመሆኑ ደግሞ ጃፓኖች እንዲህ የሚል ምሳሌም ነበራቸው፤ በመጀመሪያ ለራስህ አንድ ዋንጫ ወይን ትጋብዛለህ፤ ቀጥሎ የጠጣኸው ወይን ሌላ አንድ ዋንጫ ይጋብዝሃል፤ ከዚያም የጠጣኻቸው ዋንጫዎች አንተን ይጠጡሃል። እውነት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የወይን ጠጅን አስቀያሚ መልክም በግልጽ አስፍሮልናል። በበዓለ ኀምሳ ዕለት ደቀ መዛሙርት በሌሎች ቋንቋዎች ሲናገሩ ሲያደምጡአቸው፥

*ሐዋ. 2፥13 ሌሎች ግን እያፌዙባቸው፥ ጉሽ የወይን ጠጅ ጠግበዋል አሉ።*

እነዚህ ሰዎች ያልሰከሩ ቢሆኑም እንኳ፥ 'እያፌዙባቸው' የሚለው ቃል የወይን ጠጅ የጠገቡ ሰዎች የሚፌዝባቸው ዓይነቶች፥ የፌዝ ዒላማዎች፥ የፌዝ ጊጤዎች ናቸው ማለት ነው።

*1ሳሙ. 1፥14 ዔሊም፥ ስካርሽ እስከ መቼ ነው? <u>የወይን ጠጅሽን ከአንቺ አርቂው</u> አላት።*

የሳሙኤል እናት ሐና በሴሎ በእግዚአብሔር መቅደስ ሳሉ ስትጸልይ አልሰከረችም፤ ሆኖም ለካህኑ ዔሊ የሰከረች መምሰሏ ይህም ቃል የወይን ጠጅን ወይም ስካርን ውጉዝነት ወይም ሊያርቁት የተገባ ነገር መሆኑን ያሳያል።

በነቢያቱ ዘመንም የወይን ጠጅ የተወገዘ ነበረ።

*ሆሴ. 4፥11 ግልሙትናና <u>የወይን ጠጅ፥ ስካርም አእምሮን ያጠፋል።</u>*

*አሞ. 12፥2 እናንተ ግን <u>ናዝራውያኑን የወይን ጠጅ አጠጣችኋቸው</u> ነቢያቱንም፥ ትንቢትን አትናገሩ ብላችሁ አዘዛችኋቸው።*

*ኢሳ. 28፥7 እነዚህም ደግሞ <u>ከወይን ጠጅ የተነሣ ይስታሉ፥ ከሚያሰክርም መጠጥ የተነሣ ይፋንናሉ ካህኑና ነቢዩ ከሚያሰክር መጠጥ የተነሣ ይስታሉ፥ በወይን ጠጅም ይዋጣሉ፥ ከሚያሰክርም መጠጥ የተነሣ ይፋንናሉ</u> በራእይ ይስታሉ፥ በፍርድም ይሰናከላሉ።*

የእግዚአብሔር አገልጋዮች የወይን ጠጅ ሰለባ ሲሆኑ ይስታሉ፥ ያስታሉ፥ ይጠፋሉ፤ ያጠፋሉ። በአዲስ ኪዳን አገልጋይና ተገልጋይ የሚባል መደብ ባለመኖሩ ሁላችንም ካህናት፥ ሁላችንም ጸጋን የተቀበልን አገልጋዮች ነን። ስለዚህ ራሳችንን ከነዚያ የብሉይ ኪዳን ሁነኛ አገልጋዮች እንደ አንዱ ብናደርግ ትክክል ነን። ደግሞም በአዲሱ ኪዳን ያለን እኛ ከነዚያ የምንለየው የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ በመሆናችን ነው።

ጠጥተው የሳቱና ከመስመር የወጣ ነገር ያደረጉ ወይም የተደረገባቸው በርካታ ምሳሌዎች ተሰጥተውናል።

ኖኅ አንዱ ነው። ኖኅ ጠጣ፥ ሰከረ፥ ዕራቁቱን ሆኖ እርቃኑ ታየ። አንድ የልጅ ልጁን ለእርግማን አሳልፎ ሰጠው።

*ዘፍ. 9፥ 20-21 እና 24 ኖኅም ገበሬ መሆን ጀመረ፥ ወይንም ተከለ። <u>ከወይን ጠጁም ጠጣና ሰከረ በድንኳኑም ውስጥ ዕራቁቱን ሆነ።</u> ኖኅም ከወይን ጠጁ ስካር ነቃ፥ ታናሹ ልጁ ያደረገበትንም አወቀ።*

ሎጥ ሌላው ነው። ሎጥ ሰከረ፤ ከሁለት ሴቶች ልጆቹ ጋር ተኛ፤ ሲተኛና ሲነሣ ወይም በመካከል የሆነውን ነገር አላወቀም።

ዘፍ. 19፥32-35 *ነዪ አባታችንንም <u>የወይን ጠጅ እናጠጣውና</u> ከእርሱ ጋር እንተኛ፥ ከአባታችንም ዘር እናስቀር። በዚያችም ሌሊት አባታቸውን <u>የወይን ጠጅ አጠጡት</u> ታላቂቱም ገባች፥ ከአባትዋም ጋር ተኛች <u>እርሱም ስትተኛና ስትነሣ አላወቀም።</u> በነጋውም ታላቂቱ ታናሺቱን አለቻት፦ እነሆ ትናንት ከአባቴ ጋር ተኛሁ ዛሬ ሌሊት ደግሞ <u>የወይን ጠጅ እናጠጣው</u> አንቺም ግቢና ከእርሱ ጋር ተኚ፥ ከአባታችንም ዘር እናስቀር። አባታቸውንም በዚያች ሌሊት ደግሞ <u>የወይን ጠጅ አጠጡት</u> ታናሺቱም ገብታ ከእርሱ ጋር ተኛች እርሱም <u>ስትተኛና ስትነሣ አላወቀም።</u>*

አርጤክስስ ሰክሮ ነበር። ይህ ንጉሥ ከመጠጡ በኋላ የሚስቱን ውበት ወደ አደባባይ ጠራ። ይህ ያልተለመደ ባህል ነበረ።

አስ. 1፥10-11 *በሰባተኛውም ቀን ንጉሡ አርጤክስስ <u>የወይን ጠጅ ጠጥቶ ደስ ባለው ጊዜ፥</u> ንግሥቲቱ አስጢን መልከ መልካም ነበረችና ውበትዋ ለሕዝብና ለአለቆች እንዲታይ የመንግሥቱን ዘውድ ጭነው ወደ ንጉሡ ፊት ያመጡአት ዘንድ በፊቱ የሚያገለግሉትን ሰባቱን ጃንደረቦች ምሁማንን፥ ባዛንን፥ ሐርቦናን፥ ገበታን፥ ዘቶልታን፥ ዜታርን፥ ከርከስን አዘዛቸው።*

የሚስቱ ፊት ብቻ እንዲታይ አይመስልም። ከዚያም ያለፈ ነገር እንደኖረ ይገመታል። ንግሥቲቱ ይህንን ጥሪ ያልተቀበለችው ዋጋ እንደሚያስከፍላት ሳታውቅ ቀርታ አይደለም። ኀፍረት ከንግሥትነት ዋጋ በላይ መሆኑን ስላወቀች ሳይሆን አይቀርም። ስካር እንዲህም ያደርጋል።

ብልጣሶር ሌላው የሰከረ ንጉሥ ነው። የወይን ጠጅ በቀመሰ ጊዜ የእግዚአብሔርን ንዋየ ቅድሳት ሊያረክስ ደፈረ።

ዳን. 5፥ 1-2፥4 እና 23 *ንጉሡ ብልጣሶር ለሺህ መኳንንቶቹ ትልቅ ግብዣ አደረገ፥ በሺሁም ፊት <u>የወይን ጠጅ ይጠጣ ነበር። ብልጣሶርም የወይን ጠጅ በቀመሰ ጊዜ ንጉሡና መኳንንቶቹ ሚስቶቹና ቁባቶቹ ይጠጡባቸው ዘንድ። አባቴ ናቡከደነፆር በኢየሩሳሌም ከነበረው መቅደስ ያመጣቸውን የወርቁንና የብሩን ዕቃዎች አምጡ ብሎ አዘዘ።</u> . . . <u>የወይን ጠጅም እየጠጡ ከወርቅና ከብር ከናስና ከብረት ከእንጨትና ከድንጋይ የተሠሩትን አማልክት አመሰገኑ።</u> . . . የመቅደሱንም ዕቃዎች በፊትህ አመጡ፥ አንተም መኳንንትህም ሚስቶችህም ቁባቶችህም <u>የወይን ጠጅ ጠጣችሁባቸው</u> ከብርና ከወርቅም ከናስና ከብረትም ከእንጨትና ከድንጋይም የተሠሩትን የማያዩትንም የማይሰሙትንም የማያውቁትንም አማልክት አመሰገንህ ትንፋሽህንና መንገድህን ሁሉ በእጁ የያዘውን አምላክ አላከበርኸውም።*

እነዚህን ሰዎች ስናይ በአስካሪ መጠጥ ግፊት ደፋሮች ሆነው ከመስመር የወጣ ነገር ሲያደርጉና ሲሆኑ እናገኛለን። ባይሰክሩ ኖሮ ምናልባት እንዲህ ያለውን ድፍረት ባላደረጉም ነበር። ስካር ያደፋፍራል፤ ደፋር ያደርጋል። የሌለ ወኔ ይሰጣል፤ የሌለ ጉልበት ይጨምራል። መጠጥ ኀፍረትን ያስወግዳል። ድፍረቱ ደግሞ ለመጥፎ ግብና ዓላማ ነው። በመጠጥ ኃይል ዓይን አፋሩ ዓይን አውጣ ይሆናል። ጭምቱ ይደነፋል፤ ፈሪው ፎካሪ ይሆናል። ምስጢር ብሎ የያዘውን ዝክዝክ አድርጎ ይዘረግፋል፤ ሆድ

ያባውን ብቅል ያወጣዋል እንዲሉ። አምስተኛው ነጥብ የወይን ጠጅ ወይም አስካሪ መጠጥ አስከፊ መልክ አለው የሚል ነው። 5ኛ ነጥብ።

6. የጠቢቡ ምክር

ጠቢቡ ንጉሥ ሰሎሞን ነው። ሰሎሞን ራሱ ወይንን የሚያውቅ፥ የወይን ጠጅን የቀመሰ፥ ያጣጣመ፥ የጠጣ፥ ሰውነቱን በወይን ጠጅ ያስደሰተ ሰው ነውና በመጽሐፈ ምሳሌ እና መጽሐፈ መክብብ ውስጥ የሰጣቸው ምስክርነቶችና ምክሮች የንድፈ አሳብ ብቻ ሳይሆኑ ከጠንካራ የሕይወት ልምምድ የተገኙ ናቸው።

> መክ 2፥3 *የሰው ልጆች በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ ከፀሐይ በታች ሊሠሩት መልካም ነገር ምን እንደ ሆነ እስካይ ድረስ ልቤ በጥበብ እየመራኝ፥ ሰውነቴን በወይን ጠጅ ደስ ለማሰኘት ስንፍናንም ለመያዝ በልቤ መረመርሁ።*
>
> ምሳ. 20፥1 *የወይን ጠጅ ፌዘኛ ያደርጋል፥ ብርቱ መጠጥም ጠበኛ ያደርጋል በዚህም የሳተ ሁሉ ጠቢብ አይደለም።*
>
> ምሳ. 21፥17 *ተድላ የሚወድድ ድሀ ይሆናል፥ የወይን ጠጅንና ዘይትንም የሚወድድ ባለጠጋ አይሆንም።*
>
> ምሳ. 23፥20 *የወይን ጠጅ ከሚጠጡ ጋር አትቀመጥ ለሥጋም ከሚሣሡ ጋር።*
>
> ምሳ. 23፥29-35 *ዋይታ ለማን ነው? ኀዘን ለማን ነው? ጠብ ለማን ነው? ጩኸት ለማን ነው? ያለ ምክንያት መቍሰል ለማን ነው? የዓይን ቅላት ለማን ነው? የወይን ጠጅ በመጠጣት ለሚዘገዩ አይደለምን? የተደባለቀ የወይንን ጠጅ ይፈትኑ ዘንድ ለሚከተሉ አይደለምን? ወደ ወይን ጠጅ አትመልከት በቀላ ጊዜ፥ መልኩም በብርሌ ባንጸባረቀ ጊዜ፥ እየጣፈጠም በገባ ጊዜ፥ በኋላ እንደ እባብ ይነድፋል፥ እንደ እፉኝትም መርዙን ያፈስሳል። ዓይኖችህ ጋለሞታዎችን ያያሉ፥ ልብህም ጠማማ ነገርን ይናገራል። በባሕር ውስጥ እንደ ተኛ ትሆናለህ፥ በደቀልም ላይ እንደ ተኛ። መቱኝ፥ ያውም አልተሰማኝም ጐሰሙኝ፥ አላወቅሁምም። መቼ እነሣለሁ? ደግሞ ጨምሬ እሻታለሁ ትላለህ።*
>
> ምሳ. 31፥4-6 *ለነገሥታት አይገባም፥ ልሙኤል ሆይ፥ ነገሥታት የወይን ጠጅ ይጠጡ ዘንድ አይገባም። መሳፍንትም፥ ብርቱ መጠጥ ወዴት ነው? ይሉ ዘንድ። እንዳይጠጡና ሕግን እንዳይረሱ፥ የድሀ ልጆችንም ፍርድ እንዳያጐድሉ። ለጥፋት ለቀረበው ሰው ብርቱ መጠጥ ስጡት፥ ነፍሱ ለመረረውም የወይን ጠጅ ስጡት። ይጠጣ ድህነቱንም ይርሳ፥ ጕስቍልናውንም ከእንግዲህ ወዲህ አያስብ።*

መጽሐፍ ቅዱስ መስከርን መከልከሉ እውነት ነው። 'የወይን ጠጅ መጠጣትን አይከለክልም' ብሎ ለመጠጣት ከመጋበዝ ይልቅ፥ አለመምከሩንና አለማደፋፈሩን ማጉላቱ አግባብ አይሆንም ወይ? ይህ ክፍል አለመምከርንና አለማደፋፈርን ብቻ ሳይሆን አለመጠጣትንም ብቻ ሳይሆን አለማየትንም ሲመክር ይታያል። 'አትጠጣ' ብቻ ሳይሆን 'ወደ ወይን ጠጅ አትይ! አትመልከት፤ ከሚጠጡት ጋርም አትቀመጥ።'

ነው ያለው። ስለዚህ 'ቃሉ አትስከር ነው የሚለው እንጂ አትጠጣ አይልም' ለሚሉት 'አትስከር ብቻ ሳይሆን አትመልከት፤ ከጠጪዎች ጋርም አትቀመጥም ይላል' ማለት ትክክለኛ መልስ ሊሆን አይችልም? ይችላል።

የመጠጥን መዘዞችና ውጤቶች ሲዘረዝር ዋይታ፥ ኀዘን፥ ጠብ፥ ጩኸት፥ መቁሰል፥ የዓይን ቅላት፣ ጋለሞታን ማየት፥ ጠማማ ነገርን መናገር፥ ፌዘኛ መሆን፥ ጠበኛ መሆን፥ ሕግን መርሳት፥ ፍርድን ማጉደል፥ ድኃ መሆን አሉበት። ይህ እንግዲህ ከዚህ ክፍል ብቻ፥ ከላይ ከተጠቀሱት አራት ክፍሎች ብቻ ነው።

አንዳንድ የመጠጥ ተመርኳዦች፥ 'አልኮል ለሥርዓተ-ሰውነታችን ያስፈልገዋልና ስለዚህ መጠጣት ጥቅም አለው' ይላሉ። የሕክምና ጠበብት ትንታኔን ከተከታተልን ግን፥ ሰውነታችን ከምንወስደው ከማናቸውም ሙብልና መጠጥ የሚያስፈልገውን ሁሉ መቀመም የሚችል ተፈጥሮ እንዳለው ይነግሩናል። እነዚሁ የሕክምና ሊቃውንት የሰውነትን አሠራር ለመርዳት አልኮልና አስካሪ መጠጥ በምንም መንገዱ መውሰድ ግን ጉዳቱ ብዙ መሆኑንም በግልጽ ያስረዱናል። የዘመናችን ጠቢባንም ከጠቢቡ ምክር ጋር ስምም ናቸው ማለት ነው። ስለዚህ ከመጠጥ አፍቃሪ ሰካራሞችና ከዶክተሮች ምክር የቱ ይመረጣል? ግልጽ ነው። ከሁለቱም ምክር ደግሞ የበለጠው የቃሉ ምክር ነው።

ለጥፋት የቀረበው ግን እንዲጠጣ መመከሩ ከጥፋት፥ ጥፋት የሚለው ቃል ይህንም የሚያሳይ ነውና ራሱን ከማጥፋት ወይም ከመግደል እንዲታቀብ ይመስላል። ሰክሮ ጉስቍልናውን ይርሳ የተባለው ሰው ቀድሞውኑ ጐስቋላ ሰው ነውና ራስን ማጥፋት ደግሞ ከጉስቍልና የከፋ ነው። መጠጥ ለጊዜው ያ ሰው ራሱን እንዳያጠፋ ይከላከልለታል እንጂ ዘላቂ መፍትሔ አይደለም። ለጊዜውም ቢሆን ራሱን ከማጥፋት ከተከላከለለት መጠጣቱና መስከሩ፥ ከገሃዱ ዓለም ወደ ምናባዊው ዓለም መሻገሩ፥ ዕድሜው ረዝሞለት በቀጣዩ ቀን እንደገና ወደ እውኑ ዓለም ሲመለስ ወደ ልቡናው እንዲመለስ ዕድል እንዲያገኝ ይረዳዋል።

## 7. የጌታ ምሳሌነት

ቀደም ሲል ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ መለወጡን አይተናል። ምን ብቻ ሳይሆን፥ ለምን እንዳደረገም ታሪኩን ተመልክተናል። ጌታ እየበላና እየጠጣ መምጣቱን ተናግሮአል። ይህ ከመጥምቁ ዮሐንስ ጋር ራሱን በማነጻጸር የዘመኑን አይሁድ ለመውቀስ የተናገረው ነው እንጂ በዋናነት አስካሪ መጠጥ መጠጣትን ለማደፋፈር ማስታወቂያ እየተናገረ አይደለም።

> ማቴ. 11፥19 *የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጣ፥ እነርሱም፦ እነሆ፥ በላተኛና የወይን ጠጅ ጠጭ፥ የቀራጮችና የኃጢአተኞች ወዳጅ ይሉታል። ጥበብም በልጆችዋ ጸደቀች።*

> ሉቃ. 7፥33-34 *መጥምቁ ዮሐንስ እንጀራ ሳይበላ የወይን ጠጅም ሳይጠጣ መጥቶ ነበርና። ጋኔን አለበት አላችሁት። የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጥቶአልና።*

> *እነሆ፥ በላተኛና <u>የወይን ጠጅ ጠጭ፥</u> የቀራጮችና የኃጢአተኞች ወዳጅ አላችሁት።*

ትኩረቱ የእርሱ መብላትና መጠጣት ላይ ሳይሆን የሰዎቹ እርሱን አለመቀበል ነው። ይሁን እንጂ፥ እየበላና እየጠጣ መጥቶአል። የወይን ጠጅ ጠጭ ያሉት ግን እነርሱ እንጂ ጌታ ራሱን አይደለም እንደዚያ ያለው። እየጠጣ የመጣው ወይን ይሁን ወይን ጠጅ አናውቅም። ዮሐንስ ምንም አልጠጣም ነበርና። ይህንን ቀደም ሲል ስለ ናዝራውያን ስንመለከት አይተናል። ኢየሱስ ናዝራዊ ተብሎአል፤ ግን ናዝራዊነቱ እንደ ብሉይ ኪዳን ናዝራዊነት ሳይሆን በናዝሬት ያደገና የኖረ ስለሆነ ነው ናዝራዊ የተባለው።

ጌታ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የመጨረሻ ራቱን በበላ ጊዜ ጽዋን አንሥቶ አመስግኖ እንዲጠጡ ሰጣቸውና እንዲህ አላቸው፤

> ማቴ. 26፥29 *ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር <u>ከዚህ ከወይን ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት</u> እስከዚያ ቀን ድረስ ከዛሬ ጀምሬ አልጠጣውም።*

ይህም ወይን ወይም እዚህ፥ ‘የወይን ፍሬ’ የተባለው የወይን ጠጅ እንደሆነ መገመት እንጂ እርግጥ ነው ብለን መናገር አንችልም። አስካሪ መጠጥ ከቶም ሊሆን አይችልም። አይችልም የምለው፥ ከዚህ በኋላ ጌታ ወደ ጌቴሴማኒ ሊሄድ ነውና፥ ይህንን ደግሞ ራሱም ያውቀዋልና፥ እንደሚሄድ ብቻ ሳይሆን ለምን እንደሚሄድም ያውቀዋልና፥ ይህንን የመጨረሻ ገድል በተበረዘ አእምሮ፥ በሰከረ ሰውነት ሊጋደል ነው ብንል በመስቀሉ ሥራ ላይ ሰይፍ መምዘዝ ይመስላል።

በመስቀል ላይ ሳለ የወይን ጠጅ ቀርቦለት ነበር፤ አልተቀበለም።

> ማቴ. 27፥34 *በሐሞት የተደባለቀ <u>የወይን ጠጅ ሊጠጣ አቀረቡለት፤ ቀምሶም ሊጠጣው አልወደደም።</u>*

> ማር. 15፥23 *ከርቤም የተቀላቀለበትን <u>የወይን ጠጅ እንዲጠጣ ሰጡት፤ እርሱ ግን አልተቀበለም።</u>*

ወይኑ በሐሞት እና/ወይም ከርቤ የተቀላቀለ ነው። አንዱ ወንጌል ሐሞት ሲለው፥ ሌላው ከርቤ ይለዋል። ምናልባት ሁለቱም የተቀላቀሉበት ነው። ጌታ ለምን ሊጠጣው አልወደደም? ወይም ለምን አልተቀበለውም? ይህ የተቀላቀለ መጠጥ አስካሪና ምናልባት አስካሪ መጠጥ ብቻ ሳይሆን አደንዛዥ መድኃኒትም ነው። የሚሰቀሉ ሰዎች ሕመማቸው እንዳይሰማቸው ሰውነታቸው እንዲደነዝዝ የሚቀርብላቸው መጠጥ ነው። ጌታ ይህንን አልወሰደም፤ አልጠጣም። ወሰደ ብንል አበሳችንን በደነዘዘ አካሉ ተሸከመ ልንል ነው። አላደረገውም። ቃሉም በግልጽ ጌታ ይህን መጠጥ እንዳልወሰደ በግልጽ ጽፎልናል። በመስቀል የሚሰቀሉ ሰዎች የሚስገበገቡለት ነገር ቢሆንም እንኳ ጌታ ግን ይህን ሊያደርግ አልወደደም። ይህች የመጨረሻዋ ድነታችንን ሊፈጽም የመጣባት ሰዓት ናትና።

8. የጳውሎስ ትምህርት

ስምንተኛውና የመጨረሻው የጳውሎስ ትምህርት ነው። ጠጪዎች ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤጲስ ቆጶሳት መስፈርት ሲዘረዝር 'የማይሰክር' ማለቱ (1ጢሞ. 3፥3) 'መጠጣት ይችላሉ መስከር ግን አይችሉም ማለት ነው' ይላሉ። ይኸው አባባል 'መስከር ማለት መጠጣት ማለት ነው' ካሰኘ፥ አለመስከር ማለት ደግሞ፥ 'ጨርሶ የማይጠጣ ማለቱ ነው' ሊባል እንደሚችልም ሊጤን የተገባ ነው። የሚሰክር የሚጠጣ ከሆነ፥ የማይሰክር የማይጠጣ ለምን አይሆንም?

ስለ ዲያቆናትም እንዲህ አለ፤

> 1ጢሞ. 3፥8 *እንዲሁም ዲያቆናት ጭምቶች፥ በሁለት ቃል የማይናገሩ፥ ለብዙ ወይን ጠጅ የማይጎመጁ፥*

አሁንም ጠጪዎች፥ 'ብዙ የወይን ጠጅ ነው የተባለውና ብዙ አይሁን እንጂ ጥቂትስ ይፈቀዳል ማለት ነው' ይላሉ። ብዙ ማለት ስንት ዋንጫ ነው? ጥቂትስ ስንት ጽዋ ወይም ስንት መለኪያ ነው? ብዙና ጥቂትን ለኪውና ወሳኙስ ማን ነው? ላንተ ሁለት ጽዋ ብዙ ከሆነ ለኔ አራት ዋንጫም ጥቂት ቢሆንስ? እኔ አራት ፋጋ ስጠጣ ያየ ሌላው ያንን ቁጥር መነሻው ቢያደርገውስ? ለኪውና ወሳኙ ማን ነው? ጠጪው ራሱ? ወይስ ቤተ ክርስቲያን ውስጠ ደንብ አውጥታ፥ 'ሁለት ብርጭቆ፥ ሦስት ብርሌ፥ አራት መለኪያ' ማለት አለባት?

ለጢሞቴዎስ ስለሆዱ ሕመም የተነገረውስ?

> 1ጢሞ. 5፥23 *ስለ ሆድህና ስለ በሽታህ ብዛት ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣ እንጂ፥ ወደ ፊት ውኃ ብቻ አትጠጣ።*

ይህ ለአንድ ጢሞቴዎስ ለተባለ ሰው፥ ለዚያውም ለሆዱ ሕመም የተነገረ ነውና እንደ ደንብ ወይም የፈቃድ ወረቀት መታየት አይገባውም። ጳውሎስ ሐኪም አይደለም፤ ግን ሐኪም የሆነው ሉቃስ አብሮት ነበረና የእርሱ ምክር ወይም ትእዛዝ እንደሆነ መገመቱ ከትክክል የራቀ አይመስለኝም። የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት የሚሉት ውኃው የሆድ ሕመም ፈጣሪ ተዋኃስያን ስለሚኖሩት ምናልባት በውኃው ውስጥ ወይም ያለ ውኃው ጥቂት የወይን ጠጅ እንዲጠጣ ተነገረው።

የዘመናችን መፍቀሬ መጠጦች ይህንን ጥቅስ ለመጠጥ መደጎሚያ ብርቱ መከራከሪያ ሲያደርጉት ያንን መምሰል አለባቸው ማለት ነው። እና አንደኛ፥ የሆድ ሕመምተኞች ናቸው? ሁለተኛ፥ ንጹሕ ውኃ ማግኘትና መጠጣት በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ ነው የሚገኙት? ሦስተኛ፥ ደግሞስ የቱ ሐኪም ነው ያዘዛቸው? የዘመናችን ሐኪሞች ለውኃችን ክሎሪን ወይም ለሆድ ሕመማችን ሌላ መድኃኒት እንድንወስድ ይነግሩናል እንጂ የወይን ጠጅን እንደ መድኃኒት ከቶም አያዝዙም። ሐኪሞች ከአስካሪ መጠጥ እንድንርቅ ያበረታቱናል እንጂ እንድንቀርብ አያደፋፍሩንም። ስለዚህ ለጢሞቴዎስ

ወይን ታዟልና እኛንም ይመለከተናል የሚሉ ሰዎች በጢሞቴዎስ ስፍራ መገኘት አለባቸው ማለት ነው።

ወይንን በተመለከተ የጳውሎስ ሁለት ዐበይት ምክሮች እነዚህ ናቸው፤ አንደኛ፥ በወይን ጠጅ መስከር በወይን ጠጅ ቁጥጥር ስር መሆን ነው። በመንፈስ ቅዱስ መሞላትም በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር መሆን ነው።

> ኤፌ. 5፥18 *መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ <u>በወይን ጠጅ አትስከሩ</u> ይህ ማባከን ነውና፤*

ቁጥጥር ቁጥጥር ነው። ትንሽ ከጠጣን በጥቂቱ ይቆጣጠረናል። በብዙው ከጠጣን በብዙው ይቆጣጠረናል። አሁንም የቁጥጥሩን መጠን ወሳኙ ማን ነው? የማይታወቅ የቁጥጥር ድንበር ከሚበጅ ጭራሽ ቢቀርስ? እውነትም በወይን ጠጅ መስከር ማባከን ነው፤ ገንዘብን፥ አእምሮን፥ ኅሊናን፥ ትዳርን፥ አካልን፥ ወዳጅነትን፥ ጓደኝነትን፥ ክብርን፥ ስምን፥ አገልግሎትን ማባከን ነው።

ሁለተኛ፥ የኛ መኖር ሌላውን ማነጽ እንጂ ማፍረስ መሆን የለበትም። መደገፍ እንጂ ማሰናከል የለበትም።

> ሮሜ. 14፥21 *ሥጋን አለመብላት <u>ወይንንም አለመጠጣት ወንድምህም የሚሰናከልበትን አለማድረግ መልካም ነው።</u>*

ሌላውን ሰው ላለማሰናከል ሥጋ ከቶ ስላለመብላት ከተነገረ ወይን ከቶውኑ ባይጠጣስ? ቢቀርስ? በመጽሐፈ ምሳሌ እንደተጻፈው አለመጠጣት ብቻ ሳይሆን ባይታይስ? ወይንን መጠጣት ለራሳችን ደስታ ብለን የምናደርገው ከሆነ አለመጠጣት ለሌላው ጥንቃቄ የምናደርገው ነው ማለት ነው። የዚህች ምድር ኑሮአችን የክርስቶስን ፈለግ የምንከተልበት ከሆነ እርሱ ራሱን ለማስደሰት እንዳልጣረ እኛም ሌሎች እንዳይሰናከሉ ብለን ብንኖርስ?

ይህንን ትምህርት ሳጠቃልለው፥ የአዲስ ኪዳን አማኞች ከወይን ጠጅ የምንታቀበውና የምንርቀው 'አትጠጡ፥ አትቅመሱ፥ አትንኩ' የሚል ትእዛዝ ተቀብለን ሳይሆን፥ በነዚህ ምክንያቶች ነው።

1. አልኮል ምንም ሁነኛ ጥቅም ስለሌለው ነው። አንዳንዶች፥ 'ለአካላችን የተወሰነ የአልኮል መጠጥ እንደሚያስፈልገው በሳይንስ የተረጋገጠ ነው።' ይላሉ። ሳይንሱን ወይም ሳይንቲስቱን ወይም ሐኪሙን ግን አይጠቅሱም። ይልቅስ የዚህ ተቃራኒ፥ ባለመጠጣታችን የሚደርስብን ጉዳት የለም የሚል ነው።

2. በአካልና በአካል ብልቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳትና ጠንቅ ስለሚያስከትልና አካላችን ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ስለሆነ፥ በክብካቤም መጥጠበቅ ስላለበት ነው። አካላችን ከአስካሪ መጠጥ ብቻ ሳይሆን ከአደንዛዥም ከአነቃቂ ዕጾችና

መድኃኒቶችም መጥጠበቅ አለበት። አስካሪ መጠጥ በአካላችን ብቻ ሳይሆን በግንኙነቶቻችን እና በንብረታችን ላይም ክፉ ተጽዕኖ ያመጣል።

3. መጠጥ ተቆጣጣሪ ኃይል አለው፤ እኛ ለአርነት ተጠራን እንጂ በምንም ነገር ቁጥጥር ስር ወይም የምንም ሱስ ተገዥ መሆን የተገባን አይደለንም።

4. ሌላው በኅሊና ሊጎዳበትና በመንፈሳዊ ጉዞውም ሊሰናከልበት ስለሚችል ነው። አስካሪ መጠጥን በመጠጣት ሌላ ሰው የሚፈርስበት እንጂ የሚታነጽበትን ምንም ነገር ማድረግ አይቻልም። ስንጠጣ ቢያየን ለመጠጣት ይደፍራል። ወደ እስራትም ይሄዳል።

5. አስካሪ መጠጥን በመጠጣት እግዚአብሔርን የሚያስከብር ምንም ነገር ማድረግ አይቻልም። የምናደርገውን ነገር ሁሉ ደግሞ <u>በጌታ ስም ለእግዚአብሔር ክብር</u> እንድናደርግ ተነግሮናል። በየቀኑ የምናደርገው ተደጋጋሚ ነገር እንኳ እንደዚያ ሊሆን ነው የተነገረን። 1ቆሮ. 10፥31 *እንግዲህ የምትበሉ ወይም <u>የምትጠጡ</u> ብትሆኑ ወይም ማናቸውን ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት።* የምንበላው፥ <u>የምንጠጣውም</u> ለጌታ ክብር መሆን አለበት። ምንድነው የምንጠጣው? ማለት፥ ለጌታ ክብር የምንጠጣው? አስካሪ መጠጥን ለጌታ ክብር ልንጠጣ እንችላለን? ወይም በሌላ አገላለጥ፤ አስካሪ መጠጥ ጠጥተን ጌታን ልናከብርበት እንችላለን?

እኛ ክርስቲያኖች የማንጠጣው፥ ወይም መጠጣት የሌለብን በነዚህ ምክንያቶች ነው።

## ምዕራፍ ፳፤

# ክርስቲያንና ቁማር

ቁማር ኃጢአት ነው? በአሜሪካ የቁማር ዋና ከተማ በሆነችው በላስ ቬገስ እንደኖረ ወይም እንደሚኖር ሰው በዚህ ጉዳይ ላይ በጣም ሰፊና ጥልቅ ምርምር ባላደርግም በመጠኑም ቢሆን መናገር የምችል ይመስለኛል። ወደዚህች ከተማ ከመጣሁ በኋላ ስለዚህ ጉዳይ አንድ ቀን እንደምናገር ሳስብና ሳሰላስል ቆይቻለሁ።

አሜሪካ ውስጥ በሕጋዊ ቁማር የሚታወቁት ሁለት ትልልቅ ከተሞች ላስ ቬገስ እና አትላንቲክ ሲቲ የሚባሉት ከተሞች ናቸው። በሁለቱ ታላላቆች መካከል በጣም ብዙ የቁማር ከተሞች ይገኛሉ፤ ብዙዎቹ 'ሕንዳውያን' በሚባሉት በመጀመሪያዎቹ የአገሪቱ ሕዝቦች ይዞታ (reservation ወይም ካናዳ ውስጥ reserve ይሉታል) ውስጥ የተገነቡ መቆመሪያዎች ናቸው። ቀድሞ በግድ መሬታቸውን ስለወሰዱባቸው ከቀረጥና ከግብር ነፃ ሆኖ የተሰጣቸው መሬት በመሆኑ የፈለጉትን እንዲያደርጉበት መብት ያላቸው ይዞታም ስለሆነ፥ በሕግ ሳይታገዱ ወይም ሕግ ሳያግዳቸው ምንም ነገር ማድረግ ይችላሉ። እና አንዳንዶቹ የቁማር መቆመሪያዎች እነዚህ ቦታዎች ላይ ተሠርተዋል። ላስ ቬገስ ግን ታዋቂዋ የአሜሪካ የቁማር ዋና ከተማ ናት።

በጉዳዩ ላይ በተለይም ከቅርብ ወራት ወዲህ በተለያዩ ጊዜያት ብዙ ጥያቄዎችም ደርሰውኛል። ለምሳሌ፥ ቁማር መቆመር ኃጢአት ነው ወይ? እንዴት? ገንዘብ አስይዞ መወራረድስ? ሎተሪ መግዛትስ? ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ለማሠራት ዕቃዎች ገዝታ ቶምቦላ ብትሸጥስ ይህስ ኃጢአት ነው? ካርታ መጫወትስ? ወዘተ፥ የሚሉ ይገኙበታል። በጊዜው ረዘም ያሉ የተሟሉ መልሶች መስጠት ባለመቻሌ፥ በአጭሩ መልሼ፥ አንድ ቀን በሰፊው እንደምመለስበት ስናገር ቆይቻለሁ። ለብዙዎቹ የምመልስላቸው አጭሩ መልሴ፥ አንድ ቀን በስፋት እመጣበታለሁ። እስከዚያ ግን በአጭሩ፥ አዎን፥ ቁማር ኃጢአት ነው። እምነትን ከእግዚአብሔር ወስዶ ዕድል ወይም ገድ ወደሚባል ጣዖት የሚወስድ ኃጢአት ነው የሚል ነው። እዚህ የማቀርበው የሰፊው መልስ እጥርጥር ያለው መልስ ይኸው ነው፤ ቁማር ኃጢአት ነው።

ይህንን መልስ ሳዘጋጅ ካሲኖዎችን ወይም መቆመሪያዎችን ጎብኝቻለሁ። ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ቬገስ የመጣሁ ጊዜ ጓደኞቼ ወስደውን፥ በጥቂት ሳንቲሞች ተጫውቻለሁ።

ሳንቲሞች ነው፤ ብሮች አላልኩም። ምን እንደሚመስል ለማየት፤ ተበላሁ፤ አልቀጠልኩም። ባሸንፍ ወይም ብበላ ኖሮ እቀጥል ነበር? አላውቅም፤ ግን አይመስለኝም። አስቀድሜም ስለ ቁማር በቂ እውቀት ስላለኝ አልቀጥልም። ኋላ አነሣዋለሁ፤ ቁማር ሱስም ይሆናል። እና ሱስ እስኪሆን ብጫወትስ? 'ብጫወት' ከማለት ብቆምር ማለቱ ይሻላል፤ መጫወት ሲባል ጨዋታ ይመስላል፤ ቁማር ጨዋታ አይደለም። እና ሱስ ቢሆንስ መላቀቅ እችላለሁ? እዚህ ላይ ነው አደጋው። እመለስበታለሁ።

ይህንን ትምህርት በማዘጋጅበት ጊዜ ስለ ጉዳዩ መጣጥፎችን አንብቤአለሁ፤ ትርጉሞችን ፈልጌአለሁ፤ መርምሬአለሁ፤ ስብከቶችን ሰምቻለሁ፤ ስለ ቁማር ምንነት እንዳውቅ ረድተውኛል። በተለይ ጆን ማካርተር በጉዳዩ ላይ በ1995 የሰበካቸው ሁለት ተከታታይ ስብከቶች ሰምቻለሁ። ያኔ ለትምህርት መጥቼ ወደ አገር ቤት ከመመለሴ በፊት ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማኋቸው። ደግሜ የማገኛቸው አልመሰለኝም ነበር። ስለ ቴክኖሎጂ ጌታ ይመስገን፤ ፈልጌ አገኘኋቸው፤ እንደገና ደጋግሜ ሰማኋቸው።

ከዚህ ሌላ፥ ነገሩን በቅርብ ለማወቅ ቁማር የሚያስቆምሩ አስቆማሪዎችን አነጋግሬአለሁ። የተበሉቱ ንብረታቸውን ወስደው የሚሸጡባቸውን pawn shops ጎብኝቻለሁ። መጎብኘት ብቻ ሳይሆን ከሳሪዎቹ ሰዎች ሲሸጡም አይቻለሁ። ክቡር ዕቃን በርካሽ ዋጋ ነው የሚሸጡት።

አንዳንድ ሰዎች ቁማርን ምንም እንዳልሆነ፥ እንደ ጨዋታ ብቻ ያዩታል። መጫወት ሲባልም እውነትም መጫወት ብቻ ይመስላል። መጫወት ስንል ቃሉ ነገሩን ራሱን ያቀልለዋል። ለነዚህ ጨዋታ ነው። ሌሎች ደግሞ ለቅሶ ቤት ካርታ መጫወትን/መቆመርን እንኳ እንደ ነውርና እንደ ኃጢአት ያዩታል። አንዳንዶች በሁለቱ አቋሞች መካከል ሆነው ይዋልላሉ። 'ቁማር ኃጢአት ነው? ወይስ አይደለም?' ከመባሉ በፊት፥ 'ለመሆኑ ቁማር ምንድር ነው?' ብሎ መጠየቅ ይቀድማል። በዚህች ከተማ ስለኖርኩ ወይም ስለ ጉዳዩ ስለተጠየቅሁ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል ስለዚህ ጉዳይ የሚለው ስላለው፥ አዎን ስላለው በጉዳዩ ላይ መናገር ተገቢ ነው። ማንም አገልጋይ ስለዚህ ጉዳይ ሳይንተባተብ በግልጽ መናገር አለበት ብዬ አምናለሁ። መናገር እንኳ ባይችል ማወቅ አለበት።

አሁን በዘመነው ዓለም ቁማር ለመቆመር ሰዎች በአካል ቁማርን በሕጋዊነት ወደሚቆምሩባቸው ከተሞች መሄድ የለባቸውም። ብዙዎች ወደዚህች ወዳለንባት ከተማ ለመቆመር ይመጣሉ። በኮቪድ ዝግ እንኳ በ2020 ብቻ በጉብኝት 19 ሚሊየን ሰዎች ወደ ላስ ቬገስ እንደመጡ ተመዝግቧል። ከኮቪድ በፊት በዓመት በአማካይ 42 ሚሊየን ጎብኚዎች ይመጡ እንደነበር ተመዝግቧል። ወደ አንዲት ከተማ ነው ይህ ሁሉ ሕዝብ የሚመጣው። ይህ የአንዲት ከተማ መልክ ብቻ ነው። እርግጥ ነው የሚመጡት ሁሉ የሚመጡት ለመቆመር ነው ማለት አይደለም። ትልልቅ ስብሰባዎች ይደረጉባታል። በዓለም አንደኛዋ የሆቴሎች ክፍሎች ብዛት ያለባት ከተማ ናት። ከተማዋ ከ150 ሺህ በላይ የሆቴል ክፍሎች አሏት። አንዱ ትልቁ ሆቴል 5ሺህ 44 ክፍሎች አሉት። እስከ 12 ሽህ ሰዎች በአንዴ ማስተናገድ ይችላል። ሁሉ ለመቆመር ባይመጡም የከተማዋ መታወቂያ ነውና ሳይቆምሩ የሚመለሱ ብዙ አይደሉም።

በአሜሪካ ሙሉ በሙሉ ምንም ዓይነት ቁማር፥ ሎተሪንም ጨምሮ የማይፈቀድባቸው ሁለት ግዛቶች ብቻ ናቸው፤ Utah እና Hawaii። የቀሩት በአንድ መልኩ ወይ በሌላው ይፈቅዳሉ። በ2021 የአሜሪካ መንግሥት ከቁማር ቀረጥ ያገኘው ገቢ $44 ቢሊየን ዶላር ነው። ሚሊየን ሳይሆን ቢሊየን! የኒቫዳ መንግሥት በ2021 $3.5 ቢሊየን አግኝቷል። ከላይ ከተባሉት ከሁለቱ በቀር፥ እያንዳንዱ ግዛት የራሱ የቁማር ቀረጥ ገቢ አለው። ልብ እንበል ይህ ለቁማር የወጣው ገንዘብ ሳይሆን ለቁማር ከወጣው ገንዘብ የተገኘ የመንግሥት <u>ቀረጥ</u> ነው። ቀረጥ ብቻ። ለዚያውም በሕግ የታወቀው ብቻ።

$44 ቢሊየን ማለት በኢትዮጵያን የዓመት በጀት ሲሰላ የ3 ዓመት ተኩል በጀት ማለት ነው። የኢትዮጵያ የ2021-2022 በጀት 561.67 ቢሊየን ብር ወይም $12.9 ቢሊየን ዶላር ነው። $44 ቢሊየንን በ10% ታክስ ብናሰላው ቢያንስ $440 ቢሊየን በዓመት ተቆምሯል ማለት ነው። ይህ በጣም በስሱ ሲሰላ ነው። ያውም የሰው እንቅስቃሴ እና የኢኮኖሚ አቅም በብዙ መጠን በተገደበበት በኮሮና ጊዜ ነው ይህ የገባው። ደግሞም ይህ ከሕጋዊው ቁማር ብቻ ነው። ሕጋዊ ያልሆነው ገንዘብ ሲታከልበት በትሪሊየን የሚቆጠር ነው ይባላል። ገና በ1990ዎቹ መጨረሻ (ከ20 ዓመት በፊት ማለት ነው፤) እስከ 1ትሪሊየን በዓመት ይቆመር እንደነበር የተሰላ ግምት አለ። ቁማር ደግሞ በፍጥረቱም ቁማር ነውና የማይታይ ብዙ ገንዘብ ይወጣበታል። ከቤት ሳይወጡ ኦንላይን ገብቶ በኢንተርኔት መቆመር፥ መብላትና መበላት በጣም የተለመደ ሆኗል።

ቁማር ዓይነቱ ብዙ ነው። ለዕርዳታ ወይም በጎ አድራጎት የሚደረግ ዕጣ አለ፤ ራፍል ይሉታል ወይም ቶምቦላ፥ የስፖርትና እሽቅድድሞች ውርርድ፥ ሎተሪ፥ ገንዘብ ወይም ቺፕስ አስይዘው የሚቆምሩት የካርታና መሰል ቁማር፥ በዓይነት ብዙ የሆነ የኢንተርኔት ቁማር፥ ሌሎችም አሉ። አስቆማሪ ሰው የማይፈለግበትና በኮምፒዩተር የሚታገዙት slot machine በጣም የተለመደው መጫወቻ ነው። እነዚህ መጫወቻዎች ከትንንሽ ሳንቲሞች እስከ ብሮችና ክሬዲት ካርዶች የሚቀበሉ መቆመሪያዎች ናቸው። በኮምፒዩተር ስለሚታገዙ ቁማሩ ራሱ እዚያ ውስጥ ነው። በነዚህ የኮምፒዩተር መቆመሪያ ሳጥኖች አቋማሪው ኮምፒዩተር ነው፤ ምን ማድረግ እንዳለበት አስቀድሞ ፕሮግራም ተደርጓል። ይህኛው ሰው አይቁምለት እንጂ ብዙዎቹ ቁማሮች በሰዎች የሚደረጉ በመሆናቸው ብዙ መቶ ሺህ ተቀጣሪዎች ያሉበት ትልቅ ኢንዱስትሪም ነው ቁማር።

ከቁማር አደጋዎች መካከል አንዱ ቀደም ሲል ያልኩት ጨዋታ መባሉ፥ ጨዋታ መምሰሉና አደጋ አለመምሰሉ ነው። ወይም ተቀባይነት ያገኘ ጎጂ ልማድነቱ ነው። ጉዳት አይመስልም። ኃጢአትም አይመስልም። በአማካይ ሰው የሚጠቀምበት ቃል ራሱ መቆመር ሳይሆን መጫወት ነው። አንዳንዶችም እንደ ጨዋታ ነው የሚያዩትና የሚቆጥሩት። ሎተሪ ያልተጫወተ ወይም ያልቆረጠ ሰው ይኖር ይሆን? ሕንጻ ለማሠራት አብያተ ክርስቲያናት ለአሸናፊዎች መኪና፥ ሞተር ቢስኪሌት፥ ቲቪ፥ ወዘተ፥ የሚሰጥበት ቶምቦላ አዘጋጅተው የሸጡ የሉም? ለማኅበረ ሰብ ግንባታ፥ በአንዳንድ መንግሥታት፥ 'የበጎ አድራጎት ቁማር' የሚባለው ውስጥ ታሳታፊ የሆኑ የመንግሥት ቢሮዎች የሉም? አሉ፤ ይህ እውነት ነው።

ቁማር ኃጢአት ነው፤ በሦስት ምክንያቶች ኃጢአት ነው፤ ሦስቱንም ልናገርና በዝርዝር እሄድባቸዋለሁ።

1. ጤናማ ባለ አደራነት ወይም መጋቢነት አይደለም።

2. በእግዚአብሔር መታመንን ወይም መደገፍን አእምሮን መጠቀምንም ከስፍራው የሚያስወግድ ነው።

3. ዕድል ወይም ገድ (መጽሐፍ ቅዱስ ጉድ ይለዋል) የሚባሉ አማልክትን ማምለክ ነው።

## 1. ቁማር ጤናማ ባለ አደራነት ወይም መጋቢነት አይደለም።

ቁማር የማይጨበጥ የገንዘብ ተስፋን የሚሰጥ፥ የችግርን ሁሉ መፍትሔ፥ ምናባዊ መፍትሔ፥ የሚሰጥ ወጥመድ ነው። ቁማር ተስፋ ይስጥ እንጂ፥ ተስፋው የማይጨበጥ ነው። ቁማር ለመብላት ተብሎ ወይም ለመብላት በሚል ተስፋ ገንዘብ የሚያስቀምጡበትና ለውጤቱ ምንም አካላዊ ድጋፍ፥ ምንም አእምሯዊ ተሳትፎ የማይደረግበት አየር ላይ እንደተበተነ፥ ወይ በንኖ እንደሚጠፋ፥ ወይ፥ ተስፋ እንደሚደረገው፥ ሰብስቦ እንደሚዘንብ ያለ ግን የማይዘንብ ገንዘብ ነው።

ቁማርን ከመጽሐፍ ቅዱስ እይታ አንጻር ስናየው ከመጋቢነት ወይም ባለ አደራነት አቅጣጫ ነው መመልከት ያለብን። መጋቢነት ያልኩት አዲስ ኪዳን የ1954ቱ ትርጉም መጋቢነት ስለሚለው ነው። ቃሉ ባለ አደራነት ማለት ነው። አብራራዋለሁ። ቃሉ የተጠቀሰባቸውን ጥቂት ጥቅሶች እንይ፤

1ቆሮ. 9፥17፤ *ይህን በፈቃዴ ባደርገው ደመወዝ አለኝና፤ ያለ ፈቃዴ ግን ባደርገው መጋቢነት በአደራ ተሰጥቶኛል።*

ኤፌ. 3፥2 *ለእናንተ ስለ ተሰጠኝ ስለ እግዚአብሔር ጸጋ መጋቢነት በእርግጥ ሰምታችኋል፤*

ቆላ. 1፥25፤ *ስለ እናንተ እንደ ተሰጠኝ እንደ እግዚአብሔር መጋቢነት፥ የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽሜ እንድሰብክ እኔ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆንሁ፤*

በነዚህ ጥቅሶች መጋቢ፥ መጋቢነት የሚለው ቃሉ በግሪክ οἰκονόμος እና οἰκονομία የሚል ነው። በእንግሊዝኛ ኢኮኖሚክስ የሚለው ቃል የተገኘበት ቃል ነው። ቃሉ ከሁለት ቃላት የተሠራ ነው። ኦይኮስ ቤት ማለት ነው፤ ኖሞስ ሕግ ወይም ደንብ ማለት ነው። οἰκονομία የቤት ሕግ፥ የቤት ደንብ፥ የቤት ወግ ማለት ነው በቀጥታ ሲተረጎም። ሰውየው οἰκονόμος ደግሞ የቤት አስተዳዳሪ ማለት ነው። ዘመናዊው ኦይኮኖሚክስ ወይም ኢኮኖሚክስ ከገንዘብ አስተዳደር ጋር የተቆራኘ ቢሆንም ገንዘቡን ብቻ ሳይሆን የገንዘቡ ባለቤት መኖሩንም አመልካች ነው። በጠቅላላው የአዲስ ኪዳኑ አሳብ ባለ አደራነት ማለት ነው። ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን

እንደ ታሪክ አካል ሆኖ የተጠቀሰበት ሉቃ. 16 ይበልጥ ግልጽ ያደርግልናልና ያንን ክፍል እንይ። ይህ ትርጉም ደግሞ ሁላችንንም ይመለከተናል።

በሉቃ. 16፥1-4፤ *ደግሞም ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፦ መጋቢ የነበረው አንድ ባለ ጠጋ ሰው ነበረ፥ በእርሱ ዘንድ፦ ይህ ሰው ያለህን ይበትናል ብለው ከሰሱት። ጠርቶም፦ ይህ የምሰማብህ ምንድር ነው? ወደ ፊት ለእኔ መጋቢ ልትሆን አትችልምና የመጋቢነትህን ሂሳብ አስረክበኝ አለው። መጋቢውም በልቡ፦ ጌታዬ መጋቢነቱን ከእኔ ይወስዳልና ምን ላድርግ? ለመቈፈር ኃይል የለኝም፥ መለመንም አፍራለሁ። ከመጋቢነቱ ብሻር በቤታቸው እንዲቀበሉኝ የማደርገውን አውቃለሁ አለ።*

የዚህ መጋቢ ታሪኩ ይቀጥላል፤ ግን ዋናው አሳብ የባለቤቱን ገንዘብ የሚያስተዳድር ሰው መሆኑን በግልጽ አመልካች ነው። የተፈለገውም ትርጉም ያ ነው። ይህ መጋቢ የራሱ ያልሆነ ገንዘብ በኃላፊነት በእጁ ተሰጥቶታል። የተከሰሰው ይህ ሰው የተሰጠውን በሚገባ ይዞ የሚያስተዳድር ሳይሆን የሚበትን መሆኑ ተጠቅሶ ነው። ይህ ማባከን ወይም መበተን የሚለው ቃል (διασκορπίζω ዲያስኮርፒዞ) መብሳት፥ መቅደድ ማለት ነው፤ ከረጢት መቅደድ፥ እውስጥ ያለውን መዝራት፥ መበተን ማለት ነው።

ይህ ትርጉም ሁላችንንም ይመለከተናል ብያለሁ፤ እውነት ነው። ሁላችንም የእግዚአብሔር ባለ አደራዎች ወይም መጋቢዎች፥ ወይም ንብረት ያዦች ነን። አንድ ወይ ሌላ፥ ወይ ጥቂት ወይ ብዙ የተሰጠን ሰዎች ነን። የተሰጠንን ነገር እንደ ባለ አደራ የምንይዝ ነን? ወይስ ቀዳዳ በስተን የምንበትን ነን? ቀጥሎ እንደምንመለከተው ቁማር ከረጢትን መቅደድ ነው።

ሁላችንም፥ ይብዛም ይነስ ከእግዚአብሔር በአደራ የተሰጠን የኛ ያልሆነ ነገር አለን። ልክ በማቴ. 25 እንደተጻፈው ለባሪያዎቹ መክሊቶች ሰጥቶ እንደሄደው ጌታ ባሪያዎች ነን ማለት ነው። ለአንዱ አምስት፥ ለሌላው ሁለት፥ ለሌላው አንድ። ባለ አምስቱና ባለ ሁለቱ ሄደው ነገዱበት፤ ሠሩበት፤ አተረፉበት፤ እጥፍ ሆነላቸው። አምጥተው ዋናውን ከነትርፉ ለጌታው ሰጡት። ስለ ባለ አንዱ የተባለው ግን ይህ ነው፤ *አንድ የተቀበለው ግን ሄዶ ምድርን ቈፈረና የጌታውን ገንዘብ ቀበረ።* ይህ ሰው ቢያንስ የተሰጠውን ባይጨምርም ሳያጠፋ አምጥቶ አስረክቧል። ሁለቱ አትራፊዎች፥ ‘አንተ በጎ፥ ታማኝ ባሪያ’ ተብለው ተሸልመዋል። ሦስተኛው ግን፥ ‘አንተ ክፉ፥ ሐኬተኛ ባሪያ’ ተብሎ ተቀጣ። ሐኬተኛ ማለት ሰነፍ፥ ሊሠራ የማይወድድ፥ ኃላፊነትን የሚጠላ ማለት ነው።

ይህ የቀበረው ሰው ተጠይቆ መልስ ሲሰጥ የራሱን ስንፍና አልተናገረም፤ ይልቁን የጌታውን ጨካኝነት ነበር የተናገረው። ቁጥር 24-25 *አንድ መክሊትም የተቀበለው ደግሞ ቀርቦ፦ ጌታ ሆይ፥ ካልዘራህባት የምታጭድ ካልበተንህባትም የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን አውቃለሁ፤ ፈራሁም ሄጄም መክሊትህን በምድር ቀበርሁት፤ እነሆ፥ መክሊትህ አለህ አለ።* ነበር ያለው። ጌታውን ነው እየከሰሰ ያለው። ካልዘራበት አጫጅ፥ ካልበተነበት ሰብሳቢ፥ ጨካኝ አለው። ስለ ራሱ ምንም አላለም። ሁላችንም ባለ አደራዎች ነን። አደራ በተሰጠን *መሥራትና ማትረፍ* እንጂ መቅበር የለብንም። ይልቁንም መቅበር ሳያንሰን ከሳሽ ባለ አደራዎች መሆን የለብንም።

መቅበር እንደ ሰነፉ ባሪያ ጉዳት የሌለበት ይመስለን ይሆናል። እንደ ሉቃ. 16ቱ መጋቢ ማባከን ከረጢትን መቅደድ ነው። ቁማር ደግሞ ከነዚህ የባሰ ለነፋስ መበተን ነው። ቁማር ገንዘብን ለነፋስ መበተን ነው።

ቁማር ሱስ ነው። ወደዚህኛው የሱስነቱ ችግር እመለስበታለሁ። አንዳንድ ቁማር ጉዳት የሌለው የሚመስል፥ ሱስነትም የሌለው የጨዋታ ማሟሟቂያ ገንዘብ ማስያዝ ነው። አንዳንድ ሰዎች ጨዋታን ሞቅ ለማድረግ ገንዘብ በማስያዝ ይቆምራሉ። ጨዋታው ለምሳሌ፥ የቅርጫት ኳስ ወይም ኡኖ የሚባል ካርታ ወይም እንቆቅልሽ ሊሆን ይችላል። የሚያስይዙት የማይጎዳቸውን ገንዘብ መጠን ሆኖ አሸናፊው ከጨዋታው በኋላ ለምሳ ወይም ለቡና ይዟቸው ይወጣና እዚያም ምሳ እየበሉ ወይም ቡና እየጠጡ ይጫወታሉ ያወጋሉ። አንዳንዶች፥ ይህ ክፋት ላይኖርበት ይችላል ይላሉ። ሌሎች ደግሞ ምንም ገንዘብ ከተደረገበትና የተሠላ ሊስተካከል የማይችል፥ ከኛ ቁጥጥር ውጪ ለሆነ ነገር የሚተው ከሆነ ይህም ተገቢ አይደለም ይላሉ።

ባለ አደራነት ሲባል ተግባርና ሥራ ላይ መሳተፍን ይጠይቃል። ሰው ሲፈጠር ለሥራ ነው የተፈጠረው እንጂ ቁጭ ብሎ የ40 ቀን እድሌ እንዲል አይደለም። ቁጭ ብሎ ሌላው እንዲያበላውም አይደለም። ዘፍ. 2 ውስጥ ሰው ሲፈጠር ለተግባር እንደተፈጠረ ተጽፏል። ከውድቀት በፊትም፥ ከውድቀት በኋላም ሥራ ነበረ። ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣም፥ ሥራና ታታሪነት፥ ትጋትና ብርታት የተመሰገነ ተግባር ነው። ሊሠራ የማይወድ እንዳይበላ ነው የተነገረው። የጌታ አገልጋዮች ሠራተኞችና ባለ ሙያዎች ነበሩ። ቁርበት ፋቂ፥ ድንኳን ሰፊ፥ ዓሳ አጥማች፥ ባለ መድኃኒት፥ የናስ አንጥረኛ፥ ጸራቢ፥ ላም ጠባቂ፥ ወርካ ለቃሚ፥ ወዘተ። በአይሁድ ዘንድ ሥራ የተወደደ በረከት ነው።

'የብልጽግና ወንጌል' የሚሉት ልዩ ወንጌል መሠረታዊ ችግር ይህ ያልለፉበትን ያልሠሩትን ሊያገኙ የሚመኙት በሽታ በመሆኑ ነው። የብልጽግና ወንጌል የሥራና የታታሪነት ገዳይ ነው። ሠራተኞቹና ታታሪዎቹና ትጉሐኑ መበልጸግ ይገባቸዋል። ብልጽግና ጤናማ የተግባር ውጤት ነው። ደግሞም ትጉሐኑ ሠራተኞች እንዴት አድርገው እንደለፉና እንደሠሩ ስለሚያውቁ አያያዙንም ያውቁበታል። ካልተዘራበት ስላልበቀለ ሲያጭዱ ዘሩንም እያስታወሱ ነው። እንዲያው ዱብ የሚልላቸውም የሉም ማለት አይደለም። ምንም ሳይለፉ የወላጆቻቸውን ወይም የአያቶቻቸውን የሚወርሱ ሊኖሩ ይችላሉ። ታዲያ እነዚህ ወራሾች አይልፉ እንጂ ወላጆቻቸው ወይም አያቶቻቸው አልለፉም ማለት አይደለም። ብዙ ጊዜ እነዚህ ሳይለፉ የሚወርሱት ቅንጡዎች ናቸው፤ ደልቃቃዎችና ሞልቃቃዎችና አባካኞችም ናቸው። ልፋትን አልለፉማ!

'የብልጽግና ወንጌል' ሰባኪዎች 'ወራሾች' ናቸው። ውርሱ ግን ከወላጆች ወይም ከአያቶች ሳይሆኑ የሚሰብኳቸው ሰዎች የመዋጮ ወራሾች ናቸው። ልክ እንደ ቁማር ሁሉ ውሸታም ተስፋ የሚያጎርሱ ቀጣፊዎች ናቸው። ቁማር የሌለ የማይጨበጥ ተስፋ ነው የሚሰጠው። 'የብልጽግና ወንጌል' ሰባኪው፥ የማይጨበጥ ተስፋ ይሰጥሃል እንጂ፥ ያንተን ግን የሚጨበጥ ገንዘብ ነው የሚወስድብህ። በዚህ ቁማርና 'የብልጽግና ወንጌል' አንድ ናቸው። ምክንያቱም ትምህርታቸው ሁሉ እንደ ሎተሪ ዓይነት ነገር

ነው። ለነሱ አቅርብ መሥዋዕትህን፥ ስእለትህን፥ ቁርባንህን፤ ከዚያ እነሱ ከመረቁህ ትባረካለህ። ቁማርን ሁሉ አይበላውም እንጂ ከበጣም ብዙ አንድ ይበላል። ለምሳሌ፥ ብሔራዊ ሎተሪ (በነገራችን ላይ ብሔራዊ ሎተሪ መንግሥት ቁማር ሲጫወትና ሲያጫውት ማለት ነው።) በዓመት ስንቴ እንደሚያወጣ፥ ከአንዱ ሎተሪ በአንድ ሎተሪ ስንት እንደሚሸጥ፥ ጠቅላላው ቁጥር ስንት እንደሆነ፥ ይወስናል። ስንቱ እንደሚያሸንፍ፥ ምን ያህል እንደሚያሸንፍ የሚወስነው ድርጅቱ ነው። በምዕራቡ ዓለም በሎተሪ መልክ የሚታወቀው 6/49 የሚባለው ነው። ከ0-49 ካሉት 50 ቁጥሮች ሁለት ሁለት ጥንድ በመሆን ስድስት ቁጥሮች አንድ ላይ ሲወጡ አሸናፊ ይሆናሉ። የአሸናፊው ቁጥር የማሸነፍ ዕድል ከ18 ሚሊየን አንድ ነው። እሱም ያልተገዛ ቁጥር ሊሆን ይችላል። አንድ ሰው እንዲበላ ስንት ሰው እንደተበላ መገመት ብቻ ነው። ለዚያውም እንደ ዕቁብ የተሰበሰበው በሙሉ አይደለም ለበላው ሰው የሚሰጠው። እንግዲህ የነዚያ የተበሉ ሰዎች ልቅምቃሚ ነው የበዪውን ከረጢት የሚሞላው።

'የብልጽግና ወንጌልም' ልክ እንደዚህ ነው፤ ሰዎቹ ያዋጡት ገንዘብ ነው የአያ ሰብስቤን ኪስ የሚሞላው። እንጂ የተፈጠረ ገንዘብ አይደለም፤ እነዚህ እነ ኢዩ ጩፋ፥ እነ ኢዮብ ጪሮ ከምንጣፍ ስር፥ ከቦርሳሽና ከኪስህ ውስጥ ያላወቅከውን ገንዘብ ፈጠርን ሲሉ አባቶችህ ያላወቁትን፥ አንተም ያላወቅከውን አማልክት እናምልክ እያሉህ ነው። አይፈጥሩም፤ እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው፤ ሁሉን ፈጥሮአል፤ ገንዘብ ግን የሰው ሥራ ነው፤ ፍጥረት አይደለም። አንዳንዶች ስለ ገንዘብ መፍጠር ሲነገር ከዓሳው አፍ ስለወጣው እስታቴር ይጠቅሳሉ፤ ያ እስታቴር ዓሳው በሆነ ምክንያት የጎረሰው፥ ያልዋጠው እስታቴር ነው። ለመፍጠር ለመፍጠርማ፥ ለምን ወደ ባሕር ሂድ አለው? ለምን መቃጥን ጣል አለው? እዚያው መፍጠር እየቻለ? ገንዘብ እንዲህ የሚፈጥሩት ከሆነማ እነ ጳውሎስ ስለምን ድንኳን መስፋት ትተው ወንጌል ብቻ አይሰብኩም? ለሚያስፈልጋቸው መግዣ እስታቴሮች እየፈጠሩ ለምን አልሰበኩም?

አንዳንዶቹ አጭበርብረው ጌታ ባረከኝ ሲሉ አያፍሩም። እነዚህ የሞራል መለኪያቸው የተሰበረባቸው ሰዎች ናቸው። በዚህ ሁሉ የሐሰት አስተማሪዎቹ ይበለጽጋሉ፤ የሚበለጽጉት ደግሞ ሠርተው ሳይሆን፥ ጥረው ሳይሆን፥ ግረው ሳይሆን ግጠው ነው፤ ሌሎችን ግጠው። ሠርቶ ማግኘት ትክክለኛ ባለ አደራነት ነው።

አንደኛው ነጥብ፥ ቁማር ጤናማ ባለ አደራነት ወይም መጋቢነት አይደለም። የሚል ነው። ሁላችንም ባለ አደራዎች ነን። አደራ የተሰጠንን እንደ ባለ አደራ መጠበቅ ይገባናል። ድንገት ልንበላ እንችላለን ብለን ልንቆምርበት የተገባ አይደለም። እነዚያ መክሊት የተሰጣቸው ሄደው ነግደውበት፥ ሠርተውበት ነው ያተረፉት። ሥራ አለ፤ ልፋት አለ። በቁማር ግን ሥራ የለም፤ ልፋት የለም፤ ማሰብ የለም። ይህ አንደኛው ነጥብ ነው።

## 2. ቁማር በእግዚአብሔር መታመንን ወይም አእምሮን የማይጠቀም አሠራር ነው።

ቁማር በእግዚአብሔር መታመንን ወይም መደገፍን ከስፍራው የሚያስወግድና አእምሮን የማይጠቀም አሠራር ነው።

ቁማር በእግዚአብሔር መታመንን ከስፍራው የሚያስወግድ፥ ራስን ለራስ አደራረግ አሳልፎ የሚሰጥ፥ ለራስ አደራረግ ብቻ ሳይሆን በሦስተኛው ክፍል እንደምንመለከተው ከራስ ላለፈ አደራረግም አሳልፎ የሚሰጥ ልምምድ ነው።

ቁማር ሱስ እንደሆነ እመለስበታለሁ ብያለሁ። አዎን ቁማር ሱስ ነው። በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ከቁማር መላቀቅ ያቃታቸው ሱሰኛ ቁማርተኞች (compulsive gamblers ወይም addicted gamblers ይባላሉ) አሉ። ይህ ማለት ካልቆመሩ ውሎ ማደር አይችሉም። ገንዘባቸውን እንከት ተደርገው እየተበሉ፥ ከክሬዲት ካርድ ይበደራሉ፤ ቀጥሎ ያላቸውን ጌጥና ንብረት ማስያዝ ይጀምራሉ። ከራሳቸው አልፈው ቤተሰቡን ያራቁታሉ። ይህ ሁሉ የሚሆነው ለማሸነፍ አንድ እርምጃ እንደቀራቸው በማሰብ ነው። ጥቂት ያልሆኑ ሰዎች የሆኑትና ያደረጉት ሲታሰባቸው ቁጭት ይይዛቸውና ራሳቸውን ያጠፋሉ።

አንዳንድ ቁማርተኞች የመዳን ተስፋም የሌላቸው የገንዘብ ራብተኞች ናቸው። ቁማር ሊሰጥ የማይችለውን የውሸት ተስፋ በመስጠትና የማይደረስበትን ከሩቅ በማሳየት እያታለለ የሚጎትት የጎታች ገመድ ነው። ቁማርተኞች የሱስ እስረኞች ናቸው። ቁማር ሱስ ነው፤ ልክ እንደ ዕጽና እንደ መጠጥ ሱስ ዓይነት ነው። እስራት ነው። ልዩነቱ ይህኛው እንደሌሎቹ የሚታኘክ፥ የሚጠጣ፥ የሚቃም፥ የሚዋጥ፥ የሚሸተት፥ የሚሳብ፥ ወይም በመርፌ የሚወሰዱት ሳይሆን የማይታይና የማይዳሰስ ስውር እስራት ነው። እንደ ሌሎቹ ሱሶች ሁሉ በአእምሯችን ውስጥ ባሉት የነርቭ ስሮችና ቅመሞች አማካይነት ፍላጎታችንን የሚቆጣጠርና፥ 'አምጣ አምጣ' የሚል ሱስ ነው።

ማናቸውም ሱስ ደግሞ እስራት ወይም ትብታብ ሆኖ ሰዎችን በማይታይ ገመድ የሚይዝና ገመዱ በየጊዜው እያጠረ፥ እያጠረ የሚሄድ ነው። በገጠር እረኛ የሌላቸው ሰዎች ከብቶቻቸውን በገመድ አስረው ገመዱን ዛፍ ወይም ጉቶ ላይ ያስሩታል፤ እዚያ የሚበሉትን ሳር፥ ገለባ፥ ጭድ ሌላም ይጥሉላቸዋል። ትናንሽ እንስሳት፥ ጥጃ፥ ፍየልና በግ ከሆኑ ችካል ይቸከልና ይታሰራሉ። እነዚህ ከብቶች አንዳንዴ እየዞሩ እየዞሩ፥ ገመዱን ዛፉ ወይም ችካሉ ላይ እየጠመጠሙ፥ የሚዞሩባት ቦታ እየጠበበች ትመጣለች። እስራት እንደዚያ ነው። አንዳንዴ ገመዱን ይበጥሳሉ፤ በጠሱ ማለት ነጻ ወጡ ማለት ይመስላል፤ ግን አይደለም፤ ገመዳቸውን ያሳጥሩታል፤ በቅሎ ገመዷን በጠሰች ቢሉ ለራሷ አሳጠረች እንዲሉ።

እያየን ያለነው ሁለተኛ ነጥብ፥ ቁማር በእግዚአብሔር መታመንን ወይም መደገፍን ከስፍራው ማስወገዱ ነው። የአሜሪካ ታዋቂ አርማ ወይም መፈክር፥ In God We Trust ነው። 'በእግዚአብሔር እናምናለን ወይም እንታመናለን' የሚል ነው። እርግጥ

ነው በአሜሪካ ጅማሬ የመጀመሪያ ዓመታት ውስጥ መንፈሳዊነትና መጽሐፍ ቅዱሳዊነት የጎላ ስፍራም፥ ሚናም ነበረው። ይሁን እንጂ በታሪኳ ውስጥ ይህ በእግዚአብሔር መታመን ነበረ ወይ? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። እርግጥ ነው ኋላ የመጡት መናኞች ከአውሮጳ በእምነታቸው ምክንያት ተሰደው የመጡ ናቸውና ክርስቲያናዊ ግብረ ገብነት ጉልህ ስፍራ ነበረው። ሆኖም የመጀመሪያዎቹ የነክሪስቶፈር ኮሎምበስ አቅኚዎች ቀድሞውኑ ቁማርን ይዘው ወደ አዲሱ ዓለም ገብተው ነበርና ቁማር ቀድሞውኑም ይታወቅ ነበረ።

አሜሪካ ስትቀረቀር፥ አዳዲስ ከተሞች ሲከተሙ ለከተማዎቹ ለሚያስፈልጉ አንዳንድ ግብዓቶችና ግንባታዎች ለሚያስፈልገው ገንዘብ ማግኛና የአስተዳደር ወጪም የሎተሪ ቲኬቶች ይሸጡ ነበር። የአሜሪካ አባት ተብሎ የሚታወቀው ጆርጅ ዋሺንግተን ስለ ቁማር ክፋት በግልጽ ተናግሯል፤ ይናገር እንጂ ግን ራሱም ቁማር ይቆምር ነበረ። የአሜሪካ አብዮት (The American Revolution የሚባለው የ1776ቱ አብዮት) የተደጎመው በሎተሪ ነበረ። ኋላ ዋሺንግተን ዲሲ የተባለው ቀድሞ ሲቀረቀር 'ፌዴራል ሲቲ' ይባል የነበረው ከተማ ሲቆረቆር የገንዘብ ምንጩ ሎተሪ ነበር፤ ራሱ ጆርጅ ዋሺንግተን ነበር የመጀመሪያውን ቲኬት የገዛው። የመጀመሪያዎቹ ግዛቶች በመንግሥት የተደገፈ ሎተሪ ይሸጡ ነበር። ብዙ ዩኒቨርሲቲዎችና አብያተ ክርስቲያናትም ሳይቀሩ የራሳቸውን ሕንጻዎች ለመሥራት ገንዘብ ለመሰብሰብ ሎተሪ ይሸጡ ነበር። ዛሬም እንኳ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ሕንጻ ሲገዙ ቀብዱን ለመክፈል ወይም የተወሰነ ገንዘብ ለማውረድ ሲሉ ሎተሪ ይሸጣሉ።

በመጀመሪያዎቹ የአሜሪካ የሎተሪ ቁማር ዓመታት ቤተ ክርስቲያን በዚህ ጉዳይ ላይ ድምጽ አልነበራትም፤ ቢኖራትም ድምጿ ጎልቶ አይሰማም ነበር። በአብዛኛው ልክ እንደዛሬው ለዘብተኛ ነበረች። ድምጻቸውን ያሰሙ ሙሉ በሙሉ አልነበሩም ማለት አይደለም። ጥቂቶች ነበሩ። ካትን ማተርስ (Cotton Mathers) ከቀድሞዎቹ የቅድስና ጉባኤዎች ወይም ቤተ ክርስቲያኖች ሰባኪዎች አንዱ፥ ቁማር የእግዚአብሔርን መግቦታዊ ቁጥጥር መካድ መሆኑን አበክሮ ሰብኮ ነበር። ይህንን ተቀብለው ያስተጋቡ ሌሎችም ነበሩ። በአንጻሩ ደግሞ የአንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች 'ክርስቲያን' ልሂቃንና ሊቃውንት፥ አንዳንዶቹም የስነ ምግባር ምሑራን ሎተሪን ወይም ቁማርን ያበረታቱት ነበር።

አንዳንድ ስመ ጥር የሆኑ፥ ግን የቤተ ክርስቲያን ሥልጣንና መሪነት ያልነበራቸው ተራ ሰባኪዎች ይህንን ተቃውመው ሲሰብኩ፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዝም ያሰኟቸው ነበር። አንድ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ኤጲስቆፖሳዊው ሰባኪ፥ የሕግ ባለ ሙያና ገጣሚ ፍራንሲስ እስኮት ኪይ (Francis Scott Key) የአሜሪካን ብሔራዊ የባንዲራ መዝሙር የደረሰው ሰው በ1817 ለተደረገው የአሜሪካ ኤጲስቆጶሳዊ ጠቅላላ ጉባኤ የጽሑፍ የአቋም መግለጫ ረቂቅ ጽፎ አቅርቦ ነበር። ያቀረበውም ያ ጉባኤ ቁማርን እንዲያወግዝ እና የሚያወግዘውም 1ኛ፥ ቁማር ከክርስቲያን ንቃተ ሕሊና ጋር የሚጋጭ በመሆኑ፥ 2ኛ፥ ለቤተ ክርስቲያን አባላት የስነ ምግባር አደጋ በመሆኑ እና 3ኛ፥ ለክርስቲያኖች ባሕርይ ፈጽሞ የማይመጥን በመሆኑ ነበር። ጉባኤው ግን ያቀረበውን ረቂቅ ጽሑፍ፥ 'አላስፈላጊ!' በሚል አንድ ቃል ውድቅ አደረገው። ቤተ ክርስቲያን

በገሐድ ያላወገዘችው ምናልባት በቀጥታ በቃሉ ውስጥ፥ ልክ 'አትስረቅ' ወይም 'አታመንዝር' እንደተባለው 'አትቆምር' ተብሎ ስላልተጻፈ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ጥቂቶች ድምጻቸውን በተናጠል ብቻ ሳይሆን አንዳንዶች በአንድነትም ለማሰማት ጥረት አድርገዋል። በዚህ ጥምር ትግል በ1894 መንግሥት እስፖንሰር የሚያደርገውን ሎተሪና ቁማር ለማስቆም ችለው ነበር። ይህ ቀላል እርምጃ አልነበረም። ይህ ከ1894 እስከ 1964 ለ70 ዓመታት ድረስ የቆየ ውሳኔ የቁማርን እንቅስቃሴ ገድቦና አግዶ ነበር። ከዚያ እንደገና ሲፈቀድ ግን ልክ እንደ ግርሻ ብሶበት ቀጠለ። ከ30 ዓመታት በኋላ በ1994 ብቻ 400 ቢሊየን ዶላር በሕጋዊ ገንዘብ ተቆምሯል።

በቁማር የሚገኘው ገንዘብ ብዙውን ጊዜ ከወንጀሎች ጋር እየተቆራኘ ነው ወጪ የሚሆነው። በተለይ በፖርኖግራፊ እና ሴተኛ አዳሪነትን በማስፋፋት ላይ ይውላል። ቁማር ሕጋዊ በሆነባቸው ሴተኛ አዳሪነትም አብሮ ሕጋዊ የመሆን ጠባይ አላቸው።

ብዙ ጊዜ ቁማርን የሚቆምሩት ያልፍልኛል በሚል ተስፋ ስለሆነ ድሆች እና ገቢያቸው በዝቅተኛው ከድህነት መስመር በታች በሆኑ ሰዎች ነው የሚዘወተረው። ሀብታሞቹ አይቆምሩም ማለት አይደለም። ግን ተስፈኛ የሆኑ ድሆች ናቸው የሚቆምሩት። ተስፋ የሚለው ቃል ይሰመርበት። ያልፍልኛል፥ ከድኅነቴ እወጣለሁ በሚል ተስፋ ቀድሞውኑ ድሆች የሆኑት ናቸው የሚቆምሩት። ቀድሞውኑ ድሆች ከሆኑ ቀድሞውኑ በቂ የመኖሪያ ገንዘብም የላቸውም ማለት ነው። ከትርፋቸው አይደለም የሚቆምሩት። አንዳንዶቹ በሌላቸው ገንዘብ በብድር ወይም በክሬዲት ካርድ ነው የሚቆምሩት።

## 3ኛ ቁማር ጣዖት አምላኪነት ነው።

በመጀመሪያ ቁማር ምን አለመሆኑን እንመልከት። ቁማር ሥራ ወይም ተግባር አይደለም፤ በላብ ወይም በወዝ ውጤት ገንዘብ ማግኘት አይደለም። ነግዶ በማትረፍ የተገኘ ገቢ አይደለም። አእምሮን አሠርቶ፥ አውጥቶ አውርዶ የሚገኝ ውጤትም አይደለም። የተሰላ ማማኪት ወይም ማማጥጉ ያለበት እንቅስቃሴ አይደለም። ማማኪት ወይም ማማጥጉ ምሕጻረ ቃል ነው፤ አብራራዋለሁ። ማማኪት፥ ማግኘትና ማጣት፥ ኪሣራና ትርፍ ማለት ነው። ማማጥጉ ማግኘትና ማጣት፥ ጥቅምና ጉዳት ነው። በእንግሊዝኛ risk የሚባለው ነገር ነው። አንዳንዶች riskን አደጋ ይሉታል። risk አደጋ አይደለም። risk የተረገዘ ጥቅምና ጉዳት፥ ወይም ትርፍና ኪሳራ ማለት ነው። ለዚህ ነው፥ ማማኪት ወይም ማማጥጉ ያልኩት።

ማናቸውም ነገር፥ ሕይወት ራሱም፥ ማማኪት ወይም የተረገዘ ጥቅምና ጉዳት አለበት። ነገ ምን እንደሚሆን አናውቅም። ለምሳሌ፥ ገበሬ ሲያርስና ሲዘራ ያንን አስልቶ ነው። 30 ወይም 60 ወይ መቶ እጥፍ ሊያተርፍ ይችላል። ወይም በረዶ ወይ ድርቅ፥ ወይ አንበጣና ተምች ሰብሉን ሊያጠፋበት ይችላል። ግን አንርሳ! በአእምሮ እየተሰላና ሥራ እየተሠራ ነው። ሌላ ምሳሌ ብንወስድ፥ ነጋዴ ዕቃ ሲገዛና ከሩቅ አገር ይዞ ሲመጣ ትርፍ አስልቶ ነው። 10 ወይ 20 ወይ 30% ሊያተርፍ ይችላል። ግን ሁሌም ላያተርፍ ይችላል። ዕቃው በድንገት አላስፈላጊ ይሆናል፤ ወይም ብዙ ነጋዴዎች ያንን ዕቃ

አምጥተው አቅርቦቱ ከፍላጎቱ በዝቶ ዋጋው ሊረክስ ይችላል። ጥቅምና ጉዳት አለበት። ግን ልብ እንበል፤ በአእምሮ እየታሰበ፥ አውጥቶ እየተወረደ፥ ሥራ እየተሠራ ነው። ታስቦበት የተገባ ነገር ነው።

ሌላ ምሳሌ ብንወስድ፥ አንድ ተማሪ ዋጋ ከፍሎ አንድ የትምህርት መስክ ውስጥ ገብቶ ሊማርና ጥሩ ሥራ ሊይዝ ተስፋ ሊያደርግ ይችላል። ብዙ ሺህ ብር ተበድሮ ትምህርቱን ጨርሶ የፈለገውን ሥራ ሊያገኝ ይችላል፤ ወይም ወዲያው ላያገኝ፥ ወይም ምናልባት ጭራሽም ላያገኝ ይችላል። ግን ይህም ታስቦበት የተገባ ነገር ነው። እንዲህ እያልን ስለ ብዙ መስኮች ማውራት እንችላለን። እነዚህ ጥቅምና ጉዳት፥ ማግኘትም ማጣትም፥ ማትረፍም መክሰርም ያለባቸው እንቅስቃሴዎች ናቸው። ተሰልተው የሚደረጉ ነገሮች ናቸው።

ጌታ ስለ ደቀ መዝሙርነት ሲያስተምር ዋጋን ስለ ማስላት ምሳሌ በመስጠት አስተምሮ ነበር፤ ሉቃ. 14፥25-33

> *25፥ ብዙም ሕዝብ ከእርሱ ጋር ይሄዱ ነበር፥ ዘወር ብሎም እንዲህ አላቸው፡- ማንም ወደ እኔ የሚመጣ ቢኖር አባቱንና እናቱን ሚስቱንም ልጆቹንም ወንድሞቹንም እኅቶቹንም የራሱን ሕይወት ስንኳ ሳይቀር ባይጠላ፥ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም። ማንም መስቀሉን ተሸክሞ በኋላዬ የማይመጣ፥ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።* (ቀጥሎ ይህንን ለማብራራት ሁለት ምሳሌዎችን ይሰጣል።)
>
> *28፥ ከእናንተ ግንብ ሊሠራ የሚወድ ለመደምደሚያ የሚበቃ ያለው እንደ ሆነ አስቀድሞ ተቀምጦ ከሳራውን የማይቆጥር ማን ነው?* (ከሳራ የሚለው ቃል ዋጋ ወይም ስሌት ማለት ነው፤ ዋጋን መተመን፥ ዋጋን ማስላት ማለት ነው።) *ያለዚያ መሠረቱን ቢመሠርት፥ ሊደመድመውም ቢያቅተው፥ ያዩት ሁሉ፥ ይህ ሰው ሊሠራ ጀምሮ ሊደመድመው አቃተው ብለው ሊዘብቱበት ይጀምራሉ።* (ይህ አንደኛው ምሳሌ ነው። ቀጥሎ ሁለተኛውን ይሰጣል።)
>
> *31፥ ወይም ሌላውን ንጉሥ በጦርነት ሊጋጠም የሚሄድ፥ ከሁለት እልፍ ጋር የሚመጣበትን በአንድ እልፍ ሊገናኝ የሚችል እንደ ሆነ አስቀድሞ ተቀምጦ የማያስብ ንጉሥ ማን ነው? ባይሆንስ ሌላው ገና ሩቅ ሳለ መልክተኞች ልኮ ዕርቅ ይለምናል። እንግዲህ እንደዚሁ ማንም ከእናንተ ያለውን ሁሉ የማይተው ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።*

ሁለቱንም ምሳሌዎች ብናስተውል ዋጋ ማስላት አለባቸው። ‘ግንብ ጀምሮ መጨረስ ይቻላል ወይስ አይቻልም?’ የሚል ጥያቄ አለ። ጦርነት ሊገጥሙ ሲወጡ፥ ‘ማሸነፍ ይቻላል ወይስ አይቻልም?’ የሚል ማሰብ አለበት። ጀምሮ የመጨረስና የማሸነፍ ጥቅምና ጀምሮ የመተውና የመሸነፍ ጉዳት አለባቸው። የሚታሰቡ የተሰሉ እርምጃዎች ናቸው። ሕይወት በማማኪት የተያዘ ጉዞ ነው። ሕይወት risk አለበት። ደቀ መዝሙርነትም እንዲሁ ዋጋ ማስላት አለበት።

ነገ ምን ይዞ እንደሚመጣ አናውቅም፤ ያዕቆብ ይህንን አሳምሮ ነግሮናል፤ ያዕ. 4፥13-15 *አሁንም፦ ዛሬ ወይም ነገ ወደዚህ ከተማ እንሄዳለን በዚያም ዓመት እንኖራለን እንነግድማለን እናተርፍማለን የምትሉ እናንተ፥ ተመልከቱ፥ ነገ የሚሆነውን አታውቁምና። ሕይወታችሁ ምንድር ነው? ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁና። በዚህ ፈንታ፥ ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ማለት ይገባችኋል።* ነገን አናውቅም። ስለ ነገም አናውቅም። ነገ ምን ይዞ እንደሚመጣም አናውቅም። ነገ ራሱ እንደሚመጣና እንደማይመጣም አናውቅም። ወይም እኛ ወደ ነገ እንደምናልፍና እንደማናልፍም አናውቅም።

ባናውቅም ግን፥ 'ጌታ ቢፈቅድ፥ ብንኖርም' እያልን ግን እንሰማራለን በመስካችን። እናርሳለን፤ እንማራለን፤ እንነግዳለን። ይህ ታዲያ ቁማር አይደለም። ስሌት አለበት። የታሰበ ጉዳይ አለበት። እነዚህ ጥቅምና ጉዳት የተረገዘባቸው ጤናማና ተለምዶአዊ ነገሮች ናቸው። እነዚህ ነገሮች ቁማር አይደሉም። እነዚህ ነገሮች ከቁማር የሚለዩት፥ ጥቅምና ጉዳቶቹ በአእምሮ የታሰበበባቸውና፥ ጥበብ ያለባቸው፥ ማውጣት ማውረድ ያለባቸው፥ 'እንዲህ ቢሆን እንዲህ አደርጋለሁ፤ አተርፋለሁ፤ ካልሆነ ደግሞ የኪሳራው ማካካሻ እንዲሆን እንዲህ አደርጋለሁ።' ተብሎ የተሰላባቸው ሂደቶች በመሆናቸው ነው። ሕይወት እንዲህ ነው። ምንም ነገር ብናደርግ ትርፍ ሊኖረው፥ ኪሳራም ሊኖርበት ይችላል። ብናርስም ብንነግድም፥ አዲስ ነገር ብንፈጥርም፥ ያንን ነገር ለመፍጠር ብዙ ዋጋ ብናወጣም፥ ኋላ ያ ነገር ልፋታችንን እና ወጪያችንን ሊመልስልንና ትርፍም ሊሰጠን ይችላል፤ ወይም ልንከስርም እንችላለን። ይሁን እንጂ አስበንና ዋጋውንና ከሳራውን አስልተን፥ አውጠንጥነን ነው የምንወስነው። ሁኔታዎችን አይተን የምንከስርበት ከሆነ ምናልባት ጥቂቱን ልናስተርፍም እንችል ይሆናል።

ቁማር ግን እንዲህ አይደለም። እንደዚህ ያለ አሳብ አይታሰብበትም። ስሌት የለበትም። አእምሮ አይሠራበትም። ሎተሪህን ስትገዛ ከቁጥር ቁጥር ልታማርጥ ትችላለህ። በዘመናዊው ሎተሪ ቁጥሩን እራስህም ትመርጣለህ፤ ኮምፒዩተር እንዲመርጥልህም ታደርጋለህ። ከዚያ በኋላ ያ ቁጥር እንዲያሸንፍ ምንም አስበህ፥ አሰላስለህ የምታደርገው ጥረት የለም። ቁጥሩን መለወጥም አትችልም።

'በአክሲዮን ማኅበር ውስጥ ገብቶ አክሲዮን መግዛት፥ ቦንድ መግዛትስ ቁማር አይደለም ወይ?' የሚሉ አሉ። አይደለም፤ ይህ ቁማር አይደለም። ይህ እንደ ንግድ ያለ አሠራር ነው። የንግድ ዋጋ ተካፋይነት ነው። የኩባንያው ባለቤትነት ውስጥ ለመግባት የሚደረግ እርምጃ ነው። ታስቦበት ተሰልቶበት፥ ባለ አክሲዮኑን ኩባንያ በማወቅ፥ ታሪኩንም በማጥናት፥ የአክሲዮኑ ኃላፊዎች ምን ያህል አስበውበትና አቅደውበት እንደሆነ በመረዳት፥ ለሕዝባዊ ባለቤትነት ኩባንያው ራሱን ሲያቀርብ እስካሁን ምን አደረገ? ምን ብልህነትና ጠቢብነት የተሞላበት እርምጃ ተራመደ? ተብሎ ተጠይቆ፥ ከዚህ በፊት አትራፊ ነው? ወይስ አይደለም? የንግዱ መስክስ? ወይም ምርቱስ ወደ ፊት ተፈላጊ ነው? ወይስ አይደለም? ብሎ አስበውበት የሚወስዱት እርምጃ ነው። ሊያተርፍም ሊያከስርም ይችላል፤ ቢሆንም ታስቦበት የሚደረግ ነው። በአእምሮ ተሰልቶ፥ በጥበብ የሚደረግ እርምጃ ነው። ደግሞም ልንቆጣጠረው የምንችለው ነገር ነው። አትራፊ ካልሆነ ወይም ካልመሰለን አክሲዮናችንን ልንወስድ ወይም ለሌላ

ልንሸጥ እንችላለን። ቁማር ግን እንዲህ አይደለም። አይታሰብበትም። ስሌት የለበትም። አንዴ ከተጣለ ለነፋስ ተጣለ ነው።

ቁማር ምን አለመሆኑን አየን። የሆነውን ምንነቱን ደግሞ እንይ። ቁማር ታዲያ ምንድር ነው?

ቁማር ምንም አሳቢነትና አሰላሳይነት የማይጠይቅ፥ ማንም ምንም ቁጥጥር ሊያደርግበት የማይችልበት ነገር ነው። ቁማር በዕድል፥ በገድ ላይ የተመሠረተ 'ጨዋታ' ነው፤ ጨዋታ ከሆነ። አእምሮን አይጠቀምም፥ በአእምሮ ማሰብንና ማሰላሰልን አይጠይቅም፤ አመክንዮን አይጠይቅም፤ ቁጥጥር የለበትም፤ የሆነ ቦታ አቁሜ ወደ ኋላ ልመልሰውና እንደገና እንዲንቀሳቀስ ላድርገው አይባልም፤ ጣልቃ ልግባበት አይባልም፤ ጉልበትንም አይጠይቅም፤ ልምድን፥ ብልህነትን ወይም ብልሃትንም አይጠይቅም፤ ሙሉ በሙሉ በዕድል ብቻ ላይ የተደገፈ መቆመር ነው። አሸንፈው የሚሸለሙት እንደ ሩጫ፥ ወይም ዒላማ፥ ወይም ውርወራ፥ ወዘተ፥ የመሰለ የሰውነት እንቅስቃሴና ቅልጥፍና የሚገለጥበት፥ ወይም ሂሳብ ወይም ሎጂክ ሆኖ አእምሮ የሚያሰላውና ከሌላው ቀድሞ የሚደርስበትና የሚያሸንፈው ነገር አይደለም። እነዚህ የምንቆጣጠራቸው፥ አካላችንና አእምሮአችን የሚሳተፍባቸው ተግባራት ናቸው። ቁማር እነዚህ ነገሮች ጨርሰውኑ የማይሳተፉበት ነው። ቁማርን ጀን ማካርተር ሲተረጉመው፥ “The activity or practice of playing at <u>a game of chance</u> for money or other stakes.”

ቁማር ማማኪት ወይም risk ያለበት ውጤት የምንጠብቅበት የተሰላ አካሄድ አይደለም። ቁማር አንድ ሰው አንድን ዋጋ ያለው ነገር (አንዳንዴ ዕቃ ሊሆን ይችላል፤ ብዙ ጊዜ ግን ገንዘብ ነው) ያንን ገንዘብ የሚያስይዝበት ውርርድ ነው። የሚሰጠውም ካስያዘው ዕቃ ወይም ከሚጫወትበት ገንዘብ መጠን የበለጠ ገንዘብ ለማግኘት ተስፋ በማድረግ ነው። ተስፋ የሚደረግበት ወይም ተስፋውን ይሰጣል ተብሎ የሚጠበቀው ነገር ደግሞ ከሚቆምረው ሰው ከቁጥጥሩ ውጪ የሆነና ቆማሪውም የማያስብበት፥ ቁማሩ ራሱም ማሰቢያ የሌለው፥ ይህንን ወይም ያንን ምላሽ አገኛለሁ ብሎ ምንም ነገር የማይጠበቅበት ዕድል ወይም ገድ የሚባል ግዑዝ ኃይል ነው። ቁማር ገንዘብን ዕድል ወይም ገድ ለሚባል ነገር አሳልፎ የሚሰጥበትና ብዙ ገንዘብ ከዕድል ወይም ከገድ ሊያገኙ ተስፋ የሚደረግበት ውርርድ ነው።

አንዳንድ ሰዎች ቁማር ሲቆምሩ፥ ብዙ ከቆመሩ የማሸነፍ ዕድላቸው የሚጨምር ይመስላቸዋል። ነገር ግን ምንም መቆጣጠሪያ በሌለበት ስፍራ የማሸነፍ ዕድል የሚባል ነገር የለም። ዕድል ምንም ስሌት የሌለበት ጨዋታ ነው። ለማንም አይደርስም ማለት አይደለም። ከእጅግ ብዙ ለአንድ ይደርሳል። ምንም ቁጥጥር የሌለበት በመሆኑ ማስላት አይቻልም። ዕድል የሚባለው ጣዖት የገጠመው ከሚሊየኖች አንዱ ሊያሸንፍ ይችላል። ያሸነፈውም አስልቶ ሳይሆን በድንገተኛ አጋጣሚ፥ በዕድልና ገድ ነው።

ቁማር ማለት ይህ ነው። በቀጣይ ክፍል ከቁማር ጋር የተቆራኙ ኃጢአቶችንና ራሱ ቁማር ኃጢአት መሆኑ በምን ምክንያት መሆኑን እንመለከታለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አታመንዝር ወይም አትመኝ የሚል ትእዛዝ እንዳለው አትቆምር የሚል የለም።

ስለዚህ መቆመር ይቻላል ማለት ነው? መቆመር ከገንዘብና ከገንዘብ ፍቅር ጋር የተቆራኘ በመሆኑና መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ስለነዚህ የሚናገረው አለውና በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ ይናገራልና ልንሰማውም ልንናገርበትም የተገባው ጉዳይ ነው።

ይህንን ትምህርት በተከታታይ ማካፈል ከጀመርኩ በኋላ የቀረቡ ጥያቄዎች አሉ። አንዱ፥ ‘ዕጣስ ቁማር ነው ወይ?’ ካህኑ ዘካርያስ ሊያገለግል ዕጣ ደረሰለት ተብሏል።’ የሚል ይገኝበታል። ገንዘብ ከሌለበት ዕጣ ቁማር አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዕጣ የሚል ቃልም ዕጣ የተጣለባቸው ታሪኮችም ይገኛሉ። በዘሌ. 16 በሁለት ፍየሎች ላይ ዕጣ ተጥሎ አንዱ ዕጣ የሚወጣበት ለመሥዋዕት፥ ሌላው ወደ ምድረ በዳ ለመነዳት ይሆናሉ። በዘኁ. 33፥54፤ ኢያ. 17-19 ምድሪቱን በዕጣ ሲወርሱ ይታያል። በዳዊት ዘመን ሌዋውያን አገልጋዮች በ24 ቡድን ተከፍለው የአገልግሎት መደባቸው በዕጣ ነበር የተሰጣቸው፤ 1ዜና 25-26። ምሳሌ ውስጥ ስለ ዕጣ እንዲህ ተብሎአል፤ *ዕጣ በጉያ ይጣላል፤ መደብዋ ሁሉ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።* ምሳ. 16፥33። *ዕጣ ክርክርን ትከለክላለች፥ በኃያላንም መካከል ትበይናለች።* ምሳ. 18፥18።

ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣም በጥያቄው ውስጥ የተጠቀሰው፥ በሉቃ. 1፥9 የተጻፈው የዘካርያስ አገልግሎት በዕጣ የተመደበ አገልግሎት ነው። በይሁዳን ፈንታ ሐዋርያ እንዲሆን የተመረጠው ማትያስ በዕጣ ነበር የተመረጠው፤ ሐዋ. 1፥26። በዚያ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ገና አልወረደም ነበርና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ያንን ቢያደርጉ አስገራሚ አይደለም።

እነዚህ ሁሉ በብሉይ ኪዳንም በአዲስ ኪዳንም የምናገኛቸው ዕጣዎች ዕጣ ቢሆኑም ገንዘብ የተወራረዱበት ዕጣ አይደሉም። ስለዚህ ቁማር አይደሉም። ዕጣ የአንድ አሻሚ ነገር ውሳኔ መፈጸሚያ ወይም ፈቃድ ማወቂያ እንጂ ቁማር አይደለም። ይህ የጥያቄው መልስ ነው።

ወደ ነጥባችን ስንመለስ፥ ቁማር ኃጢአት ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ኃጢአቶች ጋርም የተጋመደ፥ የተደጋገፈ ኃጢአትም ነው። አንዱ ሌላውን የሚመግቡ ኃጢአቶች ተሰግስገውበታል። ቤተ ክርስቲያን አንዱን ኃጢአት እያወገዘችና እየሰበከችበት በሌላው ኃጢአት ላይ ጆሮ ዳባ ማለት የለባትም። ከተሐድሶው አባቶች መካከል ዮሐንስ ካልቪን በጠቅላላዋ በጀኔቫ ከተማ ቁማር እንዳይኖር አግዶ ነበር። ማርቲን ሉተር፥ ‘በቁማር የሚገኝ ገንዘብ በራስ ወዳድነትና በኃጢአት የተገኘ ገንዘብ ነው።’ ብሎ ሰብኮ ነበር። ዛሬም ቤተ ክርስቲያን ስለቁማር ብትጠየቅ ለመናገር መሳቀቅ የለባትም።

ምንድናቸው እነዚህ ከቁማር ጋር የተጋመዱ ኃጢአቶች?

1) የገንዘብ ፍቅር። የገንዘብ ፍቅር ደግሞ የክፋት ሁሉ ስር ነው። *ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፥ አንዳንዶች ይህን ሲመኙ፥ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ።* 1ጢሞ. 6፥10። የገንዘብ ፍቅር የሚወጋ ፈተናና ምኞት ነው። ሰዎች ቁማር ሲጫወቱ በገንዘብ ፍቅር ተጠምደው፥ ግባቸውን ገንዘብ አድርገው ነው።

2) የምድራዊ ተድላ ወይም ቁሳቁስ ፍቅር የሆነ አለመርካትና ያለኝ ይበቃኛል፤ ኑሮዬ ይበቃኛል አለማለት ሌላው ነው፤ *አካሄዳችሁ ገንዘብን ያለ መውደድ ይሁን፥ ያላችሁም ይብቃችሁ፤ እርሱ ራሱ፦ አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና፤* ዕብ. 13፥5። አለጠግብ ማለት፤ አግበስባሽ መሆን። ቁማር አልጠግብ ባይነትና ኑሮዬ ይበቃኛል አለማለት ነው።

3) ቁማር በዝባዥነት ነው። ሰዎች ቁማር ሲቆምሩ አንዱ በድንገት ወይም በአጋጣሚ ሊያሸንፍ ወይም ሊበላ ይችላል። ሆኖም ያ ሰው እንዲያሸንፍ እጅግ ብዙዎች ከስረዋል፤ ተበልተዋል። እና ያ ሰው የበላው ሰው የበላው የሌሎችን ገንዘብ ነው። 'ወደው ነው የቆመሩት እንጂ ተገደው አይደለም ስለዚህ ዝርፊያ መባል የለበትም።' ሊባል ይቻላል። ግን፥ 'የተጫወቱት ለምን ተጫወቱ?' ብሎ መጠየቅና ለምን እንደተጫወቱ ማወቁ ወደው ወይም ተገዝተው እንደተጫወቱ ሊያመለክት ይችላል። ቀደም ሲል ቁማር ሱስ መሆኑን አይተናል። ቁማርተኞች በሥርዓት ራሳቸውን መያዝና መግዛት የማይችሉ ደካሞች ናቸው። ደግሞም ቁማር የሚቆምሩት ያልፍልኛል ብለው ያለቻቸውን ለአደጋ አሳልፈው የሚሰጡ ተስፋ የቆረጡ ተስፈኞች ናቸው። ከገሐዱ ዓለም የተፋቱ የምናብ ዓለም ነዋሪዎች ናቸው። ብዙዎቹ ድሆች ናቸው። ሪሰርቹ እንደሚያሳየውና ቀደም ሲል እንዳየነውም ቁማር የሚጫወቱት በዝቅተኛ ገቢ እርከን ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ናቸው። ብዙዎቹ ያልተማሩና ራሳቸውን ማሻሻል የማይችሉ ሰዎች ናቸው። ለመሥራት ፍላጎት የሌላቸው ሐኬተኞች ሰዎች ናቸው። ያለቻቸውን ከችግረኛ ቤተ ሰባቸው ነጥቀው ለነፋስ የሚበትኑ ሰዎች ናቸው። ገንዛባቸው ሲያልቅ ትዳራቸው የሚፈርስ፥ አእሯቸውን የሚስቱና የሚቀውሱ፥ ራሳቸውን የሚያጠፉ፥ ወይም የሚቆምሩበትን ገንዘብ ለማግኘት ወንጀል የሚፈጽሙ ሰዎች ናቸው።

እና ይህ ዕድል ደርሶት ያሸነፈ ሰው የእንደዚህ ያሉ ምስኪኖችን ገንዘብ ነው ሰብስቦ የወሰደው ማለት ነው። ቁማር እጅ አዙር የድሆች ብዝበዛ ነው። በዚህ ብዝበዛ መንግሥት ራሱ የቁማርና ሎተሪ ንግድ በማስፋፋት ድሆች ይበልጥ ድሆች እንዲሆኑ በማድረግ ተባባሪ መሆኑ ግብዝ ያደርገዋል። መንግሥት በአንድ ወገን ድሆችን ለመርዳት ይጥራል፤ በሌላ በኩል ከድሆች ገንዘብ ይለቅማል።

4) *ሥራ* ጠልነትና *ሥራ ፈ*ትነት። *ሥራ* እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጠው ስጦታና ጸጋ ነው። *እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔድን ገነት አኖረው።* ዘፍ. 2፥15። ይህ ከውድቀት በፊት የሆነ ታሪክ ነው። ከውድቀት በኋላም ሕጉ ያው ነው፤ ሰዎች ሠርተው በወዛቸው፥ በላባቸው እንዲበሉ አዝዟል። *ወደ ወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ፤* ዘፍ. 3፥19። በአዲስ ኪዳንም የነ ጳውሎስ ትምህርት ይኸው ነው፤ *ደግሞ ከእናንተ ጋር ፦ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘናችሁ ነበርና።* 2ተሰ. 3፥10። እየሠራ ያገለግል ነበር ጳውሎስ።*እነዚህ እጆቼ በሚያስፈልገኝ ነገር ለእኔና ከእኔ ጋር ላሉት እንዳገለገሉ እናንተ ታውቃላችሁ።* ሐዋ. 20፥34። ቁማር የዚህ ተቃራኒ ነው። ቁማር ያልለፉበትን የማግኘት አባዜ ነው።

5) *ሥራን አለማበረታታት ብቻ ሳይሆን፤ ተቀምጦ የሌላውን ገንዘብ መመኘትንና መጓጓትን የያዘ ኃጢአት ነው። ቁማር መመኘት ነው። መመኘት ኃጢአት ነው፤*

*አትመኝ የቃሉ ትእዛዝ ነው። የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤ የባልንጀራህን ሚስት፥ እርሻውንም፥ ሎሌውንም ገረዱንም በሬውንም አህያውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ።* ዘጸ. 20፥17 እና ዘዳ. 5፥21።

6) በእግዚአብሔር አለመታመንን የሚያበረታታ የክህደት አካሄድ ነው። እግዚአብሔር የሚጠነቀቅልን አምላክ ነው። ቁማር ይህንን አምላክ ሳይሆን ሌላ ኃይልን ተስፋ በማድረግ መራመድ ነው። እንዲያውም፥ ዕድል ወይም ገድ (መጽሐፍ ቅዱስ ጉድ ይለዋል) የሚባሉ አማልክትን ማምለክ ነው። ቁማር የተበላሸ ወይም መስመር የሳተ ባለ አደራነት ወይም መጋቢነት ብቻ ሳይሆን፥ ቁማር በእግዚአብሔር አለመታመን ብቻም ሳይሆን፥ ቁማር ዕድል ወይም ገድ የሚባል ጣዖት ማምለክም ነው። ቁማር ጣዖት አምላኪነት ነው።

ዕድል የሚባል ነገር አለ። ዕድል የሚባል ቃልም አለ። ግን ይህ ዕድል የሚባለው ነገር እግዚአብሔር የሚጠቀምበት፥ የመላ፥ የአቦ ሰጡኝ ዓይነት አሠራር ነው? ወይስ ሰዎች ዕድልን ፍለጋ እንዲኳትኑ የሚያደፋፍር አሠራርና አካሄድ ነው? እግዚአብሔር በዕድልና በአጋጣሚ፥ በድንገትና በመላ ምት የሚሠራ አምላክ ነው?

*እኔም ተመለስሁ፥ ከፀሐይ በታችም ሩጫ ለፈጣኖች፥ ሰልፍም ለኃያላን፥ እንጀራም ለጠቢባን፥ ባለጠግነትም ለአስተዋዮች፥ ሞገስም ለአዋቂዎች እንዳልሆነ አየሁ፤ <u>ጊዜና እድል</u> ግን ሁሉን ይገናኛቸዋል።* መክ. 9፥11። እዚህ ፈላስፋው ሰባኪ የሚናገርበት ቃል ነው ይህ ዕድል። መክብብ ምድራዊ ሕይወትን ከምድራዊ ሰው እይታ አንጻር ነው የተመለከተውና ወደ ድምዳሜ የደረሰው። እንጂ ጊዜና ዕድል ከሉዓላዊ እግዚአብሔር አንጻር ሲታዩ ምንም ማለት አይደሉም።

ቁማር ዕድልን ሲያስመልክ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት በማስካድ ነው። እግዚአብሔር ሉዓላዊ መሆኑን ይክዳል፤ ያስክዳል። ዕድል ወይም ገድ የሚባል ጣዖትን ያስመልካል። እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ፥ ሁሉን አድራጊ፥ ሁሉን አዋቂ ነው። እግዚአብሔር ተአምራዊ በሆነም፥ ተፈጥሮአዊም በሆነ መንገድ የሕዝቡን መግቦት የሚከውን ጌታ ነው። ሲፈልግ ተአምራት ያደርጋል፤ ሲፈልግ ምንም ተአምር ሳይሆን፥ ምንም ልዕለ ተፈጥሮ የሆነ ነገር ሳይሆን በተፈጥሮአዊ አደራረጉ ሥራውን ይፈጽማል። ጥቃቅኗ ነገር ሁሉ ሳትቀር ሁሉን ይቆጣጠራል። በእግዚአብሔር አሠራር ዕድል፥ አጋጣሚ፥ ገድ፥ የሚባል ነገር የለም። እርሱ መንግሥቱ ሁሉን የምትገዛ አምላክ ነው፤ መዝ. 103፥19። ከአገዛዙ ውጪ ያለ ነገር የለም። እርሱ አስቦ ይወስናል፤ ይመርጣል፤ ያደርጋል። የወደደውን ይሾማል፤ ያልወደደውን ይሽራል፤ የወደደውን ይሰጣል ወይ ይነሣል። እጁን የሚከለክልና ምን ታደርጋለህ የሚል የለም። *በምድርም የሚኖሩ ሁሉ እንደ ምናምን ይቈጠራሉ፤ በሰማይም ሠራዊት በምድርም ላይ በሚኖሩ መካከል እንደ ፈቃዱ ያደርጋል፤ እጁንም የሚከለክላት ወይም፦ ምን ታደርጋለህ? የሚለው የለም።* ዳን. 4፥35።

ዕድል ደግሞ የሌለ ነገር ነው። በእግዚአብሔር አሠራር አጋጣሚና ድንገተኛ የሚባል ነገር የለም። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ድንገት፥ አጋጣሚ የሚሉ ቃላት የሉም ማለት አይደለም። ግን እነዚህ ነገሮች ለሰዎች የሚመስሉ ሰውኛ ቋንቋ ቃላት ናቸው እንጂ

ዕድል የሚባል ነገር በእግዚአብሔር አሠራር አለ ማለት አይደለም። ለምሳሌ፥ *ሄደችም፥ ከአጫጆችም በኋላ በእርሻ ውስጥ ቃረመች፤ እንደ ኢጋጣሚውም የአቤሜሌክ ወገን ወደ ነበረው ወደ ቦዔዝ እርሻ ደረሰች።* ሩት 2፥3። እውነት ይህ ዕድል ቀንቷት፥ የ80 ቀን ዕድሏ ሆኖ ነው ሩት ወደ ቦዔዝ እርሻ የደረሰችው? አይደለም፤ ቦዔዝ ሩትን ሊቤዡ ከሚችሉት ሁለት ሰዎች አንዱ ነው፤ ኋላ እንዲያውም ራሱ ከሁለቱ ሰዎች ውስጥ ያ ሰው ሆኖ ተገኘ። የእግዚአብሔር እጅ አለች ወይስ ድንገት ነው? ድንገት አይደለም። ለሰዎች በሚገባ ቃል አጋጣሚ ይባል እንጂ አጋጣሚ አይደለም።

መጽሐፍ ቅዱስ ዕድል ፈንታ የሚል ቃልም ይጠቀማል ዕድል ፈንታ እና ዕድል ይለያያሉ። ዕድል ፈንታ ክፍል ወይም ድርሻ ማለት ነው። ይህንን ቃል ብዙ ጊዜ ይጠቀመዋል። ዕድል ፈንታ ከዕድል ጋር አይምታታብን። ዕድል የሚመለክ አምላክ መሆኑን የሚያሳይ ክፍል አለ ያንንን እንመለከታለን።

ኢሳ. 65፥11-12 እንዲህ ይነበባል፤ *እናንተን ግን እግዚአብሔርን የተዋችሁትን፥ ቅዱሱንም ተራራዬን የረሳችሁትን፥ ጉድ ለተባለ ጣዖትም ማዕድ ያዘጋጃችሁትን፥ እድል ለተባለ ጣዖትም የወይን ጠጅ ለመጠጥ ቍርባን የቀዳችሁትን፥ እድላችሁን ለሰይፍ አደርገዋለሁ፥ ሁላችሁም ለመታረድ ትጐነበሳላችሁ፤ በፊቴም ክፉ ነገርን አደረጋችሁ፥ ያልወደድሁትንም መረጣችሁ እንጂ በጠራሁ ጊዜ አልመለሳችሁልኝምና፥ በተናገርሁም ጊዜ አልሰማችሁኝምና።*

እዚህ ሁለት ጣዖታት ተጠቅሰዋል፤ ጉድ እና ዕድል።

*ጉድ የሚለው ቃል ?፤ ጋድ የሚለው ቃል ነው። ጋድ የሰውም የቦታም ስም ነው። የመጀመሪያው ጋድ የተባለው ሰው ከያዕቆብ ልጆች አንዱ ነው። የልያ ባሪያ የወለደችው እና ልያ ስሙን ጋድ ያለችው ልጅ ነው። ስሙ በተጻፈበት ስፍራ የተጻፈው አጻጻፍ የስሙን ትርጉም ገላጭ ነው፤ እንዲህ ይላል፤ ዘፍ. 30፥10-11 የልያ ባሪያ ዘለፋም ወንድ ልጅን ለያዕቆብ ወለደች። ልያም፦ ጉድ አለች፤ ስሙንም ጋድ ብላ ጠራችው።* ጉድ ስትል ጋድ አለችው! በአማርኛም ጉድ! ጉድ እኮ ነው! ጉድ በሉ! ተገረሙ! ተደነቁ! ማለት ነው።

አንድ የዱሮ 3ኛ ክፍል ተማሪ አስተማሪው ተማሪዎቹን፥ 'ጥሩ በእንግሊዝኛ ምንድነው?' ሲል እጁን አወጣና፥ ጉድ! አለ። ያንኑ ተማሪ በጣም ጥሩስ? ሲል ትንሽ አሰበና፥ 'ቬሪ ጉድ!' አለ። ከዚያ፥ 'እጅግ በጣም ጥሩስ?' ሲል አላወቀምና ተቀመጠ። ሌላው እጁን አወጣ። 'እሺ አንተ መልስ፤' አለው አስተማሪ። ልጁም፥ 'በጣም ጥሩ በእንግሊዝኛ፥ ቬሪ ጉድ፥ እጅግ በጣም ጥሩ ደግሞ፥ ወቸ ጉድ!' አለ።

ወቸ ጉድ የአድናቆት ቃል ነው፤ ያልታሰበ ነገር ሲሆን የመገረም ቃል ነው። አጋጣሚ ወይም ገድ ማለት ነው። በአማርኛም ገድ እንላለን አይደል? ጋድ ማለት ገድ ማለት ነው። ገደቢስ ማለት ዕድለቢስ ማለት ነው። እስኪ ገድ በለኝ ይባላል የመጀመሪያ ገዢ ሲመጣ። የገዢዎቹን በር በርግድልኝ፤ ክፈትልኝ ማለት ነው። ሰውየው አይደለም ከፋቹ ግን ጥንቆላዊ አምልኳዊ አሠራርን መማጠን ነው። ወደ እግዚአብሔር መለመን አይደለም። ገድ የሚባል ነገርን መለማመን ነው። *እናንተን ግን እግዚአብሔርን*

*የተዋችሁትን፥ ቅዱሱንም ተራራዬን የረሳችሁትን፥ ጉድ ለተባለ ጣዖትም ማዕድ ያዘጋጃችሁትን፥* ሲል ገድ ለተባለ ጣዖት ማለት ነው።

ሁለተኛው አምላክ እድል ነው። *እድል ለተባለ ጣዖትም የወይን ጠጅ ለመጠጥ ቍርባን የቀዳችሁትን፥* ይላል። ቃሉ እድል የሚለው ቃል፥ ቁጥር ወይም ዕጣ እንደ ማለት ነው። ዕድል ወይም ዕጣም አምላክ ወይም ጣዖት ሆኖ ነው እዚህ የቀረበው። ዕድል፥ ዕጣ፥ ገድ፥ አጋጣሚ፥ ቁማር፥ ሎተሪ፥ ቶምቦላ እነዚህ ምንም ደንብና ሕግ፥ እውቀትና ጥበብ የሌለባቸው ድንገቴ ነገሮች ናቸው። በኢሳይያስ ዘመን አይሁድ እድልንና ጉድን ያመልኩ ነበር፤ ይሠዉ ነበር።

እግዚአብሔር ደግሞ ቀደም ሲል እንዳየነው አውቆ አስልቶ የሚሠራ ሉዓላዊ አምላክ ነው እንጂ የድንገቴ አምላክ አይደለም። የዕድል፥ የመላ፥ የነሲብ፥ የዕጣ፥ የቁማር አደራረግ አድራጊ አይደለም። ዕጣ ቀደም ሲል እንዳየነው፥ በብሉይ ኪዳንም በአዲስ ኪዳንም ጥቂት ቦታዎች ላይ ተጠቅሶአል። የተጠቀሰበትን አጠቃቀስም በመጠኑ አሳይቻለሁ። እዚህም ልበለው፤ ዕጣ በሰውኛ አሠራር መረዳት ሲገለጥ እንጂ እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግ ግራ ገብቶት ለመወሰን ተቸግሮ ያደረገው ነገር አይደለም። በአዲስ ኪዳን ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ በፊት አንዴ ዕጣ ጥለው ሐዋርያት በይሁዳ ፈንታ ሐዋርያ ሲመርጡ እግዚአብሔር የወደደውን እንዲፈጽም ለምነውና ጸልየው ነው። ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ በኋላ ዕጣ ሲደረግ አልታየም። መሪው በልብ ውስጥ አድሮ ይመራላ! ዕጣ ከዚያ በኋላ ሲደረግ አልታየም።

ስናጠቃልል፥ ቁማር ከላይ የሚታይ ነገር ነው። ከስሩ የተጎዘጎዙ ጉዝጓዞች አሉ፤ የተነጠፉ፥ የተነሰነሱ ኃጢአቶች አሉ። ከላይ እንዳየናቸው፥ ቁሳዊ ፍቅር አንዱ ነው፤ ነገሮችን ወዳድነት፥ ዕቃዎችን፥ ሸቀጦችን ማፍቀር አለበት። ስግብግብነት ሌላው ነው፤ ቁማር ስስት አለበት። የቃሉ ምክር፥ *የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ፥ ከመጐምጀትም ሁሉ ተጠበቁ አላቸው።* ነው። ሉቃ. 12፥15። ቁማር አለመርካት፤ ያለኝ ይበቃኛል የማለት ተቃራኒ፤ የፊል. 4፥11 ተቃራኒ ነው። ቁማር ብዝበዛ አለበት። አንዱ ሲያሸንፍ ብዙ ሺህዎችና ብዙ መቶ ሺህ የከሰሩ አሉ፤ በግልጽ መውሰድ አይደለም፤ መዝረፍ አይደለም። ግን በእጅ አዙር መዝረፍ ነው። ቁማር ስንፍና አለበት፤ የተከበረ *ሥራ* አይደለም፤ የተከበረ ቀርቶ ጨርሶውኑ *ሥራም* አይደለም። ሠርቶ እንጀራን መብላት አይደለም፤ ምሳ. 6፤ 13፤ 15፤ 21፤ 24 ስለ ታካችና ሐኬተኛ ሰው ይናገራል፤ ሐኬተኛ ሰው *ሥራ* አይሠራም። ቁማር ሱስ ነው፤ መተብተብና መታሰር ነው። ቁማር እግዚአብሔርን አለማመን፤ እግዚአብሔር ይሞላብኛል፤ እረኛዬ ነው ከማለት የወረደ ነው። ቁማር ከእግዚአብሔው ውጪ በሆነ ኃይል መታመን ነው፤ ዕድል በሚባል፥ ገድ በሚባል ጣዖት መታመን ነው። ቁማር እቅድና ጊዜ መውሰድን ጤናማ ባለአደራነትን የሚንቅ ነው፤ የተሰጠንን ከመጠበቅ ጋር የሚቃረን ነገር ነው። መክሊትን ከማትረፍ ጋር የተጣላ ነው። ቁማር አንድ ቀን ሎተሪ ይወጣልኛል ብሎ እየገዙ በመኖር ተስፋ ተጥዶ መብሰል ሳይሆን ማረር ነው።

በውጤቱ ቤት ይፈርሳል፤ ልጆች ይበተናሉ፤ ባልንጀራን አለመውደድ ይመጣል፤ ያቆሸሻል፤ የችግረኞችን ጉስቁልና ያበራክታል፤ ለሌላው አሳቢ አለመሆንን

ይጨምራል፤ የምታደርጉትን ሁሉ ለጌታ ክብር አድርጉት ነው የተባልነው፤ ይህ ለጌታ ክብር አደርጋለሁ ብለን ከማናደርጋቸው ነገሮች አንዱ ነው።

ቁማር በጨዋ ዓለማውያን ዘንድም የተጠላ ነገር ነው። በዓለማውያን የተጠላ ከሆነ ክርስቲያኖች ምን ይሠራሉ? ቁማር አእምሮን አለመጠቀምና በነሲብ መደገፍ ነው። ቁማር ውርርድ አይደለም። ውርርድ ውድድር አለበት። ውርርድ አእምሮአዊና፥ ጥበባዊ፥ አካላዊና ስልታዊ ነገሮችን መጠቀምና ማሸነፍ ነው። 'እንወራረድ እኔና አንተ በሺህ ሜትር ሩጫ ብንወዳደር እኔ አሸንፋለሁ።' ብልና 100 ብር እናስይዝ ብል። ለማሸነፍ ስል ብዙ ነገሮችን አደርጋለሁ፤ አእምሮዬን አሠራዋለሁ፤ ወጥቼ እለማመዳለሁ፤ ሳንባዬ አየር መማግ፥ እግሮቼ፥ ጅማቶቼ ፥ አጥንቶቼ፥ ጡንቻዎቼ ከዚያ በፊት ሆነው የማያውቁትን ነገር አስደርጋቸዋለሁ። ወደረኛዬ ከኔ የበለጠና የተሻለ ልምምድ ካደረገ፥ ወይም ቀድሞም የሰለጠነ ከሆነ ያሸንፈኛል፤ ካልሆነ አሸንፈዋለሁ። ይህ ቁማር አይደለም። ነገር ግን እኛ በምንሮጥበት ሩጫ ሌሎች ሰዎች፥ 'እገሌ ያሸንፋል፤ የለም እገሌ ያሸንፋል።' ብለው ቢወዳደሩ፥ ያ ቁማር ነው። የምንሮጠው ሁለታችን ብቻ ከሆንን የማሸነፍ ዕድላቸው 50% ነው። አብሮ ቁጭ ብሎ ጨዋታ ማየትና በጨዋታው መደሰት እና በጨዋታው እገሌ ያሸንፋል ብሎ ገንዘብ ማስያዝ ቀላል ሊመስለን ይችላል፤ ጨዋታና ፌዝ ሊመስለን ይችላል። ግን ይህ ሙያ አድርገው የሚኖሩበት ሊሆንም ይችላል። ማሸነፋቸው ዕድልን ተስፋ በማድረግ ብቻ ነው። ዕድል ግዑዝ ጣዖት ናት። አምላክ ናት። በዕድል ማመን በእግዚአብሔር አለማመን ነው።

ቁማር ኃጢአት ነው ስል ዋና ዋና ምክንያቶች አድርገን ያየናቸው ነጥቦች 1. ቁማር ጤናማ ባለ አደራነት ወይም መጋቢነት አይደለም። 2. ቁማር በእግዚአብሔር መታመንን ወይም መደገፍን ከስፍራው የሚያስወግድና አእምሮን የማይጠቀም ጨዋታ ነው። 3. ቁማር ከሌሎች ኃጢአቶች ጋር የተቆራኘና የተጋመደም ኃጢአት ነው። ዕድል ወይም ገድ (መጽሐፍ ቅዱስ ጉድ ይለዋል) የሚባሉ አማልክትን ማምለክ ነው። ናቸው።

ቁማር ኃጢአት ነው። ክርስቲያኖች ከቁማርና ቁማርን ከሚመስል ማናቸውም ነገር መራቅ አለብን።

## ምዕራፍ ፱፤

# ክርስቲያንና ዘፈን

## ክርስቲያኖችን ዘፈናም የሚያደርጓቸው ስድስት ፍልስፍናዎችና ስድስት ሰበቦች።

በዘፈን ጉዳይ ራሱን የቻለ *እንዝፈን ወይስ እንዘምር?* የተሰኘ መጽሐፍ ስለጻፍኩ ሙሉውን አሳብ ለማግኘት ያንን መጽሐፍ መመልከት ተገቢ ይሆናል። በዚያ መጽሐፍ አፍቅሮተ ዘፈንን፥ በዘፈን ተጠልፎ መወሰድን፥ በዘፈን ደዌ መመታትን ዘፈናምነት ብዬዋለሁ። እዚህ የዚያን መጽሐፍ ጭማቂ እና ከዘፈናምነት ጀርባ ያሉ ፍልስፍናዎችን እንዲሁም ሰበብ ወይም ምክንያት ተደርገው የሚጠቀሱ ነጥቦች ለማሳየት እሞክራለሁ። ዘፈን ከክርስቲያን ፈተናዎች አንዱም ሆኖአልና ወይም ነውና ከዚያ አንጻር ነው የምንመለከተው። እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ ዘፈን የክርስቲያን (የወንጌላዊ ክርስትና) መከራከሪያና መደራደሪያ ርእስ ሆኖ አያውቅም ነበር። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን እየሆነ መጣ።

መዝሙርና ዘፈን የሚጋሯቸው የጋራ ንጥር ነገሮች አሏቸው። ሁለቱም ዜማ አላቸው። ሁለቱም የሚጻፉት በግጥም ወይም በቅኔ ነው። ጥልቀቱ ቢለያይም ሁለቱም ለስሜት የሚናገሩም ናቸው። ሁለቱም ተደራሽ ወይም አድማጭ አላቸው። ሁለቱም በሙዚቃ ይታጀባሉ፥ ሳይታጀቡም ሊቀርቡ ይችላሉ። ሁለቱም ኪነ ጥበባዊ ረቂቅነትን ያስተናግዳሉ። በነዚህና በሌሎችም ጥቂት ያልተጠቀሱ ነጥቦች ዘፈንና መዝሙር ተመሳሳይ ናቸው። በቅርጽ ይመሳሰላሉ።

ሁለቱም የተለያዩም ናቸው። ዘፈንን ከመዝሙር ወይም መዝሙርን ከዘፈን የሚለየው ውጪያዊው መልክ ወይም ቅርፊቱ ሳይሆን፥ ውስጣዊ ምንነቱ ወይም ይዘቱ ነው፤ መልእክቱ ነው። 'ለማን ነው የሚተላለፈው?' ወይም፥ 'እንዴት ነው የሚተላለፈው?' ብቻ ሳይሆን፥ 'ምንድር ነው የሚተላለፈው?' ነው መጥጠየቅ ያለበት። በመልክ እንፈርጃቸው ካልን ዘፈን ዓለማዊ ነው፤ መዝሙር መንፈሳዊ ነው፤ ወይም ለኛ ለክርስቲያኖች መዝሙር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወይም ክርስቲያናዊ ነው።

ዘፈንን የሚሰሙ ብቻ ሳይሆኑ የዘፈን ቤቶችን የሚያዘወትሩ ክርስቲያኖች እንዳሉ ይታወቃል። በመጽሐፌ ውስጥ ለነዚህ ክርስቲያኖች የሰጡኋቸው ስያሜ ዘፈናም ሲሆን፥ አባዜውን ዘፈናምነት ብዬዋለሁ። አንዳንድ ዘማሪዎች ዘፈናሞች ከመሆናቸው የተነሣ፥ የመዝሙራቸው ቅላጼና አዘማመራቸው ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ዜማዎች እስከሚያስተዛዝቡ ብቻ ሳይሆን እስከሚያሳፍሩም በቀጥታ ከዘፈን የተወሰዱ ናቸው።

ክርስቲያኖችን ዘፈናም የሚያደርጋቸው ምንድር ነው?

ይህንን ጥያቄ ከሁለት አቅጣጫ ወይም አቀራረብ ለመመለስ እሞክራለሁ። አንዱ ተግባራዊ አቀራረብ ሲሆን ሌላው ፍልስፍናዊ አቀራረብ ነው። ሰዎች ክርስቲያኖችንም ጨምሮ ዘፈናሞች የሚያደርጓቸው ብዙ ምክንያቶችና የሙግት መነሻዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ምክንያቶቹና ሙግቶቹ እንደ አቅማቸውና ጉልበታቸው መጠን ሰዎችን ሊያማልሉ ይችላሉ። የማማለላቸው ኃይልም የዘፈኖቹ ጉልበትና የአድማጮቹ ድካም ላይ የሚጫወት ይሆናል። እዚህ ስድስትና ስድስት አድርጌ እመለከታቸዋለሁ። ቁጥራቸው ያ ብቻ ነው ወይም በዚያ ብቻ ይወሰናል ማለት አይደለም። በኔ የአሁን መረዳቴ ለአድማጮች በሚቀርቡበት መልኩ ነው እንዲህ ያቀረብኳቸው። ተጨማሪ የሙግት መነሻዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ እስማማለሁ። በመጀመሪያ ከተግባራዊ አቀራረብ አንጻር ምክንያቶች የምላቸውን ስድስት ፍልስፍናዊ ግፊቶች አቀርባለሁ። ከዚያ ወደ ስድስቱ ጎታች ሰበቦች አልፋለሁ።

## ስድስቱ ፍልስፍናዎች

ከዘፈናምነት ጀርባ የሚሠሩ ፍልስፍናዎች አሉ። እነዚህ ፍልስፍናዎች በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር ሰዎች በጠቅላላውና እኛም ክርስቲያኖች ዘፈንን እንድንወደውና ዘፈናሞች እንድንሆን የሚጣሩ ተጣሪዎች ናቸው። የመጀመሪያው እንድርድረቴ ይህ ከአሳቡ፥ ከዘፈናምነት ጀርባ ያሉ የተሳሳቱ ፍልስፍናዎች ይሆናሉ ማለት ነው።

ተጣሪዎች ናቸው ስል በግሪክ አፈ ታሪክ ሆሜር የተረከው ትረካ አለ፤ በዚያ ልጀምር። ኦዲሲየስ ወይም በሮማይስጥ ዩሊሲስ ከትሮይ ጦርነት ወደ አገሩ ወደ ኢቲካ ሲመለስ የሆነው ነገር ነው። አስቀድሞ የተነገረ ንግርት አለ ያ ለዚህ ታሪክ አስፈላጊ አይደለም። ኦዲሲየስ በትሮይ ጦርነት ዝነኛ የሆነ ሰው ነው። አስተዋይና ብልህም ሰው ነው። ትክክለኛ ነገር ማድረግና አማልክትን መስማትና መታዘዝ የሚፈልግ የተወደደ ሰው ነው። በተለይ ሰርሲ (Circe) የምትባለው ሴት አምላክ የምትለውን በጥንቃቄ ያደምጣል ይታዘዛታልም።

ኦዲሲየስ ከትሮይ ወደ ኢቲካ በመርከብ ሲመለስ ሰርሲ ያስጠነቀቀችው አንድ ነገር Sirens ወይም መለከቶች የሚባሉ እጅግ በጣም የሚያስደስት ድምጽ ባላቸው እጅግ

በጣም ውብ ሴቶች ሊያጠምዱት እንደሚጠሩት ነው። እነዚህ ግሩም ድምጽ በጣም ውብ ገጽታ ያላቸው ሴቶች፥ በእርግጥ ሴቶች ሳይሆኑ በሴቶች የተመሰሉ አስፈሪ አራዊት ናቸው። እነዚህ አስፈሪ ፍጡራን ድምጻቸውና መልካቸው ሰዎችን መሳቢያ ነው። የሚፈልጉት እነዚህን ሰዎች ለማዝናናትና በድምጻቸው ለማስደሰት ጋብዘው ወደ ደሴታቸው ሲደርሱ መርከባቸው ተሰባብራ ሲሞቱ ማየት ነው። የሰርሲ ምክር ከዚያ ወጥመድ እንዴት እንደሚያመልጥ ነው።

በባህሩ እየተጓዙ አንዲት ውብ ደሴት ከሩቅ አዩ፤ መርከበኞቹ ወደዚያ ለመሄድ ጓጉ። ኦዲሲየስ ግን ደሴቱ የመለከቶች ወይም የውቦቹ ግን ገዳዮቹ ሴቶች ደሴት መሆኑንና ወደዚያ ቢሄዱ እንደሚሞቱ አስጠነቀቃቸው። እነዚህ ሴቶች እውኃው ዳርቻ ተቀምጠው ወርቃማ ጸጉራቸውን እያበጠሩ በመረዋ ድምጻቸው እያዜሙ ጆሮ ጣል አድርገው የሚሰሟቸው ላይ አስማት ወይም ድግምት እንደሚጥሉባቸው ነገራቸው። ሰዎችን ልክ መግነጢስ ብረትን እንደሚስብ ወደ ደሴታቸው በውበታቸውና በድምጻቸው እንደሚስቡ፥ መርከባቸውም ከውኃው በታች ካለው ዓለት ጋር ተላትሞ እንደሚሰባበርና ከዚያ በፊት ከሞቱት ጋር እንደሚደባለቁም ነገራቸው።

ሰርሲ ኦዲሲየስን ስትመክረው፥ መርከበኞቹ የነዚህ መልከ መልካምና ድምጸ መረዋ ሴቶች ድምጽ አንዳቸውም እንዳይሰሙ ወደ ደሴቷ ከመቅረባቸው በፊት ጆሮቻቸውን በሰም መድፈን እንዳለበት ነግራዋለች። 'አንተ ድምጻቸውን መስማት ከፈለግህ ግን መርከበኞችህ አንተን የመርከቡ ምሰሶ ላይ ከፍ አድርገው እመሃሉ ላይ ጠፍረው እንዲያስሩህ አድርግ።' ብላዋለች። ሰርሲ የጆሮ መድፈኛ ሰምም ሰጥታው ነበርና ለመርከበኞቹ ሁሉ እየቆነጠረ አደለ። ሁሉም ጆሮዎቻቸውን ከመድፈናቸው በፊት እርሱን በመርከቧ ምሰሶ እንዲያስሩት ነገራቸውና አሰሩት። ጆሮዎቻቸውንም ጥርቅም አድርገው ደፍነው ወደ ደሴቲቱ ቀርበው መቅዘፋቸውን ቀጠሉ።

ወዲያው የፍቅር ዜማቸው አየሩን ሞላው፤ ኦዲሲየስን መጣራት ጀመሩ፤ በዜማ አድርገው እርሱ የተደነቀ ባለ ዝና ጀግና እንደሆነ አሞጋገሱት፤ በለምለም ደሴታቸው ጥበብን እንደሚያስተምሩት፥ ከማር ይልቅ የሚጣፍጥ ፍቅር እንደሚያቀምሱት፥ በድምጻቸው ኀዘኑን እንደሚያስረሱት ዘፈኑለት። ሰማቸው፤ ነፍሱ ከውስጡ ተመንጥቃ ልትወጣ ደረሰች፤ በባሕሩ እየዋኘ ወደነርሱ ሊደርስ ተመኘ። ከታሰረበት ገመድ ራሱን ሊያላቅቅ ታገለ። አጥብቆ በታገለ ቁጥር ገመዱ ወደ ሥጋው ውስጥ መግባት ጀመረ። እየተሰቃየም ከገመዱ እስራት ሊላቀቅ በጣም ለፋ። መርከበኞቹ ጆሮቻቸው በሰም ስለተደፈነ የመለከቶቹን ሴቶች ድምጽም፥ የኦዲሲየስን ድምጽም አይሰሙም። በምልክት ዓይኖቹን ሲያፈጥጥባቸውና ሲያጉረጠርጥባቸው ይበልጡኑ በፍጥነት መቅዘፋቸውን ቀጠሉ። ርቀውም ሄዱ፤ የመለከቶቹ ሴቶች ድምጽም እየራቀ፥

እየሳሳ፥ እየጠፋ ሄደ። ከራቁ በኋላ ዩሮሎከስ የተባለው ከመርከበኞቹ አንዱ፥ አሁን ወደ አቅሉ የተመለሰውን የአለቃውን እስራት ፈታለት።

ይህንን ታሪክ በዩኒቨርሲቲ የስነ ጽሑፍ ትምህርቴ ስለ ጥንታዊ የግሪክ አፈ ታሪክ ስንማር ነው መጀመሪያ ያነበብኩት። ፕሮፌሰራችን ሲስተር ዶሎረስ እስሚዝ ስትተርከው ትረካው አስገራሚ ነው። አፈ ታሪክ ቢሆንም ዘፈን ይስባል። ኦዲሲየስን የሴቶቹ ዘፈን አቅሉን አሳጥቶት ነበር። ጥሪው ወደ ሞት መሆኑንም ያውቅ ነበር። ያልሰሙት ጀሮቻቸው በሰም የተደፈኑት አልተሳቡም። ባለመስማታቸው ሁሉም ከሞት ተረፉ።

ዛሬም ዘፈን ያማልላል፤ ያታልላል፤ ይስባል፤ ይጎትታል፤ ወደ ጥፋት። በጠቅላላው ዘፈንን እንደ ቀላልና ጎጂነት እንደሌለው አድርገው የሚያዩና የሚያሳዩ ዘፈናሞች የተለያዩ መሳቢያዎች ያቀርቡልናል። አንዳንዶቹ መሳቢያዎች ፍልስፍናዎች ናቸው። ራሳቸው ዘፈናሞቹ የነዚህ ፍልስፍናዎች ሰለባዎች ናቸው። ዘፈናሞች ስል፥ ዘፈናም የሚለው ቃል እንደ ስድብ ወይም ሽርደዳ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። ዘፈናም ማለት በመጽሐፌ በሰፊው አብራርቼዋለሁ፤ በአጭሩ፥ ይህ የምንነጋገርበት ጉዳይ የሆነው ዘፈን የወረረው፥ አፍቅሮተ ዘፈን የወረሰው፥ የዘፈን አድናቆት የማረከው፥ በዘፈን የተወሰደ ሰው ማለት ነው። ሰፊው ትርጉም በመጽሐፌ ይገኛል። እነዚህ ፍልስፍናዎቹ እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት አይደለም። እዚህ ግን ስድስቱን አቀርባለሁ።

አንዳንድ የዘፈን ጠበቃዎች ምናልባት፥ 'እነዚህ ፍልስፍናዎች የዘፈን አድናቂዎች መሠረቶችና መንደርደሪያዎች አይደሉም።' ሊሉ ይችላል። ግን፥ ፍልስፍናዎቹ ግባቸውና መድረሻቸው የዘፈን ትርጉሞቻቸውን እንድንጋራ የሚያደርጉ በመሆናቸው እነርሱ ባይቀበሏቸውም እንኳ ጉዳዮቹ እመሬቱ ላይ ያሉት እውነታዎች ናቸው። ምንድር ናቸው እነዚህ ፍልስፍናዎች? እንመልከታቸው።

እነዚህ ፍልስፍናዎች፥ 1. አርነታዊነት (libertarianism)፥ 2. አንጻራዊነት (relativism)፥ 3. ገቢራዊነት Pragmatism፥ 4. ጠቃሚያዊነት (utilitarianism)፥ 5. ዓለማዊነት (Secularism)፥ 6. ተደሳሳችነት (Hedonism) ይባላሉ። ሁሉንም በአጭር በአጭር እገልጣለሁ። ለገሚሱ ትርጉም የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላትን ተጠቅሜአለሁ። ዘፈናሞች ከክርስትና እሳቤዎችና እሴቶች እና ከመጽሐፍ ቅዱሳዊነት ይበልጥ በነዚህ ፍልስፍናዎች እግር ተወርች የታሰሩ ሰዎች ናቸው።

## 1ኛ፥ አርነታዊነት (libertarianism)

Liberalism አይደለም። ሊበራሊዝም የፖለቲካ አቋም ነው። ሊበራሊዝም ወይም ለዘብተኛነት የፖለቲካ አቋም ነው። በወግ አጥባቂና በተራማጅ ፖለቲካ መካከል የሆነ መሐል ሰፍፈር አቋም ነው። ኋላ ቀር መሆን አይፈልግም፤ ለውጥ ይፈልጋል፤ ማናጋትና ማንጓጓት ግን አይፈልግም፤ ለአዲስ አስተሳሰብና አመለካከት ክፍት ነው፤ ርቆ መሄድና አለመቻቻል እንዲሰፍን ግን አይፈልግም። እየተቻቻሉ መቀመጥን ይመርጣል፤ በመንግሥትም፥ በፖለቲካም፥ በኢኮኖሚም ልቅነት እንዳይኖር ይፈልጋል።

ይህኛውም libertarianismም እንደ ሊበራሊዝም የፖለቲካ አቋም ወይም ፍልስፍና ነው። መንግሥት ሁሉን ነገር በመዳፉ ስር አስገብቶ መቆጣጠር የለበትም የሚል አቋም ነው። ነፃነት ከመንግሥት ይቀነስና ለሕዝብ ይጨመር፤ ሕዝብ ይበልጥ ነፃ ይሁን ባይ ናቸው። ሕዝብ አርነቱን እስከ ጥግም ባይሆን በጣም መቀዳጀት አለበት ባይ ናቸው።

ወደኛው ወደ ዘፈናምነት ጉዳይ ስንመጣ፥ አንዱ ጎታችና ጎትጓች አሳብ፥ ዘፈን ከመልካም እስከ መጥፎው አለበትና፥ 'ፍርዱን ለራሳችን አድርገን መርጠን ልንዘፍንና ልንሰማ እንችላለን፤ ነፃነታችን መደፈር ቀርቶ መነካትም የለበትም።' ማንም፥ 'ይህንን አትስማ፥ ያንን ስማ' የሚለን መኖር የለበትም። እኛ ከአትንካ፥ አትቅመስ ነፃ የወጣን የአርነት አድናቂዎች ነን።' የሚል የአርነት አመለካከት ነው። ከLiberalism ጋር የሚቀራኘው ስሙም ለዘብተኛነት ነው። እነዚያ መንግሥት ነፃነታችንን አይግፈፈን እንደሚሉት እዚህም፥ ቤተ ክርስቲያን ወይም መሪዎች፥ ወይም ቃሉ አርነታችንን አይወስኑብን የሚል ነው።

አርነታዊነት ወይም ለዘብተኛነት በዚህ ክፍል ከምንመለከታቸው ፍልስፍናዎች ከሌላው፥ ከአንጻራዊነት ጋር የሚቀራረብ ነው። ይህ አርነታዊነት ወይም ለዘብተኛነት ስልታዊ የሆነ ክርስቲያኖችን ዘፈናም የሚያደርጋቸው ብርታት ሰጪ መድኃኒት ነው። ከሙዚቃ ሞያተኞችም፥ ከስነ መለኮታውያንም ከባቢ ይህ ሲደመጥ፥ እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሾችን ይበልጥ ወደ ዘፈን ሰፈር ሄደው እንዲሰፍሩ ብቻ ሳይሆን እንዲከትሙም ያደርጋቸዋል።

አንዳንዶች፥ 'እኛ አገር ብቻ ነው እንዲህ ያለው መሚዘዝ ያለው እንጂ በውጪው ዓለም ዘፈንን ዓለማዊ መንፈሳዊ አድርጎ መለያየት ብሎ ነገር የለም' የሚሉት ፈሊጥም አላቸው። ግን ውሸት ነው። እንደዚያ የሚሉ የሉም ማለት ግን አይደለም። በምሥራቁም በምዕራቡም፥ በኛም አገር ዘፈንን ውጋ ረጭተው ቀድሰው፥ መስቀል አሳልመው፥ ክርስትና አስነሥተው፥ የክርስትና ስምም ሰጥተው፥ 'ቅጥ ያጣ ፈንጠዝያ ነው የተከለከለው እንጂ ዘፈን አይደለም፤' ብለው እንዳይዋጋ፥ እንዳይቧጭር፥ ቀንዱንና ጥፍሩን ቆርጠው፥ ከርክመው የሚያቀርቡልን አሉ። የምዕራቡ ሥርዓት እሴት ትክክልና እውነት እንኳ ቢሆን፥ የኛ መለኪያ የምሥራቁ ወይም የምዕራቡ ባህል መሆን አለበት ወይ? የምሥራቁም ሆነ የምዕራቡ ባህል ሊመዘንበትና ሊበየንበት

የሚችልበት ወግና፥ ባህልና፥ ትውፊትና፥ ከሁሉም በላይ፥ ቃል አለን ወይስ የለንም? አለን። ያ ቃል ምን ይላል? ያ ቃል ምን ይላል? ወደ ትውፊቱም እመጣለሁ።

የለም ቃሉ ራሱ ልክ አይደለም፤ እኛ ነን ዘፈን ያሰኘነው እንጂ በተጻፈበት ቋንቋ ዘፈን አይልም ሊባልም ተሞክሯል። አይገርምም? ደርሶ የግሪክ ሊቃውንት ሆነው ገላ. 5፥ 21ን ይበልቱታል። ዘፈን የሚለው ቃል በብሉይም በአዲስም ኪዳናት ቋንቋዎች ከ15 በሚበዙ የተለያዩ ቃላት ተገልጦአል። የቃላቱ መብዛት ያ ቃል በነዚያ ቋንቋዎችና ባህሎች ውስጥ ያለውን ደማቅ ስፍራ አመልካች ነው። ይህንንም አሳብ እመጣበታለሁ። በባህላችንና በቋንቋችንም ዘፈን የተገለጠበትና የተተረጎመበት መንገድ ክርስቲያናዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከሆነው በተቃራኒ መንገድ ነው። በመንፈሳዊ ሳይሆን በዓለማዊ መልኩ ነው። የምዕራቡም ዓለም ሙዚቃንም ጨምሮ 'ዓለማዊ' የሚባሉ ነገሮችን ያውቃል። ዓለማዊ የሚባለው ቃልም አለው። ዓለማዊ የሚለው ቃል ራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም የሚገኝ ቃል ነው። ዘፈን መንፈሳዊ ሳይሆን ዓለማዊ መሆኑን ለማስረዳት በመፈላሰፍ ርቀን መሄድ አይኖርብንም። ዓለማዊነት ራሱን የቻለ ከፍልስፍናዎቹ አንዱ ሆኖ ስለሚቀርብ ለብቻ እናየዋለን።

ዘፈንን እና ዘፋኝነትን የሚያወግዙ ምንባባት በቃሉ ውስጥ በግልጽ ይገኛሉ። በቃሉ ውስጥ በግልጽ የተጻፉ ምንባባት እንዲያው ባይኖሩም እንኳ፥ ቅዱሳን፥ 'ከመንፈሳዊነት ትንሽም እንኳ ያርቀኛልና ይቅርብኝ፤ ለሥጋዬ አርነት አልሰጥም የሚሉት ነገር ከኖረ ወይም ቢኖር፥ ይህንን መብላት ያረክሰኛል፤ ያንን ማየት ያቆሽሸኛል፤ ይህንን መንካት ያበላሸኛል፤ ይህንን መስማት ይመርዘኛል፤ ይቅርብኝ . . .' የሚሉት ነገር ቢኖር፥ በዚያ 'ይቅርብኝ' ብለው በሚሄዱበት መስመር ማበረታታት ነው ያለብን? ወይስ ያንን ነገር እንደ ቀላል እንዲያዩትና እንደ ምንም እንዲቆጥሩትና በአርነታዊና ለዘብተኛዊ ፍልስፍና እንዲደፍሩት ማድረግ? የትኛውን ነው ማበረታታት ያለብን? ለሥጋና ለሥጋዊነት አርነትን ማላበስ ከእውነተኛ ደቀ መዛሙርት የሚጠበቅ ነገር አይደለም። 'ዳሌና ተረከዝ' ነው የተከለከለው እንጂ እኮ ፍንጭቷና እንደገበቴ ውኃ አልተከለከሉም የሚል ጋባዥ ሾልከው ከመንፈሳዊው ሕይወት ወጥተው ወደ ዘፈናምነት የሚገቡበትን ቀዳዳ እየከፈተላቸው ወይም ቀዳዳውን እያሰፋላቸው ነው። አንዱ ፍልስፍና ይህ አርነታዊነት እና ለዘብተኛነት ነው።

## 2ኛ፥ አንጻራዊነት (relativism)

አንጻራዊነት ማለት እውነትና ግብረ ገብነት የሚኖሩት ከባህል፥ ከማኅበረ ሰብ እና ከታሪክ አንጻር ስለሆነ ፍጹማን አይደሉም። ማናቸውም ግብረ ገባውያን እውነቶች እነዚህን እውነቶች በሚይዙት ሰዎች ላይ የሚደገፉ ናቸው። እንደየ ሰዉ ይለያያሉ፤ ላንተ እውነት የሆነው ለሌላው እውነት ላይሆን ይችላል። ፍጹም እውነት የለም። ላንተ እውነት የሆነው ለሌላው እውነት ካልሆነ ሁለታችሁም ልክ ልትሆኑ

ትችላላችሁ። ግብረ ገብነትም፥ እውነትም ራሷ ፍጹማን አይደሉም የሚል አመለካከት ነው።

አንጻራዊነት ምን መሆኑን ከመዝገበ ቃላት ላሳይ፤ ማሌ መዝገበ ቃላት ገጽ 295-296 ይህን ይላል፤

> አንጻራዊነት (relativism) የነገሮችንና የክስተቶችን አንጻራዊ ባህርይ ፍጹማዊ አድርጎ የሚያቀርብ ማንኛውም እውቀት አንጻራዊ ብቻ ነው የሚል ሐሳባዊ አስተምህሮ ነው። ከተፈጥሮ ውስብስብነት፥ ከእውቀት በጊዜና በቦታ መወሰን የተነሣ የሰው ልጅ ግንዛቤ ምን ጊዜም ቢሆን ከአንጻራዊነት ሊያልፍ አይችልም የሚል አመለካከት ነው። . . .
>
> አንኳሩን አሳብ ነው ያነበብኩት፤ ገጽ 295-296።



**አንፃራዊነት**
(*Relativism*)

የነገሮችንና የክስተቶችን አንፃራዊ ባሕርይ ፍጹማዊ አድርጐ የሚያቀርብ ፣ ማንኛውም ዕውቀት አንፃራዊ ብቻ ነው የሚል ሐሳባዊ አስተምህሮ ነው ። ከተፈጥሮ ውስብስብነት ፣ ከዕውቀት በጊዜና በቦታ መወሰን የተነሣ የሰው ልጅ ግንዛቤ ምንጊዜም ቢሆን ከአንፃራዊነት ሊያልፍ አይችልም የሚል አመለካከት ነው ።

አንፃራዊነት በአንድ በኩል ፍጹማዊ አመለካከትን የሚዋጋ በመሆኑ ቀኖናዊ ነትን የመታገል ጠንካራ ጎን ያለው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉም ነገር አንፃራዊ ነው በማለት እራሱን ቀኖና አድርጐ ስለሚ ያቀርብ ድክመት ይታይበታል ። ባጭሩ አንፃራዊነት የሰውን ልጅ ዕውቀት አንፃራ ዊና ኅሊናዊ ስለሚያደርግ የኢታዋቂነትና የኅሊናዊ ሐሳባዊነት አንዱ ገጽታ ነው ።

በመሠረቱ ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ባጠቃላይ በማያቋርጠው እንቅስቃሴ ውስጥ የግንዛቤን አንፃራዊ መሆን ይቀበላል ።እቀ ባበሉ ግን ነባራዊ እውነትን በመካድ ሳይሆን ማናቸውም ዕውቀት በአንድ ታሪካዊ ወቅት የምርት ኃይሎችና ሳይንስ በደረሱበት የዕድገት ደረጃ እንደሚወሰን አድርጎ ነው ። አንፃራዊነት የዕውቀትን ታሪካዊ ባሕርይ ባለ መገንዘብ ዕውቀት እየተሟላና እየዳበረ የሚ ሄድ መሆኑን አይቀበልም ።

(ኅሊናዊ ሐሳባዊነትን ፣ ኢታዋቂነትን ፣እው ነትን ፣ ፍጹማዊና አንፃራዊ እውነትን ይመ ለከቷል ።)

የማሌ መዝገበ ቃላት ገጽ 295 - 296።

እንደዚህ ፍልስፍና እሳቤ፥ ምንም ፍጹም ነገር የለም። ሁሉ ነገር አንጻራዊ ነው። አንተ ከአንጻርህ ስታየው ላንተ የመሰለህ ነገር ለሌላው ባይመስለው የመሰለውም፥ ያልመሰለውም ልክ ልትሆኑ ትችላላችሁ የሚል እሳቤ ነው።

የዚህ ፍልስፍና ችግር፥ 'እኛ እንደ ክርስቲያኖች የምንቀበለው ፍጹም እውነትና ፍጹም ግብረ ገባዊነት (ወይም absolute morality) አለ፤ ያም በቃሉ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈውና በክርስቶስ ሕይወት የተገለጠው ነው፤' ከምንለው ክርስቲያናዊ መርህ ጋር ስለሚጋጭ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑ በምን ይታወቃል? እና ክርስቶስ መኖሩስ የሰው ፈጠራ አለመሆኑስ በምን ይታወቃል? የሚሉ ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ ከክርስትና ማዕቀፍ ውጪ ያሉቱ ስለሆኑ ይህኛው

ጉዳይ አይመለከታቸውም። የምንነጋገረው ስለ ዘፈን እና ስለ ክርስቲያኖች ዘፈናምነት ነው።

የምንነጋገረው ስለ ዘፈን ከሆነ፥ ዘፈንን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ነገር አለ። ያንን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ነገር በምንም ሌላ፥ አዲስ፥ እና ተለዋዋጭ ፍልስፍና ልንለውጠው የተገባን አይደለም። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የምናገኛቸው ቅዱሳን ሕይወትና ትምህርት የሚያመለክተን ልንከተለው የሚገባን ምሳሌ አለን፤ ያ መመሪያችን ነው። ፍጹም እውነት አለ፤ ፍጹም ግብረ ገባዊነት አለ።

ሁሉም ነገር ለሁሉም ልክ፥ ከፊሉ ነገር ደግሞ ለከፊሉ ልክ ይሆንና ለከፊሉ ልክ ያልሆነው ነገር ከሆነው ጋር ቢጋጭም በአንጻራዊነት መነጽር በማየት ማለፍ ነው። ድኩም ፍልስፍና መሆኑን የምናስተውለው፥ ሁለት ተቃራኒ ነገሮች ሁለቱም በአንድ ጊዜ ልክ ሊሆኑ ለማይችሉ ነው። 'ወንጀለኛ መቀጣት አለበት፤' ወይም፥ 'ወንጀለኛ መቀጣት የለበትም፤' ብንል ሁለቱም በአንድ ጊዜ ትክክል መሆን አይችሉም። 'ሰው በእግዚአብሔር ተፈጠረ' እና፥ 'ሰው በአዝጋሚ ለውጥ መጣ' በአንጼ ትክክል መሆን አይችሉም። ለጊዜው ነው መቻቻል የሚኖረው እንጂ የኋላ ኋላ አንዱ ሰልቃጭ መሆኑ አይቀርም።

ፍጹም እውነትና ፍጹም ግብረ ገባዊነት ካለ፥ እንደ መጽሐፍ ቅዱሳውያን ክርስቲያኖች፥ 'ለኔ ልክ የሆነው ላንተ ልክ ባይሆን ሁለታችንም ልክ ነን።' ልንል አንችልም። ይህ ነው አንጻራዊነት። እዚህ ላይ ወይም ይህንን ፍልስፍና ስናስብ መርሳት የሌለብን ዐቢይ ነጥብ፥ 'ሁሉ አንጻራዊ ነው ካልን፥ 'ሁሉ ልክ ነው' ማለታችን ነው። 'ሁሉ ልክ ነው' ካልን፥ 'ልክ አይደለም' የምንለው ነገር ፈጽሞም ሊኖር አይችልም። ከሆነ ተቃራኒ ነገሮችን ለማስታረቅና ለማቆራኘት በመጣር የተገጫጨ ዓለም ውስጥ ነው የምንኖረው።

ይህ ሁሉም ልክ፤ አንተም ልክ እኔም ልክ የሚል ፍልስፍና ነው።

# 3ኛ፥ ገቢራዊነት Pragmatism

ገቢራዊነት የፍልስፍና ቅርንጫፍ ሆኖ እውነትን መተርጎም የምንችለው ከውጤቱና ከተግባራዊ ጠቀሜታው አንጻር ነው የሚል ነው።

የማሌ መዝገበ ቃላት እንዲህ ይተረጉመዋል፤

> ገበረ (አደረገ) ከሚለው የግዕዝ ቃል የመጣ ሲሆን ገቢራዊነት አንድን ነገር ለማመስገንም ሆነ ለመንቀፍ የተግባሩን ውጤት ማወቅ ያሻል፤ ከንድፈ አሳብ ይልቅ በአመዛኙ በተግባር ውጤት ላይ ማትኮር ያስፈልጋል የሚል አስተምህሮ ነው። . . . እንደ ገቢራዊነት አባባል ፍልስፍና ውጤት በሌላቸው ንትርኮች ላይ ሲያተኩር ሳይንስ ግን በተጨባጭ ሁኔታዎችና በተግባር በመመራት ጠቃሚ ውጤቶችንና ሁለንተናዊ ያስተሳሰብ ዘዴን ፈጥሮአል።
>
> ስለሆነም ፍልስፍና በአውጠንጥኖት ላይ ብቻ ሳይወሰን እንደ ሳይንስ ውጤት ለማስገኘት በተግባር በመመራት የትክክለኛ ዕውቀት መመዘኛ መርህ ተግባር መሆኑን መቀበል ይኖርበታል። ገጽ 440።

**ገቢራዊነት**

***(Pragmatism)***

ገብረ (አደረገ ፥) ከሚለው የግዕዝ ቃል የመጣ ሲሆን ገቢራዊነት አንድን ነገር ለማመስገንም ሆነ ለመንቀፍ የተግባሩን ውጤት ማወቅ ያሻል ፤ ከንድፈ ሐሳብ ይልቅ በአመዛኙ በተግባር ውጤት ላይ ማትኮር ያስፈልጋል የሚል አስተምህሮ ነው ።

ዕውቀት ከተግባር ግኝት ይመነጫል የሚልና የዕውቀትን ትክክለኛነት ወይም እውነትነት የሚያረጋግጥ ተግባር እንደሆነ አድርጐ ለመውሰድ የሚሞክር ሐሳባዊ ፍልስፍና ነው ። እውነትንና ጥቅምን አንድ አድርጐ የሚወስድ ፥ እውነት ማለት ጥቅም (ጠቀሜታ)፥ ጥቅም ማለት ደግሞ እውነት እንደሆነ የሚሰብክ ፥ ዕውቀትን አስመልክቶ በአዲስ መልክ የቀረበ ፥ ዳሳሽነትንና ምክኑያዊነትን ለማስታረቅ የሚጥር ንድፈ ሐሳብ ነው ።

ይህ ንድፈ ሐሳብ በ19ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ መጨረሻ ላይ ከአሜሪካ ተነሥቶ ወደ አውሮፓ ተሰራጭቷል ። እንደገቢራዊነት አባባል ፍልስፍና ውጤት በሌላቸው ንትርኮች ላይ ሲያተኩር ሳይንስ ግን በተጨባጭ ሁኔታዎችና በተግባር በመመራት ጠቃሚ ውጤቶችንና ሁለንታዊ ያስተሳሰብ ዘዴን ፈጥሮአል ።

ስለሆነም ፍልስፍና በአውጠንጥኖት ላይ ብቻ ሳይወሰን እንደሳይንስ ውጤት ለማስገኘት በተግባር በመመራት የትክክለኛ ዕውቀት መመዘኛ መርህ ተግባር መሆኑን መቀበል ይኖርበታል ።

የማሌ መዝገበ ቃላት፤ ገጽ 440።

የዚህ ፍልስፍና ዋና አሳብ የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው ነው።

እንደ ክርስቲያኖች ደግሞ መፈጨቱን ብቻ ሳይሆን፥ ተፈጭቶ፥ ተሰልቆ፥ ዱቄት ሆኖ መምጣቱን ብቻ ሳይሆን፥ የተፈጨው ነገር ምንድር ነው? የሚፈጨው እንዴት ነው?

ፈጪውስ ማን ነው? እንላለን። ውጤቱ ብቻ ሳይሆን <u>ምንጩና ሂደቱ</u> ላይም እናተኩራለን።

ምንጩ ስል መንፈሳዊ የሚመስሉ የሌላ መንፈስ፥ የርኩስ መንፈስ ግብዓቶች እንዳሉ ስለምናውቅ ነው። ሂደቱ ስልም በሂደቱ ውስጥ የሚሳተፉት ተሳታፊዎች የሚያስተላልፉት የራሳቸው አመለካከት ስላለ ነው።

እንደ ገቢራዊነት ፍልስፍና ዘፈንን በተመለከተ የዘፈኑ ውጤት ላይ ብቻ በማትኮር ውጤቱ ተግባራዊ ጠቀሜታ አለው? ሥራው ገቢ አለው? ዘፈኑ ዝነኛ ያደርጋል? ስሜት ያነሳሣል? ብቻ ሳይሆን፥ ማስደሰቱ ላይ ብቻ ሳይሆን፥ ስሜት መንካቱ ላይ ብቻ ሳይሆን፥ 'ኧረ ጎራው! ተኳሽ እወዳለሁ ገዳይም አልጠላ!' ብሎ ጦር ሜዳ መስደዱ ላይ ብቻ ሳይሆን፥ አካሄዱም ላይ፥ አስኪያጆቹም ላይ፥ ይዘቱም ላይ፥ መልእክቱም ላይ፥ መልእክተኞቹም ላይ እናተኩራለን።

ስለዚህ፥ እንደ መጽሐፍ ቅዱሳውያን ክርስቲያኖች፥ 'ውጤቱ ጥሩ ከሆነ ጥሩ ነው። ሰውን ካስደሰተ፤ ስሜትን ካረካ፥ ዝነኛ ካደረገ፥ ወኔ ከቀሰቀሰ፥ ወዘተ፥ ጥሩ ነው፤' ልንል አንችልም። ውጤታቸው ጥሩ የሚመስሉ ግን ያልሆኑ፥ እና ውጤታቸው በአንጻራዊነት 'ጥሩ' የሆኑ መጥፎ አፈጫጨቶችም አሉ።

እንደ መጽሐፍ ቅዱሳውያን ክርስቲያኖች ዘፈንን ከውጤቱና ከተግባራዊ ጠቀሜታው አንጻር ጠቃሚ ነው ማለት አንችልም። እኛ ዘፈንን የምንለካበት ሌላ መለኪያ አለን። ያም መጽሐፍ ቅዱስ ይባላል። ዘፈንን ወይም ሌላ ነገርን ከተግባራዊ ጠቀሜታ አንጻር ማየትና መለካት በጎዶሎ ሜትር እንደመለካት ነው። 70 ሳንቲ ሜትርን 100 ነው ወይም 1 ሜትር ነው ብለን ብንለካ ውጤቱ አሳሳች ነው። ከአንድ ሜትር 30 ሳንቲ ሜትር ነው የምናጎድለው ትልቅ ላይሆን ይችላል። ከመቶ ሜትር 30 ሜትር እየሰረቅን ነን። ከመቶ ኪሎ ሜትር 30 ኪ. ሜ. እየሰረቅን ነን።

ከተግባራዊ ጠቀሜታ አንጻር ከሄድን ደግሞ ዘፈን ለክርስቲያን የሚሰጠው አንዳችም ተግባራዊ ጠቀሜታ የለም። ትዝታን ጎትቶ ሊያመጣ ይችል ይሆናል፤ ስሜታዊ ሊያደርግ ይችል ይሆናል፤ ወኔያም ሊያደርግ ይችል ይሆናል፤ መንፈሳዊ ጠቀሜታ ግን የለውም። እኛ ደግሞ ነገሮችን መለካት ያለብን ከመንፈሳዊ ጠቀሜታቸው አንጻር ነው። ይህ ገቢራዊነት ነው። ሌላው ስሑት ፍልስፍና።

# 4ኛ፥ ጠቃሚያዊነት (utilitarianism)

በ17ኛው መቶ የታወቀና የተስፋፋ የፍልስፍና ዘርፍ ነው። ጠቃሚያዊነት የፍልስፍና ንድፈ አሳብ ሆኖ፥ 'ማንኛውም ግብረ ገባዊ ትክክለኛነት መለኪያው ለብዙዎች የሚሰጠው መጠነ ሰፊ ወይም ብዛት ያለው ጥቅም ነው።' የሚል ነው። ክላሲካዊው የጠቃሚያዊነት ፍልስፍና አንድን ደንብ ወይም ሕግ ወይም ድርጊት ግብረ ገባዊ መልካም ወይም ግብረ ገባዊ ትክክል የሚያሰኘው የሚሰጠው ጥቅም መጠን ነው። ጠቃሚያዊነት ከገቢራዊነት ጋር ኩታ ገጠም ናቸው።

ትርጉሙን፥ በቀጥታ ከመዝገበ ቃላት ትርጉሙ ልውሰደው። የማሌ መዝገበ ቃላት ገጽ 463-464 ይህን ይላል፤

> የማንኛውም ግብረ ገብ ትክክለኛነት መመዘኛው የሚሰጠው ጥቅም ነው የሚል የቡርዧ ሥነ ምግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ነው። ይህም ንድፈ ሐሳብ በያንዳንዱ ግለ ሰብ ጊዜያዊና ግላዊ ፍላጎት መሟላት ላይ የተመሠረተና የማንኛውም ተግባር ትክክለኛነት ወይም ስሕተተኛነት በሚያስከትለው የደስታ ወይም የስቃይ መጠን እንደ ሒሳብ ስሌት ሁሉ ሊተመን ይችላል የሚል ነው። . . . ይላል።

ገጽ 463-464።


ጠቃሚያዊነት
(Utilitarianism)

የማንኛውም ግብረገብ ትክክለኛነት መመዘኛው የሚሰጠው ጥቅም ነው የሚል የቡርዧ ሥነ ምግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ነው ። ይህም ንድፈ ሐሳብ በያንዳንዱ ግለሰብ ጊዜያዊና ግላዊ ፍላጐት መሟላት ላይ የተመሠረተና የማንኛውም ተግባር ትክክለኛነት ወይም ስህተተኛነት በሚያስከትለው የደስታ ወይም የሥቃይ መጠን እንደ ሒሳብ ስሌት ሁሉ ሊተመን ይችላል የሚል ነው ።

እንደጠቃሚያዊነት አመለካከት ሕግና መንግሥት መደባዊ መሠረትና ይዘት የላቸውም ። ስለዚህም ሕግና መንግሥት ሰመላው ኅብረተሰብ እንደቆሙ በመቁጠር መኖራቸውን ጠቃሚ አድርጐ ይቀበላል ። ይህ አመለካከት በግላዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተና የነገሮችን ውስጠ ባሕርይ ጠልቆ የማይመራመር ነው ። ነገሮችን ከጠቀሜታቸው አንፃር የማየት መርህ እያደረ ገቢራዊነት ለተባለው የቡርዧ ፍልስፍና መነሻ ሆኗል ።

(ገቢራዊነትን ፣ ተጨባጫዊነትን ፣ ዊሊያም ጀምስን ይመለከቷል ።)

የማሌ መዝገበ ቃላት ገጽ 463 - 464።

በአጭር ቃል፥ አንድ ነገር ትክክል ነው የምንለው፥ ጥቅሙ ለብዙዎች ከሆነ ጥቂቶች ቢከፋቸውም ምንም አይደለም። ወይም፥ ጥቅሙ ብዙ ከሆነና ጉዳቱ ከጥቅሙ ያነሰ ከሆነ ተመራጭ ነው ማለት ነው። ሞራላዊ ወይም ግብረ ገባዊ ክብር ወይም ብቃት አንድ ነገር ለብዙ ሰዎች በሚሰጠው ደስታ ሊለወጥ ወይም ሊካካስ ይችላል። ለምሳሌ፥ ስለ ዘፈን ነው የምንነጋገረውና፥ ዘፈን ትክክል ነው ወይም አይደለም የምንለው ደስታ በመስጠቱ፥ ደስታው መጠኑ ትልቅ በመሆኑ፥ ደስታው ጥቂቶችን ቢያስከፋም፥ ብዙዎችን በማስደሰቱ ነው ማለት ነው። የትክክለኛነት መለኪያ ይህ ነው። ይህንን መለኪያ ለሌሎቹም ነገሮች ሁሉ ልናደርግ እንችላለን፤ ለመጠጥም፥ ለዝሙትም፥ ለነፍስ መግደልም፥ ለሌላውም ሁሉ።

ከዚህኛው ፍልስፍና ጋር ተቆራኝቶ መታየት ያለበት ነገር፥ 'ጥቅሙን የሚለኩት ሰዎች መለኪያቸው ምንድር ነው?' የሚለው ነው። የራሳቸው ስሜት ነው መለኪያው? የብዙኃኑ ስሜት ነው? ሌሎች ምዕራባውያን ወይም ምሥራቃውያን አገሮችና ባህሎች ናቸው? አንቱ የምንላቸው ሰዎች አስተያየቶች እና ፍልስፍናዎች ናቸው? ማኅበራዊ ሚድያ ነው? የተጻፈ ሕግና ደንብ አለ? ያልተጻፈው ስነ ቃላዊው ባህላችንና ትውፊቱ ነው? ለኪው ማን ነው? መለኪያው ምንድር ነው? ሚዛኑ ምንድር ነው? መዛኙስ ማን ነው? የሚለው ነው።

በዚሁ ልክ፥ ለምሳሌ ዘፈንን፥ እነዚያ ለከተው፥ መዝነው፥ 'ዘፈን ልክ ነው፤ ተመችቶናል' ባሉበት አካሄድ፥ ክርስቲያኖች ደግሞ ዘፈንን ለክተው፥ 'አይመዝንም፥ አይከብድም፥ ገለባ ነው፥ ውኃ አያነሣም፥ አያንጽም፥ ይህ ከጥሪያችን ጋር፥ ከሰማያዊ ዜግነታችን ጋር አይሄድም፥ እኛ የንጉሥ ካህናት ነን እንጂ የዚህ ዓለም ጨፋሪና አስጨፋሪ አይደለንም፥ ዘፈን ለካህን አያምርበትም።' ቢሉና ለዚህ አባባላቸው ደግሞ የተጻፈውን ቅዱስ ቃሉን ቢያቀርቡ ይህ ለምን የተከበረ አሳብ ነው ተብሎ አይወሰድም? ለምን? ይህ ጠቃሚያዊነት አራተኛው ፍልስፍና ነው።

## 5ኛ፥ ዓለማዊነት (Secularism)

ዓለማዊ የሚለው ቃል ቃሉ በመጽሐፍ ቅዱስም ይገኛልና ለትርጉሙም ለማብራሪያውም መጽሐፍ ቅዱስን እጠቀማለሁ። አንድ ስድስት ጊዜ ተጽፎአል፤ ዓለማዊነት በመጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ትርጉም አለው። አንደኛው ትርጉም ሥጋዊ ማለት ሲሆን ሁለተኛው ምድራዊ ማለት ነው። ጥቅል ትርጉሙ የዓለም፥ ዓለም የምትወድደው፥ ለዓለም የሚጥም፥ ለዓለም የሚመች፥ ለሥጋ የሚመች፥ ለሥጋዊ ክርስቲያንም የሚመች ማለት ነው።

አንዳንድ ቦታዎች፥ ለምሳሌ፥ 2ቆሮ. 1፥17 *እንግዲህ ይህን ሳስብ ያን ጊዜ ቅሌትን አሳየሁን? ወይስ በእኔ ዘንድ አዎን አዎን አይደለም አይደለም ማለት እንዲሆን ያን የማስበው በዓለማዊ* ልማድ ነውን? ሲል በሥጋዊ አእምሮ ወይም በሥጋዊ አስተሳሰብ ማለቱ ነው። መንፈሳዊ ባልሆነ ሥጋዊ ማለቱ ነው። ወይም ሥጋዊ ሲል መንፈሳዊ ያልሆነ ማለት ነው። በ2ቆሮ. 10፥12 *በዓለማዊ ልማድ እንደምንመላለስ በሚቆጥሩን በአንዳንዶች ላይ አምኜ ልደፍር አስባለሁ፥ በዚያ እምነት ግን ከእናንተ ጋር ሆኜ እንዳልደፍር እለምናችኋለሁ።* ሲልም ይህንኑ አሳብ መናገሩ ነው። በሥጋ ልማድ እንደምንመላለስ ማለቱ ነው። ወይም በ2ቆሮ. 11፥18 *ብዙዎች በዓለማዊ ነገር ስለሚመኩ እኔ ደግሞ እመካለሁ።* ሲልም ያንን ማለቱ ነው። እንዲያውም ዝቅ ብሎ

ይዘረዝራቸዋል ዓለማዊ ከሚላቸው ነገሮች ጥቂቶቹን። ቃሉ σάρξ ሳርክስ ወይም σαρκικός ሳርኪኮስ ነው። *ሥጋ፥ ሥጋዊ* ማለት ነው።

በቆላ. 2፥8 *እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን፥ እንደ ሰው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ በፍልስፍና በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ።* ሲል ደግሞ የምድር ወይም ምድራዊ ማለቱ ነው። ይህኛው ከላይ እንዳየነው *ሥጋዊ* ወይም *ሥጋዊነት* ሳይሆን የዚህችን ዓለም ነገር አመልካች ነው። ቃሉ κόσμος ኮስሞስ ወይም κοσμικός ኮስሚኮስ የሚል ነው። በእንግሊዝኛ worldly የምንለው ነው። ዓለም እንደምታስተምረው ባለው ትምህርት ተማርካችሁ አትወሰዱ እንደማለት ነው። በቆላ. 2፥20-22 *ከዓለማዊ ከመጀመሪያ ትምህርት ርቃችሁ ከክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ፥ እንደ ሰው ሥርዓትና ትምህርት። አትያዝ፥ አትቅመስ፥ አትንካ ለሚሉት ትእዛዛት በዓለም እንደምትኖሩ ስለ ምን ትገዛላችሁ? እነዚህ ሁሉ በመደረግ ሊጠፉ ተወስነዋልና።* በሚለው፥ ከዓለማዊ ከመጀመሪያ ትምህርት የሚለው አሳብም ይህንኑ ምድራዊ ትምህርት መናገሩ ነው።

ቲቶ 2፥11-13 *ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤ ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፤* ይህም ከላይ በቆላስይስ ውስጥ እንደተጻፈው ያለው ቃል ነው፤ ምድራዊ ማለት ነው። ምድራዊ ምኞትን ክደን። ከሰማይ የሚመጣውን የእርሱን መገለጥ፥ የእርሱን መምጣት ሳይሆን የዚህችን ምድር ነገር፤ የላይኛውን ሳይሆን የታችኛውን ነገር ማሰብን፤ ከላይኛው ሳይሆን ከታችኛው ጋር መጣበቅን መናገሩ ነው።

ጉዳያችን ወደሆነው ወደ ዘፈንና ዘፈናምነት ስንመጣ፥ ዘፋኝነት ወይም ዘፈን ከዓለማዊነት ጋር የተቆራኘ ነው። የተቆራኘ ነው ስልም በሁለቱም ትርጉሙ፥ በሥጋዊነትም በምድራዊነትም የተቆራኘ ነው ማለቴ ነው። ሙዚቀኛ ዮናስ ጎርፌ ስለ ዘፈን ሞገስ በጻፈው <u>ቤት ያጣው ቤተኛ</u> መጽሐፉ፥ ዓለማዊ የሚለውን አሳብ secular ይለዋል። ሲተረጉመውም በሚገርም መንገድ አቅልሎና አቆንጅቶ ይተረጉመዋል። እንዲያውም ማኅበረ ሰባዊና ኅብረተ ሰብዓዊ በማለት ተርጉሞታል። ስለዚህ ጉዳይ ከመጽሐፌ ውስጥ (እንዝፈን ወይስ እንዘምር) ለዚያ አተረጓጎም ምላሽ ከሰጠሁባቸው ገጾች ከሁለት ቦታዎች ልውሰድ፤

በመጽሐፌ ገጽ 44-45 እንዲህ ተጽፏል።

ማኅበረ ሰቡ በየትኛውም እርከን ቢሆን ዘፈንን ከመንፈሳዊ ሕይወት መግለጫነቱ አንጻር ከቶም አያየውም። ዘፈን ዓለማዊ ወይም Secular ነው። Secular መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃልም ነው። የአዲስ ኪዳን ቃልም ነው። ከአዲስ ኪዳን ትርጉም አንጻር Secularism ሥጋዊነትና ዓለማዊነት ነው። ዓለማዊነት ምድራዊነትና ለዚህች ዓለም ሥርዓትና ፈቃድ ተሰጥቶ መገዛት ነው። ዓለማዊነት ኢመንፈሳዊነት ነው። ቃሉን ከአዲስ ኪዳን ወጣ ባለ ሕዝባዊ መልኩ ብናየው Secular ለሚለው ቃል ከመጽሐፋዊው ከWebster እስከ ድረ ገጻዊው Wikipedia ድረስ ብንፈትሸው፥ 'ሃይማኖታዊ ያልሆነ፥ ከሃይማኖታዊነት የራቀ፥ ዓለማዊ፥ ምድራዊ፥ የጊዜው፥ ሥጋዊ፥ ከምንም ሃይማኖት ወይም የቅድስና ጉዳይ ጋር ትስስር ወይም ግንኙነት የሌለው፥ ወዘተ፥' ብለው ነው የሚተረጉሙት። Secular ቃሉ ራሱ Secularis ከሚል የላቲን ቃል የተወረሰ ነው። የሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ተቃራኒ የሆነ ምድራዊ፥ [እንዲሁም] የዘላለማዊው ተቃራኒ የሆነ ጊዜያዊ ማለት ነው።

በአጭር ቋንቋ ይዘትን በተመለከተ ዓለማዊ መዝሙር እንደሌለ ሁሉ መንፈሳዊ ዘፈንም የለም። እነዚህ ጎራ የለዩ ሁለት ክልሎች ናቸው እንጂ መመሳሰልም፥ መወራረስም የላቸውም። እርግጥ መንፈሳዊነት ወይም መጽሐፍ ቅዱሳዊነት የሌለባቸው፥ ጉዳትም ሆነ ረብም የሌላቸው ዘፈኖች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህን ለመስማትና በእነዚህ ለመደሰት የሚሻው የክርስቲያን ሕዝብ ምን ያህሉ እንደሆነ መገመትና በዚያ ላይ መናገር ይቻላል። በዚህ ዘመን ዘፈናም ክርስቲያኖች እየጠየቁ ያሉት ግን ዘፈን በዘፈንነቱ ግምጃ ተነጥፎለት እቤት ይግባ የሚል ነው። ይህ ደግሞ ክፉ አባዜ ነው። ዘፈንን ክርስቲያኖች ቤት አስገብተው ቤተ ሰብ ሊያደርጉት ይቅርና ቤተኛም ሊያደርጉት አይገባም። እንኳን ቤተኛ፥ ጥገኛም፥ ጎረቤትም ሊያደርጉት አይገባም።

ገጽ 63፤

የሙዚቀኛ ዮናስ መጽሐፍ ዓለማዊ የሚባል ዘፋኝ እንደሌለ ሊያሳምን ሞክሮአል። ዓለማዊ ዘፋኝ ከሌለ እና የsecular ትርጉም ማኅበረሰባዊ ይባል ከተባለ፥ ማኅበረሰባዊ ዘፋኝ አለ ማለት ነው። ማኅበረ ሰባዊ ሙዚቀኛ ወይም ዘፋኝ ከኖረ ማኅበረሰባዊ አናጢ፥ ማኅበረ ሰባዊ መካኒክ፥ ማኅበረሰባዊ አብራሪና ዶክተር አለ ማለት ነው። ዓለማዊ (secular) የሚለውን ቃል ማኅበረሰባዊ ብሎ እንደተረጎመው ሌሎች ቋንቋዎች ማኅበረሰባዊ ብለውታል? ሊሉትስ ይችላሉ? ሌሎች ሙያዎችስ ማኅበረሰባዊ ብለውታል? ሊሉትስ ይችላሉ? በእውነቱ፥ ቃላት አሻሚ ሲሆኑ እንግሊዞች እንደሚተርቱት አካፋን አካፋ ከማለት የተሻለ የቋንቋ ትርጉም አካሄድ ሊኖር አይችልም። ዓለማዊ ሙዚቀኝነት ከኖረ ዓለማዊ ያልሆነ ክርስቲያናዊ ወይም መንፈሳዊ ሙዚቀኝነት አለ ማለት ነው። ዓለማዊ ሙዚቀኝነት ዘፈንን የሚያጅበው ከሆነ ክርስቲያናዊውን መዝሙር የሚያጅበው ደግሞ መንፈሳዊው ስለምን አይሆንም? የቤተ ክርስቲያን ልጆች ናይት ክለብ ሄደው እንዲጫወቱ ወይም የዘፈን ሙዚቀኞች ቤተ ክርስቲያን መጥተው እንዲሞዝቁ ስለምን ተፈለገ?

እንደ ክርስቲያን ዓለማዊ የሚለውን ቃል ለመጠቀም መፍራትና መሳቀቅ የለብንም። ምክንያቱም ቃሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃልም ነው። ዓለማዊ የሚለውን ቃል ከዓለማዊ ባነሰ ምንዛሪ መመንዘር ከዋጋው ባነሰ መመንዘር ስለሆነ ኪሳራ ነው። ዓለማዊ የሚለውን ቃል ማኅበራዊ ወይም ማኅበረሰባዊ ብሎ መተርጎም ሽፍጥ ነው። መንፈሳዊው ንጥረ ነገር ከውስጡ እንዲወጣ ታስቦና ተሰልቶ ካልተተረጎመ በቀር

> secularism ኢመንፈሳዊነት እንጂ ማኅበረ ሰባዊነት ሊሆን አይችልም። ማኅበረ ሰባዊነት ማኅበረ ሰባዊነት ነው። በእንግሊዝኛም social, societal, communal ወዘተ፥ ያሉ አቻ ቃላት አሉት። Secularism/ worldliness በጥሬው ዓለማዊነትና ዓለምን መውደድ ነው። ዓለማዊነት ተድበስብሶ የሚታለፍ ቃል ሳይሆን የአዲስ ኪዳን ቃልም ነው። ከአዲስ ኪዳን ትርጉም አንጻር ሥጋዊነትና ዓለማዊነት የተለያዩ ቃላት ሆነው Secularismን አሳምረው ይፈቱታል። ዓለማዊነት ኢመንፈሳዊነት ነው።

እንዲህ ያለው የዮናስ ትርጉም ከሌላ ፕላኔት የመጣ ካልሆነ በቀር በዚህ ዓለም የሚገኝ የዓለማዊነት ትርጉም አይደለም። ትንሽ ስለ ቋንቋና ስነ ጽሑፍ ስለተማርኩም ቃል እንዴት እንደሚተረጎም አውቃለሁ። ዓለማዊነት ሥጋዊነትና ምድራዊነት እንጂ ማኅበረ ሰባዊነትና ማኅበራዊነት አይደለም። ይህ ዓለማዊነት ነው።

## 6ኛ፥ ተደሳሳችነት (Hedonism)

ይህ ንድፈ አሳብ የስነ ምግባር ፍልስፍና ዘርፍ ሆኖ፥ ‘ደስታ ወይም መደሰት (happiness and pleasure) የሰው ልጅ የመጨረሻው ትልቁ መልካም ነገሩ፥ እርካታው ወይም ግቡ ነው፤’ የሚል ነው። Hedonism ከግሪክ ቃል የመነጨ ሆኖ፥ ἡδονισμός (ሄዶኒስሞስ) ደስታ ወይም እርካታ ማለት ነው።

አንዳንድ ሄደኒስቶች፥ ለምሳሌ፥ ኤፊቆሮሳውያን (Epicureans) የሚባሉት ዓይነቶቹ የስሜት ሕዋሳትና የሥጋዊ አካል ብቻ ሳይሆን የጠቅላላው የአእምሮም ደስታ ዒላማ መደረግ አለበት ባይ ናቸው። ሌሎቹ ግን ራስን ማስደሰትና ደስ የሚል ነገርን ማድረግ፥ ደስታን መፈለግ፥ ኀዘንን ወይም ሕማምን መራቅ የሰው ልጅ ትልቁ እርካታ ነው ባዮች ናቸው።

ወደ ጉዳያችን ወደ ዘፈን ስንመጣ፥ ብዙ ሰዎችን ወደ ዘፈን ቤት እንዲሄዱ የሚያነሳሣቸው የምን ፍላጎት ወይም ምን ፍለጋ ነው ብንል ደስታ፥ መደሳሰት፥ ስሜታዊ ወይም አካላዊ እርካታን ፍለጋ ነው። ለነዚህ ሰዎች ዘፈን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም የአካላዊ፥ ሥጋዊ፥ ስሜታዊ ደስታን ማሳደድ ግባቸው ነው። ዘፈንን በተመለከተ ለምን ወደ ዘፈን እንደሚያዘነብሉ ሲጠየቁ የሚመልሱት፥ ‘ደስ ያሰኛል! ያስደስታል፤ ያረካል።’ ነው።

ሰሎሞን በመክ. 2፥8 *አዝማሪዎችንና አርሆዎችን የሰዎች ልጆችንም ተድላ እጅግ የበዙ ሴቶችንም አከማቸሁ።* ይልና ሌሎችንም ዓይኖቹ የፈለጉትን ነገሮች ምንም እንዳልከለከላቸው ይጽፍና ያንን ክፍል ሲደመድም፤ ቁጥር 11 ላይ፥ *እነሆ፥ ሁሉ ከንቱ*

*ነፋስንም እንደ መከተል ነበር።* ይላል። ወደ ልቡ የሚመለስ ሰው፥ hedonism ወይም ተደሳሳችነት የሰው ሁለንተና አለመሆኑን ያውቃል።

ይህንን ክፍል ሳጠቃልል፥ በመከለስ ልደምድም። ሰዎችን ዘፈናም የሚያደርጉ ስድስት ስሑት ፍልስፍናዎች ወይም ፍልስፍናዊ አካሄዶች እነዚህ ናቸው። 1. አርነታዊነት libertarianism፥ ነጻ ነኝ፤ ልክ ነኝ፤ ማንም ምንም አይበለኝ። ማንም አይናገረኝ። 'ደሞ ባይኔ ማናለኝ ከልካይ ያሻኝን ባይ።' ዓይነቶች ናቸው። 2. አንጻራዊነት relativism፥ አንተም ልክ እኔም ልክ ነን፤ አንተም ባንዳ፥ እኔም ባንዳ፤ ምን አጣላን በሰው በረንዳ? እንደሚሉት ማለት ነው። 3. ገቢራዊነት Pragmatism፥ እስካገለገለ ድረስ ልክ የሚል ነው። 'የትም ፍጪው ዱቄቱን ብቻ አምጪው።' ባይ ነው። 4. ጠቃሚያዊነት utilitarianism፥ ጥቅሙ ካመዘነ ልክ የሚል ነው። 'ምንም ይሁን ጥቅሙ ከከበደ፥ ሚዛን ከደፋ፥ ከጉዳቱ ጥቅሙ ከበለጠ ልክ ነው፤ እልል ብለን፥ አጨብጭበን እንቀበለው።' የሚል ነው። 5. ዓለማዊነት Secularism፥ ዓለም የምትወደው፥ ዓለማውያን የሚወድዱት፥ ለሥጋ የሚመች ከሆነ ልክ ነው፤ የሚል ነው። 6. ተደሳሳችነት Hedonism፥ ነገሩ፥ (ወይም እንደጉዳያችን ዘፈኑ) ሥጋንና ስሜትን ካስደሰተ ልክ ነው፤ የሚሉት ናቸው።

## ስድስቱ ሰበቦች

## 1. የዘፈን ስሜታዊ ጉልበት

ዘፈን ትልቅ ስሜታዊ ጉልበት አለው። ይህ እንዳለውም በማንም ይታወቃል። ዘፈን ግዙፍ ስሜታዊም፥ ስሜት ፈጣሪም ኃይል አለው፤ በእንግሊዝኛ emotional and sentimental የሚሉት ማለት ነው። እኛ ክርስቲያኖች ጌታን በተቀበልን ሰሞን የሰማናቸውን መዝሙሮች ከብዙ ዓመታት በኋላ ስንሰማቸው ወደዚያ የመንፈሳዊ ጅማሬያችን ዘመን እንነጉዳለን፤ እንሄዳለን። በፍቅር እንሰማዋለን። ስሜትን ብቻ ሳይሆን ነፍስና መንፈሳችንንም ይነካዋል።

በልጅነታችን ወይም በወጣትነታችን የሰማናቸውን ዘፈኖች በድንገት ስንሰማቸው ጥንት ያንን ዘፈን የሰማንበት ጊዜው፥ ቦታው፥ ሁኔታው በትዝታ ፈረስ ጋልቦ ከነሙሉ ግዝፈቱና ከሙሉ ክብደቱ ጋር ይመጣል። አንዱ የዘፈናችን ቅኝት ራሱ ትዝታ ነው አይደል? በስሜት ሕዋሳት ውስጥ እንደሚዘልቁ ሌሎች ነገሮች፥ እንደ ሽታና መዓዛ፥ ቃናና ጣዕም፥ በጆሮ የሚደመጥ ዘፈንም የስሜት አንቀሳቃሽ በመሆን ወደ ሌላ ቦታና ወደ ሌላ ጊዜ በምናብ ይወስደናል፤ ያዘዋውረናል። ስለዚህ ፈልገውትም ይሁን ሳይፈልጉት መስማት ብቻውን የሚፈጥረውና የሚያስገባው ሌላ ዓለም አለ። ያ ዓለም

የማናውቀው ምናባዊ ዓለም ብቻ ሳይሆን የምናውቀውና የነበርንበት ዓለምም ነው። ያንን ዓለም ፍለጋ፥ ያንን ጊዜ ፍለጋ ሰዎች ዘፈንን ያደምጡታል። ዘፈን በግስጋሴ መጥቶ የሚጋልበንም፥ ጋልበነው የምንጓዝበት መጓጓዣም ነው። ስሜታዊ ጉልበት አለው።

ሌሎች ዘፈንን ስለ ሙዚቃዊ ውበቱና ልቀታዊ ቅንብሩ ሲሉ በአድናቆት ያደምጡታል። በጥንቃቄና በሙያዊ ስልት የተደራጁትን አጣጣሎች (scores) መስማት ይመስጣቸዋል። በተለይ የቆዩትን ከዘመናዊዎቹ፥ እንደነገሩ የተሠሩትን በሙያዊ ጥራት ከተቀናጁቱ፥ በይዘት ገለባ የሆኑትንና በማጀቢያ የቆነጁትን በቅኔ ውበት ከላቁት ጋር በማስተያየት፥ ልክ ዓይን በስነ ስዕል እንደሚደነቅ በሚሰሙት ረቂቅ ሥራ ይገረማሉ። እነዚህ በመሣሪያ የተቀነባበሩ ሥራዎች አስቀድሞ የተዜሙ ዘፈኖች ወይም መዝሙሮች ሙዚቃዎች ሊሆኑ ይችላሉ፤ ወይም ምንም ዘፈንም መዝሙርም ያልተዜመባቸው አዲስና ወጥ የሆኑ ሥራዎች ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ሙዚቃዎች አዲስና ያልተዘፈነባቸው ሥራዎች ከሆኑ ለሙዚቃዊ ልቀታቸውና ውበታቸው የሚደመጡ ናቸው። ዘፈኖች ከሆኑ ደግሞና ሰሚዎቹ ዘፈኖቹን የሚያውቋቸው ከሆኑ ዘፈንን የሚርቁ ሰዎች ሊፈተኑባቸው ይችላሉ። በተለይ እነዚህ ሰዎች ዘማሪዎች ከሆኑ ሙዚቃዊ ወይም ድምጻታዊ ስልቶችን ለመቅሰም ሲሉ ይሰሟቸው ይሆናል። አንዳንድ ዘማሪዎች ሳያውቁት በዘፈን ዜማ የሚዘምሩት ለዚያም ነው። ዘፈን ጉልበታም ነው፤ ስሜታዊ ጋላቢ ጉልበት አለው። ስለዚህ ሰዎች በዘፈን ይጠመዳሉ፤ ክርስቲያኖችም ዘፈናሞች ሊሆኑ ይችላሉ።

ዘፈን ስሜታዊ ጉልበት አለው ስል ስሜታዊና ስሜት ፈጣሪነቱ ብቻ ሳይሆን አካላዊ ነገሩንም ጭምር ነው። ውዝዋዜውን፥ ጭፈራውን፥ ሰው ከሰው መነካካቱንም ይጨምራል። ጭፈራው ዛሬ ወደ ቤተ ክርስቲያን መድረክም ስለመጣ ዘፈንና መዝሙር በዚህ ረገድ ድንበራቸው ሚሙቶ እየጠፋ ነው። ደግነቱ ጭፈራው ያለው ፍየሎቹ ቤት ነው እንጂ በጎቹ ቤት አይደለም። አንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት የየባሕሉ ጭፈራ ሰለባ እየሆኑ ናቸው።

የጨፋሪዎቹ ጭፈራም ያሳፍራል፤ ያሸማቅቃል። እንደ ምሽት የዘፈን ቤት እንደሚባለው ዓይነት ነው። ዛሬ የጨፋሪዎቹ ቤተ ክርስቲያናት ጭሱም፥ ቦግ እልም መብራቱም፥ የዳንስ ቤቱን ያስንቀዋል፤ ያስከነዳዋል። ጨዋነት ወዲያ ተሽቀንጥሮ የተጣለ ይመስላል። ብዙዎቹ ስሜታቸውን አስተንፍሰው ይወጣሉ፤ ለአንዳንዶች ጭፈራው የታመቀ ጉልበት መቀነሻ ነው። ለአንዳንዶች ያሉበትን የገሃዱን ዓለም መርሻ ነው። አንዳንዶች ደግሞ የጭፈራ አምሮት ማራገፊያ ነው። በየትኛውም ሂሳብ ቢሰላ ግን፥ ይህ አምልኮ ሳይሆን ጭፈራ ነው። ይህ አዲስ ወግ፥ አዲስ ልማድ ነው። ግን አዲስ እንጂ የአዲስ ኪዳን ወግና ትምህርት አይደለም። የዝማሬዎቹ ምቶችም፥ ዜማ አወራረዶችም ለዚህ ተሰናድተው የተቀረጹ ናቸው። በዚያ ላይ ባህላዊው ውዝዋዜ ሲታከልበት ስሜትን ከመስመር ያወጣል። ስሜታዊ ጉልበት ይህንንም ይጨምራል። እነዚህ ተሰርቀው ከዘፈንና ከዘፈናምነት ባህል ወደ ቤተ ክርስቲያን የመጡ አካሄዶች ናቸው።

በዚህ የዘፈናምነት ወይም የዘፈን ስሜታዊ ጉልበት ጉዳይ አንዳንዶች፥ 'በመጽሐፍ ቅዱስ በተለይም በብሉይ ኪዳን እንዲህ ያደረጉ ሰዎች አሉና ይህ እንደ ችግር መወሳት የለበትም፤' ይላሉ። የዘፈንን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጠቀስ ራሱን የቻለ ሰበብ አድርገን ለብቻ እናየዋለን። እዚህ ግን ስሜታዊነቱ ላይ እንቆይ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአምልኮ ውስጥ የተደረጉ አካላዊ እንቅስቃሴዎች እንደነበሩ ታሪክን እናነብባለን፤ ታሪክ ማለት ደግሞ ትእዛዝ አይደለም። አንዳንዶች ዳዊትን እንደ ምሳሌና ምስክር ያቀርባሉ፤ ይህንን የዳዊትን መዝለል የሚቃወሙትን ደግሞ በሜልኮል መስለው ያቀርባሉ። እርግጥ ነው ዳዊት ዘልሎአል፥ ተጫውቶአል፤ ዘፍኖአል (በአማርኛው ዘፍኖአል ነው የሚለው፤ ደንሶአል እንደማለት ነው።)

ታሪክ ውስጥ የተጻፈ ነገር ሁሉ ይደረጋል፤ ይደገማል ማለት ግን አይደለም። ይህ ለዘፈን ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ለማናቸውም ጉዳዮች የምንወስደው እውነት ነው። ይህ ነገር በቀጣይነት ታየ? ተደረገ? ሌሎችም እየዘፈኑ፥ እየዘለሉ ቀጠሉ? ከሁሉም በላይ ታዘዘ? ይልቁንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተከሰተ? ብሎ መጠየቅ ታዳጊ ወይም ከስሕተት የሚታደገን ጥያቄ ነው። የአንዳንድ ዘፋሪዎችን (ዘፋሪ ማለት ዘማሪም ዘፋኝም ማለት ነው።) የአንዳንድ ዘፋሪዎችን አካሄድ ስናይ የብሔረ ሰባዊና ባህላዊ ዳንኪራ ኩረጃና ሽሚያ እየተደረገ ለመሆኑ ምንም አጠያያቂም አጠራጣሪም አይደለም። እነዚህ አካላዊ እንቅስቃሴዎች ከመንፈሳችን ይልቅ ለስሜቶቻችንና አካላችን ቅርብ ናቸው። እግዚአብሔር መንፈስ ነውና የሚመለከው በመንፈስና በእውነት ነው፤ ዮሐ. 4፥24። ስሜት የለንም ማለት አይደለም። መንፈሳዊ ግንኙነት ግን በአካላዊ እንቅስቃሴ አይለካም።

ይህ በዝማሬ አካላዊ እንቅስቃሴ መኖር የለበትም ማለት አይደለም። ባህላዊ ጭፈራዎችንና ስሜታዊ እንቅስቃሴዎችን የአምልኮ ማድመቂያ ማድረግ ግን አግባብ አይደለም። በእንደዚህ ያለው እንቅስቃሴ ሰዎች ናቸው የሚታዩት እንጂ የተቀደሰ ግንኙነት አይከናወንም። አትኩረቱ እንቅስቃሴና ውዝዋዜ ላይ ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት ልብን የማፍሰስ ነገር በጨፋሪውም፥ በሌላው ጉባኤተኛም አይከናወንም። ዓይናችንን ካልጨፈንን የመድረክ ሰዎችንና እንቅስቃሴያቸውን አለማየት አንችልም። ይህ ጭፈራና እንዲህ ያለው አካላዊ እንቅስቃሴና ስሜታዊ መወሰድ ሰዎችን በሳምንት አንድ ቀን እጉባኤ ውስጥ ጨፋሪ ብቻ አድርጎ አያስቀራቸውም። በአዘቦቱ ቀንም ዘፈናም እንዲሆኑ ጥርጊያን ይከፍትላቸዋል።

## 2. የሙዚቃና የዘፈን ባለ ሙያዎችና ሞያተኞች ሚናና ጫና

በሙዚቃ መስክ የተሰማሩ አንዳንድ ባለሙያዎች ክርስቲያን ሙዚቀኞችን የመዝሙር ብቻ ሳይሆን የዘፈን ሙዚቀኞችም እንዲሆኑም ሲሞግቱ ብቻ ሳይሆን ሲያደፋፍሩም ይታያል። ይህንን ሲያደፋፍሩ አንዳንዶች ሙዚቃ እና ሙዚቀኛ መዝሙርን እና ዘፈንን፥ ሁለቱንም በእኩል ማገልገል፤ ለሁለቱም እኩል አጋፋሪ መሆን አለበት በማለት ነው። ሙዚቃ እንደ ሙዚቃነት ከሁለቱም የማይወግንና ሁለቱንም የሚያቆነጅ ጥበብ ነው። ሙዚቃ ከማንኛውም መወገን ባይኖርበትም አንዳንዶች

ደግሞ በመለየት ሳይሆን ሁሉንም አንድ ቅርጫት ውስጥ በመክተት፥ 'ሙዚቃ ሁሉንም ነገር ነው፤ ዘፈንም መዝሙርም ነው፤ ድንበር የለሽ ነው፤' በማሰኘት ነው ተቀባይነት እንዲያገኝ የሚታትሩት።

ይህ ጉዳይ በሙዚቃ ባለ ሙያዎች እና ሞያተኞች አካባቢ ውስጥ ውስጡን ሲያነጋግር ጥቂት ዓመታት ቆይቶ ጎልቶ የወጣው ከሙዚቀኛ ዮናስ ጎርፌ ቤት ያጣው ቤተኛ መጽሐፍ ሕትመት በኋላ ነው። በመዝሙሮቻችን ይዘት ላይ፥ በይዘቶቹ ላይ፥ ከዚያ በፊትም ለዓመታት እየሠራሁ ብቆይም፥ ብጽፍበትም፥ የኔ መጽሐፍ በከፊል የዮናስ መጽሐፍ ምላሽም ነው። የሙዚቃ ባለ ሙያዎች እና ሞያተኞች ልዩነት አላቸው። ባለሙያዎቹ የሙዚቃ ጠበብት ሲሆኑ ሞያተኞቹ ለመኖሪያ ሙዚቃን የሚጠቀሙበት ናቸው። ጌታ በዮሐ. 10 <u>እረኛና ሞያተኛ</u> እንዳለው የመሰለው ልዩነት ማለት ነው።

ሙዚቃም አጃቢና አገልጋይ ሲሆን ከሁለቱ አንዱን ካላገለገለና ካላጀበ ንጹሕ የመሣሪያ ቅንብር ነው። በመሣሪያ የተቀነባበሩ ሥራዎች አስቀድሞ የተዜሙ ዘፈኖች ወይም መዝሙሮች ሙዚቃዎች ሊሆኑ ይችላሉ፤ ወይም ምንም ዘፈንም መዝሙርም ያልተዜመባቸው አዲስና ወጥ የሆኑ ሥራዎች ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ሙዚቃዎች አዲስና ያልተዘፈነባቸው ሥራዎች ከሆኑ ለሙዚቃዊ ልቀታቸውና ውበታቸው የሚደመጡ ናቸው። ሙዚቀኛ ሞያተኛና ለገንዘብ የሚሠራ ከሆነ ለማንና ለምን እንደሚሠራ መወሰን አለበት። ዓላማና ግቡ ምን እንደሆነ ማወቅ አለበት። 'እኔ ባለ ሙያ ነኝና ማንንም ማጀብ እችላለሁ፤ ነገሩም ኪነ ጥበብ ነውና የአንዱ ብቻ እንድሆን መገደድ የለብኝም።' ሊል ይችላል። ያንን ከማለት ጋር አብሮ፥ 'ማጀብ ብቻ ሳይሆን የማጅበው ማንን ነው? ለምንድር ነው?' ማለትም ይጠበቅበታል። የሚተላለፍ መልእክት አለና የመልእክቱ ተባባሪና አስተላላፊም ነው። መልእክቱን አጅቦ የሚያቀርብ ሰው ነው። አንድ ንጉሥ ወይም የአገር መሪ እንደሚታጀብ ያለ አጀብ አጃቢ ነው። የሚያጅበው መልእክቱን ነው። ያ መልእክት የሚያስተላልፈው እሴት ምንድር ነው? ዘፈንን ያለ ጥርጥር እንድንቀበል አስውቦና አስጊጦ፥ ቀምሞና አጣፍጦ፥ አሽሞንሙኖ የሚያቀርብልን ባለሙያ አጃቢነቱን ሙያ ብቻ ካለው የዋኀነት ነው።

ዘፋኝንም ራሱን እንደ ባለሙያ ብቻ አድርገን እንድንመለከትና የትኛውንም ሙያ እንደምናከብር ይህንንም ማክበር እንዳለብን የሚቀርብበት የሙያነት ሙግትም አለ። ሙዚቀኛ ዮናስ ጎርፌ ከመጽሐፉ መታተም በፊት እንደ ማስታወቂያ ባሰራጨው የኦዲዮና ቪድዮ ስርጭት እና በመጽሐፉ የጀርባ ሽፋን ስለ መጽሐፉ ሲናገር፥ *'ይህ መጽሐፍ፥ 'እኔ ሙዚቃ እንደ ማንኛውም ሙያ (አናጢነት ይሁን ዶክተርነት፥ ጋዜጠኝነት ይሁን ፖለቲከኛነት) በማቀርበው ስነ ምግባር ልገምገም እንጂ በደፈናው መወገሬ ይብቃ።'* የሚል የሲቃ ጩኸት የምታሰማበት የሙዚቃ የራሷ ድምጽ ነው።' ብሏል። ሙያን የተመለከተውን ክፍል ብቻ ነው የወሰድኩት።

ጠቅላላው ጉዳይ ዘፈን ስለሆነና ዘፈን እና ሙዚቃ ሞክሼ ሆነው ስለቀረቡ፥ 'እኔ ሙዚቃ' የሚለውን 'እኔ ዘፈን' ብለንም መውሰድ እንችላለን። የመጽሐፉ ዐቢይ አሳብ የኢትዮጵያ ትውፊት እና የኢትዮጵያዋ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሱ ያልኮነነውን ዘፈንን እና ዘፋኞችን ኮንና የሲዖል ማገዶ አደረገቻቸው የሚል ብርቱ ክርክር ነው። እስከ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ጽ/ቤት በመሄድ ቃሉ እንዲለወጥም ጥያቄ

እስከማቅረብ የደረሰው ዘፈን ወይም ዘፋኝነት የሚለውን ቃል ነው። እውነትም የ1997ቱ አዲስ ትርጉም ዘፈን የሚሉትን ቃላት በሙሉ ለቅሞ በማውጣት፥ 'ቅጥ ያጣ ፈንጠዝያ' እያለ ለወጠው። ዮናስ ሙዚቃን ወይም ዘፈንን አቆራኝቶ በሙዚቃ ነው የሚጠራው። እኔ ሙዚቃ ብሎ ንጽጽሩ ከአናጢነትና ዶክተርነት፥ ጋዜጠኝነትና ፖለቲከኝነት ጋር ነው። ፍልስፍናዎቹን ስናይ ገቢራዊነትና ጠቃሚያዊነት በሚሉት ውስጥ ሙያዊና ተግባራዊ ጫናዎችንም ለማሳየት ሞክሬአለሁ።

እነዚህ ነገሮች አናጢነትና ዶክተርነት፥ ጋዜጠኝነትና ፖለቲከኝነት ሙያ ናቸው፤ አውቆ ይሁን እነዚህን ምድቦች የመረጣቸው አላውቅም። ግን ሁለት ዓይነት ሙያ ናቸው። ሌሎቹንም ሙያዎች ብንኮለኩላቸው ከዚሁ ምድብ ይወድቃሉ። አንዱ ወገን የእጅ ጥበብ ሙያ ነው። ሌላው መልእክት አስተላላፊ ሙያ ነው። ቀዶ ጠጋኝ ዶክተር ወይም የቁስል ሐኪም፥ ወይም መደርደሪያና ጠረጴዛ የሚሠራው አናጺ የሚያክመው ሕክምና ወይም የሚያመርተው ውጤት ላይ ነው የማተኩረው እንጂ ከዚያ አልፌ ማንነቱን አልመረምርም። ያ ሙያተኛ ሙያውን ማወቁና መተግበሩ እንጂ ወንድ ወይ ሴት፥ ሽማግሌ ወይ ጎልማሳ፥ አማኝ ወይ ከሐዲ፥ ነጭ ወይ ጥቁር መሆኑን አልጠይቅም። ሐኪም ቤት ሄዶ የዶክተሩን ሃይማኖት የሚጠይቅ ታካሚ የለም። በአንጻሩ ግን ጋዜጠኛውና ፖለቲከኛው መልእክት አስተላላፊ ነው። ንጽረተ ዓለም አስተላላፊ ነው። ብዙ ጋዜጠኞች ለምንድነው ዘጋቢ ከመሆን ባሻገር አንዱ ርዕዮት ላይ ብቻ የሚያተኩሩት? አንድ ፓርቲ፥ አንድ ጎሳ ላይ ብቻ የሚያተኩሩት? ግብ ስላላቸው ነው። ሰባኪዎች ናቸው። ፖለቲከኞችስ? ፖለቲከኞችም እንዲሁ የአንድ ጎራ ሰዎች ናቸው። ካድሬዎች ናቸው፤ ሰባኪዎች ናቸው። እንድንወግን ያደርጉናል፤ ይገፉናል፥ ይጎትቱናል። ቢያንስ ይጎነትሉናል። የሚያስተላልፉት መልእክት አለ።

ዘፋኞችም ሙያተኞች ናቸው፤ ግን የዶክተሮቹ ዓይነቶቹ ሳይሆኑ የካድሬዎቹና የሰባኪዎቹ ዓይነቶቹ ናቸው። የሚያስተላልፉትና የሚያካፍሉት ርዕዮተ ዓለም አለ፤ ንጽረተ ዓለም አለ፤ አይዲዮሎጂ ማለት ነው። እና ዘፋኝን ሙያተኛ ብቻ ነውና እንስማው ብሎ ነገር ለክርስቲያን ዓይንህን ጨፍንና ልምራህ ማለት ነው። ማየት ካልቻልክ እሺ ተመራ፤ ማየት ከቻልክ ለምን ትጨፍናለህ? ዘፋኞች መልእክተኞች ናቸው። መልእክታቸው ምንድነው? ብሎ ያንን መቀበልና አለመቀበል እንዲያው በድፍኑ ብቻ ብናየው እንኳ የምርጫ ጉዳይ ነው መሆን ያለበት። ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ደግሞ ቃሉ ስለ ዘፈንና ዘፋኞች ምን ይላል የሚለውን ስንመረምር ምን አቋም ሊኖረን እንደሚገባ በጣም ግልጽ ነው።

ስለዚህ፥ የሙዚቃና የዘፈን ባለ ሙያዎችና ሞያተኞች ሚናና ጫና መታየት ያለበት ከዚህ አንጻር ነው። ነገሩ እውን ሙያ ነው? አዎን ነው። ግን ሙያ ብቻ ነው? አይደለም። ስብከት ነው፤ መልእክት አስተላላፊነት ነው። 'አዎን መልእክት አስተላላፊነት ነው፤ ግን ታዲያ መርጠን ለምን አንሰማም?' ሊባል ይቻላል። ለመምረጥ እኮ መስማት አለብህ። ለማጣጣም እኮ መቅመስ አለብህ። የምትቀምሰው ከውስጥህ የማይወጣ ከሆነስ? ሱስ የሚያስይዝህ ከሆነስ? አየህ? አየሽ? ዘፋኝ ባለ ሙያ ብቻ አይደለም። ዘፋኝ ካድሬ ነው። ዘፋኝ ሰባኪ ነው። ዘማሪም ሰባኪ ነው።

ዘፋኝ ባለ ሙያ ብቻ አይደለም። የዘፈን ባለ ሙያዎችና ሞያተኞች ሚናና ጫና ስል ይህንን ማለቴ ነው።

## 3. የዘፈን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጠቀስ

'ዘፈን በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሷል፤ የእግዚአብሔር ሰዎችም ዘፍነዋል።' በማለት ዘፈንን ተቀባይነትን ለማቀዳጀት የሚለፉ ሰዎች አሉ። እርግጥ ነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተዘፍኖአል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለተጻፉት ዘፈኖች ምንነት በመጽሐፌ ዘፈን እና መዝፈን የሚሉት ቃላትና ግሦች የተጠቀሱባቸውን ቦታዎች በሙሉ ነቅሶ በማውጣት በእያንዳንዱ ጥቅስ ላይ የቃሉን ትርጉም እና በቂ ማብራሪያ በመስጠት አስረድቻለሁ።

በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ዘፈን እየተባለ የተተረጎመው ቃል በምንጭ ቋንቋዎች በብዙ ቃላት ተገልጧል። መጽሐፍ ቅዱስ በሦስት የምንጭ ቋንቋዎች ነው የተጻፈው፤ በዕብራይስጥ፥ በአራማይስጥ እና በግሪክ። እነዚህን ቃላት በሙሉ ለቅሜ አውጥቼ ከትርጉማቸውና ከዐውዳቸው ጋር አሳይቻለሁ።

> በዕብራይስጥ እኛ ዘፈን ላልነው ቃል 10 የተለያዩ ቃላት ይገኛሉ፤ 1. שִׁיר ሺይር ወይም שִׁירָה ሺይራህ፤ 2. מְחוֹלָה ምኾላህ፥ ምሖላ፤ חוּל ኹውል ወይም חִיל ኺይል 3. צָחַק ጻኻቅ፤ שָׂחַק ሣኻቅ 4. עָנָה ዓናህ עַנּוֹת አኖውት፤ 5. כָּרַר ካራር 6. חָלַל ኻላል፤ 7. רָקַד ራቃድ፤ 8. נְגִינָה ንጊይናህ፤ 9. דּוּץ ዱውጽ፤ 10. מִרְזַח ሚርዛኽ፤ በአራማይስጥ ደግሞ זְמָר ዝማር፤ ተብሎአል። አንድ ላይ በብሉይ ኪዳን 11 ቃላት አሉ ማለት ነው። ከተደራቢዎቹ ጋር ከዚያ በላይ ናቸው። በግሪክ ቋንቋ እኛ ዘፈን ያልነው ቃል በ7 የተለያዩ ቃላት ተገልጦአል፤ 1. ὀρχέομαι ኦርኬኦማይ፤ 2. συμφωνίας ሱምፎኒያስ 3. χορῶν ኮሮን፤ 4. κῶμος ኮሞስ፤ 5. παίζω ፓይዞ፤ 6. τρυφήν ትሩፌን፤ እና ἐντρυφῶντες ኤንትሩፎንቴስ፤

ዘፈን ለሚለው ቃል ከተዳበሉት ቃላት ጋር በጠቅላላው ከ20 የሚበልጡ የምንጭ ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ። በነዚህ 20 ያህል ቃላት 50 ጊዜያት ያህል ተጽፎአል። ቃላቱ በቁጥር ብዙ መሆናቸው የሚያሳየን ትልልቅ ነገሮች አሉ። (1) ዘፈን በባህላቱ ውስጥ ሰፊ ቦታ እንደነበረው፥ (2) ቃሉ የተጻፈባቸው ቋንቋዎች ምን ያህል የዳበሩ፥ የደረጁ መሆናቸውን፥ (3) ቃሉ በድኃ ቋንቋ ምክንያት የፈለገውን እንዳይል ወይም ያልፈለገውን እንዲል ሊገደድ እንደሚችል ነው። ቃሉ የማይለውን እንዲል ከማስገደድ እንድንታቀብ መጠንቀቅ ያለብን ምንጩ ቃል በበቂ ሁኔታ ትርጉሙ ስለሚታወቅ ነው። የአማርኛውን ገላ. 5፥21 ሲተረጉሙት መጥፎ ሰርጀሪ ሠሩበት ካልን እጅግ ብዙ ቃሉን የምንፈትሽበት መፈተሻዎች እንዳሉን መርሳት የለብንም። በጣም ብዙ መፈተሻዎች አሉን። መነሻችን የዘመናችን ፍልስፍናዎችና ባህል መሆን የለበትም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተደረጉት ታሪኮች ሁሉ እንድናደርጋቸው የታዘዝናቸው ወይም የተፈቀዱ ናቸው ማለት አይደለም። ይህንን ከሰበቦቹ ውስጥ አንደኛውን የዘፈናምነት ሰበብ ስንመለከት አንሥተነዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተሳደቡት ስለተሳደቡ አንሳደብም። የገደሉት ስለገደሉ አንገድልም። የሰከሩት ስለሰከሩ አንሰክርም። ወይም በአንጻሩ፥ የለገሡት ስለለገሱ፥ የዘመሩት ስለዘመሩ፥ ያረሱት ስላረሱ፥ የሠዉት ስለሠዉ፥ የገነቡት ስለገነቡ፥ እነዚህን ነገሮች እናደርጋለን ማለት አይደለም። አድርጉ የተባልነውን እንጂ ስለተደረገ ብቻ አናደርግም። የዘፈኑት ስለዘፈኑም አንዘፍንም። አድርጉ ከተባልን ግን እናደርጋለን። አታድርጉ ስለተባልንም አናደርግም። አድርጉ የተባልነውን ካላደረግን፥ ወይም አታድርጉ የተባልነውን ካደረግን ተላልፈን የራሳችንን አሳብ እየፈጸምን ነን ማለት ነው። ዝፈኑ ካልተባልንና ከዘፈንን፥ ወይም አትዝፈኑ ከተባልንና ከዘፈንን እየተላለፍን ነን።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዘፈን ተጠቅሶአል፤ ሰዎችም ዘፈን ዘፍነዋል። ከባህል መግለጫነት የተነሣ ዘፍነዋል፤ ለሠርግና ለደስታ ዘፍነዋል፤ ስለ ድል አድራጊነትና ስለ ጀብድ ሥራ ዘፍነዋል። ማንም ሕዝብ ባህልና ወግ አለው። ስለዚህኛው ስለ ባህል ነጥብ ለብቻ እመለሳለሁ። ዘፈንም በየባህሉ ውስጥ ስፍራና ሚና አለው። ዘፈን ከባህል መገለጫዎች አንዱ ነው። ስለዚህ ሕዝብ ባለበት ዘፈንም አለ። አይሁድ ሕዝብ ናቸው፤ ስለዚህ ዘፈንም አላቸው።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የምናገኛቸው አንዳንዶቹ ዘፈኖች መዘፈናቸው ብቻ ሳይሆን ይዘታቸው ተጽፈውልናልና መልእክታቸው ምን መሆኑን እናውቃለን። ለምሳሌ፥ በ1ሳሙ. 18፥7 *ሴቶችም፡- ሳኦል ሺህ፥ ዳዊትም እልፍ ገደለ እያሉ እየተቀባበሉ ይዘፍኑ ነበር።* በተባለበት ነገሩ ዘፈን ተብሎአል። መዝፈናቸው ብቻ ሳይሆን የዘፈናቸው ምንነትም ተገልጦአል። ይህ ጉሮ ወሸባዬ ጉሮ ወሸባ እንደሚባለው ዓይነት የጀግና መወድስ ነው። ውዳሴ ዳዊት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ፥ በዘጸ. 15፥20-21 *የአሮን እኅት ነቢይቱ ማሪያምም ከበሮ በእጅዋ ወሰደች ሴቶችም ሁሉ በከበሮና በዘፈን በኋላዋ ወጡ። ማርያምም እየዘመረች መለሰችላቸው። በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤ ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባሕር ጣለ።* የዘፈናቸው ወይም የመዝሙራቸው ይዘት ግልጽ ነው። ይህኛው ለእግዚአብሔር የቀረበ መወድስ ነው። ሁለቱም ዘፈን ተብሎአል። ነጥቡ የዘፈኑት ወይም ያዜሙት ነገር፥ መልእክቱ ምንድር ነው? የሚለው ነው እንጂ ነገሩ ዘፈን መባሉ አይደለም። ዘፈን ቅርጹ ወይም ስሙ ነው፤ መልእክቱ ይዘቱ ምንድር ነው? ብለን ነው መጠየቅ ያለብን።

ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት መዝፈኑ በቃሉ ተጽፎአል፤ 1ሳሙ. 6። በስፍራው የዘፈነው ነገር ምን መሆኑ አልተጻፈም። ግን ስፍራውን ስናጠናው ምን ሊሆን እንደሚችል መረዳት አይሳነንም። የዳዊት ዘፈን ለሰዎች ወይም ለነገሮች የተሠዋ ዘፈን አለመሆኑን የምናውቀው በመዝሙር መጽሐፍ (ወይም መዝሙረ ዳዊት) ውስጥ የተጻፉትን የእርሱን ስም የያዙ ከ70 በላይ መዝሙሮች ይዘት ስናጤን ነው። ዘፈን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጽጻፉ ብቻውን፥ ወይም የተከበሩ የእግዚአብሔር ሰዎች መዝፈናቸው መነገሩ ብቻውን ዘመናዊውን ወይም የዘመናችንንና የባህላችንን ዘፈን ቀድሰን እንድንቀበል የሚያደርገን አካሄድ አይደለም። ዘፈን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጠቀሱ

ብቻውን አያጸድቀውም። የዘፈንን ምንነት እና የዘፈኑን ይዘት አስቀድመን ማወቅ አለብን። ይህ ሦስተኛው ሰበብ ነው። የዘፈን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጠቀስ ዘፈንን ፈቃድ አይሰጠውም።

## 4. የባህልና ትውፊት ጉዳይ

በአንድ በኩል አንድ ማኅበረ ሰብ የባህልና የትውፊት እስረኛ ነው። እንደ ሕዝብና እንደ ዜጋ ወይ ባህላችንን ከማክበራችን የተነሣ ከእምነታችንም የምናስቀድም ንልሆን እንችላለን ወይም የምናመቻምች እና በባህሉ የምንወሰድ ልንሆን እንችላለን፤ ወይም ባህሉ ለእምነት መገዛት አለበት የምንል ሃይማኖተኞች ነን። ባህልና እምነት በተቀየጡበት ሃይማኖታዊ ባህል ወይም ባህላዊ ሃይማኖት ባለበት ይህ ችግር አይደለም። እንደ አማኝ ወይም ክርስቲያን ደግሞ እምነታችን ከባህላችን ይበልጣልና፥ ይቀድማልና፥ የእምነታችን መመሪያ ከባህላችን ይቀድማል።

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈባቸው ቋንቋዎች ሕዝቦች ባህል ነበራቸው። ብሉይ ኪዳን በዕብራይስጥ ነው የተጻፈው (ከጥቂት ክፍሎች በአራማይስጥ መጽጻፍ በቀር።) ይህ የአይሁድ ቋንቋ ነው። አይሁድ ባህልና ወግ አላቸው። ሕጉ ቢጨመርበትም ወግ ነበራቸው። አዲስ ኪዳን በግሪካዊና ሮማዊ ባህልና ወግ ውስጥ ነው የተጻፈው። በሁለቱም ኪዳናት ሕግ ያልሆኑ፥ በሕጉ ውስጥ ያልተጻፉ ልማዶች መኖራቸው አልፎ አልፎ ፍንጥቅ ተደርጎልናል። ለምሳሌ፥ ሩት. 4፥7-8 ላይ በዘመኑና ከዚያም በፊት የግዢ ማጽኛ እንዲሆን ጫማ አውልቆ መስጠት የተለመደ መሆኑ ተጽፎአል። በሕጉ የለም፤ ልማድ ግን ነውና በባህላቸው ቦታ ነበረው። በ1ሳሙ. 2፥13 ሕዝቡ መሥዋዕት ሲያቀርብ ሥጋው ሲቀቀል የካህኑ ሎሌ በሜንጦ ይወስድ ነበር። ልማድ ተብሎአል። በአዲስ ኪዳን ለአገር መሪ በበዓል የወደዱትን አንድ እስረኛ የመፍታት ልማድ ነበረ፤ ማቴ. 27፥15። የአገናነዝ ልማድም ነበራቸው፤ ዮሐ፣ 19፥40።

ስለ ብሉይ ኪዳን አይሁዳዊ ባህል እና አዲስ ኪዳን የግሪክና ሮም ባህል በመጠኑ ካየን <u>ባህል ምንድር ነው? ብለን መጠየቅ አለብን።</u> ባህል ተቀባይነትን ያገኘ የአንድ ሕዝብ ወይም የአንድ የሕዝብ ክፍል መታወቂያ ወይም መለያ የሆነ ልማድ፥ ደንብ፥ ወግ፥ አመለካከት ነው። ሕዝባዊ ወይም ማኅበራዊ መስተጋብር ነው። አንድን የሕዝብ ክፍል ከሌላ ለይቶ ማወቂያም ነው። ባህል በቋንቋና ስነ ቃል፥ ስነ ጥበቦች፥ በተለያዩ ድርጊቶች፥ አምልኮዎችና ሥርዓቶች ከአንዱ የዚያ ሕዝብ ትውልድ ወደ ቀጣዩ ትውልድ ይተላለፋል። ባህል የማይሰረዝ በድንጋይ ላይ የተጻፈና ለሁሉም እና ለሁልጊዜ ሊሆን የተገባው ሕግ አይደለም። ባህል ያድጋል፣ ይቀየራል፤ ይለወጣል፤

ይሟሟል፤ ይወርሳል፤ ይወረሳል፤ ይታወሳል፤ ይዘነጋል። ከሌላ ባህል ይወስዳል፤ ለሌላ ባህል ይሰጣል።

እንደሌላው ሕዝቦች ባህሎች ሁሉ በአገራችን ባህሎችም ዘፈን የተወደደ ሕዝባዊና ዓለማዊ እሴት ነው። ባህላችን ዘፈን ወዳድ ስለሆነ ብንዘፍንስ? ዘፈን ከመልካም እስከ መጥፎው አለበትና፥ 'ፍርዱን ለራሳችን አድርገን መርጠን ልንዘፍንና ልንሰማ እንችላለን፤' ቢባልስ የሚል አመለካከት ጥቂት ባልሆኑ ሰዎች ዘንድ ይገኛል። ይህ ቀደም ሲል በፍልስፍናዎቹ ውስጥ ካየነው የአርነትና የለዘብተኛነት ወይም አንጻራዊነት አመለካከት ጋር ይያያዛል። ባህላችን ዘፈንን ወደደ ማለት ግን ሕዝቡ ሁሉ፥ ዜጋው ሁሉ ዘፋኝ ይሆናል፥ ዘፈንን ያደንቃል ማለት አይደለም። ባህላችንም ዘፈንን ይውደድ እንጂ በዓለማዊ ዘፈን እና በመንፈሳዊ ወይም ሃይማኖታዊ ዝማሬ መካከል ያለውን ልዩነት ያውቃልም፤ ያከብራልም።

ከባህላችን ጋር ትውፊታችንም አብሮ መወሳት አለበት። ባህል በአንድ የተወሰነ ወቅት ያለ የአንድ ሕዝብ ልማድና ወግ ከሆነ፥ ትውፊት ደግሞ ከአንድ ትውልድ ወደ ቀጣይ ትውልድ የሚተላለፍ የአንድ ሕዝብ የባህል፥ የልማድ፥ የሃይማኖት፥ የስነ ቃል ተላላፊ ክምችት፥ ቅርስ፥ ወይም ውርስ ነው። ትውፊት በዘመናት ውስጥ የዳበረና የዳጎሰ ስለሆነ፥ የብዙ ትውልዶች ድምር ውጤትም ስለሆነ በአንድ ትውልድ ውስጥ አንለውጠውም። ትውፊታችን ዘፈንን ዓለማዊ ካለው እኛ ዓለማዊ አይደለም ለማለት የትውፊታችንን ያህል መኖር ወይም መቆየት አለብን። ትውፊትን አብዮት አካሂደን አንቀይረውም።

በአገራችን ትውፊትም ዓለማዊ ዘፈን እና መንፈሳዊ መዝሙሮች የተሰመረላቸው መስመር አለ። ትውፊታችን መንፈሳውያን ወይም ሃይማኖታውያን ሰዎች እንዲዘፍኑ ወይም ዘፈንን እንዲያደናንቁ አያደፋፍርም፤ አያበረታታም። ሆኖም በባህላችን ዘፈን ሰርጾ የገባ በመሆኑ በብዙ የኑሮ ክፍላችን፥ ከልደት እስከ ሞት ባለው ሂደትና እርከን ሁሉ ዘፈንን እናገኛለን። ባህላችን ወደ ሃይማኖት ያደሉ በሆኑት ዘንድ በቀር የዘፈን አፍቃሪነትን ያበረታታል። በጥቅሉ በትውፊታችን ግን ዘፈን የተሰመረለት መስመር አለ። ዘፈን ዓለማዊ ነው። እንግዲህ ዘፈናምነት ሲጫንብን ባህላችንም ትውፊታችንም ተረግጦ መሆኑ ይግባን። ዘፈንን እንደ ላባ የለሰለሰ ልብስ አልብሰው ወደ ክርስቲያኑ ልቡና ለማስረጽ የሚፈልጉ ሰዎች ይህ የዘፈን ጥላቻ የትውፊታችን ችግር እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ አለመሆኑን ሊያሳዩ ሲዳክሩ በአንድ በኩል ትውፊቱ ዘፈንን ዘፈን ማለቱን እያመኑ መሆናቸው ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ዘፈንን በተመለከተ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ያልደገፈውን ትውፊቱ አለመደገፉንም እያመኑ ናቸው። ይህ አራተኛው ነጥብ ነው። ባህል ዘፈንን ስለወደደ አንወድድም፤ ትውፊት ዘፈንን ስላጸደቀ ወይም

ስላወገዘም አይደለም ዘፈንን የምንጠላው ወይም የምንወደው፤ ቃሉ በሚለን ነው የምንሄደው።

## 5. ባህላዊ አመቻማችነት

ከባህል ጋር የተያያዘ ሆኖ ሳለ፥ ግን ለብቻ እንድንመለከተው ያስፈለገበት ምክንያት ባህላዊ አብዮቶች ሲካሄዱ መንፈሳዊ እሴቶች ስለሚጨፈለቁ ነው። የባህልን እና ክርስትናን መስተጋብር በመጠኑ በትነን እንድናይ ያስፈለገው ብሔረ ሰባዊነት የአንድ አገር ፍልስፍና ዐቢይ ክፍል ሲሆን ባህል ይገዝፍና፥ ባህል ሁሉንም ነገር ይሆንና ሃይማኖትንም ለመዋጥ ይቃጣዋል።

ባህል ተቀባይነትን ያገኘ የአንድ ሕዝብ ወይም የአንድ የሕዝብ ክፍል መታወቂያ ወይም መለያ የሆነ ልማድ፥ ደንብ፥ ወግ፥ አመለካከት ነው። ሕዝባዊ ወይም ማኅበራዊ መስተጋብር መሆኑን አይተናል። በባህሎች ውስጥ ስንቅር ባህል ወይም ንዑስ ባህል የሚባል ደግሞ አለ፤ (subculture) ይባላል። በአንድ ሕዝባዊ ባህል (mainstream culture) ውስጥ የሚገኝና ከባህሉ ገዢ አቋም በመጠኑ ያፈነገጠ ሆኖ ችለውት የሚኖሩት አናሳ ባህል ነው። በአለባበስ፥ በአነጋገር ዘዬ፥ በሰውነት አያያዝ፥ በጺም እና ጸጉር አስተዳደግ፥ ወዘተ ሊገለጡ ይችላሉ። ይህም ሰዎችን የመጠምዘዝ የራሱ መጠነኛ ጉልበት አለው። ባህል የማይሰረዝ በድንጋይ ላይ የተጻፈና ለሁሉም እና ለሁልጊዜ ሊሆን የተገባው ሕግ አይደለም። ባህል ያድጋል፣ ይቀየራል፤ ይለወጣል፤ ይሟሟል፤ ይወርሳል፤ ይወረሳል። ከሌላ ባህል ይወስዳል፤ ለሌላ ባህል ይሰጣል። የተለያዩ የሕዝብ ክፍሎች በአንድ አገር ሲኖሩ አንዱ ባህል ጎልቶ ወይም ገንኖ ሊወጣ ይችላል፤ ወይም የሁሉም ባህል የሚካሄድባት ኅብረ ባህላዊ (multicultural) አገር ልትሆን ትችላለች።

ከባህሉ ማፈንገጥ ደግሞ በአንድ ማኅበረ ሰብ አንድ ትውልድ ውስጥ የሚገኝ ክፍል ወይም ወገን ባህሉን ሲንቅ፥ ሲጥስ፥ አዲስ የራሱን ባህል ሲመሠርት ነው፤ አጸፋ ባህል (counterculture) ይባላል። በአሜሪካ በ1960ዎቹ ወጣቱ ትውልድ የተጀመረው የቢትኒክስ፥ ሂፒስ፥ ዉድስቶክስ አካሄድ ዓይነቱ ነው። ይህ አጸፋ ባህል በ1970ዎቹ ቢደበዝዝም አሻራው ሳይደበዝዝ ቆይቷል። በአሜሪካ የተከበሩ ባህሎችን፥ ማኅበራዊ እሴቶችን መናቅ፥ በቡድን አብሮ መኖርና ነፃ ፍቅር የሚሉትን ወሲባዊ ልቅነትን መለማመድ፥ ማሪዋና እና ሌሎችም ሱስ አስያዥ ዕፆችን መውሰድ፥ ፖለቲካዊ አቋሞችን መናቅ፥ ወዘተ፥ ይገኙበታል።

ይህ ባህልን በጠቅላላው መልኩ ስንመለከት ነው። ወደ ክርስትና ስንመጣ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ባህል ሙሉ በሙሉም ባይሆን በአብዛኛው የአይሁድ ባህል ነው። ይህ ታዲያ ንጥር እና ንጹሕ፥ የሁሉም ሊሆን የተገባ ባህል ነው ማለት አይደለም። የአይሁድ ባህል፥ እንደ ሌላው ባህል ሁሉ ነው። ልብ እንበል፤ አይሁድ ገና ሕዝብ ሳይሆኑ ነው ወደ ግብጽ የገቡት። ወደ ግብጽ ሲገቡ ቁጥራቸው አንድ መቶም አይሞላም ነበር። ከዚያ በፊት ከአብርሃም እስከ ያዕቆብ ያለው ሦስት ትውልድ ከከለዳውያን ዑር ባህል፥ ከሁለት ወንዞች መሐል (ወይም መስጴጦምያ) ባህል እና የተስፋዋ ምድር ከተባለችው የከነዓናውያን አገር ባህል ጋር ትከሻ ለትከሻ የተጋፋ ባህል ነው። ኋላ የግብጽ ሲጨመርበት የአራት ሕዝብ ባህል ቅይጥ ነበር ማለት ነው። አይሁድ ሕዝብ የሆኑት እነዚህን ባህላዊ ዳራዎች ይዘው በግብጽ ውስጥ ነውና የግብጻውያንን ባህልም ሸምተዋል።

ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን የተወለደችው በአይሁድ ባህል ውስጥ ቢሆንም ያ ዘመን ግሪካዊና ሮማዊ ባህልና አመለካከት ዓለሙን የገዛበት ዘመን ነበር። ቤተ ክርስቲያን ብዙ ሳይቆይ ወደ አሕዛብ ውስጥ ሰርስራ ልትገባ ችላለች። ከሁለቱ፥ ማለት፥ ከአይሁድ እና ከአሕዛብ አንድ የራሱ የሆነ አካል መሥራት የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ነበረ። ለብዙዎቹ የአሕዛብ ወገኖች ባህል ከሃይማኖት ጋር የተቆራኘ ነው። የብዝሃ አማልክት እና ጣዖት አምላኪዎች እንደመሆናቸው ሃይማኖቱና ባህሉ አብሮ የተለወሰ ነው። ዛሬም በአንዳንድ አሐዳውያን ማኅበረ ሰቦች (unitary society) ሃይማኖትና ባህል የተቆራኙ ናቸው።

የክርስቶስ ወንጌል ነጻ ካወጣቸው በኋላ በአዲስ ኪዳን የምናገኛቸው አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ከቀድሞ ልማዳዊ ሃይማኖታቸው ሲላቀቁ ከባህላቸው ውስጥ የቱ ማኅበራዊው፥ የቱ ሃይማኖታዊው መሆኑን ለመለየት ሲቸገሩ ይስተዋላል። የገላትያ፥ የቆላስይስ፥ የሮሜ እና የቆሮንቶስ መልእክቶች እነዚህን ጉዳዮችም ያወሳሉ። ጴጥሮስ የጻፈላቸው የተበተኑ ወገኖችም ይህ ችግር ነበረባቸው። ይህንን ሰበብ ስጀምር ብሔረ ሰባዊነት የአንድ አገር ፍልስፍና ዐቢይ ክፍል ሲሆን የየብሔረ ሰቡ ባህል ይገዝፍና፥ ባህል ሁሉንም ነገር ይሆንና ሃይማኖትንም ለመዋጥ ይቃጣዋል ብያለሁ። ይህ እውነት ነው።

ባህላችን ተጨቁኖ ነበር የሚሉ ወገኖች ባህላቸውን ማደሳቸው መልካም ሆኖ ሳለ ማግነናቸውና ሌላውን ባህል በተራው እንዲጨቁን ወይም የሃይማኖት ምትክ እንዲሆን መሠልጠን ሲጀምር አደጋ ነው። ወደ ዘመናችን ባህሎች ስንመጣ ደግሞ፥ ድኅረ ዘመናዊነት ሁሉን ተቀባይ የሚያደርጋቸው በመሆኑ ይህንን ታክከው ባህሎች ራሳቸውን የቻሉ ሃይማኖቶች እስከመሆን እየደረሱ ነው። ስለዚህ ኃጢአት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገባ ቀንዳምና ጥፍራም ሳይሆን ቀንዱን ተከርክሞ፥ ጥፍሩን ተቆርጦ

ነው። ቆይቶ ግን ቀንዱም፥ ጥፍሩም ያድጋሉ። ዘፈንም እንደ ሕዝባዊ ባህል አንድ ገጽታ ወይም ንዑስ ባህል ድኅረ ዘመናዊነትን ተተግኖ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊገባ እየተንደረደረ ያለ ይመስላል። የሚገባበት አንዱ መንገድ ባህላዊነትን ተተግኖና ተላብሶ ነው። ባህላዊ ልብስ መልካም ነው። ባህላዊ ልብስን ተላብሶ ባህላዊ ጭፈራም ሲመጣስ? ያ ችግር ነው። 'ባህላዊ ልብስ ወድደን ባህላዊ ጭፈራ እንዴት እንጠላለን?' ሊባል ይቻላል። ጥሩ ጥያቄ ነው። የምንጠላው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ልብሱ ሳይሆን ስለ ዘፈኑና ስለ ጭፈራው የሚናገረውና የሚያስተምረው ስላለው ነው።

ይህ ባህላዊ አመቻማችነት ራሱን ችሎ ለብቻው በሌላ ጊዜ እናገርበታለሁ። ግን ክርስቲያኖች ላይ ከሚደረግ ባህላዊ ጫና የተነሣ፥ ለባህል ከሚሰጥ ክብር የተነሣ እምነትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና ላይ ጫና ተደርጎ እንደ ቃሉ ያልሆኑ ነገሮችም ተቀባይ እንዲሆኑ ሲደረጉ ቆም ማለት አስፈላጊ ነው። ከባህል ውስጥ ሁሉም ነገሮች ለባህሉ ሰፊ ተካፋዮች ወይም ቢያንስ፥ ለሰፊው ሕዝብ፥ መልካም የመሰሉ እንጂ በባህሉ ውስጥ ላሉትም መቶ በመቶ ተቀባይነት ያላቸው ላይሆኑ ይችላሉ። ይልቁንም በአንድ የሕዝብ ክፍል ተቀባይነት የኖራቸው ባህሎች በሌላ የሕዝብ ክፍል የተጸየፉ ሊሆኑም ይችላሉ። በዚህ ረገድ የባህላዊ ስነ ሰብእ (Cultural Anthropology) ጥናቶች ብዙ ምሳሌዎችን ያቀርባሉ። ባህል የማኅበራዊ መስተጋብር መገለጫ ዘዬ ነው። ይህን በመጀመሪያ እንያዝ።

ሌላው፥ በዚያው በአንዱ ባህል ውስጥ ያሉት ነባር ባህሎች ራሳቸው በማኅበረ ሰቡ ማኅበራዊ ስነ ልቡና ማደግ ወይም የሕሊና ንቃት መዳበር የተነሣ አሮጌና ኋላ ቀር ተደርገው ሊናቁና ሊጣሉ ይችላሉ። በአገራችን በደርግ ዘመን መጀመሪያ ሰፊ መሠረት ተጥሎለት የተጀመረው የቻይና ቅጂ 'የባህል አብዮት' ይህን ሊያደርግ ሞክሮ ነበር። ከንቃተ ሕሊና በተጨማሪ መንፈሳዊ መረዳት ወደ ግለ ሰቡ ወይም ማኅበረ ሰቡ ክፍል ሲገባ ከመንፈሳዊ እሴቶቹ ጋር ነው የሚገባው። መንፈሳዊ ስል ጠቅላላ መንፈሳዊ ኹነትን መናገሬ ቢሆንም ይህኛው ጉዳያችን ስለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘት ስለሆነ በተለይ ስለ ክርስትና መናገሬ ነው። ወንጌል ወደ አንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ወይም ወደ አንድ የሕዝብ ክፍል ሲገባ መንፈሳዊው እሴት ባህላዊውን ቀለም ብዙውን ጊዜ ይበርዘዋል፤ ቆይቶም ይለውጠዋል። የወሊዱና የጋብቻው፥ የቀብሩና የልቅሶው፥ የሥራና ግንኙነቶች መስተጋብሮች ቅርጽና ይዘት በቃሉ መታየትና መከርከም ይጀምራሉ።

ይህ ብረዛና ቅየራ ጥሩ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ እንደ ባህሉ ጠቃሚነትና እንደ ተሟጋቾቹ ጥንካሬ አከራካሪ ሊሆን ይችላል። ወደ ዘፈን ስንመጣ ዘፈን፥ መዝሙር፥ ዜማ፥ ቅኔ፥ ሙዚቃ፥ የሙዚቃ መሣሪያዎች፥ ወዘተ የባህል መንጸባረቂያ መሣሪያዎች እንዲሁም ራሳቸው ነጸብራቆቹም ናቸው። የባህል ገጽታዎች ናቸው።

ታዲያ ስለሆኑ ብቻ በእምነት ላይም ሊሰለጥኑ ይገባል ወይ? አይገባም። ክርስትናና ባህል ለምርጫ ቢቀርቡ መራጩ ክርስቲያን መምረጥ የተገባው እምነቱን ነው። እምነቱ በባህሉ ላይ ጫና ሊፈጥር ይገባዋል እንጂ ባህሉ እምነቱን ሊቀርጽለት መልቀቅ እና መፍቀድ የለበትም። ባህል መልካም ገጽታዎች እንዳሉት ግልጽ ነው፤ ክርስትና ግን በመላው መልካም ስለሆነ በባህሉ ውስጥ የሚገኙት መልካም ነገሮች ሁሉ በዚህ ውስጥም ይገኛሉ።

ወንጌል ወደ አይሁድም ወደ አሕዛብም ሲገባ በመጀመሪያ የለወጠው ባህልን አይደለም። ባህልን የመለወጥ ተልእኮም አይደለም ጌታ የሰጠው። ዓለማችን የሚያስፈልጋት የባህል ለውጥ ወይም የባህል አብዮት አይደለም። የዓለማችን ወይም የሰው ልጆች መሠረታዊ ችግር ባህል ሳይሆን ኃጢአት ነው። ችግሩ ኃጢአት ከሆነ መፍትሔው የባህል ቅየራ ሳይሆን አዳኝ ነው። አዳኙም ኢየሱስ ነው። ወንጌል ውስጥን፥ መንፈስን፥ መንፈሳዊ ማንነትን ነው በመጀመሪያ የሚለውጠው። ይህ ውስጣዊ ለውጥ ከውስጥ ይጀምርና አድማሱ እየሰፋ ይሄዳል። ይህ የተለወጠ ማንነት ባህሉን ሊፈትሽና ከቃሉ ጋር ከተጣጣመ ሊቀበለውና አዲሱንና ዋናውን ተልእኮውን ሊያስርጽበት፤ ካልተጣጣመ ደግሞ ሊገፋውና ወዲያ ሊለው ይችላል፤ ይገባልም። ባህል በአዲሱ ማንነቱ ላይ በግዴታ ሊጫንበት አይገባም። በአገራችን አንድ ሰው ጌታን ሲቀበል የሚደርስበት አንዱ ስደት ባህሉን መጣሉ ነው። ከሃይማኖታውያኑ ዘንድም እንኳ ከሃይማኖት ይልቅ ስለ ባህላቸው ነው ለመበቀል የሚነሡት። ከእነዚህ ተበቃዮች አንዳንዶቹ ስለ ሃይማኖታቸው እንዲያውም እውቀትም፥ ደንታም የሌላቸው ናቸው።

በባህል ውስጥ ወደሚገኝ ዘፈን ወይም ዝማሬ ስንመጣ በየትኛውም ዓለም ዓለማዊና ሥጋዊ ዘፈን እና መንፈሳዊ መዝሙሮች ምንም ድንበር የሌላቸው አይደሉም። በምዕራቡም ሆነ በምሥራቁ ዓለም ይህ ድንበር የተሰመረ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ የወንጌል ተልእኮ ባለ አደራ ሆነው ወንጌልን ይዘው የመጡልን መልእክተኞች (ሚስዮናውያን) በብዙው ምዕራባውያን ናቸውና ዘፈኑንም መዝሙሩንም እኩል ባስተማሩን ነበር። ዛሬ ዘፈናሞች ሊያደርጉን የሚፈልጉ ሊነግሩን እንደሚሞክሩት በአሳባሪ፥ በጥሻና በጓሮ ሳይሆን በጎዳና ወደ ቤተ ክርስቲያን ባስገቡልን ነበር። 'ዘፈን ምንም ችግር የለውም፤ እኛም እንሰማለን እናንተም ስሙ' ማለት ይችሉ ነበር። አላሉንም። እስከ ዛሬ ድረስም ዘፈንና መዝሙር እንደ ወረተኛ ጓደኞች ቆሎ እየተጓረሱ አብረው በኖሩ ነበር። በእርግጥ ቢፈለጉና ቢመረመሩ ምናልባት፥ ምናልባት እንዲህ ያሉ ዘፈንና መዝሙርን በአንድ ቀንበር ጠምደው ሊያርሱበት የሚፈልጉ ከሺህ አንድ ወይ ሁለት አይታጡ ይሆናል። ከሺህ ስንዴ አንድና ሁለት እንክርዳድ አይደንቅም። ግን እንዲህ አይደለም። ከወንጌላዊ ክርስትና ስር መስደድ ከአንድ ክፍለ

ዘመን በኋላ ዘፈን አሁን ጉዳይ መሆኑ የሚያሳየው እስከ ዛሬ ላለፉት መቶ ያህል ዓመታት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዘፈን ስፍራ ኖሮት እንደማያውቅ ነው።

ልብ እንበል፤ ይህች ዓለም በአዳም ስትወድቅ ሁለመናዋ ነው የወደቀው። ይህ የሰውን መንፈሳዊ ማንነት ወይም ሁኔታ ብቻ የሚናገር አይደለም። የሰው ስሜታዊ፥ ሞራላዊ፥ አእምሮአዊ፥ አካላዊ፥ ማኅበራዊ፥ ባህላዊ ማንነቱ ሁሉ ነው የተበከለው። ባህላችን (የትኛውም ባህል) ከወደቀ ሰው የመነጨ ነው። ባህል ራሱ ተዋጅቶ ለእግዚአብሔር ክብር መዋል የተገባው እንጂ እንደ ተቋም ከክርስቶስ አካል ጋር መደራደርና ቦታ መሻማት ያለበት ነገር አይደለም። ባህል የረከሰ ሰው የሠራው ማኅበራዊ ግኝት ነው እንጂ አስቀድሞ የተፈጠረ 'ንጹሕ ባህል' የሚባል ነገር ኖሮ ሰው ኋላ ተፈጥሮ እዚያ ውስጥ አልገባም። ባህልን የሠራ ሰው ነው፤ ወይም ባህል የሰው ሥራ ውጤት ነው።

ዘፈን የባህል መግለጫም እንደመሆኑ መጠን፥ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ በባህል ውስጥ የተጻፈ በመሆኑ ዘፈን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጉልህ ተጽፎ ይገኛል። ቀደም ሲል እንዳየነው ዘፈን እንደ ስም እና እንደ ግስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከ50 ጊዜያት በላይ የተጠቀሰ ቃል ነው።ከጅምሩ መታወቅ ያለበት ቁም ነገር የቃሉ ምን ያህል መጠቀስ ብቻ ሳይሆን የቃሉ ምንነትና ተግባራዊ ግንዛቤው ነው። ዘፈንን እና መዝፈንን በተመለከተ እውነት ላይ፥ ማለትም፥ ቃሉ ላይ ቆመን በእውቀት መነጋገር አለብን። ቅንዓታችንም በእውቀት የሆነ ቅንዓት ሊሆን ተገቢው ነው። ሙዚቃንና ዘፈንን በተመለከተ ኢትዮጵያዊው ክርስቲያን ማኅበረ ሰብ (ይህን ስል ጠቅላላውን ወንጌላውያን አማኞች ማለቴ ነው) አሁን ያለውን የዘፈን መረዳት ያገኘው ከባህሉ ሳይሆን ከቃሉ መሆኑ መታወቅ አለበት።

ባህላችንም ሆነ የአገራችን ባህላዊ ሃይማኖቶች ዘፈን ወዳድ ቢሆኑም እንደ ክርስቲያን የዘፈን ትርጉማችን እና ግንዛቤያችን ከባህላችን ወይም ከሌላው አገር ባህልም መሆን የለበትም። ቃሉ ስለ ዘፈን የሚለውን ማወቅ ብቻ ሳይሆን መቀበልም ግዴታችን ነው። ባህሎቻችን ክቡር የመሆናቸውን ያህል ጉድፎችም አሉባቸው። አገራችን ብሔረሰቦችንና ባህሎቻቸውን ማድነቋ ድንቅ ቢሆንም፥ ለክርስቲያኖች ባህሎችን በቅዱስ ቃሉ መፈተሽና መመዘን እንጂ በጅምላ መግዛት አልተፈቀደም። ለባህል ማጎብደድና ቃሉን በውኃ ማቅጠን ክርስቲያናዊ አካሄድ አይደለም። ለሥልጣንና ለሥራ፥ ለመመረጥና ለመሸለም ተብሎም ጤናማ ያልሆኑ ባህላዊ ንጥረ ነገሮችን መቀበል የግዴታ ቀንበር ሆነው በአማኞች ላይ ሊጫኑ የተገባ አይደለም። ባህላዊ አመቻማችነት ጤናማ አይደለም። ባህላዊ አመቻማችነት ለባህል ለማጎብደድ ሲባል እምነትን ለውርርድ የማቅረብ ስሕተት ነው። የባህላዊ አመቻማችነት ጉዳይ አምስተኛው ነጥብ ነው።

## 6. ዘፈን ኪነጥበብ ነው።

'ዘፈን ከፊልም ወይም ቴያትር የተለየ ኪነ ጥበብ አይደለም፤ ዓለማዊ ፊልም ካየህ ዘፈን አለመስማት ወይም ማውገዝ ግብዝነት አይደለም ወይ? ግጥም የምትሰናማ የምታነብብ ከሆንክ፥ ግጥሙ ላይ ዜማ ሲጨመርበት ለምን ትጠየፈዋለህ?' የሚለው ሙግት ነው። ይህ ሁሉ ገብ ያልሆነ ደካማ ሙግት ነው። ሙዚቀኛ ዮናስ ጎርፌ ለመጽሐፉ መጽጻፍ መንደርደሪያና ማኮብኮቢያ የሆነው በአንድ መጽሐፍ ምረቃ ላይ ተገኝቶ ያንን የተመረቀውን መጽሐፍ መሳይ ወይም ያንኑ መጽሐፍ ራሱን በዜማ አድርጎት፥ በሙዚቃ አጅቦት ቢያቀርበውና ታዳሚውን ቢጋብዝ ይመጣሉ ወይስ አይመጡም የሚል አሳብ ነው።

በሌሎች ብዙ የተናገረባቸው መድረኮች ላይም በድግግሞሽ ያነሣው አሳብ፥ 'ግጥምን ወድደን ግጥም ላይ ዜማ ስንጨምርበት ለምን ነው የተጠላ የሚሆነው?' የሚለው ነው። ምክንያቱ ቀላልም ግልጽም ነው። ይህንን አሳብ በመጽሐፌም ጠቅሼዋለሁ። <u>ዜማ የግጥሙ ሙጫ ነው።</u> ዜማ ግጥሙን አእምሮአችን ውስጥ የሚለጥፈው መለጠፊያው ነው። ምርጊቱ ነው። በልጅነታችን ያነበብናቸውን ግጥሞች ከብዙ ጥቂቱን ልናስታውሳቸው እንችላለን፤ ልንረሳውቸም እንችላለን። አንዳንዶቻችን ከሌሎቻችን ይበልጥ ልናስታውስ እንችላለን። ግጥም ላይ ዜማ ስንጨምርበት ግን ልክ እንደ ብረት ማጎተም ነው። ቅርጽ ይዞ የማይለቅቅ ይሆናል።

ግጥም በዜማ ከቀረበ ያ ዜማ ወይ መዝሙር ወይም ዘፈን ይሆናል። መጽሐፍ ግን በዜማ አይቀርብም። እንደ ኦፐራ ያሉት ረጃጅም ግጥሞች እንደ መጽሐፍ ካልተቆጠሩ በቀር፥ መጽሐፍ በዜማ አይቀርብም። ፍቅር እስከ መቃብርን ወይም ኦሮማይን፥ ወይም ሌላ ዳጎስ ያለም ያላለም መጽሐፍ በዜማ አይቀርብም። በእልህ አቀርባለሁ የሚል ሙዚቀኛ ሊኖር አይችልም አይባልም፤ ይችላል። ቢቀርብም ያኔ ለምርጫ ልንጋበዝ እንችላለን። ይህ ነገር ጆሮ ሊሰጡት የተገባው ነው? ወይስ አይደለም? የማለት ምርጫ። ነገሩም ጠቅላላው፥ ወይ ዘፈን ወይም መዝሙር ይሆናል። ለምሳሌ፥ ጥቁር ደምን (አንዳርጌ መስፍን)፥ ወይም መናኙ ወንጌላዊ (የወንጌላዊ ዮሐንስ አንሼቦ ታሪክ በተመስገን ሳህለ)፥ በዜማ ቢቀርብልን፥ ወይም ቤት ያጣው ቤተኛን ራሱን 275ቱንም ገጽ፥ ወይም መዝሙረ ዳዊትን በሙሉ፥ መጽሐፉን በሙሉ፥ 150ውንም ምዕራፍ በዜማ ቢያቀርቡልን፥ አንዱ የብቀላ ዘፈን ነው፤ ሁለተኛው የወንጌላዊ ዜና ሕይወት ነው፤ ሦስተኛው የሙዚቃና መዚቀኝነትና ዘፈናምነት ዘፈን ነው፤ አራተኛው

ግን ቃሉን የሆነ መዝሙር ነው። አሁንም ምርጫው የራሴ ነው። ይዘቱ፥ ምንነቱ ይበልጥ ግልጽ ያደርግልኛል እንድመርጠው ወይም እንድጥለው።

ዘፈን ኪነ ጥበብ ነው? አዎን፤ ነው። ኪነ ጥበብ ሁሉ ዘፈን ነው? አይደለም። አንዱ ከሌላው ይልቅ ጠልቆ የመግባት ባህርይ አለው? አለው። የግጥም ሥራዎችን ወይም ፊልምን ወይም ልብ ወለድ ሥራን ወይም ስነ ስዕልን ከዘፈን ተርታ የማናስቀምጠው፥ አንደኛ፥ ዘፈን ገብቶ የማይወጣ በመሆኑ ነው። ሁለተኛም፥ <u>በቃሉ ውስጥ የታገደ፥ የተከለከለ በመሆኑ ነው።</u> አራት ነጥብ። ቃሉ አይልም የሚለውን ድኩም ብቻ ሳይሆን ውሸታም ሙግት አይተነዋል፤ ቃሉ በሮሜ 13፥13፤ 1ጴጥ. 4፥3፤ ገላ. 5፥21 ይከለክለናል። ኮሞስ በሚለው ቃል መቆመር እንደማንችል በመጽሐፌ በሰፊው ጽፌበታለሁ።

መጽሐፌ ታትማ መውጣቷን ተከትለው የተላኩልኝ በርካታ ጥያቄዎች አሉ። ከዚህ አሳብ ጋር የተያያዘው አንዱ ጥያቄ እንዲህ የሚል ነው፥ '*የዘፈን ሀጥያትነትን ልታሳይ ከሄደችበት ኢ-ምክኑአዊ መንገድ . . .*' ይልና፥ መጽሐፏን ማለቱ ነው፤ '*መጽሐፍዎ ዘፈንን ከጥበብ ሰፈር ልታኖረው ባትወድም የሰውን የውስጥ ማንነት (ነፍስ እና መንፈስን) ዘልቀው ከሚገቡት ወይም እንደሚይዙ የጥበብ ስራዎች እንደ አንዱ ታስቀምጥልናለች። ሙዚቃ እና ግጥምን ለየቅል እንደ ጥበብ ተቀብለን የሁለቱ ተዋህዶ በደፈናው ጥበብ ሊሆን አይችልም ማለት በምን አይነት ምክንያታዊነት ነው? ሌላው የጥበብ ስራ ሁሉ ግድ መንፈሳዊነት ሊኖረው ይገባል ወይ?*' የሚል ጥያቄ ነው።

ግጥም ጥበብ ነው፤ ዜማም ጥበብ ነው። ሁለቱን ሲደባለቁም ጥበብ ነው። ዘፈንም ጥበብ ወይም አርት ነው። ጥበብነትን መቃወምና አለመቃወም ወይም መካድና ማጽደቅ አይደለም ጉዳዩ። እኔ በመጽሐፏ ውስጥ ዘፈንን በምክኑያዊ ወይም ኢምክኑያዊ መንገድ አይደለም ኃጢአት መሆኑን ለማሳየት የሞከርኩትም የምሞክረውም። ዘፈን ኃጢአት መሆኑን ለማሳየት ምክኑያዊነትን ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስን ነው የተጠቀምኩት። ቃሉ ኃጢአት ካለው፥ ካወገዘው፥ የኛ ሎጂክ ወይም ምክኑያዊነት ከላይ አንድ ቀለም ልጦ ሌላ ቀለም ሊቀባው ይችላል እንጂ ውስጡን አይለውጠውም። የኛ ሎጂክ ምንነቱንና ውስጡን ካልለወጠው ደግሞ የነገሩን ትክክለኛ ምንነቱን የምናነብበውና የሚመራን መጽሐፍ ባሳየን መልኩና ባሳየን ልኩ እንናገራለን።

እንዝፈን ወይስ እንዘምር? በኢትዮጵያ በተመረቀች ዕለት ቃል ያቀረበው ወንድም ጌታሁን ሔራሞ ነበረ። ከ1ነገ. 3 የሰሎሞንንና የሁለቱን ጋለሞቶች ታሪክ ሲያካፍል አንዲቱ የሞተውን የራሷን ልጅ ወስዳ በሌላዋ ብብት ካደረገች በኋላ ሕያው የሆነውን

የዚያችኛዋን ወስዳ አቅፋው አደረች። በማግሥቱ የሕያዉ ልጅ እናት በብብቷ ያለው የሞተው ሕጻን የራሷ ልጅ አለመሆኑን አወቀች። ያ ነበር ወደ ሰሎሞን ጉዳዩ የደረሰበት ምክንያት። ልክ እንደዚያው፥ ዘፈናምነት የራሳችን የሆነውን ሕያው የሆነ የአምልኮ ዜማና ዝማሬያችንን ወስዶ የኛ ባልሆነ በሙት ዘፈን ሊተካብን የሚወድ አታላይም፥ ዘራፊም ነው። ሕያው በረከታችን በሙት ባእድ እንዲለወጥብን መፍቀድ የለብንም። ዘፈናምነት እንደ ቫይረስ ነው። ቫይረስ በራሱ ሕይወት ስለሌለው ሙሉ ሴል ስላልሆነ፥ የሚጣበቅበትን ነገር፥ ሌላ ሴል፥ ሕይወት ያለው ሴል ይፈልጋል። እንደ ኮሮና ቫይረስ ወይም እንደ ኤድስ ቫይረስ፤ ራሱን ከሕያው ሴል ጋር ያጣብቃል። ደግሞም በቀላሉ የሚገባ፤ ከዚያ በቀላሉ የማይወጣ፥ ወይም ቢወጣና ሲወጣ የሚተወውን ነገር ተክሎ የሚወጣ፥ ወይም ጭራሹኑም የማይወጣ ቫይረስ ነው ዘፈን።

ክርስቲያን እና ዘፈን የሚለው አሳብ ሲወሳ የምንቆምበትና የምንከራከርለት ጉዳይ ዘፈን የኛ አይደለም፤ አይመስለንም፤ እንደ ክርስቲያን ዘፈንን ልንዘፍንና ልናዘፍን፥ ልናጅብና ልንታጀብበት፥ ልንሰማውና ልናጣጥመውም የተገባን አይደለንም፤ ዘፈን ኃጢአት ነው የሚል ነው። ይህንን ስንል ዋና የሥልጣን ምንጫችን መሆን ያለበት ምንም ሳይሆን ቅዱስ ቃሉ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ቃሉ ተሳስቷል፤ ተሳስቶ ተተርጉሟል የሚል ውኃ የሚያነሣ መከራከሪያ ከኖረ መልካም ነው። በዚያ እንከራከራለን።

መከራከሪያችን ታዲያ የምዕራቡ ወይም የምሥራቁ ባህል መሆን የለበትም፤ ራሱ ቃሉ ነው መሆን ያለበት። 'ቃሉ ሊል የፈለገው ይህ ነው' ብለን ስሜታችንን እና ዘመናዊ አገሮችና ባህሎችና ፍልስፍናዎች ዘፈንን የሚተረጉመበትን መንገድ እናጢን ከተባለም ድንቅ ነው፤ ያንንም ቀደም ሲል ፍልስፍናዎቹን ባየንበት ልክ እናየዋለን። ያ ግን ለክርስቲያን ከቃሉ በታች የሆነ መሚገቻ ነው። ከቃሉ ቀጥሎና ከቃሉ በታች የሆኑ ሌሎች መሚገቻ ነጥቦች ሊኖሩ ይችላሉ፤ እኔም አሉኝ። እነዚህን ከቃሉ ቀጥሎና ከቃሉ በታች የሆኑ ሌሎች የምላቸውን ስድስት ፍልስፍናዎችና ስድስት ሰበቦች ነው እዚህ ያወሳሁት። እነዚህ ሁሉ 12ቱም፥ ሌሎችም ተጨምረውበት፥ ሁሉም ከቃሉ በታች ናቸው። ቃሉ አንዴ ብቻ እንኳ አትዝፈኑ፤ ዘፈን የሥጋ ሥራ ነው፤ በዘፈን የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃል፤ በቀን እንደምንመላለስ በአገባብ እንመላለስ፥ በዘፈን አይሁን ካለ በቃ ሌላ ምን እንፈልጋለን?

በመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት አዳዲስ እንቅስቃሴዎች ይወለዳሉ ያድጋሉ። አንዱ እንቅስቃሴ Theological Interpretation of Scripture ወይም TIS የሚባለው ነው። የTIS ዓላማ ቤተ ክርስቲያንን መሠረት ያደረገ ከዘመናዊው እና ድኅረ ዘመናዊው ዘመን በፊት ወደነበረው ለውጥ ፈጣሪ የቃሉ አጠናን እና አፈታት ላይ ማተኮር ነው። እነዚህ ዘመናዊዎቹ አፈታቶች የራሳቸውን አጀንዳ ወደ ቃሉ ውስጥ

እየሳጉ ቃሉን ያላለውን እንዲል እያደረጉት ናቸው። ለምሳሌ፥ Feminist አነባበቦች ይገቡና Feminist Theology ይፈጥራሉ። Homosexual አነባበቦች ይገቡና Homosexual Theology የተቀቡ አስተምህሮዎች ይዘው ይወጣሉ። ቃሉን ማክበር ትተን የሰዎችን ስሜት ማንበብ ስንጀምር፥ ያንን ስሜት ይዘን ወደ ቃሉ ስንገባ የሰዎችን ስሜት ማገልገል እንጀምራለን። ዘፈናምነትን ይዘን ወደ ቃሉ ስንገባ ዘፈን ዘፈን ሳይሆን ቅጥ ያጣ ፈንጠዝያ ነው እንዲል እናደርገዋለን።

ፈንጠዝያ በአማርኛ ብንጠቀምበትም የአማርኛ ቃል አይደለም። ፈንጠዝያ አለቃ ደስታ ተክለ ወልድ በመዝገበ ቃላታቸው እንዳመለከቱት[3] ቃሉ የግሪክ ምንጭ ያለው ነው። φαντασία (ፋንታሲያ) የሚል ነው። ግሱ ወይም ምንጩ φαντάζω (ፋንታዞ) የሚል ነው። የሚታይ ማድረግ፥ የሚመለከቱት ማድረግ ማለት ነው። የእንግሊዝኛው fantasy, fantasize, fantastic, phantasm, phantasma, phantasmagoria, phantom ወዘተ፥ ከዚህ የመነጩ ናቸው።

ትርጉሙ የሚታይ ነገር፥ አስደናቂ ትእይንት፥ የሚታይ የሚመስል ነገር ማለት ነው። በዓይን ወይም በአሳብና በምናብ የሚያዩት ግሩም ነገር ማለት ነው። ያለ የሚመስል የሌለና የማይጨበጥ ነገርም ነው። አንዳንዴ አስፈሪና አስደንጋጭ የሆነ የሚታይ ነገርም ሊሆን ይችላል። ቃሉ በአዲስ ኪዳን ውስጥ አንድ ጊዜ ተጽፎ ይገኛል፤ በሐዋ. 25፥23 አግሪጳና በርኒቄ በብዙ ግርማ እንደመጡ በተጻፈበት። ብዙ ግርማ የሚለው ነው። አብረቅራቂ መልክን ለማሳየት የተጠቀሰ ቃል ነው። የሚታይ የተጠቀሰው። ዘፈንን (κῶμος ኮሞስ) ቅጥ ያጣ ፈንጠዝያ ለማለት ከአማርኛ ወደ ወደ ኋሊት ወደ ግሪክ የተሄደበት አካሄድ አስገራሚ ብቻ ሳይሆን በራሱ ቅጥ ያጣ አካሄድ ነው።

ዘፈን ወዳድ ወይም ዘፈናም ትውልድ ድምጹን ከፍ አድርጎ ሲጮህ፥ እንደ ምዕራቡ ዓለም ግብረ ሰዶማውያን ድምጹ ሰሚ ያገኛል፤ ቀልብ ይቀልባል። እንደ ገደል ማሚቶ መስተጋባት ይጀምራል። ከቃሉ ጋር የሚያቆራኙለት ይፈልጋል። ጥቂት ጥቅሶች ፈልገው ሲያቆራኙለት ይንጠለጥልባታል። 'ዘፈን እኮ ጥበብ ነው፤ ጥበብ ደግሞ መልካም ነው። ከጥበብ አንዱን መርጠህ ሌላውን መጥላት አድልዎ ነው።' ይሉሃል። አድልዎ ሳይሆን ቃሉ ነው ዘፈንን ያወገዘውና የከለከለው። እውነቱ ይህ ነው። ቃሉ፥ ሦስት አራቴ አይደለም፤ አንዴ ብቻ ካለም ያ በቂ ነው። የቃሉ አፈታት ስሜት ከሰጠ ሌላ ስሜት አትፈልግለት። የቃሉ ትርጉም ትክክል ከሆነ ሌላ ትርጉም አትፈልግለት።

ስደመድም ስድስቱን ወደ ዘፈን የሚጠሩንን ሰበቦች እንደገና ልጥቀሳቸው፤

---

[3] *ደስታ ተክለ ወልድ ገጽ 987።*

1. የዘፈን ስሜታዊ ጉልበት። 2. የሙዚቃ ባለ ሙያዎችና ሞያተኞች ሚናና ጫና። 3፣ የዘፈን በቃሉ መጠቀስ፤ 'ዘፈን በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሷል፤ የእግዚአብሔር ሰዎችም ዘፍነዋል።' የሚል ሰበቡ መሆን፥ (excuse ይሉታል በእንግሊዝኛ) ሰበብ ፈላጊነት። 4. የባህልና ትውፊት ጉዳይ ባህላችን ዘፈን ወዳድ ስለሆነ ብንዘፍንስ? ዘፈን ከመልካም እስከ መጥፎው አለበትና፥ 'ፍርዱን ለራሳችን አድርገን መርጠን ልንዘፍንና ልንሰማ እንችላለን፤' የሚል የለዘብተኛነት ወይም የአርነት አመለካከት። 5. ባህላዊ አመቻማችነት፤ ለባህል ለማንብደድ ሲባል እምነትን ለውርርድ ማቅረብ። 6. ዘፈን ኪነጥበብ ነው። 'ዘፈን ከፊልም ወይም ቴያትር የተለየ አይደለም፤ ዓለማዊ ፊልም ካየህ ዘፈን አለመስማት ወይም ማውገዝ ግብዝነት ነው፤ ግጥም የምትሰናማ የምታነብብ ከሆንክ፥ ግጥሙ ላይ ዜማ ሲጨመርበት መጠየፍ ግብዝነት ነው፤' የሚለው ደካማ ሙግት ናቸው።

## ምዕራፍ ፲፤

# ክርስቲያንና ዝና

# (ተጸናቂነትና ታዋቂነት)

ዝና ወይም ዝነኝነት የሚለውን ቃል ገናናነት፥ ስመ ጥርነት፥ በሚሉ አቻ ቃላት መጠቀምም ይቻላል። ስመ ጥር እና ስመ ጥሩ ተመሳሳይ አይደሉም። ስመ ጥሩ ጥሩ ስም ያለው ማለት ሲሆን ስመ ጥር ስሙ የተጠራ ማለት ነው። የስም መጠራት በጠቅላላው መታወቅ፥ የስም መታወቅ ወይም ዝነኝነት ነው። የስም መታወቅ በመልካም መጠራትም ላይሆን ይችላል። በመጽሐፍ ቅዱስ በዱሮ ዘመን ስማቸው የታወቀ ኃያላን የተባሉ የመጀመሪያ ሰዎች ኔፊሊም ናቸው፤ ዘፍ፣ 6፥4።

በብሉይ ኪዳን ቋንቋ ዝና ማለትና ስም ማለት አንድ ናቸው። የዝና መሰማት የስም መጠራት ነው። ለምሳሌ፥ በዘኍ. 14፥15 ዝናህን የሰሙ አሕዛብ፦ ሲል ዝና የሚለው ቃል የስም መጠራት፥ መደመጥ ወይም መሰማት (שֵׁמַע ሼማዕ በሌሎች ጥቅሶች שׁמַע ሾማዕ፥ שְׁמוּעָה ሽሙውዓህ) ነው። በዘኍ. 16፥2 ዝናቸውም የተሰማ የማኅበሩ አለቆች የተባሉት ስማቸው የወጣ እንደማለት ነው፤ ዝና የተባለው ስም (שֵׁם ሼም) ነው። ዝና እውቅና ነው። ከላይ በሁለቱ ጥቅሶች ውስጥ እንዳየነው ለእግዚአብሔርም ለሰውም ውሎአል። በኢያ. 9፥9፤ ኢሳ. 66፥19፤ ዳን. 9፥15፤ ዕን. 3፥2፤ ለእግዚአብሔር ተነግሮአል። በኢያ. 6፥27 ለኢያሱ፥ በ1ነገ. 4፥31፤ 10፥1-7፤ 2ዜና 9፥1-6፤ ለሰሎሞን፥ በ2ዜና 26፥8 እና 15 ለዖዝያን፥ በአስ. 9፥4 ለመርዶክዮስ፥ ለሌሎችም ተጠቅሶአል። የአገርም ዝና ይወጣል፤ ሕዝ. 16፥14-15። በአዲስ ኪዳንም ቃሉ መሰማት፥ መደመጥ፥ የስም መውጣትና መግነን ነው፤ ለጌታ ተጠቅሶአል፤ ማቴ. 9፥26፤ 14፥1፤ ሉቃ. 4፥14፤ 7፥17።

ገናና ሰው ዝነኛ ይሆናል። ዝና የገናናነት አቋራጭ ነው። መግነን የዝና መብዛትና መባዛት፥ አየሩንና አገሩን መሙላት ነው። ዝና ከሞገስም ጋር ተቀራራቢነት አለው፤ ግን የተለያዩም ናቸው፤ ምሳ. 3፥4 *በእግዚአብሔርና በሰው ፊትም ሞገስንና መልካም ዝናን ታገኛለህ።* ይላል። ይህ ውጤት ነው። የሆነበት ምክንያትም በቁ. 1 እንደተጻፈው ሕጉን ባለመርሳትና ትእዛዛቱን በመጠበቅ የሚሆን ነው። ይህ ሞገስ የስም መጠራት ብቻ አይደለም፤ ከምስጋናና መወደድ ጋር የተያያዘ ተቀባይነት ነው።

## ታዋቂነት የጨዋታው ስም ነው።

እዚህ የምንመለከተው ዋና የዝና አሳብ ታዋቂነት ነው። ከታዋቂነት ጋር ተደናቂነትም አብሮት አለ። ስለዚህ፥ 'ክርስቲያንና ዝና' ስል ክርስቲያንና ታዋቂነት ወይም ተደናቂነት ማለቴ ነው። በእንግሊዝኛ ይህ አሳብ የሚናኝባቸው በርካታ ቃላት ቢኖሩም፥ fame, status, influence, charisma, renown ጥቂቶቹ ናቸው። አሁን ታዋቂ የሆነውና በስፋት የሚዘዋወረው መደበኛ ቃል celebrity የተባለው ነው። የተደናቂነት ጥማትና አባዜ ነው። ይህን አሳብ በዚህ ዝግጅት ውስጥ ዝና ወይም ዝነኝነት ከማለት ይልቅ በአብዛኛው ተደናቂነት የሚለውን በመጠቀም እቀጥላለሁ። ተደናቂነት ጤናማ ያልሆነው ዝነኝነት ማለት ነው። አድናቆትን እስኪጠግቡና ከጥጋብ በላይም መብላት እንደማለት ነው። ብዙ መብላት ያስገሳል፤ ያስተፋል። ሁለቱም የመብሉ ወይም የተበላው ነገር ተረፈ ምርቶች ናቸው።

ሰዎች ስማቸው እንዲጠራ፥ እንዳይረሳ፥ ታዋቂና ተደናቂዎች እንዲሆኑ ይፈልጋሉ። አንዳንዶች ያንን ይሆናሉ። መሆናቸውን ለጌታ ክብር የሚያውሉት፥ በመታወቃቸው ወንጌሉ እንዲሰበክ፥ ጌታ እንዲነገር የሚያደርጉ ይኖራሉ። ሌሎች ብዙዎች ደግሞ ታዋቂነትን ግባቸው አድርገው ብቻ ይኖራሉ። በራሳቸው ዝና ራሳቸውን ጠቅልለው መጠቅለያውም፥ ዕቃውም እነሱኑ ሆነው ይኖራሉ።

ዝነኝነት በጥሩ ዝና፥ በጥሩ ስም ሊወጣ ይችላል። ጥንትም ዛሬም ሰዎች ታዋቂ ለመሆን ጀብድ መፈጸም፥ ምርኮን መማረክ፥ ግዳይ መጣል፥ ሕዝብን ከጠላት መታደግ፥ ወይም ሥርቶ መበልጸግ፥ ለሌላ መትረፍ እና የመሳሰሉትን ያደርጋሉ፤ እነዚህ ነገሮች ስምን ያስጠራሉ። ወይም ግፍን እንቢኝ ብሎ፥ አልታዘዝ ብሎ መሸፈትና ማሸፈትም ስምን ሊያስጠራ ይችላል። በሙያቸውና በቁም ነገራቸው ታዋቂ የሆኑና የላቁ ሰዎች ዝናን ያተርፋሉ። ስም በመጥፎም ሊጠራ ይችላል፤ በጭካኔና በክፋትም ሰዎች ታዋቂ ይሆናሉ። ወራሪ ሆነው፥ ሰዎችን ፈጅተው፥ መንግሥት ገልብጠው፥ ሥልጣን ጨብጠው ታዋቂ ይሆናሉ። በእንግሊዝኛ በጎዎቹ famous እንደሚባሉት፥ ክፉዎቹ notorious ይባላሉ። የስም መጠራት በሁለቱም በኩል ሊሆን ይችላል።

አንዳንድ ሰዎች ዝና ወዳድ ናቸው። መታወቅን፥ መደነቅን አብዝተው ይፈልጋሉ። ለመታወቅና ለመደነቅ የማይቆፍሩት ጉድጓድ፥ የማይነቀንቁት አጥር የለም። ዝና ወይም የስም መጠራት በራሱ ጥሩም መጥፎም አይደለም። ዝና ታዋቂነትን ይወልዳል። ታዋቂነትን አፈንፍኖ የመፈለግ ልክፍት ሰዎችን ጨምድዶ ሲይዝና እነዚህ ሰዎች መታወቅን፥ መደነቅን፥ ሁሌ መወሳትን፥ አለመረሳትን ግባቸው አድርገው ሲራመዱ በድጥ መንገድ ላይ እየሄዱ መሆናቸውን አያስተውሉም። መታወቅና መደነቅ በራሱ ወጥመድ ሊሆንም ይችላል።

የተደናቂ ወይም celebrity አካሄድ ከመደነቅ አልፎ ወደ መመለክ መጠጋት ነው። ይህ ራሳቸውን ከፍ፥ ሌሎችን ዝቅ የሚያደርግ አካሄድ ብቻ ሳይሆን ራሳቸውን የሚነጥል አባዜ ነው። እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን አብዝተው ከፍ ያደርጋሉ፤ ያተልቃሉ፤ ዋጋቸውን ያንራሉ፤ ይለያሉ። የታዋቂነትና ተደናቂነት ችግርም ይህ ራስን የማላቅ፥

የማተለቅና የመለየት ጉዳይ ነው። ይህ ትልቁ ችግር ነው። በተለይም ባለንበት በዚህ በዲጂታልና ኢንተርኔት እንዲሁም የማኅበራዊ ሚድያ ዘመን ሰዎች በቀላሉ ዝናን ሊያተርፉ ይችላሉ። እዚህ የማወሳው ስለ ክርስቲያኖች ነው፤ ወይም በዋናነት ክርስቲያኖችን ታሳቢ አድርጌ ነው ይህን ጉዳይ የምመለከተው።

ታዋቂ ሰዎች ታዋቂነታቸውንና ተደናቂነታቸውን ለበጎ ተግባር፥ ግብና ዓላማ ሊያውሉት ይችላሉ። አንዳንድ ክርስቲያኖች ያንን ታዋቂነት ለመንግሥቱ መስፋትና ለወንጌሉ መበሰር ሊያውሉት ይችላሉ። ሌሎች ደግሞ፥ ክርስቲያኖችም ጭምር፥ ለራስ ከፍታ ይገለገሉበታል። ታዋቂነት ስውር ኃይል አለበት፥ ሌሎችን የመሳብ መግነጢሳዊ ጉልበት አለው፤ የሚሳቡ ሰዎች ደግሞ አቻ ሳይሆኑ የበታችና አድናቂዎች ናቸው። ከዚያ ሰው ጋር መሆን፥ ጥቂት ጊዜ አብሮት ማሳለፍ፥ ፊርማውን ማግኘት፥ እጁን መጨበጥ፥ አብሮ ፎቶ መነሣት ተፈላጊ ነገሮች ናቸው።

ለባለ ዝናዎቹ ተደናቂዎች ይህ የሰዎች ግርግርና ጋጋታ የእኔነታቸው (የegoዋቸው) ምግብና መጠጥ ነው። ተደናቂና ተፈላጊነታቸውን የሚያንረው፥ የሚያጦዘው፥ ወደ ሰማይ የሚያጉነው ጉልበት ነው። እውነተኛና ጤናማ ዝነኝነት ብዙውን ጊዜ ተፈልጎ አፈንፍነውት የሚመጣ አይደለም። ከትልቅ ቦታም የሚመነጭ አይደለም። ብዙ ታዋቂ ሰዎች ከትንንሽና አልባሌ ቦታዎችና መነሻዎች የበቀሉ ናቸው። ቴዎድሮስ ባይኖር ቋራን የምናውቅ ጥቂቶች የቀበሌው ሰዎች ብቻ ናቸው። ምኒልክን ባናውቅ አንኮበርንም፥ ኃይለ ሥላሴን ባናውቅ ኤጀርሳ ጎሮን፥ ወይም ዐቢይ ባናውቅ በሻሻንም እንዲሁ አናውቅም። ሰዎቹም የሚጠብቃቸውን ዝናና አድናቆት አያውቁትም። የመጽሐፍ ቅዱሳችን ሐደሳ አስቴርን እንደምትሆን አታውቅም ነበር። እነዚህ በጊዜያቸው ማድረግ ያለባቸውን አድርገው ዝና ተከትሎአቸዋል።

አንዳንድ ታዋቂዎች ታዋቂ የሚሆኑት ቆይተው ነው። ከሆኑ በኋላ ግን ያልታወቁ የነበሩበትን ዘመንና ሁኔታ በፍጥነት ይረሱታል። የJoel Osteenን የመጀመሪያ ስብከት ሰምቼ ወድጄለት ነበር። ፍርሃቱና ትሕትናው፥ ቃሉን እንደ ቃሉ ማካፈሉ ትዝ ይለኛል። ከዚያ በፊት አባትየውን ኦስቲን (ጆን ኦስቲንን) ነው በስምና በአንዳንድ ጽሑፎች የማውቀው። በአጭር ጊዜ ግን፥ ከጥቂት ወራትና ዓመታት በኋላ ሌላ ሰው ሆነ። ተደናቂነት ከአናቱ በላይ ሄደ። ከእግዚአብሔር ይልቅ የሰዎች አገልጋይ በመሆን ሰዎችን ከቶም የማያስከፋ ነገር ብቻ ሰባኪ ሆነ።

ሰዎች ጊዜያዊና ምድራዊ ዝና ከዘላለማዊው ይልቅ ያምራቸዋል። ጌታ የላካቸው ሰባዎቹ አጋንንት እንኳ ስለተገዙላቸው ደስ እያላቸው፥ ሳስባቸው እየፈነጠዙና እየፈነደቁ ተመልሰው ዘገባ አቀረቡ። *ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው፦ ጌታ ሆይ፥ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት።* ሉቃ. 10፥17። ጌታ ከዚህኛው የበለጠ ሊያስደስታቸው የተገባውን ነገር ነገራቸው። ስማቸው በመንግሥተ ሰማያት ስለተጻፈ። የሰማይ መዝገብ ስማቸውን ስላወቀ ከዚያኛው ይልቅ ተደንቀም መፈንጠዝ ነበረባቸው፤ የሆኑ ግን አይመስልም። ከዘላለማዊው ይልቅ የጊዜው እጅግ ማረካቸው።

ታዋቂዎች ታዋቂ ካደረጋቸው በላይ የሚታወቁ ናቸው። በክርስትና መንዝረን ዋጋውን ብንቆጥር፥ ሰባኪው ከሚሰብከው ኢየሱስ በልጦ ሊታይ ይችላል። ፈውሰኛው ወይም

ፈዋሹ ከሚፈውሰው ኢየሱስ ይልቅ ሊደነቅና ደምቆ ሊታይ ይችላል። የጨዋታው ስም መደነቅ ነው።

## ተደናቂዎች ሩቆች ስለሆኑ ብቸኞች ናቸው።

ተደናቂነት ሰዎችን ከታዋቂነት ተርታ ከፍ ተደርገው እንዲታዩ ያደርጋቸዋል። ወደ አምልኮተ ሰብእ እርከን ያወጣቸዋል። አድናቂዎቻቸውን አድናቂ ብቻ ሳይሆን በጭፍን ተከታይ ያደርጓቸዋል። ጣዖት ይሆኑባቸዋል። ጣዖታት ደግሞ ጣዖታት ናቸውና ከአምላኪዎቻቸው ጋር ሕያው ግንኙነት የላቸውም። በቅርብ ስለዚህ ጉዳይ ያነበብኩት መጽሐፍ የተደናቂነትን (celebrity) ትርጉም፥ social power without proximity ይለዋል።[4] በታዋቂ ተደናቂና በተከታዩና አድናቂው መካከል ቅርርብ የለም። ቅርርብ ብቻ ሳይሆን ግንኙነትም የለም። እናም ተደናቂዎች ብቸኞች ይሆናሉ። ብቸኞች የሚሆኑት ደግሞ ብቸኝነትን ባይወድዱትም እንኳ የአድናቆቱን አስካሪነት ከብቸኝነቱ ጎጂነት በላይ ስለሚፈልጉት ነው።

ይህ የቴክኖሎጂና የማኅበራዊ ሚድያ ዘመን ብዙዎችን ከቤታቸው ሳስይወጡ በዓለም እንዲናኙ ያደርጋቸዋል። ግንኙነት ግን የለም። ከትንሿ ከኔ የማኅበራዊ ሚድያ አቅም እንኳ ሲያዩኝ እንደ ሐረግ የሚጠመጠሙብኝ ሰዎች አሉ። ግን አላውቃቸውም፤ አላወራኋቸውም፤ ደስታቸውንም ችግራቸውንም ተካፍዬ አላውቅም። እርግጥ ጥቂቶች አሉ የቅርብ ጓደኛ ያህል የተዋወቅንና ጓደኞችም የሆንን። በብዙው ግን ቅርርብ የሌለበት የርቀት ግንኙነት ነው።

በተለይ ከቴክኖሎጂ መስፋት ወዲህ እና በዘመናችን የኖሩትንና ያሉትን ታዋቂ ዝነኞችና ተደናቂዎችን ስንመለከት ብቸኞች ናቸው። አንዳንዶቹ ራሳቸውን በራሳቸው እጅ ሲያጠፉ ከዚያ በፊት ያለፉበት የውጣ ውረድ ሕይወት ቆይቶ ሲታወቅ ብቸኛ ተጓዦች እንደነበሩ ይታያል። ሲሞቱ ብቻ ሳይሆን ሲኖሩም ብቸኞች ወይም ርቀታቸው የረዘመ ሰዎች ናቸው። ብዙዎቹ ሁለት ዓይነት ሰዎች መሆናቸው በዚህ ርቀት በጥንቃቄ ይጠበቅላቸዋል። በሚድያና በመድረክ ያለው የሚደነቀው ማንነታቸውና ከመድረክና ከቀረጻ ሲወርዱ ያላቸው ስብእና ፈጽሞ የተለያየ ነው። ብዙውን ጊዜ ይህንን በጣም ጥቂቶች ካልሆኑ በቀር ማንም አያውቀውም። ይህ መጋረጃቸው ነው። ከመድረክ መጋረጃ ወደ ግል መጋረጃ ይገባሉ።

በመጋረጃ ብቻ ሳይሆን በሰዎችም ይጋረዳሉ። ብቸኝነታቸው ራሳቸውን የማተለቅ አባዜያቸውም ነው። እጅግ ርቀውና ልቀው መታየታቸው አይደረሴ ያደርጋቸዋል። በአገራችን ዝነኛ የመድረክ ሰዎች (አቀንቃኞች) አድናቂዎቻቸው እስከ መድረክ እየሄዱ ስመዋቸው ብር ሸጉጠውላቸው ይወርዳሉ። ይህ የአድናቆት ስሜታቸው ነው መወጪያ ነው። በውጪው ዓለም ይህ እንደ ነውር ይታያል። የሚካሄደውን የመድረክ ነገርም የሚያስተጓጉል መሆኑ እውነት ነው። ስለዚህ መድረኩ የተጠበቀ ነው።

---

[4] *Celebrities for* Jesus, Beaty, Katelyn. P. 17.

የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችም አይደረሴነት በታጃቢነት ተገልጦ ታይተዋል። ከዚህ በፊት፥ የዘመናችን 'ሐዋርያት' ኢየሱስ በሚል ርእስ ስር ከጻፍኩት ነጥቦች አንዱ ታጃቢው ኢየሱስ የሚለው አሳብ ነው። ዘላለም ጌታቸው (ፖዝ) በታጃቢ መሄዱን በኩራት ሲናገር እንዲህ ብሎአል፤

> *መጀመሪያ በጋርድ የሄድኩት እኔ ነኝ። ሁሉ ነገር ስፍራ አለው፤ እስታንዳርድ አለው፤ ደረጃ አለው፤ አሠራር አለው። . . . በጋርድ መሄድ ምንድነው ፐርፐዙ? ዓላማው ምንድነው? ደግሞስ ሲቀጥል፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ወይ? ጌታ ኢየሱስጋ ሰዎች ሕጻናት ልጆች ይዘው መጡ ይላል። ደቀ መዛሙርቱ ከለከሏቸው ይላል። ጌታ ኢየሱስ አትከልክሏቸው አለ ይላል። በሌላ አማርኛ ጌታ ኢየሱስጋ ማንም ሰው ከመድረሱ በፊት ደቀ መዛሙርቱ ይከለክሉ ነበር ማለት ነው። . . . ሉቃስ የሚለው ፊልም ላይ አይተሻል? ጅራፍ ይዞ ገርፎ አስወጣቸው፤ ከዚያ በኋላ ሰዎች ተበጣበጡ፤ ደቀ መዛሙርቱ ከለሉት። ፊልሙ ላይ ያየሁትን ነው ምነግርሽ። . . . ሪያሊቲው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው።*[5]

ፖዝ ፊልምን እንደ ምስክር መጥቀሱ እጅግ በጣሙን ቢያሳፍርም፥ ስለ ፕሮቶኮልም ተናግሮአል። ለመታጀቡ ዋና ማስረጃ አድርጎ ያቀረበው ሐዋርያቱ ሕጻናትን መከልከላቸውን ነው። ይህን ክፍል ሳያነብብ ሲጠቅስ ልክ እንደተጻፈ አስመስሎ ነው የተናገረው። 'ደቀ መዛሙርቱ ከለከሏቸው' ብሎ ነው የተናገረው። ይህ ታሪክ በሦስቱ ወንጌላት (ማቴ. 19፤ ማር. 10፤ እና ሉቃ 18) ተጽፎአል። በሦስቱም ወንጌላት ሕጻናቱ ወደ ኢየሱስ መጥተዋል። ወደ ኢየሱስ ደርሰዋል። ካመጡ በኋላ ነው ደቀ መዛሙርቱ ያመጧቸውን ሰዎች የገሠጹት እንጂ ሳያመጡ ከሩቅ አላገዷቸውም። ኢየሱስን እንደ ክብር ዘብ ሆነው አልከለሉትም። ቢሆንማ ኖሮ ያመጧቸው ተግሣጽ ለመቀበል ወይም ኢየሱስም ሕጻናቱን ለመባረክ ዕድሉ ባልኖረም ነበር።

ዛሬ በአጃቢ የሚሄዱ ሐሰተኛ ሐዋርያትና ሐሰተኛ ነቢያት መኖራቸው አያስደንቅም። ወደ ክፍል ሲገቡ ብድግ ብለው የሚቀበሏቸው፥ ሳይቀመጡ የማይቀመጡ፥ የእግራቸው መርገጫ ለመሆን የሚጣደፉ ተደናቂ ሰዎችና መሪዎች አሉ። መነካት የሌለባቸው፥ እንዳይነኩ የተጋረዱ ታጃቢዎች አሉ። ፖዝ በአገራችን የመጀመሪያው ታጃቢ አይደለም፤ የመጨረሻውም አይሆንም። በምድር ላይ እና በታሪክ ውስጥ መታጀብ የነበረበት አንድ ነበረ፤ ኢየሱስ። እንዲያውም በሰው አጃቢዎች ሳይሆን በኪሩቤል መታጀብ ነበረበት። ኢየሱስ ግን የታጀበ ሳይሆን የሚቀርቡት፥ የሚዳስሱት፥ የሚነኩት፥ የሚወድቁበት ያህል ለሰዎች ቅርብ ነበረ።

ኢየሱስ ታጃቢ አልነበረም። የክርስቶስ ሐዋርያትም የኢየሱስ አጃቢዎች አልነበሩም። እንዲያውም በቀውጢዋ ሰዓት በቅርቡ የነበሩትም ጥለውት ነበር የሸሹት። ጌታ ብዙ ጭፍራ የመላእክት ሠራዊት እንዲከላከሉለት ማድረግ እየቻለም አላደረገም። ጌታ አማኑኤል ነበረ፤ እግዚአብሔር ከሰው ጋር። ጸጋና እውነትን ተመልቶ በሰዎች ያደረ ጌታ ነበረ። ኢየሱስ፥ 'ወደ እኔ ኑ' ብሎ የጋበዘ ጋባዥ ነበረ። ኑ ሲል ብረት ለበስ ታጣቂዎች አቁሞ አልነበረም። ኢየሱስ ታጃቢ አልነበረም። ዘበናይ ሐዋርያት በአጀብ ቢሄዱ፥ ግምጃ ይነጠፍልን፥ ሳር ይነስነስልን፥ ቈጠማ ይጎዝጎዝልን፥ ማንም አይንካን፥

---

[5] ከቤቲ ታፈሰ (Exodus Show) ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ። የቪድዮ ቃለ መጠይቁን ከዚህ ምንጭ ማየት ይቻላል፤ https://www.youtube.com/watch?v=vXh_XvSeR8o። በአራት ተከታታይ መሰናዶዎች የተሰራጨ ነው።

ከላይ ፀሐይ፥ ከጎን የሰው ዓይን አይውጋን፤ ጋርዱን፥ ከልሉን፥ ከደኑን፥ ሸፍኑን ቢሉ አያስደንቅም። የሚያስደንቀው እና ይልቁንም የሚያሳፍረው ግን ኢየሱስንና የኢየሱስን ሐዋርያት የዚህ ስንፍናቸው ምስክር አድርገው ሲጠሩ ነው።

ተደናቂዎች መታጀብ ብቻ ሳይሆን በተክለ ሰውነታቸው ላይ ልዩና ከልክ ያለፈ ትኩረት ያደርጋሉ። ልብሳቸው፥ ጫማቸው፥ ቀበቷቸው፥ ሰዓታቸው፥ ጠጉራቸው፥ ሌላውም ሁሉ ልዩ ጥንቃቄ የተደረገበት ነው። ዋናው ጉዳይ ምስል ወይም በተመልካች ዓይን የሚፈጥሩት image ነው። አንዳንዶች የተፈጥሮ ማንነታቸውንም ለሰው ዓይን ግብዓት ሲሉ ይቀይሩታል። ፕላስቲክ ሰርጀሪ ይደረጋሉ፥ ጠጉር ያስተክላሉ፥ የዓይን ቀለም መቀየሪያ ሌንስ ያደርጋሉ፥ ሌላም ያደርጋሉ። 30 ደቂቃ ከመድረክ ወይም ከካሜራ ፊት ለሚሆኑት እስከ ሦስት ሰዓት ከዚያ በፊት ያጠፋሉ። በእርግጥም ማጥፋት ስለሆነ ነው ያጠፋሉ ያልኩት። ተደናቂዎች ከረጢቱም በከረጢቱ ውስጥ ያለው እህልም እነሱ የሆኑ ሰዎች ናቸው። በራሳቸው ከረጢት ራሳቸውን የጠቀጠቁ ሰዎች ናቸው።

ለሚታየው ማንነት የሚጠነቀቁትን ያህል ለማይታየው ግን አይጠነቀቁም። ይህ ከማይታየው ይልቅ ለሚታየው መጠንቀቅ ወይም ከሚታየው ይልቅ ለማይታየእው ግድየለሽ መሆን፥ የወደቁ ክርስቲያኖችን ገመና የመረመሩና የገለጡ ሰዎች በደማቁ የጻፉት ጉዳይ ነው። እነዚህ ሰዎች እንደ ከዋክብት ሲደምቁ፥ እንደ ጨረቃና ፀሐይ ሲያበሩ የሚወክሉት እምነትም አብሮ ይደምቃል። ግን ቀልለው ሲገኙ ወድቀው ሲገኙ ብቻቸውን አይደለም።

## ተደናቂዎች ቅንጡዎች ናቸው።

ተደናቂዎች ከአድናቂዎቻቸው አድናቆትን ብቻ አይደለም የሚቀበሉት። እንዲታወቁ ያደረጋቸው ነገር የገንዘብ መሥሪያቸው ሲሆን አድናቂዎቻቸው የገንዘብ ምንጫቸውም ናቸው። በአኗኗራቸው ቅንጡዎች ናቸው። ብዙዎቹ የገንዘብ ፍላጎት የተጠናወታቸው በመሆናቸው ገንዘብ ሲሰበስቡ ዳርቻ የላቸውም። ከቱጃሮችም፥ ከምስኪኖችም ያለ ርኅራኄ ነው የሚያጋብሱትም የሚለቅሙትም።

አለባበሳቸው፥ ጌጦቻቸው፥ አኗኗራቸው፥ የሚነዷቸው መኪናዎች፥ ሌላውም ሁሉ በዙሪያቸው ያለውን ሰፈር ከቶም የማያውቁት ያስመስላቸዋል። ወደ ዙሪያቸውና ከበባቸው ታላላቅና ዝነኛ ሰዎችን መሰብሰብ፥ ባለ ሥልጣኖችን በመዳፋቸው ውስጥ ማድረግ፥ በዚህም ሥልጣናትን መከታ በማድረግ ሕግን መቆልመምና መስበር፥ ወንጀል ፈጽመው ምንም ተጠያቂ አለመሆን፥ ባለ ልዩ ማዕረግተኛ ሆኖ መመላለስ ይታይባቸዋል።

ቢሊ ግሬሃም በአንድ ወቅት የወር ደመወዙ ሲወሰን በዚያ እርሱ በሚኖርበት ካውንቲ (ወረዳ እንደማለት ነው) የሚያገለግሉ አገልጋዮች ደመወዝ የትልቁና የትንሹ አማካይ እንዲሆን አድርጎ ነበር። በዘመኑ ሁሉ ኑሮው የተንደላቀቀ አልነበረም። ግቡ ወንጌል፥

ዓላማው የጌታ ክብር ነበረ። እንዲህ ያሉ ታዋቂዎችና ተደናቂዎች አሉ። ታዋቂነታቸው ብቻ ሳይሆን ኑሮአቸውም ጌታን ያሳየ ሰዎች ናቸው እነዚህ።

በ1980ዎቹና 90ዎቹ በአሜሪካ የነበሩ ቴሌወንጌላውያን አንድ የተከሰሱባቸው አንድ ትልቅ ወንጀል ቅንጦት ነው። ቅንጦት በራሱ ችግር ሆኖ ሳይሆን ለወንጌል ተብሎ በሚለገስና በሚሰጥ ገንዘብ ድሎትን ሲያጣጥሙና ገንዘቡን ያለ አግባብ ላልተፈለገበት ምክንያት ሲያባክኑ መገኘታቸው ነው። ያ ገንዘብ የአገልግሎት እንጂ የግላቸው ገንዘብ አይደለም። ኬነት ኮፐላንድ ለምን የግል አውሮፕላን እንዳስፈለገው ሲናገር፥ በሕዝብ አውሮፕላን ከመንጋ አጋንንት ጋር መሄድ እንደሌለበት በመናገር ነበር። መንጋ አጋንንት ያለው ተሳፋሪ ሰዎችን ነው። ራሳቸውን ያለ ልክ ሲያርቁ እንዲህም ያደርጋሉ። የግል አውሮፕላን የሚገዙት ደግሞ በግል ገንዘባቸው ከቶም አይደለም፤ ለአገልግሎት በተሰጠ ገንዘብ ነው። በምዕራቡ ዓለም መንግሥት አገልግሎቶችን የሚፈትሽበት መስመር ቢኖረውም አንዳንዶች የለ ምንም ችግር ኬላውን ሰብረው ይጓዛሉ። ገንዘብን በተመለከተ ተደናቂዎች ሸቀጡም ሻጩም እነሱው ናቸው።

አሳዛኙ እውነታ፥ ተደናቂዎቹ በድሎት ሲኖሩ አብረዋቸው የሚያገለግሉትና የሥራውን ሸክም ትከሸሻቸውን ዝቅ አድርገው የሚሸከሙት ሰዎች የሚያገኙት የዚያን ሽራፊ መሆኑ ነው። ከሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ሐዋርያት ጋር የሠሩ ብዙዎች የሚያቀርቡት ስሞታ ይህ ነው። በአገራችንማ የንዋይ ቁጥጥር መስመር ስለሌለ የሚሰበሰበው ገንዘብ ምን ያህል መሆኑና ምን ያህሉ ወደ ማን እንደሄደ መናገር አይታሰብም። ገንዘብ በራሱ ጤናማ ነገር መሆኑንና ችግሩ ገንዘብን መውደድ መሆኑን ክርስቲያንና ንዋይ የሚለውን ስንመለከት አይተናል። ከተደናቂነት አባዜዎች አንዱ ቅንጦት ነው። ተደናቂዎች ራሳቸውን የሚያዩት፥ አድናቂዎቻቸውም እነሱን የሚያዩት ቅንጦት የተገባቸው እንደሆኑ ነው።

አንዳንዶች የሚያገኙትን ገንዘብ ለድሆች መጠቀሚያ ሲያደርጉ፥ ወይም ድሆችን ሲረዱበት ይታያሉ። አንዳንዶች ግን ለሕሊና መሸንገያነት ብቻ የረዱ ለመምሰል በአደባባይና በሚድያ ቀርበው ለታይታ ይፈጽሙታል። ሀብት በራሱ መልካም ሆኖ ሳለ የማራቅ ችግርም አለው። ሀብታም ብጤውን ይፈልጋል፤ ብጤዎች ደግሞ ብዙ አይደሉም። እና ተደናቂነት በራሱ በሚያርቀው ርቀት ላይ ይህኛውም ሲጨመርበት ርቀቱ የትየለሌ ይሆናል።

ቅንጦቱና ድሎቱ ገንዘብ ብቻ ሳይሆን አካላዊና ወሲባዊ ልቅነቶችንም ይይዛል። ከታዋቂ ሰው ጋር መሆን፥ መገኘት በራሱ የሚፈጥረው ስሜት እንደተጠበቀ ሆኖ አድናቂዎች የተደናቂዎች ፈቃደኛ ሰለባዎችም ይሆናሉ። ብዙውን ጊዜ ተደናቂዎቹ የሚፈልጉትን ለማግኘት ራሳቸውን ባለ መብት አድርገው ሲያዩና ሲያሳዩ፥ ሲቀርቡና ሲያቀርቡ፥ አድናቂዎችም ራሳቸውን ለነዚህ ሰዎች በነጻና በፈቃድ መሥዋዕት አድርገው ያቀርባሉ። ባለፉት አሥር ዓመታት በሰሜን አሜሪካ የተፈጸሙት ወሲባዊ መተላለፎችና ጥቃቶች የነዚህ የሁለቱ መስተጋብር ውጤቶች ናቸው።

ጉዳቶች ከደረሱ በኋላ ያንን ተደናቂ ለመጠበቅ ሲሉ ተጠቂዎች እንደ ተበዳይ እንዳይቆጠሩ ይደረጋሉ። ይህ በማስፈራራትም፥ በስምምነትም ሊሆን ይችላል።

አንዳንዴ የተደናቂውን ስም ወይም በስሙ የተጠራውን ድርጅት ዝና ለመጠበቅ ሲባል እንዲህ ያሉ ጭምጭምታዎች ከተሰሙ፥ ነገሩ እውነት ነው ወይ? ይህ ነገር ተፈጽሞአል ወይ? ብለው መሪዎች ተደናቂውን ለመጠየቅ አይደፍሩም። ለመፈተሽም (ፈታሽ ለመሆን)፥ ለመፈተሽም (ተፈታሽ ለመሆን) የበቃ ተደናቂና አመራር ሲገናኙ አገልግሎት ስኬታማ ይሆናል። ይህ በሌለበት ግን አደጋና ስብራት ይፈጠራል።

## ተደናቂዎች ሲወድቁ ብዙዎችን ይዘው ይወድቃሉ።

ከተደናቂነታቸው ጋር ከርቀታቸው የተነሣ በኃጢአት የወደቁ አያሌ አገልጋዮች ይገኛሉ። ሌላ የወደቀ ሰው ከመጥቀስ ይልቅ ቀደም ሲል፥ ክርስቲያንና ወሲብ በሚለው ክፍል የጠቀስኩትን አንዱን ራቪ ዛካሪያስን እንደገና ላውሳው። ራቪ የአገልግሎቱ ቢሮ በሚገኝባት ከተማ አጠገብ ሁለት እስፓዎች (የማሳጅ ወይም መታሻ ቤቶች) ነበሩት። አንድ እውቅ የምካቴ ክርስትና ሰው ለምን ከአንድም ሁለት እስፓ ገዝቶ ንግድ እንደሚሠራበት ለብዙዎችም፥ ለኔም አልገባኝም። ጥቂት የማይባሉ ሴቶች ወደ አደባባይ ወጥተው ወሲባዊውን መተላለፍ ገለጡ። RZIM የተባለው አገልግሎቱ ጉዳዩን በግልጽ ተናግሮ ይቅርታ ጠይቆ፥ በሕግ ሂደቶችም በተጠያቂነት ተሳትፏል። ከላይ ባልኩት ክርስቲያንና ወሲብ በሚለው ክፍል አራት ነጥቦችን ያካፈልኩ ሲሆን፥ አራተኛ፥ እና የመጨረሻው፥ እንጠንቀቅ የሚል ነው።

እዚያ ካልኩት ጥቂት ዐረፍተ ነገሮችን ልድገም። ታዋቂ ሰዎች፥ በሥልጣን ላይ፥ በወንበር ላይ፥ በትልልቅ የማስተማሪያ መድረክ፥ በቤተ ክርስቲያን ጉባኤም ይሁን በማኅበራዊና ሕዝባዊ ስርጭቶች የምንገኝ ማናችንም ብረት ለበሶች አለመሆናችንን ማወቅ አለብን። የቆምን እና የምንቆም ብቻ እንጂ ከቶም የማንወድቅ አዕማድ አድርገን ራሳችንን ማሰብ የለብንም። ራሳችንን እንፈትሽ፤ ተጠያቂ ከመሆን አንሽሽ፤ ለቤተ ክርስቲያን ሰዎቻችን፥ ለመሪዎች፥ ለጓደኞች ክፍት እንሁን፤ አንታበይ፤ ታዋቂነታችን አናታችን ላይ ወጥቶ አያስክረን። ምንም የማንሆን አይምሰለን፤ እንጠንቀቅ፤ በጸሎት የምንሸፈን የምንከደን እንሁን። መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎቻችን ቡትቱ ያልሆኑ፥ ያልተቀደዱ፥ ያልተቦጨቁ መሆናቸውን አስረግጠን እንፈትሽ፤ አሳምረን እንልበስ። ስንወድቅ ይዘናቸው የምንወድቃቸው ሰዎች መኖራቸውን አንርሳ። ፍጹማን ሰዎች አለመሆናችንን አውቀን በሚያድጥ መንገድ ላይ በድፍረት አንራመድ። እንጠንቀቅ።

ራቪ በየዓመቱ ከ200 ቀናት በላይ ከቤቱ ርቆ በተለያዩ የዓለም አገሮች የታወቀውንና የታወቀበትን የምካቴ እምነትና በተለይም የምካቴ ክርስትና አገልግሎት የሚያገለግል ሰው ነው። ከነዚህ ጊዜያት በአንዳንዶቹ ከማንም እይታ ውጪ የሚሆንባቸው ጊዜያት ነበሩ። እነዚህን ከሬዳር እይታ ውጪ የሚሆንባቸውን ጊዜያት አብረውት የሚያገለግሉትና የሚጓዙት ሰዎችም ለእርሱ የብቸኝነት፥ የጸጥታና የጥሞና ጊዜ ብቻ አድርገው ነበር የሚያዩት። ወደ አራት የሚያህሉ ስልኮችን ሲጠቀም ማንም፥ 'ስልክህን

ልፈትሽ' ብሎት አያውቅም፤ ይህንን የተቀመመ ሊቅና በዕድሜም የበሰለ ሰው ማንስ ይጠረጥረውና! ሆኖም በተለያዩ ድርብርድ መጋረጃዎች የተጋረደና በተለያዩ ዘዴዎች ተደብቆ የቆየ ድርብ ሕይወትን ሲመራ ኖሯል።

ዝና ሲወጣ፥ ታዋቂነትና ተደናቂነት ሲወጣ ተጠያቂነትም አብሮ ካልወጣ አደጋ አለ። በራቪ መውደቅ ግራ የተጋቡ ክርስቲያኖች ብዙ ናቸው። ትልልቅ ሰዎች ሲወድቁ ብቻቸውን አይወድቁም። ቢያንስ ዙሪያ ገባቸው ይደረማመሳል። አንዳንድ ታዋቂዎች መታወቃቸው በራሱ መጋረጃ ብቻ ሳይሆን የመታበይ ምክንያታቸውም ይሆናል።

በመግቢያው ላይ ዝናቸው እንደወጣ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ከጠቀስኳቸው መካከል አንዱ ዖዝያን የተባለው የይሁዳ ንጉሥ ነው። በ2ዜና 26፥15 እስኪበረታም ድረስ እግዚአብሔር በድንቅ ረድቶታልና ዝናው እስከ ሩቅ ድረስ ተሰማ። ተብሎለታል። ዝና ያሰክራል፤ ያስታብያል። ቀጥሎ ያለው ጥቅስ እንዲህ ይላል፤ ነገር ግን በበረታ ጊዜ ለጥፋት ልቡ ታበየ፥ አምላኩንም እግዚአብሔርን በደለ፤ ወደ መቅደስ ገብቶ በዕጣን መሠዊያ ላይ ዐጠነ። ይህ ሰው ባበረታው በእግዚአብሔር ላይም ሊበረታ ፈለገ። ይህ የውድቀቱ መጀመሪያም መጨረሻም ሆነ። በአጭር ጊዜ ውስጥ ተቀሰፈና ከገባበት መቅደስ ለምጻም ሆኖ ወጣ። ከእግዚአብሔር ቤት መቆረጥ ብቻ ሳይሆን ወደ ሌላ ቤት እንኳ እንዳይገባ በተለየ ቤት ውስጥ እስኪሞት ቆየ።

# ተደናቂዎች ተጠያቂዎች ናቸው

እጅግ ዝና ያተረፉ ስመ ጥሮችና ተደናቂም ሆነው ንጹሕና የጠራ ኑሮ ኖረው ያለፉ ቅዱሳንም አሉ። አሁን ያሉ ወደ ዘመናቸው መደምደሚያ የደረሱም አሉ። ቢሊ ግሬሃም አንዱ የተወደደ አገልጋይ ነው። ስለዚህ ምስጢር ተደጋግሞ ተጠይቆ እስሩም ሌሎችም የቅርቦቹ የተናገሩት ነገር ገና አገልግሎታቸው አፍላ በነበረበትና ወደ ሰፊው ሕዝብ እይታ እየገባ በነበረበት ጊዜ ጥቂት ጓደኛሞች የሆኑ አገልጋዮች የተጋቡት ቃል ኪዳን ነበረ።

በ1948 በሞዴስቶ፥ ካሊፎርኒያ የጀማ ስብከታቸው ወቅት (ኋላ የሞዴስቶ ማኒፌስቶ እየተባለም ተጠርቷል) የገቡት ቃል ኪዳን ነበር። ዋናዎቹ ነጥቦች፥ 1ኛ፥ ከሚስቶቻቸው ብቻ ጋር ካልሆነ በቀር ከሌላ ሴት ጋር ብቻቸውን መገኘት እንደሌለባቸው። 2ኛ፥ ገንዘብን በተመለከተ ፍጹም ንጽሕናና ግልጽነት ማሳየት እንዳለባቸውና ደመወዛቸውን ራሱን ቦርድ እንዲወስንላቸው። ቁጥርን በተመለከተ የገንዘብን ብቻ ሳይሆን የተሳታፊ ሰዎችንና የዳኑ ሰዎችንም ቁጥር ዘገባንም ይጨምራል። 3ኛ፥ አገልግሎታቸውን ከሚያገለግሉባቸው ከተሞች አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ሙሉ በሙሉ በመተባበር ብቻ እንዲያገለግሉ ነበር።

እውነተኛ ዘገባ ሲባል በቅርብ በአገራችን ከተጀመሩት የሐሰተኛ ነቢያት ማኅበራት አንዱ 3 ሚሊየን አባላት እንዳሉት ተናግሮ ነበር። እውስጥ ካሉት ሰዎች መካከል የተሸማቀቁበትና ውሸት መሆኑን የነገሩኝ ነበሩ። የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች ካውንስል በተመሠረተ ሰሞን ራሳቸውን ሲያስመዘግቡ የአባላት ቁጥር ሲሰጡ

የነበረው መጋነንም ያስደነግጥ ነበር። በዚያ ሰሞን ብቻ የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች ቁጥር ከ20 ያህል ሚሊየን ወደ 40 ተጠግቶ ነበር። ይህ ውሸት የገጽታ ግንባታ ነው። ታዋቂዎች ለገጽታ ግንባታ ለአካላቸውም፥ ለስማቸውም፥ ለድርጅታቸውም የሚሰጡት ስፍራ እጅግ የገነነና ለበጣ የበዛበትም ነው። ታዋቂነት ይህንንም ያጠቃልላላ!

እነ ቢሊ ግሬሃም ታማኝ የነበሩት በዘገባቸውም ጭምር ነበር። ደግሞም እስኪሞቱ ድረስ ለገቡት ቃል ኪዳን ታማኞች ሆኑ። አንዱ ሌላውን በፍጹም ግልጥነት መጠየቅ ይችሉ ነበር። ዛሬም በአሜሪካ ወንጌላውያም አብያተ ክርስቲያናት መጋቢዎች መካከል የሚገኙ የተጠያቂነት ቡድኖችና አገልግሎቶች አሉ።

ተጠያቂነት በሌለበት ተደናቂዎች ልጓም የሌለው ፈረስ ሆነው ይፋንናሉ። ታዋቂ አርቲስቶች (ለምሳሌ ዘማሪዎች) ከሆኑ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንኳ የሌላቸው ናቸው። መሪና መጋቢ የሌላቸው ይሆናሉ። መሪዎች ከሆኑ ደግሞ የሚመሩትን ድርጅት፥ ወይም አገልግሎት፥ ወይም ቤተ ክርስቲያን ብቸኛ የበላይ ሆነው ይገዛሉ። ቤተ ክርስቲያንንም እንኳ እንደ ኩባንያና ድርጅት ነው የሚቆጥሩትና የሚያስመዘግቡትም። የበላይ ስለሆኑ በምንም እርከን የሚጠይቃቸው የለም። ሕጉ በነሱ ይቀረጻል፤ ደንቡ በነሱ ይረቅቅና ይጸድቃል። ድርጅቱ በመልካቸው እንደ ምሳሌያቸው ይፈጠራል። በነዚህ ዓይነቶቹ ኩባንያ መሰልና አከል ድርጅቶች የገንዘብ ዝርፊያ፥ የሥልጣን መባለግ፥ የግብረ ገብነት እጦት በውስጥም ከውጪም የሚታየው ስለዚህ ነው። ተደናቂነት ባለበት ተነቃፊነት የሚኖረውም ስለዚህ ነው። ስለዚህ ተጠያቂነት የግድ ይላል።

ተጠያቂነት የግንኙነት መስመሮቻቸው ክፍት መሆናቸውንም ይመለከታል። አንድ ሐሰተኛ ነቢይ በጸሎት ስም ሌላ ሦስተኛ ሰው ሳይኖር ከሌላ ሴት ጋር በአንድ የእንግዶች ማደሪያ ወይም የሆቴል ክፍል ውስጥ መገኘት ምን የሚሉት ጸሎት ነው። ወንዶች ብቻ አይደሉም ሴት ሐሰተኛ ነቢያትም ይህንን አድርገዋል። የኢሜይል እና የስልክ ግንኙነቶቻቸው ድንገት ይፈተሹ ቢባል ፈቃደኛ መሆን አለባቸው። ከላይ የጠቀስኩት ራቪ አራት ስልኮች ይዞ ይዞር ነበር። የሰዎችን ነፃነት ማክበር እንደተጠበቀ ሆኖ፥ በአንድ ወይም ጥቂት ሰዎች ድንገት እንደሚፈተሽ ቢታወቅ ይህ መልካም ነው። ተጠያቂነት የተደናቂነት ጠላት ሆኖ ከታየ አደጋ ነው።

የኛዎቹ ተደናቂዎች ብዙዎቹ 'መሥራችና ባለ ራእይ' ተብለው ስለሚጠሩ ከነሱ በላይ ማንም የለምና በማንም የማይፈተሹ ሆነው ይኖራሉ። የመሪዎች ቦርድ ወይም ቡድን ቢኖርም እንኳ የዚያ ቡድን መሪዎችና በዚያ ውስጥ የሚገቡ ሰዎችን መራጮች እነሱ ናቸው። ከስፍራ ስፍራ ወይም ከአገር አገር ሲጓዙም ማንም በቅርብ የሚከታተላቸው የለም፤ እንዲኖርም አይፈቅዱም። እነሱ ሌሎቹን ይቆጣጠራሉ እንጂ ማንም እነሱን አይቆጣጠርም።

ተደናቂዎች ሰዎችን አስከታዮች ናቸው። ተከታዮች ከሩቅ ሲከተሏቸው ደስ ይላቸዋል። ሊቀርቧቸው አይፈልጉም። ከቀረቧቸው ገመናቸው ይታያል። እነሱም ሰዎች፥ ደካሞች፥ ኃጢአተኞች፥ አንዳንዶቹም አጭበርባሪዎች፥ አምታቾች፥

ለሥጋቸው ያደሩ፥ ለገንዘብ የተገዙ፥ ሱሰኞች መሆናቸው ይታወቅባቸዋል። ስለዚህ ርቀት ይጠበቃል። ከላይ ታዋቂነት ቅርርብ የሌለበት ኃይል ወይም ሥልጣን ነው የተባለው ማለት ነው።

የነዚህ ታዋቂዎች ገመና ከታየና መውጣት ከጀመረ ወይም ካፈተለከ ቀዳዳውን ለመድፈን የማያደርጉት መፍጨርጨርና መንፈራፈር የለም። አንዳንዱን በገንዘብ በመደለልና በመሸንገል፥ ሌላውን በማስፈራራትና በማስመታትም ዝም ሊያደርጉ አይመለሱም። ከኛዎቹ ሐሰተኛ ነቢያት በቤት ውስጥ ሰዎችን ያሰሩና ያስደበደቡ አሉ። ከገንዘብ ጋር የተያያዘው በስምምነት የሚደረግ ስለሆነ ብዙም አይታወቅም። ግን ዋናው አፍ መዝጊያ ነው። አንዳንዶች ይህንን ዘዴ የገንዘብ ማግኛም አድርገው ይጠቀሙበታል። ኃይልን ሌሎችን ለማስፈራሪያ መጠቀም እንዲያው በድንገት የሚከሰት ነገር አይደለም። አስቀድሞ የተጠራቀመ ጉልበት አለ ማለት ነው። ይህ ደግሞ ከባሕርይ ጋር ቁርኝት ያለው ነገር ነው።

አብረዋቸው ሊሠሩ የማይወድዱትን ወይም ማናቸውንም ዓይነት ጥያቄ የሚያነሡ ሰዎችን ሲጀመርም አያቀርቧቸውም፤ ከቀረቡ በኋላ ከሆነ ደግሞ ያስወግዷቸዋል። ውስጥ አዋቂዎች ከሆኑም ከዛቻና ማስፈራሪያ ጋር፥ ወይም ከአፍ መዝጊያ ገንዘብ ጋር ይለያያሉ።

## ተደናቂ? ወይስ ተጠሪ፥ ተማሪ፥ ተሸካሚ

ብዙዎች ተደናቂዎች አገልጋይ ይመስላሉ እንጂ አገልጋዮች አይደሉም። የተለመዱትን መጋቢና ወንጌላዊ አስተማሪ ሰባኪን አይፈልጉትም። አገልጋይ የሚለውን ስምማ አይወዱትም። ነቢይና ሐዋርያ ብቻ የተወደዱ ማዕረጎች ናቸው።

እነዚህ ሰዎች በቀረቤታ ሲታዩ በአገልጋይ ውስጥ ብዙም ሳይበረበሩ መታየት ያለባቸው አራት ነገሮች የሏቸውም።

1. ጥሪ የላቸውም። የራሳቸው ሿሚ ባለ ሥልጣኖች ናቸው እንጂ የጉባኤም፥ የእግዚአብሔርም ተጠሪዎች አይደሉም። አልተጠሩም፤ ጥሪ የላቸውም።

2. ጸጋውም የላቸውም። የጸጋ ስጦታ ያላቸው መስለው ድራማውን ተክነውታል፤ ስለዚህ አፍም ዓይንም የሚያስከፍቱ ነገሮችን ይናገራሉ የተፈጸሙ ያስመስላሉ፥ ተስፋም ይበትናሉ እንጂ እውነተኛው ጸጋ የላቸውም። ተደናቂነት ግባቸው ስለሆነ ተዋናይነትን ተለማምደውታል።

3. ትምህርት የላቸውም። ተማሪዎች አይደሉም። ስለሚያገለግሉበት መስክ ምንም የቀሰሙት ትምህርት የላቸውም። ግን ራሳቸውን ከአስተማሪዎችም በላይ አድርገው በመቁጠር አስተምረው፥ አሰልጥነው ከአቅማቸው በላይ በሆኑ ወረቀቶች ለማስመረቅ ድፍረቱ አላቸው።

4. ሽክም የላቸውም። ከማኅበራቸው ጋር ግንኙነት የላቸውም። ቀደም ሲል ያልኩት ቅርርብ የለም። ታጅበው ይገባሉ ይወጣሉ፤ እነሱን ለማግኘት ብዙ መሰናክል ማለፍ ይጠይቃል። ለጸሎታቸው ብዙ ክፍያ ያስፈልጋል።

እነዚህ ሰዎች ተደናቂነትን የተራቡና የተጠሙ ስለሆኑ ናፍቆታቸው ይህ ብቻ ነው። ከሚያዩአቸው ሰዎች ፊት መራቅ አይፈልጉም፤ እነሱን መቅረብ ግን አይፈልጉም። ብቸኞች ናቸው ግን ለብቻቸው ከጌታ ጋር መሆንን አይለማመዱም። ይህ የቅርቦቻቸው እና የወደቁቱ ወዳጆች ምስክርነት ነው። ከብጤዎቻቸው ጋር ተገናኝቶ አንዱ ሌላውን ሞቅ ሞቅ ማድረግን ግን ያደርጉታል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ (ባለፉት አሥር ዓመታት ብቻ) የምዕራቡን ዓለም ክርስትና እጅግ ያስነቀፉ ብዙ ውድቀቶች ተከስተዋል። ወሲባዊ መተላለፎች፥ የገንዘብ ብክነቶች፥ የሥልጣን አምባ ገነንነቶች፥ ሌላው ቀርቶ የተመሳሳይ ጾታ ወሲቦች ተፈጽመው ብዙዎችን በወንጌላዊ እምነት ላይ እምነት እንዳይኖራቸው አድርገዋል። ምክንያቶቹ የተደናቂዎች አባዜ ብቻ አይደለም። ከላይ ያየናቸው የተጠያቂነት ችግሮች ብቻ አይደሉም። ሰዎቹ ከልባቸው አገልጋዮች አለመሆናቸውም ጭምር ነው። ተደናቂነት ከአገልጋይነት ጋር የተፋታ ሕይወት ነው።

አገልጋይነት ከአማኞች ጋር መተሳሰርን ይጠይቃል። ተደናቂዎች ከአማኞች ይልቅ አላማኞችን ለመሳብ ይጥራሉ። ይህ ወንጌልን መስበክ ስለሆነ መልካም ይመስላል። ነገር ግን ወንጌልን አይሰብኩም፤ ራሳቸውን እንጂ ክርስቶስን አያሳዩም፤ አላማኞች ኃጢአተኞች እንደሆኑ እንዲያውቁ ምንም ጥረት አያደርጉም። ወደ ጉባኤያቸው ሲመጡም ከአዳራሹ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን እንዳይመስል ጥረት ተደርጎበታል። በመድረኩ፥ በቤቱ ግድግዳም፥ በጣራውም መስቀል የለም። መስቀል አለመኖር ብቻ ሳይሆን መስቀሉ ከቶም አይሰበክም። መድረኩ ሌጣ ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ ባንዲራ፥ ሌላ ጊዜ ከናይት ክለብ ባይበልጥ የማይተናነስ ብልጭልጭ መብራትና ጢስ ይንቦለቦላል። መብራቱና ጢሱ ብቻ ሳይሆን ራሱን ናይት ክለብን ሆኖ የተገኘባቸው ከሆኑስ?

አንድ ሰው የታዋቂነትን እርከን ከተሻገረ በኋላ የሚለውን ነገር ሁሉ ለመስማት ሰዎች ይንጠለጠሉበታል። ምንም የማይረባና የማይጥም ነገር እንኳ ቢናገሩ እንደ ጣፋጭና ጠቃሚ ነገር ይቆጠርላቸዋል። ከዚህ የተነሣ የፈለጉትን ሊናገሩ ይደፋፈራሉ። ከቃሉ ጋር የሚጋጭ ነገር ቢናገሩም ልክ እንደ እግዚአብሔር ቃል ተደርጎ ይወሰድላቸዋል። ይህ ከቃሉ ጋር የተጋጩ ነገሮችን መናገር ከላይ ከጠቀስኩት የተማሩ አለመሆን ጋር የተቆራኘም ነው። እነዚህ ተደናቂዎች ቃሉን ያልተማሩ በመሆናቸው አያስተምሩም አይሰብኩም። የሚሰብኩትም ለስነ ፍታቴ ደንቦች ግድ የሌላቸውና የሰዎችን ቀልብ ጭምድድ አድርጎ የሚይዝ ምሳሌያዊ አፈታትና የአዎንታዊ ንግግሮች ዶቃዎችን በመደርደር ነው።

እንደ መደምደሚያ ቃል ስለ ተደናቂነት የምለው፥ ተደናቂነት ሊወጡና ሊያመልጡት የተገባ እስክርክሪት መሆኑን ነው። ከተደናቂነት አባዜና እሽክርክሪት መውጫው ተራ መሆንን ማወቅና መለማመድ፥ ከጌታ ጋር ጊዜ ማሳለፍ፥ ከሰዎች ጋርም ጊዜ ማሳለፍ

ነው። ከጌታ ጋር ያልኩት የማካፍለው ክርስቲያኖችን በተመለከተ ስለሆነ ነው። ራሱ ጌታም የተወደደና የተደነቀ ሳለ ለብቻው ይሆን ነበር። ጳውሎስ ጌታን ከተዋወቀ በኋላ ለዓመታት የት እንደነበረ እርሱ ባይነግረን አናውቅም ነበር። የቀድሞ አሳዳጅነቱ ብቻ ተደናቂ አገልጋይ ሊያደርገው ይችል ነበር። ግን ያንን መገድ አልሄደበትም።

ተደናቂዎች ብቸኞች ናቸው፤ ይህ ጤናማ ያልሆነ ብቸኝነት ነው። የብቻነት ጊዜ ቢያስፈልግም ከተርታና መደዴ ሰዎች ጋር ትከሻ ለትከሻ መጋፋት ከእውነተኛ ማንነታችንን ጋር ተጠፋፍተን ከሆነ ያገናኘናል። ልዩ ፍጡርና ብረት ለበስ አለመሆናቸውን ሊያውቁ የግድ ነው። ተደናቂዎች ሊወድቁ ይችላሉ። የወደቁ ቀን እንደ ትልቅ ዛፍ ብዙዎችን ይዘው ነው የሚገነደሱት። አደጋው ቀላል አይደለም። ስለዚህ ተጠያቂዎች መሆናቸው ሊጠፋቸው አይገባም። ተጠያቂነት ብዙ እርከኖችና ገጽታዎች ቢኖሩትም ዋናው ነገር ዓይነቱ ቢለያይም ራሱ ተጠያቂነት መኖሩ ነው።

ተደናቂዎች አገልጋዮች ከሆኑ ጥሪ፥ ሸክም፥ ትምህርትና ጸጋ ሊኖራቸው ግድ ነው። ከሁሉም በላይ ሞዴል አገልጋይ የሆነው የኢየሱስ እውነተኛ ደቀ መዛሙርት ሊሆኑ ግድ ነው። እርሱን ሊመስሉና ሊከተሉት ግድ ነው። እርሱን መምሰልና መከተል ተደናቂነት ቢመጣም ቦታውንና ልኩን አውቆ በስፍራው እንዲሆን ማድረግ ይችላል።

## ምዕራፍ ፲፩

# ክርስቲያኙና ባህል (ባህላዊ አመቻማቹነት)

የክርስትና ግብ ባህል ቀያሪነት አይደለም። ክርስቲያን በባህል መጠለፍም የለበትም። የክርስትና ግብ አዲስ ፍጥረትነት ነው። አዲስ ፍጥረት የሆነ ሰው ደግሞ ውስጡ ተለውጦ ውጪውም ይለወጣል።

ማናችንም ተወንደን ያደግንበት ማኅበረ ሰብ አለን። ያ ማኅበረ ሰብ ደግሞ ባህል አለው። ባህልን ስናስብ የሕይወታችንና የኑሯችን ድርና ማግ ሆነው የሚመጡልን ብዙ ምስሎች አሉ። ሠርግ፥ ትዳር፥ ለቅሶ፥ ቀብር፥ ወሊድ፥ ዐውደ ዓመት፥ ድግሶች፥ አመጋገብ፥ ጉርምስና፥ ኩርድና፥ ቤተ ዘመድ፥ ሠላምታ፥ ጥየቃ፥ አለባበስ፥ የወንጀል ምርመራ፥ አውጫጭኝ፥ ብቀላ፥ ሽለላ፥ ቀረርቶ፥ ዘፈን፥ ሽምግልና፥ እርቅ፥ ካሳ፥ የአረጋውያን ክብር፥ የመሪዎች አክብሮት፥ ዝምድና፥ ጋብቻ፥ አምቻ፥ ጉዲፈቻ፥ አበ ልጅነት፥ አምልኮ፥ የተክለ ሰውነት አያያዝ፥ ወዘተ፥ ወዘተ። ከአምልኮ ጋር የሚቆራኘው የሃይማኖት ጉዳይ የተለየ ቢሆንም በአንዳንድ ባህሎች ባህሉና ሃይማኖቱ ተደባልቀው ይገኛሉ። ወይ ባህሉ ሃይማኖታዊ ባህል፥ ወይም ሃይማኖቱ ባህላዊ ሃይማኖት ይሆናሉ። እዚህ አንዱን ከሌላው መለየት ይከብዳል። ቢሆንም በዚህ ጉዳም ማይማን መሆን የለብንም።

ባህል ሰፊ ነገሮችን በውስጡ ይይዛል። እዚህ ላይ ባህል ምንድር ነው? ብለን መጠየቅ አለብን። ባህል ምንድር ነው? ባህልን በቀላሉ መተርጎም ያዳግታል። የሚያዳግተው የብዙ ነገሮች ቅይጥና ድርና ማግ ሥሪት ስለሆነ ነው። ክርስቲያንና ዘፈን በሚለው ትምህርት ውስጥ ስለ ዘፈንና ባህል ግንኙነት ሳካፍል ስለ ባህል ያልኩትን እዚህም እለዋለሁ። ይህኛው ስለራሱ ስለ ባህል የማካፍለው ነውና እዚህ በትንሹ ሰፋ አደርገዋለሁ።

ባህል ተቀባይነትን ያገኘ የአንድ ሕዝብ ወይም የአንድ የሕዝብ ክፍል የጋራ መታወቂያ ወይም መለያ የሆነ ልማድ፥ ደንብ፥ ወግ፥ አመለካከት ነው። ባህል ሕዝባዊ ወይም ማኅበራዊ መስተጋብር ነው። አንድን የሕዝብ ክፍል ማኅበረ ሰብ ከሌላ የሕዝብ ክፍል ለይቶ ማወቂያ ወይም መታወቂያም ነው። ባህል ከማኅበረ ሰቡ የቀደመ ታሪክ የተወረሰ፥ የአሁን ማንነቱን በሚገልጡ ብዙ ገጽታዎች የዳበረና ተጠላልፎ፥ ተገማምዶ የተያያዘ ነው። ይህ የአንድ ማህበረ ሰብ ሕዝባዊ ባህል ወይም ዋና ባህል ነው። Mainstream culture ይባላል።

ባህል በቋንቋ፥ በስነ ቃል፥ በስነ ጥበቦች፥ በተለያዩ ድርጊቶች፥ አምልኮዎችና ሥርዓቶች ከአንዱ የዚያ ሕዝብ ትውልድ ወደ ቀጣዩ ትውልድ ይተላለፋል። አንድ ባህል ወይም የትኛውም ባህል የማይሰረዝ በድንጋይ ሰሌዳ ላይ የተጻፈና ለሁሉም ሰዎች እና ለሁልጊዜ ሊሆን የተገባው ሕግ አይደለም። ባህል ይወለዳል፥ ያድጋል፤ ይቀየራል፤ ይለወጣል፤ ይሟሟል፤ ይታወሳል፤ ይዘነጋል። ባህል ይወርሳል፤ ይወረሳል፤ ከሌላ ባህል ይወስዳል፤ ለሌላ ባህል ይሰጣል። በዚያው በአንዱ ማኅበረ ሰብ ውስጥም እንኳ በአንድ ትውልድ ጊዜ ውስጥ፥ ወይም ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሻገር የሚለዋወጡ ባህላዊ እሴቶች ይኖራሉ።

ብዙ ሕዝብና ማኅበረ ሰቦች ባሉበት እንደኛ ባለ አገር በቁጥርም በዓይነትም ብዙ የሆኑ ባህሎች እናገኛለን። አንድ ሰው በአንድ ነጠላ ባህል ውስጥ ወይም ከአንድ ባህል በላይ የሆኑ ባህሎች ውስጥ ሊያድግና ሊኖር ይችላል። ባህሎች ከአስተዳደጋችን ጋር የተጣበቁ ስለሆኑ በደስታ ነው የምናስባቸው። አንዳንድ ባህሎች መልካም ናቸው፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ጎጂ ናቸው። ያደግንባቸው ባህሎች ስለሆኑ ጎጂዎቹንም እንደ ጎጂ አናስባቸውም፤ እንደ ጎጂ አንቀበላቸውም። ለምሳሌ፥ የሴቶች ግርዛት ጎጂ ባህል ነው። ይህንን በማያውቁት ዘንድ እንዲያውም ወንጀል ነው። ያደግንበት ባህል ከሆነ ግን ጎጂ አድርገን አንቀበለውም። ብዝሐ ጋብቻ በብዙ አገሮች ነውርና ሕገ ወጥነት ነው፤ በአንዳንዶች ዘንድ ደግሞ ወንጀል ነው። ባደግንበት ባህል የተለመደ ከሆነ እንኳን ወንጀል፥ ነውርም አይመስለንም። ደም መመለስ ወይም ብቀላም እንደዚያው። ሌሎችም ብዙ መዘርዘር ይቻላል።

ከባህል ምንነት ጋር ሦስት ቃላትን እንይ። ዋና ባህል (mainstream culture የሚባለውን ተመልክተናል። ሦስቱ ንዑስ ባህል፥ አጸፋ ባህል እና ትውፊት ናቸው።

1. ንዑስ ባህል ወይም ስንቅር ባህልም ይባላል፤ (subculture ይሉታል።) ይህ በአንድ ሕዝብ ባህል (mainstream culture) ውስጥ የሚገኝና ከባህሉ ገዢ አቋም በመጠኑ ያፈነገጠ፥ ታግሰውት፥ ችለውት የሚኖሩት አናሳ ባህል ነው። በአለባበስ፥ በአነጋገር ዘዬ፥ በሰውነት አያያዝ፥ በጺም እና ጸጉር አስተዳደግ፥ ወዘተ፥ ሊገለጥ ይችላል።

አንድዳንድ ማኅበረ ሰብ ውስጥ ባህሎች በእርከን ይለዩና ከፍ ያሉና ዝቅ ያሉ ተብለው ይለያሉ። ዝቅ ያለው ዝቅ ያለ የሚባለው የሰፊው ሕዝብ ስለሆነና ከፍ ያለው የጥቂት ልሂቃንና ምሑራን ባህል ስለሆነ ነው። ይህ የአነጋገር ዘዬንና አጻጻፍንም ያጣቅሳል (የጥንቱ ግሪክ ክላሲካል ግሪክ እና ኮይኔ ግሪክ እንደ ምሳሌ ሊወሰድ ይችላል። በዘመናችንም Hign German እና Low German ምሳሌ መሆን ይችላል በቋንቋ ረገድ።) የተለያዩ የሕዝብ ክፍሎች በአንድ አገር ሲኖሩ አንዱ ባህል ጎልቶ ወይም ገንኖ ሊወጣም ይችላል፤ ወይም ያቺ አገር የሁሉም ባህል የሚካሄድባት ኅብረ ባህላዊ (multicultural) አገር ልትሆን ትችላለች።

2. አጸፋ ባህል፤ ይህኛው ደግሞ አፈንጋጭ ባህል ነው። በአንድ ማኅበረ ሰብ ውስጥ አንድ ትውልድ ወይም በአንድ ትውልድ ውስጥ የሚገኝ የተወሰነ ክፍል ባህሉን ሲንቅ፥ ሲረግጥ፥ ሲጥስ፥ አዲስ የራሱን ባህል ሲመሠርት ያ አጸፋ ባህል ወይም አፈንጋጭ ባህል ይባላል። በእንግሊዝኛ counterculture ይባላል። በአሜሪካ በ1960ዎቹ በወጣቱ ትውልድ የጀመረው አካሄድ ዓይነቱ ነው። ይህ አካሄድ በ1970ዎቹ ቢደበዝዝም አሻራው እስካሁንም ሳይደበዝዝ ቆይቷል። እነዚያ ወጣቶች፥ ቢትኒክስ፥ ሂፒስ፥ እና ዉድስቶክስ ይባላሉ። የሮክ ሙዚቃ፥ ጸጉር ማሳደግ፥ ለአለባበስ ግድ የለሽ መሆን፥ በአሜሪካ የተከበሩ ነባር ባህሎችን፥ ማኅበራዊ እሴቶችን መናቅ፥ በቡድን አብሮ በመኖር ነፃ ፍቅር የሚሉትን ወሲባዊ ልቅነትና ግብረ ወጥነት መለማመድ፥ ማሪዋና እና ሌሎችም ሱስ አስያዥ ዕጾችን መውሰድ፥ ሌሎችም ይገኙበታል። ፖለቲካዊ አቋሞችንና መንግሥትንም መናቅና መቃወም አለበት፤ ጦርነትን መቃወም፥ የሴቶች መብትና የሲቪል መብቶች ንቅናቄዎች ላይ ድምጽ ማሰማትና እነዚህን የመሰሉ ቢኖሩም፥ እነዚህ ራሳቸውን የቻሉ የጊዜው ንቅናቄዎች ናቸው እንጂ የአጸፋ ባህሉ ውጤት አይደሉም። ለአጸፋ ባህሉ ያ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ትልቁ አጀንዳቸው አልነበረም። ከፖለቲካ ሌላዎቹ ነገሮች ግን የአጸፋ ባህል መገለጫ ነው።

3. ትውፊትስ፤ ትውፊት ከባህል ይለያል። ባህል የአንድ የተወሰነ ማኅበረ ሰብ ወይም የአንድ ሕዝብ የአንድ ወቅት ወይም ቀጣይነት ያለው ልማድና ወግ ነው። ትውፊት ደግሞ ከአንድ ትውልድ ወደ ቀጣይ ትውልድ፥ እና ተከታታይ ትውልዶች የሚተላለፍ የአንድ ሕዝብ የባህል፥ የልማድ፥ የሃይማኖት፥ የስነ ቃል፥ ወዘተ፥ ተላላፊ ክምችት፥ ቅርስ፥ ወይም ውርስ ነው። ትውፊት በዘመናት ውስጥ የዳበረና የዳጎሰ ስለሆነ፥ የብዙ ትውልዶች ድምር ውጤትም ስለሆነ፥ በአንድ ትውልድ ውስጥ አንለውጠውም። ትውፊትን አብዮት አካሂደን አንቀይረውም።

ይህ ባህልን በጠቅላላው መልኩ ስንመለከት ሲሆን፥ ነጥባችን ክርስቲያንና ባህል ነውና ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊው አሳብ እንምጣ። ወደ ክርስትና ስንመጣ መጽሐፍ ቅዱስ

የተጻፈበት ባህል ሙሉ በሙሉም ባይሆን በአብዛኛው የአይሁድ ባህል ነው። አይሁድ ሕግን የተቀበሉ ሕዝብ ብቻ ሳይሆኑ ሕዝብም ናቸውና፥ ሕዝብ ስለሆኑ ባህልም አላቸው። ይኑራቸው እንጂ ታዲያ፥ ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይጻፉም እንጂ፥ ይህ ባህል ንጥር እና ንጹሕ፥ ወይም የሁሉም ሊሆን የተገባው ባህል ነው ማለት አይደለም። የአይሁድ ባህል፥ እንደ ሌላው ባህል ሁሉ ነው።

የአይሁድ ባህል ራሱም ንጥር የአይሁድ ባህል አይደለም። አይሁድ ገና ሕዝብ ሳይሆኑ ነው ወደ ግብጽ የገቡት። ወደ ግብጽ ሲገቡ ቁጥራቸው አንድ መቶም አይሞላም ነበር። ከዚያ በፊት ከአብርሃም እስከ ያዕቆብ ድረስ ያለው ሦስት ትውልድ ከከለዳውያን ዑር ባህል፥ ከሁለት ወንዞች መሐል ወይም ከመስጴጦምያ ባህል፥ እና የተስፋዋ ምድር ከተባለችው የከነዓናውያን አገር ባህል ጋር ትከሻ ለትከሻ የተጋፋ ብቻ ሳይሆን የተቀያየጠም ባህል ነው። ኋላ የግብጽ ሲጨመርበት የአራት ሕዝብ ባህል ቅይጥ ነበር ማለት ነው። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሕግ ወይም ትምህርት እንጂ <u>መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባህል የሚባል ነገር የለም።</u>

አይሁድ ሕዝብ የሆኑት እነዚህን ባህላዊ ዳራዎች ይዘው በግብጽ ውስጥ ነውና የግብጻውያንን ባህልም ሸምተዋል። በእርግጥ ቀድሞ ከብት ወይም እንስሳ አርቢዎች ስለሆኑና አርብቶ አደሮች ደግሞ በግብጻውያን ዘንድ የተጠየፉ ስለሆኑ ለብቻቸው ለምለም በሆነው በጌሤም ኖረዋል። በዚህ ተለይቶ መቆየት ባህላቸው የተጠበቀላቸው ይመስላል። ይሁን እንጂ ባሪያዎች ከሆኑ በኋላ ያ ባህል የተጠበቀ ነበረ ማለት አይቻልም። በዚህ የተቀያየጠ ባህል ማዕቀፍ ውስጥ እያሉ ነው አርነት የወጡትና ሕጉ የተሰጠው።

ሕጉ ባህል አይደለም። ሕጉ ባህል ዘለልም፥ ድንበር ዘለልም፥ ዘመን ዘለልም ነው። ኪዳኑ እንደ ኪዳን ከአንድ ሕዝብ፥ ከአይሁድ ሕዝብ ጋር የተገባ ቢሆንም፥ ኪዳኑ በአዲስ ኪዳን እስካልተተካ ድረስ በዚያ ሕዝብ ላይ ነዋሪ ነው፤ ጉልበታም ነው። እስካልተተካ ድረስ ነው ያልኩት። ኪዳኑ ደግሞ ተተክቷል፤ አሮጌው ኪዳን ገና ሕያው ሳለ እግዚአብሔር አዲስ ኪዳን እንደሚገባ ተናግሮ ነበር፤ *እነሆ፥ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር፤* ኤር. 31፥31።

አዲሱ ኪዳንም በክርስቶስ ደም ተደረገ ወይም ተገባ፤ *ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።* ማቴ. 28፥28። ከመስቀሉ ወዲህ ኪዳኑ ተለውጧል፤ እኛ የአዲሱ ኪዳን ሰዎች ነን፤ *እርሱም ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን፤ ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል።* 2ቆሮ. 3፥6። ሕጉና ኪዳኑ እንዲህ ነው መታየት ያለበት።

የአይሁድ ባህል ግን እንደሌላው ባህል ሁሉ፥ ከላይ ካየነው የመወራረስ ባህርይ ባሻገር ዘመን ዘለልነትና ሁሉን አቀፍነት ባህርይ የለውም። ዘመን ዘለሉ ቃል ግን በባህል ውስጥ ይናኛል ይተገበራል። ቃሉ ተለዋዋጭ አይደለም። ቃሉና ባህል ሲጋጩ ቃሉ ባህሉን ይለውጣል እንጂ ባህሉ ቃሉን አይለውጥም። ወደዚህ ነጥብ እመለሳለሁ።

በአዲስ ኪዳን፥ ቤተ ክርስቲያን የተወለደችው በአይሁድ ባህል ውስጥ ቢሆንም ያ ዘመን ግሪካዊና ሮማዊ ባህልና አመለካከት ዓለሙን የገዛበት ዘመን ነበር። ከሮማውያን ቀደም ሲል ግሪካውያን ነበሩ ያንን ዓለም የገዙት። ቤተ ክርስቲያን ተወልዳ ብዙ ሳይቆይ ወደ አሕዛብ ውስጥ ሰርስራ ልትገባ ችላለች። ከሁለቱ፥ ማለት፥ ከአይሁድ እና ከአሕዛብ አንድ የራሱ የሆነ አካል መሥራት የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ነበረ። በዘመኑ ለነበሩት ለብዙዎቹ የአሕዛብ ወገኖች ባህላቸው ከሃይማኖታቸውም ጋር የተቆራኘ ነው። ብዙዎቹ የብዝሐ አማልክት እና ጣዖታት አምላኪዎች ናቸው። አንዳንዶቹ አንድ ጣዖትን ወይም አምላክን ከሌሎቹ ጣዖታት በላይ አድርገው ያመልካሉ እንጂ አንድና አንድ ብቻ አምላክ የሚሉ አልነበሩም። የብዙዎቹ ባህላቸውና ሃይማኖታቸው አብሮ የተለወሰ ነውና አሐዳውያን ነበሩ ማለት ይቻላል። ዛሬም በአንዳንድ አሐዳውያን ማኅበረ ሰቦች (unitary society) ሃይማኖትና ባህል የተቆራኙ ናቸው።

የክርስቶስ ወንጌል ነጻ ካወጣቸው በኋላ በአዲስ ኪዳን የምናገኛቸው አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ከቀድሞ ልማዳዊ ሃይማኖታቸው ሲላቀቁ ከባህላቸው ውስጥ የቱ ማኅበራዊው፥ የቱ ሃይማኖታዊው መሆኑን ለመለየት ሲቸገሩ ይስተዋላል። የገላትያ፥ የቆላስይስ፥ የሮሜ እና የቆሮንቶስ መልእክቶች እነዚህን ጉዳዮችም ያወሳሉ። ጴጥሮስ የጻፈላቸው የተበተኑ ወገኖችም ይህ ችግር ነበረባቸው። ክርስቲያኖች ባህልን በተመለከተ ግልጽ አቋም ሊኖራቸው የተገባ ነው።

ቤተ ክርስቲያን በባህል ተደፍጥጣ ባህሉን የምትመስል ወይም በዓለም ቅርጽ ተጨፍልቃ ዓለምን እንድትመስል የተጠራች አካል አይደለችም። *የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።* ሮሜ. 12፥ 2። አማኞች ዓለምን እንዳይመስሉ ብቻ ሳይሆን በተቃራኒው ክርስቶስን በመምሰል ዓለምን እንዲለውጡ የተጠሩ ናቸው። *ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወሰናቸልና፤* ሮሜ 8፥29።

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈባቸው ቋንቋዎች ሕዝቦች ባህል ነበራቸው። ብሉይ ኪዳን በዕብራይስጥ ነው የተጻፈው (ከጥቂት ክፍሎች በአራማይስጥ መጽጻፍ በቀር።)

አራማይስጥ ከአይሁድ የሰፋ ሕዝብ ቋንቋ ቢሆንም ሁለቱም የአይሁድ ቋንቋዎች ናቸው። አይሁድ ባህልና ወግ አላቸው። ሕጉ ቢጨመርበትም ቀድሞም ወግ ነበራቸው። አዲስ ኪዳን በግሪካዊና ሮማዊ ባህልና ወግ ውስጥ በግሪክ ቋንቋ ነው የተጻፈው። በሁለቱም ኪዳናት ሕግ ያልሆኑ፥ በሕጉ ውስጥ ያልተጻፉ ልማዶች መኖራቸው አልፎ አልፎ ፍንጥቅ ተደርጎልናል። ለምሳሌ፥ ሩት. 4፥7-8 ላይ በዘመኑና ከዚያም በፊት የግዢ ማጽኛ እንዲሆን ጫማ አውልቆ መስጠት የተለመደ መሆኑ ተጽፎአል። ይህ በሕጉ ውስጥ የለም፤ ልማድ ግን ነውና በባህላቸው ቦታ ነበረው። በ1ሳሙ. 2፥13 ሕዝቡ መሥዋዕት ሲያቀርብ ሥጋው ሲቀቀል የካህኑ ሎሌ በሜንጦ ይወስድ ነበር። ልማድ ተብሎአል። በአዲስ ኪዳን ለአገር መሪ በበዓል የወደዱትን አንድ እስረኛ የመፍታት ልማድ ነበረ፤ ማቴ. 27፥15። በዮሐ፣ 19፥40 የአገናነዝ ልማድ የሚባልም ተጠቅሶአል። እነዚህ ልማዶች ወይም የባህል ገጽታዎች ናቸው።

አንድ ማኅበረ ሰብ ሃይማኖት ኖሮትም የባህል ወይም የትውፊት እስረኛ ሊሆን ይችላል። በሃይማኖትና ባህል መስተጋብር ሦስት ዓይነት አቀባበሎች ወይም መቀባበሎች ሊኖሩ ይችላሉ። እንደ ሕዝብና እንደ ዜጋ፥ አንደኛ፥ ባህላችንን ከማክበራችን የተነሣ ከእምነታችንም የምናስቀድም ልንሆን እንችላለን፤ ሁለተኛ የምናመቻምች እና በባህሉ የምንወሰድ ወይም ሁለቱንም ልናስደስት የምንታገል ልንሆን እንችላለን፤ ወይም ሦስተኛ፥ ባህሉ ለእምነት መገዛት አለበት የምንል ሃይማኖተኞች ልንሆን እንችላለን።

ባህልና እምነት ተቀይጠው ሃይማኖታዊ ባህል ወይም ባህላዊ ሃይማኖት ባለበት ይህ አቀባበል ወይም መቀባበል ችግር አይደለም። ሃይማኖትንም ባህልንም በእኩል ዓይን ለሚያዩ፥ እኩል ክብደት ለሚሰጡ ሰዎች ይህ ችግር የለበትም። ነገር ግን፥ እንደ አማኝ ወይም እንደ ክርስቲያን ደግሞ እምነታችን ከባህላችን ይበልጣልና፥ ይቀድማልና፥ የእምነታችን መመሪያ በባህላችን ላይ መሠልጠን ወይም ባለ ሥልጣን መሆን አለበት። ብዙዎቹ የባህል መገለጫዎች መልካም ቢሆኑም፥ እነዚህ ሁለቱ ከተጋጩ ትክክለኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊው ትምህርት ይሆናል ማለት ነው።

ይህ ክፍል የባህልን እና ክርስትናን መስተጋብር በመጠኑ በትነን እንድናይ ያደርገናል። እንደ አገራችን ባለ ብሔረ ሰባዊነት (ወይም የጎሳ ፌዴራላዊነት) የአንድ አገር አስተዳደርና ፍልስፍና ዐቢይ ክፍል ሲሆን የጎሳው ባህል ይገዝፍና፥ የበላይ ይሆንና፥ ሁሉንም ነገር ለመዋጥ ይቃጣዋል። ሃይማኖትንም ጭምር። በአንዳንድ ባህላዊ በዓላት መገኘትና፥ መገኘት ብቻ ሳይሆን ተሳታፊ መሆንም ግዴታ እስከ መሆን ይደርሳል። ያ በዓል ባህላዊ ብቻ ሳይሆን ሃይማኖታዊ ወይም ከጣዖት አምልኮ ጋር የተቆራኘ ከሆነና ክርስቲያኖች ለመገኘት ባይፈቅዱ ችግር ላይሆንባቸው ይችላል። ነገር ግን መገኘትም መሳተፍም ግዴታው የሚሆንበት ክርስቲያን ሊኖር ይችላል። ያኔ መቆም ያለበትን

አቋቋም ማወቅ አለበት። ይህ አምልኮም ሊሆን ስለሚችል በዳን. 3 እንደተጻፉት ወጣቶች የመሰለ የጀርባ አጥንት ያስፈልጋል።

ክርስትና የባህል አብዮትን እንዲያካሂድ መጠበቅም ማሰብም የለብንም። ወንጌል ወደ አይሁድም ሆነ ወደ አሕዛብ ሲገባ በመጀመሪያ ባህልን አልለወጠም። ጌታ የሰጠው ተልእኮ ባህልን የመለወጥ ተልእኮም አልነበረም። ዓለማችን የሚያስፈልጋት የባህል ለውጥ ወይም የባህል አብዮት አይደለም። የዓለማችን ወይም የሰው ልጆች መሠረታዊ ችግር ባህል ሳይሆን ኃጢአት ነው። ችግሩ ባህል ቢሆን ኖሮ መፍትሔው የባህል ቅየራ ሊሆን በተገባም ነበር። ነገር ግን ችግሩ ባህል ሳይሆን ኃጢአት ስለሆነ መፍትሔው ደግሞ አዳኝ ነው። አዳኙም ኢየሱስ ነው።

ወንጌል ውስጥን፥ መንፈስን፥ መንፈሳዊ ማንነትን ነው በመጀመሪያ የሚለውጠው። ይህ ውስጣዊ ለውጥ ከውስጥ ይጀምርና አድማሱ እየሰፋ ይሄዳል። አካልን ይለውጣል፥ አእምሮን ይለውጣል፤ ስሜትን ይገዛል፥ ይማርካል፤ ቤተ ሰብን ይቀይራል፤ ወደ አኗኗርና አካሄድ ይዘልቃል፤ ወደ ባህልም ይሰርጻል። ይህ የተለወጠ ማንነት ባህሉን ሊፈትሽና ከቃሉ ጋር ከተጣጣመ ሊቀበለውና አዲሱንና ዋናውን ተልእኮውን ሊያሰርጽበት፤ ካልተጣጣመ ደግሞ ሊገፋውና ሊፋታው፥ ወዲያም ሊለው ይችላል፤ ይገባልም። ባህል በአዲሱ ማንነቱ ላይ በግዴታ ሊጫንበት አይገባም። በአገራችን አንድ ሰው ጌታን ሲቀበል የሚደርስበት አንዱ ስደት ባህሉን መጣሉ ነው። ከሃይማኖታውያኑ ዘንድም እንኳ ከሃይማኖት ይልቅ ስለ ባህላቸው ሲሉ ነው ለመበቀል የሚነሡት። ስለ ባህላቸው መሆኑን የምናውቀው፥ ከእነዚህ ተበቃዮች አንዳንዶቹ ስለ ሃይማኖታቸው ስለ ራሱ ምንም እውቀትም፥ ደንታም የሌላቸው በመሆናቸው ነው። ስለ ሃይማኖታቸው ማይማን ሆነው ለባህላቸው ግን ተቆርቋሪ ናቸው።

በሁለት አጫጭር መጣጥፎች አንዴ በኢሬቻ በዓል እና አንዴ በመስቀል በዓል ላይ ጽፌአለሁ። እነዚህ ባህላዊም ሃይማኖታዊም በዓላት ናቸው። መስቀል ስሙ አዲስ ኪዳናዊ ቢሆም በዓሉና አከባበሩ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። የአዲስ ኪዳኑ መስቀል የሚሸከሙት የደቀ መዝሙርነት መታወቂያ እንጂ የሚያከብሩት በዓል ሆኖም አያውቅም። ክርስቲያኖች በነዚህ በዓላት ሲሳተፉ ምን እያደረጉ መሆናቸውን በውል ማወቅ ይኖርባቸዋል። አንዱ የኢሬቻ ጉዳይ ጽሑፌ አንድ ክርስቲያን ለጻፈው መጣጥፍ ምላሽም ነው። ይህን 'ክርስቲያናዊ' መጣጥፍ ኢሬቻን ክርስትና አስነሥቶ (ማስመሣት የሚባል ነገር ከኖረ) ፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሊያደርገውና ክርስቲያኖችም በሙሉ ልብ እንዲሳተፉበት የሄደበት የትየለሌ ርቀት ነው ምላሽ እንድሰጥበት ያደረገኝ። ክርስቲያኖች በባህላዊና ሃይማኖታዊ ከባቢዎች ሲገኙና ሲሳተፉ እምነታቸውንና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አቋማቸውም መሠሪያ ላይ ኢጋድመው

መሆን ፈጽሞም የለበትም። ክርስትና ባህልን መቀየር ዋና ግቡ ባይሆንም በሂደት ውስጥ በባህል ላይ ተጋቦትን ያሳድራል እንጂ የባህል መርፌ ተወግቶ ልምሻ አይይዘውም።

አንዳንድ የአፍሪቃ አገሮች ከቅኝ ገዢዎች ነፃ ሲወጡ የነጮችን ቀንበር አርቀው የጣሉና የተበቀሉ እየመሰላቸው፥ ዘመናዊ እውቀትን ከቀሰሙ በኋላም እንኳ ከቅኝ አገዛዝ ዘመናት በጣም በፊት የነበሩ የቀደሙ ትውልዶችን ልማዶችና ባህሎችን ከመነመኑበትና አንዳንዶቹንም ከሞቱበትም እያወጡ ሲተገብሩና ሲኖሩባቸው ይታያሉ። ክርስትናን የሚቃወሙ አንዳንድ ዘመናዊ የስነ ሰብእ አጥኚዎች ወንጌል ወዳልደረሰባቸው የሕዝብ ክፍሎች ወንጌል እንዳይደርስ አጥብቀው ከሚታገሉበት ምክንያቶች አንዱ፥ 'ነባሩ ልማዳቸውና ባህላቸው ስለሚጠፋ ነው' ይላሉ። እነዚህ 'ሊቃውንት' የማያስተውሉት ነገር አንዳንዶቹ ጎሳዎች በወንጌል ምክንያት ባይተርፉ ኖሮ እንኳን ልማዶችና ባህሎች ሊተርፉላቸው፥ ራሳቸው ሰዎቹም ሊገኙ እስከማይችሉ ድረስ የሚገዳደሉ፥ ግድያ፥ ብቀላ፥ ደም መላሽነት፥ የሰው ሥጋ የመብላት ጭራቅነት፥ ሕጻናትን መግደል ወይም ለአራዊት መስጠት፥ የባህሎቻቸው ገጽታዎች የሆኑ ሰዎችም ነበሩ። ዛሬም እንዲህ ያሉ ባህሎችና ልማዶችን የሚያስተናግዱ ጎሳዎች ይገኛሉ። በአገራችንም አሉ።

አንድ ባህል እንደ ባህል በመላው ክፉ ወይም በሁለንተናው ጥሩ አይደለም። የአንድ ማኅበረ ሰብ ባህልም ከሌላው የተለየ ነው እንጂ የበለጠ ወይም ያነሰ አይደለም። ባህልን ስናስብ፥ ባህል የሰው ሥሪት መሆኑን ማወቅ አለብን። ማናቸውም የሰው ሥሪት የሆነ ነገር ፍጹም አይደለምና በፍተሻ ነው መቀበል ያለብን። ሰው ክቡር ነው፤ ግን የወደቀም ነው። እንደ እግዚአብሔር ፍጡር ክቡር፥ በአዳም ደግሞ የወደቀ ነው። ባህሎች እነዚህን ሁለት ገጽታዎች ማንጸባረቃቸው የማይቀር ነው። ስለዚህ በባህሎች ውስጥ ጎጂም ጠቃሚም ገጽታዎች ይታያሉ።

ልብ እንበል፤ ይህች ዓለም በአዳም ስትወድቅ ሁለመናዋ ነው የወደቀው። ይህ ውድቀት የሰውን መንፈሳዊ ማንነት ወይም ሁኔታ ብቻ የሚናገር አይደለም። የሰው ስሜታዊ፥ ሞራላዊ፥ አእምሮአዊ፥ አካላዊ፥ ማኅበራዊ፥ ሌላውም ሁሉ ማንነቱ ነው የተበከለው። ባህላችን እና የትኛውም ባህል፥ ከወደቀ ሰው የመነጨ ነው። ለክርስቲያን፥ ባህል ራሱ ምርቱ ከግርዱ፥ ጎጂው ከጠቃሚው ተለይቶ ለሰው ጥቅም፥ ለእግዚአብሔርም ክብር መዋል የተገባው እንጂ እንደ ተቋም ከክርስቶስ አካል ጋር መደራደርና ቦታ መሻማት ያለበት ነገር አይደለም። ባህል የረከሰ፥ የወደቀ፥ ከክብር የጎደለ ሰው የሠራው ማኅበራዊ ግኝት ነው እንጂ አስቀድሞ የተፈጠረ 'ንጹሕ ባህል' የሚባል ነገር የለም። ንጹህ የሚባል ባህል ኖሮ ሰው ኋላ ተፈጥሮ እዚያ ውስጥ አልገባም። ባህልን የሠራ ሰው ነው፤ ባህል የሰው ሥራ ውጤት ወይም ሥሪት ነው።

እንደ ክርስቲያን የባህል ንጥረ ነገሮች ትርጉማችን እና ግንዛቤያችን ከባህላችን ወይም ከሌላው አገር ባህልም መሆን የለበትም። ቃሉ ስለ ባህል ወይም ወጎች የሚለውን ማወቅ ብቻ ሳይሆን መቀበልም ግዴታችን ነው፤ ማር. 7፥8-13 ይህንን ይነግረናል። በዚህ ምንባብ፥ *የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል* የተባለውን ትንቢት የጠቀሰበት ነው። *ወጋችሁን ትጠብቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እጅግ ንቃችኋል።* ያለበት ነው። ወጉ ከቃሉ የበለጠበት አካሄድ ይታያል።

ማናቸውም ባህል፥ የኛም ባህሎች ክቡር የሆኑ ያሉባቸውን ያህል ጉድፎችም አሉባቸው። አገራችን ብሔረሰቦችንና ባህሎቻቸውን ማድነቋ ድንቅ ቢሆንም፥ ለክርስቲያኖች ባህሎችን በቅዱስ ቃሉ መፈተሽና መመዘን እንጂ በጅምላ መግዛት አልተፈቀደም። ለባህል ማጎብደድና ለባህል ሲባል ቃሉን በውኃ ማቅጠን ክርስቲያናዊ አካሄድ አይደለም። ለሥልጣንና ለሥራ፥ ለመመረጥና ለመሸለም ተብሎም ጤናማ ያልሆኑ ባህላዊ ንጥረ ነገሮችን መቀበልና፥ በተለይም ከአምልኮ ጋር የተያያዙትን መተግበር የግዴታ ቀንበር ሆነው በአማኞች ላይ ሊጫኑ የተገባ አይደለም። ባህላዊ አመቻማችነት ጤናማ አይደለም። ባህላዊ አመቻማችነት ለባህል ለማጎብደድ ሲባል እምነትን ለውርርድ የማቅረብ ስሕተት ነው። ባህላዊ አመቻማችነት ክርስትናን ሊጎዳ የሚችል አካሄድን መሄድ ነው። የክርስትና ዋና ግብ ባህልን መለወጥ ሳይሆን ውስጥን መለወጥ ነው። የተለወጠ የውስጥ ሰው፥ የተለወጠ አእምሮና አመለካከት፥ የተለወጠ አካልና የራስ አያያዝ፥ የተለወጠ ቤትናና ቤተ ሰብ፥ የተለወጠ ማኅበረ ሰብም ይፈጥራል። ግን የሚጀምረው ከውስጥ ነው። መንፈሳዊ ለውጥ መሠረቱ ነው።

ወደ ዘመናችን ባህሎች ስንመጣ፥ ድኅረ ዘመናዊነት ሁሉን ተቀባይ የሚያደርጋቸው በመሆኑ ይህንን ታከከው ባህሎችና ባህላዊ መገለጫዎች ራሳቸውን የቻሉ ሃይማኖታዊ ተቋማት እስከመሆን እየደረሱ ነው። ቀደም ሲል ከቅኝ አገዛዝ ነጻ የወጡ ሕዝቦች የቀደሙ ትውልዶችን ልማዶችና ባህሎችን ከመነመኑበትና አንዳንዶቹንም ከሞቱበትም እያወጡ ሲኖሩባቸው ይታያሉ ብያለሁ። አንዳንዶቹን ባህሎች ወደ ሃይማኖት ቀይረው ሲያመልኩባቸውም ይታያሉ። ክርስቲያኖችም ይጠመዱባቸዋል፤ ሃይማኖቶች የባህል ለምድ ለብሶ በባህል ስም ስለሚቀርቡ አሰናካይነታቸው አይታይም። ስለዚህ መሰናክል ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገባ ቀንዳምና ጥፍራም ሳይሆን ቀንዱን ተከርክሞ፥ ጥፍሩን ተቆርጦ ነው። ቆይቶ ግን ቀንዱም፥ ጥፍሩም ያድጋሉ።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባህል የሚባል አንድ ባህል ኖሮ ቢሆን ያንን መከተል በተገባን ነበር። ግን የለም። ባህል የማኅበራዊ መስተጋብር መገለጫ ዘዬ ነውና፥ ከባህል ውስጥ ሁሉም ነገሮች ለባህሉ ሰፊ ተካፋዮች ወይም ቢያንስ፥ ለሰፊው ሕዝብ፥ መልካም የመሰሉ እንጂ በባህሉ ውስጥ ላሉትም መቶ በመቶ ተቀባይነት ያላቸው ላይሆኑ ይችላሉ። ይልቁንም በአንድ የሕዝብ ክፍል ተቀባይነት የኖራቸው ባህሎች በሌላ

የሕዝብ ክፍል የተጸየፉ ሊሆኑም ይችላሉ። በዚህ ረገድ የባህላዊ ስነ ሰብእ (Cultural Anthropology) ጥናቶች ብዙ ምሳሌዎችን ያቀርባሉ።

ሌላው፥ በዚያው በአንዱ ባህል ውስጥ ያሉት ነባር ባህሎች ራሳቸው በማኅበረ ሰቡ ማኅበራዊ ስነ ልቡና ማደግ ወይም የሕሊና ንቃት መዳበር የተነሣ አሮጌና ኋላ ቀር ተደርገው ሊናቁና ሊጣሉ ይችላሉ። በአገራችን በደርግ ዘመን መጀመሪያ የዕድገት በኅብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ የተባለው የተማሪዎችና ምሑራን ዘመቻም በዚህ ረገድ ብዙ አድርጓል። ሰፊ መሠረት ተጥሎለት የተጀመረው የቻይና ቅጂ 'የባህል አብዮት' ይህን ሊያደርግ ሞክሮ ነበር። ጎጂ ባህሎች ብሎ ጥቂት ያልሆኑ ማንቂያዎችን አድርጓል። በባህል ስም ሃይማኖትን ሲነቅፍ ግን ከግድግዳ ጋር ነበር የተላተመው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ባህላዊ ብቻ ሳይሆን ሃይማኖታዊ መሆኑን አላስተዋለም። በተለይ ወንጌላዊ ክርስትናን ለመምታት በደርግ የተደረገው ጥረት ከዚህ አንጻር የሚታይ ነው።

ከንቃተ ሕሊና በተጨማሪ መንፈሳዊ መረዳት ወደ ግለ ሰቡ ወይም ማኅበረ ሰቡ ክፍል ሲገባ ከመንፈሳዊ እሴቶቹ ጋር ነው የሚገባው። መንፈሳዊ ስል ጠቅላላ መንፈሳዊ ኹነትን መናገሬ ቢሆንም ይህኛው ጉዳያችን ስለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘት ስለሆነ በተለይ ስለ ክርስትና መናገሬ ነው። ወንጌል ወደ አንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ወይም ወደ አንድ የሕዝብ ክፍል ሲገባ መንፈሳዊው እሴት ባህላዊውን ቀለም ብዙውን ጊዜ ይበርዘዋል፤ ቆይቶም ይለውጠዋል። የወሊዱና የጋብቻው፥ የቀብሩና የልቅሶው፥ የሥራና ግንኙነቶች መስተጋብሮች ቅርጽና ይዘት በቃሉ መታየትና መከርከም ይጀምራሉ። ክርስቲያኖቹ እንደ ክርስቲያን ሲኖሩና ሲሠሩ ለውጥ ፈጣሪ ይሆናሉ።

ይህ ለውጥ፥ ወይም በአንዳንዶች እይታ፥ ብረዛና ቅየራ፥ ጥሩ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ እንደ ባህሉ ጠቃሚነትና እንደ ተሟጋቾቹ ጥንካሬ አከራካሪ ሊሆን ይችላል። አንዳንዶች የባህል አብዮታውያን ሸንጣቸውን አሸንፍጠው ጎጂ እንኳ ቢሆኑ ባህሎች በሃይማኖቶች መለወጥ ቀርቶ መደፈርና መነካትም የለባቸውም የሚል ግልጽ አቋም ይይዛሉ። በዚህም ክርስትና የገባባቸውን አንዳንድ ሕዝቦችን ባህሎች መለወጥ በጸጸት በማሰብ ክርስትናን ይኮንናሉ። በአንጻሩ ደግሞ በማገዳደል በዘር ማጽዳት ፈጽመው ሊጠፉ ይችሉ የነበሩ ሕዝቦች ባህሎች በወንጌል አማካይነት በመወገዳቸው ምክንያት ባህሉ ቢጠፋም ሕዝቡ ሊተርፉና ሊደላደሉ ስለቻሉ ሕዝቦች በማሰብ የሚያደንቁና የሚያመሰግኑ አሉ። አንዳንድ ሃይማኖቶች ከባህሎች ጋር ባህላዊ ቅርሶችንም ከማውደም አይመለሱም። የታሊባን መንግሥት ለምሳሌ፥ ከእስልምና በፊት የነበሩ የቡድሂዝም የባህልና ሃይማኖት ቅርሶችን ዩኔስኮ እየተማጸነም እንኳ፥

አውድሞአቸዋል። አንዳንድ ሃይማኖቶች ደግሞ በአንጻሩ፥ ባህሎችን አጥበውና አጽድተው የሃይማኖቱ መገልገያ ያደርጉታል።

ወደ አይሁድ ባህል ስንመጣ፥ የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን አዳምና ሔዋን ሲፈጠሩ ጀምሮ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የነበራቸው ቢሆኑም ከውድቀት በኋላ ይህ ግንኙነት ተበላሽቶአል፤ ተሰብሮአል። ከሰዎች መብዛት እንዲሁም፥ ብታኔና ዝርወት በኋላ ባህልና ሃይማኖት የተቆራኙ ገመዶች ሆነው ሕዝብን ሲያስተሳስሩ ኖረዋል። እግዚአብሔር ጥቂት ሆነው ወደ ግብጽ የወረዱትን አይሁድ እንደ ሕዝብ ሲያወጣቸውና ሕግ ሲሰጣቸው ቀድሞ ባህል የሌላቸው ሰዎች አልነበሩም። ሲወልዱ ወይም ሲያሳድጉ፥ ሲሞቱና ሲቀብሩ፥ ሲዳሩና ሲጋቡ፥ ሲገበያዩና ሲዋጉ የሚያደርጉት ወግ የሌላቸው አልነበሩም።

የተሰጧቸው ሕግጋትም መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ብቻ የሚመለከቱም አልነበሩም። ሕጉ ማኅበራዊ አወቃቀራቸውንም የዳሰሰ ነው። እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች ለርስቱ የተለየ ሕዝብ አድርጎ ሲመርጣቸው በአኗኗራቸው በዙሪያቸው ከነበሩት አሕዛብ የተለየ እንዲሆኑ ነው። ይህ መለየት ባህልንም ይነካል። በዋናነት የተጠሩት የእርሱ ወኪል ሕዝብ ሆነው እንዲኖሩ ስለሆነ የእርሱ ሲሆኑ የእርሱ መሆናቸውን የሚያንጸባርቁት የተለየ ማንነት አላቸው። ስለዚህም፥ ሌሎቹ ባህሎቻቸው የሕጉ ተገዢ ሆነው የማንነቱና በእርሱ ያገኙት ማንነታቸው ነጸብራቅ ይሆናሉ። ይህ ትክክለኛ የባህል በመለኮታዊ ሕግ ስር የመሆን መንገድ ነው። ልብ ማለት ያለብን፥ እነዚህ ሰዎች የተጠሩትና እየተቀረጹ የነበረው በጠቅላላ፥ ማለትም፥ እንደ ሕዝብ ሆነው ነው።

ብዙ ሳይቆዩ ግን እነዚህ ሰዎች ወይም አይሁድ፥ ለእግዚአብሔር የርስቱ ሕዝብ መሆናቸው ቀርቶ፥ ሕጉን እንደ ማነቆ አዩት፤ ወደ ነበሩበት ወደ ግብጽ መመለስም ተመኙ። እንደተመኙት አልተመለሱም፤ ወደ ተስፋዋ ምድር ገቡ። ልባቸው ግን ከአምላካቸው ጋር አልነበረም። ከገቡ በኋላም፥ ለእግዚአብሔር ልዩ ሕዝብ እንደመሆናቸው መጠን በመኖር እግዚአብሔርን ማንጸባረቅ ሲገባቸው፥ በዚህ ፈንታ፥ በዙሪያቸው ከነበሩት አሕዛብ ጋር ነበር የተመሳሰሉት። ተደባለቁ፥ ተቀየጡ እንጂ ማንነታቸውን አልጠበቁም። ተወረሱ እንጂ አልወረሱም። ምድሪቱንም እንኳ በወጉ አልወረሱም።

እነዚህ ሰዎች በእውነት እንደታሰበላቸው ኖረው ቢሆን ከአይሁዳዊ ሕዝባዊ ባህል በተለየ መልኩ 'መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባህል' የሚባል ነገር ሊኖር በቻለና የዚያንም ባህል መልክ በተገነዘብን ነበር። ግን አልሆነም። ይህን በተመለከተ፥ ከላይም እንዳመለከትኩት፥ ላሰምርበት የምወደው ዋና ጉዳይ ሃይማኖትን (በዚህ ዐውድ

ክርስትናን) የሚወርረው ባህል ሳይሆን ባህልን የሚወርረው ሃይማኖት መሆኑን ነው። ሃይማኖቱ ባህሉን በመላው ላይቀይረው ይችላል። ክርስትናና ባህል ለምርጫ ቢቀርቡ መራጩ ክርስቲያን መምረጥ የተገባው እምነቱን መሆኑ ግን ግልጽ ነው። እምነቱ በባህሉ ላይ ጫና ሊፈጥር ይገባዋል እንጂ ባህሉ እምነቱን ሊቀርጽለት መልቀቅ እና መፍቀድ የለበትም። ባህል መልካም ገጽታዎች እንዳሉት ግልጽ ነው፤ ክርስትና ግን በመላው መልካም ስለሆነ በባህሉ ውስጥ የሚገኙት መልካም ነገሮች በዚህ ውስጥ ይገኛሉ።

ስደመድም፥ እንግዲህ የአይሁድ ባህል የምንለው ምኑን ነው? የአይሁድ ባህል የምንለው አብርሃም ከአገሩና ከሕዝቡ ተለይቶ ሲወጣ ካደገበትና ከኖረበት ጀምሮ ወደ በተስፋይቱ ምድር የኖረበትን፥ እርሱም ይስሐቅም በተስፋዋ ምድር ቀዬ እና እስከ ግብጽ በኖሩባቸው የነበረውን፥ ያዕቆብም በሁለት ወንዞች መካከል በኖረበት ዘመንና ወግ የደለበውን፥ ወደ ግብጽ ወርደው በኖሩበት ከ400 በላይ ዓመታት የተጠቀጠቀውን፥ ወደ ተስፋዋ ምድር ከገቡ በኋላ ከዙሪያቸው አሕዛብ ጋር ተደባልቀው በኖሩባቸው ዘመናት ያካበቷቸውን፥ በምርኮ ምድር የቋጠሯቸውን ባህሎች ሁሉ ማለታችን ነው።

ወደ ክርስትና ስንመጣ ወንጌል ወደ አይሁድም ወደ አሕዛብም ሲገባ በመጀመሪያ የለወጠው ባህልን አይደለም ብለናል። ባህልን የመለወጥ የወንጌል ተልእኮም አይደለም። የወንጌል ተልእኮ ደቀ መዛሙርት ማድረግ ነው። ጌታ የሰጠው። ዓለማችን የሚያስፈልጋት የባህል ቅየራ ሳይሆን የዓለማችን ወይም የሰው ልጆች መሠረታዊ ችግር የሆነው የኃጢአት መወገድ ነው። የኃጢአት መፍትሔውም አዳኙ ኢየሱስ ነው።

ወንጌል ውስጥን፥ መንፈስን፥ መንፈሳዊ ማንነትን ነው በመጀመሪያ የሚለውጠው። ይህ ውስጣዊ ለውጥ ከውስጥ ይጀምርና አድማሱ እየሰፋ ይሄዳል። ይህ የተለወጠ ማንነት ባህሉን ሊፈትሽና ከቃሉ ጋር ከተጣጣመ ሊቀበለውና አዲሱንና ዋናውን ተልእኮውን ሊያሰርጽበት፤ ካልተጣጣመ ደግሞ ሊገፋውና ወዲያ ሊለው ይገባል። ባህል በአዲሱ ማንነቱ ላይ በግዴታ ሊጫንበት አይገባም። ይህ በነጠላም በወልም ነው። ክርስቲያኑ ማኅበረ ሰብ በአሮጌው ማንነቱ የተገዛላቸው የባህሉ መንጸባረቂያዎች በአዲሱ ማንነቱ ላይ ገዥ ሆነው ሊቀጥሉ መፈቀድ የለበትም።

ባህላዊ አመቻማችነት ከክርስቲያን የሚጠበቅ አይደለም። ይህች ዓለም በአዳም ስትወድቅ ሁለመናዋ መውደቁ፥ የሰውን መንፈሳዊ ማንነት ወይም ሁኔታ ብቻ ሳይሆን፥ የሰውን ስሜታዊ፥ ሞራላዊ፥ አእምሮአዊ፥ አካላዊ፥ ማኅበራዊ፥ ባህላዊ ማንነቱ ሁሉ ነው የዳሰሰ ብክለት ነው። እነዚህ ነገሮች ሁሉ የማንነቱ መገለጫዎች

ናቸውና ሰው በክርስቶስ ሲዋጅ ከእነዚህ ተጽዕኖዎች ሁሉ አብሮ ነጻ መውጣት አለበት። በወደቀ ሰው ዘንድ ንጹህ ባህል የሚባል ነገር የለም፤ ባህል የሰው ሥራ ነው። ባህል የረከሰ ሰው ማኅበራዊ ግኝትና ሥሪት ነው። ሰው በኃጢአት የወደቀ ነውና በክርስቶስ ያልተዋጀ ሰው ጽድቅ በእግዚአብሔር ፊት ርኩሰት እና የመርገም ጨርቅ ነው። ባህላችን (የትኛውም ባህል) ከወደቀ ሰው የመነጨ በመሆኑ፥ ባህል ራሱ ተዋጅቶ ለእግዚአብሔር ክብር መዋል የተገባው እንጂ እንደ ተቋም ከክርስቶስ አካል ጋር መደራደርና ቦታ መሻማት ያለበት ነገር አይደለም። ባህላዊ አመቻማችነት ከክርስቲያን የሚጠበቅ አይደለም።

ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን።